# የብርሃን አንጓዎች

## ግለ ሰብ፣ ቤተ ሰብ እና ቤተ ክርስቲያን ተኮር ተሐድሶአውያን መጣጥፎች

ጳውሎስ ፈቃዱ

የብርሃን አንጓዎች

ሚያዝያ ፳፻፬ ዓ.ም    የመጀመሪያ እትም

አሳታሚ    ጳውሎስ ፈቃዱ

ይህንን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ በማንኛውም ዐይነት መንገድ
ለማባዛት በቅድሚያ ከጸሓፊው ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright© 2012 Paulos Fekadu

በዚህ መጽሐፍ ከሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡-
አ.መ.ት የሚሉት በ1993 ዓ.ም ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጒም፣
የ1980 ትርጒም የሚለው፣ ቀለል ባለ አማርኛ በ1980 ዓ.ም ከታተመው
የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ሲሆኑ፣
የቀሩት በሙሉ ከቀኃሥ ትርጒም (1954 ዓ.ም) የተወሰዱ ናቸው።

የሽፋን ሥዕል ልዑል ገብርኤል

የጸሓፊው አድራሻ
ጳውሎስ ፈቃዱ
የመ.ሣ.ቁ. 6394
አዲስ አበባ

E-mail: paulosvictory@yahoo.com

ለሶፊ

ከፍቅር + ከበሬታ + ኀዘኔታ + ...

ጋር!

## ማውጫ


ፊር መያዣ 5

መግባቢያ 6

ገለታ 8

፩. እናት አልፈልግም! 9

፪. የሕማም ሰው 16

፫. ጸሎታችንን ራሳችን ብንመልሰውስ?! 31

፬. ደ'ሞ ምርጫ መጣ! 39

፭. የንጽሕና ዋጋ 53

፮. ምርጥ ምርጥ ተዋንያን 58

፯. ትዳርና እሳት 72

፰. ያልተጻፉ ጥቅሶች 85

፱. ቄስ አብደላ 89

፲. ሥጋ ቤቶቹ እና ወንድማማቾቹ 105

፲፩. የሽለቆ ጩኸት 123

፲፪. ስላልተመለሱ ጸሎቶቼ አመሰግንሃለሁ! 125

፲፫. የቱ ይቅርታ? 139

፲፬. ዕፍረትን ያያችሁ!? 154

፲፭. "የተገኘውን" እንሰብካለን! 161

፲፮. ሰው መሆኔን ማን ይንገረኝ!? 167

፲፯. ያልተመለሰው የኢየሱስ ጸሎት? 183

፲፰. አቋም የለሽ አቋም 197

፲፱. "ተዘልሎ መኖር"? 226

፳. ምን አገባኝ?! 238

፳፩. ሞትን ማን ያመልጣል?! 247

ቦንሆፈር - ጨለማውን የሰነጠቀ ኮከብ 257

ዋቢ ጽሑፎች 259




# ፊር መያዣ

*እያንዳንዳችሁንና ሁላችሁንም ሰላም እላለሁ::*

*እውነት ብርሃን ነው፤ ጉድለትን ይገልጣል:: ብርሃን በሌለበት መጓዝ አደጋ አለው፤ ምን እንደሚረግጡ አይታወቅም:: የብርሃን መኖር ግን ነጻ ያወጣል:: እንጉል ከመራመድ ይታደጋል:: መንገድን ያሳያል:: መድረሻን ብቻ ሳይሆን አሁን የት እንዳሉም ይነግራል:: ብርሃን አስደንጋጭም ነው፤ አስደንግጦ ግን ያድናል::*

*ምሉእ እውነትን በአንዴ ጠቅልሎ መያዝም ሆነ መግለጥ ይቻል አይመስለኝም፤ ከትልቁ እውነት፣ ከግዙፉ ብርሃን ላይ አንዳንድ እንጓዎችን፣ አንዳንድ ጠጠሮችን ነው የምናገኘው:: ሁላችንም እጃችን የገባውን የብርሃን ጠጠር ማስወንጨፋችን ይልቁኑ ቁምነገር ነው፤ የብርሃን ትንሽ የለውምና!*

*ግና ብርሃን እንጓ አለውን? እንዴታ! ሳይንሱ እንደሚነግረን ብርሃን በማይከፋፈል ሞገድነት ብቻ ሳይሆን፣ በተለያዩ ቅንጣቶች ቅጥልጥልነትም ይታወቃል፤ ይህን ለዓለም በማሳወቁ አነስታይን በፊዚክስ የኖቤል ሽልማት አግኝቷል:: ብርሃን ሞገድም ነው፤ ቅንጣትም ነው፤ በአንድ ጊዜ ሁለቱንም የመሆን ልዩታ ታድሏል! እዚህ፣ "የብርሃን እንጓዎች" የተባሉትም ከበርካታ የብርሃን (የእውነት) ቅንጣቶች የተቆነጠሩ ናቸው!*

*የእውነት ብርሃን የሕይወት ምንጭ ነው፤ በአደጋ ታጥሮ የሚገኝ፤ በእሾኽ እንደ ተከለለ የንስር እንቁላል:: እናት ንስር ጥንቃቄ የሚሹ እንቁላሎቿን እሾኽ መኻል መጣሏ ሳያንስ፣ ሲፈለፈሉም ለአደጋ እያጋለጠች ታሳድጋቸዋለች፤ አደጋ የዕድገት ማበረታቻ፣ እንዲሁም የለውጥ ማትጊያ ነውና! የእውነት መኖሪያም ከዚህ አይርቅም፤ እንዳይገልጡት ጭንቅ፣ እንዳይተዉት ሕይወት! አሁን ከምንጋጠማቸው የእውነት እንጓዎችም በእሾኽ የተከበቡ አይጠፉም፤ የእሾኹን አጥር በጥንቃቄ ማለፍ ከቻልን ግን ሕይወትን እናገኛለን:: እውነትን የመግለጥ መነሻ ዓላማ፣ መድረሻ ተስፋም ከዚሁ ጋር የተጋመደ ነው!*

*እግዚአብሔር ይረዳናል!*

# መግባቢያ

ይህ ያልተንኳኩ በሮች ቊጥር ሁለት አይደለም::

መጽሐፍ በዚህ ጊዜ ለማሳተም አልወጠንኩም ነበር፤ የትዳሩን ዓለም የምቀላቀልበት ወቅት ሲቃረብ ግን፣ “ለምን አስቀድሜ ጠረጴዛዬን አላጸዳም?” በሚል ወረቀቶቼን መልክ የማስያዝ ጥረት ጀመርኩ:: ይህም ስለ ፍቅርና ትዳር ጒጒቴን፣ ሥጋቴንና ሽሽቴን የጫጫርኩት ሁሉ ባተግባር ሊፈተን መቃረቡን አስታወሰኝ፤ ትዳር አንዳንድ ጽሑፎቼን የማስቂየሩ አይቀሬነትም ታየኝ:: ታዲያ፣ ዛሬ ከትዳር ወዲህ ሆኜ ያሰብኩትን ነገ ማወቅ ብፈልግ፣ ላላገኝ ነው እንዴ? የሚለውን ወጣሪ ጥያቄ ለማምለጥ በማሳተም መቅደሙን መረጥኩ::

በሌላ በኩል ደግሞ ከወትሮው የተለየ የሥራ ጫናና የጤና መጓደል መጽሐፉን የመጨረስና ወደ ማተሚያ የመስደድ ጣሬን አብዝተውታል:: የማሳተሚያ ዋጋ ንረትም ለብቻ የማይሸከሙት ቀንበር ሆኗልና ይህ መጽሐፍ እንዲታተም ሌሎች ሁለት መጽሐፎቼን ከገበያ ለማጥፋት ተገድጃለሁ::

ቤተ ሰብ ነክ ምዕራፎቹ ወጣቶችን በመኮርኮር ወደ ንባብ ለማምጣትም ያግዛሉ:: ግና ዐቢይ ሸከሞቹ ቀሪዎቹ የቤተ ክርስቲያን ጒዳዮች ናቸው:: ስለዚህም የቤተ ክርስቲያንን አገራዊ ኀላፊነት ለማስታወስ፣ ወደ ተባረከው መጽሐፍ እንድንመለስ፣ ጥንተ መነፅራችንን ፈልገን እንድናጠልቅ፣ መሪዎች ቃለኞች ብቻ ሳይሆኑ ተግባረኞችም እንዲሆኑ፣ አማኞች የጣልነውን መልካም እንድናነሣና መጣል ያለብንን እንድንጥል በሚጠይቁ ሐሳቦች ዙሪያ የሚያደሩ መጣጥፎች እዚህ መድብል ውስጥ አሉ፤ ያዘኑ እንዲጽናኑ፣ የሳቱ እንዲመለሱ፣ ያንጎላጁ እንዲነቁ፣ ግትሮች እንዲለዝቡ መልእክት አዝለዋል::

እንዲህ የምጽፈው በርካቶች እንደሚገምቱት ደፋር ስለሆንኩ አይደለም፤ ስለምፈራ እንጂ! የእግዚአብሔርን ቤት የራስ የማድረግ ሩጫዎች ሲገዘፉና ከቅዱሱ መጽሐፍ መራቃችንን የሚያሳዩ መገለጫዎች ሲበራከቱ የቤተ ክርስቲያን ዕጣ ፈንታ ያስፈራኛል:: ጉሙ እንዳይውጠን እፈራለሁ፤ ዝምታዬ መታረሚያ ማሳጣቱ ደግሞ ያሳስበኛል:: “ባለቤቱ ቢጠይቀኝስ?” የሚል ብርቱ ፍርሀትም አለብኝ:: መጻፌ ምን ጣጣ ያመጣብኝ ይሆን? እያልኩም ፈርቻለሁ፤ በተለይ ቤተ ሰብ ለመመሥረት በምዘጋጅበት በዚህ ጊዜ:: ፍርሀቴ ከመሥራት እንዳያቅበኝ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ቅስም ሆኖኛል!

ሥነ ጽሑፍ ሞያዬ አይደለም፤ እንጎቻም አላበስልበትም፤ መልእክቴን ተሸካሚ ሠረገላ ብቻ ነው:: ስጽፍ ሰዎችንም ሆነ ራሴን ለማስደሰት አይደለም:: አንዳንዶቹን በብዙ ኀዘን ነው የጻፍኳቸው:: መንፈሴ ሲበሳጭብኝ በቊጣ የጻፍኳቸውም አሉ:: ግራ በመጋባት ጽፌ ዐውቃለሁ:: ታምቄ እንዳልፈነዳ የእፎይታ ጥጋት ፍለጋም ጽፌአለሁ:: አንዳቸውንም ግን ዳር ቆሜ አልጻፍኳቸውም፤ በእንባዬና በላቤ ቀልመዋል:: ስጽፍ ራሴን ነጻ አድርጌ አይደለም፤ አንዳንዶቹ ከሕይወቴ የተቀዱ፣ የሥጋቴ፣ የጭንቀቴና የናፍቆቴ ውልዶች ናቸው!



የአንባቢው አቀባበልና ምላሽ እንደሚለያይ ዐውቃለሁ:: አንዳንዱ፣ “የሚሰብከኝን አልፈልግም” ባይ ነው:: ሌላው ደግሞ ለችግሩ ፍቱን መፍትሔ፣ ለጥያቄው እርኪ መልስ ባለማቅረቤ ይከፋዋል:: “ቆሽሸሃል” እየተባለ እንኳ፣ “ታጠብ” ተብሎ እንዲነገረው የሚጠብቅ አለ:: “እግርህ ያነከሳል” ተብሎ ሲነገረው፣ ስለ ጤናማው እጁ ባለመወራቱ የሚናደድም ይኖራል::

ግና እግዚአብሔር ለውጥ ለማምጣት ብዙ ሰዎች እስኪሰባሰቡ አይጠብቅምና፣ “ሁሉ ሰምተውኝ ይመለሳሉ” የሚል ገራገር ናፍቆት የለኝም:: በምድረ በዳ እንደማልጮኽም ዐውቃለሁ:: ለነገሩማ፣ “በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ” የተባለውን ነቢይ ሰምተው በንስሓ የተመለሱ ከነበሩ፣ በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር የሚከውነውን ማን ያውቃል? ገና ተስፋ ቀርቶልናልና!

በዚህ ጥራዝ ጒድለቶችን ጠቅሻለሁ፤ ወቀሳ አለበት:: ከአሁን በፊት የተለያዩ አስተማሪና አጽናኝ መጻሕፍትን እየተረጐምኩ ለአማኙ አቅርቤአለሁ:: በዚያ መንገድ ካስተማርኩ ዘንዳ፣ ጒድለቶችን የመንቀፍ መብትስ አይኖረኝምን? ሆኖም ዐቢዩ ሰበብ፣ መብትን የመጠቀም አይደለም፤ የተሐድሶ ረኃብ የወለደው ቊጣ እንጂ! በለውጥ አልባ ሕይወትና ርምጃ ላይ መሰላቸት የጫረው ቊጣ ደግሞ የተሐድሶ ማዋለጃ እንባንና ምጥን ያዘለ ነው!

ከሌላ ለወሰድኳቸው ለአማናዊው ሕይወት የሚያግዙ ሐሳቦች ምንጬቻቸውን በአግባቡ ጠቅሻለሁ፤ ከመንፈሳዊ መጻሕፍት በተጓዳኝ የታሪክና የግለ ታሪክ መጻሕፍትን ስለማዘወትር ምንጬቼም እኔኑ ይመስላሉ፤ የትም ብጎርስና ባላምጥ ወደዚህ ዘሬ ነው የምውጠው! የግድ መንፈሳዊ መጻሕፍት ካልሆኑ ደግሞ አይባልም፤ የእውነት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነውና!

ክርስትና መለኮታዊ እውነት ነው፤ ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ ናትና “አበቃላት” ሲባል እንኳ ትነሣለች:: ታሪክ ምስክር ነው:: ዛሬም ግን ተሐድሶ ያስፈልገናል! የኢያቶቻችን ቤተ ክርስቲያን እንድትታደስ እየተመኘን፣ እኛ እንደማያስፈልገን ካሰብን ግብዞች ነን:: ተሐድሶ ደግሞ አዲስ ነገር ማምጣት ሳይሆን፣ ወደቀደመው ቀና መንገድ ምልሰት ነው:: ይህን ለማየት እጽፋለሁ!

በዚህ ሁሉ ግን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ አላግባብ ነቅፌ እንዳይሆን የእግዚአብሔርን ምሕረት እማጠናለሁ!

ጳውሎስ ፈቃዱ

ሚያዝያ 2 ቀን 2004 የምሕረት ዓመት

# ገለታ

ይህ መጽሐፍ በስሜ ቢታተምም የብዙ ሰዎችን ልፋትና ርብርብ ጠይቋል። ሶፋኒት ታመነ በየዕለቱ ምን እንደ ሠራሁ በመከታተል፣ ከጨረስኩም በኋላ መሠረታዊና ጠቃሚ አስተያየቶችን በማቀበል ጉልበት ሆናኛለች። በንስር ዐይኗ ደቃቅ እንከኖችን እንኳ ከመንቀስ ባሻገር፣ "አሜን" ሳታስብለኝ እንዳትመለስ ምላ የምትመጣባቸው ቀናትም ነበሯት! ዐውቃለሁ፤ ለዚህ መጽሐፍ ባለ እንኳር አስተዋጽኦ ናት፤ ግና እኔን አግኝታለችና ይበቃታል! (ሌላው ምስጋና ምን ይረባታል?!)

በተጨማሪም በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)፣ ስሜ ታደሰ (መጋቢ)፣ ሚክያስ በላይ፣ ዳዊት ጺጋዬ፣ ዳዊት መንግሥቱ ከተጨናነቀ ጊዜአቸው ቆርሰው፣ በተደራራቢ ኀላፊነቶቻቸው ላይ አክለው ሙሉውን ጥራዝ በማንበብ አርመውኛል፤ አይደከሜው ሚኪማ ልፋቱ ብዙ ነበር። መድኅነ ዓለም ብድራታቸውን ይክፈለው!

እየመረጥኩ የሰጠኋቸውን የተለያዩ ምዕራፎች ያነበቡልኝም አሉ፤ ተስፋዬ ሮበሌ፣ ማሙሻ ፈንታ፣ ሰለሞን አበበ፣ ዮሐንስ መሐመድ (መጋቢ)፣ መስከረም በቀለ፣ ፍቅር ፈቀደ፣ ሰለሞን ሱፋ፣ አብዱ መሐመድ፣ ሥዩም በሻህ፣ ... እግዚአብሔር ይስጣችሁ!

እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማጣቀሻነት ከተጠቀምኳቸው መጻሕፍት ገሚሶቹ የራሴ ናቸው። ይህም የሆነው የምፈልጋቸውን መጻሕፍት ስጠይቃቸውም ሆነ ሳልጠይቃቸው የላኩልኝ (ያመጡልኝ) ሰዎች ስላሉ ነው። በባሕር ማዶ ወዳጆቼ ማረፊያ መንግሥቱና መዝሙረ ደረጀ ቅንነት እደነቃለሁ፤ ክብረት ይስጥልኝ። ግርማቸው ሀብቴን፣ እመቤት ጉልላትን፣ አማረ ታቦርንና መሠረት ወልደ አብን ካላመሰገንኩስ ማንን አመሰግናለሁ?

ቤተ ሰቦቼን ማስቀደም ነበረብኝ። ቤት ደርሼ፣ የእግዜር ሰላምታ እንኳ ሳላቀርብ መጽሐፎቼና ወረቀቶቼ መኻል ስደበቅ፣ "ራት ደርሷል ና" ከማለት በቀር ወቀሳ አላበዙብኝም። አንዳንዴ ጊዜ ሰጥቼ ሳጫውታቸው ከፊታቸው የማነብበው ፈገግታ ብዙ እንዳሳጣኋቸው ይጠቍመኛል (ለነገሩማ አንደኛውኑ ትቻቸው ልወጣ አይደል?)። ይሁን እንጂ፣ "ያጣችሁኝ በከንቱ አይደለም" ልላቸው እፈልጋለሁ፤ ደስታቸውም ይኸው ነው!

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ ዘአፈጸመኒ በደኅና።

# እናት አልፈልግም!

"እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ
እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ?"

ይህ ዐፄ ቴዎድሮስ ተወዳጅዋ ሚስታቸው ተዋበች ሲሞቱ እያለቀሱ የገጠሙት ሲሆን፣ "ሚስት ናት ገረድ" የሚለው አገላለጽ፣ "ሚስት፣ እናት፣ ገረድ" ለማለትም ነው። በእርግጥም ተዋበች ለቴዎድሮስ ተንከባካቢ ሚስታቸው፣ መካሪ እኅታቸው፣ አሳቢ እናታቸው እና አገልጋይ ገረዳቸው ነበሩ። በቅርብ ሁኔታውን ያጠናው ዎልድሜየር የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥቷል፤

> ንጉሥ ቴዎድሮስን ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች ይጠብቋቸዋል። ... እቴጌዪቱ እንደ አበሾች ባህል ሁሉ ንጉሡን በምግባቸው በኩል ይንከባከቧቸዋል። ንጉሡ የሚበሉትንም ሆነ የሚጠጡትን ከእቴጌዪቱ እንጂ ከማንም አይቀበሉም። ሴትዬዋ ብልህና ጠቢብ ስለሆኑ ንጉሡ ብዙ መጠጥ በሚጠጡበት ጊዜ ወይም እየደጋገሙ ሲጠጡ ሲያዩዋቸው 'ንጉሥ አስካሪ መጠጦችን ደጋግሞ አይጠጣም' በማለት ይመክሩአቸዋል። በዚህም ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ያነቡላቸዋል። ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲያድርባቸውም ይነግሩዋቸዋል።[1]

የንጉሡን አስፈሪ ነበልባላዊ ቍጣ ማስታገሥ የሚችሉትም እቴጌዪቱ እንደ ነበሩ ይነገራል። ስለዚህ እቴጌ ተዋበች ሲሞቱ የቴዎድሮስ ቍጣ መቈጣጠሪያ ተነቀለና ሁሉንም ችግሮች በኀይል ለመፍታት እየሞከሩ ብዙ ጥፋት አደረሱ። ይህም ተደራርቦ ራሳቸውን ለማጥፋት አበቃቸው።

"ለነገሩ ጥሩ ሚስት ለባሏ ምን የማትሆነው አለ?" ሲ. ኤስ ሌዊስ ከአራት ዓመት አብሮነት በኋላ በሞት ስለ ተለየችው ሚስቱ የተናገረው ነው፤ ከዚያም ሚስቱን፣ "ልጄ፣ እናቴ፣ ተማሪዬ፣ መምህሬ፣ ተገዢዬ፣ ገዢዬ ... ታማኝ ምስጢረኛዬ፣ ባልንጀራዬ፣ አብሮ ተጓዤ፣ የትግል ጓዴ" በማለት ይሥላታል።[2]

በእኛም ዘመን ባሎች ሚስቶቻቸውን በተለያየ ስም ሲጠሩ መስማት ተለምዷል። "እናትዬ" የሚለውን ግን ሴቶችም እጅግ ሳይወዱት አይቀሩም! አንዳንዴማ በሌላ ስም ከተጠሩ ያኮርፋሉ፤ "ዬ" ተቈርጣ በመቅረቷ ብቻ ባላቸውን "እዬዬ" ያስብሉታል። እስቲ፣ "እናቴ ካላልከኝ" ብሎ ሙግት ምን

ይባላል!? ወንዶቹም እናት እንደሚፈልጉ ያስታውቅባቸዋል:: ስለዚህ ወ/ሮ ሚስት ልጆቿን ብቻ ሳይሆን ባሏንም አብራ ማሳደግ ሥራዋ ይሆናል::

የውጪ አድናቂዎች የባልየውን ዕድለኛነት እና የትዳሩን ስምረት ለማሞገስ "ፐ!! እናት የሆነች ሚስት ነው ያለችው" ወይም "እናቱ እኮ ነች!" ይላሉ። አቶ ባልም በወዳጆቹ መኻል፣ "እግዚአብሔር እናት ነው የሰጠኝ" በማለት በኩራት ሚስቱን ሊያደንቅ ይችላል። አንዲት ወጣት፣ "እየሰማሁ የኖርኩትና የመልካም ሴት ልኬት ነው ብዬ የምመኘው ነገር ለባል እናት መሆንን ነው። እስካሁን የሰማኋቸው ወንዶች ሁሉ ሚስታቸውን 'እናቴ' ካሉ ያቺ ሴት ጥሩ የትዳር ተጓዳኝ መሆኗ ስለሚታሰብ፣ ለባሌ እንዴት እናት እንደምሆንለት ያሰብኩበት ጊዜ ብዙ ነው። 'እናትዬ' ብሎ ሲጠራኝ የባሰ እንድወደውና እንድሰጥለት ያደርገኛል" ብላለች፤ ስለ እጮኛዋ ስታወራ።

እንደ ታናሽ እኅቴ አባባል ከሆነ፣ "አንድ ወንድ አንዲትን ሴት፣ 'እናቴን ትመስይኛለሽ' ካለ፣ ሊያገባት ፈልጓል ማለት ነው":: ስለዚህ ወንዶች "እናት የሆነች ሚስት ስጠን" እያሉ ለአምላካቸው ስለት ቢሣሉ አይደንቅም። ሚስትን "የእናቴ ምትክ" ብሎ መጥራት የተጀመረው ግን መቼ ነው? ይስሐቅ ሚስት ሲያገኝ ከእናቱ ሞት መጽናናቱ ይታወቃል (ዘፍ. 24፥67)፤ ያኔ ይሆን? ሚስት ሌላ፤ እናት ሌላ! ሰው ለማግባት ጉዞ የሚጀምረው እናትና አባቱን በመተው ነው:: እናትን ትቶ መጥቶ ሌላ እናት ይገኛል እንዴ ታዲያ?! እሺ፤ እናቱን በሚስቱ ተካ፣ አባቱንስ ማን ሊተካለት ነው?

እናቶች ይመቻሉ:: ልጁ እናቱ ቤት ሳለ አንድ ጊዜ ሽሮ በልቶ ስለታመመ፣ "ሽሮ አልበላም" ብሎ ዐመፀ፤ ስለዚህ እናቱ ከሌሎች ልጆቻቸው ለይተው ድስት እያዘጋጁለት አደገ:: ትዳር ከያዘ በኋላ ወንድሞቹ ወደ ቤቱ ሲሄዱ አጅሬ ሽሮውን ሲሰለቅጥ ያገኙታል:: "ሽሮ ትበላለህ እንዴ?" አሉት በመገረም:: "እናት ቤት ነው የሚቀበጠው!" ነበረ መልሱ ("እኔ እናትህ እያለሁ?!" የእናቴ መፈከር ነው):: የእናታቸውን ቤት ቅብጠትና መዝናናት እያስታወሱ ወንዶች ሁሌም በአንቀልባ መታዘልና ምቾታቸውን ማስጠበቅ ይፈልጋሉ:: በመሆኑም ሚስታቸው ብቻ ሳትሆን ሴት ልጃቸውም እናታቸው እንድትሆንና እንድትከባከባቸው ይሻሉ:: አንድ አንጋፋ የአገራችን ደራሲ የሴቶችን ለባላቸው እናት የመሆን "ጸጋ" ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፤

> እናቴ እኔ ላይ የነበራትን ሥልጣን ነው [ለሴቶቹ] ያስረከብኳቸው:: ሚስቶቼም ይሁኑ ዝም ብሎ ራቅ ያሉ ፍቅረኞችም ይሁኑ እንደ ፈለጉ ነው የሚነዱኝ:: ሲፈልጉ ሲኖራቸው ያለብሱኛል:: ያስዘንጡኛል:: እኔ ብቻ ያለኝን ገንዘብ ሰጥቼ የለሁብትም:: ሁልጊዜም ሴትዮዋ ውስጥ እናት አለች:: ልጅም እንኳ



> እናት የምትሆንበት ጊዜ አለ:: ... እና ልጅ ሌላ ምንም አይደለችም፤ ከአንተ አንሳ የተፈጠረች እናት ነች:: አንዳንድ ጊዜ ልትቆጣ ትችላለች:: የምትለብሰውን ልትመርጥልህ ትችላለች:: የምትመገበውን ጭምር ወስና የምትጠብቅህ እሷ ናት:: ስለዚህ ስታስበው ወደ ሚስትህ የተላለፈውን የእናትነት አገዛዝ ወደ ልጅህ ታስተላልፋለህ:: ምናልባትም ለልጅ ልጅህም ... [3]

መጽሐፉ የሚነግረን ሚስትን መከባከብ የባል ሥራ መሆኑን ነው (ኤፌ. 5፥28-29)፤ ግና ለባላቸው የእናቱ ምትክ መሆን የሚያምራቸው ሴቶች ብዙ ናቸው ("ምትኬ" የሚል የዳቦ ስም እናውጣላቸው ይሆን?)

በቦክስ ስፖርት ታሪክ ለአራት ጊዜ የዓለም የከባድ ሚዛን ሻምፒዮን የሆነው ኢቫንደር ሆሊፊልድ አንድ ወቅት አዲስ አበባ መጥቶ ነበር:: የሰውነቱ የጡንቻ ክምር ሲታይ፣ ሰዎች በእርሱ ተመትተው ይቅርና ሰንዝሮ ቢስታቸው እንኳ በብርድ መመታታቸው እንደማይቀር ያሳብቃል:: ታይሰን የተባለው ሌላ ቡጢኛ ከዚህ ቋጥኝ የሚያህል ሰው ጋር ተጋጥሞ ሲያቅተው በጥርሱ ጆሮውን የዘነጠለው ወድዶ አልነበረም:: ሆሊፊልድ በአንድ ጓደኛዬ ገለጻ መሠረት፣ "ከሥጋና ከደም ሳይሆን ከጥርብ ድንጋይ የተሠራ ይመስላል::" ታዲያላችሁ ይሄ መንዲስ ሰውዬ 5 ጊዜ ትዳር እንደ መሠረተ ይነገራል:: ስለ እነዚህ ትዳሮቹ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ዘጋቢ ጥያቄ ሲቀርብለትም፣ "ሁሉም ሴቶች እንደ እናቴ እንዲሆኑ ማሰቤና መፈለጌ አልቀረም:: ... እኔ ፍቅር ስሰጣቸው፣ ልክ የእናቴን ያህል አፍቅረው ምላሽ እንዲሰጡኝ እፈልጋለሁ" ብሎ መልሷል::[4] ስንት እናት እንዲኖረው ነው ፍላጎቱ? ያገባት ሴት ሁሉ እናቱ የምትሆነውስ በምን ሒሳብ ነው? ወንዱን ምን ነክቶታል!?

ሚስቶችንና እናቶችን ምን አመሳሰላቸው? እንዴ ቂይ ትዝ አለኝ:: በአንድ ነገር ይመሳሰላሉ፤ በምክር:: እናቶች ምክር ይወዳሉ፤ ሚስቶችም መምከር ይወዳሉ ("መጨቅጨቅ" ማለት ፈርቼ ነው):: "በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምክር አገልግሎት" መሆን አለመሆኑን ግን አላውቅም:: እናቶች በእናትነት ሥልጣናቸው ይመክራሉ፤ ሚስቶች ደግሞ የሚስትነት መብታቸውን ተጠቅመው እንደሚመክሩ እገምታለሁ:: ከዚህ ውጭ እናትና ሚስት የሚጋሩት ነገር ይኖር ይሆን? ታዲያ ሚስት የእናት ምትክ ትሆናለችን? (ባትምክረው ነው የሚሻላት!)

የእናቶችና የሚስቶች ሥራ ተቃራኒ መሆን ነው ያለበት:: ልጅ በልጅነቱ ለመብላት፣ ለመልበስ፣ ለማሰብና ለማወቅ ሳይቀር በከፍተኛ ደረጃ የወላጆቹን ድጋፍ ይፈልጋል:: እናትነት እረኝነት ቢሆንም፣ በዚህ ሁኔታ መቀጠል የለበትምና ልጅ ራሱን ወደ መቻል መምጣት አለበት:: ስለዚህ እንደ ወላጅነቷ

ልጁ በዚህ ዓለም ላይ ለመኖር የሚያስፈልገውን ዕውቀትና ጥበብ በምክር እያስታጠቀች ራሱን ችሎ ያለ እርሷ ለመኖር እንዲችል የምታበቃው እናቱ ናት:: ለሁሉ ነገር የእርሷን ድጋፍ የሚፈልገውን ልጅ ከራስዋ ነጻ ታወጣዋለች:: ለጋ አገዳው እንዲጠነክርና በራሱ እንዲቆም፤ ከዕቅፏ እያወጣች (እያመማትም ቢሆን) ልጁን ሰው ታደርገዋለች::

ልጅም ማደጉን መናፈቁ አይቀርም:: ለሚጠይቃቸው ብዙ ጉዳዮች፣ "ስታድግ ትደርሳለህ" የሚል ምክንያት ስለሚቀርብለት እድገ ለመገኘት ይጓጓል:: የልጅነት ጊዜዬን ሳስታውስ ማንገቻ የሌለው ሱሪ ለመልበስና የትምህርት ቤት ክፍያዬን ለታላቅ እኅቴ ሳይሆን ለእኔ ለራሴ ተሰጥቶኝ ለመክፈል ምን ያህል እመኝ እንደ ነበር ትዝ ይለኛል:: ጥያቄውን በተደጋጋሚ አቀርባለሁ፤ "ስታድግ" የሚል ምላሽ እንደሚወረወርልኝ ግን ዐውቃለሁ:: አቤት ማደግ እንዴት ሩቅ ሆኖ እንደሚታየኝ! ያልነበረውን ጢሜን ያለ ጊዜው እንድፈትግ ያደረገኝም ይኸው ነበር::

አንዱ እንደ እኔ የተቸገረ ልጅ ማደግ አለማደጉ የሚታወቅበትን ማረጋጋጫ ጠየቀ:: አላስገባ አላስወጣ ያላቸው ወላጆቹም የዐልጋቸውን ራስጌና ግርጌ እያሳዩት፣ "ስታድግ ከዚህ ጫፍ እስከ እዚያኛው ትደርሳለህ" ብለው መለሱለት:: ከአጭር ጊዜ በኋላ ድንገት ያሉበት ተከሰተና ማደጉን እንዲያውቁለት ጥያቄ አቀረበ:: "እንዴ መቼ ዐልጋውን ከጫፍ እስከ ጫፍ ደረስክ?" ብለው ጠየቁት:: እጃቸውን ወደ ዐልጋው እየጎተተ ወስዶ አሳያቸው፤ በትክክልም ቁመቱ ከአንዱ የዐልጋ ጠርዝ ወደ ሌላኛው ደርሷል:: ወላጆቹ መሣቅ ጀመሩ፤ ምክንያቱም ትንሹ ልጃቸው ወደ ጎን ነበር የተዘረጋው:: የዐልጋውን ርዝመት ከላይ ወደ ታች መድረስ ስላልተቻለው "በቁረጣ" ማደጉን ማሳየት መረጠ::

ልጅን ከተደጋፊነት ራሱን ወደ ማስቻል ማድረስ ለእናቶች ቀላል አይደለም፤ ግን ግድ ነው:: ካደገ በኋላም እናቱ ላይ ተለጥፎ የሚኖር ልጅ ከተገኘ ወይ እናቱ፣ ወይም ልጅየው፣ ወይም ሁለቱም ያሉበት ሁኔታ የጤና እንዳልሆነ መናገር ይቻላል::

ሚስትስ? የእርሷ ደሞ የእናት ሥራ ተቃራኒ ነው:: እናት ሞግዚት ፈላጊውን ልጅ ወደ ነጻነት ታመጣለች ብለናል፤ ሚስት ደግሞ ነጻ የወጣውን ሰው ወስዳ የእርሷን ሞግዚትነት እንዲቀበል ታስገድደዋለች:: በሁለት እግሮቹ መቆም ጀምሮ የነበረው ሰው ቢበዛ በአንድ እግሩ ብቻ ነው መቆም የሚችለው፤ ለመቆም ሚስቱን ደገፍ ማለት አለበት ("ራሱን ከቻለማ ተነሥቶ ቢሄድስ?") እንዲህ ከሆነ ሚስቶች በአብዛኛው ያለባቸውን የደኅንነት ሥጋት ከሚቀርፉበት አንዱ መንገድ ይሄ ነው ማለት ነው፤ ነጻነቱን ጥሎና ረስቶ ያለ



እነርሱ "ዕውር ድምት" መሆኑን እንዲያስብ (ቅኝ ተገዢነቱን እንዲያውቅ) ማስቻል! ብዙ ጊዜም ይሳካላቸዋል::

የእናቱን ቤት ምቾት የለመደውም ወንድ ይህን ሲያገኝ ይደሰታል:: ጥሩ ያልለበሰ ቀን እንኳ ሰዎች፣ "ሚስቱ ቤት የለችም እንዴ? እንዲህ ሲለብስ እንዴት ዝም አለችው?" ነው የሚሉት:: ራሱ ልብስ መግዛትና የገዛውንም መርጦ ለብሶ የማያውቅ ይመስል፣ አሁን ልብስ ሲገዛ የምትመርጥለት፣ ወይም መልበስ ሲፈልግ የትኛውን መልበስ እንዳለበት የምትወስነው ሚስቱ ትሆናለች:: አሁንም እንደ ልጅነቱ ለሁሉ ነገር የሌላ ሰውን ማረጋገጫ ይጠይቃል፤ ("የእናቴን ምትክ ስጠኝ" በማለት ማን ጸለይ አለው?):: ስለዚህ ሚስቱን (ሞግዚቱን ማለትም ይቻላል) ያጣ ቀን ድንብርብሩ ይወጣል (ራሱን አልቻለማ!)::

ከእናቴም ጋር ከምንጣላባቸው ጉዳዮች አንዱ የክብካቤ ነገር ነው:: እርሷ ፍቅሯን ለመግለጥ በሁሉ ነገር ውስጥ ልትከባከበኝ ትሻለች፤ እኔ ደግሞ የበዛ ክብካቤ ነጻነት ስለሚያሳጣኝ አንስማማም:: ቤት ስገባ፣ "እርሱ ጋ ይበርድሃል፤ እዚህ ጋ ሁን" ትለኛለች፤ የት መቀመጥ እንዳለብኝ የማላውቅ ይመስል:: በጠራራ ፀሐይ ከቤት ስወጣ እያየች፣ "ጃኬት ደርብ እንጂ!" ማለቷ የተለመደ ነው (ጃኬት እንደማልወድ ደግሞ ታውቃለች):: የምበላው ገና ሳይጋመስ ትመጣና፣ "ይጨመርልህ?" ትለኛለች:: "እንግዳ ነኝ እንዴ? ካልጠገብኩ ራሴ 'ጨምሩልኝ' እላለሁ" እላታለሁ፤ ሁሌም ግን እጠየቃለሁ:: ቤታችን ውስጥ ይህ ዐይነቱ ክብካቤ የሚመቻቸው ሞልተዋል:: እኔና እርሷ ግን በዚህ አንስማማም:: ታዲያ አሁንም ሚስቴ የእናቴ ምትክ ወይም እናቴ እንድትሆን መናፈቅ አለብኝ? በሰላም አገር?! (ግን ይቀርልኝ ይሆን?)

ሚስቴ እናት እንድትሆነኝ አልፈልግም:: እንደገና ወደ ልጅነቴ ልመለስ? አላደርገውም! ሁሌ እንደ ልጅ እያዩ ካታከቱኝ ወላጆቼ እጅ መንጭቄ ያገኘሁትን "ትልቅነት" በትዳር ስም አስነጥቄ ወደ ልጅነቴ አልመለስም:: ለሚስቴ አባት መሆን የማልሻውን ያህል፣ ለሚስቴ ባል እንጂ ልጅ መሆንም አያሻኝም:: እንደ ሕፃን "እናቴ" እያልኩ ላልቅስ እንዴ ደግሞ?! አድጌያለሁና አሁን ሚስት እንጂ እናት አታስፈልገኝም::

ሚስቶችም አባታቸውን ትተው ስለሚመጡ አባት ነው የሚፈልጉት:: ባላቸውን "አባቴ" በማለት መጥራት ደስ የሚያሰኛቸው ይመስላል:: ስለዚህ አንዳንዶቹ ግፋ ቢል ቢቆዩ ልጅ እስኪወልዱ ነው:: ከዚያማ ማሞ ወይም ማሚቱ "አባዬ፣ አባቢ፣ አባባ" ማለት ሲጀምሩ እናትም እነርሱን ተከትላ ባሏን፣ "አባዬ፣ አባቢ፣ አባባ" ማለት ትጀምራለች:: እናቴ አባታችንን "አባቢ" ስትለው በሰማሁ ቁጥር፣ "ለአንቺ እኮ አባትሽ አይደለም፤ የእኛ አባት ብቻ

ነው" አላት ነበር፤ "አባቴን ትቼ የመጣሁት ለእርሱ ስል አይደል?" የእርሷም የዘወትር መልስ ነበር።

ባልና ሚስት "ማሚ" እና "ዳዲ" እየተባባሉ መጠራራታቸውን ስሰማ ልቤ የተነካበትና የተደሰትኩበት ወቅትም ትዝ ይለኛል፤ ጠቤ ከቃሎቹ ጋር ሳይሆን ቃሎቹ ካዘሉት ሐሳብ ጋር ነው። ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ ለሰባት ዓመት ያህል ልጅ ማግኘት አልቻሉም። ይህም ብዙ ብዙ ነገር በሕይወታቸው እንዲያልፍ ሰበብ ሆኖአል። በዚህ ጉዳይ የቤተ ሰብ ጣልቃ ገብነት ስላማረራቸው፣ ልጅ እናቱን "ከዛሬ ጀምሮ ቤቴ እንዳትመጪ" በማለት አቋም እንዲወስድም ተገዷል። በዚህ መካከል ግን ባልና ሚስቱ፣ በባል አገላለጽ፣ "አንቺ ልጅ ትሆኚኛለሽ፤ እኔም ልጅሽ እሆናለሁ" ተባባሉ። ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባል ሚስቱን "ማሚ" ብሎ ሲጠራት፣ ሚስትም "ዳዲ" ትለዋለች። ከሰባት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጆች ሰጥቶአቸው እንኳ በዚያው መንገድ መጠራራታቸውን ቀጥለውበታል። ይህ ሰው ለቤተ ሰብ ሸክም ያለው በሳል መጋቢ ሆኖ ቢገኝ ታዲያ ምን ይደንቃል?

ይህም ሆነ ያ፣ እኔ ሚስትን ሳስብ ጓደኛ ነው የማስበው፤ ፍቅረኝነት እንዲቀጥል ነው የምመኘው።

1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስንማር ፕሮግራም እየያዘ ከሚስቱ ጋር ሆቴል የሚያድር አስተማሪ ነበረን። በጊዜው ድርጊቱ የፍቅረኛሞች እንጂ የባለ ትዳሮች መገለጫ ተደርጎ አይወሰድም ነበርና በጉዳዩ የሁሉም ሰው (መምህራንን ጨምሮ) ጣት መጠቋቆሚያ ሆኖ ነበር። ያን መምህር ግን ዛሬ አደንቀዋለሁ፤ ሚስቱን ፍቅረኛው ማድረግ ችሏልና።

ሚስታቸውን ፍቅረኛቸው ማድረግ ያልቻሉ ወንዶች "ፉራ" ናቸው። ፍቅረኛቸውን ሚስታቸው ማድረግ ችለው ከነበረ፣ መልሰው ሚስታቸውን ፍቅረኛቸው ማድረግ እንዴት ያቅታቸዋል? ባልና ሚስት ሁሌም ፍቅረኛ መሆን አለባቸውና የገባው ወንድ ሚስቱን ጓደኛው ብቻ ሳይሆን ፍቅረኛውም ያደርጋታል።

ከተጋቡ ጀምሮ ይኸው ሁለት ልጆችን ወልደው እንኳ እስካሁን (ለዐሥር ዓመት) ስለ ሚስቱ ማውራት ያልሰለቸውና የፍቅር ግጥም መጻፍ ያልታከተው አንድ ጓደኛ አለኝ። አድናቂው ነኝ። ተከታዩ ባልሆንም አብሬው መጓዜ አይቀርም። ሚስትን ማፍቀር የክርስቲያን ባል የሁልጊዜም ተግባር መሆን አለበት (ኤፌ. 5፥25)። ለነገሩ ፍቅር የማይሸፍነው ጉድ የለም (ክርክርን ለማሸነፍም ሳይጠቅም አይቀርም!)።



ማፍቀር የአንድን ሰው ሁለንተናም ለመግዛት አዋጭ ነው። በኀይል ለመግዛት መሞከር ውጤቱ ዐመፅ እንደ ሆነ ታሪክ አስተምሮናል፤ በፍቅር ግን መግዛት ይቻላል። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሚስቶችን፣ "ለባሎቻችሁ ተገዙ" ብሎ፣ ባሎችን "ሚስቶቻችሁን ውደዱ" በማለት የሚመክረው (ኤፌ. 5፥21-30)። መውደድና መግዛት አይነጣጠሉም፤ የእግዚአብሔር ሕግ ነው። ሚስቶቻችሁ እየተገዙላችሁ መኖር የምትፈልጉ ወንዶች "ተገዢ" የሚል ጭቅጭቃችሁንና ስብከታችሁን ትታችሁ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ ፍቅራችሁን በቃላትና በተግባር ግለጹ፤ ፍቅረኞችሁ አድርጓቸው። እግዚአብሔር እንኳ የእኛን መገዛት የሚጠይቀው በፍጹም ፍቅር ከወደደን በኋላ ነው።

ነገሩን ካነሣነው አይቀር፣ መጽሐፍ ቅዱስ "መግዛት" የሚለው ዝቅ ብሎ ማገልገልንም ያካትታል። ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ ለዚህ አርአያችን ነው (ዮሐ. 13፥1-14)። ባል ሚስቱ የተገዛችለት የሚመስለው፣ ሶፋ ላይ ተኮፍሶ ቴሌቭዥን ላይ ሲያፈጥ፣ እጁን አስታጥባ ምግብ ስታቀርብለት ከሆነ ተሳስቷል። ጌታ ኢየሱስ መሬት ወርዶ እግራቸውን ቢያጥብም፣ ማን መሪ እንደ ሆነ ማንም አልተምታታበትም። እንደዚሁም ባል ሚስቱን ዝቅ ብሎ ቢያገለግልም፣ ማን ራስ እንደ ሆነ መለየት አስቸጋሪ አይደለም፤ ድርጊቱ ራስነቱን አያስቀርበትምና![5]

ሚስትን ፍቅረኛ ማድረግ በእግዚአብሔር በሰውም ፊት ለጸጸት የማይዳርግ በሳል አካሄድ ነው። በመሆኑም እኔ በበኩሌ ለሚስቴ ("በሚታሰብ" የሚባል ነገር አለ አይደል?) ባሏ፣ ፍቅረኛዋና ጓደኛዋ ነው የምሆነው። አባቷ አልሆንም፤ የማንም ምትክ አይደለሁም። ምትኩን ፈልጋ ከመጣችም ተሳስታለች። የማገባት ሴት ሚስቴ፣ ፍቅረኛዬና ጓደኛዬ እንጂ እናቴ አትሆንም። "እናትዬ" ካልኳትም ተሳስቼ ነው፤ ወይም ከዐንገቴ ነው።

## ማስታወሻ


1. ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ቴዎድሮስ* (አዲስ አበባ፣ 1985 ዓ.ም) ገጽ 111-112።
2. C. S. Lewis, *A Grief Observed* (London: Faher and Faber, 1961), 41.
3. አለማየሁ ገላጋይ፤ *ሰብለት ገብረእግዚአብሔር፡ ሕይወትና ክህሎት* (አዲስ አበባ፣ ማኅሌት አሳታሚ፣ 2000 ዓ.ም) ገጽ 22-23።
4. አዲስ አድማስ ጋዜጣ፤ ግንቦት 15 ቀን 2001 ዓ.ም።
5. John Piper, *Desiring God: Meditations of a Christian Hedonist* (Nottingham, England: IVP, 2003), 217.

# የሕማም ሰው

*"እግዚአብሔር ክፉ እንዳይኖር ከማድረግ ይልቅ ከክፉ ውስጥ መልካም በማውጣቱ የተሻለ አድርጓል።"*

*ቅዱስ አውግስጢኖስ*

* * *

እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ሕይወት ዓላማ አለው። ከዓላማው የተነሣ የምናልፍበት መንገድ ግን ይለያያል።

ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ሐዋርያው ጴጥሮስን "ተከተለኝ" ከማለቱ በፊት በምን ዐይነት ሞት እግዚአብሔርን እንደሚያከብር ነገረው፤ እርሱን የመከተሉን ዕጣ አሳየው። ጴጥሮስ ይህን ሲሰማ ከኋላ ሲከተላቸው የነበረውን የዮሐንስን ዕጣ ፈንታ ጠየቀ። "እስከመጣ እንዲቈይ ብወድስ አንተ ምን ቸገረህ?" ነበረ መልሱ (ዮሐ. 21፥18-23)። የዮሐንስ ሌላ ጒዳይ ነው፤ የሚያልፍበት መንገድ የተለየ ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንችን የራሱ ፈቃድና መስመር አለው። ሌላው የሚያገኘው ስኬት፣ የግድ የእኛም መሆን የለበትም። የአንዱ መንገድ ከሌላው ይለያል። ስለዚህ የአንዳችንን በመከራ ማለፍ፣ በፈታኝ መንገድ መጓዝ ከሌላኛው ባለ ደልዳላ መንገድ ተጓዥ ጋር ማወዳደር አንችልም።

ያዕቆብ ሲታሰርና ሲገደል (የሐዋ. 12፥2-3)፣ መልአክ ጴጥሮስን ከታሰረበት አወጣው (ቊ. 3-11)። እኩል ከተመረጡትና ከተሾሙት ሰባት ዲያቆናት መካከል እስጢፋኖስ ተገደለ (የሐዋ. 7)። አብሮት ለአንድ አገልግሎት የተመረጠው ፊልጶስ ግን በመነጠቅ ማገልገል ጀመረ (የሐዋ. 8፥39)። ያውም ቅዱስ ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ከመስበኩ አስቀድሞ ለአሕዛብ (ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ) ወንጌል የሰበከው እርሱ ነው። በተመሳሳይ ወቅት፣ ለተመሳሳይ አገልግሎት የተሾሙ ሰዎች በተለያየ አጨራረስ ዐልፈዋል። የእኛም እንዲሁ ነው፤ ሆኖም እያንዳንዳችን እግዚአብሔር ባስመረልን መንገድ ማለፍ ከቻልን እግዚአብሔር ይከበራል።

እያንዳንዱ ሰው የራሱ መንገድ፣ የራሱ መከራ አለው።



ሰዎች በመከራ የሚያልፉት እግዚአብሔር ስለማያስብላቸውም ሆነ ስለማይጠነቀቅላቸው አይደለም። እግዚአብሔር ለጢሞቴዎስ እንደሚጠነቀቅ እናውቃለን። ሆኖም ጢሞቴዎስ በተደጋጋሚ ሕመም ይጠቃ ስለ ነበር የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሐዋርያው ጳውሎስ መክሮታል (ዛሬ ግን ለሆዳችን ሕመም ኪኒን አለልን!)፤ ሆኖም ፈውስ ስለ መቀበሉ የተነገረ ነገር የለም (1ጢሞ. 5፥23)። እግዚአብሔር ለያዕቆብም ይጠነቀቃል፤ ያዕቆብ ግን በምስክርነቱ ምክንያት የሄሮድስ ሰይፍ አገኘው (ሐዋ. 12፥2)። እግዚአብሔር ለዮሐንስም ይጠነቀቃል፤ ነገር ግን ዮሐንስ እንዲሰደድና በአንድ ብቸኛ ደሴት ላይ ብቻውን እንዲቀር ፈቅዷል (ራእይ 1፥9)። ለእስጢፋኖስም ቢሆን መጀመሪያ ከተወረወረበት ድንጋይ አንሥቶ ሕይወቱን እስካሳለፈችው የመጨረሻዋ ድንጋይ ድረስ እግዚአብሔር ይጠነቀቅለት ነበር (ሐዋ. 7፥59-60)። ለጳውሎስ ባልንጀራውና ለአገልግሎቱም እጅግ አስፈላጊ ለነበረው ጥሮፊሞስ እግዚአብሔር ይጠነቀቃል፤ ሲታመም ግን ጳውሎስ ትቶት ለመሄድ ተገድዷል (2ጢሞ. 4፥20)። እግዚአብሔር በትግልና በእንግልት በመኖራችን ይደሰታል እያልኩ አይደለም፤ ቃሉ እንደሚነግረን ግን አማኞች በመከራ ማለፋቸው አይቀሬ ነው።[1]

ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ለሃይማኖታዊ ሥዕሎች ቦታ እንደማንሰጥ እንናገራለን። "በሥዕል አናምንም" ስንልም እንደመጣለን። እውነቱ ግን የምናምንባቸው ሥዕሎች ያሉን መሆኑ ነው። ብዙዎቻችን ብዙውን ጊዜ ወደ አእምሮአችን የሚመጣ የክርስቶስ ምስል አለ፤ የምናውቀውና የምናምነው ኢየሱስ በሥዕል ላይ ያየነውን ነው። ለስላሳ፣ ፈገግታው ደስ የሚል፣ ትንሽዬ ግልገል ያቀፈ፣ ደስ የሚያሰኙ ተግባራትን የሚፈጽም ...

ምን ዐይነት ኢየሱስ ነው የምናውቀው? ውብና ሲያዩት መስሕብ ያለው? ሰዎችን በደስታና በሣቅ የሚሞላ? ነገር ግን፣ እርሱን ጽጌረዳ አበባ ላይ እንዳለ ጤዛ አሳምረን ከማቅረባችን የተነሣ ብዙዎች ኢየሱስን አጥተውታል፤ ወይም ፊታቸውን መልሰውበታል። አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ የመጣው ደስ ደስ የሚሉ ነገሮችን በመፈጸም እኛን ለማስደሰት ብቻ ይመስላቸዋል። ይህ ዐይነቱ ለስላሳ ኢየሱስ ደግሞ ከተከታዮቹ ምንም አይፈልግብንም፤ ውሳኔንም ሆነ መሰጠትን አይጠይቅም። ለምን? ይህ ምስል እውነትንና ኀይልን ያጣ ምስል ነውና።[2]

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ነው የሚመስለው? ኢየሱስ የተገፋ ነው። ሥቃይ ያልተለየው የሕማም ሰው ነበር። የሚስብ ውበት ወይም ግርማ የለውም፤ የሚያስወድድ ደም ግባት አልነበረውም። የተናቀ፣ የተጠላና ሰዎች ፊታቸውን የሚያዞሩበት ነው (ኢሳ. 53)። በቤተ ሰቡ የተገለለና እንደ ዕብድ የሚቈጠር ነበር (ማር. 3፥21)። የሚያገለግላቸው ይሰድቡታል፤ ሰዎች "ጋኔን አለብህ"

ይሉት ነበር (ዮሐ. 8፥48)፡፡ ወዳጆቹ ከድተውታል፤ የቅርቡ ሰው ከቶ እንደ ማያውቀው እየማለና እየተገዘተ ተናግሯል (ማቴ. 26፥69-74)፡፡ ብዙውን ጊዜ ኀዘንተኛ ነው፤ መደሰቱ የተነገረን እጅግ በጣም ጥቂት ቦታ ብቻ ነው፡፡ በሚያ ደርገው መልካም ሥራ ተገቢውን ምስጋናም አያገኝም ነበር፤ "ነጥቆ በረሮች" ነበር የከበቡት፡፡ ዐሥር ሰዎች ተፈውሰው አንዱ ነው ሊያመሰግነው ተመልሶ የመጣው (ሉቃ. 17፥12-19)፡፡ መልካም ድርጊቱ በተደጋጋሚ ውዝግብና ተቃውሞ ያስነሣበት ነበር፡፡

በታሪክ ውስጥ የሚወለድበትን ቤተ ሰብ፣ ቦታና ጊዜ አስቀድሞ መወሰን የቻለው እርሱ ብቻ ነበር፡፡ ሆኖም ምርጫው ውርደት፣ መገለል፣ መከራና ዕፍረት ሆነ፡፡ በከብቶች በረት፣ በተናቀ ስፍራ ተወለደ፡፡ ካላገባች ድንግል ተወለደ፡፡ የመስቀል ሞትን መረጠ! ለችግራችንና ለመከራችን ማብራሪያ ከመስጠት ይልቅ ችግራችንንና መከራችንን ተካፈለ!

ጌታችን ይህንን ይመስላል! ይህን ማወቅ ለተገፉና ለተናቁ ሰዎች ወሳኝ ነው፡፡ የሚሰብ ገጽታም ሆነ ደም ግባት ለሌላቸውና ሰዎች ፊት ለሚነሧቸው ይህ ገጽታው አስፈላጊ ነው፡፡ በቤተ ሰቦቻቸው ሳይቀር መገለል ለሚደርስባቸውና የበታችነት ለሚሰማቸው ሰዎች ይህንን መልኩን መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ሕመም የማያጣቸው የመከራ ሰዎች የኢየሱስን ትክክለኛ መልክ መገንዘብ በብዙ ያበረታቸዋል፡፡ ከከፍታ ቦታ ለወረዱ የእርሱ ከክብር መውረድ፣ ለመልካም ሥራቸው ክፉ የተመለሰላቸው እርሱ ሲያገኝ የነበረውን ምላሽ ማየቱ ዐቅም ይሆናቸዋል፡፡

እኛን ማዳን ለኢየሱስ ቀላል ሥራ አልነበረም፡፡ መቍሰል ነበረበት፡፡ መቈረስ ነበረበት፡፡ ልቡ በኀዘን መድማት ነበረበት፡፡ መቍሰል በሌለበት መዳን አይኖርምና! "የቈሰለ ፍቅር ልዩ ፍቅር ነው፡፡ ቍስሉ ልዩ ያደርገዋል፡፡"[3]

ሲ ኤስ ሌዊስ እንዳለው፣ "ኢየሱስ ሕይወትን የተሞላ ስለ ነበር መሞትን በፈለገ ጊዜ የሌሎችን ሞት መበደር ነበረበት፡፡[4]

ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥ ቶማስ አልነበረምና ትንሣኤውን አላመነም፡፡ ስለዚህ የእጁንና የጎኑን ቍስል ካላየ እንደማያምን ተናግሯል፡፡ ስለዚህ ጌታ ዳግመኛ ሲገለጥላቸው ቶማስን፣ "ና እጅህን ቍስሌ ውስጥ ክተት" በማለት ጋበዘው፡፡ ቍስሉ መታወቂያው ነው፡፡ ቍስሉ ማንነቱ ነው፡፡ የሞትን ቀንበር የሰበረው ጌታ ቍስሉንና ጠባሳውን ግን አቈይቶታል፡፡

ቶማስም የጌታን ቍስል ሲያይ፣ የአምላኩን ጠባሳ ሲዳስስ፣ "ጌታዬ አምላኬ" በሚል አስደናቂ ንግግር መረታቱን ዐወጀ፡፡ እግዚአብሔር የሰዎችን



መከራ ለመካፈል ዝቅ ማለቱን ቶማስ በመገለጥ ብልጭታአየ፡፡ እግዚአብሔር እንኳ ከመከራ ራሱን ነጻ አላደረገም፡፡ በመከራ ተሞክሮ የሰዎችን ሕይወት፣ የሰዎችን ኑሮ ተካፈለ፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር ደግሞ መጎዳት ነው፤ ማዘን ነው፡፡ መከራና ሕመም ሕይወትን ይገልጣል፡፡[5]

ጌታ ይህንን ሁሉ የሆነው ለእኛ ሲል ነውና የእርሱ በዚህ መንገድ ማለፍ እኛ እንዳናልፍ ነው ብለን እናስብ ይሆናል፡፡ ምሉእ እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ እርሱ በዚህ መንገድ ያለፈው ምሳሌአችንም ሆኖ ነው - እኛም የእርሱን ዱካ (ፈለግ) እንድንከተል፤ በመከራ እንድንመስለው፡፡ እንዲያውም መከራ ከምንቀበልበት ወቅት በላይ ኢየሱስን የምንመስልበት ጊዜ ያለ አይመስለኝም!

በምድር ስንኖር ለሁሉ ጥያቄ መልስ አናገኝም፡፡ ያልዳነ ቍስል ደግሞ ያልተመለሰ ጥያቄ ነው፡፡ የሰው ዘር ቍስል በሙሉ መልስ ያላገኘ ጥያቄ ነው፡፡[6] እኛ ደግሞ በምድር የእርሱ አካል ነን፡፡ ታዲያ አንዳንድ ቍስሎቻችን የእርሱም ቍስሎች ናቸው ማለት አይደለምን?

"የተጠራችሁለት ለዚህ ነው፤ ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌውን ሊተውላችሁ ነው" ይላል ሐዋርያው ጴጥሮስ (1ጴጥ. 2.21 - አ.መ.ት)፡፡ "ክርስቶስ ሞቶልናልና እኛ መከራ አይነካንም" ማለት አንችልም፡፡ በእውነት ላይ እየዋሸን መኖር መርጠን ካልሆነ በቀር፣ በዚህች ምድር ላይ እንደ ክርስቶስ በጽድቅ መኖርና ለእውነት መቆም መከራ እንደሚያስከትል ነጋሪ አያስፈልግም፡፡

ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም (ማቴ. 10፥24-25)፡፡ ይህ አባባል ታዲያ መከራንስ አይመለከትም? ጌታችን ወደዚህ ምድር ሲመጣ መከራን ከተቀበለ፣ አማኞች በምድር ከምንም ዐይነት መከራ ነጻ ናቸው ብሎ መናገር እንዴት ይቻላል? የኢየሱስን መከራ ብቻ መተረኩ በቂ ይሆናል? የእኛስ የመከራ ተሞክሮ? በፍሬድሪክ ቡችነር ዕይታ፣ አንድ አገልጋይ የሚናገራቸው ሁለት ታሪኮች ይኖሩታል፤ አንዱ የኢየሱስ ሲሆን፣ ሌላኛው የራሱ ታሪክ ነው፡፡[7]

ጌታ ኢየሱስን ልንመስል ተጠርተናል፡፡ ጆን ፓይፐር እንደሚሉት፣ "እርሱ አሁን በምድር ላይ ስለሌለ አካሉ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በመከራዋ የእርሱን መከራ እንድትገልጥ ይፈልጋል፡፡ እኛም የእርሱ አካል በመሆናችን መከራችን የእርሱም መከራ ነው፡፡ እኛ የእርሱ ቅጣዮች ነን፡፡"[8]

ስለዚህ ሰዎች ከእርሱ የተነሣ ቀንበር ይሸከማሉ፡፡ መራራ ጽዋ ይጠጣሉ፡፡ መሥዋዕትነት ይከፍላሉ፡፡ እርሱ ወደ ሕይወታችን ሲገባ ሰልፍ ይጀምራል፡፡ ጕዳናችን ይሻከራል፡፡ እናም፣ "በክርስቲያናዊ ጥሪአችን መንገድ ላይ

[በጽድቅ እየኖርን] የሚያገኘን የትኛውንም ዐይነት መከራ 'ከክርስቶስ ጋር'፣ 'ለክርስቶስ' የምንቀበለው መከራ ነው::"[9]

ሲ. ኤስ ሊዊስ ሚስቱ በካንሰር ምክንያት በሞት ስትለየው በጻፈው መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤ "ማስጠንቀቂያ ደርሶኝ ነበር:: ለምድራዊ ደስታ ቦታ እንዳልሰጥ ራሴንም አስጠንቅቄ ነበር:: መከራ እንደሚገጥመን ቃል ተገብቶል ናል:: መከራ የመርሐ ግብሩ አካል ነው:: 'የሚያዝኑ ብፁአን ናቸው' ተብሎ እንኳ ተነግሮናል፤ እናም ተቀብዬዋለሁ:: ውሉ ላይ ያልተስማማሁበትን ነገር አይደለም የተቀበልኩት::"[10]

ጌታ ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ በመንፈስ ድኾች የሆኑ፣ የዋሆች፣ ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ፣ የሚምሩ፣ የሚያስተራርቁ ብፁአን መሆናቸውን ማስተማሩ ብዙ አይገርም ይሆናል (ማቴ. 5፥3-11):: ነገር ግን የሚያዝኑስ ለምን ብፁዐን ሆኑ? ሐዝነው የሚያለቅሱ፣ እንባ ከዐይናቸው፣ የኀዘን እንጉር ጉሮ ከልባቸው የማይጠፋ ሰዎች ለምን ብፁዐን ተባሉ?

በኒኮላስ ዎልተርስቶርፍ አገላለጽ፣ እያንዳንዱ የኀዘን እንጉርጉሮ የፍቅር መዝሙር ነው::"[11] በዚህ ምድር ላይ ፍቅር መከራ ነው:: እግዚአብሔር ለፍቅር ሲጋብዘን ለመከራ ነው የሚጋብዘን:: አንዳንዶች ግን ብዙ እንባ የላቸውም፤ ብዙ አላፈቀሩምና![12]

ማንባት የእምነት መጕደልን አያሳይም:: ጥርጥርንም አያሳይም:: አለ ማመንን አያሳይም:: አሊያ ጌታ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት እየቻለ ለምን አነባ?

ጌታ ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ማዘኑንና ማንባቱን እናውቃለን:: ወዳጁ አልዓ ዛር ሲሞት (ዮሐ. 11፥35)፣ ጥፋቷ የደረሰውን የኢየሩሳሌም ከተማ ሲያይና (ሉቃ. 19፥41) የሚጠብቀውን የመከራ ፅጣ ሲያውቅ:: ኒኮላስ ዎልተርስቶርፍ ከልጁ ሞት መጽናናት ሲያቅተው የመለኮት ሙላት የተገለጠበትን የኢየሱስን እንባ በማሰብ ሊሆን ይችላል፣ "የታሪክ ትርጕም የእግዚአብሔር እንባ ነው" በማለት የተናገረው::[13] ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ገጽታ ውን አሳየን፤ ገጽታውም እንባ ነበረበት![14] ስለዚህ፣ "እግዚአብሔር ሕመምን ያውቃል ወይ?" በሚል ጥያቄ መቸገር የለብንም፤ የእግዚአብሔርን መልክ በኢየሱስ አይተነዋልና::

ምናልባት እኛም የእርሱን እንባ የምናየው በእኛው እንባ በኩል ሊሆን ይችላል::[15] ብዙዎቻችን ግን እንባ የሴቶችና የደካሞች ብቻ እንደ ሆነ ነው የምናስበው:: ስለዚህ ወንዶች ደካማ መሆን ስለሌለባቸው እንባ ሊኖራቸው



እንደማይገባ የሚያስቡ ክርስቲያኖች ሞልተዋል:: ክርስቲያን የእንባ ሰው መሆን የለበትምን?

መከራ መቀበል ዓለምን በእንባ መነፅር ማየት ነው:: ስለዚህ ምናልባት በደረቁ ዐይኖቻችን ማየት ያልቻልናቸውን ብዙ ነገሮች ማየት የምንችለው በእንባ በረጠቡና በእንባ በራሱ ዐይኖቻችን ቢሆንስ?[16] "ዐይን ላይ እንባ ከሌለ ለነፍሳችን የሚታይ ቀስተ ደመና አይኖርም::"[17]

ብዙዎቻችን መከራን ጕዳዬ ብለን አስበነው ስለማናውቅ ሲከሰት ድን ብርብራችን ይወጣል፤ ኀዘን ያጥለቀልቀናል::[18] የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንም ስለ መከራ ለመናገር፣ ስለ መከራ ለማስተማር፣ ስለ መከራ ሕዝቧን ለማንቃት ፍላጎት ያላት አትመስልም:: የመከራ ርእስ ጕዳይ ከተነሣም ጥረቷ መከራን እንዴት መቃወም እንደሚቻል እንጂ መከራው ምን አስተምሮን እንደሚያልፍ ለመናገር አይደለም:: በመከራ ላሉትም ምን ማድረግ እንደሚገባ የሚያስተምር አገልጋይ ብዙም የለም::

ጌታችን "ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ" መባሉ ከመከራ የሚገኝ ፋይዳ መኖሩን ያሳያል (ዕብ. 5፥8):: በእርግጥ ጌታ ኢየሱስ ኀጢአት የለበትምና (ዕብ. 4፥15) ካለመታዘዝ ወደ መታዘዝ አይደለም የመጣው:: "መታዘዝን መማር" ማለት በመታዘዝ ተሞክሮ ከእግዚአብሔር ጋር በጥልቀት ማደግ ነው::[19] በሰማይ አዛዥ እንደ ነበረ ብናውቅም፣ ወደ ምድር መምጣቱ ደግሞ ከመጀመሪያውም መታዘዙን ያሳያል:: በአንጻሩ ኑኃሚን ከተቀበለችው መከራ ማጕረምረምን ተማረች (ሩት 1፥20-22):: ሐዋርያው ጳውሎስ የሥጋ መውጊያ ነበረበት፤ ይህም የሰይጣን መልእክተኛ ነበር:: ስለዚህ ሰይጣን በጳው ሎስ ችግር ውስጥ ዓላማ ነበረው ማለት ነው:: እግዚአብሔር ግን ጳውሎስ በመገለጥ ከፍታ እንዳይታበይ ተጠቀመበት፤ መከራውን ለራሱ ዓላማ ለወ ጠው (2ቆሮ. 12፥7-8):: መከራ ሰዎችን የሚያስተምረው ትልቅ ፋይዳ ስላለው እግዚአብሔርም ሰይጣንም በመከራ ውስጥ የሚኖረንን ምላሽ ይፈልጉታል:: ታዲያ ምን ምላሽ ነው የሚኖረን?

የሰዎች መከራ አንድ እንዳልሆነ ሁሉ ሰዎች ለመከራ የሚሰጡትም ምላሽ እንዲሁ የተለያየ ነው:: ሰዎች መከራ ሲደርስባቸው፣ "እግዚአብሔር የለም" እስከ ማለት ሊደርሱ ይችላሉ:: በመከራ እጅ ብርቱ በትር የደረሰበት ኢዮብ ግን የእግዚአብሔርን ሕልውና ለመካድ አልሞከረም፤ የእግዚአብሔርን ሕልውና እንዴም ጥያቄ ውስጥ አልከተተም::

በናዚ የማሠቃያ ካምፕ ውስጥ ብዙ መከራ ያየው አይሁዳዊው ኤሊ ዊዘል አንድ ራባይ ሲያገኝ ለረጅም ጊዜ ሲያስቸግረው የነበረውን ጥያቄ አቀረበ

ላቸው፤ "መምህር፤ አሽዊትዝን ካዩ በኋላ እንዴት በእግዚአብሔር ማመን ቻሉ?" አላቸው:: ራባዩም ለረዥም ጊዜ በዝምታ ቆዩና፣ "አሽዊትዝን ዐይተህ እንዴት በእግዚአብሔር ላታምን ታችላለህ?" በማለት በለሆሳስ መለሱለት:: ያለ እግዚአብሔር ዓለም ምን ሊመስል እንደሚችል ማሳያው አሽዊትዝ ነውና::[20]

ስለዚህ ክፉ ባይኖር መልካም አይታወቅም ነበር ማለት ነው:: አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር (ፍጹም መልካም የሆነ አምላክ) መኖሩን የሚያምኑት ከመከራ የተነሣ ነው::

ይህ ሁሉ መከራ የመጻኢውን የእግዚአብሔር መንግሥት ክብር አመልካችና ጉትጓች ሊሆን ይችላል ማለት ነው:: መከራ የሌለበት፣ የእግዚአብሔር ሰላም የሰፈነበት፣ እንባ የሚታበስበት ሌላ ዓለም መኖሩን እንድናውቅና እንድንናፍቅ የሚያደርገው መከራ ነው:: ምክንያቱም ሕይወት ፍጹም አይደለችም፤ እዚህ (በምድር) ሳለንም ፍጹም ልትሆን አትችልም:: በእኛም ሆነ በአካባቢያችን የተለያዩ ችግሮችን ባናይና ሁላችንም ሁሉ ቢሞላልን የጌታን መምጣት ተስፋ ማድረጋችን ራሱ አጠራጣሪ ነው:: ለማዶች ነን፤ ምድርን እንለምዳለን፤ ከተመቸን እዚሁ መቈየት እንፈልጋለን:: መከራው ግን የድሉን ጌታ መምጣት እንድንናፍቅ ያደርገናል:: ጆኒ ኤሬክሰን አንድ ታሪክ ትነግረናለች፤

> ሰውዬው በሕመም አልጋው ላይ ሆኖ ሞቱን ይጠብቃል:: መጋቢው መኝታው አጠገብ ተቀምጦ እጁን በመያዝ ያጫውተዋል:: ታማሚው ለአፍታ እንቅልፍ ሸለብ አደረገውና ሲነቃ፣ "ፓስተር፣ አንተ ነህ?" በማለት ጠየቀ::
>
> መጋቢውም "አዎን እኔው ነኝ፤ አሁንም አብሬህ አለሁ" አለው::
>
> "እህ" ብሎ አቃሰተ ታማሚው:: "በጣም ቅር ተሰኝቻለሁ:: ኢየሱስን ላየው ነው ብዬ ነበር ያሰብኩት፣ ግን አሁንም አንተው ነህ!"[21]

ምድራዊው መከራ ባይኖር ሰዎች መከራ፣ ኀዘንንና እንባ የሌለባትንና በጉ የሚያበራባትን ከተማ አይናፍቁም:: እዚሁ የተመቸ ኑሮ መኖርን ይናፍቃሉ:: ይህ ደግሞ ፍጻሜው አሳዛኝ ነው:: ስለዚህ የመከራ አለመኖር ሰውን ለሌላ ትልቅ መከራ ይዳርጋል:: መከራ በሌለበት ሕይወት ትርጒም የለውም፤ ሕይወት ካለ መከራ አለ:: ቁምነገሩ ያለው፣ "ከሚገጥመን መከራ ምንድን ነው የምንማረው?" ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው መልስ ላይ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "በሆነልኝና በሞቱ በመሰልኩት" ያለው በከንቱ ነውን?



አንድ ወቅት መጽሐፈ ኢዮብን ትኩረት ሰጥቼ ለማንበብ ወሰንኩ:: አዲሱ መደበኛ ትርጒምን ከተለያዩ ባለቀለም እርሳሶች ጋር ይዤ ንባቤን ጀመርኩ:: በመጀመሪያ ቀን ንባቤ ኢዮብ የተናገረባቸው ምዕራፎች ላይ ብቻ አተኰርኩ:: ሁለተኛው ቀን የሦስቱን የኢዮብ ጓደኞች፣ በሦስተኛው ቀን ደግሞ የኤሊሁን ንግግር አከታተልኩ:: የመጨረሻው ቀን ተረኛ ደግሞ እግዚአብሔር ለኢዮብ የሰነዘረው ምላሽ (ጥያቄ) ነበር:: ከዚያ በኋላ ያቀለምኩትን ሳየው የኢዮብ መጽሐፍ አብዛኛው በቀለም ተዥጎርጉሯል:: አንብቤ ስጨርስ አንድ ነገር አስተዋልኩ - መጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ሕይወት አለ፤ ወይም ሕይወት ያለው እዚያ ነው::

የመከራ ሸለቆ ነፍስ የምትበጅበት፣ ሕይወት የምትሠራበት ስፍራ ነው::[22] ለዚህም ነው በአብዛኛው በመከራ ያለፉ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያውቁት:: ጠባሳዎቻችንና ሕመሞቻችን በሕይወታችን ያለውን የክርስቶስ ውበት፣ የእግዚአብሔርን መልክ አይነጥቁንም:: ነገሮችን በግዴለሽነት ኢቃልሎ የመመልከት ባዶ ኩራት፣ ከምድራዊ ነገር ጋር መጣበቅና ከልክ ያለፈ ብልጥግና ናቸው ይህንን የሚያስከትሉት:; እነዚህ ቆሻሻ ንጣፎች ተደራርበው የክርስቶስን እውነተኛ ምስል ይሸፍኑብናል::[23]

ኢዮብ በዚያ ሁሉ ሥቃይ ካለፈ በኋላ ወዳጆቹን፣ "እኔ ስለ እግዚአብሔር እጅ አስተምራችኋለሁ" ብሏቸዋል (27፥11):: ወዳጆቹ የነገረ መለኮት ዕውቀታቸው (በተለይ በአጠቃላይ ዕውቀታቸው) የጠለቀና የሰፋ ነው:: ራእይ የማየት ተሞክሮም ሳይኖራቸው አይቀርም (4፥12-17):: እግዚአብሔርን ግን አያውቁትም:: በመከራ ከማለፉ የተነሣ ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር እጅ፣ ስለ እግዚአብሔር ጣት ሊያስተምራቸው ይችላል::

እግዚአብሔርን በስብከት ብቻ ማወቅ አንችልም:: በትምህርት ብቻም በጥልቀት ልናውቀው አንችልም፤ ከሌሎች የምናገኘው ዕውቀትም በቂ አይደለም፤ በዝማሬም እንዲሁ:: "በጸጋ ስጦታ" በማገልገልም እግዚአብሔር በሙላት አይታወቅም:: እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻለው በመከራ ሕይወት ሲታለፍ ነው:: በስብከት፣ በትምህርት፣ በዝማሬ፣ በማንበብ፣ በአገልግሎት የማናውቀውና በመከራ በማለፍ ብቻ የምናውቀው የእግዚአብሔር ገጽታ አለ:: የእግዚአብሔር ጸጋ ጒልበት፣ የእኛ ደካማነት፣ የእግዚአብሔር ጠሊቅነትና ቅሩብነት የሚገባን በመከራ ስናልፍ ነው፤ "መጽሐፍ ካስተማረው፣ መከራ የመከረው" እንዲሉ::

የኢዮብ መከራ መቀበል እግዚአብሔር ወዳሰበው መድረሻ መንገዱ ነው:: መከራው ቀረ ማለት ራእዩ ቀረ ማለት ነው::

ከተወለደችበት 19ኛ ወር ጀምሮ ማየት፣ መስማትና መናገር የተሳናት ሄለን ኬለር ስትናገር፣ "ጉድለቴ እግዚአብሔርን፣ ራሴንና አገልግሎቴን እንዳገኝ አግዞኛል" ትላለች::[24] ሄለን ኬለር መከራዎቿን ሁሉ ተቋቁማ በአስተማሪዋ እና ሱሊቫን አጋዥነት ብሬል ማንበብንና ፊት በመዳሰስ የሰዎችን ስሜት መረዳት ተምራ ከኮሌጅ ተመርቃለች:: በዚህም ሳትወሰን በርካታ መጻሕፍትን በመጻፍ ዕውቅና አግኝታለች:: "በምድር ላይ ያለው ደስታ ብቻ ቢሆን ኖሮ ብርቱ (ጀግና) እና ታጋሽ መሆንን በፍጹም መማር አንችልም ነበር" ያለችው ለዚህ ነው (We could never learn to be brave and patient, if there were only joy in the world.)::[25]

መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚነግረን ብዙዎችን ጌታ የተገናኛቸው ከበሽታቸውና ከጉድለታቸው የተነሣ ነው:: ከጤነኞች ጋር የነበረው መስተጋብር እምብዛም አልተገለጠም:: ጌታ የዳሰሳቸው፣ ያናገራቸው፣ ቤታቸው የገባው ከመከራቸው የተነሣ ነው:: በጆን ፓይፐር አገላለጽ፣ "የሰዎችን ልብ የማግኛው ፈጣኑ መንገድ በቍስላቸው በኩል ነው::"[26]

አማኞች ሁሉ የአንድ አካል የተለያዩ ብልቶች መሆናችን እሙን ነው:: ብልቶቻችን ሁሉ ደግሞ አንድ ዐይነት አይደሉም:: ብርቱ ብልቶች እንዳሉን ሁሉ፣ ደካማ ብልቶችም አሉን፤ የከበሩ ብልቶች እንዳሉን ሁሉ፣ የተናቁ የምንላቸው ብልቶችም አሉን፤ የማናፍርባቸው ብልቶች እንዳሉን ሁሉ፣ የምናፍርባቸው ብልቶችም አሉን (1ቆሮ. 12፥22-23):: ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚናገረው ደካማ የተባሉት ብልቶች ይልቁኑ አስፈላጊ ናቸው (ቍ. 22):: ለተናቁት ብልቶቻችን ደግሞ ይበልጥ ክብር እንሰጣቸዋለን:: የምናፍርባቸውን ብልቶች ደግሞ ይበልጥ እንንከባከባቸዋለን (ቍ. 23)::

አማኞች ሁላችን በክርስቶስ አንድ አካል ነን:: ስለዚህ የአንዱ መጎዳት የሌላኛውም መጎዳት ነው:: ስለዚህ በመከራና በችግር ላሉት ተገቢውን ክብርና ትኩረት ልንሰጥ ይገባል:: በአንድ ልብ ሆነን የሌላውን መከራ እንደ ራሳችን አድርገን መውሰድ አለብን (1ጴጥ. 3፥8):: መንፈሳዊ ቤተ ሰብ ነን:: አንዱ የሌላኛውን ሸክም መሸከሙን የምንገልጠው በዚህ መንገድም ነው (ገላ. 6፥2)፤ ክርስቲያናዊ ፍቅርን መግለጫም ነው:: በመከራ ያሉትን ማሰብ እንደ አንድ አካል ብልትነታችን አንዳችን ለሌላኛችን እንደምናስፈልግ ማሳያም ነው:: መከራ ትስስርን ይፈጥራል፤ አንዱ ብልት ሌላኛውን "አታስፈልገኝም" ሊለው አይችልምና::

ግን የዘመናችንን ቤተ ክርስቲያን ትኩረት ስናይ ለደካሞች፣ ለተናቁ፣ ለምናፍርባቸው ብልቶች የተለየ ክብካቤና ክብር እየሰጠች ነውን? አስፈላጊነታቸውንስ ትቀበላለች? በዚህ ዐውድ መከራ የማያጣቸውን አማኞች ማለቴ ነው:: የጆን ዌስሊ እናት ከልጆቻቸው መካከል ማንን ይበልጥ እንደሚወዱ ሲጠየቁ፣ "የታመመው ድኖ እስኪነሣ፣ ከቤት የወጣው ወደ ቤት እስኪመለስ" ይበልጥ እንደሚወዱት ተናግረዋል::[27]



"የተናቁ ለሚመስሉን ብልቶች ይበልጥ ክብር እንሰጣቸዋለን፤ ደግሞም የምናፍርባቸውን ብልቶች ይበልጥ እንንከባከባቸዋለን" (1ቆሮ. 12፥23):: ለእኔ መነፅሬ ጉድለቴ ነው:: መነፅር ባላደርግ አጥርቼ አላይምና ወንዱና ሴቱ ሊምታታብኝ ይችላል:: እያንዳንዱ አማኝም የየራሱን ጉድለት ራሱ ያውቃል::

አንዳንዶች እንዲህ ዐይነት ጉድለቶቻቸው መጥፎ ስሜት እንደሚያመጡባቸውም ይናገራሉ:: በርካቶች ክብካቤ እንዲደረግልን አንፈልግም:: ደካማነታችንን መቀበል ያመናል:: ከጉድለታችን የተነሣ ሰዎች ሊከባከቡን ሲጥሩ ትምክሕታችንን ይነኩብናል፤ ደካማና ሕፃን የሆንን ይመስለናል:: ሁላችንም በአካሉ ላይ በደካማነት መታየት አንፈልግም:: የአካሉ ጠንካራው ክፍልነትን ነው የምንመኘው:: መከራ ይህንን ነው የሚመታብን! በጉድለታችን ምክንያት የምናገኘው ክብካቤ ጉድለት እንዳለብን፣ ሰዎች መሆናችንን፣ ከማንም አለመብለጣችንን ያሳየናል::

መከራ ደካማነታችንን ያስተምረናል፤ ልካችንን ያሳየናል:: በእግዚአብሔር ላይ ጥገኝነታችንን ያሳስበናል:: ትዕቢትንና ምኞትን አስጥሎ ያለ እግዚአብሔር ጸጋ ዋጋ ቢሶች መሆናችንን ያሳውቀናል፤ ሸክላነታችንን ያስታውሰናል:: በውስጣችን የከበረ መዝገብ መኖሩ እውነት ነው፤ ውጭው ግን ሸክላ ነው:: በውስጥ ያለው የከበረው መዝገብ የሚገለጠው ደግሞ ሸክላው ሲሰበር ነው:: እግዚአብሔር የተሰበረን፣ የተዋረደን፣ የተቀጠቀጠን ሰው የማይንቀው ለዚህ ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ሰው ሲገኝ እግዚአብሔር ይሠራበታል:: ምክንያቱም ከመከራ የተማረ ሰው፣ "ጉልበቴ፣ ብርታቴ፣ ጾም ጸሎቴ፣ የቃል ዕውቀቴ፣ ትጋቴ - እኔ" የማለት ዝንባሌ የለውምና::

መከራ እውነትን ያወጣል:: ክፍል ውስጥ፣ "አለሁ፣ አለሁ" የሚሉ ፈተና ላይ ግን የሚከስሙ ተማሪዎችን ዐውቃለሁ:: ክፍል ውስጥ የማይታዩ፣ ፈተና ላይ ግን እንደ ከዋክብት የሚደምቁ ተማሪዎችም ነበሩ:: ፈተና ልክን ያሳውቃል:: መከራ ፈተና ነው:: በመከራ ያላለፈ ሰው ስለ ሕይወት የተሳሳተ ምልከታ ነው የሚኖረው፤ ስለ ራሱም የተሳሳተ ግንዛቤ ነው የሚይዘው:: የአንድ ሰው ትዕግሥት፣ እምነት፣ መሰጠት፣ ትጋት እውነተኝነት መጠን የሚታወቀው በመከራ ሲያልፍ ነው::

"በመከራ ውስጥ በእምነት መሆን ከመከራው ከመዳን ይበልጣል:: ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት መስቀልን ከማምለጥ ይመረጣል:: ትሕትና ከሥጋ መውጊያ ነጻ ከመውጣት የበለጠ ዋጋ አለው::"[28] ሐዋርያው ጳውሎስም የትሕትና ጸጋን የተቀበለው ከመከራው ነው:: የሥጋው መውጊያ ባገኘው ዕውቀትና በደረሰበት የመገለጥ ከፍታ እንዳይታበይ ጠበቀው:: የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ እንደ ሆነ፣ ስለዚህም ሲደከም ያን ጊዜ ኀይለኛ እንደሚሆንና የእግዚአብሔር ኀይልም በድካሙ እንደሚገለጥ ተረዳ:: መከራው ሌላ ጸጋ አስገኘለት (2ቆሮ. 12፥7-10):: ብዙውን ጊዜ ጸጋ ከችግር ያያስጥለንም፤ በችግሩ ውስጥ ልባችን እንዳይወድቅ ይደግፈናል እንጂ (ጸጋ እንዲጨመርልን እንፈልጋለን?)::

አንድ ጊዜ ጥርሴን አሞኝ ሐኪም ዘንድ መሄዴን አስታውሳለሁ:: ሐኪሙ ሲያክመኝ ግን ሌላ ሕመም ነው የጨመረልኝ:: ከወንበሩ ተነሥቼ መሮጥ አምሮኝ ነበር:: ይህኛው ሕመም ግን ለዚያኛው ሕመም መፍትሔ ሰጭ ነበር:: ግን ሕመሙን ፈርቼ ሕክምናውን ባቋርጥስ ኖሮ? ለመሆኑ ጽናትን ያለ መከራ ማግኘት ይቻላል? ትዕግሥትንስ?

ቅዱስ ያዕቆብ ሲናገር፣ "ወንድሞቼ ሆይ፤ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፤ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ:: ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉኣን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም" ይላል (ያዕ. 1፥2)::

ስለ ትዕግሥት ስንጸልይ መከራን እየጋበዝን ነው፤ መከራ በሌለበት ትዕግሥት ትርጉም የለውምና:: በእምነት ስለ ማደግ ስንጸልይ መከራን እየጠራን ነው፤ መከራና ፈተና በሌለበት እምነት አያድግምና!

ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም:: የእምነት ትኩረት ውስጥ ሁሌም ኢየሱስ አለበት፤ የእርሱን መከራ ያልተካፈለ ደግሞ ወደ እርሱ ሊቀርብ አይችልም:: ይህንን የጌታችንን መከራ መከተል ደግሞ እውነተኛ እምነትን ይጠይቃል::[29]

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፣ "በዚህ ሁሉ ግን በወደደን ከአሸናፊዎች እንበልጣለን" በማለት ይናገራል:: "በዚህ ሁሉ" ማለት ምን ማለት ነው? በየትኛው ሁሉ? "ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን ..." በማለት መልሱን ከተል ያደርጋል (ሮሜ 8፥37-38):: በዚህ ሁሉ ውስጥ ብናልፍም በክርስቶስ ከተገለጠው ፍቅር አይለየንም እያለ እንጂ አናልፍም እያለ አይደለም:: በሞት እያለፍን እንኳ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ማለት ነው:: ጸንቶ ለሚያልፍ ክርስቲያን ሞት ሽንፈት አይደለም::



አንድ ጊዜ አንዲት ሴት በልጇ ሞት ልቧ ተሰብሮ መፍትሔ ፍለጋ ወደ አንድ ጠቢብ ትሄዳለች:: ጠቢቡም አንድም ሰው ካልሞተበት ቤት አንድ ነገር እንድታመጣለት ይነግራታል:: መጀመሪያ ወዳገኘችው ቤት ሄዳ ሰው ሞቶባቸው እንደ ሆነ ስታጣራ አባት እንደ ሞተባቸው ነገሯት:: ወደ ቀጣዩ ሄደች፤ ልጅ ሞቶባቸዋል:: የሚቀጥለው ደግሞ እኅት፣ ሌላኛው ወንድም፣ ባል፣ ሚስት፣ አጎት፣ አክስት፣ አያት፣ ... ብቻ ማለዳ ማለዳ እየተነሣች ብትዳክርም ሰው ያልሞተበት ቤት ልታገኝ አልቻለችም:: ቀስ በቀስ በእርሷ የደረሰው በሁሉ የደረሰ፣ የሰው ልጅ ዕጣ መሆኑ ይገባት ጀመር:: እናም ብቻዋን አለ መሆኗ እያጽናናት ስለ መጣ፣ ተመልሳ ጠቢቡ ጋ መሄድ አላስፈለጋትም::

ከሰው የተለየ መከራ አልደረሰብንም፤ አይደርስብንምም!

ሆኖም በመከራ ሳለን አንዳንዴ እግዚአብሔር ሊደበቅብን ይችላል:: ነቢዩ ኢሳይያስ "አዳኙ የእስራኤል አምላክ ሆይ፤ አንተ በእውነት ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ" በማለት የተናገረው ለዚህ ነው (ኢሳ. 45፥15 - አ.መ.ት)::

ይህ ሁሉ እየተከሰተም ስለ መከራ አስቀድመን ስለማናስብ ሰዎች በመከራ ሲያልፉ ምን ልናደርግላቸው እንደምንችል አናውቅም:: እነዚያን ሰዎች እንደ ደካማ፣ እንደማያስፈልጉ፣ እምነት እንደ ጎደላቸው፣ የተደበቀ ኀጢአት እንዳለባቸው (የኢዮብ ወዳጆች ኢዮብን ሲሉት እንደ ነበረው) እንቈጥራቸዋለን፤ ለእነርሱ ቦታ የለንም:: የብልጽግናና የስኬት ስብከታችን የማይሠራበት ሁኔታ ለመኖሩ ምስክር ስለሚሆኑብን ፊት እንነሣቸዋለን፤ እንሸሻቸዋለን:: መፍትሔ አልባው የሚስቱ ሕመም ድንገት ሕይወቱን የመከራ ያደረገበት ጆን ፈይንበርግ እንደሚናገረው፣ አንዳንድ ቅኖችን የሚያሸሻቸው ግን "የተሳሳተ ነገር እናገር ይሆናል" የሚል ሥጋት ይመስላል::[30]

አንዳንዶች ደግሞ ሲንደረደሩ በመምጣት መከራ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ ማተት ይቀናቸዋል:: መከራ ከየት እንደ መጣ ማስተንተንን ይመርጣሉ:: ሰዎቹን ስለ እምነታቸው መኰነል መገሠጽ ያስቀድማሉ:: ይህ እገዛ አይደለም::

የኢዮብ ወዳጆች ለኢዮብ ያደረጉለት ምርጥ የኀዘኔታ ሥራ ቢኖር፣ መጀመሪያ ላይ ብቻ ነው፤ ለ7 ቀናት ያህል አብረውት በዝምታ ሲቀመጡ (ኢዮብ 2፥13):: ("ዝም ካልከም ርዳታ ነው!" ትለኛለች እናቴ፣ በማይሆንልኝ ጉዳይ "ምን ልርዳሽ?" እያልኩ ልቧን ሳወልቅ::) ኢዮብም የሚለምናቸው ዝም እንዲሉ ነበር (13፥5)::

የኢዮብ ወዳጆች እንደዚህ ነው የሆኑት:: ኢዮብን ከማጽናናት ይልቅ መልስ ለመስጠት፣ ስለ መከራ አመጣጥ ለማስተንተን ነው የሞከሩት::

ኢዮብን በእምነት ማጣት እንደሚከሱት እንደ አንዳንድ ጨካኝ የዘመናችን ሰባኪዎች ሁሉ እነርሱም በኀጢአተኝነት ይከስሱት ጀመር:: ኢዮብን፣ "ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ" መሆኑን የመሰከረለት እግዚአብሔር ነው፤ ያውም በተደጋጋሚ (1፥8፤ 2፥3):: እግዚአብሔር እንዲህ የመሰከረለትን ሰው በእምነት ጒድለት መውቀስ ከጭፍንነት የሚመዘዝ ደፋር እርግጠኝነት ነው:: በዚህም ላይ ችግሩ ኢዮብ ላይ ለምን እንደ ተፈጠረ መጽሐፉ በግልጽ እያስረዳ (ሰይጣንና እግዚአብሔር ባካሄዱት ንግግር)፣ ኢዮብን ባለ ማመን መክሰስ አላዋቂነትን ብቻ ሳይሆን ግትርነትንም ያሳያል::

እንደዚህ ዐይነት ጓደኞቹን ኢዮብ፣ "እናንተ የምታደክሙ አጽናኞች ናችሁ" ይላቸዋል (16፥2):: አብዛኞቻችንም መጽናናት የሚገባቸውን ሰዎች የምናደክምና የምናስጨንቅ በመሆናችን ከዚሁ ጎራ ነው የምንመደበው:: በመከራ ያሉትን ሰዎች ማጽናናት የሚችለው በመከራ ያለፈ ሰው ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ ነው የሚነግረን፤ "እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፤ ስለ ዚህም፣ እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን" (2ቆሮ. 1፥4)::

በመከራ ማለፍ እውነተኛና ጠቃሚ አጽናኞች ያደርገናል:: ሄነሪ ኑዌን ደጋግሞ እንደሚለው፣ "እውነተኛ ፈዋሽ የቈሰለ ፈዋሽ ነው::"[31] ስለዚህም ሰላ ምንም ሆነ መጽናናትን ከፈለግን ከድኾች ጋር ድኻ፣ ከተናቁት ጋር የተናቀ፣ ከሕሙማን ጋር የሕማም ሰው የሆነው ጌታ ላይ ዐይናችንን ማሳረፍ አለብን:: እውነተኛ መጽናናት፣ እውነተኛ ፈውስ፣ እውነተኛ ሰላም፣ እውነተኛ ዕረፍት ያለው እዚያ ነው:: እርሱ የትኛውንም መከረኛ "የእጅህን ነው ያገኘኸው" በማለት መልሶ አያውቅም::

ራሱ በመከራ ዐልፎ የተጽናና ሰው በመከራ የሚያልፉ ሰዎች ሲገጥሙት ስለ መከራ ትንታኔ ለማቅረብና ሰዎቹን በእምነት ማጣት ለመንቀፍ አይጣደፍም:: የሰዎቹን መከራና ሕመም ለመረዳት ቅድሚያ ይሰጣል:: መልስ ለመስጠት ከመጣጣር ይልቅ ከመከረኞቹ ጎን መሆንን ይመርጣል፤ ኀዘናቸውን ይካፈላል:: ንግግራቸውን ብቻ ሳይሆን በንግግራቸው ውስጥ ያለውን ስሜት ያዳምጣል:: ውስጣቸው የተከማቸው ጥያቄና ቅይማት ወጥቶ እንዲያልቅ ዕድል ይሰጣል::

እግዚአብሔርም መጀመሪያ ኢዮብን ረዘም ላለ ጊዜ ዝም እንዳለው ይታወቃል:: ኢዮብ ገና የመጀመሪያውን ቃል ሲተነፍስ ምላሽ ያልሰጠው ለምንድን ነው? ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን ተናግሯል፤ እግዚአብሔርን ለሙግት ጋብዟል፤ እግዚአብሔር ግን ኢዮብ በልቡ ያለውን ሓሳብ ሁሉ ተናግሮ እስኪጨርስ ድረስ አልተናገረውም::



ለሁሉ መከረኛ መልስ ለመስጠት አንሞክር፤ ሁሉን አናውቅምና! እግዚአብሔር ለኢዮብ ጥያቄዎች መልስ አልሰጠም:: ይልቁኑ፣ ማን ነኝ ብሎ እንደሚያስብ ጠየቀው:: ፍሬዲሪክ ቡችነር እንደሚለው፣ ኢዮብ እንዲብራራለት የጠየቃቸውን ነገሮች ማብራራት የአነስታይንን ንድፈ ሓሳቦች ለትንሽ ልጅ እንደማስረዳት ነው::[32]

በመከራ ለሚያልፉ ሰዎች ስለ መከራው አመጣጥ ትንታኔ መስጠት ቀዳሚ ሥራችን ሊሆን አይገባም፤ ልናዳምጣቸው ነው የሚያስፈልገው:: "ሌሎችን ማገልገል ካለብን፣ ምን እንደሚሰማቸውና እንዴት እንደሚሰማቸው ማወቅ አለብን::"[33] ስለዚህ አስቀድመን አብረናቸው መሆንና ኀዘናቸውን መካፈል ይኖርብናል:: ሌላው ይደርሳል:: ደካማ የአካል ክፍሎች የበለጠ ትኩረት፣ የበለጠ ክብር እንደሚሹ ግን አንዘንጋ::

* * *

*"እግሬ ላይ ከተሰካው እሾህ የተነሣ፣ ጤነኛ እግር ካላቸው ሰዎች ይልቅ ወደ ላይ መዝለል ችያለሁ::"*

*ሶረን ኪርኪጋርድ*

ማስታወሻ


1. Joni Eareckson Tada, *A Place of Healing: Wrestling with the Mysteries of Suffering, Pain, and God's Sovereignty* (Colorado Springs: David C. Cook, 2010), 50.
2. Tada, *Place of Healing*, 31.
3. Nicholas Wolterstorff, *Lament for a Son* (Grand Rapids, Michigan: William B. Eerdmans Publishing Company, 1987), 59.
4. Tada, *Place of Healing*, 205.
5. Philip Yancey, *What Good is God? In Search of a Faith That Matters* (New York: FaithWords, 2010), 27.
6. Wolterstorff, *Lament*, 68.
7. Philip Yancey, *Soul Survivor: How My Faith Survived The Church* (London: Hooder, 1989), 238.

8. John Piper, *Desiring God: Meditations of a Christian Hedonist* (Nottingham, England: IVP, 2003), 270.
9. Piper, *Desiring*, 257.
10. C. S. Lewis, *A Grief Observed* (London: Faber and Faber, 1961), 32.
11. Wolterstorff, *Lament*, 6.
12. ዝኒ ከማሁ፣ 81
13. ዝኒ ከማሁ፣ 90፡፡
14. Philip Yancey, *Reaching for the Invisible God: What Can We Expect to Find?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2000), 139.
15. Wolterstorff, *Lament*, 80.
16. ዝኒ ከማሁ፣ 26፡፡
17. Piper, *Desiring*, 130.
18. Lewis, *Grief*, 33.
19. Piper, *Desiring*, 267.
20. Yancey, *What Good*, 30.
21. Tada, *Place of Healing*, 169.
22. Wolterstorff, *Lament*, 97.
23. Tada, *Place of Healing*, 86.
24. Philip Yancey and Dr. Paul Brand, *The Gift of Pain* (Michigan: Zondervan, 1997), 302.
25. Microsoft ® Encarta ® 2009. © 1993-2008 Microsoft Corporation. All rights reserved
26. Piper, *Desiring*, 80.
27. Philip Yancey, Brenda Quinn, *Meet the Bible* (Grand Rapids: Zondervan, 2000), 579.
28. Philip Yancey, *Prayer: Does It Make Any Difference?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2006), 325.
29. Tada, *Place of*, 44.
30. John S. Feinberg, *Where Is God? A Personal Story of Finding God in Grief and Suffering* (Nashville, Tennessee: Broadman & Holman Publishers, 2004), 29.
31. Yancey, *Soul Survivor*, 291.
32. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 244.
33. Feinberg, *Where Is God?*, 13.



# ጸሎታችንን ራሳችን ብንመልሰውስ?!

ብዙውን ጊዜ እራቴን ከአባቴ ጋር ነው የምበላው፤ ስለ ምግቡ የሚያመሰግነውም እርሱ ነው፡፡ እኔ ስለ ምግቡ የማመሰግነው ግን ከራበኝ ብቻ ነው፤ የእርሱ ጸሎት ስለሚረዝምብኝ፡፡ አንዳንዴ ሲርበኝማ፣ "በኢየሱስ ስም" ብዬ ብቻ ለመብላት እቸኩላለሁ፤ ያኔ፣ "ምግቡን ገሥጽከው እንጂ መቼ ጸለይክ?" ይለኝና እኔ እየበላሁ እርሱ እንደገና ጸልዮ ይከተለኛል፡፡ የባሰብኝ ጊዜ ደግሞ፣ "በልተን ብናመሰግንስ?" የሚል ጥያቄ አቀርባለሁ (ሰው ከበላ በኋላ አይደል፣ "ስብሐት" የሚለው?)፡፡ እናም እስከ ዛሬ ከእርሱ ጋር ለማዕድ ስቀርብ፣ እኔ ስለ ምግቡ የጸለይኩባቸው ወቅቶች በጣት የሚቈጠሩ ናቸው፡፡

በላተኛ ጓደኞችም አሉኝ ("ጓደኛህን ንገረኝና ማንነትህን ..." እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ)፤ "አባታችን ሆይ" ሲጸሊይ እንኳ "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" የሚለው ጋ ሲደረስ ነው ድምፃቸው ጐልቶ የሚሰማው፡፡ ከእነርሱም ጋር ስበላ ስለ ምግብ የመጸለይ ዕድል አላገኝም፤ ተጣድፈው ይጸልያሉ፡፡ ምግብ ቤት ብቻዬን በምበላበት ቀን ግን ዐይኖቼን ጨፍኜ እጸልያለሁ፡፡ ምናልባት ከተመልካቾች መካከል አንድ ሰው ሲጸለይ በማየት ብቻ የእግዚአብሔርን መኖር ቢማርስ? እያልኩ አስባለሁ፡፡ ትሪውን ግን በእጆቼ አጥብቄ እይዛለሁ ("እግዚአብሔርን አምናለሁ፤ ግመሌንም እሥራለሁ" እንዲል ዐረብ)፡፡

እንግዲህ የብዙ ሰዎችን የምግብ ጸሎት እንዳስተዋልኩት ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ ነው፡፡ አባቴ ሲጸልይ እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር ሳልሳሳት በውስጤ አብሬው ማለት እችላለሁ፤ የሌሎቹንም እንዲሁ፡፡ በርካቶች ስለ ምግብ ሲጸልዩ፣ "ያጡትን ወገኖች አንተ አስባቸው" ወይም "ይህን አጥተው ለሚንከራተቱ ከማያልቀው በረከትህ ስጣቸው" የምትለዋ ዐረፍተ ነገር አትቀርም፡፡

ለድኾችና ለተቸገሩ መጸለይ ብስለት ነው፡፡ መጸለያችን በውስጣችን ለድኾች ኀዘኔታ እንዲፈጠር ይረዳን ይሆናል፡፡ ጸሎታችን ሌሎች ሰዎችን ለዚህ ሰናይ ተግባር ሊያነሣሣ ይችላል፡፡ በመጸለያችን ብቻ ኀላፊነታችንን ተወጣን ማለት ግን አይደለም፤ ተግባሩም እኛኑ ይጠብቃል፤ ጸሎት ኀላፊነትን መሸሻ (ማምለጫ) አይደለምና!

አንዳንድ ሰዎች ጸሎትን የድርጊት ምትክ አድርገው ስለሚወስዱት፣ ትኾ (passive) ወደ መሆን ያመራል የሚል ሥጋት አለኝ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን በሁለቱ (በጸሎትና በሥራ) መካከል ምንም ዐይነት ተቃርኖ አላሳየም፡፡ ረጅም

ሰዓት በጸሎት ያሳልፍና ረጅም ሰዓት የሰዎችን ጉድለት (አስፈልጎት) ሲሞላና ችግራቸውን ሲፈታ ይውላል፡፡ በሐዋርያት ሥራ የምናያት ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ሥራ ነው ስትሠራ የነበረው፤ ጸሎትና ሥራን በቅጡ ማጣመር ችላለች፡፡ መበለቶችን ለመከባከብ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሐዋርያት መከሩ፤ ከዚያም ሌሎች መሪዎችን ለወሳኙ የጸሎት ሥራ ነጻ ለማድረግ ዲያቆናትን ጸልየው ሰየሙ (ሐዋ. 6፥1-7)፡፡ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ስላለው የባህል ውዝግብ አብረው ጸለዩና በመቀጠልም ማስማሚያ ሓሳብ ለማቅረብ ተሰበሰቡ (ሐዋ. 15)፡፡ ፊሊፕ ያንሲ እንደሚገልጹት፣

> ሐዋርያው ጳውሎስ ለቀደሙት አብያተ ክርስቲያናት በትጋት ቢጸልይም፣ በዚህ ሳይወሰን መልእክትና መመሪያ ይጽፍላቸውና ይጐበኛቸውም ነበር፡፡ ጸሎትንና ትግባሬን በእኩልነት ነው የሚያስኬደው፡፡ በመርከብ ጉዞው ወቅትም ከእርሱ ጸሎት የተነሣ ተሳፋሪዎቹ ሁሉ ከመርከብ አደጋ እንደሚተርፉ ካረጋገጠ በኋላ 276 ተሳፋሪዎችን ለማትረፍ ማስተባበርና መምራት ጀመረ (ሐሥ. 27፥21-25፤ 33-36)፡፡[1]

ጸሎታችንን በተግባር መደገፍ አለብን፡፡ ስለዚህ እኛ "ላጡት ወገኖች አንተው ራስህ ስጣቸው" በማለት ጸሎታችንን አድርሰን ቀሪውን ነገር ለእርሱ ልንተውለት አንችልም፡፡ ፊሊፕ ያንሲ ይቀጥላሉ፤

> አንዳንዴ፣ የሒሳብ የቤት ሥራውን ቤተ ሰቦቹ እንዲሠሩለት ጠይቆ እርሱ ቪዲዮ ጌም እንደሚጫወት ልጅ እኛም ራሳችን ልንሠራው የሚገባንን ነገር እግዚአብሔር እንዲሠራልን እንጠይቀዋለን፡፡ እስራኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ሌላ ትድግና ትፈልግ ነበር፤ "የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፣ ተነሥ፣ ተነሥ ኀይልንም ልበስ፤ በቀድሞው ወራትና በጥንቱ ዘመን በነበረው ትውልድ እንደ ሆንህ ተነሥ" በማለት ትጮኽ ነበር (ኢሳ. 51፥9)፡፡ ምላሹ የመጣው በቀጣዩ ምዕራፍ ላይ ነበር፤ "ጽዮን ሆይ፣ ተነሺ፣ ተነሺ፣ ኀይልንም ልበሺ" (52፥1)፡፡[2]

ከእነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች እንደምናየው ጸሎትና ትግባሬ በተጓዳኝ መጓዝ አለባቸው፡፡ "ላጡት ስጣቸው" ብለን ጸልየን ሥራውን ለእግዚአብሔር መተው መሠረት የለውም፡፡ "መልካሙ ጌታ ሆይ፤ የምንጸልይላቸውን ነገሮች ራሳችን መፈጸም እንድንችል ጸጋ ስጠን" እንዳለው ነው ሰር ቶማስ ሙር፡፡[3] ስለዚህ "ይህን አጥተው ለሚንከራተቱት ወገኖች አንተው ስጣቸው" የሚለውን ጸሎታችንን ራሳችን ብንመልሰውስ?



ስለዚህ ችግረኞችን መርዳት ኀላፊነታችን ሊሆን ይገባል፡፡ መጸለይ ብቻ ሳይሆን፣ ጸሎታችንንም ራሳችን መመለስ አለብን፡፡ ድኾችን መርዳት የወንጌሉ መሠረታዊ አካልም ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ከጌታ በተቀበለው ጸጋ ለሐዋርያነት ሲሰማራ የቤተ ክርስቲያን አዕማድ የሆኑት ያዕቆብ፣ ኬፋና ዮሐንስ ቀኝ እጃቸውን የሰጡት አንድ ዐደራ ጨምረው ነው፡፡ ይህንንም ሲናገር፣ "... ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤ ድኾችን እናስብ ዘንድ ብቻ ለመኑን፤ ይህንም ደግሞ ላደርግ ተጋሁ" ይላል (ገላ. 2፥10)፡፡

በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በከባድ ስደት ውስጥ ሆና እንኳ ድኾችን ትከባከብ ነበር፡፡ ያኔ ክርስቲያኖች ባሮችን ነጻ ለማውጣት ራሳቸውን ሸጠዋል፤ ድኾቹ ሳይቀሩ በልግስናና በጾም ይሰጡ ነበር፡፡ አረመኔው ንጉሥ ጁልያን ስለ ክርስቲያኖች ሲናገር፣ "እነዚህ አማልክት የሌሏቸው የገሊላ ሰዎች የራሳቸውን ድኾች ብቻ ሳይሆን፣ የእኛዎቹንም ይመግባሉ" ብሏል፡፡[4] ለድኾች በመራራት ጉዳይ የኢዮብ ሕይወትም አስተማሪነቱ ፈክቶ የሚወጣ ነው (29፥12፤ 30፥25፤ 31፥16)፡፡

ድኾችን የምናስብበት ቀዳሚው ምክንያት የወንጌሉ ዋነኛ አካል በመሆኑ ነው፤ ከላይ እንደ ተገለጸው፡፡ ጌታ ኢየሱስም የመጣው "ለድኾች የምሥራች ለመስበክ" መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ በተለይ ክርስቲያን ችግረኞችንና ቤተ ሰቦቻቸውን በሚመለከት ኀላፊነታችን ይጠነክራል (ገላ. 6፥10)፡፡

ቤተ ክርስቲያን ሁሉን አቀፋዊት እና የሁሉም ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው ስታጠምቅ ድርጊቱ ይመለከተናል፤ የተጠመቀው ሰው የእኛም ራስ ከሆነው እና አባል ከሆንንበት አካል ጋር ነው የሚያያዘው፡፡ አንድ ሰው ሲሞትም ሰው ሁሉ በአንድ ደራሲ የተጻፈ መድብል ነውና ጉዳዩ ይመለከተናል፡፡[5] አንድ ሰው ሲቸገርም እኛኑ የሚመለከት ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ ኀላፊነት ራሳችንን ልናገል አንችልም፡፡

የድኽነትን መነሻ ምክንያት መርምሮ ስለ ማግኘት መወያየቱ ምናልባት መልካም ሊሆን ይችላል፡፡ መጸለዩም ጥሩ ነው፤ የድርጊት ምትክ ግን ሊሆን አይችልም፡፡ ድርጊቱ ፍቅርን ያሳያል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ፍቅርን በመሆን ብቻ ሳይሆን በሚተርካቸው ውብ ታሪኮችም አስተምሯል፡፡ የደጉ ሳምራዊ ታሪክ ይኸው ነው፡፡ ሳምራዊው ፍቅርን በተግባር የገለጸው በባህልና በሃይማኖት የሚቃረነውን አይሁዳዊ በመርዳት ነው፡፡ እኛም ከእርሱ እንደተማርነው ድኾችን መርዳት ብንጀምርስ?

ቤተ ክርስቲያን የጌታ ኢየሱስ አካል መሆኗን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ስለዚህ የእኛ እጅ የእርሱ እጅ ነው፡፡ የእኛ ስጦታ የእርሱ ስጦታ ነው፡፡

እኛም ብንሆን እግዚአብሔር እንዲያደርግልን የጸለይናቸው ነገሮች በሰዎች በኩል ተደርገውልን ያውቃሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም "እግዚአብሔር ይስጥህ" ያልናቸውን እርሱ በእኛ በኩል ነው የሚሰጣቸው፡፡ ስለዚህ እኛ እንድንሰጣቸው ኢጅ እጃችንን ያያልና ይህንን ዐይነቱን ጸሎታችንን ራሳችን ብንመልሰው ያዋጣናል፡፡

በዘመናችን ብዙ የስኬት፣ የብልጽግና እና የመነቃቂያ መልእክቶችን ከቤተ ክርስቲያን እንሰማለን፡፡ ሰዎቻችንም በገንዘብና በቁሳቁስ ተባርከው አይተናል፡፡ ውድ መኪና ሲነዱ፣ ውድ ቤት ውስጥ ሲኖሩ፣ ውድ የኑሮ ዘይቤ ሲከተሉ የሚስተዋሉ አማኞች ቍጥር እየጨመረ ነው፡፡ በጤናማ መንገድ ያገኙት እስከ ሆነ ድረስ ይህ ክፋት የለውም፤ እነኚህ ወገኖች ለድኾች ማዘናቸውንና ድኾችን መርዳታቸውን መጠየቅ ግን አግባብ ነው፡፡ ሕይወት የሣቀችላቸው ሕይወት ላስለቀሰቻቸው በጥቂቱ እንኳ ካልራሩ ከሰው መፈጠራቸው ምኑ ላይ ነው!?

ዝናብ ቢኖር በጃችሁ
ምን ያደርጋል?
　　እንዲት ጠብታ ሞታችሁ፤
አዝመራችሁ ወፍ አይቀምሰው
የለማኝ አቁፋዳ አያውቀው፡፡
እንደሌላው አንድ አፍ ሲፈጥርላችሁ
አይደል የበደላችሁ?
ያዘመራችሁትን እንዳትበሉ
　　የጕሮሮአችሁ ጥበቱ፡፡
ያላችሁን እንዳታድሉ
　　የእጃችሁ እጥረቱ፡፡[6]

በተገኘው መንገድ ሁሉ ለራሳችን "ገንዘብ ለመሥራት" እየተጣጣርን፣ ለድኾቹ ግን "አንተ ስጣቸው" ብለን ጉዳዩን ለእግዚአብሔር የተውንለት ይመስላል፡፡ መዳናችንን የምንገልጽበት አንዱ መንገድ ለድኾች ማዘን አይደለምን?

ጌታችን፣ "ድኾች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና" (ማቴ. 26፥11) በማለት ሲነግረን ልባችንን ለመፈተን የቤት ሥራ መስጠቱ ይመስለኛል፡፡ ኀላፊነቱ የእኛ ነው፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንረዳው በምድር ላይ እግዚአብሔር ያቋቋማቸው ሦስት ተቋማት አሉ፤ እነዚህም ቤተ ሰብ፣ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን (የቅዱሳን ኅብረት) ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፡፡ ስለዚህም መንግሥትን ለጊዜው ከዚህ ብናወጣው፣ እንደ ቤተ ሰብና እንደ ቤተ ክርስቲያን ድኾችን መርዳት ኀላፊነታችን ነው፡፡



እንደ ቤተ ሰብ ጉዳዩ ይመለከተናል፤ እንደ ቤተ ክርስቲያንም ይመለከተናል፡፡ በንሆፈር እንደሚለው፣ "ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የምትሆነው ለሌሎች ስትኖር ብቻ ነው" (The church is the church only when it exists for others.)፡፡[7] ሆኖም በተለይ ይህ መልካም ሥራ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ እምብዛም ትኩረት እንዳልተሰጠው ይታወቃል (ኀላፊነታቸውን እየተወጡ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚኖሩ ግን ተስፋ አደርጋለሁ)፡፡ ረዳት የሚሹ፣ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ሲመጡ፣ "ለዚህ በጀት የለንም" ተብለው የሚመለሱበት ጊዜም ጥቂት አይደለም፡፡ ይህም የዲቁና አገልግሎትን በቅጡ እንዳልተረዳነው ያሳያል፡፡

የዲቁና አገልግሎትን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በውስን ኀላፊነቶች እንዲገደብ ልማድ አደረግነው እንጂ በዋናነት አገልግሎቱ ለድኾችና የድኾች ነው፡፡[8] ድኾችን በጊዜአዊነት መርዳት ብቻ ሳይሆን፣ መንግሥት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎቹ ድኾችን ከግምት እንዲያስገባና ጉዳት እንዳያገኛቸው መታገል ሁሉ አለብን፡፡ ወደ ድኽነት የከተታቸውን ምክንያት ከምንጩ ለማድረቅም መጣር የእኛው ኀላፊነት ነው፤ ማንም መጥቶ አይሠራልንም፡፡ ወንጌል የነፍስ መዳን ዋነኛ ትኩረቱ ቢሆንም፣ ከዚያም ያልፋል፡፡

በእርግጥ ሁሉን ነገር ለቤተ ክርስቲያን መተው አንችልም፡፡ እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን ትኩረቷን ለወንጌል ስብከትና የጽቀ መዝሙር ትምህርት ላይ እንድታደርግ ኀላፊነቱን ምዕመናን ልንወስድ ነው የሚገባው፡፡ የብዙዎች ራእይ መድረኩ ላይ መውጣት ሆኖ እንጂ ድኾችን መርዳት ሽሚያ ውስጥ የማንገባበት ያልተነካና የማያልቅ የአገልግሎት መስክ ሊሆነን ይችላል፡፡ የራሳችንን ድርሻ ከቤተ ክርስቲያን ድርሻ ጋር ማምታታትም የለብንም፡፡

እንደ ኅብረትም ብንታይ ብዙ ኅብረቶች አሉን፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የኮሌጅ ምሩቃን፣ የጸሎት፣ የሰፈር፣ የአካባቢ ተወላጆች ኅብረቶች አሉን (ከጽዋ ማኅበር በቀር)፡፡ እነዚህም በቻሉት መጠን ጉዳዩ ይመለከታቸዋል፡፡ "አንተው ስጣቸው" ብንለው፣ አምላካዊው ምላሽ "እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው" የሚል ይሆናል፡፡

"እግዚአብሔር ሞቷል" በሚለው ስብከቱ የታወቀው ፈላስፋ ፍሬድሪክ ኒቼ በክርስትና ላይ እንዲህ ጠንካራ አሉታዊ አመለካከት ለምን እንደ ያዘ ተጠይቆ ነበር፡፡ "የዳነ ሕዝብ መሆናቸውን የሚያስታውቅ ትንሽ ሁኔታ እንኳ ቢታይባቸው ኖሮ በድነታቸው አምን ነበር" ብሎ መልሷል፡፡[9]

እውነት የዳነ ሕዝብ እንመስላለን? የራሳችን ማማር ብቻ የሚያሳስበን ይመስል ጸሎታችን፣ ዝማሬአችን፣ ምስጋናችን ሁሉ ከ"እኔ" ጋር የተጣበቀ

ነው፡፡ የምንታወቀው በመብላት እንጂ (እምነታችን የመብል ሃይማኖት ይመስል) ድኾችን በማብላት አይደለም፡፡ የእኛ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ነዳያን የማይበዙት እነርሱ ለድኾች ይራራሉ ተብለን "ስለማንታማ" ሊሆን ይችላል፡፡ በአገራችን በሚደርሰው ተደጋጋሚ ድርቅና ድንገተኛ አደጋዎች ጊዜም የወንጌላውያን ክርስቲያኖች አስተዋጽኦ ጐልቶ አይስተዋልም፡፡ ምክንያቱም፣ ለተቸገሩ በትልልቅ እጆቹ እርሱ ራሱ (እግዚአብሔር) እፍስ አድርጎ እንዲሰጣቸው ጣጣውን ወደ እርሱ ትከሻ አሸጋግረናልና!

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር እንዲህ አለ፤ "ምሳ ወይም እራት ባደረግህ ጊዜ እነርሱ ደግሞ በተራቸው ምናልባት እንዳይጠሩህ ብድራትም እንዳይመልሱልህ ወዳጆችህንና ወንድሞችህን፣ ዘመዶችህንም፣ ባለጠጎች ጎረቤቶችህንም፣ አትጥራ፤ ነገር ግን ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ድኾችንና ጉንድሾችን፣ አንካሶችንም፣ ዕውሮችንም ጥራ፤ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ፤ በጻድቃን ትንሣኤ ይመለስልሃልና" (ሉቃ. 14፥12-14)፡፡

አንዳንዴ ቢሆንም የሰርጋቸውን ድግስ ጐዳና ተዳዳሪዎችን በማብላት ወይም ለድግስ ያዘጋጁትን ገንዘብ ለምግባረ ሰናይ ድርጅቶች በመስጠት የሚጋቡ ቡሩክ ሰዎች ያጋጥሙናል፡፡ ልጁ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ነው፡፡ ለሰርጉ 500 ሰው ለመጥራት ወስኗል፤ 5 አብሮ አደግ ጓደኞቹንና 495 ችግረኞችን፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ችግረኞች ወደሚበዙባት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የጋብቻ ሥነ ሥርዐቱን እዚያው ፈጸመ፡፡ የጌታም ትእዛዝ ይኸው ነው፡፡ ለመሆኑ ከጌታ ትእዛዛት መካከል የፈለግነውን ብቻ መርጠን መታዘዝና ያልፈለግነውን ደግሞ መተውና አለማመን ተፈቅዶልናል?

በየሳምንቱ የምንጠራባቸውን የሰርግ ሥነ ሥርዐቶችን ብቻ በማየት ተቃራኒው እየተፈጸመ መሆኑን መመስከር ይቻላል፡፡ ለሰርጋችን የምንጠራቸው ሰዎች ከዚህ በፊት እኛም ሆንን ወላጆቻችን ለበላነው ድግስ ብድር ለመክፈል የሚያበቁንና ነገ ደግሞ ብድር የሚመልሱልን ናቸው፡፡ በደስታችን ዕለት ብድራት የማይመልሱልንን ሰዎች ብቻ ብንጠራስ? ጌታን ለመታዘዝ ማለቴ ነው፡፡ ይህም ቢቀር እንኳ፣ በሰርግና በትዳር መካከል ያለውን ልዩነት ለምን ማየት እንዳቃተን አይታወቅም፡፡ ጥሩ ሰርግ ለጥሩ ትዳር ዋስትና ነው ብሎ የሰበከን ማን ነው? ስለዚህ የዘንድሮ ተጋቢዎች ድግስ መደገስ ቢያምረን እንኳ ድኾችንና ብድር የማይመልሱልንን ሰዎች በማብላት መታዘዛችንን ብንገልጽስ?

ድኾችን መርዳት በረከትንም ያመጣል (እዚህ ጋ የተሻለ ትኩረት እንደ ማገኝ ዐውቃለሁ)፡፡ "ለድኻ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፤ በጐነቱንም መልሶ ይከፍለዋል" (ምሳ. 14፥17)፡፡



በየአብያተ ክርስቲያናችን አምልኮ በዋናነት ከዝማሬ ጋር ተያይዞ ሲነገር እንሰማለን፡፡ ዘማሪዎቹም መድረኩ ላይ ሲወጡ፣ "በመንፈስና በእውነት" እግዚአብሔርን ስለ ማምለክ ሁሌም አጫጭር ገለጻ ያደርጉልናል (ምን ማለት እንደ ሆነ ባይነግሩንም)፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ ግን ስለ አምልኮ በመካከላችን ብዙም ያልተስተዋለ ሐሳብ አስተላልፎልናል፡፡ "ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፣ ... ነው" (ያዕ. 1፥27)፡፡

ድኾችን ስናግዝ እግዚአብሔርን በመካከላቸው ልናገኝ እንደምንችልም ማሰብ አለብን፡፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ ፍቅርና ደግነት ከልባችን የምንረዳው እዚያ ነው፡፡ እግዚአብሔር በድኾች መካከል ነው!

ጉዳዩ ፍርድም ያመጣል፡፡ ድነት በእምነት ቢሆንም፣ ፍርድ በሥራ ነው፡፡ ጽድቅ በሥራ አይደለም፡፡ ለጽድቅ ምንም አላዋጣንም፤ ማዋጣትም አንችልም፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍርድ በሥራ ላይ ተመሥርቶ ነው የሚካሄደው፤ እያንዳንዷ የሠራናት ነገር ትመዘናለች፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚለው፣ "በበጎ ሥራ በመጽናት ... የማይጠፋን ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል" (ሮሜ 2፥7)፡፡ ስለዚህ በእውነት የጸደቁ በበጎ ሥራ ይጸናሉ፤ የዘላለምንም ሕይወት ይቀበላሉ፡፡ በበጎ ሥራ ያልጸኑ ያልጸደቁ ናቸው፡፡

እኛ ጸጋ ላይ ብቻ ብናተኩርም መጽሐፍ ቅዱስ "ጸጋና ሥራ" እንጂ "ጸጋ ወይም ሥራ" አይልም፡፡ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ... መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" (ኤፌ. 2፥8-10፤ በተጨማሪም ፊል 2፥12-13)፡፡

ጌታ ሲመጣ፣ "ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር ነው" ብሏል (ራእ. 22፥12)፡፡ እንደ ሥራችን የምናገኝ መሆኑ ተደጋግሞ የተነገረ፣ ነገር ግን በቅዱሳን ዘንድ ችላ የተባለ አስተምህሮ ነው፡፡ መጽሐፉ ግን ደጋግሞ እንደሚናገረው እንደ እምነታችን ሳይሆን እንደየ ሥራችን ነው የሚከፈለን (መዝ. 62፥12፤ ኤር. 17፥10፤ ሮሜ 2፥6፤ 1ጴጥ. 1፥17)፡፡ ታዲያ ድኾችን ከመርዳት በላይ ዋጋ የሚያስገኝ ምን ሥራ አለ?

ጌታ ሲመጣ እረኛ በጎቹን ከፍየል እንደሚለይ ሕዝቡን እርስ በርስ የሚለየው በዚሁ ጉዳይ ነው፡፡ በቀኝ ያሉትን "እናንተ የአባቴ ቡሩካን ... መንግሥት ውረሱ፡፡ ተርቤ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፤ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ... " ይላቸዋል፡፡ በስተ ግራ ያሉትን ደግሞ፣ "እናንተ ርጉማን ... ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ፡፡ ተርቤ አላበላችሁኝም ..." ይላቸዋል፡፡ የሁለቱም ወገን ጥያቄ ተመሳሳይ ነበረ፤ "ጌታ ሆይ ተርበህ፣ ወይ ተጠምተህ ... መቼ አይተንህ?" የሚል፡፡ መልሱም ተመሳሳይ ነው፡፡ ርጉማኑን፣ "ከሁሉ ከሚያንሱ

ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም" በማለት ይመልስላቸዋል። ቡሩካኑንን ደግሞ፣ "ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት" ይላቸዋል (ማቴ. 25፥31-46)።

ጌታ ኢየሱስ አሁን በሥጋ አብሮን ቢሆን ኖሮ እያንዳንዳችን ለእርሱ ለማድረግ የምንናፍቃቸው ነገሮች ይኖሩናል፤ እነዚህን ያሰብናቸውን ነገሮች ዛሬ ለችግረኞች ብናደርግ ለእርሱ እንዳደረግን ይቈጠራል። ስለዚህ መንገድ በራብ የወደቀውን ሰው ስንመግብ፣ ኢየሱስን እንደምንግብ የሕመምተኛውን ቍስል ስንጠርግ የኢየሱስን ቍስል እንደምንጠርግ ማወቅ አለብን።

በዚህ ዓመት፣ እንዲህ ዐይነቱን አምልኮ ለመጀመር ብንወስንስ? በአካባቢያችን ካሉት ችግረኞች መካከል አንድ ልጅ ፈልገን የትምህርት ቤት ክፍያ በመክፈል፣ የዩኒፎርምና የዓመት ልብስ ወጪ በመሸፈን አምልኮአችንን ብንገልጽስ? "አሁን በመስጠት እናመልካለን" የሚባለው መባ ለመሰብሰብ ጊዜ ብቻ ነውን? ለየብቻ ማድረግ ካልተቻለ ለሁለትና ለሦስት ተባብሮ ማድረግም ይቻላል! ጸሎታችን እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ ምላሹ ላይም እኛው ብንተጋ ምናለበት!? የአንድ ሰውን እንባ እንኳ እንድናብስ እግዚአብሔር እጃችን እንዲፈለቅቅ ይርዳን!

## ማስታወሻ


1. Philip Yancey, *Prayer: Does It Make Any Difference?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2006), 113.
2. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 127።
3. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 125።
4. ሮበርትሰን መኩልከን (ትርጕም ገበየሁ አየለ)፤ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ ምግባር፣ የመግቢያ ሐሳቦች* (አዲስ አበባ፣ ኤስ አይ ኤም፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 567-568።
5. John Donne, *Devotions Upon Emergent Occasions* (Michigan: The University of Michigan Press, 1986), 109.
6. ደበበ ሰይፉ፤ *ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ* (አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም) ገጽ 33።
7. Dietrich Bonhoeffer, *Letters and Papers from Prison* (York: Macmillan, 1953), 382.
8. ስለ ዲቁና አገልግሎት በደንብ ለመረዳት ቀጣዩ መጽሐፍ ጠቃሚ ነው። ተፈሪ ሙዘይን እና ሲ/ር ኬርቱ ኒዩገሬን፤ *ዲቁና (ተግባራዊ ክርስትና)፤* (አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክ መካነ ኢየሱስ፣ 1998 ዓ.ም))።
9. Philip Yancey, *Church: Why Bother?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1998), 20.




# ደ'ሞ ምርጫ መጣ!

አንድ ጊዜ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን በስብከት እንዳገለግል ተጋብዤ ሳለ የመጋቢው ሚስት ወደ መጋቢው ቢሮ አስጠራችኝና፣ "እባክህን ቆ እዚህ አንዲት ሴት አለችና ልትጸልይላት ትችላለህ?" በማለት ጠየቀችኝ።

"ስለ ምንድን ነው የምጸልይላት?"

"ለማግባት ትፈልጋለች፤ ሆኖም እስካሁን ድረስ ባል አላገኘችም።"

"እሺ አስገቢያት።"

ወደ ቢሮው ስትገባ በደንብ አየኋት፤ ሠላሳ ዓመት የሚሆናት ሴተ ላጤ ናት።

"ባል ለማግኘት ስንት ዓመት ጸለይሽ፤ የኔ እኅት?" በማለት ጠየቅኋት። "ከዐሥር ዓመት በላይ" ብላ መለሰችልኝ።

"ታዲያ በእነዚህ ዐሥር ዓመታት ሁሉ እግዚአብሔር ጸሎትሽን እንዴት አልመለሰም?" ብዬ ጠየቅኋት። "ለመሆኑ ምን ዐይነት ባል ነው ስትጠይቂ የነበረው?"

ትከሻዋን ነቀነቀችና፣ "እንዴ! ይህማ የእግዚአብሔር ጒዳይ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል" አለች።

"ስሕተትሽ እዚህ ላይ ነው። እግዚአብሔር በጭራሽ በራሱ አንዳች አያደርግም፤ በአንቺ በኩል ብቻ እንጂ። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ምንጭ ነው፤ ይሁን እንጂ በአንቺ ጥያቄዎች በኩል ብቻ ነው የሚሠራው። እንድጸልይልሽ በትክክል ትፈልጊያለሽ?"

"አዎን!"

"እንግዲያውስ፤ አንድ ነጭ ወረቀትና እርሳስ አምጪልኝና ፊት ለፊቴ ተቀመጭ።" ልክ ቁጭ ስትል፣ "ለጥያቄዎቼ መልስ ከሰጠሽኝ እጸልይልሻለሁ። አንደኛ አንቺ አሁን ከልብሽ ባል ትፈልጊያለሽ፤ ታዲያ ምን ዐይነት ባል ነው የምትፈልጊው? ፈረንጅ፣ እስያዊ ወይስ ጥቁር?"

"ፈረንጅ።"

"እሺ፤ እንደ እርሱ ብለሽ ጻፊ። ሁለተኛ፤ አንድ ሜትር ከሰማንያ የሚረዝም ይሁን ወይስ አንድ ሜትር ከአምሳ ገደማ የሆነ አጭር?"

"እሱማ ቁመተ ረጅም ባል ነው የምፈልገው!"

"ይህንንም ጻፊው። ሦስተኛ፤ ባልሽ ቀጠን ብሎ የደስ ደስ ያለው ቢሆን ይሻልሻል ወይስ ደስ የሚል ወፍራም?"

"ኧረ ቀጭን ነው የምፈልገው!"

"እሺ፤ ቀጭን ብለሽ ጻፊ። አራተኛ፤ ምን ዐይነት ዝን ባሌ እንዲኖረው ነው የምትፈልጊው?"

"የሙዚቃ ዝንባሌ ይኑረው።"

"ደኅና፤ ሙዚቀኛ ብለሽ ጻፊ። አምስተኛ፤ ምን ዐይነት ሥራስ ይኑረው?"

"አስተማሪ።"

"ጥሩ፤ አስተማሪ ብለሽ ጻፊ።" እንዲህ እንዲህ እያልኩ ዐሥር ነጥቦችን ሳስጽፋት ቈየሁና፣ "እስቲ አንዴ ዝርዝሩን ጮክ ብለሽ አንብቢው" አልኳት። እያንዳንዱን ነጥብ ከአንድ ጀምራ እስከ ዐሥር ድምጿን ከፍ አድርጋ አነበበች። ከዚያም፣ "እስቲ ዐይኖችሽን ጨፍኚና የባልሽ ምስል አሁን ይታይሽ እንደሆን ንገሪኝ" አልኳት።

"አዎን በግልጽ እያየሁት ነው።"

"ጥሩ፤ አሁን እንዲመጣ እንዘዘው። በሐሳብሽ በግልጽ ካልታየሽ እንዲመጣ ልታዝ አትችይም፤ እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን ጸሎት አይመልስምና። መጸለይ ከመጀመርሽ በፊት በግልጽ ልታዪው ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ሽፍንፍን ጸሎቶችን አይመልስም።"

ስለዚህ ተንበረከከችና እጆቼን በላይዋ ጭኜ፣ "አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤ አሁን ባሏን ዐውቃዋለች። እኔም ባሏን አየዋለሁ። አንተ ደግሞ ባሏን ታውቀዋለህ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዘዋለን" አልኩኝ።

"እኅቴ ሆይ፤ ዝርዝሩ የተጻፈበትን ይህን ወረቀት ወደ ቤትሽ ውሰጂና መስታዎትሽ ላይ ለጥፊው። ማታ ማታ ከመተኛትሽ በፊት እነዚህን ዐሥር ነጥቦች ጮክ ብለሽ አንብቢያቸው፤ በየማለዳው ከእንቅልፍሽ ስትነቂም እነዚህኑ ዐሥር ነጥቦች እንደገና ጮክ ብለሽ አንብቢያቸውና ስለ መልሱ እግዚአብሔርን አመስግኚ።"



ከአንድ ዓመት በኋላ በዚያ አካባቢ ሳልፍ የአገልጋዩ ሚስት ስልክ ደውላ ጠራችኝ። "መጋቢ፣ ወደ እኛ ብቅ ብለህ ምሳ መብላት ይመችሃል?" ብላ ጠየቀችኝ።

"እሺ፤ እችላለሁ" አልኳትና ምሳ ልበላ ሄድኩ። ወደ ምንመገብበት ቦታ ስደርስም፣ "ልጅቷ እኮ አገባች! ያቺ ልጅ አገባች!" አለችኝ።

"ማናት ያገባችው?"

"ያቺ የጸለይክላት ሴት ናታ! ታስታውሳታለህ? እነዚያን ዐሥር ነጥቦች እንድትጽፍ ያደረካት ሴት? እርሷ ናት ያገባችው!"

"አዎ አስታውሳታለሁ! እስቲ ዝርዝሩን አጫውቺኝ?"

"በዚያኑ ክረምት አራት አባላትን የያዘ የመዝሙር ቡድን የመዝሙር አገልግሎት ለማቅረብ ለአንድ ሳምንት ያህል ወደ ቤተ ክርስቲያናችን መጥቶ ነበር። ከእነርሱ መኻል አንደኛው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙዚቃ መምህር ሲሆን፣ ገና ትዳር ያልመሠረተ በመሆኑ ወጣቶቹ ሴቶች በሙሉ ዐይናቸውን ጥለውበት ነበር። ስለዚህ አብረውት ጊዜ ማሳለፍ ቢፈልጉም ይህ ወጣት ግን ወጣቶቹ ሴቶች ትኲረቱን አልሳቡትም። ይሁን እንጂ በዕድሜዋ ከእነርሱ ከፍ ወደምትለው ወደዚያች ሴት ቀልቡ መወሰዱ አልቀረም። ታዲያ አዘውትሮ በዙሪያዋ ሲያንዣብብ ቈየና ከዚህ ከመሄዱ በፊት ለጋብቻ ጠየቃት። እርሷም ብዙም ሳታመነታ መስማማቷን ገለጠችለት።

"ከዚያም በዚያው ቤተ ክርስቲያን የጋብቻ ሥርዐቱን ፈጸሙ። በጋብቻቸው ቀንም እናቷ እነዚያ ዐሥር ነጥቦች ያሉበትን ወረቀት በሕዝቡ ፊት ካነበበችው በኋላ ቀዳደደችው።"

እናንተን የሚመለከትን ነገር እግዚአብሔር የሚሠራው ከእናንተ ጋር ነው። ስለዚህ ከጌታ ዘንድ መልስ ማግኘት የምትፈልጉ ከሆነ ፍላጐታችሁን በግልጽ ማሳወቅ አለባችሁ። ዝም ብላችሁ፣ "እግዚአብሔር ሆይ ባርከኝ፤ ባርከኝ!" አትበሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ያህል በረከቶች እንዳሉ ታውቃላችሁ? ከ8,000 በላይ ናቸው። እንዲሁ ብቻ፣ "እግዚአብሔር ሆይ ባር

> ከኝ" የምትሉ ከሆነ ምናልባት እግዚአብሔር፣ "ከ8,000 ከሚበልጡት የተሰፋ ቃሎች መካከል ምን ዐይነት በረከት ነው የምትፈልጉት?" ብሎ ሊጠይቃችሁ ይችላል:: ስለዚህ ግልጽ ሁኑ:: ማስታወሻ ደብተራችሁን አውጡና ጻፉት:: ከዚያ እዩት::[1]

ይህንን ታሪክ የተረኩት ኮሪያዊው መጋቢ ያንግ ቾ ናቸው:: ታሪኩ ስለ ትዳር ለማውራት ጥሩ መንደርደሪያ የሚሆን ይመስላል:: በእርግጥም የትዳር ጓደኛ ለማግኘት መጸለይ መልካም ነው:: ነገር ግን ይህ ጸሎት እንደ እግር ኳስ ጨዋታ ቴክኒክና ታክቲክ የበዛበት ነው (አቤቱ አምላኬ!)::

እግዚአብሔር ያለ እኛ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል ማሰብ ጤናማነት አይደለም፤ ትዕቢተኝነትም ነው:: እንዲህ ዐይነት ጸሎት ካልጸለይን እግዚአብሔር እንደማይሰማን መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም:: ይልቁኑ ክርስትና ላይ አንዳንድ የሩቅ ምሥራቅ ሃይማኖቶችን አስተምህሮ ለመቀየጥ የተደረገ ሙከራ እንጂ ክርስቲያናዊ ልምምድም አይደለም:: ምናልባት ጸሎቱ ውጤት ያስገኘ መስሎ ቢታይ እንኳ በአጋጣሚ እንጂ እግዚአብሔር ስለ ተቀበለው ላይሆን ይችላል!

ለመሆኑ የምናገባውን ሰው ከመተዋወቃችን በፊት ይህንን ያህል እናውቀዋለን ማለት ነው? ከመገናኘታችን በፊት ይህ ዐይነቱን ዝርዝር ከየት እናገኛለን? ለዚህ ለዚህማ እርጥቡን ጭቃ እግዚአብሔር ቢሰጠንና የምንፈልገውን ሰው እንደኛውኑ እኛው ጠፍጥፈን እንድንሠራ ቢፈቅድልን አይሻልም?

ይህ ታሪክ እንደ መመሪያ ከተወሰደም ችግር ያመጣል:: የአንዳንድ ሰባኪዎችም ችግር ይኸው ነው:: አንዲት ነጠላ ምሳሌ ወይም በአጋጣሚ የተከሰተ ነገር ይወስዱና አጠቃላይ መመሪያ ማድረግ ያምራቸዋል፤ መንገደ ብዙውን እግዚአብሔር በአንድ መንገድ ይወስኑታል:: ጌታ ኢየሱስ ጭቃ ቀብቶ ፈውሷል (ዮሐ. 9፥1-7)፤ ቃል ብቻ ተናግሮ ፈውሷል (ማቴ. 8፥5-13)፤ እየዳሰሰ ፈውሷል (ማቴ. 8፥1-3)፤ እየዳሰሱትም ፈውሷል (ሉቃስ 8፥43-45):: አሠራሩ ልዩ ልዩ ነው:: በነጠላ ተሞክሮዎች ላይ የተመሠረቱ ትምህርቶች ለማሳትና ለማሳሳት የተጋለጡ መሆናቸውን ማወቅም ይጠቅማል::

ትዳርን አንዳንዶች ሥጋዊ ብቻ ያደርጉታል፤ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረውን ይረሱታል:: ሌሎች ደግሞ ጉዳዩን በሙሉ መንፈሳዊ ያደርጉትና ያወሳስቡታል:: ስለዚህ በትዳራችን እኛ ለራሳችን ደስታ ማግኘታችን እምብዛም አስፈላጊ አይመስላቸውም:: ትዳር ግን ሥጋዊም መንፈሳዊም ነው፤ ለእኛም ለእግዚአብሔርም ጥቅም ነው::



ሆኖም ጋብቻ ሲጠቀስ፣ ማነው የሚመርጠው? ከሚለው ጀምሮ ነው እንደ ሜዳ አኽያ የተዝጎረጎረ ሓሳብ መንሣት የሚጀምረው:: ጀርመናዊው የነገረ መለኮት ሰው ቦንሆፈር ፍቅር ሲይዘው እንደተናገረው፣

> የትዳር ጓደኛን የመምረጥ ነጻነት በአምሳሉ ከፈጠረን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ ነው:: ለምድራዊ ተድላና ደስታ ያለን ፍላጎትም ከእግዚአብሔር ተደብቀን ሰርቀን የምናመጣው ነገር ሳይሆን፣ እንድንፈልገው እግዚአብሔርም የሚሻው ነገር ነው:: ይህ ጉዳይ እኛን ብቻ የሚመለከት አድርገን በማሰብ ከእርሱ ለመደበቅ በመሞከርም ሆነ በሃይማኖተኝነት ስም የፍላጎታችንን ሕልውና በመካድ ይህንን የሕይወት ክፍልና ጋብቻ ከእግዚአብሔር ልንነጥለው አይገባም::[2]

ዴሪክ ፕሪንስ የተባሉት ዕውቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ የትዳር ጓደኛን የሚመርጥልን እግዚአብሔር እንደ ሆነ በአጽንኦት ያስተምራሉ:: የመጀመሪያ ሚስታቸውን እግዚአብሔር ነበር የመረጣላቸው:: እኚህ ሚስታቸው ሲሞቱባቸው ደግሞ ባልገመቱት መንገድ እጃቸውን ይዞ ሁለተኛ ሚስት የሰጣቸውም እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይናገራሉ:: ስለዚህ ከራሳቸው ሕይወትና የአዳምና ሔዋንን ትዳር በማስተንተን "God Is a Match Maker" በሚለው መጽሐፋቸው የእግዚአብሔርን መራጭነት ያስተምራሉ:: ነጥብ በነጥብ ካስቀመጡት መዘርዝር ውስጥ ቀዳሚዎቹ 5 ነጥቦች እነዚህ ናቸው፤

1. በሰው ታሪክ መጀመሪያ ላይ ጋብቻን የጀመረው ራሱ እግዚአብሔር ነው:: ይህን በማቀድ ውስጥ ሰው አንዳችም አስተዋጽኦ አላደረገም:: ያለ መለኮታዊ መገለጥ ሰው ጋብቻን የሕይወቱ (የኑሮው) አካል ሊያደርገው ይቅርና ሊያስተውለው እንኳ አይችልም::
2. አዳም ማግባት እንዳለበት ውሳኔው የመጣው ከእግዚአብሔር እንጂ ከአዳም አልነበረም::
3. ሰው (አዳም) ምን ዐይነት ረዳት እንደሚያስፈልገው ያወቀው እግዚአብሔር ነው፤ አዳም አይደለም::
4. ሴቷን ለወንዱ ያዘጋጃትም እግዚአብሔር ነው::
5. ሴቷን ወደ ወንዱ ያመጣትም እግዚአብሔር ነው:: ወንዱ እርሷን ለማግኘት ፍሊጋ ማካሄድ አላስፈለገውም::[3]

ዶ/ር ማይልስ ደግሞ በዚህ አይስማሙም:: "እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ያቀራርበናል፤ መምረጥ ግን የእኛ ድርሻ ነው" ይላሉ:: እግዚአብሔር ሔዋንን ወደ አዳም ያመጣት ለሚስትነት ቢሆንም፣ እርሳቸውም ሐሳባቸውን ለማስረዳት ከአዳምና ሔዋን ሕይወት ነው የሚንደረደሩት::

> የእግዚአብሔር ኀላፊነት ሴቲቱን ወደ ወንዱ ማቅረብ ብቻ መሆኑን ማስተዋል ጠቃሚ ነው:: ለአዳም እግዚአብሔር አልመረጠለትም:: እርሷን ወደ አዳም በማቅረብ ላይ ብቻ ራሱን ገድቦ የሰውን የመምረጥ ችሎታ አከብሮአል:: አዳምም ያን ውሳኔ ለራሱ ወሰነ:: መረጣት:: ዛሬም እንዲሁ ነው፤ እግዚአብሔር የትዳር ጓደኛ አይመርጥላችሁም:: ይህንን ካደረገ የመምረጥ መብታችሁን መጣስ ይሆንበታል::
>
> እግዚአብሔር የትዳር ጓደኛ ከመረጠላችሁ፣ የመምረጥ መብታችሁን መጣስ ብቻ ሳይሆን፣ ለግንኙነታችሁ ኀላፊነት መውሰዱም ይሆናል:: ስለዚህ ግንኙነታችሁ፣ ስኬታማ ካልሆነ በእግዚአብሔር ልታሳብቡ ነው ማለት ነው:: ይህ ወሳኝ ነገር ነው፤ ምክንያቱም በዚህች ፕላኔት ላይ እግዚአብሔር ለእነርሱ አንድ ሰው ፈጥሮ ስለ ማስቀመጡ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው በርካታ ግለ ሰቦችን በማማከር አገልግዬ ዐውቃለሁና::
>
> የትዳር ጓደኛን በተመለከተ ሕይወት ወደ እናንተ ካቀረበቻቸው ግለ ሰቦች መካከል የሚሆናችሁን የመምረጥ መብትና ችሎታ (ብቃት) እንዳላችሁ መረዳት አለባችሁ:: የእግዚአብሔርን ቃል፣ ጥበብና ይህንን ምርጫ ለማካሄድ የሚያግዛችሁን ጠባይ ብትጠቀሙም ባትጠቀሙም ምርጫችሁ የሚያስከትለውን ውጤት ሙሉ ኀላፊነት መቀበል አለባችሁ:: ሆኖም ጉዳዩን ከልክ በላይ፣ "አታመናፍሱት" (መንፈሳዊ አታድርጉት):: ማቀራረብ የእግዚአብሔር ኀላፊነት ሲሆን፣ የትዳር ጓደኛችሁን መምረጥ ግን የእናንተ ኀላፊነት ነው:: የመንፈስ ቅዱስን እገዛ መተማመን ትችላላችሁ፤ የመምረጥ ኀላፊነታችሁን ወደ እርሱ ለማዛወር ግን አትሞክሩ::[4]

ዶ/ር ማይልስ ሐሳባቸውን ለማስረዳት ከአዳምና ከሔዋን መነሣት የነበረባቸው አይመስለኝም:: እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠራትም ሆነ ወደ አዳም ያመጣት ለሚስትነት መሆኑ ግልጽ ነው:: ዶ/ር ማይልስ ይህንን መቀበል አልፈለጉም:: እርሳቸው እንደሚሉት፣ አዳም የመምረጥ ዕድል ከነበረው ማንን ከማን አወዳድሮ ነው የሚመርጠው? ለመሆኑስ፣ አዳም ሔዋንን በሚስትነት ከመቀበል በቀር ሌላ አማራጭ ነበረው ወይ? ብለን ብንጠይቅ ምላሻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አልችልም:: ምናልባት ትኩረት ያደረጉት፣ የራሳችን ምርጫ በእኛው እጅ እንጂ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ እንዳልሆነ መናገሩ ላይ ይመስለኛል:: የአዳም ሕይወት ለዚህ ማስረጃ መሆን ባይችልም፣ ዶ/ር ማይልስ ግን በማስረጃነት ይጠቀሙበታል:: እኚህ ሰው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የሌላቸው ሌሎች አስደንጋጭ አስተምህሮዎችም እንዳሏቸው ይታወቃል::[5]



ችግሩ እዚህ ላይ ነው፤ የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትምህርት ያስተምራሉ፤ ሚዛናዊነት የሚፈለገው ለዚህ ነው:: ስለ ጋብቻ የምንሰማቸው ነገሮች አብዛኛውን ጊዜ ተቃራኒና እርስ በእርስ የሚጣረሱ ናቸው:: የዚህም ጽሑፍ ዓላማ አቋራጭ መንገድና ግልጽ መመሪያ (manual) ለማቅረብ አይደለም:: ለነገሩ ሰው ለመርሕ እንጂ ለደረቅ መመሪያ ለምን ይጨነቃል? ታዲያ እርስ በርሳቸው እንዲህ በተጣላለፉና በሚጋጩ መንገዶች መኻል የራስን መንገድ ፈልጎ ማግኘት አይከብድም?

ምን ይሄ ብቻ? "እንደ አዳም ብትተኙ ሚስት ታገኛላችሁ" ብለው የሚሰብኩንም አሉ፤ ሞኛቸውን ይፈልጉ! እንኳን ተኝተን ነቅተንም በሆነልን! ("በግ በመፍዘዙ ታረደ" ይላሉ እኅቶቼ):: ስንት ከብርሃን የፈጠነ ጭልፊት ባለበት መኝታ? የመኝታ ጊዜ ዐልፏል:: ሴቶች ነፍስ (ሕይወት) ያለው ወንድ ይወዳሉ፤ ሕይወት ያለው ደግሞ ይንቀሳቀሳል::

እኛ እንደ ይስሐቅ፣ ወላጆቻችን ደግሞ እንደ አብርሃም ሆነው የትዳር ጓደኛ እንዲመርጡልን (arranged marriage) የሚያስቡም ሞልተዋል፤ ይህም ዘመን ዐልፎበታል:: እንደ ያዕቆብ ሚስት ፍለጋ ለባርነት ራሳችንን በመስጠት ውድ ዋጋ እንዳንከፍልም በገበያው ላይ "አቅርቦቱ" ስለ በዛ የምንከፍለው ዋጋ እየቀነሰ ነው (ምናልባት ዕድሜ ከሰጠን ይከፈለንም ይሆናል!)::

ከዚህ ሁሉ ጭንቀት ሴቶች ቢጠይቁ (ቢመርጡ) ምናለበት? በሴት ስም ከተሰየሙት ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ የሩትን ታሪክ ስናነብ ለዚህ የሚሆን ድጋፍ እናገኛለን:: ሩት ማንነቷን ካስረዳችው በኋላ፣ "የትዳር ጓደኛዬ እንድትሆን እፈልጋለሁ" በማለት ቦዔዝን እንደ ጠየቀችው ተነግሯል (ሩት 3፥9 - የ1980 ትርጉም):: ("እስቲ ልጸልይበት፣ ላስብበት..." የማለት ወግ ብናይ እኛስ ይጠላብናል እንዴ?)

አንድ ጊዜ ተሰብስብን ስንጨዋወት አንዲት ጓደኛችን የነገረችኝን ልንገራችሁ:: የወደደችውን ወንድ መጀመሪያ፣ "ጓደኛ አለችህ?" ብላ ጠየቀችው፤ እንደሌለችው ነገራት:: "አብረን ብንሆን ደስ ይለኛል" አለችው ወዲያውኑ:: ሆኖም ይህ ጉዳይ ከባድ ጥንቃቄ ይፈልጋል:: እዚያው መኻላችን ከነበሩ ወን

ዶች በርካቶቹ፣ "ሴቶቹ ሲጠይቁን ቀርቶ፣ እኛ ጠይቀን ቶሎ 'እሺ' ሲሉን እንኳ ዋጋቸው ይቀልብናል" የሚሉ ተገኝተዋል:: እነዚህ ናቸው የወንዶችን ጣር የሚ ያበዙት (የሥራቸውን ይስጣቸው!)::

አንዳንድ ወንድ ይህን መቀበል ስለሚከብደው (ሽንፈት ስለሚመስ ለው) ሴቶችን ከባድ ዋጋ ሊያስከፍላቸው ይችላልና ሴቶች ወንድን ከመጠየቅ ቢታቀቡ ይመረጣል:: ወይም ወንዱ ስለዚህ ጉዳይ ያለውን የአረዳድና የአስ ተሳሰብ ልክ አስቀድመው መሰለል አለባቸው፣ ብዙም የሚያስኬድ ግን አይመ ስልም (እስቲ እግዜር ያሳያችሁ፤ በአበሻነት ላይ "የእኛ አገር" ከርስትና!)::

ወንዶች ትዳርን ስናስብ ትልቁ ጥያቄያችን ምርጫ ነው፤ ከምርጫ መሸሽ አንችልም (ምርጫ ደግሞ ችግር አያጣውም አይደል?):: አንድ ወገን ያሉ፣ "ዋናው ውጫዊ ውበት፣ ቁመናና ገጽታ ነው:: ውስጣዊውን ማንነትና ጠባይ፣ መንፈሳዊነትና አቋም ቀስ ብለን፣ ጊዜ ወስደን እናበጀዋለን" ይላሉ:: አንዳንዶቹማ የራሷ ማንነት ያላትን ሳይሆን፣ ባዶ ወረቀት የሆነች ሴት ተሰጥታ ቸው የፈለጉትን እንደሚጽፉባት ነው የሚያስቡት:: እራስ ልጅ ካላገቡ በቀር ይህ በውኑ ዓለም መቼም ቢሆን የማይከሰት ቅዠት ነው! ለወንድነት ያልተገባ ዋጋ መስጠትም ይመስላል::

በሌላ ጐን የሚገኙት ደግሞ፣ "ዋናው ውበት ውስጣዊ ነው:: ውጫዊ ውማ ለጥሩ ትዳር ዋስትና አይሆንም" ይላሉ:: "ውበት ሐሰት ነው፤ ደም ግባ ትም ከንቱ ነው" (ምሳሌ 31፡31) የሚለውን መሳይ ጥቅሶች ይጠቃቅሳሉ:: እንደ እነዚህኞቹ ከሆነ፣ ትዳርን ያህል ክቡር ነገር በማንኛውም ከፉ አጋጣሚ ሊጠፋና ሊበላሽ በሚችል ውጫዊ ሁኔታ ላይ ማሳረፍ ተገቢ አይሆንም:: በዚ ህም ላይ "ቆንጆ ሴቶች ቅብጥብጥ ይሆናሉ፤ ከነገሮችም ሁሉ በላይ በውበታ ቸው ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፤ ፈላጊያቸውም ብዙ ስለሆነ ውድ ናቸው" በማ ለት ይናገሩባቸዋል:: ሴቶቹም ቢሆኑ፣ "መልኩን ስጠኝ እንጂ፣ ሞያውን ከጐረ ቤት እማራለሁ" ብላ የጸለየችውን ሴት ይመስላሉ::

ለአእምሮዋ ቦታ ሳይሰጡ ውጫዊ ውበትን ብቻ በማየት ሚስት መም ረጥ አሥጊ ይመስላል:: ወደ ፊት ወገቧ ሲሰፋ፣ ጠጕሯ ሲሸብትና ሲሳሳ እን ዴት ነው አቶ ባል በእርሷ የሚደሰተው? ዋጋ የሰጣቸው ነገሮች ሁሉ እያረጁና እየወደቁ ነዋ! ጡቶቿ ሲወድቁስ፣ "[በ]ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ፤ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ" (ምሳሌ 5፡19) የተባለው ቃል እንዴት ነው የሚፈጸመው? ስለ ዚህ ከውጫዊ ነገር በዘለለ ለውስጣዊ ውበት፣ በተለይም ለአእምሮ ቦታ መስ ጠት ብልኅነት ነው:: ባለአእምሮ ሴት ማግባት፣ በብዙ መሠረታዊ ውሳኔዎች ላይ በሳል አማካሪ ከጎን አድርጎ መኖር በመሆኑ ከሁሉ የተሻለ ነው:: ሁል ጊዜም ደስ ለመሰኘት ይጠቅማል::



ሆኖም ሴቶች ለውበታቸው የሚሰጡት ትኩረትም ቀላል አይደለም:: ስለዚህ በየጊዜው "ቆንጆ ነሽ" እንዲባሉ ይፈልጋሉ:: በተጨማሪም የእነርሱ የሆነ ወንድ የሌላ ሴት ቆንጅና ሲያደንቅ ከሰሙ ጉድ ይፈላል:: በተለይ ተናጋ ሪው ሰው ተሳስቶ ከእርሷ ጋር ሲያነጻጽራት ከሞከረ ... (እኔ የለሁበትም!):: የራሱ ናትና ከሁሉ እንደምትበልጥበት ማወቅ አለበት::

ታዲያ ምን ተሻለ? Hardware ይሻለናል Software? ሁለቱን የምታ ሟላ ከተገኘችማ፣ "እሰይ ስለቴ ሰመረ" በማለት እየዘመሩ መጠቃለል ነው:: እዚህ ጋ መስተዋል ያለበት ነገር ትዳር የዕድሜ ሙሉ ስምምነት መሆኑ ነው:: ዛሬ የወደድነውን ነገር ዕድሜያችንን ሙሉ እየወደድን ለመቀጠል ስለምንወስን በውጫዊ ነገር ላይ ብቻ መመሥረት ምን ያህል ያስኬዳል? ውበት እንደ መነሻ መስህብ ብቻ ቢታይ የሚሻል ይመስላል:: አስደናቂ ነው ያላችሁትን ውበት ቀረብ ብላችሁ ስታዩት እንከን አታጡበትም፤ ከርቀት እንከን የለሽ ቢመስልም ጠጋ ስትሉ ብዙ ጉድለት ተሸክሞ ታገኙታላችሁ:: በዚህም ላይ ውበትን ሐሰሳ ከፊት ዐይንና አፍንጫ፣ ከኋላ ደግሞ ሌላ ነገር ስናይ ከከረምን ዐይናችን ተንከ ራታች ሆኖ መቅረቱ ነው::

ትኩስ ጎረምሳ ሳለሁ የገጠመኝ ነው፤ የሞላ ታክሲ ውስጥ ሆነን ስንጓዝ ከውጪ አንዲት ቆንጆ ታክሲውን ለማስቆም ምልክት ትሰጣለች:: የታክሲው ረዳት ሊጭናት ፈልጎ ሹፌሩ ታክሲውን እንዲያቆም ጠየቀው:: ሹፌሩ ግን ከፊቱ ትራፊክ ፖሊስ ሊያጋጥመው እንደሚችል ስለ ፈራ፣ "ሞልቷል እኮ፤ መከ ሰስ ፈልገሃል!" በማለት አስጠነቀቀው:: "አታያትም እንዴ እንዴት እንደምታ ምር! ይቺንስ እከሰስባታለሁ!" አለ ረዳቱ:: ሁላችንም ዞር ብለን አየናትና በንግ ግሩ ሣቅን፤ ሹፌሩን ግን ተቀየምነው ("ቢጭናት ምናለበት! ይከሰሳ!" እያልኩ ሳስብ የነበርኩት እኔ ብቻ ነበርኩ እንዴ?)::

ትምህርት ቤትና መሥሪያ ቤት አካባቢ የማውቃቸው "ቆንጆ የማያ ልፉ" በርካታ ወንዶች ነበሩ:: ሁሌም የተለያዩ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶችን ይዘው ነው የሚታዩት (አገሪቷስ የቆንጆዎች አገር አይደለች?):: ከእነዚህ ወንዶች መካከል ወደ ትዳር ውሳኔ የመጡቱ እንዳቸውም ቆንጆ ሴት አላገቡም:: ለብዙዎቻችን ጥያቄ ነበር:: እነርሱ ግን፣ ትዳር በመልክ ቆንጅና እንደማይመሠ ረትና እንዲያውም ውበት ለትዳር ይህ ነው የሚባል አስተዋጽኦ እንደሌለው በየጨዋታው ይናገራሉ:: ትዳር ከውበት ያለፈ ብዙ ነገር የሚጠይቅ ተቋም ነው::

ቆንጆ ማየት ደስ ይላል:: ሆኖም ውበትን መፍራት የምን "ፎቢያ" እን ደሚባል ባላውቅም፣ በጣም ጥቂት ወንዶች ቆንጆ ሴትን ማግባት ይፈራሉ::

አንድ ወቅት አንዱ ጐረምሳ በርቀት የሚያውቃትን ቈንጆ እንዲያግባቡት በጓደኞቹ በኩል በእጅ በእግር ገብቶ ተዋወቃትና ራት ጋበዛት:: በቅርበት ሲያያት በጣም ታምራለች:: ምንም ጣጣ ሳያበዛ የዚያኑ ቀን የልቡን ነገራት፤ "አሁን እንደማይሽ ከሆነ በጣም ታምሪያለሽና ይቅርብኝ:: ከዛሬ በኋላ ባንገናኝ ይሻላል" በማለት ራሱን ከውድድሩ አሰናበተ::

ቈንጆዎችን ብቻ የሚያሳድዱ ወንዶች ደግሞ ለሰው የሚኖሩ ይመስላል:: "አቤት ሚስቱ ስታምር!" እንዲባል ብቻ የሚፈልግ ወንድ ሞልቷል:: አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች ደግሞ ውጫዊውን ውበት ብቻ በማየት፣ "ትበዛበታለች (ይበዛባታል)" ማለት ይወዳሉ:: እንዲህ የተባለ ወንድ ደግሞ ከእርሱ ወስደው ለሌላ የሚሰጡበት እየመሰለው ሚስቱን ከቤት እንዳትወጣ ለማድረግ ይደከማል:: ቢሆንለት መላ አካሏን በ"ሂጃብ" ተሸፋፍና ብትኖር ይመርጣል:: ታዲያ ይህ ሰው "ሚስት አገባ" ነው የሚባለው፣ ወይስ ቤቱ ሴት አስቀመጠ?

አንዳንዶቹ ደግሞ እነርሱ የወደዷትንና የተቀበሏትን ሴት ሁሉም ጓደኞቻቸው "ቈንጆ ናት" ብለው ካላረጋገጡላቸው ይጨነቃሉ:: ከራሳቸው ምርጫ ይልቅ የጓደኞቻቸውን አስተያየት ያምናሉ:: በዚህ ነገር የተቸገረ ሰው የገጠመው ወዳጄ፣ "በማኅበር ነው እንዴ የምታገቧት?" በማለት ጠይቋል::

ስለ ውበት ሲነሣ፣ "ዋናው 'ስታይል' ነው" ባዮችም አይጠፉም:: "ስታይል" ሲባል አለባበስን፣ አረማመድን፣ አነጋገርን፣ አሣሣቅን ... ያካትታል:: ከአካል ጋር የሚስማማና እርስ በርሱ የተጣጣመ አለባበስ ለሚያዘወትሩ እኅቶች አድናቆት ይቸራሉ:: ልጅት "ስታይሊሽ" ከሆነች ሚዛን ትደፋባቸዋለች:: ከሰውነት ጋር የሚስማማና የቀለም ምርጫው የተጣጣመ አለባበስ ለተመልካች ብቻ ሳይሆን ለራስም ጥሩ ስሜት ሳይፈጥር አይቀርም::

አዳም ከዚህ ሁሉ የምርጫ "ሥቃይ" ተገላግሏል:: በጊዜው የነበረችው አንዲት ሴት ብቻ ስለነበረች ውበትን፣ አስተሳሰብንና ሞያን ተንተርሶ የማወዳደር የእኛ ዐይነት በረከተ-መርገም (blessing in disguise) አልገጠመውም:: ያኔ ልብስ ይለበስ ስላልነበር የእግዚአብሔርን የእጅ ሥራ በቀጥታ ከማድነቅ በቀር አለባበስን የመገምገምም "ዕድል" አልነበረውም፤ ሁሉን ነገር እንደ ወረደ መመልከት ግን ይችል ነበር::

ፍቅር ላይ የሚያተኩሩ ደግሞ አሉላችሁ፤ "ከተዋደድን ምንስ ብትሆን (ቢሆን) ምን ቸገረኝ?" ይላሉ፤ ፍቅር የትኛውንም መስፈርት ይሽራልና:: ለእነዚህ ፍቅር እንደ "ጆከር" ነው:: በሁሉ ቦታ ይገባል፤ ሁሉን ጉድለት ይሸፍናል፤ በሁሉም ነገር ይመነዘራል:: ፍቅርን ካነሣን አይቀር ፍቅርና ዘፈን ምን እንደሚያያይዛቸው ብጠይቅ ደስ ይለኛል::



ቀድሞ እሠራበት የነበረበት ቦታ አንዱ ፍቅር የያዘው ወጣት ቢሮ ውስጥ የፍቅር ዘፈን ካልተከፈተለት መሥራት አይችልም ነበር:: በተለይ የአስቴርን ዘፈን ካልሰማ መቆሚያ መቀመጫ ነበር የሚያሳጣን፤ በዚህ ላይ ያለቅሳል:: ዋናውን ስሙን ትተን፣ "ፍቅሩ" ብለን ነበር የምንጠራው:: በመጨረሻ ግን ከሚወዳት ልጅ ጋር ተጣልቶ ተለያየ (አቤት እንዴት እንደ ተደሰትን!):: ያኔ ከዘፈን ነጻ እንደምንወጣ ነበር ያሰብነው:: ሆኖም፣

> አሁን መጣ ቀረ የምለው የለ
>         የሚያናድደኝ የማናድደው፣
> የሚያስቀይመኝ የማስቀይመው፣
> ይቅርታ 'ሚለኝ ይቅርታ ምለው፣
> ነጻ ነኝ!

የሚል ዘፈን ይዞብን መጣ::

ይህ እዚያ ብቻ ሳይሆን እዚህም አጋጥሞኛል:: አንድ ክርስቲያን ወንድሜ ከሚወዳት ልጅ ጋር ለከሰዓት በኋላ ቀጠሮ ቢይዝም ገና በጠዋቱ መቁነጥነጥ ጀምሮታል:: ስንት ሰዓት እንደ ሆነ ጠየቀኝ (እጁ ላይ ግን ሰዓት አሥሯል):: ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ከአምስት መሆኑን ነገርኩት:: ትንሽ ቈየና፣ "አሁንስ?" አለኝ፤ "ከስድስት" ብዬ መለስኩለት:: በእርሱ ቤት ብዙ ቈይቶ መጠየቁ ነው:: ልቡ እንደ ጥንቸል ይበራል፤ ሰዓቱ ግን እንደ ዔሊ ይንቀራፈፋል:: ምን እየሠራ እንደሚቈይ ግራ ገብቶታል:: "በእናትህ፤ የፍቅር መዝሙር የለም እንዴ?" ብሎ ድንገት ጠየቀኝ (የዚያን ቀን እርሱ ባይኖርልኝ ኖሮ "የዕለት ሣቄን" ላጣ ነበር!)::

እኛ ሰፈር እኅቶቻችን የሚዘምሯቸው፣ "ናልኝ የእኔ ፍቅር፤ ናልኝ የኔ ጌታ" የሚሉ ዐይነት መዝሙሮች ብቻ ናቸው ያሉት:: አንዳንዶቹ መዝሙሮችማ "ኢየሱስ" የሚል ቃል ስለሌላቸው "እወድሃለሁ" የሚሉት ማንን እንደ ሆነ እጅግ ግራ ያጋባል::

ፍቅር ለትዳር ወሳኝ ቅመም ቢሆንም፣ ከአእምሮ ጋር ግን መፋታት የለበትም:: ሰዎች ነንና ስናፈቅርም መዝነን ነው፤ ያ ሰው የሚወደድለት ነገር ያለው በመሆኑ ለእኛ እንደሚሆነን በማሰብ ነው:: አንዳንዴ የፍቅርን ሸንጋይነት ያዩ ሌሎች ወገኖች ግን ፍቅር ላይ *ብቻ* ተማምኖ ትዳር መመሥረትን ይቃወማሉ:: እስቲ፣ "ፍቅር ወደ ትዳር መምራት አለበት" በማለት ለሚያሳስባት ፍቅረኛዋ አንዲት እኅት ከጻፈችለት ማስታወሻ ላይ ጥቂት እንቃርም፤

> ፍቅር ወደ ጋብቻ የሚያደርስ ድልድይ ነውን? ነው ወይ? ፍቅር'ኮ የጠቆረውን አፍዝዞ፣ የቆሸሸውን ንጹሕ አርጎ የሚያሳይ ሰፊ መነፅር ነው:: ፍቅር ጥላቻን ከልሎ፣ ጉድለትን ሞልቶ፣ ሸፋፍኖና አሳምሮ የሚያቀርብ ውሸታምና ደላይ መጽሐፍ ነው::
>
> ፍቅር ዳሰሶ ብቻ የሚገምት በትክክል የማያይ ሽማግሌ ነው:: ፍቅር እውነት ሊሆን ይችላል፤ ፈጽሞ ግን እውነተኛ አይደለም:: ድልድይም ከሆነ ሩቁን ቅርብ፣ ጥልቁን ባሕር ትንሽ ኩሬ አድርጎ የሚያሳይ ከፋተኛ ድልድይ ነው:: እና ፍቅርን አምኖ ሰው ወደ ጋብቻ ይሂድ? እውነት ለመናገር ሰው ወደ ጋብቻ ለመሄድ አእምሮ በተባለ ሌላ ድልድይ ቢሄድ ገደሉ እንዴት ስምጥ፣ ባሕሩም እንዴት ሰፊ እንደ ሆነ መረዳት ይችላል::
>
> ጋብቻና ፍቅር ለየቅል ናቸው:: ራሱን ስለ ሌላው መሥዋዕት የሚያደርግ ሰው ቀስ እያለም ቢሆን የአንድን ሰው ልብ ማግኘቱ አይቀርም:: ያኔ ፍቅር በሚባለው ጊዜያዊና ተወዛዋዥ ማገር ምትክ፣ መዋሐድ የተባለ ብርቱና ጠንካራ ምሰሶ ይተከላል:: በእንደዚህ ዐይነት ሕይወት ውስጥ ጸጸት የለም:: ጸጸት የሚኖረው ፍቅር ባለበት ቦታ ብቻ ነው::[6]

ትዳር በፍቅር ላይ መመሥረት ያለበት መሆኑ እውነት ነው:: ምክንያቱም፣ ፈታውራሪ ተክለ ሐዋርያት እንደሚናገሩት፣

> ፍቅር ኀይለኛ ሠንሠለት ነው:: በብርቱ ያስተሳስራል:: ፍቅር በሌለበት ስፍራ ቁም ነገር አይበቅልም:: ፍቅር የሌለበት ስፍራ እንደ ጭንጫ መሬት ነው:: ፍቅር የሌለበት ልብ በበረዶ እንደ ተሞላ ማሰሮ ነው::[7]

ሆኖም ፍቅር ስሜታዊነት እያጣውምና ብዙ ጊዜ ውሳኔ ሲያዛባ እንመለከታለን:: ስለዚህ ስናፈቅር ዐይናችንን ጨፍነን መሆን የለበትም:: ማየት፣ ማመዛዘን፣ መመዘን፣ ዋጋን መተመን ያስፈልጋል:: ፍቅር ውሳኔም ነውና በስሜት ብቻ ባን'መራም፣ ስሜታችንንም ማዳመጥ አለብን:: ስሜት አለቃ መሆን ባይኖርበትም፣ ችላ መባልም የለበትም::

ተመሳሳያቸውን አሳድደው የሚጠብሱም አሉ:: "ባልና ሚስት ከአንድ ባሕር ይቀዳሉ" ሲባል ሰምተው ይመስለኛል:: በኒውተን ሕግ መሠረት ካየነው ግን፣ "ተመሳሳዮች ይገፋፋሉ፤ ተቃራኒዎች ይሳሳባሉ":: ስለዚህ ቶሎ ቢሰለቻቹ አይገርምም:: ሰው በሁሉ ነገር ራሱን የምትመስል ሴት አግኝቶ ምን ዐይነት ጣዕም ያለው ኖሮ ሊኖር ነው? "ከአንድ ምንጭ" የሚል ግጥም እነሆ!



> "ባልና ሚስት ከአንድ ባሕር ይቀዳሉ" ብሎ
> ተመሳስሎን ወ'ዶ
> ልዩነት አጉድሎ
> እኔ ካለሁበት
> ጨው አልባ ባሕር ላይ
> እሱም ተጨልፎ፣
> እንኖረው ጀመር
> ጣዕም ያጣ ሕይወት
> በማር አልባ ቀፎ![8]

በሁሉ ነገር ከራሱ ጋር የምትመሳሰል ሴት ለማግባት የሚፈልግ ሰው በእኔ አተያይ ራሱን ለማግባት የሚፈልግን ሰው ይመስላል:: ስለዚህ እንዲህ ዐይነት ሰው ሚስት ከማግባቱ በፊት ራሱን ከመፍታት መጀመር አለበት::

ተቃራኒያቸውን የሚያስሱም አጋጥመውኛል:: "እኔ ወንድ እርሷ ሴት፣ እኔ የመድረክ ሰው እርሷ ደግሞ የጓዳ፣ እኔ አንባቢ ስሆን፣ እርሷ ጸሎተኛ ናት" ብሎ ተናግሯል አንድ ሰባኪ:: የእኔ ዐይነቱ ዝርክርክም ጠንቃቃ ሴት ቢያገኝ አይጠላም:: ገንዘብ በታኙ ከ"ቋጣሪ"ዋ ጋር፣ ተናጋሪው ከዝምተኛዋ ጋር ቢጋጠም ውበት ይኖረው ይሆናል:: በመሠረታዊ ነገሮች ላይ እንኳ መመሳሰል ሳይኖር፣ በሁሉ ነገር ተቃራኒ ከሆኑ ግን ትዳር ድካም ይሆናል:: አንዱ የሚገነባውን ሌላው እያፈረሰ እንዴት ይዘለቃል?

ብቻ ሂደቱ አድካሚ ነው:: መግቢያችን ላይ እንዳየነው ጸሎት ዐይነት ሁሉን በነጥብ በነጥብ ለማስቀመጥ እንሞክር ብንል የሚሆን አይደለም:: ከዚህ ይልቅ ሕይወት ወደምትመራን እየተከተልን እግዚአብሔር ከሚያቀራርበን ሰዎች መካከል የእኛን ሰው ዐይናችንን ከፍተን መፈለግ ይበጃል፤ ስሌቱን ግን መተው ሳይሻል አይቀርም::

በተጨማሪም "ሰጥቶ መቀበል" ጥሩ ስለ መሆኑ ብዙ ሰምተናል ብዬ እስባለሁ:: ሆኖም "ሰጥቶ መቀበል" ከሚለው ይልቅ ብዙዎቻችን "ተቀብሎ መስጠት"ን ነው የምንመርጠው:: "ጌታ ሆይ ጥሩ ሚስት (ባል) ስጠኝ" ብለን እንጸልይ የለ? ከዚህም ይልቅ፣ "ጌታ ሆይ ጥሩ ሚስት (ባል) አድርገኝ" ማለት ሳይሻል አይቀርም:: ምክንያቱም ለትዳር ጓደኞቻችን አስቸጋሪነት የእኛም አስተዋጽኦ ይኖርበታልና፤ ከፋትም እኮ ተባባሪ ይፈልጋል!

አምሳ እግር ለተባለ የትል ዐይነት፣ "ለመሆኑ ስትራመድ የትኛውን እግርህን ታስቀድማለህ? ከዚያስ? እነዚህን ሁሉ እግሮችህን በምን ቅደም ተከተል ነው የምትጠቀማቸው?" የሚል ጥያቄ ቀረበለት ይባላል:: አምሳ እግሩም

ሲጓዝ የትኛውን እግሩን አስቀድሞ የትኛውን እንደሚያስከትል እያሰበ ለመጓዝ ሞከረ፤ አቃተው:: ደጋግሞ ቢሞክርም እግሮቹ እየተጠላለፉበት ከመውደቅ በቀር መራመድ አልቻለም:: ከብዙ ሙከራ በኋላ በሰላም ለመጓዝ የበቃው የእግሮቹን ቅደም ተከተል ማሰላሰሉን ትቶ በነጻነት መራመድ በመጀመሩ ነበር:: የአካሄዱን ቀመር ማወቅ አልቻለም፤ ካሰበውና ካለመው ቦታ መድረስ ግን ችሏል:: ተግባባን?

እኔም የቀናኝ እንዲህ ነው!

## ማስታወሻ


1. Dr. Paul Yonggi Cho, *The Fourth Dimension: The Key to Putting Your Faith to Work for Successful Life* (Plainfield, New Jersey: Logos International, 1979), 18-22.
2. Eric Metaxas, *Bonhoeffer - Pastor, Martyr, Prophet, Spy: A Righteous Gentile Vs. The Third Reich* (Tennessee: Thomas Nelson, 2010), 457.
3. Derek Prince, *God Is a Matchmaker: Let Him Choose!,* (UK, Derek Prince Ministries, 1986), 48-49.
4. Myles Munroe, *Single, Married, Separated and Life After Divorce* (Shippensburg, PA: Destiny Image Publishers, 1992), 13-14.
5. ይህን ለመረዳት ስለ ጸሎት የጻፋትን መጽሐፍ ማንበብ በቂ ነው:: በዚያ መጽሐፍ የምድር ባለቤት ሰው እንደ ሆነና እግዚአብሔር እንኳ በሰው ሳይጋበዝና ሰው ሳይጠራው ወደ ምድር ከመጣ *ሕገ ወጥ* እንደ ሆነ ደፍረው ጽፈዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር መሆኗን ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎችን አስቀድሞ ለሥራው የሚጠራውና የሚጋብዘው እርሱው መሆኑን ያስተምረናል::
6. በጸሓፊዋና በተጻፈለት ሰው ሙሉ ፈቃድ የተካተተ::
7. ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፤ *ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)* (አዲስ አበባ፣ አአዩ ፕሬስ፣ 1999 ዓ.ም) ገጽ 131::
8. ሜሮን ጌትነት፤ *ዙረት* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 55::




# የንጽሕና ዋጋ

ሁለት ፍቅረኛሞችን እንውሰድ:: እነዚህ ፍቅረኞች እጅግ ይዋደዳሉ:: ከተቻለ ያላቸውን ክፍት ጊዜ ተጠቅመው፣ ካልተቻለም ትርፍ ጊዜ ፈጥረው አብረው ያሳልፋሉ፤ አብረው ይዝናናሉ፤ ሲኒማና ቲአትር ይመለከታሉ:: አንድ ቦታ ለሰዓታት ተቀምጠው ያለ መሰልቸት ዐይን ለዐይን እየተያዩ ያወራሉ::

ይህ በጋራ የሚያሳልፉት ጊዜ ለእነርሱ *ሥቃይም* ነው፤ *የሥጋ ፈተናም* ውስጥ ይከትታል:: ሰዎች ሲፋቀሩ፣ አብረው ጊዜ ማሳለፍ ሲያበዙ፣ ፍቅርን መግለጽና መነካካቱ ሲጨምር ወሲብ የመፈጸም ውስጣዊ ግፊቱም አብሮ ያድጋል:: ስለዚህ በኀጢአት የሚወድቁበት ፈተና ይጨምራል:: "እሺ ተገናኝተን ተጫወትን፣ ተነካካን፤ ከዚያስ ምን? ቀኑን ሙሉ እንዲሁ ዐይን ዐይኑን ሳየው ልዋል እንዴ? …" በማለት ጠይቃለች አንዷ ስትጠየቅ::

እግዚአብሔር በጋብቻ በተሳሰሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት መካከል ብቻ እንዲፈጸም ያቀደው ቡሩክ ጥምረት ነው፤ ወሲብ:: ስለዚህ እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ፈቃዱን ለመፈጸም ከፈለጉ "ፍቅሩና ፍቅርተ" በ*ሥቃይ* ነው የሚኖሩት:: በዚህ በኩል እግዚአብሔር አለ፤ በዚያ በኩል ከሚያፈቅሩት ሰው ጋር "ፍቅር *የመሥራት*" ብርቱ የነፍስ ረኻብ አለ:: *ሥቃዩ* ደግሞ የአንድ ቀን አይደለም፤ ፍቅረኛን ባሰቡ፣ ባዩ፣ በናፈቁና ባገኙ ቍጥር ይቀሰቀሳል:: አፍቃሪ የእሳት ቋያ በጉያው ታቅፎ ነው የሚኖረው::

እነዚህ ወጣቶች ከነፍሳቸው ጉትጎታ ይልቅ እግዚአብሔርን አክብረው በዚህ *ሥቃይ* ውስጥ ሲያልፉ እግዚአብሔር ምን ይል ይሆን? ተፋቃሪዎቹ ብርቱ ፍላጎታቸውን እንደሚቃጠል መሥዋዕት ሲያቀርቡ እግዚአብሔር አይደሰትምን? የነፍሳቸውን ጩኸት፣ የሥጋቸውን ጥያቄ እምቢ ብለው፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መከተላቸው የሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ማቅረብ አይደለምን? *ሥቃያቸው* በፊቱ ዋጋ የለውምን?

ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ በብሉይ ኪዳን የተለመደ ሃይማኖታዊ ተግባር ወይም አምልኮ ነበር::

በአዲስ ኪዳንም ይህ መሥዋዕት የማቅረብ አካሄድ መልኩን (ቅርጹን) ቀየረ እንጂ ከነአካቴው አልቀረም:: የምሥጋና መሥዋዕት እናቀርባለን፤ የምን

ወደውን ነገር ለእግዚአብሔር ስንል እንተዋለን፤ ጠቦት ባናቀርብም ራሳችንን፣
ሰውነታችንን፣ ነፍሳችንን መሥዋዕት አድርገን እናቀርባለን፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንኑ ነው የሚነግረን፤ “ሰውነታችሁን
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀ
ርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚ
መች አገልግሎታችሁ ነው” (ሮሜ 12፥1)፡፡

ፍቅር መሥዋዕትነትን አዝሏልና አሁንም ስለ ፍቅር ላንሣ፡፡ ልጅት
እጅግ የምታፈቅረው ሰው ውጭ አገር ነው የሚኖረው፡፡ እንኳን ፈረንጅ አገር፣
ክፍለ አገር ሄዶ ለጥቂት ጊዜ መለያየት እንኳ ለአፍቃሪ ምን ዐይነት ጣር እንደ
ሆነ ለማስረዳት አልሞክርም፡፡ አጠገብ ለአጠገብ ተቀምጦ መነፋፈቅም እንዳለ
ካፈቀረ በቀር ማን ሊገባው ይችላል? ልጅቱ ነጋ ጠባ ሓሳቧም፣ ጸሎቷም ልጁ
ያለበት አገር ሄዶ ከእርሱ ጋር መኖር ነው፡፡ እርሱ እዚህ መምጣት አይችልም፤
ወይም አይፈልግም፡፡ ጊዜው ደግሞ ባለክንፍ ነው፤ ይበርራል፡፡ ሰው ከዐይን
ሲርቅ ከልብም የመራቁ ሥጋት፣ ትስስራቸውን እንዳያላላው ትባባለች፡፡ ታዲያ
ምን ታድርግ? ወደ እርሱ ለመሄድ የሞከረችበት ሕጋዊ መንገድ ሁሉ አልሳካ
እያላት ተቸገረች፡፡ ምን ተሻላት?

በውሸት ወይም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለመሄድ መሞከር ሌላው አማ
ራጭ ነው፤ ይሳካላትም ይሆናል፡፡ በዚህም የዘመናት ሕመሟን፣ ጸሎቷን፣ ምኞ
ቷንና ጥሟን ማርካት ትችላለች፡፡ የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ከቈረ
ጠች የምትወደውን ሰው ማጣቷ አይቀሬ ነው፤ ያደረገችውም ይህንኑ ነው፡፡
የነፍሷን መሻት፣ ደስታዋን፣ ሕልሟን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በማቅረቧም
እግዚአብሔርን እንዳስደሰተች ታምናለች፡፡

### “ሕያው … መሥዋዕት”

በብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ሲቀርብ፣ እሳቱ ከመለኮሱ በፊት እንስሳው ይታረ
ዳል፡፡ ደሙም ሲፈስስ በደሙ ውስጥ ሕይወት አለና ሕይወቱ ይፈስሳል፡፡
የሚታረደው እንስሳ የሚታረደውም፣ የሚቃጠለውም በነሐሱ መሠዊያ ላይ
ሲሆን፣ መሠዊያው ደግሞ አራት ቀንዶች አሉት (ዘፀ. 27፥1-8፤ 38፥1-7)፡፡
እንስሳው እነዚህ ላይ ስለሚታሰር በሕይወት የማምለጥ ዕድል አይኖረውም፡፡
ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ “ሕያው … መሥዋዕት” ሲል እኛም ሳንታረድ
እንቀርባለን ብለን አንጠብቅ፡፡ “እናንተ ደግሞ ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ ግን
በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ
ራሳችሁን ቍጠሩ” ይላልና (ሮሜ 6፥11)፡፡



ሕያው ማለት አንዴ ካቀረባችሁት በኋላ ዳግመኛ የማታነሡት ማለት
ነው፡፡ ፍቅረኛሞቹ ከዝሙት የሚርቁት ለአንድ ቀን ብቻ አይደለም፤ ትዳር
እስኪመሠርቱ ድረስ ነው፡፡ መሥዋዕትነት ስብከት በሰማን ጊዜ በሞቅታ ቃል
የምንገባውና ቀናት ሲያልፉ የምንረሳው አይደለም፤ ሁሌ የሚቀርብ ነው፡፡
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስንመላለስ፣ ስሜታችንን የማያስደስት ነገር ሲያጋጥ
መን ካልሞትን ከመሠዊያው ላይ ወርደን መሄዳችን አይቀርም፡፡ ግና የተጠየቅ
ነው በስሜታዊነት ላይ ያልተመሠረተ ዘላቂ መሥዋዕትነትን ነው፡፡

ሰውነታችንን (ሥጋችንን) መሥዋዕት አድርገን እንድናቀርብለት እግዚ
አብሔር ይጠይቃል፤ ይጠብቃልም፡፡ በዚህ ዐይነቱ መሥዋዕት እግዚአብሔር
ይደሰታል፡፡ አንዳንዶች አንዴ በጸጋው ድነናልና ከእንግዲህ ተቀደስን አልተቀ
ደስን እግዚአብሔር ጉዳዩ አይደለም በሚል ልቅነትን ሊያበረታቱ ይችላሉ፡፡
ሌሎች ደግሞ፣ “መቀደስ አለብን፤ ሆኖም ሥጋ ደካማ ነው” በሚል በሥጋቸው
ላይ ሥልጣን እንደሌላቸው ይናገሩ ይሆናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ግን፣ “መሥዋ
ዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ” ሲል
ይማጸናል፡፡

እግዚአብሔር እኛኑ ራሳችንን ይፈልገናል፡፡ እርሱም የሰጠን ራሱን
እንጂ በዙፋኑ ዙሪያ ካሉት መላእክት አንዱን አይደለም፡፡ እግዚአብሔር፣
“ወድጃችኋለሁ” ሲል፣ “በምን ወደድከን?” ብለው የጠየቁትን ሰዎች ምናቸው
ንም ሳያይ እንዲሁ እንደ ወደዳቸው ነግሯቸዋል (ሚል. 1፥2)፡፡ እኛንም የወደ
ደን ከምንም ተነሥቶ አይደለም፤ እንዲያውም ልንወደድ የሚገባን አልነበር
ንም፡፡ ታዲያ ነፍሳችንን መሥዋዕት ብናቀርብለት ይበዛበታል? ይህ ፍቅር የገ
ባው ሰው ራሱን (መሥዋዕቱን) ለእግዚአብሔር ይቀድሳል፤ መሥዋዕት አድ
ርጎ ያቀርባል፡፡

ገንዘባቸውን ለእግዚአብሔር ሥራ የሚሰጡ ሰዎች ዛሬም አሉ፤ እግዚ
አብሔር ይመስገን፡፡ ቅዱስ ዳዊት ልጁ ሰሎሞን ለሚሠራው የእግዚአብሔር
ቤት የሚያስፈልጉትን ወርቅ፣ ብርና ገንዘብ አሰባስቦ ዐለፈ እንጂ፣ “ገንዘብ
ስጡ” ብሎ አልሰበከም፡፡ ከዚያም፣ “ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀ
ድስ ማነው?” በማለት ነበር የጠየቀው፡፡ ትክክለኛ ጥያቄ ነው (1ዜና 29፥5)፡፡
ራሱን ለእግዚአብሔር የቀደሰ (የሰጠ) ገንዘቡን አይሰስትምና!

የተሠራለት ታላቅ ነገር የገባው ሰው እግዚአብሔርን ላለማሳዘን ይጠነ
ቀቃል፤ ፍቅር በዚህም ይገለጣልና! ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያው ጴጥሮስን፣ “ግልገ
ሎቼን አሰማራ”፣ “ጠቦቶቼን ጠብቅ”፣ “በጎቼን አሰማራ” ብሎ ከማዘዙ በፊት፣
“ትወደኛለህን?” በማለት ሦስት ጊዜ ጠይቆታል፡፡ ለአገልግሎት ከማሠማራቱ

በፊት ፍቅሩ ምን ያህል እንደ ገባው ጠይቆታል፤ ፍቅር ከአገልግሎት ይቀድማልና:: በፍቅር ማሕፀን ውስጥ ደግሞ ሁሌም መሥዋዕትነት አለ!

የመቀደሳችን፣ ነፍሳችንን መሥዋዕት አድርገን የማቅረባችን መሠረት ፍቅር ነው፤ የእግዚአብሔር ፍቅር፤ ንጹሕ ፍቅር፤ ፍጹም ፍቅር:: ከሁሉ የሚበልጥ ፍቅር:: ይህንን ፍቅር መረዳት ግድ ነው:: ፍቅር የሌለው አገልግሎት የዮናስ ዐይነት አገልግሎት ነው:: ዮናስ ጕሮሮውን ተይዞ፣ "ነነዌ ትገለበጣለች" ብሎ ተናገረ፤ ሰዎቹ ግን በንስሓ ተመለሱ:: እርሱ እሳት ወርዶ እንዲበላቸው ሲጠባበቅ እግዚአብሔር ማራቸው:: ይህ ግን ዮናስን እጅግ አናደደው::

## "ቅዱስ መሥዋዕት"

የምናቀርበው መሥዋዕት (ሰውነታችን) ቅዱስ መሆን አለበት፤ "ቅዱስ መሥዋዕት አድርጋችሁ" ይላልና:: እግዚአብሔር በተበላሸ ዕቃም ይሠራል:: ጫት በሚቅም ሰው ወንጌል ተነግሯቸው የዳኑ ሰዎች አሉ:: እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች ሠርቶባቸዋል:: በእኛም ሊሠራ ይችላል:: ራሳችንን ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን ካቀረብንለት ግን ራሱን ይገልጥብናል፤ የተጠራነው ለቅድስና ነውና:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ፣ "በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት … ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት" የሚለው ለዚህ ነው (1ቆሮ. 1:2)::

ራሳችንን ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን ስናቀርብ ሥቃይ መኖሩ እርግጥ ነው:: መሥዋዕት ደስ የሚያሰኝ አይደለም፤ ጣር አለው:: ደም መፍሰስ አለው፤ ሞት አለው፤ ጭከናም አለበት:: የነፍሳችን ፍላጐት ላይ መጨከን ያስፈልገናል:: የነፍሳችንን ጩኸት፣ የሥጋችንን ልመናና ማባበል ላለመስማት መቍረጥ አለብን:: እግዚአብሔር የሚፈልገውን የሚቃጠል መሥዋዕት ለማቅረብ መጨከን ግድ ነው::

በቤት ኪራይ ሲቸገር የነበረ አንድ ጓደኛ አለኝ:: ታዲያ አንድ ቀን የቀበሌ ቤት የሚያገኝበት ጥሩ አጋጣሚ አገኘ:: ሆኖም እጅ መንሻ መስጠት ይጠበቅበት ነበር:: ያን ካደረገ ከእንግልትና ከእንክርት ይገላገላል:: ትንሽ ገንዘብ ሰጥቶ ከቤት አልባነት ነጻ ከመውጣትና ጉቦ ላለመስጠት ወስኖ በመንከራተት ከመቀጠል የትኛው እግዚአብሔርን ያስደስተዋል?

ይህ ሰው ግን የመረጠው የእግዚአብሔርን መንገድ ነው:: እግዚአብሔር በማይከብርበት መንገድ ማረፍ አልፈለገም፤ ዕረፍቱን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ:: አሁንም የግለ ሰብ ቤት ተከራይቶ ይኖራል:: እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች አይደሰትም የሚል ካለ፣ ወንጌል ቢሰበክለት ተገቢ ነው::



## "እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ … መሥዋዕት"

መሥዋዕት መሆን መጀመሪያ ላይ አያስደስተን ይሆናል፤ እግዚአብሔርን ግን ያስደስተዋል:: የነፍሳችንን ጥማት፣ የልባችንን መሻት፣ የስሜታችንን ደስታ ስለ እርሱ ፍቅር መሥዋዕት አድርገን ስናቀርብ አምላካችን ደስ ይሰኛል፤ "እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት" ይላልና:: እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ እግዚአብሔር ሲደሰት የማታ ማታ እኛም እንደሰታለን::

አንዳንዴ በሕይወት ጕዳና ላይ ሰዎች ያልጠበቁት ፈተና ተደራርቦ ያገኛቸዋል:: የኑሮ ችግር፣ የጤና መታጣት ይገጥማቸዋል፤ ጸልየው ጸልየው መልሱ አይመጣላቸው ይሆናል:: እንዲያውም አንዳንዴ ነገሮቹ ሊባባሱ ይችላሉ:: የሚወዱት የቤተ ሰባቸው አባል ይሞታል፤ በዚህ ሁሉ ልብን የሚሰብር ውጥንቅጥ መካከል "እግዚአብሔር ሆይ በሆነው ሁሉ አዝኛለሁ:: ይህን ለምን እንዳደረግህ አላውቅም፤ ልቤ በኀዘንና ግራ በመጋባት ተሞልቷል:: ስብራት ተደራርቦብኛል፤ ሆኖም አንተን መከተሌን አላቋርጥም" ያሉ ሰዎችን ዐውቃለሁ:: እውን ይህ መሥዋዕት አይደለምን? መሥዋዕት ካልሆነስ ምንድን ነው?!

ይህን የሚያደርግ ኋላ ቀርና ተላላ ሊባል ይችላል:: ቁምነገሩ ኋላ የቀረው ለጌታ መሆኑ ላይ ነው:: እንደ ዕድለ ቢስ ቈጥረውት ከንፈራቸውን የሚመጥጡለት ሰዎችም ይኖሩ ይሆናል:: በተራራው ስብከት መሠረት ከሆነ፣ "ዕድለ ቢሶች ዕድለኞች ናቸው":: "ሁሉም ያደርገው የለም እንዴ? እናንተ ከሰው የተለያችሁ ናችሁ?" በማለት የመሥዋዕትነት ውሳኔአችሁን ማጣጣል የሚፈልጉ አይጠፉም:: "የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ" (ማቴ. 5፥48) የተባለው መለኪያው የሰማዩ ጌታ ስለ ሆነ ነው:: የመንፈሳዊ ሕይወታችን መመዘኛ እርሱ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የሚነግረን "ከሰው የተለየሁ አይደለሁም" በማለት ወደ ኋላ እንዳንል ነው:: በመሥዋዕትነት ጕዳይ ከሁሉ የሚልቀው ምሳሌአችን እግዚአብሔር ሲሆን፣ ሰው ሆኖ በመካከላችን ኖሮ የመሥዋዕትነትን ኑሮ የገለጠልን ደግሞ ጌታ ክርስቶስ ነው::

ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን አስገዝቶ በመሥዋዕትነት ያለፈው ቦንሆፈር እንዳለው፣ "ጥሪአችን የማሸነፍ አይደለም፤ ወዴትም ይምራን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመፈጸም እንጂ::"[1] ታዲያ ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ ማነው?

## ማስታወሻ

1. Eric Metaxas, *Bonhoeffer - Pastor, Martyr, Prophet, Spy: A Righteous Gentile Vs. The Third Reich* (Tennessee: Thomas Nelson, 2010), 196.

# ምርጥ ምርጥ ተዋንያን

ጠላት ተሸንፎ ባንዲራ ከተመለሰ በኋላ አርበኞች በጦር አለቆቻቸው እየ ተመሩ በሰልፍ ያልፋሉ፡፡ ሁሉም የሠራውን ጀግንነት እያስታወሰ ይፎክራል፡፡ ይሸልላል፡፡ አንዱ አርበኛ ለንጉሡ፣ "እኔ ያንተ አሽከር፣ ያንተ ቡችላ፣ ቅጠለ-በላው" እያለ ፎከረ፡፡ ብዙ በሬዎቻቸው የተወሰዱባቸው አንድ ሽማግሌ ይህን ሲሰሙ፣ "እሄሄ! የእኔን በሬዎች ማን በላቸውና አንተ ቅጠል ትበላለህ?" በማለት ተናግረዋል፡፡[1]

ሽለላው ወዲህ፣ እውነቱ ወዲያ!

ያልሆኑትን ሆኖ መቅረብ ቲአትር ሲሆን፣ ማኅበረ ሰቡመረ በተለያየ መልኩ ትወና እንደሚያካሂድ ግልጽ ነው፡፡ ሚስት በውሸት እንባ ባሏን ታሳምናለች፡፡ ለቅሶ ደራሽ፣ "ወይኔ! እኔ ድፍት ልበል" በማለት እየጮኸ ገና ከመማባቱ "ካርታ የታለ?" ይላል ግራና ቀኝ እያማተረ! ስለዚህ ቲአትር ከየዕለት ሕይወታችን ውስጥ እንደማይታጣ መናገር እንችላለን፡፡ የቲአትር ጥበብ ግን ሰዎችን ለማዝናናት እና/ወይም ለማስተማር ባለሞያዎቹ ጊዜ ወስደውና አጥንተው የሚቀርቡበት የማስመሰል ጥበብ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ተዋንያኑ በየጊዜው የተለያዩ ገጸ ባሕርያትን እየቀያየሩ መጫወት ሥራቸው ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ እዚህ አገር የሴት ተዋንያን ባልነበሩበት ወቅት ወንዶቹ ሴት ሆነው ይተውኑ ነበር፡፡ ሴትነታቸው ግን መድረክ ላይ ያበቃል፡፡ መድረክ ላይ ሲተውን ርኅሩኅ የነበረ ሰው በእውነተኛ ኑሮው ተቃራኒ ጠባይ ሊኖረው ይችላል፡፡ መድረክ ላይ ትዕግሥተኛ የነበረው ችኩል፣ ታዛዡ ዐመፀኛ፣ ቅኑ መሠሪ፣ መሪው ተመሪ፣ ትሑቱ ዕቡይ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይ ከእውነተኛ ጠባዩ ጋር ተቃራኒ ቢሆን እንኳ የተሰጠውን ገጸ ባሕርይ በአሳማኝ ሁኔታ የሚተውን ይደነቃል፤ ይጨበጨብለታል፤ እንጂ አይነቀፍም፡፡

በትወና የተካኑ ሰዎች ውጤታማ የሚሆኑባቸው ሌሎች የሥራ መስኮችም አይጠፉም፡፡ አንድ ጊዜ ሁለት የእንግሊዝ ፖለቲከኞች ስለ ፊልም ተዋንያን እየተነጋገሩ ነው፡፡ "እነዚህ ተዋንያን እንዲህ ከእኛ በላይ ዝነኛ፣ ሀብታምና ተወዳጅ መሆናቸው ግራ እያጋባኝ ነው፡፡ እኛስ ተዋንያን አይደለን እንዴ?" አለ አንደኛው፡፡ "ለዚያውም ከእነርሱ ይልቅ በአሳማኝ መልኩ የምንተውነው እኛ ነን" አለው ሌላኛው ሲመልስ፡፡



በርካታ የፖለቲካ ሰዎች ገጸ-ባሕርያትን ተላብሰው የሚኖሩ ተዋንያን መሆናቸውን የሚያውቅ ያውቀዋል፡፡ ጨካኝነታቸውንና ልበ ድፍንነታቸውን እያወቅን እንኳ ርኅሩኅነታቸውን፣ ዐዋቂነታቸውንና ሕግ አክባሪነታቸውን ሊያሳምኑን ይሞክራሉ፡፡ የድምፅ ማስተላለፊያ መሣሪያው የተዘጋ መስሏቸው ክፉና አስነዋሪ ነገሮችን ከጀርባ ሲናገሩ የተገኙባቸው ወቅቶችም አሉ፡፡ በካሜራ ፊት ያሞጋገሱትን ሰው ከካሜራው ዞር ከማለታቸው ሲሳደቡም ተገኝተዋል፡፡ ጥቃቅን የሐሳብ ልዩነቶችን ለመታገሥ ፈቃደኝነት የሌላቸው ባለሥልጣናት እንኳ ስለ ተቃዋሚዎቻቸው ሲናገሩ፣ "ግማሽ መንገድ ድረስ ሄደን እንቀበላቸዋለን" የሚል ደረቅ ንግግር ማዘውተራቸውን ለምደነዋል፡፡ የብዙዎችን ተስፋ እየገደሉ ሕይወትን ራሷን ፍርሀት አድርገው የሚቀይሩት በዚህ መልኩ ነው፤ በተለይ ለእኛ ነጋሪ አያሻንም፡፡

እግዚአብሔር ግን የትወና ሕይወት የሚኖሩ ሰዎችን አያደንቅም፡፡ አስመሳዮችን አይፈልግም፡፡ የሰዎች የመድረክ እና የእውን ኑሮ ሁሌም የተጣጣመ እንዲሆን ይሻል፡፡

ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ዐይነት ሰዎችን ግብዞች ይላቸው ነበር፡፡ ግብዝነት (hypocrisy) "መድረክ ላይ መተወን" ማለት ሲሆን፣ ሰው ያልሆነውን ሆኖ፣ ያልተሰማውን እንደ ተሰማው አድርጎ በማስመሰል የሚያቀርብበት ሂደት ነው፡፡[2] ቃሉ መደበኛ ተዋንያንን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ሲውል ቈይቷል፡፡ ጌታ ኢየሱስም አስመሳይ ሕይወት ያላቸውንና ለታይታ የሚኖሩ ሰዎችን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል፡፡

ጻፎችና ፈሪሳውያን በእርግጥም የተዋጣላቸው ተዋንያን ነበሩ፡፡ ግመልን የሚውጥ ሕይወት ቢኖራቸውም፣ በአደባባይ ትንኝን ያጠራሉ (ማቴ. 23፥24)፡፡ ለዕይታ የሚያምር የኖራ ልስን ሕይወት አላቸው፤ ተከፍቶ ሲታይ ግን በሙታን ዐጥንትና ርኩሰት ሁሉ የተሞላ ነው፡፡ በውጭ ለሰው ጻድቃን መስለው ይታያሉ፤ ውስጣቸው ግን ግብዝነትና ዐመፀኝነት ሞልቶበታል (ቍ. 27-28)፡፡ ጽዋውንና ወጭቱን ከውጭ አጥርተው፣ ውስጡን ግን ቅሚያና ስስት ሞልተውት ይሄዳሉ (ቍ. 25)፡፡ በአደባባይ ረጅም ጸሎት በመጸለይ ይታወቃሉ፤ በዚሁ ጸሎታቸው እያሳበቡ ግን መበለቶችን ይዘርፋሉ (ቍ. 14)፡፡ ጸሎታቸውን ጠጋ ብለን ብናደምጠው ደግሞ፣ "እንደ እገሌና እገሌ ስላልሆንኩ እመሰግንሃለሁ" የሚል ግብዝነት የሞላበት ነው (ሉቃ. 18፥9-14)፡፡ አባቶቻቸው የገደሏቸውን ነቢያት አክብረው ለመታሰቢያ የመቃብር ሐውልት ያሠራሉ፤ እነርሱም ደግሞ በተራቸው ነቢያትን ይገድላሉ፡፡ ከነቢያት የሚበልጠውን ጌታ ለመግደልም ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም (ቍ. 29-34)፡፡

ሕግ ዐዋቂዎችም ያው ነበሩ:: ሠርቶ የሚያሠራ አለቃ ይመስል ሰዎችን
ለሥራ ይጋብዛሉ፤ ያንን ሥራ ግን እነርሱ በአንዲት ጣታቸው እንኳ አይነኩ
ትም (ሉቃ. 11፥46)::

ከጌታ ደቀ መዛሙርትም መካከል አንዳንድ ጊዜ ሲተውኑ የሚገኙ
ነበሩ:: ሰው ሲኖርና ሳይኖር የሚናገሩትና የሚኖሩት ይጋጭባቸው ከነበሩ
ከእነዚህ ሰዎች መካከል ስምዖን ጴጥሮስን መጥቀስ ይቻላል:: ጴጥሮስ አንድ
ወቅት ከአሕዛብ ጋር ያነበረው ግንኙነት ትወና ነበረበት:: አይሁድ ካላዩት አብ
ሯቸው ማዕድ መቅረብ አይቸግረውም:: አይሁድ ሲያዩት ግን ያፈገፍጋል::
በግብዝነቱ ሌሎች ሰዎች እስኪሰናከሉ ድረስ መንታ መልክ ነበረው:: ሐዋር
ያው ጳውሎስ ግን ፊት ለፊት ገሥጾ እንዲስተካከል ረድቶታል (ገላ. 2፥11-12)::

የአስቆሮቱ ይሁዳም ቢሆን ለጌታ የሚደረገውን አምልኮ እንደ አባካኝ
ነት ለመቊጠር በሚያበቃ መልኩ ስብከቱን ሲያጧጡፍ ይታወቃል:: ላይ
ላዩን ሲያዩት የድኾች ተቆርቋሪ ይመስላል፤ እውነቱ ግን የተሰበሰበውን ገንዘብ
ከሥር ከሥር የሚቆነጥር ሌባ ነበር (ዮሐ. 12፥6):: ይህ የተውኔት ሕይወቱ
አድጎ በመጨረሻ እንደ ወዳጅ እየሳመ ጌታውን አሳልፎ ሰጥቷል (ሉቃ.
22፥47)::

ግብዞች የሚኖሩት ለታይታ ነው:: ሰው ዐይቶ እንዲያጨበጭብላቸ
ውና እንዲያደንቃቸው ያልሆኑትን ሆነው ይቀርባሉ:: ምጽዋት ሲያደርጉ በየመ
ንገዱ ዕዩኝ ዕዩኝ የሚል መለከት ያስነፋሉ (ማቴ. 6፥2):: ሲጸልዩ ለሁሉ እንዲ
ታዩ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ላይ ቆመው ነው (ቊ. 5):: ሲጾሙ ጾመኛ
ነታቸውን ሰው እንዲያውቅላቸው መጠውለግና የኀዘኔታ ፊት ማሳየት ይወዳሉ
(ቊ. 16):: ትልቁ ዓላማቸው የሰዎች ውዳሴ እንጂ በስውር የሚያየው ጌታ
አይደለም:: ስለዚህ ዋጋቸውን እዚሁ ከሰዎች ተቀብለዋል ማለት ነው (ቊ. 2፣
6፣ 16)::

ጌታ ኢየሱስ የሚፈልገው ግን ግብዝነትን አይደለም:: በሰዎች ፊት
ሞገስ ለማግኘት ሲባል ያልሆኑትን መስለው መቅረብ በፊቱ የተጠላ ነው:: ስለ
ዚህ ግብዞች (ተዋንያን) እንደሚያደርጉት አትሁኑ በማለት የእነርሱን ተቃራኒ
እንድናደርግ ነው የሚመክረን:: ምጽዋት ስንሰጥ በስውር ብናደርገው፣ በስውር
የሚያይ አባታችን በግልጽ ይከፍለናል (ማቴ. 6፥2-3):: ስንጸልይ ጓዳችንን ዘግ
ተን ብንጸልይ፣ በስውር የሚያይ አባታችን በግልጥ ይከፍለናል (ቊ. 5-6)::
ስንጾም መጾማችን ለሰዎች እንዳይታወቅ ራሳችንን ማጠውለጋችን ቢቀር፣ በስ
ውር የሚያይ አባታችን በግልጥ ይከፍለናል (ቊ. 7-8):: ይህንን የምናደርገው
ግብዝ አለመሆናችንን ለማሳየት ከሆነ ግን በሌላ ጎኑ ግብዝነት መሆኑ
አይቀርም::



ይህ የመድረክና የገሀዱ ዓለም ሕይወት ልዩነት በብሉይ ኪዳንም
ነበር:: አንዳንዶቹ ይህንን የሚያደርጉት ሲጨንቃቸውና በፍርሀት ሲዋጡ
ነው፤ ይስሐቅን መጥቀስ እንችላለን:: ይስሐቅ ሚስቴ ትወሰዳለች በሚል ፍር
ሀት ስለ ተያዘ ስለ ርብቃ ሰው ሲጠይቀው፣ "እኅቴ ናት" እያለ ይናገራል፤ ለብ
ቻቸው ሲሆኑ ግን ይዳራታል (ዘፍ. 26፥7-8):: በእርግጥ የይስሐቅን ጉዳይ
ውሸት እንጂ ግብዝነት ለማለት ይከብዳል:: ሆኖም ሰው ላይ ጥያቄ የሚፈጥር
ግንኙነት ኖሯቸው ሲጠየቁ፣ "እኅቴ ናት" እያሉ በድብቅ ግን ይስሐቅ የሚያደር
ገውን የሚያደርጉትን ሰዎች፣ "የይስሐቅ የመንፈስ ልጆች" እንበላቸው ይሆን?

ያዕቆብ ምርጥ ቲአትረኛ ነበር:: የቲአትሩ ደራሲና አዘጋጅ እናቱ ስት
ሆን፣ መሪ ተዋናዩ ደግሞ እርሱ ነበር:: ለመተወን አባቱ ዘንድ የቀረበው የመድ
ረክ አልባሳቱን ሳይቀር አሟልቶ ነው:: ተዋናዩ ዔሳውን ሆኖ ነበርና የሚጫወ
ተው፣ የልብሱ ሽታና "እጆቹ" ሳይቀሩ የዔሳው ነበሩ፤ ድምፁ ብቻ ነበር የራሱ
(ድምፅ ማስመሰል ላይ ጉድለት የነበረበት እናቱ ሥልጠናውን ሳትሰጠው በመ
ቅረቷ ሳይሆን አይቀርም!):: ብቸኛው ተመልካች (ወላጅ አባቱ) በቀላሉ የሚ
ታለል ሽምግሌ ቢመስልም፣ የተዋናዩ ድምፅ ጥርጣሬ ጭሮበታል:: ስለዚህም
"አንተ ማን ነህ?" የሚል የማረጋገጫ ጥያቄ ሰነዘረ፤ ያዕቆብ ግን በድፍረት
"ዔሳው ነኝ" በማለት አሳመነው፤ ኋላ መታወቁ ላይቀር (ዘፍ. 27)::

ያዕቆብ በዚህ ሁኔታ እንዲኖር ግን እግዚአብሔር አልወደደም:: ስለ
ዚህ ነጻ አውጥቶታል:: ያዕቆብ ትዳር ሲመሠርት፣ እርሱ ያሰባትን ሳይሆን ሌላ
ኛዋን ሴት እንዲያገባ ድራማ ተሠርቶበት የእጁን አግኝቷል:: አሊቃውም ደሞ
ዙን በየጊዜው የሚቀያይርበት ሰው ነበር:: በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዓመታት ከለፋ
በኋላ ወደ አባቱ ቤት የመልስ ጉዞ ጀመረ:: ለቀናት ሲጓዝ ከሰነበተ በኋላም
አንድ ቀን እግዚአብሔር ብቻውን አግኝቶ ሌሊቱን ሲታገለው አደረ::

ያዕቆብ ጉዞ ላይ ነው ስለ ሰነበተ፣ የእንቅልፍ ሰዓቱን በዕረፍት ማሳለፍ
አይጠላም፤ የጠበቀው ግን ብርቱ ትግል ነበር:: ሲታገል አድሮ ሲነጋጋ ሲል፣
"ስምህ ማነው?" ብሎ ድንገት እግዚአብሔር ጠየቀው፤ ያኔም አባቱ ይህንኑ
ነበር የጠየቀው:: አሁን ግን ያዕቆብ እውነቱን ተናገረ፤ ትምህርቱ ገብቶታል
ማለት ነው (ዘፍ. 32፥22-27):: ይህ ጥያቄ ያዕቆብን ከራሱም፣ ከእግዚአብ
ሔርም ጋር አስታረቀው::

የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ሳኦልም ይህ የትወና (የማስመሰል)
ስጦታ ነበረው (ንጉሥ አይደል?)፤ ለነገሩ ስለ ፖለቲከኞች የትወና ሰውነት
ቀደም ብለን አውስተናል (የማኪያቬሊም ምክር እንዲህ እንዲሆኑ ነው፤ ሳይ
ንሱ ግን እንዲህ ይል ይሆን?):: ሳኦል መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን እያ

ስለ ሲያጠፋ ቈይቷል፤ ሲጨንቀው ግን መናፍስት ጠሪ ጋ ሄዶ ምክር ከመጠየቅ አልታቀበም (2ሳሙ. 28፥3-25)።

ዳዊትን ለመግደል እያደባ እንኳ ብዙ ሲያስመስል ቈይቷል (1ሳሙ. 18፥17፣ )። ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ዳዊት ሲጠይቀውም እያለቀሰ ተውኗል (1ሳሙ. 24)።

ቀጣይ ንጉሥ የነበረው ዳዊትም ለትወና የተፈጥሮ ስጦታ የነበረው ሳይሆን አይቀርም ("ንጉሥነት እንጀራው ነበር" ማለት ነው!)። ዳዊት አንድ ወቅት ሳኦልን ሸሽቶ ጫካ ለጫካ እየተሳደደ በሚኖርበት ጊዜ ማምለጫ ቢሆነኝ ብሎ ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አንኩስ ሄዶ ነበር። የአንኩስ ባሪያዎች የዳዊትን ማንነት ጠንቅቀው ማወቃቸውን ሲያውቅ ግን እዚያ መቈየት ፈራ። ስለዚህ፣ በፊታቸው አእምሮውን እንደ ሳተ ሰው ሆነ፤ በያዙትም ጊዜ የከተማዪቱን ቅጥሮች እየበጫጨረ፣ ልጋጉንም በጢሙ ላይ እያዝረበረበ እብድ መሰለ። ንጉሡ ይህንን የዳዊትን ድራማ ሲያይ እውነት ስለ መሰለው፣ "እብድ እኮ ነው! ... ወደ እኔ ያመጣችሁት ለምንድን ነው? ... እብድ አጥቼ ነው?" በማለት ባሪያዎቹን ተቈጥቶ "ተዋናዩን" ዳዊት ከዚያ አባረረው (1ሳሙ. 21፥10-15)።

ዳዊት ይህንን የትወና ስጦታውን አላግባብ ተጠቅሞበታል። ከኦርዮ ሚስት ከቤርሳቤህ ጋር ከአመነዘረ በኋላ ሴቲቱ ስታረግዝበት አስደናቂ ፊልም ሊሠራ ሞክሯል (የዚህ ዘመን ሰዎች ቢሆኑ የመጀመሪያ እርምጃቸው ውርጃ ይሆን ነበር አይደል?)። ባሏን ከጦርነት ሜዳ አስጠርቶ ለይምሰል ካነጋገረው በኋላ ወደ ቤቱ ሄዶ ዕረፍት እንዲያደርግ አሰናበተው። የቤተ መንግሥት ምግብም እንዲላክለት አደረገ። ከጦር ሜዳ ዕረፍት አግኝቶ ከተማ የገባ ወታደር በሴት ጉዳይ እንዴት እንዴት እንደሚያደርገው የማያውቅ ይኖር ይሆን? (እንኳንስ ሚስቱን አግኝቶ ...)

የዳዊት ጥረት፣ ሴቲቱ ባሏ ከጦር ሜዳ ለዕረፍት የመጣ ጊዜ ከባሏ አረገዘች እንዲባልለት ነበር። አንዳንድ እውነተኛ ሰዎች ግን ለቲአትር አይመቹም፤ ኦርዮ ከእነዚህ አንዱ ነው። ቤት መሄዱን ትቶ ከቤተ መንግሥቱ ጠባቂዎች ጋር አደረ። በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ዳዊት በመጠጥ ሊያሳስተው ሞከረ። ኦርዮ ግን ታማኝ ወታደርነቱን በመጠጥ አሳልፎ አልሰጠም። የእግዚአብሔር ታቦትና የጦር አለቃው ከነወታደሮቹ ጦር ሜዳ እያደሩ እርሱ ከሚስቱ ጋር መደሰት አልፈለገም።

ሆኖም ዳዊት እንዲህ ዐይነቱን ቈራጥና ታማኝ ወታደር ከሹመት ይልቅ ለሞት ማጨት መርጧል። ስለዚህ የመጀመሪያው ድራማ አልሳካ ሲለው ሌላ አዘጋጀ። ኦርዮ እንዲገደል የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፎ በራሱ በተገዳዩ



እጅ ለጦር አለቃው እንዲሰጥ ላከለት (የኦርዮን ታማኝነት ስላወቀ ይሆን ደብዳቤውን ለራሱ የሰጠው?)። ታማኙ ወታደርም የራሱን የሞት ፍርድ ወስዶ ለገዳዩ አስረከቧል። (ምንስ እያሰበ ነበር ሲጓዝ የነበረው? "ቀልቡ" አልነገረው ይሆን?)

ስለ አገዳደሉ ሁኔታ ዳዊት ምርጥ ድራማ ጽፎ ነው የላከው። "ኦርዮን ጽኑ ሰልፍ ባለበት በፊተኛው ሰፍራ አቁሙት፤ ተመትቶም ይሞት ዘንድ ከኋላው ሽሹ" ብሎ አዘዘ። የኦርዮ መሞት ሲነገረውም ድራማውን አላቋረጠም። "ሰይፍ አንድ ጊዜ ይህንን አንድ ጊዜም ያን ያጠፋልና ይህ ነገር በዐይንህ አይከፋ፤ ከተማዪቱን የሚወጉትን አበርታ፤ አፍርሳትም ብለህ ለኢዮአብ ንገረው፤ አንተም አጽናው" በማለት ለመልእክተኛው ተናገረ። የዳዊት ድራማ ሰዉን ሁሉ ሊያሳምን የሚችል ነበር፤ ከእግዚአብሔርን በቀር!

ከዚያም የባሏን ሞት አስታከኮ ሴቲቱን አገባት። ዳዊት ጠቅላላ ድርጊቱ ማከቬሊያዊ ሆነ። ነገሩ ሁሉ በጥያቄ የተከበበ ነበር። ሲያገባት የስንት ወር እርጉዝ ትሆን? (ሆዷን የሚደብቅላት የሙሽራ ልብስ አግኝታ ይሆን?) አገልጋዮቹ እና የተለያዩ ሰዎች ስለ ጉዳዩ እንደየ ሁኔታው የሚያውቁት ነገር ሊኖራቸው ይችላል፤ ማንም ተቃውሞ ስለ ማቅረቡ ግን መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም። ሁሉ ዝም ብሏል። ሁሉን የሚያየው ግን ሁሉን ዐይቶአል። ጸሓፊውም፣ "ነገር ግን ዳዊት ያደረገው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ከፉ ሆነ" ይለናል (2ሳሙ. 11፥27)።

ዳዊት አሁንም ትወናውን ቀጥሏል። የአንድን ድኻ በግ ወስዶ ስላረደ ሀብታም ሰው ሲነገረው ተቈጥቶ፣ "ሕያው እግዚአብሔርን! ይህን ያደረገው ሰው ሞት ይገባዋል። ስለ በጊቱ አራት እጥፍ መክፈል አለበት" ብሎ ፈረደ። አንድ በግ የሰረቀ አራት መክፈል እንዳለበት ሕጋቸው ይናገራል (ዘፀ. 22፥1)። ከሰው ሚስት ጋር ያመነዘረ በሞት እንዲቀጣ ትእዛዝ ቢኖርም (ዘሌ. 20፥10)፣ በግ የሰረቀ ይሙት የሚል ሕግ ግን የለም! ዳዊት የራሱን ኀጢአት ቁምሳጥኑ ውስጥ ከቈለፈ በኋላ በፍርድ ወንበር ላይ ተቀመጠ። ሆኖም ራሱ የፈጸመው ኀጢአት ሚዛን አሳጥቶት ስለ ነበር የሞት ፍርድ አላግባብ ፈረደ።

ሰው ላይ ለመፍረድ ቢያንስ ፈራጁ ከተመሳሳይ ኀጢአት የጸዳ መሆን ይጠበቅበታል። ጌታ ኢየሱስ ይህንን አስተምሯል። ስታመነዝር የተገኘችዋን ሴት እንድትወገር ያመጧትን ሰዎች ይህንኑ ነው የነገራቸው። ራሳቸው ከሳሾቹም ኀጢአት ነበረባቸው። እዚህ ግን እንደ ጨዋ ሊተውኑ ይሞክራሉ። "ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት ይውገራት" በማለት ውሳኔውን አሳወቃቸው (ዮሐ. 8፥7)። ማንም ግን አልነበረም ... ከእርሱ በቀር!

በመጨረሻ ግን ነቢዩ ናታን ንጉሥ ዳዊትን ከዚህ የድራማ ሕይወት ቀሰቀሰው:: “ያ ሰው አንተ ነህ!” ነበር ቀስቃሹ እውነት (2ሳሙ. 12፥1-7)! እኛ ንስ፣ “ያ ሰው አንተ ነህ!” በማለት የሚነግረን ማን ይሆን? አብዛኞቻችን፣ “ያ ሰው እኔ ነኝ” የማለት ድፍረት የለንምና!

ማሃተማ ጋንዲ ሌሎችን ለመገሠጽ የሞራል ብቃት የሚኖራቸው ራሳቸው ነጻ በሆኑበት ጉዳይ ብቻ እንደ ሆነ ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰው ነበሩ:: አንድ ጊዜ አንዲት እናት ልጇ ስኳር እየቃመ ሲያስቸግራት ወደ ማሃተማ ጋንዲ አመጣችው፤ እርሷን አልሰማ ስላላት እርሳቸው እንዲቈጡላት ነበር ሐሳቧ:: ጋንዲ ግን በሚቀጥለው ሳምንት ይዛው እንድትመጣና ያኔ እንደሚመክሩት ነግረው መለሷት:: በቀጣዩ ሳምንት ልጇን ይዛ ተመልሳ መጣች:: ያኔ ጋንዲ ክንዱን ያዝ አደረጉና ከዚህ በኋላ ስኳር እንዳይቅም ነግረው እናትና ልጅን አሰናበቱ:: እናት ግን ወደ ኋላ ቀረት በማለት፣ “ለዚህ ለዚህማ ሳምንት መቈየት ለምን አስፈለገ? ባለፈው ሳምንት ይህንኑ ሊነግሩት አይችሉም ነበር?” የሚል ጥያቄ አቀረበች:: “አይ አይሆንም” አሉ ጋንዲ፤ “ባለፈው ሳምንት እኔም ስኳር እቅም ነበር::”[3]

ዛሬ ግን ጥቂት በማይባሉ አብያተ ክርስቲያናት የምናየው ተዋናዮችን ነው:: የሰባኪዎቻችን፣ የዘማሪዎቻችን፣ የመጋቢዎቻችን ሕይወትና አገልግሎት ትወና ይመስላል:: አንድ ጊዜ አንድ ሰው ከአንዲት ዘማሪ ጋር ስለ ነበረው ያል ተገባ ግንኙነት ለማነጋገር እርሱ በሚያስተምርባት ቤተ ክርስቲያን ተገኘሁ:: በዚያን ቀን ለመስበክ ከመቆሙ ከ2 ሰዓት በፊት ከእርሷ ጋር የሚሆነውን ሲሆን ቈይቶ ነበር:: ከዐልጋ ተነሥቶ ነው ሊሰብክ የሄደው ማለት ይቻላል (እርሷስ ወደ አገልግሎቷ ሄዳ ይሆን?):: እዚያ ስደርስ ስለ ዝሙት ሰዎችን በመገሠጽ ላይ ነበር:: ከዚህ በላይ ምን ድራማ አለ?!

ምናልባት ይህ ሰው እንዲህ የሚሰብከው ዝሙት በመፈጸሙ የዝሙት ጠንቅ የሚያሳድረው ሕመም ገብቶት ቢሆን አክብሮት ነበር የሚገባው:: ራሱ ነጻ የሆነ ይመስል ጣቱን ወደ ሌሎች መቀሰሩ ግን ይህንን ፋርሽ አድርጎታል:: እንደዚህ ደፍሮ ሌሎችን የሚዋሽ ሰው ራሱን ከመዋሸት ነው የሚጀምረው:: ፕሮፌሰር መስፍን እንዲህ ይላሉ፤ “ማንም ሰው ሲዋሽ ወይም ሲያታልል መጀመሪያ የኅሊናውን ሚዛን ሰብሮ ነው:: ለራሱ ሳይዋሽ ለሌላ መዋሸት አይችልም፤ ራሱን ሳያታልል ሌላውን ማታለል አይችልም::”[4] ስለዚህ ይህ ሰው የኅሊና ሚዛኑን ሰብሯል ማለት ነው::

ዘማሪዎችም ይህንኑ ይመስላሉ:: የአብዛኞቹ ዝማሬ የሕይወታቸው ተቃራኒ ነው:: ጅብ ቢነትትው የማይነቃው እንቅልፋም ዘማሪ ሌሊቱን እንደ



ማይተኛና ሲዘምር እንደሚያነጋ ይነግረናል:: “ታናሹን ሰው እዚህ አደረስከኝ” በማለት የሚያዜመውም ሲቀርቡት ልቡ በታላቅነት አብጦ ማየት አይከብድም:: ትንሿ ከረሜላ የምታባብለው ዐቅመቢስ ፍጥረት እንደ ልባሙ ሙሴ “የፈርኦንን ጮማ” እምቢ ማለቱን በድፍረት ይዘምራል:: “ስጥ” የሚለውን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለቅሞ አውጥቶ “ተቀበል” በሚል የተካው “አባሐና” ዘማሪ፣ “ያለኝን ሁሉ እሰጣለሁ” እያለ ያዜማል:: በሆነ ባልሆነው ማማረር የሚወደውና በእንቅልፍ ልቡ ሳይቀር የሚነጫነጨው “ስለ ሁሉ አመሰግናለሁ” ይላል:: እግዚአብሔርን በሕይወታቸው አንደኛ ያላደረጉ “ኢየሱሴ አንደኛዬ!” እያሉ ይጮኻሉ:: ከኤልዛቤልና ከደሊላ ባልተለየ ሕይወት የሚታወቁት ደግሞ የራሳቸውን “ንጹሕነት” ለማስመስከር ኤልዛቤልንና ደሊላን ያወግዛሉ፤ ይራገማሉ:: እንዴት ነው ነገሩ? እግዚአብሔርን ቀርቶ እኛንም አላሳመነንም::

ሰባኪዎችም ከዚህ የራቁ አይደሉም:: የራሳቸውን ሕይወት ለኢየሱስ ሳይሰጡ ፋከራቸው፣ “ኢትዮጵያን ለኢየሱስ” የሚል ነው፤ እነርሱ በየጊዜው ብድግ እያደረጉ ለእግዚአብሔር የሚሰጧት ይመስል! (“ኢትዮጵያን ለኢየሱስ” የሚለውን መፈክር ሲሰማ፣ “መጀመሪያስ የማን ነበረች?” ብሎ ጠይቋል አንድ ወዳጄ):: ለነገሩስ፣ “ሕይወቴን ለኢየሱስ!” ማለት አይቀድምም?! የጋራችንን ኢትዮጵያ ከመስጠት፣ የግላቸውን ሕይወት ብቻ የመስጠት ቅድሚያና መብት እንዳላቸው አያውቁ ይሆን?

እነዚህ ሰዎች ለኑሮአቸው እግዚአብሔርን ማመን አቅቷቸው፣ የማያም ኑበትን ጋብቻ እየመሠረቱ፣ አንዳንዴም የውሸት ጋብቻ ተፈራርመው ውጭ አገር ሲሄዱ እያየን፣ እግዚአብሔርን ታምኖ ስለ መጠበቅ ይሰብኩናል (የራሳቸውን ውድቀት እየተናገሩ “እኔን ያየህ ተቀጣ!” እያሉን ቢሆን ምንም ተቃውሞ ባልነበረኝ!):: ለአገልግሎት ከውጭ አገር ጥሪ ሲደርሳቸው እንኳ ቪዛ ለማግኘት የውሸት ማስረጃዎችን እንደሚያቀርቡ እናውቃለን፤ ታዲያ ስለ እውነተኝነት ሊነግሩን ይችላሉ? እውነት እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን “አገልግሎታቸውን” በአገልግሎትነት ይመዘግብላቸዋልን? በዝማሬና በስብከት ሊያስተላልፉልን የሚሟሟቱለት መልእክትስ እነርሱን የመለወጥ ጉልበት የለውም?

በእግዚአብሔር ቤት ከገቢር የተቃረነ መንፈሳዊነትና ትወና በዝቶ ተቸግረናል:: መድረክ ላይ ዐይተናቸው፣ ክንፋቸውን እንዳንረግጥ እየፈራን የተራመድንላቸው ሰዎች ከመድረክ ውጭ ስናያቸው ግን ለካ ቀንዳቸው ነበር ክንፍ የመሰለን፤ መሬት ሲጎተት የነበረውም ጭራቸው ነበር!

ዐውደ ምሕረቱ (ምስባኩ) ላይ የሚወራው ወይም የሚዘመረው ሌላ፣ በሕይወት የሚተገበረው ሌላ! እውነት ባይሆንም፣ አደባባይ ላይ የትሑት ሰው

ገጸ ባሕርይ ተላብሰው በደንብ መተወን ተክነዋል፡፡ "ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ 'ቁርበት አንጥፉልኝ' ይላል" ይላል አበሻ፡፡ የእኛዎቹ ሰዎች ግን እዚሁ የሚያውቃቸው ሰው መካከል ነው "ቁርበት አንጥፉልን" የሚሉት፡፡ ምናለ እውነተኛ ማንነታቸውን ቢኖሩት? መሆን ሌላ፣ መምሰል ሌላ! አገልጋዮች የአደባባይ ትሕትናቸውንና የእውነታውን ትዕቢተኝነታቸውን አጣጥመው መኖር የቻሉ በመምሰላቸው ብገረምም፣ ራቁታቸውን መቆማቸውን መቼም አልዘነጋውም፡፡

ዝናቸው እጅግ የናኘላቸውን አንዳንድ ነቢያትና ሐዋርያት ነን ባዮች፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጠጋ ብላችሁ ብታጤኑ እውነቱ ሌላ ነው፡፡ ሰዎች መድረክ ላይ ጥሩ ስለ ነበሩ፣ ጥሩ ስለ ሰበኩ፣ ስለ ዘመሩና ስለ ጻፉ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆኑ ማሰብ ዐደገኛ ነው፡፡ የነገሩንን ሁሉ ከማመናችንና "የእግዚአብሔር ሰው ናቸው" ብለን ከመመስከራችን በፊት ልንጠይቃቸው የሚገቡን ብዙ ጥያቄዎች አሉ፡፡ አደባባይ ላይና በሰው ፊት ያላቸውን ሁኔታ ብቻ ዐይተን ስናደንቅ፣ "የውጪ ዐልጋ፣ የቤት ቀጋ" ቢሆኑስ?

ኑሮአቸው እንዴት ነው? ከቤተ ሰባቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል? የትዳር ጓደኛቸውን ያከብራሉ? ልጆቻቸውንስ? አንድ የታወቀ ወንጌላዊ "ምን ዐይነት ክርስቲያን ነው?" ተብሎ ስለ አንድ ሰው ሲጠየቅ፣ "ገናሚስቱን ስላላገኘኋት ልነግራችሁ አልችልም" ብሎ መልሷል፡፡[5] ትክክለኛ መልስ ነው፡፡ ለመሆኑ ለቤት ሠራተኞቻቸው ወይም ከበታቻቸው ላሉት አገልጋዮች ተገቢውን ክብርና ነጻነት ይሰጣሉ? ደሞዛቸውንስ በአግባቡ ይከፍሏቸዋል? እነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ ምላሽ ካላገኙ ድራማ ሲያሳዩን ነበር ማለት እንችላለን፡፡ ሆኖም ብዙ የመድረክ አገልጋዮች እነዚህን በመሳሰሉ ጥያቄዎች ሲፈተሹ በርካታ ችግሮች አሉባቸው፡፡

ካትሪን ኩልማን፣ "ለእኔነት ሞቻለሁ" በማለት ትታወቃለች፡፡ ስትሞት ግን ብዙ ሀብት አከማችታ ነበር የሞተችው፡፡ ለልብሶቿ እጅግ ብዙ ገንዘብ እያፈሰሰች፣ ለሠራተኞቿ በጣም አነስተኛ ደሞዝ በመክፈል ዝነኛ ነበረች፡፡[6] ዛሬስ የእኛዎቹ ሰዎች እንዴት ይሆን የሚያደርጉት?

ቤኒ ሂን ደግሞ ስለ አባቱ ሥራ፣ ዳግመኛ ስለ ተወለደበት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ በተለያየ ጊዜ ሲናገር እርስ በርስ የሚጣረሱ ነገሮችን ነው የሚናገረው፡፡[7] እስራኤላዊ ዝርያ እንደሌለው እየታወቀ እንዳለው አድርጎ ያቀርባል፡፡ እርሱ ከመወለዱ በፊት እናትየው እንዳዩ የሚናገረው ሕልም እንኳ በየጊዜው ይለዋወጣል፡፡ የፈጸማቸው የአስተምህሮ ስሕተቶችም ሲነገሩት "ለምን ተነካሁ?" በማለት ዘራፍ የሚል ሰው ነው፡፡ ሲያሰኘው ደግሞ እርስ በርሳቸው የተምታቱ ማስተባበያዎችን ያቀርባል፡፡



ከልክ ያለፈ የቅንጦት ኑሮ በመኖር የሚታወቀው ቤኒ ሂን የፊት ለፊት ትሕትናው የተገለጸ ነው፡፡ በራሱ ቤተ ክርስቲያን ሲሰብክ ግን በቪድዮ እንዳይቀረጽ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ፣ "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" የሚለው ጸሎት የእርሱን ተቺዎች እንደማይመለከት አስተምሯል፡፡ እንዲያውም፣ "ይቅር አትበላቸው" እያለ ሲጸልይ ነበር፡፡ ስለ አንድ የጉምሩክ ባለሞያ ሲናገርም፣ "መግደል ብችል ኖሮ አደርገዋለሁ" በማለት ጉባዔ ላይ ዝቷል፡፡[8] ያልተፈወሱ ሰዎች እንደ ተፈወሱ ተደርገው ቀርበዋል፡፡ በእርሱ አገልግሎት መንፈስ ቅዱስ እንደ ጣላቸው ተደርጎ በቪዲዮ የሚቀርቡትም ሰዎች የሚደግፋቸው ሰው መኖሩን በፍጥነት አጣርተው ሲወድቁና ከወደቁም በኋላ ቀስ ብለው ልብሳቸውን ሲያስተካክሉ ታይተዋል፡፡[9] መቼም ቢሆን የእግዚአብሔር (እውነት) እንጂ የግለ ሰቦች ተከታይ መሆን የማያስፈልገው ለዚህ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች የተለያዩ መልካም ነገሮች እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው፤ ስለዚህ ከመልካም ነገራቸው የምንማረው አይጠፋም፡፡ በዚያው አካሄድ ደግሞ ከውድቀታቸውም መማር እንደምንችል አስባለሁ፡፡ (መቼም የጴጥሮስን፣ የይሁዳን፣ የያዕቆብንና የዳዊትን ስሕተት መናገር ተፈቅዶ የዘመናችንን አገልጋዮች ስሕተት መናገር የሚያስኰንን አይመስለኝም)፡፡

ቤኒ ሂን ሲናገር፣ "እኔ አርቲስት ነኝ ... ሁልጊዜም አርቲስት ነበርኩ፡፡ በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ሰዎች ድራማ ነው የሚፈልጉት" (I'm an artist ... I've always been an artist. And people want drama in a situation like this.) በማለት ተናግሯል፡፡[10] እዚህ እኛም ዘንድ በቅርቡ በተካሄደ "ሐዋርያዊ በዓለ ሢመት" ላይ አንድ አገልጋይ፣ "actor [ተዋናይ] ይመስለኛል" በማለት ስለ ተሿሚው ከመድረክ ሲመሰክሩ በቦታው ነበርኩ፡፡

በእግዚአብሔር አደባባይ ደጋግ መስለውና ተለሳልሰው የሚቀርቡ ሰዎች ክፉዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ "ነቢዩም፣ ካህኑም በጽድቅ መንገድ የማይሄዱ ናቸው፤ በቤተ መቅደሴ እንኳ ሳይቀር ክፋታቸውን አይቻለሁ" ብሏል እግዚአብሔር (ኤር. 23፥11 - አ.መ.ት)፡፡ እንዲህ ዐይነቶቹ ክፋታቸው በእግዚአብሔር ቤትም ጭምር ነው የሚገለጠው፡፡

እንዲያውም እንደ ሲ ኤስ ሌዊስ አባባል ከሆነ፣ "ከክፉ ሰዎች ሁሉ፣ የሃይማኖት ክፉ ሰዎች እጅግ ይብሳሉ"፡፡[11] ላያቸው ግን በወርቅ ተለብጧል፡፡ በየቦታው ጻድቅ መስለው የሚታዩት አገልጋዮች እውነተኛ ገጽታቸው በጭምብል የተሸፈነ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደ ፈጣን ሎተሪ ሲፍቋቸው ውስጣቸው ሌላ ነው፡፡ አገልጋዩን ጊዜ ሲፍቀው ከሥር ዋሾው ብቅ ይላል፤ አመንዝራው ብቅ ይላል፤ ሌባው ብቅ ይላል፤ ጨካኙና አረመኔው ብቅ ይላል፤ ክፉው ብቅ

ይላል፡፡ ላዩ ያማረ ውስጡ ግን የተበላሸ ወጭት በየምስባኩ ሞልቷል፡፡ ይህ ሁሉ የማስመሰል ጥረት ምን ይረባቸዋል? ሰዎች ዘንድ ነጥብ ማስቆጠር ፋይዳው ምንድን ነው?

ሼክስፒር፣ “ዓለም የቲአትር መድረክ ናት” ማለቱ ይነገራል፡፡ እኔም፣ “ቤተ ክርስቲያን የቲአትር መድረክ ናት፤ አገልጋዮቿም ተዋንያን ናቸው” ማለት እፈልጋለሁ፡፡ እንደኔ እንደኔ አሜሪካውያን ለፊልም ባለሞያዎቻቸው የሚሸልሙት የኦስካር ሽልማት ሁሉን የሚያካትት ቢሆን፣ ከተዋንያንና ከፖለቲከኞች በላይ የሃይማኖት ቤተ ሰዎች ጠራርገው የሚወስዱት ይመስለኛል፡፡

ምክንያቱም ኑሮአቸው ትወና! አገልግሎታቸው ትወና! ስብከታቸው ትወና! መዝሙራቸው ትወና! አለባበሳቸው ትወና! ሕይወታቸው ትወና! ሆኗልና፡፡ የእግዚአብሔር ቤት የምርጥ ተዋናዮች ቤት መስሏል! በእርግጥ እዚህ ታች ትወናው ተሳክቷል፤ ሁሉን የሚያየው ጌታ ዋጋችንን ሊከፍል የመጣ ጊዜ ተዋንያኑ ምን ይከፈላቸው ይሆን? ውስጣቸው በክፋት ተሞልቶ ለማስመሰል እንዲህ የሚጨነቁት ለምንድን ነው? ዋጋቸውን መቀበል የሚፈልጉት ከሰዎች ስለሆነ አይደለምን? ይህ ባይሆንማ ራሳቸውን ለማስተካከል ቍርጠኝነት በኖራቸው! አሁን ጭብጨባ አግኝተዋል፤ ያኔስ?

ሰዎች በአንድ አገልጋይ ትወና ተታለው ያጨበጭቡለት ይሆናል፡፡ ከመድረኩ ሲወርድና ሰው በማያየው ጊዜ የሚኖረው ሕይወት በዝማሬው፣ በስብከቱ ወይም በጽሑፉ ከሚናገረው የተለየ መሆኑን ባለማወቅ እንደ እግዚአብሔር ሰው ሊቈጥሩት ይችላሉ፡፡ ለዚህም ነው መሰል አሁን አሁን መድረክ ላይ የሚወጣ የትኛውም አገልጋይ “የእግዚአብሔር ሰው!” ሲባል ያጋጥመኛል፡፡ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን እንዴት ዐወቁ? የሰዎች ትክክለኛ ቀለም የሚታወቀው አደባባይ በሚያሳዩት ድርጊት መች ሆነና!?

እግዚአብሔር በጓዳ ኑሮአችን ኪሳራ፣ በአደባባይ ጥሩ ጥሩ ስብከት እንድንሰብክ አላዘዘም፡፡ እሳት ከሰማይ የሚያወርድ ስብከት እንድንሰብክ አልተጠራንም፤ ጥሪአችን ለእግዚአብሔር የመኖር ነው፡፡ ምርጥ ምርጥ መዝሙሮችን እንድንዘምር አልተጠራንም፤ ለእግዚአብሔር እንድንኖር ነው፡፡ አስደናቂ ጽሑፎችን እንድንጽፍ አልተጠራንም፤ ለእግዚአብሔር እንድንኖር ነው፡፡ ደስ የሚል ምክርና ትምህርት እንድናመጣ አልተጠራንም፤ ለእግዚአብሔር እንድንኖር ነው፡፡ እግዚአብሔር የጠራን በእውነት እንድንኖር ነው፡፡

ጥሩ ክርስቲያናዊ ሕይወት በራሱ አገልግሎት ነው፤ “ጥሩ” አገልግሎት ግን ሕይወት ላይሆን ይችላል፡፡ መልካም ክርስቲያናዊ ሕይወት ኖሯቸው ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ የሚሆኑ ሰዎች አይኖሩም፡፡ ጥሩ ጥሩ አገልግሎት



ኖሯቸው በፍርድ ቀን “ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዐመፀኞች ከእኔ ራቁ” የሚባሉ አገልጋዮች ግን ይኖራሉ (ማቴ. 7፥21-23)፡፡ አዎን ሰዎች ፊትን ያያሉ፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ሰው ፊትን ብቻ አያይም!

በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ይህ የማስመሰል ችግር ነበረ፡፡ “ጎስቋላና ምስኪንም፣ ድኻም ዕውርም” መሆናቸውን ችላ ብለው፣ አንዳች እንደማያስፈልጋቸው ነበር የሚያስቡት፡፡ ስለዚህ እውነተኛ ባለጠጋ ለመሆን ወርቅ፣ ኀፍረታቸው እንዳይገለጥ ነጭ ልብስ፣ አጥርተው እንዲያዩ ደግሞ ዐይናቸውን የሚኳሉበት ኩል ከእርሱ እንዲገዙ ጌታ ጋብዟቸዋል (ራእይ 3፥14-19)፡፡ ጕድለታቸውን ከመቀበል እንዲጀምሩ ነው የመከራቸው፡፡

ቅዱስ ዳዊትም በዚህ ነገር ሲቸገር እንደ ነበር ቀደም ብለን አይተናል፡፡ ስለዚህ ችግሩን ከመሸፋፈን ይልቅ አምኖበት እግዚአብሔር እንዲረዳው ድምፁን አውጥቶ ልባዊ ልመናውን አቅርቧል፤ “አቤቱ፤ ረድኤቴ መድኀኒቴም፤ የአፌ ቃልና የልቤ ሓሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን” (መዝ. 19፥14)፡፡ ዳዊት የሚናገረውና የሚያስበው፣ ለሰው የሚገልጸውና በውስጡ የሚያወጣ የሚያወርደው የተለያየ እንዳይሆን - ሁለቱም ያማሩ እንዲሆኑ ነበር ጸሎቱ፡፡ ስለዚህ ጥሩ ጥሩ ዝማሬ ስብከትና ጽሑፍ እንዲኖረን ከመትጋት፣ ከመጸለይና ከመጣጣር ይልቅ የልባችን ሓሳብ፣ ከኑሮአችን (ከሕይወታችን) ጋር የሚጣጣምና ያማረ እንዲሆን ትኩረት ብናደርግ ይሻላል፡፡ የብዙዎቻችን ትኩረት በስውር ከሚያየው ጌታ ይልቅ ግልጡን ብቻ የሚያዩትን ሰዎች ማስደመም ይመስላልና፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ “በሩቅ ሳለን በመልእክታችን በኩል በቃል እንዳለን፣ በፊቱ ደግሞ በሥራ እንዲሁ ነን” ይላል (2ቆሮ. 10፥11)፡፡ በሩቅ ሆኖ ቃሉና ሥራው ተጣጥመውለታል ማለት ነው፤ እኛም ያለን አማራጭ ይኸው ነው፡፡ ለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ጴጥሮስን ፊት ለፊት እንደ ገሠጸው የሚገሥጹንን ሰዎች መቀበል የመጀመሪያው ነው፡፡ ጌታ በተለያየ መንገድ ሊናገረንም ይችላል፡፡ ስለዚህ ራሳችንን ከመቀበል እንጀምር፤ ችግር እንዳለብን እንመን፡፡ ያዕቆብ ማንነቱን እግዚአብሔር ሲጠይቀው እውነቱን ተናግሯል፡፡ ዳዊት ችግሩ ሲነገረው አፍታ ሳይቈይ በእግዚአብሔር ፊት በንስሓ ወድቋል፡፡ እኛም ወደ እግዚአብሔር ፊት እንቅረብና እንደ ዳዊት፣ “አቤቱ፤ ረድኤቴ መድኀኒቴም፤ የአፌ ቃልና የልቤ ሓሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን” በማለት እንለምን፡፡

ይህ ብቻ ግን በቂ አይደለም፡፡ ቍርጠኝነት መኖር አለበት፡፡ ሰዎችን ለማስደሰት ከመሞከር ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ለማግኘት ብቻ ለማገልገል መወሰን ያስፈልገናል፡፡ ምክንያቱም በመጨረሻው ቀን ለፍርድ የምንቀር

በው በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንጂ ዛሬ በትወናችን ባስደመምናቸው ሰዎች ችሎት ፊት አይደለምና። ስለዚህ ከዚህ በኋላ የሆንነውንና እየኖርን ያለነ ውን ብቻ ለመናገር እንድፈር። ለዚህም ድካማችንን ከማመን እንጀምር፤ እን ዲህ ከሆነ ራሳችንን ብቻ ሳይሆን የሚሰሙንንም እናድናለን። የምንኖረው ለእ ግዚአብሔር መሆኑንም ሁልጊዜም ማስታወስ ግዴታ ነው። ይህንን ስንዘነጋ ችግር ውስጥ እንገባለን።

መጽሐፍ ቅዱስ "ቅድስና ለእግዚአብሔር" ይላል፤ የብዙዎች ትኩረት ግን ለሰው ሆኗል። ቅድስና ለሰው! ትሕትና ለሰው! ... ስለዚህ በሰዎች ዘንድ የተደነቁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ሳይኖራቸው፣ በሰዎች ፊት ዋጋ ያልተሰጣ ቸው ደግሞ በአምላክ ፊት ዋጋቸው ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ዛሬ በየመድ ረኩ፣ በየኮንፈረንሱ፣ በየፖስተሩ ... ግርግር ሲፈጥሩ የምናያቸውን ሰዎች ነገ በእግዚአብሔር መንግሥት እናያቸው ይሆን? ጉዳዩ ማርቲን ሉተርን ያስታውሰ ኛል። ሉተር በመንግሥተ ሰማይ ሦስት ነገሮች ሊያስደንቁት እንደሚችሉ ይናገ ራል። እነዚህም፣ (1) እዚያ ይገኛሉ ብሎ የማያስባቸው ሰዎች እዚያ መገኘታ ቸው፣ (2) እዚያ እንደሚገኙ በእርግጠኝነት ሲያስባቸው የነበሩ ሰዎች እዚያ አለመገኘታቸው፣ (3) እርሱ ራሱ እዚያ መገኘቱ ናቸው።[12]

* * *

እንዳይረፍድብኝ ሠግቼ ከእግሬ ነጠቅ ነጠቅ እያልኩ እራመዳለሁ። አንድ ታክሲ ራቅ ብሎ ታየኝ። ጮክ ብዬ መጣራት ስላልፈለግሁ (እራቱን ጣቶቼን አፌ ካልጨመርኩ ደግሞ ማፏጨት አልችልም) እጄን ከፍ አድርጌ እያሳየሁ ርምጃዬን ጨመርኩ። ረዳቱ አየኝና፣ "አንድ ሰው ነህ?" የሚል ጥያቄ ከርቀት ላከብኝ። ውስጤን ያየብኝ መሰለኝና ደንግጬ፣ "አይደለሁም" በማለት መጮኼ አማረኝ። ናፍቆቴ ምን ሆነና!

አንድ ሰው አይደለሁም! ሰው ሲያየኝና ሳያየኝ የተለያየ ሰው ነኝ። ለሰ ዎች የማወራው (የማሳየው) እና እውነተኛ ማንነቴ ይለያያል። እውነተኛ ማን ነቴ የሚገለጠው ስንበረከክ ብቻ ነው። ያኔ፣ "ጌታ ሆይ አግዘኝ፤ እኔ ደካማ፣ ኀጢአተኛና ዐመፀኛ ሰው ነኝ። አንተ ካልረዳኸኝ እንደሚጠፋት እሆናለሁ" እላለሁ፤ እውነተኛ ማንነቴ ይሄ ነው! ከተንበረከክሁበት ተነሥቼ ስሄድ ግን፣ "እኔ ብርቱ፣ ቅዱስና ቅን ሰው ነኝ" ማለት እጀምራለሁ!

አባት ሆይ ምሕረትህን ብቻ እማጠናለሁ፤ ከአንተ በቀር በጎነት የለኝምና!



"ቃሌና አረማመዴ
አንድ አልሆነም ጌታ ሆይ
አታስተካክለኝም ወይ?" የሚለው መዝሙር የማን ነበር?

## ማስታወሻ


1. መርስዔ ኀዘን አበበ፤ *ሙሻዙር* (አዲስ አበባ፣ 1981 ዓ.ም) ገጽ 56።
2. *Harper's Bible Dictionary* (New York: Harper & Brothers, 1952).
3. Philip Yancey, *Soul Survivor: How My Faith Survived the Church* (London: Hodder, 2003), 162-3.
4. መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቱኒ ተምረን ወጣን* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 149።
5. ዴሪክ ፕሪንስ (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *የጋብቻ ኪዳን* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም) ገጽ 31።
6. Jamie Buckingham, *Daughter of Destiny* (Plainfield, N.J.: Logos International, 1976), 153, 149.
7. G. Richard Fisher and M. Kurt Goedelman, et al, *The Confusing World of Benny Hinn* (Saint Louis, Missouri: Personal Freedom Outreach Plainfield, 2001), 1-41.
8. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 265-6።
9. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 259-60።
10. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ xi።
11. Philip Yancey, *The Bible Jesus Read* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1999), 135.
12. R. T. Kendall, *Second Chance* (London: Hodder & Stoughton, 2009), xix.

# ትዳርና እሳት

ወሩ የሠርግ፣ ዕለቱም ሰንበት በመሆኑ የሙሽራ መኪኖች ጡሩንባ በየቦታው ይሰማል። ከሚግተለተሉት መኪኖች አንደኛው ድንገት እኔ የነበርኩበት አካባቢ ቆመ፤ በውስጡ ሙሽራው ከነሚዜዎቹ ይታያል። አጠገቤ ከነበሩት ጐረምሶች የተወሰኑቱ፣ ሚዜዎቹን ተጣርተው፣ "ምነው ባካችሁ? ጓደኛችሁን ተባብራችሁ እሳት ውስጥ? ምነው ምነው?!" በማለት ጮኹ። ንግግራቸውን የሰማነው ሁሉ ሣቅን። ትዳርና እሳት!

አንድ ባለትዳርም፣ "ላገባ ነው" በማለት የነገረውን ጓደኛውን፣ "እርግጠኛ ነህ?" በማለት ከጠየቀው በኋላ፣ "ማን ተቃጥሎ ማን ይቀራል!? በል ግባበት!" በማለት መልሶለታል። አሁንም ትዳርና እሳት!

ትዳር "በሦስት ጉልቻ" ተመስሎ እየተኖረ ባለበት አገር ትዳርና እሳትን መነጣጠል እንዳይቻል ዐውቃለሁ። እሳት ባይኖር ጉልቻ ምን ያደርጋል?! "ሦስት ጉልቻ" የሚል ግጥም አስታወስኩ፡-

ለትዳር ተስማምተን
  ስንጫወት ስንቱን
ጉልቻውን እንጂ
  መች አየን እሳቱን!"'

እሳት ጠቃሚም ጐጂም ነው፤ ለማብሰልም ለማቃጠልም ይውላል። አንዳንዴ ያስፈራል፤ በብርድ ሰዓት ግን ይናፈቃል። ሕፃናት እንዲደርሱበት አይመከርም፤ ዐዋቂዎች ግን ይጠቀሙበታል። ሴቶች እሳትን ማያያዝና ማቀጣጠል ይሆንላቸዋል፤ ወንዶች ግን ይፈሩታል፤ ልክ እንደ ትዳር።

ይህንን ሐሳብ ሲያነሱና ሲጥሉ የዋሉ ሐሳቦች ነበሩ። እርስ በርስ የሚቃረኑ ሐሳቦች ከአንዱ ጥግ ወደ ሌላኛው ሲፈናጠሩ መታደም መታደል ነው፤ ወተትና ማር እንደ መጥባት ይቈጠራል - ላወቀበት። "ወንዶች ለምን እሳቱን (ትዳርን) ይፈሩታል?" የሚል ነበር የሐሳቦቹ ሙግት።

አንደኛው ጀመረ፤ "ፍቅር ለወንድ ልጅ የድካም ቦታ፣ ትዳርም ስስ ብልቱ ነው። ከነጥንካሬው መኖር የሚሻ ለትዳር እጅ መስጠት የለበትም። ሰው በገዛ እጁ ድካምን ይጋብዛል? ያላገባ እንደ በረታ ይኖራል። ስታገባ ትልፈ[illegible]ፈሳለህ። በምንም ነገር ልታስፈራራው የማትችል የነበረውን ሰው ካገባና ከወ



ለደ በኋላ 'ዐርፈህ ልጆችህን ብታሳድግ ይሻልሃል!' ማለት ብቻ ነው የሚጠበቅብህ። ታዲያ መድከም ካላማረህ ትዳር ምን ያደርግልሃል?" ብሎ ጠየቀ።

"መስሎሃል! ሁሉ የየራሱ ድካም አለው። ሰው ሆኖ ስስ ብልት የሌለው የለም፤ ድካሙ ያልተገለጠ እንጂ! ትዳር የተደበቀውን ድካምህን ይገልጣል እንጂ ድካም አይፈጥርልህም። ለያዕቆብ ሹልዳው ጥንካሬውና ብርታቱ ነበር፤ የሹልዳው መነካት ብርታቱን ድካም አደረገው። ከዚያ ማንከስ፣ ሲራመድ እግሩን መጎተት፣ መድከም ጀመረ (ዘፍ. 32፥22-32)። የሰው ድካሙ፣ የብርታቱ ሌላኛው ጎን ነው። ብርታትህ ተመትቶ የምታነከስባትን ያቺን ቦታ ደግሞ እግዚአብሔርም ይፈልጋታል። ያኔ ዐቅመ ቢስነትህን ተገንዝበህ ከእርሱ ጋር ትጣበቃለህ። ጸጋውን ታምነህና ተደግፈህ ትኖራለህ። ጠቃሚና ትሑት ትሆናለህ። ስለዚህ ከነብርታትህ መኖር ብትፈልግም አታመልጥም፤ ብርታትህ ተመትቶ በድካምነት መገለጡ አይቀርልህምና አትድከም። ከትዳር በመሸሽ ድካምህን ቀብረህ አትኖርም።" በማለት ተረጋግቶ መለሰለት።

ሐሳቡ ተቀባይነት ያላገኘለት የመጀመሪያው ተሟጋች ወንዶች ትዳርን የሚፈሩት የኑሮን ቀንበር እየሸሹ መሆኑን ማስረዳት ቀጠለ። "አንድ ሰው ብቻውን ከሆነ ቢበላ ባይበላ፣ ቤት ቢኖረው ባይኖረው ያን ያህል ፈታኝ ላይሆንበት ይችላል። ከአንዱ ቤት ሲያባርሩት ቀጣይ ሥራው ሌላ አካባቢ ለመኖር ደላላ ማፈላለግ ብቻ ነው። 'እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል፤ ድሃ ሞኝ ነው ሞቱን ይመኛል' ነው ነገሩ። ሥራው ባይመቸው ትቶ ይወጣና ሌላ ሥራ ይፈልጋል።

"ትዳር ሲባል ግን ቋሚ ገቢና የመኖሪያ ስፍራ እንደሚያስፈልገው ማሰብ ይጀምራል (ቋሚ ሳይሆኑ ቋሚ ገቢ መፈለግ አይገርምም?)። 'ነገ ሥራ ብፈታ ምን ይውጠኛል? የመሠረትኩትን ቤተ ሰብ፣ ሚስቴንና ልጆቼን ምን አበላለሁ?' እያለ ይጨነቃል። ሥራ ቦታ ማጐብደድ ይጀምራል። የተደላደለ ነገር ከሌለው አብሮነትን የሲኦል ያህል ይፈራል። ትዳር እኮ ለወንድ ልጅ ቀንበር ነው! ስለዚህ ይሮጣል፤ ይሮጣል፤ ዐቅሙ ሲደክምና ማምለጫ ሲያጣ ግን ተሸንፎ ይገባበታል። ከዚያ የቻለውን ያህል ይሸከመዋል።

"ይህ የኑሮ ፍትጊያና ውጥረት ግን አግብቶም አይለቀውም። ለመሆኑ ከባሎችና ከሚስቶች ቀድሞ የሚሞተው ማነው? አሁን ጥናት ላቀርብልህ ባልችልም ወንዱ ላይ ስኳርና ደም ብዛት የሚረባረቡበት ለቤቱ ባለው ሐሳብና ጭንቀት አይደለምን? አደጋና የተለየ ሁኔታ ካልተከሰተ በቀር ወንዱ ነው ቀድሞ የሚሞተው። ወንዱ በብዙ አቅጣጫ ሰጪ ነው፤ ሴቷ ደግሞ ተቀባይ። ስለዚህ ለቤቱ አስፈላጊውን መስጠትና ማቅረብ ካልቻለ ቅስሙ ይሰበራል። ለሰው ይናገራል ብለህ ደግሞ አትጠብቅ፤ ቢያለቅስም ለብቻው ነው። 'ወንድ

ልጅ ብቻውን ነው የሚያለቅስ' ብለው ይሞግቱታላ![2] ሴቶቹ'ኮ በእንባ ይወጣላቸዋል! ወንዱ ግን ኀዘኑና ጭንቀቱ ሲጠራቀም ያለ ጊዜው ይቺን ሕይወት 'ቻው' ሳይል ውልቅ ይላል! ትዳር የብዙ በሽታዎች ምክንያት ነው። ይህንን ለማወቅ ዐይኖችህን ከፍተህ አካባቢህን በቅጡ እጢን።

"ወንዱ ትዳርን ሲፈራ፣ ሴቶቹ ግን መናፈቃቸው ምንም ምስጢር የለውም። እነርሱ ምናለባቸው ልጁ? 'ሥራው ምንድን ነው? ቤት አለው? መኪናስ?' እያሉ ያማርጣሉ። 'ምን ሊያበላኝ ነው? ለሽሮ ለሽሮማ የእናቴ ቤት አይሻለኝም እንዴ?' በማለት ይዘባነናሉ። ታዲያ እነርሱ እንደ ማቱሳላ ቢኖሩ አያስደንቅም እኮ!

"በዚህ ላይ ደግሞ ገንዘብ አይበቃቸውም። 'ይገዛ' ማለት ይወዳሉ። የባንክ ደብተሩን ለሚስቱ የሚያሳይ ወንድ ሞኝነቱ ያበሽቀኛል። እነርሱ ገንዘብ ካዩ የሆነ ያልሆነውን ያወሩና ማሳረጊያቸው 'ይገዛ' ነው! ካገባህ የሚስትህን እጅ ይዘህ መዞር መልመድ አለብህ። ሰው የፍቅር ሊመስለው ይችላል። ሞያ በልብ ነው። ከለቀቅካትማ ያየችውን ዕቃ ልትገዛ ትሄድልሃለች!

"ሌላ ምን እንደሚገርመኝ ልንገርህ? እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን ሲፈጥርለት መነሻው፣ 'ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት' የሚል ነበር (ዘፍ. 2፥18)። አሁን ግን ረዳትዋና ረዳት የሚያስፈልገው ሰው ቦታ ተቀያይረዋል። ባል የሚስቱ ረዳት መሆን ጀምሯል። ታዲያ ሰዎቹ ቦታቸውን ከተቀያየሩ ነገሩስ ተቀይሮ፣ 'ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም ነው' ማለት አንችልም?" አለ የመጀመሪያው ሐሳብ።

ሌላኛው ሐሳብ ደግሞ የዚህን ሐሳብ ሌላ ጐን ማሳየት ነው የመረጠው። "ወንዶች 'ሥራ፣ ገቢ' እያሉ እየተጨናነቁ ትዳርን አድካሚ ያደርጉታል፤ ስለዚህ በማሰብ ብቻ ይደከማቸዋል። መሞታቸው ላይቀር ጣር ያበዛሉ! ሴቶችን እያቸው እስቲ? ከወደዱህ አለቀ፤ ያገቡሃል! የወደዱት ሰው ሥራ ቢኖረው ባይኖረው 'ኬር' የላቸውም።

"በእርግጥ 'ይገዛ' ማለት ይወዱ ይሆናል፤ ማብቃቃት ላይ ግን ጎበዞች ናቸው። 'ወንድ ልጅ የማይፈልገውን 20 ብር የሚያወጣ ዕቃ በ30 ብር ሲገዛ፣ ሴቶች ግን የሚፈልጉትን 20 ብር የሚያወጣ ዕቃ በ15 ብር ይገዛሉ' ይባል የለ?! አንተ ሳታገባ በፊት ለወር የመደብከው ወጪ አለ እንበል። ሚስት ብታገባና ብሩን ለእርሷው ብትሰጣት ግን በዚያው ብር የተሻለ ልትኖሩ ትችላላችሁ።

"'ሠርተን እናድጋለን' ብለውም ያምናሉ፤ ልበ ሙሉነት ይታይባቸዋል። የዚህችን ዓለም ኑሮ ደግሞ ተጨናንቀህ አትችለውም ወንድሜ። እግዚአብሔርን እየፈራህ ተደሰት! ገና ለገና፣ 'ነገ ምን ይሆናል?' እያልክ ጭንቅላትህን



አትዘውር። በእጅህ ባለው ነገር ኑር! 'ነገ ስለ ራሱ ይጨነቃል' ይላል መጽሐፉ። 'Have fun!' ያኔ ስኳር ምናምን ከሚባል ጣጣ ትገላገልና ረጅም ዕድሜ ትኖራለህ፤ የማቱሳላንም ባይሆን የሴቶችን ያህል!

"'ከሚስቶች ይልቅ ለባሎች ሞት ቅርብ ነው' ብለሃል፤ እውነት ነው። እኔ ደግሞ በደንብ የተጠና ጥናት ልንገርህ። ትዳር ዕድሜ ያረዝማል! ከባለ ትዳሩ ወንድ ይልቅ ሽጋው ወንደላጤ ነው ቀደም ብሎ ሒሳቡን የሚዘጋው። አትሞኝ፤ መኖር ከፈለግህ አግባ! 'በአማካይ ሲታይ ባለትዳሮች በጤና፣ በሀብትና በደስታ ካላገቡት የተሻለ ኑሮ እንደሚኖሩ ጥናቶች ይጠቁማሉ።'[3] ያለ ዕድሜያቸው የሚሞቱ ብቻቸውን የሚኖሩ ሰዎች የሞት መጠን ከባለ ትዳሮቹ በዕጥፍ፣ ራሳቸውን የሚገድሉ ላጤዎች መጠን ከባለትዳሮቹ በአምስት ዕጥፍ ይበልጣል። ያላገቡ ሰዎች ላይ የሚደርስ አደጋ ባለትዳሮቹ ላይ ከሚደርሰው አደጋ አራት ዕጥፍ በላይ ለሞት ሲያደርስ፣ በካንሰር ደረጃ እንኳ በካንሰር ሕመም የተያዙ ባለትዳሮች በካንሰር ከተያዙ ላጤዎች የበለጠ ዕድሜ ይኖራሉ።[4]

"ባለትዳሮች ቶሎ አይሞቱምና ዕወቅበት። ከገባህ አግብተህ ትኖራለህ! ቅዱሱ መጽሐፍ ትክክል ነው፤ 'ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም።' ትዳርን የጀመረው እግዚአብሔር መሆኑን አትዘንጋ፤ ያውም ኀጢአት ወደ ሰው ከመግባቱ በፊት! ሆኖም የሰው ልጅ ፍጹም ባለመሆኑ፣ እንደ ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር የጀመረው ይህ ተቋምም ችግር እንዳጋጠመው መካድ አንችልም። ተጋቢዎቹ ፍጹማን ካልሆኑ ትዳር እንዴት ፍጹም ሊሆን ይችላል? ይህ ግን ለሽሽት ምክንያት አይሆንም። ጠባይህን አሳምረህ ብታገባ ነው የሚሻልህ፤ እንዳለማግባት እኮ እርግማን የለም" በማለት አስረዳ።

ሌላኛው ሐሳብ ቀጠለ። "እኔ የምለው ፈረንጅ አገር የተካሄደ ጥናት ሁሌም እኛን ይወክላል እንዴ? እውነት በእኛ አገር ኑሮ ትዳር ዕድሜ ያረዝማል ብለህ ታምናለህ? ኑሮ ለተሳካላቸው ሰዎች ምናልባት ይሆን ይሆናል፤ ከዚህ ውጪ ላሉት ግን ጥናቱ የሚሆን አይመስለኝም። በእኛ አገር የተካሄደ ጥናት የሚኖረን መቼ ይሆን?

"እውነት ነው፣ ትዳርን እግዚአብሔር ነው የጀመረው። ትዳርን ሙሉ በሙሉ እንዳልቃወም ዋነኛ ምክንያቴም እርሱ ነው፤ እግዚአብሔር የመሠረተው ነገር በመሠረታዊ ሁኔታ መልካም እንደ ሆነ አምናለሁ። ግን ከትንሣኤ በኋላ ትዳር እንደ ሌለ መጽሐፉ ይናገራል። ከውድቀት በፊት ተጀምሮ ከትንሣኤ በኋላ የማይቀጥል ነገር! ለማንኛውም ትዳርን በጥቅሉ ከመቃወም የትዳርን ችግሮችና ሥጋቶች መጥቀሱ ይሻለኛል።

"ይኸውልህ ሴቶች ካገቡህ ባል ብቻ አድርገው የማስቀረት ዐቅምም አላቸው። 'ራስን መፈለግና መሆን፣ በመከሊቴ መነገድ፣ ለትውልድ የሚተርፍ *ሥራ መሥራት*' የሚል ትልቅ ሓሳብ ካለህ ባታገባ ይሻልሃል፤ አሊያ ባል ብቻ ሆነህ ትቀራታለህ! እነርሱ ከዕለት ዕለት ኑሯቸው ውጭ ለዚህ ዐይነቱ ጉዳይ እምብዛም ትኩረት አይሰጡም። እነርሱ የሚያስቡት የእነርሱ (የሚስትህና የልጆችህ) ሆነህ መቅረትህን ብቻ ነው፤ የቻሉትን ያህል ተጣጥረው ገንዘባቸው ሊያደርጉህ ይሟሟታሉ። 'የሆነ ነገር ላከናውን' ብለህ ከተነሣህማ የሁሉ ልትሆንባቸው ነው! ዝነኛነትህን ይወዳሉ፤ የዝነኛ ሰው ሚስት መሆንንም ከምንም በላይ ይፈልጋሉ፤ ዝነኛነትህ ወይም ስኬታማነትህ የሁሉ ገንዘብና በሁሉ ተወዳጅ እንዲያደርግህ ግን አይፈቅዱልህም። ይህ ከሚሆን ዐርፈህ መቀመጥህን ይመርጣሉ።

"ስለዚህ አንተ ለትውልድ የሚጠቅም፣ ስምህን ከመቃብር በላይ የሚያስጠራ ጉዳይ ተሸክመህ እነርሱ ለጥቃቅኗ ጉዳይ ነው የሚብሰከሰኩት። ስለ ዓለምና ስለ አገር እንዳታስብ በማጀት ወሬ ናላህን ያዞሩታል። ለሓሳቤ ዋቢ ልጥቀስ። ባራክ አባማ የአሜሪካ ፕሬዚደንት ከመሆናቸው በፊት ገና ሴናተር እያሉ የተፈጠረ ታሪክ ነው። በወንድና በሴት መካከል ያለው የአስተሳሰብ ቅኝት ለየቅል መሆኑን በደንብ ያሳይሃል። ሴቶች አንቱ ሲባሉ እንደማይወዱ ስለሚነገር፣ ሚስትየውን በአንቺታ ባቀርብ እንደማትቀየመኝ ተስፋ አደርጋለሁ" በማለት መጽሐፉን ገለጥ ገለጥ አድርጎ ማንበብ ጀመረ።

"*ታሪኩ እንዲህ ነው።* ባራክ አባማ ያንን ቀን 'ጥሩ ሙድ' ላይ እንደነበሩ ይናገራሉ። በጥቍር ገበያ የሚካሄደውን የጦር መሣሪያ ሽያጭ የሚያግድ የሕግ ረቂቅ ከሌላ ሴናተር ጋር በመተባበር አዘጋጅተው መጨረሳቸው ነው። ረቂቅ ሕጉንም ለማጽድቅ የተመቻቹ ሁኔታዎች ስለ ነበሩ ይህንኑ መልካም ዜና ለሚስታቸው ሚሼል ለመንገር ይፈልጉና ስልክ ይደውላሉ፤ ወደ ቺካጎ። የሚደውሉት ከዋሽንግተን ዲሲ ግዛት ነበር።

አባማ የሕጉን ፋይዳ መተንተን ይጀምራሉ፤ ለሚስታቸው። ከቅለታቸው የተነሣ በትክሻ ተይዘው የሚወነጨፉ ሚሳይሎች በክፉ ሰዎች እጅ ከገቡ፣ የንግድና የሕዝብ ማጓጓዣ አውሮፕላኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርሱ *ሥጋታቸውን* ይገልጣሉ። ከቀዝቃዛው ጦርነት ማከተም በኋላ እዚህም እዚያም የተዝረከረኩት የጦር መሣሪያዎች በዓለማችን ላይ በተለያዩ ቦታዎች የሚለኮሱትን ግጭቶች ምን ያህል እንዳባባሱ እያስረዱ እያለ ሚስታቸው ታቋርጣቸዋለች።

"ጉንዳን ቤታችን ገብቷል።"



"እኸ ... "

"ጉንዳኖች ኩሽና ገብተዋል ነው የምልህ፤ ፎቅ ላይ ያለው መኝታ ቤትም ገብተዋል።"

"እሺ ..."

"ነገ ወደ ቤት ስትመጣ የጉንዳን ማጥፊያ ገዝተህ እንድታመጣ እፈልጋለሁ። ራሴ መግዛት እችል ነበር፤ ግን ልጆቻችን ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ሐኪማቸው ጋ ልወስዳቸው አስቤአለሁ። እና ይህንን ልታደርግልኝ ትችላለህ?"

"በትክክል። ጉንዳን ማጥፊያ አይደል ያልሽኝ?"

"አዎን ጉንዳን ማጥፊያ። እንዳትረሳ እሺ የኔ ማር! ደ'ሞ ከአንድ በላይ ነው ያልኩህ። እየሰማኸኝ ነው? አሁን ስብሰባ አለብኝ። እወድሃለሁ" ብለው ስልኩን ዘጉ።[5]

"ባራክ አባማ ምን አሉ መሰለህ? 'የስልኩን መነጋገሪያ አስቀመጥኩና ኬኔዲና ጆን ማኬይን ከሥራ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ጉንዳን ማጥፊያ ገዝተው ያውቁ እንደ ሆን ማሰብ ጀመርኩ' ነው ያሉት።[6]

"እስቲ እግዚአብሔር ያሳይህ፤ መልአኩ ያመልክትህ! ለዓለም ሰላም ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው *ሥራ ለመሥራት* ሲደክሙ፣ ስለ ጉንዳን ማውራት ምን ይሉት ቂልነት ነው? ደ'ሞ ይህ ብቻ እንዳይመስልህ" በማለት ይህ ሓሳብ ለሌላኛው ሓሳብ ሓሳቡን ማስረዳቱን ቀጠለ።

"ባራክ አባማ ሴናተር (የላይኛው ምክር ቤት ተመራጭ) ከመሆናቸው በፊት ለኮንግሬስ (ለታችኛው ምክር ቤት) ተወዳድረው ነበር። ያኔም ቢሆን ባራክ አባማ በምርጫ ውጥረት ውስጥ ሆነው ኩሽናውን ሳያጸዱ ከቀሩ ጦርነት ይገጥማቸው ነበር። ጠዋት ወደ *ሥራ* ለመሄድ የስንብት ከንፈሯን ሊስሙ ጠጋ ካሉ ቀዝቃዛ ጉንጭ ነበር የምታቀብላቸው። እንዴማ፣ 'አንተ ለራስህ ብቻ ነው የምታስበው' በማለት ወርፋቻዋለች።[7]

"አባማ የፓርቲያቸውን ዕጩነት ከማግኘት ጀምሮ እስከ ፕሬዚዳንትነት ምርጫው ፍጻሜ ድረስ ከሁለት ዓመታት በላይ በጉዞና በንግግር ደክመዋል። ሚስታቸው ረድታቸው ይሆን? በቅስቀሳ ወቅት አባማ ከሌላ ግዛት ልጆቻቸውን ለማናገር የሚፈቀድላቸው ከመኝታ ሰዓታቸው በፊት ከደወሉ ብቻ ነበር። የፕሬዚዳንትነትን ዕጩነት ምርጫ ማከሰኞ አሸንፈው እንኳ ለማረፍ አልታደሉም፤ ገና ደስታው ብዙም ሳይበርድ ነበር፣ 'ነገ ልጆቹን ትምህርት ቤት የምታደርሳቸው አንተ እንደ ሆንክ ዕወቅ' የሚል ትእዛዝ የሰጠቻቸው።[8]

“እና ወንዱ ባል ብቻ ሆኖ መቅረትን ፈርቶ እሳቱን ቢሸሽ ምን ጥፋት አለበት? እንዲያውም መለኛነት ነው:: ነጻ ሰውና ባለጓዝ እኩል ይጓዛልን? ለጉዞ ቅልጥፍናም ቢሆን ብቻነት ይመረጣል! የሜዳ አኽያንና የከተማችንን ባለሸከም አኽያ ማወዳደር ነው:: ባራክ አባማ ለፕሬዚዳንትነት ሲመረጡ ግን ሚስታቸውን ከማመስገን አልተቆጠቡም፤ ፖለቲካ ነዋ፤ የቤተ ሰብ ፖለቲካ::

“በምርጫ ብትሳተፍ፣ መጽሐፍ ብታሳትም፣ ሩጫ ብትወዳደር ከተሳካልህ ሚስትህን ማመስገን አለብህ:: እነዚህን ነገሮች እንዳታደርግ ተቃዋሚህ የነበረች ብትሆንም፣ ሚስትህ እንደ ደገፈችህና ያለ እርሷ እገዛ እዚህ ትደርስ እንዳልነበር ገልጸህ ካላመሰገንካት በራስህ ላይ ፍም ትነሰንሳለህ:: በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት የደረሰብኝን ዐውቃለሁ:: አንዱ ባል የጻፈውን ግጥም እስቲ ላንብብልህ፤ “ጎጆዬ” ይላል ርእሱ:: ግጥም እንደምትወድ ዐውቃለሁ::

በየቀኑ!
“ድምፅህን ስጥ” እባላለሁ::
እኔም እላለሁ፤
“በዴሞክራሲያዊ መንገድ
አንቺን መርጫለሁ!”
ፓርቲዬንም ስጠየቅ፣
“የጎጆዬ አባል ነኝ” እላለሁ::
መግለጫ ስጥ ስባል፣
ከልጆቼ ጋራ፣ ምንም ሳላቅማማ
“ትዳሬ ነው ፓርላማ”
ብዬ እናገራለሁ::
ይህን ያላወቁ!
“እሱ ከቤቱ በቀር፣
የአገር ጉዳይ አይገባውም፤
ድርጅትም አያውቀውም”
እያሉ ያሙኛል፤
ያብጠለጥሉኛል::
ይገርማል!
ፍቅርን ያህል ፖለቲካ፣
ቤቱ እንደሚቦካ፣
ሰው አያውቅም ለካ::[9]

“ሰው የሚኖረው እንዲህ ነው ወዳጄ:: የቤተ ሰብ ፖለቲካ የሚባል ነገር መኖሩን ብታውቅ ይበጅሃል:: ጨርሻለሁ አንተ ቀጥል” አለ እየተኮፈሰ::



“በል በል ወዳጄ” አለ ሁለተኛው ሓሳብ ከመጀመሪያው ሓሳብ አፍ ነጥቆ:: “አንተ ሙሉውን ሥዕል ሳይሆን ማየት የምትፈልገውን ጥግ ብቻ ነው የምታየው:: ለመሆኑ እቴጌ ጣይቱን ማስታወስ ቢያቅትህ እንኳ ብርቱካን ሚደቅሳን እያየህ ሴቶችን ለአገር ጉዳይ ባይተዋር አድርገህ ማሰብህ ያስገርማል:: በዚህም ላይ ከርክርህ ወንድና ሴት በጋራ የመሠረቱትን ኑሮ በጋራ መምራት የለባቸውም የማለት አዝማሚያ አለው ልበል?

“በተጨማሪም አንተን ጨምሮ ከወንዶች የተሰወረ አንድ ትልቅ ጉዳይ አለ፤ ለውጥ የሚጀምረው ከራስ ነው:: ቤትህን ከለወጥክ በኋላ ብቻ ነው አካባቢህን፣ ሰፈርህን፣ ክልልህን፣ አገርህን፣ ከዚያም ዓለምን መለወጥ የምትችለው! ወንዶች በአንዴ ማማው ላይ ለመውጣት እንጋጠው ነው የሚራመዱት፤ መውደቅ ከየት የሚመጣ ይመስልሃል? መሰላሉን ለመውጣት ከታች መጀመር አለብህ:: ቤትህ ሰላም ሳይሰፍን ዓለም ላይ ሰላም ለማስፈን መጣጣር ባዶ ምኞት ነው:: መሠረቱን ሳትጥል ቤቱን አየር ላይ ትሠራዋለህ እንዴ?

“ሁሉ ነገር ከጥቂት፣ ከራስ፣ ከቤት መጀመር አለበት:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሚነግረው ይህንኑ ነው፤ ‘እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?’ (1ጢሞ. 3፥2-5):: ‘ዲያቆናት ልጆቻቸውንና ቤተ ሰቦቻቸውን በአግባቡ የሚያስተዳድሩ መሆን አለባቸው ...’ (3፥12 - አ.መ.ት):: ሌላ ሰፍራ ሰላም ለማውረድ ከመወራጨት የቤትን ኀላፊነት መወጣት ይቀድማል:: ገብቶሃል ወዳጄ? የቤት ሥራቸውን፣ የቤት ኀላፊነታቸውን ሳይሠሩ ‘የዓለም ሰላም’ እያሉ መሯሯጥ አይሠራም:: ሴቶች ቤታቸው ላይ በማተኮራቸው በጣም ትክክል ናቸው:: ‘የዓለም ሰላም ከቤት ይጀምራል’ ሲባል ሰምተህ አታውቅም?

“ሴቶች ያገቡትን ወንድ ባል ብቻ አድርገው እንደሚያስቀሩ ሥጋት እንዳለህም ገልጸሃል:: ይሄ መነፅርህ ገልብጦ ነው ያሳየህ::

“ቅድም የጠቀስካቸው ባራክ አባማ ሚስታቸውን ያመሰገኑት በሰላም ለመኖር ሲሉ ብቻ ይመስልሃል? ‘ሚስትን ማመስገን ፖለቲካ ነው’ ያልከውን ማለቴ ነው:: ምስጋናውን ለእጅ መንሻነት ወይም ለመሸንገያ እንዳቀረቡት ካሰብክ ተሳስተሃል:: ባራክ አባማ ከላይ የጠቀስካቸውን ውጥረቶች ካለፉና አብራው ከሰከነ በኋላ ረጋ ብለው ሲያስቡት የተረዱትን ጽፈውልሃል እኮ! እዚያው መጽሐፍህ ላይ አሳይሃለሁ፤ ወዲህ በል መጽሐፉን” አለና ቀጣይ ሓሳቡ ቀጠለ::

“ይኸውልህ ባራክ አባማ እንዲህ ነው ያሉት፤

'እነዚያ ፈታኝ ዓመታት ካለፉና ልጆቻችንም ዐድገው ትምህርት ቤት መሄድ ሲጀምሩ የኋላዬን ዘወር ብዬ ሳየው ብቻ ነበር በዚያን ወቅት ሚስቴ እያለፈችበት በነበረው ሁኔታ ላደንቃት የጀመርኩት፡፡ ትግሏ ሌሎችም ሥራ ውለው የሚገቡ የዛሬዎቹ ሴቶች የሚያልፉበት ትግል ነው፡፡ ምንም ራሴን ነጻ አስተሳሰብ ያለው ሰው አድርጌ ብቈጥርም፣ እኔና እርሷ እኩል ባለድርሻዎች (አጋሮች) መሆናችንንና የእርሷም ሕልምና ምኞት የእኔኑ ያህል ጠቃሚ እንደ ሆነ ባስብም እንኳ ልጆቻችን ሲመጡ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ የምታዘጋጀው እርሷ እንጂ እኔ አልነበርኩም፡፡ በእርግጥ አንዳንዴ ባግዛትም በራሴ መርሐ ግብርና በራሴ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ መኻል ግን ለቤት ውስጥ ኀላፊነቷ ስትል የቢሮ ሥራዋን የምትበድለው እርሷው ነበረች፡፡ ልጆቻችን ምግብ መብላታቸውንና መታጠባቸውን ከመተኛታቸው በፊት ማረጋገጥ የእርሷ ሥራ ነው፡፡ ልጆቻችን ሲታመሙ ወይም ሞግዚታቸው መምጣት ሲያቅታት በስልክ ብቻ በመናገር ከሥራዋ ወይም ከሰዎች ጋር ካላት አስፈላጊ ስብሰባ የምትቀረውም እርስዋ ነበረች፡፡'[10]

ብለው ገልጸውታል፡፡ገባህ?

"ቅድም ገሚሱን ብቻ ነጥለህ ጠቀስከው እንጂ 'ለራስህ ብቻ ነው የምታስበው' ካለቻቸው በኋላ፣ 'ቤተ ሰቡን ብቻዬን እንደማሳድግ (እንደማስተዳድር) በፍጹም አላሰብኩም ነበር' ነው ያለቻቸው፡፡[11] ባራክ አባማ የልጆቹን ጉዳይ ችላ ብለው ለምርጫ ሲሯሯጡ ነበር የቤት ኀላፊነታቸውን እንዲያስታውሱ የሸነቆጠቻቸው፡፡

"ሚስትህ አንተ በመረጥከው የሕይወት ጐዳና ቀጥተኛ እገዛና ተሳትፎ ባይኖራት እንኳ አንተን መውደድና ልጆቻችሁን መከባከብን ጨምሮ ሌሎቹን የቤት ኀላፊነቶች መሸከሟ ለአንተ ጉዞ የሚኖረውን በጎ አስተዋጽኦ መካድ ትችላለህ? ጽናቷስ ዋጋ የለውምን? እርሷ የቀነሰችልህን ሸክም ሁሉ ብቻህን ለመሸከም ብትሞክር ኖሮ ሩጫህን በቅጡ መሮጥና የምትፈልገው ቦታ ደርሰህ የምትሻውን ለውጥ ማምጣት ባልሆነልህም!

"ስለዚህ ለባራክ አባማ እዚህ መድረስ የሚስታቸው ድርሻ ወሳኝ ነበር፡፡ ባል ብቻ አድርጐ የሚያስቀርህ ትዳር አይደለም፤ የሴቲቱ ብስለት ነው፡፡ ባል ብቻ አድርጋ ልታስቀርህ የምትችል ሴት የምታጋጥምህን ያህል፣ ባል ብቻ ሆነህ እንዳትቀር የምታተጋህ ሴትምሞልታለች፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዳለው፣ 'ሚስት ትሠራሃለች ወይም ትሰብርሃለች'፡፡[12] ጎበዝ ሚስት



ታበረታታሃለች፤ ከተኛህ ትቀሰቅስሃለች፡፡ ካስፈለገም ትሰድብሃለች፡፡ ስታዝን አዝና፣ ስትደሰት ተደስታ ሁሌ ከጐንህ የማትጠፋው እርስዋ ናት፡፡ አንተ ብቃቱ ኖሮህ ብቃትህን ማሳየት የምትችልበት ሁኔታ ካልተመቻቸ ማንም ሊያደንቅህ ቀርቶ ሊያውቅህ አይችል ይሆናል፡፡ ባለአእምሮ ሚስቶች ግን ማንም ያላየውን የባሎቻቸውን ችሎታ ማየት ይችላሉ፤ ማየት ብቻም ሳይሆን ዘመናቸውን ሁሉ የባሎቻቸው አድናቂ ሆነው ይኖራሉ፡፡ ብቃቱን ማንም ያላወቀለት ሰው ሚስቱ ብቻዋን ዕድሜ ልኳን አድናቂው ትሆናለች፡፡ ድካሙን እያወቀች እንኳ አድናቆቷን አታጓድልበትም፡፡ ይልቁኑ ወንዶች ያሰቡበት ከደረሱ በኋላ ሊደገፏቸው ሴት ጀርባቸውን እንዳይሰጡ ፍራ፡፡

"አንተ የፈረንጅ አገሩን ፕሬዚዳንት ተወውና ለምን ቴዎድሮስን አታስብም? ቴዎድሮስ ገና ካሣ ተብሎ በሚጠራበት ጊዜ ጀግንነቱን ያዩት የጊዜው ቁንጮ ባለ ሥልጣን ራስ ዐሊ ከእናታቸው እቴጌ መነን ጋር ተማከረው ልጃቸው ተዋበችን ዳሩለት፡፡ ደጃዝማች ብለውም ሾሙት፡፡ ደጃች ካሣም ትልቁን ሕልሙን ዘንግቶ ለባለ ሥልጣናቱ ዐደረ፡፡ የሚስቱ ተዋበች እናት ክብሩን ሲነኩበት ቢቀየምም ዐርፎ መቀመጥን የመረጠ ይመስል ነበር፡፡ ያኔ ነው ተወዳጅዋ ሚስቱ ተናድዳ 'አገር የለህምን? ታጠቅ፤ እንሂድ' በማለት የተናገረችው፡፡ ያኔ ካሣም፣ 'ምነው የለኝ?' ብሎ ሸፈተ፡፡[13] የተኛው አንበሳ በዚህ ንግግር ተቀሰቀሰ፡፡ 'የሆነ ሆኖ፣ የልጅ ካሣ የመጨረሻውና ወደ ዘውድ የመራቸው ሸፍትነት ከዚህ ጊዜ ላይ ይጀምራል' በማለት ታሪክ ይመሰክራል፡፡[14] የቴዎድሮስ የፈረስ ስም 'አባ ታጠቅ' የተባለውም ለዚህ እንደ ሆነ ይነገራል፡፡ ተዋበች ባትኖር ቴዎድሮስ ይታጠቅ ነበር?

"ካልበቃህ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ያሉትንም እጨምርልሃለሁ፤ 'በዓለም ላይ በአቋማቸው ጽኑ የሆኑ ጀግኖች አሉ፡፡ እነዚህ ብዙ ጊዜ የማይታወቅላቸው ሰዎች ሴቶች፣ ሚስቶችና እናቶች ናቸው ብዬ እገምታለሁ፡፡ አንድን ሰው ካፈቀሩ ሕይወታቸውን ሙሉ የሚኖሩት ለዛ ላፈቀሩት ሰው ነው፤ ብዙ መሥዋዕትነት ይከፍላሉ፡፡ ራስ ወዳድነት የላቸውም፡፡'[15]

"ይልቁኑ የትኛውም ባል ወደ ስኬትና ዝነኛነት የሚደርሰው ከሚስቱ ጋር የሚያሳልፈውን የግል የቈይታ ጊዜ ቀንሶ፣ የልጆቹን ኀላፊነት ለእርሷ ትቶ ነው፡፡ እኛ የምናደንቃቸው ብዙ ወንዶች አሁን የደረሱበት የደረሱት የሚስቶቻቸውን ደስታ መሥዋዕት አድርገው ነው፡፡ ሚስት ከምትወደው ባሏ ጋር ለብቻ መጫወት እየፈለገች ባል ለዓላማው ይሮጣል፡፡ ስለዚህ ሌሎች ሴቶች ይህን ደስታ እንዳልተከለከሉ እያየች በሯን ዘግታ የምታለቅስባቸው ቀናት ይኖራሉ፡፡ ለሴት ከባሏ ጋር ጊዜ ማሳለፍ በምንም የማይተካ ሕይወቷ ነው! ሕይወቷን እኮ ነው የምታሳጣት?! በተጨማሪም ልጆቻቸውም አባታቸውን በማጣት እንዳይበ

ላሹ ወይም እንዳያዝኑ እናት ብቻ ሳይሆን አባትም መሆን ይጠበቅባታል:: ለእርሷ ግን ማን ባል ይሆናታል?

"በእውነት ባለትዳር ወንድ ለአገር የሚተርፍ ነገር ቢያበረከት ሚስቱን ሕይወትና ደስታ ከልክሎ መሆኑን ዕወቀው! ስኬታማ ሲሆን ግን ሚስቱንና የልጆቹን እናት ችላ ብሎ ሌሎች ወጣት ሴቶችን የሚያማትርና ስኬቱ በሚያስ ከትለው ወጥመድ የሚወድቅ ወንድ ቊጥሩ ቀላል አይደለም:: ለዚህ ሁሉ መሥዋዕትነቷና በእርሷ ሞት ለመጣ ስኬት ብድራቷ ይሄ መሆን አለበት?! ታዲያ ሚስቱን ቢያመሰግናት ይበዛባታል?! ይህማ ሚዛን የጐደለው አስተያየት ነው፤ ምነው ጃል?" ብሎ እየጠየቀ ጨረሰ::

"እሺ ይሁንልህ! አንድ ሓሳብ ግን ይቀረኛል:: አንተ እንዳልከው ወን ዶቹ አይደሉም የሚለወጡት:: ሴቶቹ ብልጦች ስለሆኑ ባላቸው ታዋቂ መሆን ሲጀምር ሸምቀቆውን ያጠብቁበታል:: ወንዱ ከፍ ከፍ ማለት ሲጀምር ለስሙ መጠንቀቅ ይጀምራል:: ሚስቶች ይህንን ስለሚያውቁ ምንም ቢያደርጉ አቶ ባል ጨከኖ እርምጃ እንደማይወስድ ያውቃሉ:: አሊያ ሰው አፍ ሊገባና ስሙ በከፉ ሊነሣበት ነው:: መንገዱም ይበላሸበታል:: ስለዚህ የሚስቱን ፊት እያየ የሚያድር ሽቁጥቁጥና እንደ ቄጤማ የሚጐዘጐዝ ይሆናል:: ለምትጠይቀው ሁሉ 'እንዳልሽ' ማለት ይጀምራል:: 'ቢጭኑት አኽያ፣ ቢጋልቡት ፈረስ' ዐይነት!

"የሴቶቹ ብልጥነት የሚጀምረው ከልጅነታቸው ነው:: እስቲ ከወንድ ልጅና ከሴት ልጅ አፉን ቀድሞ የሚፈታው ማን ይመስልሃል? ወንዱ በልጅነቱ ሞኝ ቢጤ ነው፤ ሴቶቹ ግን በአብዛኛው ምላጮች ናቸው:: በልጅነቴ ወላጆቼ፣ 'ሞኙ' ይሉኝ ነበር፤ 'ሞኟ' ተብላ የምትጠራ ሴት ግን ታውቃለህ? ሴቷ ከሥረ መሠረቷ ብልጢት ናት፤ ባደግንባቸው ተረቶች ላይ እንዳለችው ጦጢት! ብልጥ ሰው በአንስታይ፣ ሞኙ ደግሞ በተባዕታይ ጾታ የሚገለጸው በከንቱ አይ ደለም እኮ! ታዲያ ሚስቶችን እንዴት ማሸነፍ ይቻል ይመስልሃል ወዳጄ?

"ሴት ልጅ የምታስበውን የዕድሜ እኩያዋ የሆነ ወንድ ሊያስበው አይችልም:: ሴቷ በ18 ዓመቷ የምታስበውን ወንዱ ልጅ ምናልባት በ25 ዓመቱ ቢያስበው ነው:: ወንድ ልጅ እንኳን ታላቁን ሊያገባ ይቅርና የዕድሜ አቻ ውንም ማግባት እንደሌለበት አጥብቄ የምከራከረው ለዚህ ነው:: ወንድ ልጅ በዕድሜ የግድ ከሚስቱ መተለቅ አለበት:: ሌላው ቢቀር በዕድሜው እንኳ ሚዛን ይድፋ እንጂ!

"ይህን የምለው አንድ በትዳር የቈዩ አንጋፋ የቤተ ክርስቲያን ሰው አን ድን ጀማሪ አገልጋይ የመከሩት ትዝ ብሎኝ ነው:: 'በአገልግሎት መታወቅ፣ ከፍ



ከፍ ማለትና ዝነኛ መሆን ስትጀምር የሚስትህ አሽከር ለመሆን ተዘጋጅ!' ብለ ውታል:: እውነት ይመስላል:: በየጓዳው ስንት ጉድ አለ መሰለህ? ለስምና ለክብር ሲባል ታፍኖ እንጂ! ጥሩና ጸጥተኛ መስሎ የምታየው ትዳር ሁሉ እንደ ምታየው የምር ጥሩ እንዳይመስልህ፤ ጭምብል የለበሰ ሊሆን ይችላል:: ኀበዙ ሁላ ከውጪ አምባገነኖችን እየተፋለመ በጓዳው ለአምባገነን ይገብራል፤ በማል ቀስ፣ በማኩረፍና በመነጫነጭ ፈቃዷን ለምታስፈጽም አምባገነን:: እና ሚስቶ ችን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል አባክህ? ሚስቱን አሸንፎ የሚኖር ወንድስ ታው ቃለህ?" በማለት ጥያቄውን አከታተለና የመልስ ሓሳብ መጠባበቅ ጀመረ::

"ቈይ፣ መተሳሰብና 'አንቺ ትብሽ፣ አንተ ትብስ' መባባል ሲቻል፣ መሸና ነፍን ምን አመጣው? ጥያቄህ ግን የዓለም ወንዶች ሁሉ ጥያቄ ይመስለኛል:: ቴዎድሮስን ትወዳቸው የለ? እሳቸው የተናገሩትን አንድ መጽሔት ላይ አንብቤ አለሁ:: እርሱን ልንገርህና ይብቃን" አለ:: አነጋገሩ ድካሙን ይናገራል::

አንድ ቀን አፄ ቴዎድሮስ ሲተከዙ ቈይተው መኳንንቱን "ኧረ ለመሆኑ ከመካከላችሁ ሚስቱን ገዝቶ (አሸንፎ) የሚኖር ማነው?" ሲሉ ጠየቁ [ምን አጋጥሟቸው ይሆን?]::

"እኔ" አለ ከመኳንንቱ አንዱ::

"እንዴት አድርገህ?" አሉት ዐፄ [የጓጉ ይመስላል]::

"እንዲያው ገና ሳያት በጥፊ አልሳታለሁ!"

"ተው ተው ተው:: ሌላስ?" አሉ ዐፄ::

"እኔ" አለ ሌላው:: "ገና ስንተያይ አካኪ ዘራፍ እልባታ ለሁ::" ሌሎችም ልዩ ልዩ ዘዴያቸውን ተናገሩ:: ዐፄ ሁሉንም "ከንቱ ነው" አሉ::

በመጨረሻም አንዱ ባላገር፣ "እኔ ነኝ ሚስቴን ገዝቼ እምኖር" አለ::

"እንዴት አርገህ?"

"እንዳሻሽ ብዬ"

"አንቺ በእውነት ገዛሽ!" አሉ ካሳ::[16]

* * *

የማይካደው ነገር፣ እንደ ትዳር ዐይነት አያዎ ያለ አይመስልም:: ግራ አጋቢ ነው፤ ደስታና ሥቃይ፣ ተስፋና የተዘጋ በር ተጋምደው ያሉበት ዓለም ነው:: እሳት ከውሃ ጋር ተቃቅፎና ተደጋግፎ የሚኖርበት ግዛት!

ሐሳቦቹ እዚህ ጋ የተስማሙ መሰሉና ወደ አፎታቸው ተከተቱ፡፡ አሳዳሪያቸው ጭንቅላት ምን ይውጠው ይሆን?

ማስታወሻ

1. ተስፋዬ ጎይሌ፤ ያልታተመ፡፡
2. ጸጋዬ ገ/መድህን፤ *እሳት ወይ አበባ* (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም) ገጽ 196፡፡
3. Barack Obama, *The Audacity of Hope* (New York: Three Rivers Press, 2006), 333.
4. Philip Yancey and Dr. Paul Brand, *The Gift of Pain* (Michigan: Zondervan, 1997), 276.
5. Obama, *Audacity*, 326-7.
6. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 327፡፡
7. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 340፡፡
8. *አዲስ ነገር ጋዜጣ*፣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 057፣ ኅዳር 13 2001 ዓ.ም፡፡
9. ዳዊት ጸጋዬ፤ *አርነት የወጡ ሐሳቦች* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም) ገጽ 28፡፡
10. Obama, *Audacity*, 340-1.
11. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 340፡፡
12. Clayborne Carson, *The Autobiography of Martin Luther King, Jr.* (London: Abacus, 2008), 37.
13. ተክለጻድቅ መኩሪያ፤ *ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት* (አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1981 ዓ.ም) ገጽ 77፡፡
14. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 79፡፡
15. ዳንኤል ተፈራ ጀ.፤ *ዳንዲ የነጋሶ መንገድ* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም) ገጽ 326፡፡
16. *ጠይም መጽሔት*፣ 1ኛ ዓመት ቁጥር 7 (ነሐሴ 2000 ዓ.ም) ገጽ 17፡፡



# ያልተጻፉ ጥቅሶች

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተቈጥረው በተለያዩ ሰዎች የሚጠቀሱ "ያልተጻፉ ጥቅሶች" በየጊዜው ያጋጥሙኛል፡፡ "ርዱኝ እረዳችኋለሁ" ዐይነቶቹን ማለቴ አይደለም፤ ሌሎችን ወደ ውጭ ከማየት በፊት ራሳችንን ወደ ውስጥ መመልከት ብናስቀድም እመርጣለሁና፡፡ በመሆኑም ይህኛው ትኩረቴ በእኛው መካከል፣ በተለይም በአገልጋዮቻችን የሚዘወተሩን ጥቂት "ጥቅሶች" ማሳየት ነው፡፡

"የማይሠራ አይብላ" ወይም "ያልሠራ አይብላ" የሚለውን መጀመሪያ ባነሣው ደስ ይለኛል፡፡ ይህ "ጥቅስ" በመድረኮቻችን ተደጋግሞ ሲነገር እሰማለሁ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን አላገኘሁትም፡፡ ምን ማለት ይሆን?

መሥራት ያልቻለ ሰው መብላት የለበትም? ሕፃናት መብላት የለባቸውም? አረጋውያንስ? ዐቅመ ደካሞችስ ምን ይሁኑ? "ጥቅሱ" ለማንም ዕድል አይሰጥም፡፡ "ሥራ አጥ" ወይስ "ሥራ ፈላጊ" የሚለው ክርክር ውስጥ ለጊዜው ባልገባም፣ እነርሱም መብላት የለባቸውም እንደ ማለት ነው፡፡ አካል ጉዳተኞችም እኩል ዕድል ከተሰጣቸው መሥራት እንደሚችሉ አምናለሁ፡፡ የእነርሱም ጥያቄ ይኸው ነው፤ እኩል ዕድል፡፡ ነገር ግን መሥራት እንዲችሉ ማመቻቸት ቀርቶ፣ በራሳቸው ተፍጨርጭረው እንዳይሠሩ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ መተላለፊያው እየተዘጋባቸው ይታያል፡፡ ታዲያ መብላት የለባቸውም ማለት ነው? ለመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ጭፍን ነውን?!

"ያልሠራ አይብላ" የሚለው የኮሚኒስቶች እንጂ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም! ከጥቍር አንበሳ ሆስፒታል ጀርባ "የኢትዮ ኩባ ወዳጅነት መታሰቢያ" ሀውልት ይገኛል፡፡ እዚያ መታሰቢያ ዘንድም የኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያምን ጨምሮ የ66ቱ አብዮት ቋሚ ማስታወሻ የሆኑ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ማየት ይቻላል፡፡ በጊዜው ይደረጉ ስለ ነበሩት ሰላማዊ ሰልፎችና የዚያን ጊዜ መፈክሮች ማጥናት ከተፈለገም ተመራጭ ቦታ ነው፡፡ ከመፈክሮቹም መካከል "ያልሠራ አይብላ" የሚለው አንዱ እንደ ነበር እዚያ አይቻለሁ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ነው የሚለው (2ተሰ. 3፥10)፡፡ "ሊሠራ የማይወድ" እና "ያልሠራ (የማይሠራ)" በጣም ይለያያሉ፡፡ "ሊሠራ የማይወድ ... አይብላ" የሚለው ሐረግ መሥራት ካለመፈለግ ጋር ብቻ ነው በቀጥታ የሚያያዘው፤ ትኩረቱ ሥራ ለመሥራት የመፈለግ ወይም ያለ

መፈለግ ነው:: ጥያቄው የልብ ነው:: መሥራት እየወደዱ መሥራት ያልቻሉ፣ ለመሥራት ዕድል ያላገኙ ሰዎችን አይመለከትም::

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መምከር ያስፈለገው መሥራት ላቃታቸው ሰዎች አይደለም:: የተሰሎንቄ ሰዎች፣ "ጌታ ዳግመኛ ከመጣ፣ ሥራ ምን ያደርግልናል?" በማለት ሥራ ያቆሙና ራሳቸውን ያሰነፉ ሰዎች ነበሩ:: ሥራ መፍታታቸው ደግሞ ወረኛና በሰው ጉዳይ የሚገቡ አድርጓቸው ነበር:: እነዚህ ሰዎች መሥራት እየቻሉ፣ ላለመሥራት የወሰኑ ሰዎች ናቸው:: ቅዱስ ጳውሎስ፣ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" በማለት ያዘዘው እነርሱን ነው!

ስለዚህ መሥራት የማይችሉትን ወይም እየፈለጉ ያቃታቸውን ወገኖች ከመብል የምንከለክልበት ምንም ዐይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አይኖረንም:: እንዲያውም እንደዚህ ዐይነት ሰዎችን መሰብሰብ፣ ማብላትና መርዳት አንዱ የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ነው:: መሥራት እየቻለ መሥራት የማይወድ ሰው ከመብል ቢከለከል ግን ስሕተት አይሆንም::

"ሰዎች ሊያደርጉባችሁ የማትወዱትን ሁሉ እናንተም አታድርጉባቸው" የሚልም "ጥቅስ" ሰምቻለሁ:: ይህ ጥቅስ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ይገኛልን? ምንስ ማለት ነው? በእርግጥ፣ እኛ ላይ እንዲደረግብን የማንፈልገውን ክፉ ነገር ሌሎች ላይ ላለመፈጸም መጠንቀቅ አለብን:: ለምሳሌ፣ ሰዎች ሲሰድቡን ደስ አይለንም፤ ስለዚህ መሳደብ አይኖርብንም:: የእኛ የሆነውን ነገር እንዲወስዱብንም አንፈልግምና እኛም የሌሎችን ንብረት መውሰድ የለብንም:: ሲመቱን፣ ሲጨቀጭቁን፣ ሲያሙን፣ ክብራችንን ሲነኩብን፣ መንገድ ሲዘጉብን ... ስለማንወድ፣ እኛም በተራችን በሌሎች ላይ እነዚህን እንዳንፈጽም ልንጠነቀቅ ግድ ነው::

ሰዎች ሁሉ በዚህ ወርቃማ ትእዛዝ መተዳደር ቢችሉ ሕይወት ምንኛ ባማረች! በእርግጥ ይህ ጥሩ ምክር ነው፤ ምሉዕ ግን አይደለም:: ክፉ አለማድረግ ብቻውን በቂ አይሆንም፤ መልካም በማድረግ መታገዝ አለበት:: ሲደረግብን የማንወደውን ነገር በሌሎች ላይ አለማድረግ መልካም ቢሆንም፣ ሲያደርጉልን የምንወደውን ነገር ለሌሎች ማድረግ ካላከልንበት ጐዶሎ ይሆናል:: ሰዎች እንዲያደርጉብን የማንወደውን ነገር አለማድረግ መልካም በማድረግ ካልታገዘ ወደ መኻል ሰፋሪነት (neutrality) ብቻ ነው የሚያመጣን፤ ክፉም መልካም ሳይሆኑ እንዲሁ መኻል ላይ ተንሳፍፎ መቅረት ነው:: ትኩስም ሆነ በራድ ባልሆነ ለብታ ልንመስለውም እንችላለን:: ይህ ምንባብ ግን ስለዚህ ጉዳይ ምንም አይናገርም፤ የጐዶሎነቱ መነሻም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አለመገኘቱ ነው::



ትክክለኛው የጌታ ኢየሱስ ንግግር እንዲህ የሚል ነው፤ "እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" (ማቴ. 7፥12፤ ሉቃ. 6፥31)::

ይህ ክፍል ክፉ አለማድረግን ብቻ ሳይሆን፣ መልካም ማድረግንም ይጨምራል:: ሌሎች እንዲያደርጉብን የማንፈልገውን ባለማድረግ ሳንወሰን፣ እንዲደረግልን የምንፈልገውን ለሌሎች ማድረግንም ያስተምረናል:: ክፉ አለማድረግ መልካም ማድረግን አይጨምርም፤ መልካም ማድረግ ግን ክፉ አለማድረግንም ያቅፋል:: ስለዚህ እኛም ክፉ ባለማድረግ ሳንወሰን፣ መልካም ማድረግንም ማከል ይጠበቅብናል::

በዚህ ትክክለኛ ጥቅስ መሠረት ከሆነ ባለመሳደብ ሳንገደብ፣ እንመርቃለን:: ሰዎችን ባለመጥላት ብቻ አንወሰንም፤ መውደድንም እናክልበታለን:: ውሸት አለመናገር ብቻ አይበቃምና እውነትን እንናገራለን:: የሰዎችን ንብረት አለመንካት ብቻ ሳይሆን፣ የራሳችንንም ለሌሎች እንሰጣለን:: የተሟላው የጌታ ኢየሱስ ትምህርት ይህ ነው::

"ሩጫዬን ጨርሻለሁ" የሚል ጥቅስም በየመቃብር ስፍራው ተጽፎ እመለከታለሁ፤ አንዳንዴማ በሕፃናትና ወጣቶች መቃብር ላይም ተጽፎ ይታያል:: ሩጫውን ገና የጀመረና ለመጀመር እየተንደረደረ ያለ ሁሉ እንደ ጨረሰ መታሰቡ አስቂኝ ነው:: ከዚህ የሚከፋው ግን፣ "ጳውሎስ 'ሩጫዬን ጨርሻለሁ' ብሏል" እየተባልን የምንሰበከው ነው:: እውነቱ ግን፣ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አለማለቱ ነው:: ለመሆኑስ ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ጉዳይ ሲያሯሩጥ ነበር እንዴ የኖረው? ታዲያ እንዴት 'ሩጫዬን' ይላል?

ይህን የጻፈው እግዚአብሔር የሰጠውን ጥሪና ፈለግ ተከትሎ ለ30 ዓመት ከሮጠ በኋላ መሆኑ፣ አንድን የታወቀ ሩጫ መሮጡን ያሳያል:: ስለዚህ ለእምነት ልጁ ለጢሞቴዎስ፣ "ሩጫውን (the race) ጨርሻለሁ" ብሎ ጻፈለት (2ጢሞ. 4፥7)::

ሩጫው ማንኛውም ሩጫ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር የተወሰነና "መንገዱን (the Way)" የተከተለ ሩጫ ነው:: ይልቁኑ በአገልግሎት ስም የራሳቸውን ክብር፣ ስምና ቤት ሲገነቡና ለጥቅማቸው ብቻ ሲሯሩጡ የምናያቸው የእኛው ጉዶች "ሩጫዬን ጨርሻለሁ" ቢሉ ያስኬዳል:: ያ የእግዚአብሔር ሰው ግን የሮጠው የራሱን ሩጫ ባለመሆኑ፣ "ሩጫውን ጨርሻለሁ" ካለ በኋላ "... የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል:: ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል" በማለት ተናግሯል:: እኛስ?

"ሙሴ አፈ ትብ ሰው ነበር ወይስ አፈ ትብ ሰው አልነበረም?" ብዬ የተለያዩ ሰዎችን ስጠይቅ፣ አፈ ትብ ሰው እንደ ነበር አስረግጠው ይነግሩኛል:: ምን ያድርጉ? እንዲህ እየተባለ በተደጋጋሚ ሲሰበክ እኔም ሰምቻለሁ:: የስሕተቱ መነሻ "ትብ" ማለት ከቃሉ ተቀራራቢነት የተነሣ "ተብታባ" የሚል ትርጓሜ እንዳለው መቈጠሩ ነው:: ስለዚህ፣ "ሙሴ አፈ ትብ ሰው ነበር" የሚል ያልተጻፈ ጥቅስ ያነብባሉ::

ሆኖም "ትብ" የሚለው ቃል የተገኘው ተባ ከሚለው ግስ ሲሆን፣ ትርጓሜውም "ሰላ፤ ተሞረደ፣ ቀለጠፈ (ለንግግር)" ማለት ነው፤ "የተባ ብዕር" እንደሚባለው::[1] መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚነግረን ሙሴ፣ "ጌታ ሆይ፤ አፌ ኮልታፋ፣ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ፤ ... አፈ ትብ ሰው አይደለሁም" በማለት ነበር የተናገረው (ዘፀ. 4፥10):: "አፈ ትብ አይደለሁም" አለ እንጂ "ነኝ" አላለም:: የዚህ ቃል ትርጓሜ አሳሳቢ ላይሆን ይችላል፤ ማስተካከሉ ግን ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም::

በየዐውደ ምሕረቱ የምንሰማው "የናዝሬቱ ጌታ" የሚል አጠራርም ግራ ያጋባኛል:: ምን ማለት ነው? ጌታ ኢየሱስ ናዝራዊ መሆኑን ለማሳየት "የናዝሬቱ ኢየሱስ" መባሉ ትክክል ነው (ማቴ. 2፥23፤ ማር. 14፥67፤ 16፥6፤ ዮሐ. 1፥46)፤ "የናዝሬቱ ጌታ" ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: አዎን፤ ጌታ ኢየሱስ የናዝሬትም ጌታ ነው፤ የናዝሬት ጌታ ብቻ ግን አይደለም፤ የዓለም ሁሉ እንጂ! ስለዚህ ጌታ ኢየሱስን፣ "የናዝሬቱ ጌታ" ብሎ መጥራት የአንድን አገር ፕሬዚዳንት፣ የአንድ ቀበሌ ሊቀ መንበር አድርጎ ከመጥራትም እጅግ እጅግ የከፋ ነው:: ይስተካከል::

ማስታወሻ

1. *አማርኛ መዝገበ ቃላት* (አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር፣ 1993 ዓ.ም)::



# ቄስ አብደላ

ከርቀት ሳውቃቸው ጥቂት ጊዜአት አስቈጥሬአለሁ፤ ከእስልምና ወደ ጌታ እንዴት እንደ መጡ ዝርዝር ታሪካቸውን ግን ትናንትና በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሲመሰክሩ ነው የሰማሁት። በምማርበት የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት ለምወስደው "እስልምና እና ክርስትና" ለተሰኘው ኮርስ የምሠራውን ጥናታዊ ወረቀት ሳስብ የመጀመሪያው ምርጫዬ ሆነው ተገኙ። ጥናቱ፣ ከእስልምና ወደ ክርስቶስ የሚመጡ ሰዎች በሚገጥማቸው ተግዳሮት ላይ ያጠነጥናል። ያዘጋጀኋቸውን ጥያቄዎች ትናንት ስሰጣቸው፣ ምላሻቸውን ዛሬ እንደ ማገኝ ስለ ነገሩኝ መቅረጸ ድምፄን ይዤ ወደ ቤታቸው ማዝገም ጀመርኩ።

በሩን ለመቀብቀብ ገና ነካ ሳደርገው አልተዘጋ ኖሮ ተንሻቶ ሳላስበው ገባሁ። ቄስ አብደላ ፊት ለፊቴ ይታዩኛል። ከመኻል አናታቸው የሚጀምረው ጠጉራቸው ነው ቅድሚያ የታየኝ ("ፊታቸውን ሲታጠቡ ከየት ነው የሚጀምሩት?" የሚል ጥያቄ ወደ ሓሳቤ ብቅ አለና ቶሎ ሄደ)። የግንባራቸው መሥመር ብዙ የሕይወት ሐዲዶችን ያሳያል። ቍራጭ ሥጋ ላይ የተከመረ የጉንዳን ሠራዊት የሚመስል ጢም አገጫቸውን ወርሮታል። ቤት ቤት የሚያዘወትሩት በረዶ የመሰለ ጀለቢያ ጥቍረታቸውን የበለጠ አንጸባራቂ አድርጎታል ("እኔ መቼም ለእ'ሳቸው ሕንድ ነኝ" አልኩ በሆዴ)። ፈገግ ሲሉ ግን ፊታቸው ላይ ጀምበር ትወጣለች። ጥርሳቸው!

ቄስ አብደላ የወንጌል አርበኛ ናቸው። ስማቸውን መቀየር ያልፈለጉት፣ "ስሜም ወንጌል ይስበክ" በማለት መሆኑን ትናንት ተናግረዋል። የትናንቱ ምስክርነታቸው ሌሊቱን ቁጭ አድርጎ አሳድሮኛል። ለወንጌል የከፈሉትን ዋጋ ማወቁም በአክብሮትና በስስት እንድመለከታቸው አስገድዶኛል።

"ደኅና አድረዋል ቄስ?" አልኳቸው እጅን በአክብሮት እየዘረጋሁ፤ "ቄስ" እና "አብደላ" የሚሉት ቃላት ጥምረት ለጆሮዬም ለአፌም አልገጥም ስላለኝ በሙሉ ስማቸው ልጠራቸው አልፈለግሁም።

"አህለን ወሳህለን" እያሉ የዘረጋሁላቸውን እጅ ስመው፣ የእርሳቸውንም ወደ አፌ አስጠጉልኝ፤ እንደ ትናንቱ አልደነገጥኩም። የሚያጎርሱኝ ነው የመሰለኝ። "እንኳን ደኅና ቈዩኝ" ብዬ መለስኩ፣ "እንኳን ደኅና መጣህ" ማለታቸው ስለ ገባኝ። ትናንትና ወደ ምስባኩ እንደ ወጡ፣ "አሰላም አሌይኩም" በማለታቸው፣ አጠገቤ የተቀመጡ ምዕመናን በሙሉ፣ "በኢየሱስ ስም!" እያሉ መገሠጻቸው ትዝ ሲለኝ ሽራፊ ሣቅ አመለጠኝ። አዲስ አበባ የገቡት በቅርቡ ሆኖ እንጂ ቀስ በቀስ ይተዉታል ብዬ ተስፋ አሳደርኩ።

ጨዋታ የሚያምርላቸው ከመሆኑ ባሻገር ትናንትና ቤተ ክርስቲያን
ደጅ ላይ እንደ ቀልድ የጀመርነው ወግም ጉጉት አሳድሮብኛል፤ ለዛሬ በይደር
ያቈየነው ለዚህ ነበር። ስለዚህ ገና የቤታቸውን ደረጃ እየወጣን እንኳ ጨዋታ
ችንን በቶሎ እንድንጀምር ልቤ መመኘት ጀምሯል።

አረቢያን መጅሊስ ተብሎ የሚታወቀው እግር አልባ ሶፋ ከብዙ መከዳ
ዎች ጋር የቤታቸውን አንድ ጥግ ይዞ ለማረፍ ያጓጓል። "ቤታቸው ጫት
ይቃማል እንዴ?" እያልኩ በግርታ ሳስብ፣ "ቁጭ በል" ሲሉ በእጃቸው ጋበ
ዙኝ፤ እጃቸውን የሸፈነው ጠጕር ዝግመተ ለውጥን ያስታውሳል። የዐረቢያን
መጅሊሱን ምቾት ብመኘውም፣ አጠገቤ የነበረው ባለ ሦስት እግር በርጩማ
ላይ ቶሎ ቁጢጥ አልኩ። ትንሽዬ ለስላሳ ቁርበት ጣል ስለ ተደረገበት አይ
ቆረቁርም።

* * *

"አዎን፤ ያኔ ክርስቶስን ለመከተል እንደ ወሰኑ ቤተ ክርስቲያን የገጠሞ
ትን ችግር እንዲነግሩኝ ነው የፈለግሁት። ትናንትም ነካክተውት ነበር" አልኳ
ቸው የመቅረጸ ድምፄን ቊልፍ እየተጫንኩ።

"አዎን ልክ ነህ፤ ነግረኸኛል። ይኸውልህ፤ የጌታን አዳኝነት እንዳመ
ንኩ ውሎዬ በአቅራቢያችን በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ሆነ። እንደምታው
ቀው መኖሪያ ከተማችንና በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች በአብዛኛው የእስልምና
ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። እስከ ዛሬ ከዘመዶቼ አንዳንዶቹ መጽሐፍ ቅዱሳ
ዊውን የክርስቶስ ማንነት አልተረዱትምና አሁንም ትግል ላይ ነኝ። እዚያ የም
ታገኘውን የትኛውንም ሰው ሙስሊም አድርገህ ብትገምት አትሳሳትም። በአካ
ባቢያችን ያለችው ቤተ ክርስቲያን ግን ይህንን ግምት ውስጥ ያስገባች አልመሰ
ለኝም። አሁን አሁን ሲገባኝ ቤተ ክርስቲያኒቱ የተመሠረተችው ከመኻል አገር
የሚመጡ ሰዎችን ብቻ ታሳቢ አድርጋ እንጂ የአካባቢውን ነዋሪ ለመድረስ አል
ነበረም። የተልእኮ ውስንነት ነበረባቸው።" ሲናገሩ ዐልፎ ዐልፎ ግራ ትከሻቸ
ውን ይሰብቃሉ።

"እንዴት ይህን ሊሉ ቻሉ?"

"ይኸውልህ። ኋላ እንደ ገባኝ ከሆነ ክርስቲያኖቹ እንደ ወንጌል ጠላት
ብቻ እንጂ የክርስቶስ ወንጌል እንደሚያስፈልገን ኀጢአተኞች አልነበረም የሚ
ቈጥሩን። ደፍሮ የምሥራቹን የሚነግረንና የክርስቶስን ፍቅር የሚመሰክርልን
አልነበረም። ጓደኝነታችንን አይፈልጉትም፤ ቤታችንም ድርሽ አይሉም። ወን
ጌል እንደሚያሸንፈን አይታሰብም ነበር ይመስለኛል። አሁንም ድረስ የእኔዎቹ
ዘመዶች ሻይ ሊጠጡ መቀመጣቸውን ማየት ሻይ ቤቱን ጥለው እንዲወጡ
የሚያደርጋቸው ክርስቲያኖች አሉ።



"ያኔም እዚያ የማያቸው ብዙ አሠራሮች እግዚአብሔር ራሱ በድንቅ
አጠራሩ ጠርቷቸው ከእስልምና ለሚመጡ ሰዎች የማይመቹ ነበሩ፤ ወይም
ለእኛ ሲባል እንኳ አንዳንድ ነገሮችን ዐውዳዊ ለማድረግ ጥረት እንዳልተደረገ
ያስታውቃል። በጁምዐ (ዐርብ) ዕለት ቀትር ላይ ቋሚ ፕሮግራም እንዲኖር
ብዙ ጥረት አድርጌ ነበር፤ አልተሳካልኝም። ከአካባቢው የመጀመሪያ አማኝ
ስለ ነበርኩ በአርአያነት ጒልበት የሚሆነኝ ቀዳሚ አማኝ አልነበረም። ወደ ኋላ
ለማለት ብዙ ተፈትኛለሁ።

"'እንዴት ደፈርከ?' ባትለኝ፣ ብዙው ነገር መልክና ሥርዐት እንዲኖ
ረው ብዙ ጊዜ ሓሳብ እሰጥ ነበር። ሁሉም ግን የበፊቱ ነገር እንዳልለቀቀኝና
እዚህ የምንኖረው በጸጋ እንጂ በሕግ እንዳልሆነ ነው የሚነግሩኝ። ጸጋ የሥር
ዐት ጠላት እንዲመስለኝ ነበር ያደረጉኝ። እነርሱም እንዳልገባቸው አሁን ገብ
ቶኛል፤ በጸጋ የዳነ ሕዝብ ሥርዐት ቢኖረው ተገቢ ነውና! የጌታ ጸጋ ለሰው
የማይቻለውን የማስቻሉ ልቀት አይደለም እንዴ የክርስትናስ አንዱ መገለጫ?"

"እስቲ ወደ ኋላ መለስ ይበሉና የገጠምዎትን ችግር ከመነሻው ያጫው
ቱኝ" አልኳቸው ("ነገርን ከሥሩ፣ ውሃን ከጥሩ" አይደል ተረታችንስ?)።

"ማለቂያ አለው ብለህ ነው? ለመሆኑ ጊዜ አለህ?" አሉኝ መጅሊሱ ላይ
አቀማመጣቸውን እያመቻቹ፤ እግሮቻቸውን አጠላልፈው ነው የተቀመጡት።

"አዎን፤ ቤትም ብሄድ ቴሌቭዥን ላይ ነው የማፈጠው" አልኳቸው
(ሰዓቴን መልከት ሳደርግ፣ ቢቢሲ ዜና ሊጀምር ሲል የሚያሰማውን የመግቢያ
ሙዚቃ የሰማሁ መሰለኝ። ወይ ፈተና!)።

"ይኸውልህ የመጀመሪያው ቀን ልክ ቤተ ክርስቲያን ስገባ መኪናዬ
ውስጥ የቀየርኳትን ነጠላ ጫማ ደጅ ላይ ጣል አድርጌአት ነበር። ታዲያ እዚያ
ስገባልህ ምዕመናኑ ሁሉ ጫማቸውን እንዳጠለቁ ነው፤ ማመን አቃተኝ። ሰው
ዱአ ወደሚያደርግበት (ወደ አምላኩ የሚጸልይበት) ቤት ከነጫማው ይገባል?
የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ወደ መቅደስ ሲገቡ ጫማ እንደሚያ
ወልቁ ዐውቅ ነበር። እናም ብዙ የምንመሳሰልበት ነገር እንደሚኖር ነበር
ግምቴ። እንዴ፣ ስንት የክርስትና ቡድን ነው ያለው? ታዲያ ትክክለኛው ቡድን
ውስጥ መሆኔን እንዴት ነው የማውቀው? ከነጫማቸው መሆናቸውን ሳይ
ጠላትህ ክው ይበል፤ ክው አልኩኝ። እነርሱ ግን ድንጋጤዬ አልገባቸውም።
ጭራሹኑ ባዶ እግሬን በመሆኔ በኀዘኔታና በግርታ ሲመለከቱኝ ባይተዋርነት
ስለ ተሰማኝ ትቼ መውጣት አማረኝ።

"ምን ይሄ ብቻ! ወንዱና ሴቱ በአንድ በር ገብተው ተቀላቅለው ነው
የሚቀመጡት። ሌላ ክፍል ባይኖር እንኳ ወንዶቹ ፊት ተቀምጠው ሴቶቹ

ከኋላ ቢሆኑ ምን ነበረበት? ወይም እንደ ብዛታቸው በአንድ አቅጣጫ ያለውን ረድፍ ለወንዶቹ ሰጥተው፣ ሌላውን ለሴቶቹ ሊተዉላቸውስ አይችሉም ነበር? ሴቶቹ መኻል ላለመቀመጥ ስሸሽ፣ ፊት ለፊቴ የተቀመጡት እነርሱ ይሆናሉ:: እንዴት አድርጌ መኻላቸው ልቀመጥ? ያለ ልማዴ!? መቀመጫ በሞላበት መቀመጫ አጣሁ! ያኔ ለእኔ ግድ የሚሰጠው ሰው እንዳልነበር ገባኝ!

"በዚህ ላይ አለባበሳቸው! እንዲህ መገላለጥ ምን ያስፈልጋል? ክርስትና የአለባበስ መርሕ የለውም እንዴ? እግዚአብሔር ቤት ነው ያለሁት ብዬ መቀበል አጅግ ከብዶኝ ነበር:: የሚሰበከውን አድቤ ልስማ ወይስ ...? ድንጋጤው በዚህ ብቻ ቢያበቃልኝማ እንዴት ጥሩ ነበር! ይኸውልህ በእኛ ልማድ ጁምዐ ሲደርስ ወደ መስጅድ ለመሄድ ንጹሕ ሆነን፣ ንጹሕ እንለብሳለን:: ነጭ ልብስ ካለ ይመረጣል:: እዚያ ግን አጠገቤ የተቀመጠች ሴት ቅቤዋ በጆሮ ግንዷ ይወርዳል:: በዚያ ሙቀት ቅቤ! ማዶ ያሉት ወንዶች ደግሞ ጫማቸውን ሳያስቦርሹ ነው የገቡት:: የአንዱማ የጫማው አቧራ ከለበሰው ባለ ክሬም ቀለም ሹራብ ጋር ጥሩ መጣጣም ፈጥሯል:: የጫማ ነገር ከተነሣ፣ መስጅድ ውስጥ ያለውን ምንጣፍ፣ ተለብሶ ጫማ ውስጥ በዋለ ካልሲ መርገጥ እንኳ ጸያፍ ነው:: የሚያውክ የብብት ጠረን፣ የአፍ ሽታ የሌሎችን ሰላም እስካወከ ድረስ ተገቢ አይደለም:: ፕሮግራም መሪው ያልተተኮሰ ሸሚዝ ነው የለበሰው:: የመሥሪያ ቤት አለቃ ፊት እንኳ እንዲህ አይቀረብም እኮ! በግዴለሽነት አምላኩን ለመገናኘት የሚመጣ አማኝ፣ ከክርስቲያን በቀር ይኖር ይሆን? እምነትህ የምድራዊ ኑሮህም መርሕ ሊሆን ግድ ይመስለኛል::

"ዐይኖቼን ማስቀመጫ አጥቼ ግራ ቀኝ እያንከራተትኩ ሰበካው ላይ ላተኩር ሞከርኩ:: ጥሞና ግና እዚያ የለችም፤ እስካሁንም ብዙ አላገኘኋትም:: ሰባኪው በየት በኩል ፋታ ይስጠን? 'አጠገባችሁ ያለውን ሰው እንዲህ በሉት' ሲል፣ 'ጎናችሁ የተቀመጠውን ሰው ገፋ አድርጉት፣ ፊት ለፊት እያያችሁ እንዲያ በሉት' ሲል፣ እንዴት ቀልብህን መሰብሰብ ትችላለህ? ደግሞ የሰዉ አለማፈር! አጠገቤ ያለችው ደረቷን ገልጣ ጡቷን ያሰጣች ሴት፣ ነካ ታደርገኝና የሚባለውን ትለኛለች:: እንዴ ሰባኪውን በቀጥታ የምሰማበት የራሴ ጆሮ ያኔም ነበረኝ፤ አሁንም አለኝ:: ታዲያ የእርስዋ የገደል ማሚቶነት ምን ይረባኛል? እውነተኛውን አምላክ ፍለጋ ሄጄ በሴት ስጎሻሸም ውዬ ልምጣ? አጀብ ነው!

"ስብከቱ ደግሞ ስለ ስኬት፣ ማለቴ ስለ ገንዘብ፣ ስለ ውድ ልብሶችና መኪኖች እንደ ነበር እስካሁን አልረሳሁትም:: ለዚህ ለዚህ እኮ ቤተ ክርስቲያን መምጣት አልነበረብኝም:: መኪናውን በር ላይ አቁሞ ለገባ ለእንደ እኔ ዐይነቱ ሰው ትርጉም የማይሰጥ ስብከት ነበር:: 'አሜሪካኒዝም' እና ክርስትና ተምታቱብኝ:: በረከት በሰባኪው አገላለጽ ከተለካ እኔ እኮ ገና ድሮ ተባርኬአ



ለሁ:: እንዲያውም ወደ ጌታ ከመጣሁ በኋላ ነው መከራ የቀመስኩት:: ሆኖም ብዙ በረከት አግኝቻለሁ:: የናፈቅሁት ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነገረውን መስማት ነበር::

"መጽሐፍ ቅዱስን ሊሰብክ የተጠራ ሰው የመጽሐፉን መልእክት እንዳሻው እንዳያደርግ መርሕ የለም ወይ? ደግሞስ ቃሉ የሚለውን ከማለት ውጭ ለምን መደጋገም አስፈለገ? በገለጻ ጋጋታ ሰዉ የመልእክት ግተት እንዲሸከም ለምን ይደረጋል? በምርጥና ምጥን መልእክቶች አቀራረብ፣ እንደ ውሃ የሚጠሙኝ በስምም በመልእክትም የማውቃቸው ሌሎች ሰባኪዎችም ግን አሉ::"

* * *

ሲያወሩ እንደ ብዙ ሰባኪዎች አይወራጩም፤ በእርጋታ ነው:: ትናንትም እንዲህ ነበሩ:: "እውነተኛ ሙዕሚን (አማኝ) ሃያዕ (ርጋታ) ከሌለው የመልእክቱን ክብደት ያሳንሳል" ያሉት ይህን ነበር ማለት ነው? ሌሎች ሰዎቻቸውንም በሐሳብ ለማየት ሞከርኩ፤ አብዛኞቹ እንዲህ መሆናቸው ገባኝ:: እኔ ሳወራ ግን በስሜት እጄን ስለማወራጭ ሳላስበውና ሳያስቡት ቡጢ እንዳላቀምሳቸው አድማጮቼ በመካከላችን በቂ ርቀት መፍጠር አለባቸው፤ "Safety first!"

* * *

"በሌላ ቀን 'የጸሎት ፕሮግራም ተካፈል' አሉኝና ሄድኩልህ:: የሴቶቹ ጉዳይ ማለቂያ የለውም፤ ሴት ነበረች ፕሮግራሙን የምትመራው:: የወንዶቹን ጉባኤ እንዴት ነው ሴት የምትመራው? ሲያስፈልግ የሴቶቹን ጸሎት ሴቷ ትምራ እንጂ የወንዶቹን በምን ታሪክ? 'አይደረግም!' አልኩና ወጣሁ::

"እኔ የለመድኩት በቀን አምስቴ መጸለይ ነበር:: እዚህ ግን መደበኛ የጸሎት ሰዓት የሚባል ነገር አለመኖሩ ግር ብሎኝ ነበር:: ዳንኤል በቀን ሦስት ጊዜ ይጸልይ ነበር (ዳን. 6፥10)፤ መዝሙረኛውም በቀን ሰባቴ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር (መዝ. 119፥164):: እና እኔ በለመድኩት መንገድ በቀን አምስቴ መጸለይ ብፈልግ ምን ችግር አለው? ሰዎች በፈለጉት ሰዓት ሁሉ መጸለያቸው ክፋት ባይኖረውም፣ አምስቱን የጸሎት ሰዓቶች ቢያከብሩ ምን ችግር ነበረው? ሰዓት እየጠበቅሁ፣ 'ኧረ የጸሎት ሰዓት ደረሰ!' ስል ይሥቃሉ፤ 'ይሄ አሁንም አልለቀቀውም' ይሉኛል:: ምኑ ነበር ያልለቀቀኝ?

"የሰዓት ነገር ከተነሣ የጥምቀት ትምህርት የሚያስተምረኝ ሰው እንኳ እየቀጠረኝ ሲቀርና ብዙ ሰዓት ጎልቶኝ ሲውል ይቅርታ አይጠይቀኝም ነበር:: ተቃውሞ ሳቀርብ 'ረጋ በል'፣ 'መታዘዝን ተማር' ነበር የሚለኝ (ልጃቸው ቀጠሮ ኖሯት ስትጣደፍ፣ 'ኧረ አባክሽ! ቀኑ አይለፍ እንጂ፣ ለሰዓቱ አትጨነቂ' የሚሉት እናት ታወሱኝ):: እንደዚህና እንደዚያ ሲሉኝ፣ ስለ አምላኬ ውስጤ

የሚንተከተከው ግለት በረደ፡፡ ግለቴ ሳይበርድ ትክክለኛውን አቅጣጫ ብቻ ቢያሲይዙኝ ምን ነበረበት!?" አሉኝና ቀና ብለው አዩኝ፡፡

እኔም አየኋቸው፡፡

"ስለ ጸሎት ማውራት ጀምሬ ነበረ አይደል?"

ራሴን በአዎንታ ነቀነቅኩ፡፡

"ከዚያ እሑድ እሑድ ብቻ ስካፈል ቈየሁና በሌላ ቀን ራሴን አበረታትቼ ወደ ጸሎት ጉባኤው ተመለስኩ፡፡ የዚያን ቀን ሴቶች ቢበዙም እግዚአብሔር ሲረዳኝ ጸሎቱን ወንድ ነበር የሚመራው፡፡ ከሴቶቹ መብዛት የተነሣ የኢሲሜግ (የሴቶች) ስብሰባ የምካፈል ነው የመሰለኝ፡፡ ደ'ሞ ለጸሎት እንኳ ጠጕር አይሸፈንም? መጽሐፉ፣ ያገቡ ሴቶች ሲጸልዩ ጠጕራቸውን እንዲሸፍኑ እንደሚጠይቅ ኋላ ዐውቄአለሁ (1ቆሮ. 11፥5፣ 6፣ 13)፡፡

"ጸሎቱ በመንበርከክ ነው የሚካሄደው፡፡ በተሰጠው ርእስ ላይ እንዳሻህ ትጸልያለህ፡፡ በጋራ ሲጸለይ የሰማሁት፣ 'የሐዋርያት ጸሎት' የተባለውን ነው፤ መጨረሻ ላይ፡፡ ጸሎቱ ረዝሞብኝ ተቸገርኩ፡፡ በዚህ ላይ ጩኸታቸው! በእርጋታ መጸለይ አይቻልም? ሲዘምሩ ጮኸው! ሲሰብኩ ጮኸው! ሲጸልዩ ጮኸው! ሲገሥጹ ጮኸው! ጸሎታቸውን በጩኸታቸው እየገፉ ሰማይ ሲያደርሱት የሚፈልጉ ነው የሚመስሉት፡፡

"ሲሰለቸኝ ብድግ ብዬ ፊቴን ሳዞር፣ ሴቶቹን ከኋላቸው አያለሁ፡፡ ተቀላቅሎ የመጸለዩ ችግር ጣራ የሚነካው እዚህ ላይ ነው፡፡ በየአቅጣጫው ሴቶቹ ጀርባቸውን ሰጥተው በየወንበሩ ተንበርክከዋል፡፡ አንዳንዶቹ በተመስጦ እየዘመሩና እየጸለዩ ይወዛወዛሉ፡፡ እነርሱን ማየቱ ንስሓዬን አረዘመብኝ፡፡ ዞር ብዬ ጥቂት አያቸውና ፊቴን መልሼ ንስሓ እገባለሁ፡፡ ከዚያ ለማረፍ ቁጭ እልና ወደ ንስሓዬ እመለሳለሁ፡፡

"ለመሆኑ፣ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ" (ገላ. 3፥28) ማለት፣ ወንድና ሴት ምንም ልዩነት የላቸውም ማለት ነው? 'ወንድ ሴትን በዚህ መንገድ በማየት ምንም ስሜት አይፈጠርበትም' እያለስ ይሆን? እንዴት?

"ለነገሩ ሴቶቹ ጥሩዎች ነበሩ፡፡ እስካሁንም ቤተ ሰብ ሆነውኝ የዘለቁ አሉ፤ ወደ ጌታ ስመጣ ያጣኋቸውን እኅቶቼን ተክተውልኛል፡፡ ያኔ ግን ጥበብ ጐድሏቸው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ በተደጋጋሚ ለጸሎት ስሄድና ትውውቃችን ሲጨምር፣ 'በጌታ ፍቅር እወድሃለሁ' ይሉኛል፡፡ እኔ ደግሞ አዲስ ክርስቲያን



ነኝ፤ ታዲያ ባገኙኝ ቍጥር እቅፍ ያደርጉኝና እንደሚወዱኝ ይነግሩኛል፡፡ አቤት ፈተናዬ! ሁሉም ያፈቀሩኝ መስሎኝ አሳሬን በላሁ፡፡ እነርሱ በእኅትነት ነው የወደዱኝ፤ 'በጌታ ፍቅር' የሚሉኝ ለካ ያንን ነበር፡፡ በጌታ ፍቅር! አንዲት ሴት የምታገባውንም ወንድ እኮ መጀመሪያ በዚህ መንገድ ልትወደው ግድ ነው፤ መግለጫውም የሚጀምረው ከዚህ ይመስለኛል፡፡ ለመሆኑ ከእስልምና የመጣን አዲስ አማኝ ሴቶች 'እንወድሃለን' እያሉ ሊያቅፉት ይገባል? 'በርታ፤ እኛም ከጎንህ ነን' ማለትን መልመድ ይገባቸዋል እንጂ! ጌታ ለሥራው ባይፈልገኝና በብዙ ጸጋ ባይረዳኝ ኖሮ እዚያ መኻል ብዙ ጥፋት አደርስ ነበር፡፡ መጨረሻዬም ጥፋት ነበር የሚሆነው፡፡ ደግ ጌታ አዘነልኝ እንጂ ...!

"ከዚያም በኋላ አንዳንድ የጸሎት ፕሮግራም ለመካፈል ስሄድ የሚያዩኝ ሰዎች አለባበሴንና የፊቴን ገጽታ ሲያዩ ድንገት እጃቸውን እናቴ ላይ ይጭኑና 'ውደቅ!' ብለው ይገሥጻሉ፡፡" አሉና ቄስ አብደላ በትዝታ ጭልጥ አሉ፤ ፊታቸው ላይ ኀዘን አረብቧል፡፡ የእርሳቸው መሄድ እኔንም በሐሳብ ወሰደኝ፡፡

* * *

የቄስ አብደላ ግራ መጋባት ወለል አለልኝ፡፡ ለእምነታቸው የከፈሉት ዋጋ ሳያንስ፣ የባህል ግጭቱ - ብቻ አሳዘኑኝ! ከአካባቢው አማኞች የመጀመሪያው አማኝ መሆናቸው ቀንበራቸውን አክብዶባቸው ታየኝ፡፡ "ሰኞን አታድርገኝ" ይላል የአገሬ ሰው! ምን ያድርግ? ሰኞ ከማን ይማራል? የማን ተሞክሮ ያግዘዋል? ማክሰኞ እንኳ ከሰኞ ይማራል፡፡ ረቡዕ ደግሞ ሰኞንም ሆነ ማክሰኞን ዐይቶ መማር ይችላል፡፡ ሰኞ ግን ...

* * *

"እስካሁንም የሚደንቀኝ ግን ከእነዚያ ወጣቶች መካከል አብዛኞቹ ትዳር ያልመሠረቱ መሆናቸው ነው፡፡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች አጠገብ ለአጠገብ ሆነው ማዶ ምን እንደሚጠብቁ አላውቅም፡፡ ከተግባባን በኋላ ምክንያቱን ስጠይቃቸው ነው የነገሩኝ፡፡ ትዳርን ያወሳስባሉ፤ ስሌትና ቀመር ያበዛሉ፡፡ 'የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ መጠናናት ...' የሚሉት ነገር አላቸው፡፡ ሮኬት ሳይንስ አስመሰሉትሳ! የእግዚአብሔር ፈቃድ ዓመታት ካልፈጀ አይታወቅም ያለው ማነው? እግዜርም ዘንድ ቢሮክራሲ አለ እንዴ! በነበርኩበት ሃይማኖት ሰዎች በጊዜ እንዲያገቡ ይበረታታሉ፡፡ እዚህ እንዲህ አይደረግም መሰል? እዚያ ወጣቶች በሃያዎቹ ዕድሜአቸው ያገባሉ፡፡ ጋብቻን አያወሳስቡም፤ ኑሮን በቀላሉ ነው የሚወስዱት፡፡ እዚህ ግን ሁሉ ነገር አድካሚ ነው፡፡ ላጤዎቹ ቶሎ አያጩም፤ ያጩት ቶሎ አያገቡም፤ ያገቡት ቶሎ አይወልዱም፡፡ እያንዳንዱ ነገር ጣር ይበዛበታል፡፡ እግዚአብሔርን ለኑሯቸው ማመን ያልተቻላቸው አማኞች!

"ስለ በረከት ግን ብዙ ሲወራ እሰማለሁ:: ትዳርንም ሆነ ኑሮን ለምን በቀላሉ እንደማይወስዱት እስካሁን አልገባኝም:: ጊዜ የሚወስዱት ምናልባት የፍቺን ከፉ አጋጣሚ ለመቀነስ ይሆን? ሥራም ላይ ተመሳሳይ ነገር ዐይቻለሁ:: ሥራ የማይሠሩና ውሏቸው ቤትና ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ምን እንደሚጠብቁ ያልታወቀላቸው ወጣቶችንም አይቻለሁ:: ሥራ ሲገኝ ትንሽና የማይመጥናቸው እንደ ሆነ ይቈጥራሉ:: ሲጠየቁ ጌታን እንደሚጠብቁ ይናገራሉ፤ መገለጥ ፍለጋ ይዞራሉ:: እጃቸው የገባውን ሥራ ሳይሠሩና ለሥራ ሳይሯሯጡ ለመኖር መና የሚጠብቁ ክርስቲያኖች!

"ኧረ ስንቱ ይወራል!? ለነገሩ ብርቱ ሠራተኞች፣ ጊዜአቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙ ትጉዎች፣ የጥንቁቁ ጌታ ምስክሮች እልፍ አእላፍ መኖራቸውን አልዘነጋም:: መቼም ሁሉም ብርቱ እንዲሆን አልጠብቅም፤ ቢሆንም አብዛኛው ተወቃሽ ከመሆን መልካም ምሳሌ ቢሆን ጸጋ አለው::

"በዚያው ወር አንድ የጀማ ስብከት ተካሄደ:: እነርሱ 'ክሩሴድ' ብለው ነው ያስተዋወቁት:: የነበርኩበት ቦታ፣ 'ክሩሴድ' ለተባለው ቃል ሥር የሰደደ ከፍተኛ ጥላቻ ነው ያለን:: ክሩሴድ ('የመስቀል ጦርነት') በሃይማኖት ልዩነት መተራረድ የተጀመረበት አስቀያሚ የክርስቲያኖች እርምጃ ነው:: ቤተ ክርስቲያን "የሰላም ጦርነት" አሰኝታ ያካሄደችውን ይህን እልቂት ለመቀስቀስ ስትል ጽኑውን ሰማያዊ እውነት እስከ ማራከስ ዘልቃ ሄዳለች፤ የመስቀሉን ሥራ በሰይፍ ለውጣለች:: የአገራችን ክርስቲያኖች ግን ለታሪኩ ባዳ ናቸው መሰል፣ የዘመዶቼን የሥጋት ስሜት አያስተውሉም፤ ጥንቃቄ አያውቁም:: በዚህ ላይ እኮ የአማርኛ ቃል አይደለም፤ ወይስ ብሽሽቅ አምሯቸው ነው? ኧረ ለመሆኑ ክሩሴድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተልእኮ እንዳልሆነ ብዙዎቹ የእኔ ወገኖች እንደማያውቁ ታውቃለህ? ክሩሴድ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ አይደለም::

"እዚያ ጀማ ስብከት ላይ ብዙ ሰዎች ማስታወቂያውን ዐይተው ሕሙማንን ይዘው መጡ:: ከመድረኩ በሚተላለፍ መገለጥ ሰዎች እየተጠሩ ተጸለየላቸው:: እንዴት አሰደሳች ጊዜ ነበር መሰለህ! እግዚአብሔር ቅርብ መሆኑን አስተምሮኝ ዐልፏል፤ ቁጭ ባልኩበት እንባዬ ይወርድ ነበር:: እዚያው አጠገቤ ፈውስ የተቀበሉና የመሰከሩ ሰዎችን አይቻለሁ:: መቼም የማልረሳው መልካምና አጽናኝ ጊዜ ነበር:: የኢየሱስ ጌትነት ላይነቀል በልቤ እንደገና ተተከለ::

"ግርታዎችም ግን ነበሩኝ፤ ለምሳሌ ጡቷ ላይ ዕጢ ያለባት ሴት በጉባኤው እንዳለች መልእክት መጣና ወደ ፊት ወጥታ እንዲጸለይላት ተጋበዘች:: ልጅቱ ወጣች:: አገልጋዩ እዚያው ጉባኤ ላይ ይዞ ጸለየላት:: ለነገሩ ልጅቱ ተፈውሳለች፤ ድርጊቱን ግን መቀበል አቃተኝ:: ሴት አገልጋይ እጇን ጭና እንድትጸ



ልይላት ማድረግ እንጂ አገልጋዩ ጡቷን ንክች ማድረግ አልነበረበትም:: ወይም ራሷ ለራሷ እንድትጭን አድርጎ እርሱ ከርቀት መጸለይ ይችል ነበር:: የሚያድነው እኮ የኢየሱስ ስም እንጂ የጸላዩ እጅ አይደለም:: ለእኔ ዐይነት ሰዎች ትልቅ መሰናክል ነው ይሄ!"

* * *

ሰውዬው አሁንም ሴቶቹን አልለቀቋቸውም! ከየትም በኩል ቢነሡ ዞረው እዚያው ናቸው! ለምን ይሆን? ነገር በዐይን ይገባልና ዐይናቸውን እያየሁ ጠየቅኋቸው::

* * *

"እነበርኩበት ቦታ የሁለት ሴቶች ምስክርነት እንደ አንድ ነው የሚቈጠረው:: ሚስት ስትሞት ባል ግማሹን ንብረቷን መውረስ ሲችል፣ ባል ሲሞት ግን ሚስት የባሏን ሩብ ንብረት ነው የምትወርሰው (ሱራ 4፥7-12):: ስለዚህ ሴት ግማሽ ሰው መሆኗን ሳምን ነበር የቈየሁት (2፥282):: ሴት ጐዶሎ ሰው አለመሆኗና እግዚአብሔር ጸጋን ሲሰጥ ጾታን እያየ አለመሆኑ አሰደናቂ የክርስትና አስተምህሮ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ቀዳሚ ምስክር ሆነው የቀረቡት ሴቶች የመሆናቸው አግራሞት በቀላሉ አልለቀቀኝም፤ አብሮኝ ከርሟል:: ክርስትና ለሴቶች፣ ለተናቁ፣ ለተገፉ እንዴት ምቹ እንደ ሆነ የሚገባህ እኔ ከመጣሁበት ብትመጣ ነበር::

"በተጨማሪም ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ኀጢአት መንሥኤ ባነሣ ቍጥር አዳምንም ነው የሚወቅሰው፤ ሔዋንን ብቻ አይደለም:: ይህ ገርሞህ ያውቅ እንደሆን እንጃ!

"እኔማ ሚስቶች ለባል የተፈጠሩ፣ የራሳቸው ፈቃድና ፍላጎት የሌላቸው መሆናቸውን ነበር ሳስብ የነበረው:: በዚህኛው ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ለወንድ መልካም ሥራ ሽልማት ሊደረጉ የተዘጋጁ ነበር የሚመስሉኝ::

"እዚያ ሚስትህን በተለያየ መንገድ መቅጣት ተፈቅዶልሃል:: ሲሻህ ዐልጋ ትለይባታለህ፤ ሲሻህ ደግሞ ትመታታለህ - የሃይማኖቱ መጽሐፍ ይህን ይፈቅዳል (ሱራ 4፥34)! መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ረገድ ሥር ነቀል ነው:: ባልና ሚስት የአንዳቸው አካል የትዳር ጓደኞቻቸውም እንጂ የራሳቸው ብቻ አይደለምና በቅጣት ዐልጋ የመለየት መብት እንደሌለህ እቅጩን ይነግርሃል (1ቆሮ. 7፥3-5):: ሚስትህንም እንድትወዳትና እንድታከብራት ነው የሚያስጠነቅቅህ፤ አሊያ ጸሎትህ ሊከለከል ሁሉ ይችላል (ኤፌ. 5፥28-30፤ 1ጴጥ. 3፥7):: አካላዊ ቅጣት ለመሰንዘር ጫፏን መንካት አትችልም::

"አሁን ሳስበው ሴት ልጆቼን የወለድኩት ጌታን ካወቅሁ በኋላ በመ ሆኑ ዝንታለም ማወደስ አለብኝ፤ ተጨማሪ ማመስገኛ ሆኖኛል:: በተለይ ትል ልቆቹ ምሕረትና ሕይወት ከዘመዶቼ ሴት ልጆች ጋር ሲገናኙ የልጆቼ ልበ ሙሉነት ጎልቶ ይወጣል፤ የሥነ ልቦና የበላይነታቸውን ላስረዳህ ይቸግረኛል:: የፈለጉትን መማር፣ የመረጡትን መሥራት፣ የወደዱትን ማግባት እንደሚችሉ ያውቃሉ:: ኢየሱሴ ነፍሴን ማዳኑ ሳይበቃው ለሴት ልጆቼ ነጻነት አጎናጸፈ ልኝ::" በዐይኖቻቸው ከንፈር እንባ ተንቸርፏል::

* * *

ጥሩ እመጡት ጨዋታውን፤ የሴት ልጆቻቸውን ቁንጅና አልተናገሩም እንጂ ... ። በተለይ ቅድም ሻይ ሰጥታኝ የተመለሰችው ... የመልአክ ግልገል ነው የምትመስለው! ... ቁጭ እናቷ! እናቷ ከአባቷ ጋር አብረው የሚታዩበ ትን የግድግዳ ፎቶ ዐይቼ ነው ያወቅሁት። ቁርክ የሚመስሉ እናት! የአባት የው ጥቍረት! ... ኮካና ሚሪንዳ።

* * *

"ከዚያ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ አያያዛቸው ነበር ግራ ያጋባኝ:: መጽ ሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ሕይወት ያገኘሁበት መጽሐፍ ነው:: ይህ ዐይነቱ አክብሮት የማይታይበትና ግዴለሽ አያያዛችሁን ድሮም ከመዳኔ በፊት ሳየው፣ 'መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል' ለሚለው ክርክራችን ማስረጃ እናደር ገው ነበር፤ ሰው ቅዱስ መጽሐፍን እንዲህ አይዝማ!

"እኔ የነበርኩበት ቦታ 'ቅዱስ' ነው ብለን ለምናስበው መጽሐፍ የምናደ ርገው ጥንቃቄና የምንሰጠው ከበሬታ ከፍተኛ ነው:: መጽሐፉን በጥሩ ልባስ እንሸፍነዋለን፤ ቤታችንም ከፍ ያለ ቦታ ነው የምናስቀምጠው:: ከሰማይ ወር ዷል ብለን ስለምናስብ በአክብሮት ነበር የምንይዘው:: የዚያ መጽሐፍ አንዲ ትም ጥቅስ የተጻፈችበት ወረቀት እንኳ በጥንቃቄ ትያዛለች፤ እንዷም ግንጣይ (ገጽ) እንዲሁ አትጣልም:: እዚህ ስመጣ ግን እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች እንደ ነገሩ ነው የሚይዙት:: ሻይ ሲጠጡ ስኒ ማስቀመጫውን ያስ ቀምጡበታል:: የቡና ቁርሱን ሰሃንም ሲያኖሩበት ዐይቻለሁ፤ ተራ መጻሕፍት በላዩ ይቆልላሉ:: ከመጽሐፉ ከመጥቀስ መጽሐፉን ማክበር ይቀድማል! ምናለ ስለዚህ ነገር የማስተምርበት ዕድል ቢኖረኝ! ..."

* * *

ቄስ አብደላ እያወሩ እኔ በሐሳብ ወደ አባቴ ጭልጥ አልኩ ...



በቤታችን ጣሪያ ሥር የሚኖር ሁሉ ሊከተለው የሚገባ ጥብቅ ደንብ አለ:: ቤታችን ውስጥ የትም ቦታ ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ካልሆነ ምንም መጽሐፍ አይቀመጥም:: ሌሎች መጽሐፎች ከሥር ይሆኑና መጽሐፍ ቅዱሱ ከላይ ይውላል:: ይቺን ካፋለስን አባታችን በዚያ ትልቅ እጁ ያቀምሰናል (ምግብ እንዳልሆነ ግልጽ ነው መቼም!):: አባታችን ሰው ቤትም ሲሄድ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሌላ መጽሐፍ ተጭኖ ካየ ተቈጥቶ፣ "እንሡ" ስለሚል የማፍርበት ጊዜ ነበረኝ::

የአባታችን፣ "ፋራነት" ስንጕረምስ "ተገለጠልን":: ጌታ፣ "እኔ የነገርኳ ችሁ ቃል መንፈስ ነው" ብሏል (ዮሐ. 5፥63):: ታዲያ ቃሉ መንፈስ ነው እንጂ የሚታየው መጽሐፍ ቅዱስ ነው እንዴ? ትምህርትና ዕድሜ ግን የራሳ ችንን "ፋራነት" እንዲገለጥ አገዙን:: የትምህርት መጽሐፎቻችንን እንኳ በንጽ ሕናና በጥንቃቄ ነው የምንይዘው:: ታዲያ ስንት ሕይወት ተከፍሎ፣ ስንቱን ተግዳሮት ዐልፎ የመጣውን፣ ሕይወትን ያገኘንበትንና እግዚአብሔርን ያወቅን በትን መጽሐፍ ማክበር አይገባንምን? አሁን ግን አንዳንድ ክርስቲያኖች ቤት ስንሄድ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምንም ነገር ተጭኖ ስናይ እኛም በተራችን ማዘ ንና እንደ ዐቅማችን ተቈጥተን መናገር ጀመርን::

በሐሳብ መንጎዴን ሳይነቁብኝ ተመለስኩ::

* * *

"ሌላው ችግር ደግሞ ቋንቋ ነበር:: ሙስሊም ስለ ነበርኩ አንዳንድ ዐረ ብኛ ቃላትን መጠቀም እዘወትራለሁ፤ ግን ተቈጪ በዛብኝ:: 'በረካ ሁን' ስትል ፊት ይነሱሃል፤ 'be blessed' ስትል ደግሞ ጆሮ ይሰጡሃል:: 'ኢብራሂም፣ ዳውድ፣ ...' በማለት ሳወራ ጉምጉምታ ይፈጠራል፤ ወዲያው 'David, Paul' ማለት ስጀምር ግን ጉምጉምታው ይተንናል:: ይገርምሃል፤ በአማርኛ ንግግር ውስጥ እንግሊዝኛ መቀላቀል ትችላለህ፤ ኦሮምኛ ማውራት መብትህ ነው፤ ሌሎችንም ቋንቋዎች መጠቀም ክልክል የለውም:: አማርኛና ዐረብኛ ብዙ ተመ ሳሳይ ቃላት እንዳሏቸው ይታወቃል፤ የቋንቋ ባለቤትም እግዚአብሔር መሆኑን ሲናገሩ እሰማለሁ:: ዐረብኛ ግን ሰይጣናዊ ይመስላቸዋል:: ዐረብኛ ተናጋሪ ክርስቲያኖች እኮ በዓለም ብዙ ሞልተዋል! በበዐለ አምሳ ቀን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው ልሳኖች ሲናገሩ የዐረብ ሰዎች በዚያ ነበሩ (የሐዋ. 2፥11):: ምናልባት ቋንቋቸው ዐረብኛ ሊሆን ይችላል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ስጥቷቸው በልሳን ከተናገሩባቸው ቋንቋዎች አንዱ ዐረብኛ ነበር ማለት ነው:: ሆኖም እኔ 'ኢየሱስ ጌታ ነው' በማለት ለግዙፉ የነፍሴ ጥያቄ ምላሽ ብሰጥም፣ እነርሱ ግን እነዚህን ለመሳሰሉ ትንንሽ ጥያቄዎቼ መልስ መስ ጠት አቃታቸው::

"በፊተኛው ሃይማኖቴ እንደ ኩሩ ኢትዮጵያዊነቴ በእናት ቋንቋዬ መጸለይ ብፈልግም ዐረብኛ ቅዱስ ቋንቋ እንደ ሆነ ስለ ነገሩኝ መማሬ ግድ ነበር:: ምን እርሱ ብቻ? አለባበሴም እንደ ዐረብ ነበር፤ የምጸልየው እንኳ ወደ ዐረብ ከተማ ዞሬ ነበር:: እውን አንድ ቋንቋ ከሌሎች ተለይቶ ቅዱስ መሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ ነበረኝ:: እዚህ ስመጣ ግን ጥያቄዬን ባይመልሱትም፣ ጥያቄዬን ለወጡልኝ:: እውን አንድ ቋንቋ ከሌላው ተለይቶ ርኩስ ይሆናል? እሺ አፌን የፈታሁበትን ቋንቋ ያህል በቀላሉ የማቀላጥፈውን ዐረብኛ ምን ላድርገው? ከጭንቅላቴ እንዴት ላውጣው? ለምንስ ላውጣው? ጉዳዩ እንዴት በጥብጦኝ እንደ ነበር ልነግርህ አልችልም:: ታዲያ አንድ ዐረብኛ ቃል በተጠቀምኩ ቍጥር፣ 'ውደቅ!' የሚል ግሣጼ እየተሰነዘረብኝ እንዴት እችላለሁ?

"በደቡባዊ እስያ ቤተ ክርስቲያን በሚያስደንቅ ሁኔታ እያደገች ያለችው የ'ሙስሊም' ቃላትንና ሥርዐቶችን ስትጠቀም እንደ ሆነ እንደ ታውቋል::[1] ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በጠራ ዐረብኛ ቋንቋ ከተተረጐመ በርካታ ዘመናት እንዳስቈጠረ ታውቃለህ? ግብፆች፣ ሶርያኖች፣ ዮርዳኖሶች፣ እንዲሁም ኢራንና ኢራቅ ያሉ ክርስቲያኖች አብዛኞቹ ዐረብኛ መጽሐፍ ቅዱስን ነው የሚጠቀሙት:: በእርግጥ አላህ 'የኢብራሂም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ' ተብሎ ይታወቃል:: ኢየሱስን በተመለከተ መጠሪያው ከዕብራይስጡ ጋር በጣም የቀረበ ነው፤ የሱዋ ነው የሚለው:: ውልደቱን፣ ሞቱን፣ ትንሣኤውንና ዕርገቱን በግልጽ ይናገራል፤ ዳግም ምጽአቱንም አያስቀርም::

"ጳውሎስ የአቴና ሰዎች የሚያመልኩትንም ሆነ እርሱ በክርስቶስ ያወቀውን እግዚአብሔር "theos" በሚል ተመሳሳይ መጠሪያ ለመጥራት አላመነታም (የሐዋ. 17፥16-23)::[2] ታዲያ ቢያንስ ጥላቻው ቢቀር ምን ነበረበት! ዐረብኛ ዓለም አቀፍ ቋንቋ ከመሆኑም ባሻገር ብንማረው የቀድሞ ዘመዶቼ ዘንድ የሚሰራጨውን ድብቅ አስተምህሮ ለመረዳት ያግዘን ነበር:: ትናንትና 'አሰላም አሌይኩም' ስል፣ 'በኢየሱስ ስም' የሚል ግሣጼ አዳራሹን ሲሞላው አላስተዋልክም? እኔ 'ሰላም ለእናንተ' ማለቴ ነበር:: ቅድም አንተ ራስህ 'ጌታ ይመስገን' ብለህ በዘዴ ነው የመለሰክልኝ:: 'ወአሌኩም አሰላም' በማለት፣ መልሰህ ሰላምን ለእኔ ብትመኝ ችግር ነበረው? እኔን ይቅርና 'የሚያጓጥሟችሁን ሙስሊሞች በዚህ መንገድ ሰላምታ እንዳትሰጡ የሚከለክል ምን ምክንያት አለ?'[3] ወይስ ሳታውቀው ቀርተህ ነው?" ዐይናቸው ውስጥን ሰርስሮ የሚያይ ይመስላል::

ደነገጥኩ:: "ኧረ ልማድ ሆኖብኝ ነው:: አንዳንዴማ 'ሰዓት ስንት ነው?' ስባል፣ 'ጌታ ይመስገን' እላለሁ:: እርስዎም ትናንት ያ ትንሽ ልጅ ሰዓት ሲጠይቅዎት፣ 'አል-ሃምዱ ሊላህ' በማለት እንደ መለሱት ማለቴ ነው! ከዚህ ልማድ የተነሣ የአያቴ ዘመዶች እንኳ 'በላለዴይንጣ' ሲሉኝ፣ 'ጌታ ይመስገን'



በማለት እየመለስኩላቸው ብዙ ጊዜ አዝነውብኛል:: ደጋግመው ነግረውኝ አልሰማኋቸውም" በማለት ተንተባተብኩ::

"ግዴለም አይዞህ፤ አሁንማ ብዙ ዐውቄያለሁ:: ያኔ የገጠመኝን ተግዳሮት እንድ ነግርህ ስለ ጠየቅኸኝ እንጂ ክርስቲያን ከሆንኩ ዓመታት አስቈጠርኩ እኮ፤ የእንግድነት ዘመኔ ዐልፏል:: ያኔ ነበር ብዙ ትግል የበዛብኝ:: መዝሙር ሳንጎራጉር ዜማው ወደ መንዙማ ወሰድ ካለ፣ 'በኢየሱስ ስም!' ይገሥጹልኛል፤ የተቀደሰና የረከሰ ዜማ ያለ ይመስል:: ውሃ ይዤ ወደ መጸዳጃ ቤት መማባቴ ራሱ የውይይት አጀንዳ ሆኖ ያውቃል:: የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል የነበረ አንድ የሕክምና ባለሞያ እንኳ ከጤና ጠቃሚነቱ የተነሣ መጸዳጃ ቤት ውሃ በማንቆርቆርያ ይዞ ሲገባ ስላዩት 'ሙስጠፋ' የሚል ስም አውጥተውለት ነበር::

"በዚህ ላይ አንዳንድ፣ 'ድሮስ እስላም ...' እየተባለ እዚያ እንደ ዘበት የሚነገረው ነገር ሰዎችን ይጎዳል:: ከዚያ ዐለፍ ሲልም እምነት ለመጣል የመቸገር ሁኔታ ይታይ ነበር:: በእርግጥ በዚያው መጠን ከልክ ያለፈ ቅርበትና ጥንቃቄ የሚያደርጉልንም ነበሩ፤ ወደ ኋላ እንዳንመለስ ሠግተው ይመስለኛል:: በተጨማሪም፣ ከእስልምና ወደ ክርስትና የሚመጣን ሰው ሁሉ ለሙስሊሞች ወንጌልን እንዲያደርስ እንደ ተጠራ አገልጋይ በመቍጠር ሥራውን እንዲያቆም እንደሚደረግ አሁን አሁን አያለሁ:: ሥራቸውን ያቆሙ ነጋዴዎች፣ ነርሶች፣ አስተማሪዎች ገጥመውኛል:: ሥራቸውን እንደገና እንዲጀምሩ አንዳንዶቹን መክሬአቸዋለሁ::

"አሁን ግን እዚያች ያደግሁባት ከተማ ወንጌል በስፋት ገብቷል፤ ከዐሥር በላይ አብያተ ክርስቲያናት አሉን:: ከግማሽ በላይ የሆኑት አባላት የዚያው ከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ ቤተ ሰቦቼን ጨምሮ ብዙ ሙስሊሞች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆነዋል:: ከእሑዱ ሌላ ትልቁ ፕሮግራማችን በጁምዐ ቀን ነው የሚካሄደው:: ደግሞ ልፍስፍስ ክርስቲያኖች እንዳይመስሉህ:: 'ኢየሱስ ጌታ ነው!' የሚሉት በሕይወታቸው ጨክነው ነው:: ቤታቸው የተቃጠለባቸው፣ ከዕድር የተባረሩ፣ ከውርስ የተገለሉ፣ ገንዘባቸውን የተቀሙ፣ አካላዊ ጥቃት የደረሰባቸው አሉ:: አንዳቸውም ግን ወደ ኋላ አልተመለሱም፤ ለጌታ በነፍሳቸው የተወራረዱ ናቸው:: ባሏ የተገደለባት ሚስትና የልጁ አስከሬን ከተቀበረበት ቦታ ሁለት ጊዜ ተቆፍሮ እየወጣ የተጣለበት አባት አሁንም በእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች ናቸው::

"ያን ሁሉ ፈተና አሁን ቆም ብለው ሲያዩት ምን ይሰማዎታል? ምንም መልካም ነገር አልነበረውም?" ችግሮችን እንደ ፉርጎ ማከታተላቸው ከንክኖኝ ጠየቅኋቸው::

"ጒድለት ስዘረዝርልህ የቆየሁት በአንተው ፍላጎት መስሎኝ! ያጋጠመኝን ችግር እንድነግርህ አልነበር ጥያቄህ?" ደጋግ ዐይኖቻቸው ይሥቃሉ::

"ይቅርታ ረስቼው ነው" አልኩ የምንተፍረቴን (በዚህ ዕድሜ ምንድን ነው እንዲህ የሚያስረሳኝ!?)::

ቄስ አብደላ ቀጠሉ፤ "እኔ በዳንኩበት ወቅት የሚጠነቀቅልኝ ሰው አልነበረም:: ሆኖም በዚያ መንገድ ባላልፍ ኖሮ ከእስልምና ወደ ክርስትና ለሚመጡት ዐውዳዊ አቀራረብ እንዲኖር ማሰብና ማስተማር አልችልም ነበር:: በእርግጥ ዐውዳዊነት ከፍተኛ ጥንቃቄ ይሻል:: ደግሞም አስፈላጊነቱ ከራሱ ከኢየሱስ ፍጹም ማንነት የሚጀምር መሆን ይገባዋል:: አምላክ ሆኖ ሳለ፣ 'የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ' ከሚለው መነሣት ነው ያለበት (ፊልጵ. 2፥7):: ገደብ ያልተበጀለት ዐውዳዊነት ወደ ዘቀጠ ስሕተትና መጽሐፉን ወደ መበረዝ ይወስደናልና!

"አሁንማ እኔ ራሴ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነኝ:: ወንጌላውያን በአካባቢው ወንጌል ለመስበክ ምን ዐይነት አቀራረብ መጠቀም እንዳለባቸው ትምህርትና ሥልጠና እሰጣለሁ:: ለነገሩ ከአገልጋዮቹ ብዙዎቹ እንደ እኔ ከእስልምና የመጡ ስለ ሆኑ አያስቸግሩም::

"አየህ መኖር ጥሩ ነው፤ ጌታ ደግ ቀን አመጣ! አሁን በዚያ ያለነው ክርስቲያኖች አለባበሳችን እንደ አካባቢው ነው:: ጀለቢያ እናዘወትራለን:: ጢማችንን እናሳድጋለን:: በቀን አምስት ጊዜና ከዚያም በላይ እንጸልያለን:: በነጻነት በዐረብኛ እንነጋገራለን:: በመንዙማ አቀራረብ የተዘጋጁ መዝሙሮችን ነው የምንጠቀመው፤ መስማት ከፈለግህ በኋላ እሰጥህና ትሰማለህ:: ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሄደው ወደ ኋላ ለመሄድ ፊታቸውን ያዞሩ እኛ ዘንድ ሲመጡ እንዴት እንደሚደሰቱና ነጻነት እንደሚሰማቸው ልነግርህ አልችልም:: ይህንን ነበር ያኔ ያጣሁት!

"አየህ፣ 'እስልምና የሃይማኖታዊ ሥርዐቱን 'አእማዶች' በሚያበጅበት ጊዜ ከአይሁድና ከክርስትና ልምምዶች ብዙ ወስዷል፤ ይኸውም እምነትን በአንደበት ማሳወቅን (the confession of faith)፣ ሥርዐታዊ ጸሎትን (ritual prayer)፣ ምጽዋት መስጠትን፣ ጾምን፣ ሃይማኖታዊ ጒዞን (pilgrimage) ያካትታል:: ስለዚህም የተወሰነ መቀራረብ መኖሩ አስፈላጊ ነው::'[4]

"አሁን ያ ግራ መጋባትና ባይተዋርነት መቶ ዕጥፍ ሆኖ እንደገና ቢመጣ ለአፍታም ውሳኔዬን አልቀይርም:: መልካሙ አምላክ የእኔ ዐይነቱን ጭንጋፍ ለዘላለም ሕይወት ያጨበትን ጸጋ እንዴት እረሳለሁ? ይኸውልህ፣



'ማንኛውም ሙስሊም አላህን እንደ አባቱ ማሰብ አይችልምና' እኔም እንደ ዚያው ነበርኩ::[5] አሁን ግን እግዚአብሔር አባቴ ሆነ፤ እኔም ልጁ:: ታዲያ በልጁ ልጁ ያደረገኝን ጌታ እንዴት እዘነጋለሁ ወዳጄ!? በመታጠብ ብዛት ላስወግደው ያልቻልኩትን ኀጢአቴን በቅዱስ ደሙ አጥቦ አስወገደልኝ:: አሁን ነጻ ነኝ! 'ወዶኛልና አዳነኝ' ነው መዝሙረኛው ያለው?" ተመስጠው ነው የሚያወሩት::

"እኔ እኮ በትክክልም ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ብርሃን የመጣሁ ሰው ነኝ! አባት ላልነበረኝ፣ እግዚአብሔር አባት ሆኖኛል:: ከእስትንፋሴ ይልቅ የቀረበ፣ የልቤ አምላክ ሆኗል:: ምንም ሳላደርግለት፣ ምንምም ላላደርግለት እንዲሁ የወደደኝን፣ እንዲሁ የሞተልኝን፣ ከኀጢአቴ በደሙ አጥቦ አንጽቶ ያቀፈኝን ...! ኢየሱስን፣ የሕይወቴን ጌታ ለመከተል ባደረግሁት ውሳኔ አንድም ቀን ተጸጽቼ አላውቅም! ከኢየሱስ ወዴት ይኬዳል! እንኳን እኔ ዘር ማንዘሬ ገና ይገዛለታል!!" ዐይኖቻቸው ብርሃን መርጨት ጀምረዋል:: ይህን ስመለከት ውስጣቸው በብርሃን መሞላቱን ገመትኩ፤ ግሪኮቹ እንደሚሉት፣ ዐይን የነፍስ መስኮት ነውና::

"ክርስትና ብዙ ብርሃን አሳይቶኛል:: በተለይ 'ጠላቶቻችሁን ውደዱ' የሚለው ለእኔ ስለ እግዚአብሔር ሥር ነቀል መረዳት ያገኘሁበት ነው (ማቴ. 5፥43-48):: እግዚአብሔር እኛን ገና ጠላቶቹ ሳለን አይደል የወደደን? እናም ይኸውልህ፣ 'ጠላትን አለመውደድ እንዲህ ዐይነት አምላክ መኖሩን መካድ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር እግዚአብሔርነቱ ለወዳጆቹ ብቻ ሳይሆን፣ ለጠላቶቹም ጭምር ነው::'[6] በፊት ቢሆን እንኳን ጠላቴን ልወድ፣ ወዳጄ እንኳ ከእኔ የተለየ ሓሳብ ካለው ልወደው አልችልም ነበር:: በተለይ ሃይማኖቱን ከቀየረ፣ መግደልም ተገቢ እንደ ሆነ አስብ ነበር፤ በእኔ ቤት አምላኬን አስደስቼ ሞቼአለሁ! አይ አለማወቅ! ጌታ ኢየሱስን ካወቅሁ በኋላ ነው ምን ዐይነት ጨለማ ውስጥ እንደ ነበርኩ የገባኝ:: ኢየሱስ 'ጠላቶቻችሁን ውደዱ' ያለውን ስቀበል፣ እውነተኛውን አዛኝና ርኅሩኅ አምላክ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳገኘሁት ዐወቅሁ:: መስቀል ላይ ሆኖ እንኳ፣ 'የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው' (ሉቃ. 23፥34) ማለቱን ባሰብኩት ቍጥር የፍቅሩ ግለት ልቤን ያቀልጠዋል::"

ድንገት እንደ መባነን ብለው አዩኝ፤ ፊታቸው ግን አሁንም ቦግ ብሏል::

"'ኢየሱስ ጌታ ነው' በማለት ለፍቅሩ ከተንበረከክሁ በኋላ ያለፍኩበትን ውጣ ውረድ በመጽሐፍ ባሳትመው ለትውልድ እንደሚጠቅም አስባለሁ::

እንዲያውም የመጀመሪያውን ረቂቅ እሰጥሀና በእርማቱ ትረዳኛለህ!?" ንግግራቸው ጥያቄ ሳይሆን ግብዣ ይመስላል::

"አብሽር!" ነበር መልሴ::

ማስታወሻ


1. J. Dudley Woodberry, "The Middle East: Crescent, Cross, and Plowshare". *Theology, News and Notes* (Pasadena, California: Fuller Theological Seminary, March 1992), 19.
2. Colin Chapman, *Cross and Crescent: Responding to the Challenge of Islam* (Downers Grove, Illinois: IVP Books, 2007), 245.
3. ዝኒ ከማሁ፣ 25::
4. Shah Ali, with Dudley Woodberry, "South Asia: Vegetables, Fish, and Messianic Mosques", *Theology, News and Notes* (Pasadena, California: Fuller Theological Seminary, March 1992), 12. (በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ነገር ለማግኘት ቀጣዩን ጽሑፍ ማንበብ በብዙ ይጠቅማል፤ J. D. Woodberry, "Contextualization Among Muslims: Reusing Common Pillars," *The Word Among Us*, ed. Dean S Gilliland (Word Publishers, 1989), 282-312).
5. Bilquis Sheikh with Richard Schneider, *I Dared to Call Him Father: The Miraculous Story of a Muslim Woman's Encounter with God* (Life Journey, 2004), 46.
6. ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *የወዳጅ ፍለጋ* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 148::




# ሥጋ ቤቶቹ እና ወንድማማቾቹ

የጌታ ልደት በሚከበርበት ዕለት ረፋድ ላይ ነው:: እንቶቼ ገና ከእንቅልፋቸው አልነቁም (ቢነቁም ከዐልጋ ለመውረድ ረዘም ያለ የሽግግር ጊዜ ይፈልጋሉ):: በዚህም ላይ ድፎው እንዲቈረስ አባቴ ከፍል ውሃ እስኪመለስ እንጠብቃለን፤ ሲመጣም እንቶቼ ዳቦው ሲቈረስ ማየት ያሳዝናቸዋል መሰል ቊርስ ቶሎ አላገኝም (ሲነደኝ፣ "ዳቦው ዘመዳችን ነው እንዴ?" ብዬ እጠይቃለሁ):: እናም በበዓል ከቤት ስወጣ የማይወዱት እንቶቼ ሳይሰሙ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ሰበብ ከቤት ወጣሁ፤ እግረ መንገዴን ማኪያቶ እንደማገኝ ተስፋ እያደረግሁ:: የሰፈራችን "ባቡር መንገድ" ስደርስም የፈረንጅ ስም ወደ ያዘ ካፌ እግሬ እንደ መራኝ ዘው አልሁ:: የካፌው በረንዳ ላይ የተጎዘጎዘው ቄጤማ፣ ደጅ ድረስ ከሚሰማው የባህል ዘፈን ጋር ተዳምሮ ዓመት በዓል መሆኑን ለዐላፊ አግዳሚው ይለፍፋል::

ቀድመውኝ የደረሱ ሁለት ሰዎች በረንዳው ላይ ተቀምጠዋል:: ሁለቱም የሰፈሬ ልጆች ናቸው፤ አንዱ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሲሆን፣ ልብሱ ላይ ነጠላ አጣፍቷል፤ የነጠላው ጥለት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ነው (ኮከብ ግን የለውም!):: መልኩ ለሴት የሚመኙት ዐይነት ቅላት ሲኖረው፣ ጠጕሩን በቅርብ እንደ ተላጨው ያስታውቃል:: መነፅሩ ግማሽ አፍንጫውን ከልሎት እንኳ ከሲታ ፊቱ አፍንጫ በዝቶበታል:: የነገረ መለኮት ተማሪ ሳይሆን አይቀርም:: ሌላኛውን ሰው ደግሞ ዐልፎ ዐልፎ ቤተ ክርስቲያናችን አየዋለሁ:: ደብዛዛ ካኪ ሱሪ ላይ ኮት ደርቧል፤ በለበሰው ኮት ኪስ ውስጥ መጽሐፍ አለ:: ጫማው ግን አልተጠረገም:: ጠጕሩ መኻል ግምባሩ ድረስ ነው፤ ሆኖም የጠጕሩ እግሮች ነጫጭነት ቀለም እንደሚጠቀም ያውጃል:: አጠገባቸው ወዳለው ጠረጴዛ እያመራሁ የዐንገት ሰላምታ ሰጠኋቸው፤ አላዩኝም:: ምን ይሆን የሚያወሩት? ጆሮዬን ሰደድኩ ...

* * *

"ዛሬ ብርሃን ልደቱም አይደል? ብርሃን ልደት ስትል እኮ ብርሃን የተወለደበት ማለት ነው!" ኦርቶዶክሱ ነው የሚያወራው::

"እንዴታ!" ብሎ ያኛው መለሰ፤ እጆቹን እየዘረጋ::

"ታዲያ የተወለደው ብርሃን መሆኑን ከተረዳህ እናቱ የብርሃን እናት ስትባል ለምን ይከፋሃል? 'እመ ብርሃን' መባሏ ለምን ይጐረብጥሃል? ጌታችን በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ሰው ሆኖ ከእርሷ የተወለደ አምላክ ከሆነ፣

እንዲያውም የመጀመሪያውን ረቂቅ እሰጥሀና በእርማቱ ትረዳኛለህ!?" ንግግራ ቸው ጥያቄ ሳይሆን ግብዣ ይመስላል።

"አብሽር!" ነበር መልሴ።

## ማስታወሻ


1. J. Dudley Woodberry, "The Middle East: Crescent, Cross, and Plowshare". *Theology, News and Notes* (Pasadena, California: Fuller Theological Seminary, March 1992), 19.
2. Colin Chapman, *Cross and Crescent: Responding to the Challenge of Islam* (Downers Grove, Illinois: IVP Books, 2007), 245.
3. ዝኒ ከማሁ፣ 25።
4. Shah Ali, with Dudley Woodberry, "South Asia: Vegetables, Fish, and Messianic Mosques", *Theology, News and Notes* (Pasadena, California: Fuller Theological Seminary, March 1992), 12. (በርእስ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ነገር ለማግኘት ቀጣዩን ጽሑፍ ማንበብ በብዙ ይጠቅማል፤ J. D. Woodberry, "Contextualization Among Muslims: Reusing Common Pillars," *The Word Among Us*, ed. Dean S Gilliland (Word Publishers, 1989), 282-312).
5. Bilquis Sheikh with Richard Schneider, *I Dared to Call Him Father: The Miraculous Story of a Muslim Woman's Encounter with God* (Life Journey, 2004), 46.
6. ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *የወዳጅ ፍላጻ* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 148።




# ሥጋ ቤቶቹ እና ወንድማማቾቹ

የጌታ ልደት በሚከበርበት ዕለት ረፋድ ላይ ነው። እንቶቼ ገና ከእንቅልፋ ቸው አልነቁም (ቢነቁም ከዐልጋ ለመውረድ ረዘም ያለ የሽግግር ጊዜ ይፈ ልጋሉ)። በዚህም ላይ ድፎው እንዲቈረስ አባቴ ከፍል ውሃ እስኪመለስ እንጠ ብቃለን፤ ሲመጣም እንቶቼ ዳቦው ሲቈረስ ማየት ያሳዝናቸዋል መሰል ቍርስ ቶሎ አላገኝም (ሲነደኝ፣ "ዳቦው ዘመዳችን ነው እንዴ?" ብዬ እጠይቃለሁ)። እናም በበዓል ከቤት ስወጣ የማይወዱት እንቶቼ ሳይሰሙ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ሰበብ ከቤት ወጣሁ፤ እግረ መንገዴን ማኪያቶ እንደማገኝ ተስፋ እያ ደረግሁ። የሰፈራችን "ባቡር መንገድ" ስደርስም የፈረንጅ ስም ወደ ያዘ ካፌ እግሬ እንደ መራኝ ዘው አልሁ። የካፌው በረንዳ ላይ የተጎዘጎዘው ቄጤማ፣ ደጅ ድረስ ከሚሰማው የባህል ዘፈን ጋር ተዳምሮ ዓመት በዓል መሆኑን ለዐ ላፊ አግዳሚው ይለፍፋል።

ቀድመውኝ የደረሱ ሁለት ሰዎች በረንዳው ላይ ተቀምጠዋል። ሁለ ቱም የሰፈሬ ልጆች ናቸው፤ አንዱ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሲሆን፣ ልብሱ ላይ ነጠላ አጣፍቷል፤ የነጠላው ጥለት አረንጓዴ፣ ቤጫ፣ ቀይ ነው (ኮከብ ግን የለውም!)። መልኩ ለሴት የሚመኙት ዐይነት ቅላት ሲኖረው፣ ጠጕሩን በቅ ርብ እንደ ተላጨው ያስታውቃል። መነፅሩ ግማሽ አፍንጫውን ከልሎት እንኳ ከሲታ ፊቱ አፍንጫ በዝቶበታል። የነገረ መለኮት ተማሪ ሳይሆን አይቀ ርም። ሌላኛውን ሰው ደግሞ ዐልፎ ዐልፎ ቤተ ክርስቲያናችን አየዋለሁ። ደብ ዛዛ ካኪ ሱሪ ላይ ኮት ደርቧል፤ በለበሰው ኮት ኪስ ውስጥ መጽሐፍ አለ። ጺማው ግን አልተጠረገም። ጠጕሩ መኻል ግምባሩ ድረስ ነው፤ ሆኖም የጠጕሩ እግሮች ነጫጭነት ቀለም እንደሚጠቀም ያውጃል። አጠገባቸው ወዳ ለው ጠረጴዛ እያመራሁ የዐንገት ሰላምታ ሰጠኋቸው፤ አላዩኝም። ምን ይሆን የሚያወሩት? ጆሮዬን ሰደድኩ …

* * *

"ዛሬ ብርሃነ ልደቱም አይደል? ብርሃነ ልደት ስትል እኮ ብርሃን የተወለደበት ማለት ነው!" ኦርቶዶክሱ ነው የሚያወራው።

"እንዴታ!" ብሎ ያኛው መለሰ፤ እጆቹን እየዘረጋ።

"ታዲያ የተወለደው ብርሃን መሆኑን ከተረዳህ እናቱ የብርሃን እናት ስትባል ለምን ይከፋሃል? 'እመ ብርሃን' መባሏ ለምን ይጐረብጥሃል? ጌታችን በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ሰው ሆኖ ከእርሷ የተወለደ አምላክ ከሆነ፣

እርሷ የአምላክ (የጌታ) እናት መሆኗም አይደል? 'ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው፤ እርሱም እናቱን ፈጠራት፤ ከርሷም፣ እርሱ የፈጠረውን ሥጋ ተዋሐደ' እንዲል ሃይማኖተ አበው (ሃይ. አበው ዘኤፍሬም ምዕራፍ ፵፲ ክ፩፥2)፡፡ ጌታችን ከልዕልና ወደ ትሕትና ሲመጣ፣ ያለ ዘርዓ ብእሲ (ያለ ሥጋዊ አባት) በግብረ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወለደችው እያወቅህ፣ ወላዲተ አምላክ (እመ አምላክ) መባሏን ለምን ትቃወማለህ?" ጠየቀ ባለ ነጠላው፡፡

ባለኮቱ ቀጠለ፤ "ልክ ነህ ወዳጄ፤ ድንግል ፈጣሪዋን ወልዳዋለች፣ እርሱ ግን እናቱን ፈጥሯታል፡፡ ፈጣሪዋ መገኛዋ ነው! ያለ እርሱ አልነበረችም፤ እርሱ ግን ያለ እርሷ ነበር፡፡ መረጣት እንጂ አልመረጠችውም፡፡ እርሱ ፈጣሪና አምላክ ነው፤ እርሷ አምላክ አይደለችም - ፍጡር እንጂ! ሆኖም የመስቀሉን ሥራ እንኳ ለእርሷ ለመስጠት፣ 'የተሰቀለው ሥጋ የማርያም ነው' ሲባል ሁሉ እንሰማለን፡፡ ለመሆኑ የአንተ ሥጋ የእናትህ ነው ወይስ የአንተ? አንተ ስትቆነጥጥ አንተ ነህ ወይስ እናትህ ናቸው የሚያምማቸው? ለምሳሌ፣ ኪዳነ ምሕረት የሚለው መጠሪያ የምሕረት ኪዳን ማለት ነው፤ ታዲያ ምሕረት የተቀበልንበት ኪዳን በማን ነው የተገኘው? በኢየሱስ እንጂ በእናቱ አይደለም፡፡ ስለዚህ ለእኛ ኪዳነ ምሕረት ኢየሱስ ነው፡፡ በዚህም ላይ ..."

አላስጨረሰውም፤ "ይኸውልህ የጠየቅሁህን አይደለም ልትመልስ የሞከርከው፡፡ ድንግል ማርያም የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት መሆኗን፣ ጌታ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን፣ ስለዚህም ማርያም እመ (ወላዲተ) አምላክ መሆኗን ነው እየተወያየን ያለነው፡፡ የት ትሸሻለህ? የልጇን አምላክነት የተቀበልከውን ያህል የእርሷንም እናትነት ተቀበል፤ አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ አይሆንም፡፡" ሲያወራ የላይኛው ከንፈሩን ይልሳል፡፡

"ምነው እንዲህ ውጥር አድርገህ ያዝከኝ? ችግሩ ያለው እኮ እናንተ ዘንድ ነው፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ሰው አይደለችም? ሲሻችሁ፣ 'በሓሳብሽ ድንግል ነሽ' በማለት ትገልጿታላችሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የማይናገረውን ከየት አመጣችሁት? ወደ እርሷስ መጸለይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው? የወርቅ ጫማ እንደምትጫማም ትዘምራላችሁ፡፡ ምንድን ነው የምታወሩት? ልጇ በተውሶ አኺያ እየተጓዘ፣ በተውሶ ቤት እራት እየበላ፣ በተውሶ መቃብር ሲቀበር፣ ወርቅ የምትለብስና የምትጫማ እናት ናት ማርያም? ምን ዐይነት እናት እያደረጋችኋት እንደ ሆነ ገብቷችኋል? ምነው ወዳጄ!? ምን ሆነሃል?" አለው እንዲቀጥል በእጁ እየጋበዘው፡፡

"በእመቤታችን ላይ ግርታ እዚህም እዚያም ሊኖር ይችላል፡፡ ቅድም ወገኖችህ እዚያ ማዶ ይዘውኝ ነበር፤ ሊሰብኩኝ፡፡ ሲጀምሩ 'ማርያም አታማል



ድም' ነው ያሉኝ፡፡ የድንግል ማርያምን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደማምን ነገርኳቸው፡፡ አልለቀቁኝም፤ ነጠላ በመልበሴ ይሁን፣ ክር በማሰሬ ወይም ጴንጤ ባለመሆኔ 'ማርያም አታማልድም' አሉኝ ደጋግመው፤ ከልዩነት የመጀመር አባዜ! ለመሆኑ ዓላማችሁ ሰዎች የልጇን የቅዱስ አማኑኤልን አዳኝነት እንዲያምኑ መርዳት ነው ወይስ የእርሷን እናትነት ዋጋ ማሳጣት!?" አለ ቈጣ ብሎ፡፡

ይህኛውም የተቈጣ ይመስላል፤ "በእውነትም 'ማርያም አታማልድም' ማለት ሳይሆን፣ ጌታ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ማመን ነው የሚያድነው! ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ካመንክ፣ የመስቀል ሥራው ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅህ ሲችል ሌላ መሰላል መፈለግ ምን ይበጅሃል? ወይስ ክርስቶስ አይበቃም? ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝ አይደለምን? ወይስ እርሱም፣ እናቱም፣ ቅዱሳን መላእክትም፣ ጻድቃንም፣ ሰማዕታትም ተባብረው ያድናሉ? መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ሲመጣ፣ 'አንቺም፣ ልጅሽም፣ እኔም እናድናለን' ነው እንዴ ያላት? ምነው ታዲያ ጉባኤ ኒቅያ ስለ ማርያም አዳኝነት አላወራ? ጉባኤ ኤፌሶን ስለ አማላጅነቷ ምነው አልሰበከ? ጉባኤ ቍስጥንጥንያ ምነው ወደ እርሷ ስለ መጸለይ ተገቢነት አልተነተነ? ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያናችሁ ይህን መጤ አቋም ከየት አመጣችው? ጠይቀህ ታውቃለህ?

"ዙፋኑን ትቶ ከሰማይ የወረደልህ፣ መስቀል ላይ ዕርቃኑን የተሰቀለልህ፣ ነገም በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ የሚመጣው ማነው? ክርስቶስ ኢየሱስ አይደለምን? የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል እርሱ ነው፡፡ የቅድስት ማርያም በድንግልና መውለድ እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ሥጋዊ አባት፣ ከመንፈስ ቅዱስ መፀነሱን ማሳየት እንጂ ሌላ ትርጒም የለውም፡፡ አንተ ግን የኢየሱስን ጌትነት ከመናገር፣ የማርያምን እመቤትነት መናገር ይቀናሃል፡፡ ለእናቱ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠት ከወቀስከን፣ እኔም ለጌታ የመስቀል ሥራ ተገቢውን ትኩረት፣ ክብርና አምልኮ ባለመስጠት እወቅስሃለሁ፡፡ የሚያዋጣህን አንተው ዕወቅ!"

* * *

"ታዘሃል?" አለኝ አንድ አስተናጋጅ ድንገት ፊቴ ተጋርጦ፡፡ ድምፁ ከሩቅ የሚመጣ ይመስላል፤ አቤት ቁመት!

"እ?" አልኩ ከእንቅልፉ እንደ ባነነ ሰው፡፡

"ታዘሃል?" (ማማሰያ የዋጠ ይመስላል፤ ምናለ ጎንበስ ቢል?)

"ልታዘዝ ወይስ ልዘዝ?" አልኩት፤ ሣቂ መጥቷል፡፡

"እኮ እዘዘኛ"፤ ልዩነቱ አልገባውም ማለት ነው፡፡

"ነጣ ያለ ማኪያቶ፣ ያለ ስኳር ..." ተናግሬ ሳልጨርስ ረጅም ቁመቱን ይዞ ከፊቴ መሄድ ጀምሯል።

"መቋየቴ ካልቀረ!" በማለት አሰብኩና ሁሌ ከእጄ የማይጠፋውን ማስታወሻ ገላልጬ የሰማሁትን በፍጥነት መጻፍ ጀመርኩ።

* * *

"ለመሆኑ ከዚህ በኋላ ወዴት ነው የምትሄደው?" መነፅሩን አወለቀና ዐይኖቹን ጨመቃቸው፡፡

"ወደ ቸርች" ጣቶቹን እያንቋቋ መለሰ፡፡

"እኔም የምመጣው ከቤተስኪያን ነው፡፡ ታዲያ ቊርስ በልተህ፣ ቡና ጠጥተህ፣ አረፋፍደህ የምትሄደው ዕቁብ ነው ወይስ ዕድር? ቤተ እግዚአብሔር መሆኑ ቀረ? በማለዳ እህል በአፍህ ሳይዞር አይደል አምላክህን ፍለጋ መሄድ ያለብህ? ለ1700 ዓመታት ገደማ ይህ ሥርዐት ሥር በሰደደበትና ከሕዝቡ ጋር በተዋሐደበት አገር ባዕድ ሥርዐት መትከል ምን ይባላል? ያለውንና የነበረውን ይዛችሁ ብትቀጥሉ ምን ነበረበት? ጌታችንም በአይሁድ ምኵራብ ሰበከ እንጂ የራሱን ምኵራብ አልሠራም፡፡ ችግራችሁ የአስተምህሮ ነው የባህል? እናንተ ዘንድ የመጣ ባህሉን፣ ወጉን፣ ማንነቱን መጣልና መቀየር አለበት? ለምን?" ቈጣ ያለ ይመስላል፡፡

"የማታውቀው ታሪክ ሊኖር ይችላል፡፡ ወንጌልን የነገሩን ሚሲዮናውያን ሲመጡ የራሳቸውን ምኵራብ ለማቋቋም ወስነው አልነበረም፡፡ ከቀደመችው (ከአባቶቻችን) ቤተ ክርስቲያን ጋር ተባብሮ ለመሥራት ተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ ግን ማን ያቅርባቸው? በቀናነት ሊቀበላቸው የፈለገም ሆነ የደፈረ አልነበረም፡፡ እንዳይሰብኩ ተገፍተው፣ ተቃውሞ ደርሶባቸውና ተቸግረው ነው ወንጌል ወዳልደረሰበት ስፍራ ሄደው ወንጌልን የሰበኩት፡፡

"ሰዎች ሲድኑ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን መመሥረቷ እንደማይቀር ታውቃለህ፡፡ በእርግጥ ሚሲዮናውያኑ በአዲሶቹ አብያተ ክርስቲያናት ወደ እኛ ባህል ከመምጣት ይልቅ በአንዳንድ መልኩ ዐውዳዊነትን ዘንግተው የራሳቸውን አሠራር አጉልተዋል፤ ይህም እኛን ወደ እነርሱ ወስዶናል፡፡ ለወንጌል ያላቸውን ታማኝነትና ለባህል ያላቸውን የወረደ አቋም እንዳለ ተረከበናቸዋል፡፡ ጥፋቱ የእኛም ነው፤ የሰጡንን መቀበል እንጂ 'አሜን' ከማለታችን በፊት አልጠየቅንም፡፡ አሁንም ቢሆን ሳንጠይቅና ሳንጠየቅ 'አሜን' እንላለን፡፡ እናም ከበሮ (ድቤ) የአጋንንት ነው አሉን፤ ተውንላቸው፡፡ ጊታርና አኮርዲዮን ሰጡን፤ ከራርም ሆነ በገና ትዝ ሳይሉን ተቀበልን፡፡ የምንሠራው ቤተ ክርስቲያን ምን



ዐይነት ቅርጽ መያዝ እንዳለበት የነገሩን እነርሱ ናቸው፡፡ በአገራቸው በረዶ ሲያስቸግራቸው የሚሠሩትን የጣሪያ ቅርጽ እዚህ ፀሓያማ አገር መሥራት ያስተማሩበት ቦታም አለ፡፡ በዚህም ነባሩን የቤተ ክርስቲያን ጉልላት እንዳናይ ተከለልን፡፡ 'ለምን?' ብለን አልጠየቅንም፡፡ አየህ እኛም ጋ፣ 'አትመራመር ትቀሠፋለህ' የሚል ነገር ሳይኖር አይቀርም፤ ከእናንተ የተማርነው!" አለ በሚያሾፍ ፈገግታ፡፡

* * *

ስልኬን መዝጋት እንደ ነበረብኝ የገባኝ ንዝረቷ ሲያስደነግጠኝ ነው። ሁሌም እንዲህ ነኝ፤ ስልኪቱ ኪሴ ውስጥ ስትፈራገጥ ልቤም በድንጋጤ ፍርግጥ ይላል። የሚደረገውን አድርጌ አረጋጋኂትና ቀልቤን መለስኩ። ለእነርሱ እንጂ ለእርሷ የሚሆን ጆሮ ለጊዜው የለኝም።

* * *

"'እምና ለፋሲካ ሻማ ስናበራ አደርን' አላልከኝም?"

"ብዬሃለሁ! ቤተ ክርስቲያን ለነበርነው ሁሉ አንዳንድ ሻማ ታድሎን አብርተናል፡፡"

"እና የእኛ ሻማ ማብራት ምን ክፋት አለው? ጧፍንስ ለምን ትኰንናላችሁ? ከነባሩ ሥርዐት ጋር ጠባችሁ ምንድን ነው? ግእዙን ወዲያ ብላችሁ በየመድረኩ እንግሊዘኛ ትደነቅራላችሁ፤ ለአማርኛ እንግሊዘኛ ከግእዝ ይቀርባል? ልብሰ ተክህኖውን ንቃችሁ በሱፍና ከራቫት ትታነቃላችሁ፡፡ ቀሲስን፣ ካህንን፣ መጋቢን ጥላችሁ ፓስተርን ትጠቀማላችሁ፡፡ ሴቶቻችሁ እግዚአብሔር ቤት ሲሄዱ ነጠላ ከመልበስ በጂንስ ሱሪና ታይት ይወጠራሉ፡፡ ለክርስቲያናዊ መታሰቢያ በዓላት እንኳ የአገር ባህል ብትለብሱ ምናለ? ቢያንስ የሀገራችሁን ሸማኔ ትጠቅማላችሁ!

"እኛ በጥምቀትም ሆነ በሌሎች ሃይማኖታዊ በዓላት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እንይዛለን፡፡ እናንተስ? 'አገሬ በሰማይ ነው' በማለት ትደሰኩሩና በልባችሁ አሜሪካዊነትን ታልማላችሁ ..."

"እንዴ፣ ሰንደቅ ዓላማ የያዙት አይደሉ አሜሪካን ያጥለቀለቋት!?" አለ ያኛው ጣልቃ ገብቶ፡፡

"ምነው ጃል? አታቋርጠኛ!" አለ ጥያቄውን በእጁ ለማባረር የፈለገ ይመስል እጁን እያራገበ፡፡ "ኢትዮጵያ የኖረችው ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው በተጋደሉና በሞቱ አባቶች ደም ነው፡፡ እናንተ ግን ሁሉን አቀለላችሁት፡፡ ለባህል፣ ለሀገር፣ ለቋንቋ ግድ ያላችሁ አትመስሉም፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ንቅል ብለው

ጴንጤ ቢሆኑ፣ ኢትዮጵያዊ ማንነት ይኖር ይሆን? የሚል ሥጋት አንዳንዴ ሽው ይለኛል::" ከዚያም እንዴት ሽው እንደሚለው በእጁ ለማሳየት ሞከረና ቀጠለ::

"በዚህም ላይ ኢትዮጵያንም ሆነ ክርስትናን በኢትዮጵያ ላቈዩ አባቶች ክብር አትሰጡም:: ምድራችን በመካከለኛው ምሥራቅ እንደ ነበሩት የክርስትና ምንጮች በመሐመዳውያን ላለመጥለቅለቋ ምክንያቱ እናንተ ናችሁ? ኢየሩሳ ሌም፣ ቊስጥንጥንያ፣ አንጾኪያ፣ ግብፅ ... ዛሬ የት ናቸው?

"ለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስን ቅዱስ መጽሐፍነት፣ ምስጢረ ሥላሴን፣ ነገረ ሥጋዌን ... ለየትኛው ኢትዮጵያዊ ለማስተማር ደከማችሁ? ገና ስትነግሩት አባቶች ጠብቀው ስላቈዩት ያውቀዋል:: ለመሆኑ የትኛው የሥነ መለኮት ሰዋ ችሁ ነው ስለ ሥላሴ የነገረን? ነገረ ሥጋዌን በራሳችሁ አስተምህሮ እንኳ ስን ቶቹ አገልጋዮቻችሁ ያስተነትናሉ? በመካከላችሁ ካሉት ሐዋርያ ነን እያሉ ከሚ ለፍፉቱ አንዳንዶቹ፣ ክርስቶስ በምድር ላይ ሰው ብቻ ነበር በማለት የሚያስተ ምሩ መናፍቃን አይደሉምን? ለመሆኑ ፓስተር ከምትሏቸው መካከል ስንቶቹ የክርስትና መሠረት የሆነውን ነገረ ሥጋዌን ጠንቅቀው ያውቃሉ? የነገረ መለ ኮት ትምህርት ቤቶቻችሁስ ቢሆኑ ፈረንጅ የበላውን የሚያከኩ አይደሉምን? ሌላው ቀርቶ መጠሪያ ስሞችን እንኳ ዐውዳዊ ማድረግ ችለዋል? ለፈረንጅኛ ጥላቻ ኖሮኝ አይደለም፤ ለግሪኩ፣ ለዕብራይስጡና ለላቲኑ የመጀመሪያ ስያሜ አማርኛ (ግእዝ) ይቀርባል ወይስ እንግሊዝኛ? ብትፈልግ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚ ለውን አገርኛ መጠሪያ ከእንግሊዘኛው Jesus Christ ጋር በማነጻጸር ጀምር፤ ለግሪኩ የትኛው ይቀርባል?

"ለዚህ ሁሉ እንኳን ምስጋና አታቀርቡም:: ያለ መሬትና ያለ ዘር የበቀ ላችሁ፣ ያለ መሠረት የተገነባችሁ ይመስላችኋል:: በብዙ የሊቃውንት ትንታኔ የደለበ ትምህርት እኛ ዘንድ አለ፤ ልባም ሰው እርሱን ይጠቀማል:: እውን እናንተ እሳት ስታነዱ ማገዶ አላቀበልንም?!" ኦርቶዶክሳዊው በጣም ተጭኖ ነው የሚናገረው:: አሁንም አሁንም ከንፈሩን ይልሳል ("ከንፈሩ እንደ እኔ ቢተ ልቅ ኖሮ አንዴ ለማዳረስ ስንት ዙር መላስ ይኖርበት ነበር?" የሚል ሐሳብ አመለጠኝ)::

* * *

በእርግጥም ኢትዮጵያ ውስጥ ለተካሄደው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የሚያመሰግኑ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ኀልተው አልወ ጡም። እንዲያውም የለውጣቸውን ትክክለኛነት ለሰዎች ለማስረገጥ ይመስል ከዚያ የመጡቱ አክርረው ሲቃወሟት ይታያሉ። ስለ በጎ ኦርቶዶክሳዊ አስተዋ



ጽኦ የተናገሩ ጥቂት መጻሕፍት ግን አሉ። ከእነዚህም መካከል አንዱ የመጋቢ በቀለ ወ/ኪዳን ቀዳሚ መጽሐፍ አንዱ ነው፤

> ... [ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን] በበጎ ለመነሣትዋ ምክንያቱ ሪቫ ይቫል በወና ሁኔታ ውስጥ (in a state of vacuum) ተከስቶ አለማወቁ ነው። ዳራ ያስፈልገዋል። ከዳራዎቹም ቀዳሚው ዳራ የቤተ ክርስቲያን በስፍራው መኖር ነው። ... ጴንጠቆስጤአ ዊው ሪቫይቫል በኢትዮጵያ በተለኰሰ ጊዜ ከፍተኛውን ማገዶ ያበ ረከተችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። ... ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ ነበራቸው። እናቱ በድንግልና እንደ ወለደችው፣ ስለ አምላክቱና ስለ ሰውነቱ፣ ስለ ሞቱ፣ ስለ ትንሣኤውና ስለ ዳግም ምጽአቱ ያውቃሉ። ይህንን ዕውቀት የሰጠቻቸው ያደጉባት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት።"[1]

ማለዳ ሳነብ የነበረውን የፊሊፕ ያንሲን መጽሐፍ በሓሳቤ ገለጥኩ፤ እንዲህ ይላል፤ "ሌሎችን የክርስትና እምነት ክፍሎች ማመስገንም ተማርኩ። ስለ ጸሎት መጽሐፍ ስጽፍ ከካቶሊኮች የተማርኩት ከሌላ ከማንኛውም የእም ነት ክፍል ከተማርኩት ይበልጣል። ... በተመሳሳይ ሁኔታ ምስጢራትንና አክ ብሮታዊ ፍርሀትን ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተምሬአለሁ። በሙዚቃ፣ በአም ልኮ፣ በነገረ መለኮት ... ምስጢራትን አስተምረውኛል።"[2]

በእኛ አብያተ ክርስቲያናት ስለ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግ ነገር ሲነሣ ሰምቼ ባላውቅም፣ የካቶሊክ ምሁራን በነገረ መለኮት ትንታኔ የተለየ አስደናቂ ብቃትና ዕውቀት እንዳላቸው ግልጽ ነው። አለማግባት በሙሉ ልብ የጌታን ነገር ለማሰብ እንደሚረዳ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚናገረው (1ቆሮ. 8፥32-34) አለ ማግባታቸው አግዟቸው ይሆን?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ከሌሎች የምሥ ራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋር የማትመሳሰልባቸው በርካታ አስተ ምህሮዎች እንዳሏትም ዐውቃለሁ።

* * *

"እንደ ክርስቲያን እንኳ አትቈጥሩንም እኮ፤ ቤተ ክርስቲያናችንንም በቤተ ክርስቲያንነት መቀበል ይተናነቃችኋል:: ስማችንን እንኳ የምትጠቅሱት ለስብከት ማጣፈጫነት ብቻ ነው:: ከእናንተ በቀር ሌላ ክርስቲያን በምድር የለም! እንደምታምኑት ባለማመናችን መናፍቃን ትሉናላችሁ:: እንደ ቀዳሚ ቤተ ክርስቲያንነታችሁ በማቀፍ፣ በማበረታታትና በመምከር ፍቅርና ምሕረትን ልታሳዩን የሞከራችሁበት ጊዜ ነበር? መቼ? እኛን ማሳደድና ማሠቃየት ወንጌል መስበክ ይመስላችኋል:: በእናንተ እጅ ብዙ መከራ ተቀብለናል፤ ይህንን ከየት

ኛው ሐዋርያ ነው የተማራችሁት? እናንተ አሳዳጅ፣ እኛ ተሳዳጅ መሆናችን የአ ደባባይ ምስጢር ነው! ወንጌል መሆኑ ነው? ሰው ስለ ወንጌል ይሞታል እንጂ ይገድላል? 'ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ' የምትሉት ክርስትና ይሄ ነው?

"እኛን መናፍቅ የምትሉን የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ተመ ሥርታችሁ ነው? የክርስቶስን የመስቀል ሥራ ችላ ብላችሁ በሌላ መንገድ ለመ ዳን መፈለጋችሁ ሳያንስ፣ ሰው የሚድነው ኦርቶዶክስ በመሆን ብቻ ይመስላች ኋል:: ከድንግል ማርያም ተወልዶ የሥጋን ባሕርይ ከእርሷ የወሰደውና በመስ ቀል የሞተልን ጌታ አይደል የሚያድነው? ታዲያ መቼ ነው የእናንተ ቡድን አባል በመሆን መዳን የተጀመረው? በእናንተ ቤት ከእናንተ ውጭ ሌላው የጠፋ ነው! ይህ ወንጌል ሳይሆን ወንጀል ነው:: መዳን በክርስቶስ እንጂ በሃይ ማኖት አይደለም:: እውነት ነው አስደናቂ ታሪክ አላችሁ፤ ሆኖም ታሪክን ብቻ ታቅፋችሁ የቀራችሁ ይመስላል::" አለና ጸጥ አለ:: ቶሎ ቶሎ ስለሚያወራ ትን ፋሽ አጥሮት ንግግሩን እንዳቆመ አተነፋፈሱ ያሳብቃል::

ያኛው ከአፉ ተቀብሎ ቀጠለ፤ "እናንተም እኮ አሕዛብ ትሉናላችሁ፤ ማን እስራኤላዊ እንዳደረጋችሁ ባላውቅም! ሃይማኖት እንደሚያድንም መናገር ጀምራችኋል - በተግባራችሁ:: ሰው ኦርቶዶክስ ሆኖ፣ ካቶሊክ ሆኖ ጌታ ኢየሱስን አምኖ አይድንም ያለው የትኛው መጽሐፍ ነው? ጴንጤ የሆነ ብቻ ይድናል ያላችሁ ማነው? ጽድቅና ኩነኔ የአንድ ቡድን አባል በመሆንና ባለ መሆን ነው? ሰዎች በግላቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነትና ትሥ ሥር መታየት የለበትም?

"እኛን፣ 'በሥራ ይዳናል ይላሉ' በማለት ትነቅፉላችሁ፤ ከዚያሳ? ከሥራ የተነጠለ ምውት እምነት ማቀንቀናችሁ ሳያንስ እምነታችሁን እንደ ሥራ እየቈጠራችሁ ስትመኩ ትታያላችሁ! ጸጋው በእምነት የሚያድነው ማንም በሥራው እንዳይመካ ከሆነ (ኤፌ. 2፥8-9)፣ ታዲያ መመካትን ምን አመጣው? 'በእውነት አትድኑም፤ ጌታ ምስክር ነው አትድኑም' ስትሉን ሰምተናል:: የሚድ ነውንና የማይድነውን ማን ወሳኝ አ'ረጋችሁ? የሚያድነውን ወንጌል መንገር እንጂ ማዳን አትችሉም እኮ! ይልቅስ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ብትፈጽሙ ይበጃል::" አለና እንደ ማስጠንቀቅ ዐይነት ምልክት አሳየ::

"ወንጌላውያን አማኞች ለክርስትና ብዙ መልካም ነገሮችን አምጥታች ኋል፤ ከተኛንበት እንድንነቃና በከፋይ ሸፍነን የተንተራስነውን ቅዱስ መጽሐፍ እንድንገልጥ ምክንያት ሆናችሁናል:: ነጋድራስ ገብረ ሕይወት እንዳለው፣ 'ብዙ ቄሶች ሃይማኖታቸውን ሳያውቁ ይኖሩ ነበር፤ ጵሮቴስታንቶችና ካቶሊኮች ከመጡ ወዲህ ግን ትልቁም ትንሹም የወንጌልን ቃል ዐውቆ በትርጉሙ ይከራ



ከራል:: ካህናትም ባላንጣ ቢበዛባቸው ያስተምሩ ጀመር::'[3] ወንጌል እንዲሠራ ጭም አድርጋችኋል፤ ለዚህ ብድራታችሁን ራሱ ባለቤቱ ይከፈላችሁ:: ግን ደግሞ ጥፋታችሁም እየበዛ ነው:: ልቅነትን አስፋፍታችኋል:: ቤተ ክርስቲያንን ቈራርሳችሁና ከፋፍላችሁ የግል ሱቅ አስመስላችኋታል:: ሌላውን ትንቃላችሁ፤ ትኰንናላችሁ፤ ካለ እናንተ ሰው እንደሌለ በመቍጠር ትታበያላችሁ:: ከእና ንተ ውጭ እውነት እንደሌለ ትቈጥራላችሁ:: እውነት ከእናንተ በረት ውጭ ጌታ ሌላ መንጋ የለውም? ይህንን መሪዎቻችሁን ጠይቅልኝ::

"እኛን መቍጠሪያና ሥዕል ይዞ በመጸለይ ጉዳይ ትተቹናላችሁ፤ የእና ንተ ሰዎች ግን 'የጸጋ መገናጸፊያ' በማለት ጨርቅ እየታቀፉ ሲጸልዩ እንዳላየ ታልፋላችሁ:: እኛን በጠበል ጉዳይ ትተቻላችሁ፤ ቲቢ ጆሽዋ የተጸለየበት ውሃ በጠርሙስ እያሸገ ሲቸበችብ ግን ዝም ትላላችሁ:: ችግራችሁ ከስም ጋር ከሆነ፣ በኢየሱስ፣ በመድኅኔ ዓለም፣ በአማኑኤልና በሥላሴ ስም ያሉ ጠበሎችን ትቀበላላችሁ ማለት ነው? ወይስ የእርሱ የቧንቧ፣ የእኛ ደግሞ የጒድጓድ ውሃ ስለሆነ ነው? ወይስ ቲ ቢ ጆሽዋ አይወክላችሁም?

"ለመሆኑ ዕልፍ ቦታ ተዘነጣጥላችሁ ማነው የሚወክላችሁ? እያንዳ ንዱ እየተነሣ፣ 'ጌታ ሠራዊት አስነሣልኝ ብሎኛል' ይላል:: ሲያስነሣ ያየነው ግን አራዊትን ነው፤ አንዱ የእናንተ ሰው ተናገረው ሲባል እንደ ሰማሁት::" ይህን ተናግሮ ነጠላውን አስተካከለና ከቅምጡ ሳይነሣ ተንጠራራ::

"እዚህ ጋ ነገሩ ለእኔም ግልጽ አይደለም" አለ ወንጌላዊው:: "'ባለ ራእይ ነኝ' የሚሉ ግለ ሰቦች በየጊዜው የተለያዩ ኪዮስክ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቋቁሙ እናያለን:: ወንጌልን (ኢየሱስን) እየሰበኩ እና በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቁ፣ ሰዎችን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ከማድረግ የተለየ ራእይ አለ ይሆን? ለዚያውም ደቀ መዛሙርትን ሲያፈሩ አናያቸውም:: ድርጊቱ መብያ ሰበብና ራስን ማግነኛ ዘዴ ነው:: ሊበሉ ያሰቧትን አሞራ ...::"

* * *

ሌላ አስተናጋጅ ማኪያቶዬን ይዛ መጣች:: "ነጸ ያለ ማኪያቶ አይደል ያዘ ዝከው?"

"ነጸ ያለ ሳይሆን ነጣ ያለ ነው ያልኩት::"

"ምን ልዩነት አለው?" በሚል አስተያየት አየችኝ::

"ነጸ ያለ ማለት ንጹሕ ማለት ነው:: ሁሉም ንጹሕ አይደል የምትሰ ጡን:: ነጣ ያለ ማለት ግን ..." ምኗ ከውካዋ ናት? እርሷም አስቀምጣልኝ ሄዳለች::

* * *

"ድንጋዩን ዳቦ እንዲያደርግ ሲጠየቅ እምቢ ያለውን ጌታ ነው አይደል የምታምኑት? ለመብል ያላችሁ ስሜት ግን ከፍተኛ ነው፤ ዓርብ ሮብ ትበላላችሁ:: ሚሲዮናውያኑም እንዲሁ ነበሩ:: ለመሆኑ *ዲዳኬን* አንብበሃል? የሐዋርያትን አስተምህሮ የያዘ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረ ባለ 16 ምዕራፍ ጽሑፍ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ከመጠረዙ በፊት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ስትጠቀምበት ቈይታለች:: ጽሑፉ ዓርብ ሮብ እንድንጾም ያዛል፤ ያኔ አባቶችም ይጾሙ ነበርና:: ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በፊት ገደማ የተጀመረ ጾም ነው::

"ሥራ ላይ ብትሆኑ እንኳ ከፊለ ጾም ማካሄድ ትችላላችሁ:: ሥጋንና የወተት ተዋፅኦን መተው ከአጽዋማት አንደኛው ነው፤ ዳንኤል የጾመው ዐይነት (ዳን. 10፥2-3):: እናንተ ግን የጾሙ ዐይነት በእኛ ስለሚዘወተር ብቻ ትንቁታላችሁ:: ከዚያም፣ 'አምሮብናል በቤትህ' እያላችሁ ትዘምራላችሁ:: ድሮስ ዓርብ ሮብ እየበላችሁ ላያምርባችሁ ነው?

"በጾም ቀናት የኦርቶዶክሳዊ የሥራ ባልደረቦቻችሁን ስሜት ለመጠበቅ ስትሉ እንኳ አትጠነቀቁም:: 'ወንድሜ ከሚሰናከል ለዘላለም ሥጋ አልብላ' ብሎ ለመፎከር ግን ማን ይቀድማችኋል? ለጌታ ብላችሁ አንድ የምትወዱትን ነገር መተው ብትችሉ ጾም እንደሚባል አታውቁም? 'ይህ ነገር እስኪፈጸምልኝ ድረስ ዐልጋ ላይ አልተኛም' ብላችሁ መሬት ብትተኙ ጾም አይደለም? ሻይ ትወዳለህ እንበል፤ እርሱን ለተወሰነ ጊዜ ብትተወው ጾም አይባልም? ሆኖም አለመጾማችሁ ሳያንስ ዓርብ ሮብ በሚጾም ሰው ትሳለቃላችሁ:: ዓርብ ሮብ የሚጾም ሰው አይድንም? ያ ሰው የሚጾመው ወንጌል ገብቶት ይሁን አይሁን ማጣራቱ የሚበጅ ይመስለኛል::

"በእርግጥ የትኛውም መንፈሳዊ ነገር በተደጋጋሚ ሲደረግ ልማድ የሚሆንበትና መንፈሳዊ ትርጕሙን የሚያጣበት አደጋ አለ! ነገር ግን ለዚህ ብለን አንተወውም:: ቤተ ክርስቲያን መሄድን፣ መባና ምፅዋት መስጠትን፣ ቋሚ የጸሎት መርሐ ግብሮችን በዚህ ምክንያት አንተዋቸውም አይደል? ታዲያ ጾም ከእነዚህ በምን ይለያል?" አለ ያንን ረጅም አፍንጫውን እየነካካ::

ባለ ኮቱ በመስማማት ጭንቅላቱን ነቀነቀና መናገር ጀመረ፤ "ለነገሩማ ጆን ዌስሊም ለተወሰነ ጊዜ ደረቅ ዳቦ ብቻ በመብላት ይጾም ነበር::[4] አለማወቃችን እንጂ ችግሩ ጾሙ ላይ አይደለም:: እናንተ የማትቀበሉት ጾም እኛም አለን፤ ለምግብ ከፍተኛ ትኩረት የምንሰጥ የሚመስላችሁ ይህንን ስለማታውቁ ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን በየጊዜው ጾም ስታውጅ እንጾማለን፤ ጥቂት የማይባሉ አብያተ ክርስቲያናትም በየሳምንቱ የጾም ጸሎት ፕሮግራም አላቸው:: በተ



ለይ የጳጕሜ ወር በእኛ ዘንድ በጾም ወርነት ተቀባይነት እያገኘች ነው:: በተጨማሪም እያንዳንዱ አማኝ በሚፈልገው ጕዳይ ላይ በጾም በጸሎት በአምላኩ ፊት የሚሆንባቸው ወቅቶች አሉ፤ አብያተ ክርስቲያናታችንም ይህን ያበረታታሉ" አለ በአጭሩ::

ያኛው ግን አልለቀቀውም:: "ይህ መልካም ቢሆንም፣ እናንተ የእኛ የሆነውን ሁሉ የምትጠሉ ነው የሚመስለው:: ሌላው ቀርቶ ሰዎቻችሁ ሰው በዐንገቱ ክር አሥሮ ሲያዩ እንዴት እንደሚሆኑ አስተውያለሁ:: ክሩን ሊበጥሱለት እጃቸውን ይሰድዳሉ፤ ግን ለምን? ክር ማሰር ክርስቲያንነታችንን ለመግለጽ የምንጠቀምበት እንጂ ክርስቲያን የምንሆንበት አይደለም እኮ! እስቲ ከሰሙህ ንገራቸው::"

* * *

በዐንገቴ ጥቍር ክር ሲያዩ ሊቈጡ የሚቃጣቸውን ሰዎች አስታወስኩ። የክርስቶስ መሆን የሥርዐት ጕዳይ ሆነ እንዴ? እነርሱ ከጥቍር ክር የተሠራ የዐንገት ልብስ ለብሰው እያየን፣ ሌላው ጥቍር ክር ሲያስር ያንቀጠቅጣቸዋል። እንኳን ክር አሥሮ፣ ጀለቢያም ለብሶ የክርስቶስ መሆን እንደሚቻል ማን በነገራቸው?!

* * *

"የመጀመሪያዎቹ ጥቂት መቶ ዓመታት ታሪክ የጋራ ታሪካችን ነው:: ያኔ በማርያምና[5] በሌሎች ሐዋርያት ስም የተሰየሙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ:: ሆኖም ዛሬ በማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን መሰየምን ልታደርጉት ቀርቶ ልትሰሙት እንደማትፈልጉ ዐውቃለሁ:: ግን ለምን?

"ለቤተ ክርስቲያን ስያሜ በተወሰኑ ቃላትና ሐረጋት ላይ ትሻማላችሁ:: አንዱ የወንጌል ብርሃን ሲል፣ ሌላኛው ብርሃነ ወንጌል ይላል:: አንዱ የሕይወት ብርሃን፣ ሌላኛው ብርሃነ ሕይወት ይላል:: እነዚህ ተመሳሳይ ስያሜዎች መሆናቸው ሳይገባችሁ ቀርቶ ነው? በቅርቡም FBI የተሰኘ የቤተ ክርስቲያን ስያሜ አሰምታችሁናል፤ CIA እና KGB ለተባሉትስ ምን ያህል እንጠብቅ? ምርጦቹ 7000ም ትላላችሁ፤ 144,000ውስ ለምን ተረሱ? ቈይ ግን፣ አንድ ምዕመን ሲጨመር ምርጦቹ 7001፣ ሲጐድል ደግሞ ምርጦቹ 6999 እየሆነ ስሙ ይታደሳል?

"ይልቅስ የአባቶችን ስም በስያሜነት ለምን አትጠቀሙም? በሐዋርያቱ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስና ማቴዎስ፣ በወንጌላውያኑ ሉቃስ፣ ማርቆስ ... በአባቶች ፖሊካርጵ፣ አትናቴዎስ፣ አርጌንስ (Origen)፣ አውግስጢኖስ (Augestine) ስም ቤተ ክርስቲያናችሁን ብትሰይሙ ምናለ? ልጆቻችሁን ስለ እነዚህ ሰዎች ለማስ

ተማር ጥሩ መንገድ አይመስላችሁም? ... 'እነማን ናቸው?' ሲሏችሁ፣ ዝርዝሩን ትነግሯቸዋላችሁ! የአትናቴዎስን የሃይማኖት መግለጫ ታውቁታላችሁ፤ ለዚያ መለኮታዊ እውነት፣ ለሥላሴ አስተምህሮ ምን ያህል ዋጋ እንደ ከፈለም ሳታውቁ አትቀሩም:: ታዲያ ስሙን ለምን ጠላችሁት? ያለ ሉተር ሰውም ያለ አይመስላችሁ?! ለነገሩ ሰሞኑን ኤጳፍራ የሚል ቤተ ክርስቲያን ሊከፈት መሆኑን በየስልክ እንጨቱ ከተለጠፈ ፖስተር አይቻለሁ:: በፓስተሮቻችሁ ስም የተሰየሙ አብያተ ክርስቲያናትን በቅርቡ እንደምታሳዩን ግን አልጠራጠርም፤ ሰው የግል ንብረቱን በስሙ መሰየም ይችላላ!" አለ ሁለት እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ፤ ንግግሩን ግን አላቋረጠም::

"ኦርቶዶክሳዊ ክርስትናን የሚተቹ ሰዎቻችሁ ሲሻቸው እንደ እኛ ቄሶች ናቸው፤ ከክርስትና መሠረታዊ አስተምህሮ ውጭ በማስተማር ይዘባርቃሉ:: አንዳንዶች ሁለት ክርስቶስ ያለ ይመስል፣ 'በአምላክነቱ እንዲህ አደረገ፤ በሰውነቱ ደግሞ እንዲህ አደረገ' በማለት ስለ ክርስቶስ ያስተምራሉ:: ክርስቶስ በሰውነቱና በአምላክነቱ በፈረቃ ነበር የሚሠራው? ይህ እናንተ እንኳ በምትቀበሉት ጉባኤ ኬልቄዶን የተወገዘ አቋም አይደለምን? እናንተን ምን እንበላችሁ? በመሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮ እንኳ ስሙም ያይደላችሁ ጉዶች ናችሁ! የአባቶችን መሠረት፤ የኒቅያን፣ የኤፌሶንን፣ የቊስጥንጥንያን ውሳኔ እንኳ በሚገባ ሳያውቁ የሚዘላብዱና ነባሩን መሠረት አደባይተው ሌላ መሠረት ለማስቀመጥ የሚታትሩ ርጉማን አገልጋዮች መካከላችሁ ሞልተዋል:: ሌላውን ከመንቀፋችሁ በፊት ራሳችሁን ከእነዚህ መናፍቃን አጥሩ!" ፊቱንና መላጣውን ደባብሶ ዝም አለ (የፊቱ ድንበር አብቅቶ መላጣው የሚጀምረው የት ጋ ይሆን?)::

* * *

ሣቅ ሰምቼ ዘወር ስል በረንዳው ላይ ሌሎች ሰዎችን አየሁ:: መች ይሆን የመጡት? እኔም ይህን ያህል ተመስጬ ነበር ማለት ነው? ሰዎቹ የስንት ዘመኑን ሙግት በአንድ ቀን ጨርሰው ለማደር ሳይፈልጉ አልቀረም፤ አይ ወጣትነት! በጊዜ ሒሳቤን ዘግቼ ብሄድ ነው የሚሻለው:: ሒሳብ መጠየቂያውን ወረቀት ላይ፣ "ቲፕ ስትሰጥ ከ10 በመቶ አታሳንስ" የምትለኝ የፍቅር ጓደኛዬ ትዝ አለችኝ:: የምጠየቀው ሒሳብ እስከ 10 ብር ሲሆን የዚህች ፈረንጅ መሳይ ጓደኛዬን ምክር ኵራ ብዬ እፈጽማለሁ (ያኔ ስታየኝ ደስ ይለኛል)፤ ሒሳቡ ከዚያ ሲበልጥ ግን ...

* * *

"በዋሻና በገዳም የሚኖሩትን ባሕታውያንንም አትናቁ:: ችግሩ ታሪክን ያለ ማወቅ ነው:: ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ክርስትናን ሲቀበልና ክርስትና የመንግ



ሥት ሃይማኖት ሲሆን፣ ክርስትና መበላሸት ጀመረ፤ ተበረዘ:: በርካቶች ንጉሡ የመረጠውን ሃይማኖት ለመከተል ሲሉ ብቻ እውነቱ ሳይገባቸው ግር ብለው ከመቅደስ ገቡ፤ 'እንደ ንጉሡ አጐንብሱ' መሆኑ ነው! ከዚያም ነገሥታት በቤተ ክርስቲያን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ጀመሩ:: ሕይወት ዘቀጠ፤ የስም ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ቤት ሹመኛ ሆኑ::

"ያኔ የክርስትናን መዓዛ ለማስጠበቅና ዓለማዊ ጳጳሳትን ለመቃወም ምናኔ ተጀመረ! ስደት በመቅረቱ ምናኔ አዲስ ሰማዕትነት ሆነ:: ሐሳቡም ከዓለም ሕይወት ተለይቶ ለእግዚአብሔር በጸሎትና በአምልኮ መጠመድ ነው:: ጌታስ፣ 'ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድኾች ስጥና ተከተለኝ' ብሎ የለ? ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ ደናግላንና መበለቶች ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ አላዘዘምን? ሐዋርያት የዓለም ፍጻሜ እጅግ ቅርብ እንደ ሆነ ያሳስቡስ አልነበረም? ታዲያ ዓለምን ንቆ ገዳም መግባት ምን ይገርማል? ገዳም መሠረቱ ክርስትናን ከብርዘት ለመከላከል የተደረገ ውጤታማ ጥረት ነው:: የቤተ ክርስቲያን አባቶችም - እነ ቅዱስ አርጌንስ፣ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ... መናንያን ነበሩ::" ድንገት ሁለቴ አከታታሎ አነጠሰ ("ይማርህ" ልበለው ይሆን?)::

ያኛው ግን ጊዜ አላባከነም፤ ገና ድሮ መናገር ጀምሯል፤ "እንዴ በየገዳማቱ ስንት ጉድ እንዳለ ሳታውቅ ቀርተህ ነው? በእርግጥ መነሻው ጥሩ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ሰው ከከተማ በመሸሸ ከዓለም መሸሽ ይችላል? 'ዓለምን ናቅናት' በማለት ሄደው አይደል እንዴ በልባቸው እንደ ታቀፏት ሜካ የሚገኙት? እውነቱን እንነጋገር ከተባለማ፣ ከውጭው ያልተናነሰ ነውር ነው እዚያ የሚፈጸመው፤ ያውም 'ለነፍሳችን አድረናል' በሚሉ ሰዎች::"

በአንድ ትንፋሽ ነው ንግግሩን የተወጣው:: አየሩን በኀይል ሳበ፤ ጠጕሩን አከክ አከክ አደረገና አቀማመጡን ለማስተካከል ሞከረ:: አስተያየቱ "በል ተናገራ!" የሚል መልእክት እያስተላለፈ ነው::

ባለተራው፣ "አስጨርሰኝ እንጂ" የሚል ይመስላል፤ "በአገራችንም የግራኝ አሕመድ ወረራ ክርስትናን ሙሉ በሙሉ ከምድራችን እንዳያጠፋ ማድረግ የተቻለው ዋሻዎችና ገዳማት በመኖራቸው ነው:: ብዙ መጻሕፍትንና ንዋየ ቅድሳትን እዚያ ሸሽገን አትርፈናል:: በእርግጥ ግራኝ በግፍ ከጨፈጨፋቸው ቀሳውስትና ሊቃውንት የተነሣ ቤተ ክርስቲያናችን ያኔ ከደረሰባት ዘግናኝ ጉዳት አሁንም አላገገመችም:: ከዚያ በኋላ የአገልጋዮች እጥረት ስለ ተፈጠረ ፍትሐ ነገሥት እንደሚለው፣ 'ብሉይ ኪዳንን ከዐዲስ ኪዳን አስማምቶ፣ ታሪክን ጠብቆ፣ ምስጢርን ገልጦ የሚያስተምር' ካህን ማግኘት አልተቻለም::" አለና ተረጋግቶ ማስረዳት ቀጠለ::

"እናም ታምረ ማርያምን ያነበነበን ሁሉ ቄስ ማድረግ ተጀመረ፤ 'ብሉይ ኪዳንን አዋድዶ፣ ዐዲስ ኪዳንን አመሳጥሮ' ማስተማሩ ቀረ:: ታዲያ ዘመነኞቹ ቀሳውስት መጽሐፍ ቅዱስን ችላ ቢሉ ምን ይገርማል? የማያውቁትን መጽሐፍ እንዴት ያስተምሩ? የሃይማኖታችን መሠረት የሆነው መጽሐፍ 'ሃይማኖተ አበው' ከእነርሱ የተነሣ ተዘነጋ:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የተፈተነና የነጠረ ብዙ እውነት አላት፤ የገድላት ደለል ተመርገውበት ምንም የሌላት መስየነጠረ ገድላትለች እንጂ:: አሁን የቅዱሱ ቃልና የአባቶች ትምህርት ተቃራኒ በሆኑ ገድላት ተወርረናል! እነዚህን ገድላት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማስተያየት ጥያቄ ሲቀርብ፣ ለውግዘት ይነሣሉ:: እንደ ግሪክ አማልክት ተረቶች (mythology)፣ የገድላቱን ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ ብቻ ማየት፣ ወይም መነቃቃትንና መጽናናትን ብቻ የሚያመጡ ድርሳናት መሆናቸውን እንጂ በንፍኀ መለኮት እንዳልተጻፉ መቀበል መፍትሔ ይሆናል" አለ ኦርቶዶክሳዊው በቊጭት::

ወንጌላዊው ቀበል አድርጎ ቀጠለ፤ "ዋናው ችግርማ እርሱ ነው:: እናንተም የአባቶችን መሠረት ችላ ብላችኋል:: ነገረ ክርስቶስን ስለ ማስተንተን ትነግረኛለህ፤ ነገር ግን ያወገዛችኋቸው አውጣኪያውያን (ደቂቀ አውጣኪ) የሊቃውንት ጉባዔያችሁ መካከል ሠርገው እንደ ገቡ ይታወቃል:: ለዚህም ነው የግሪኩን ጥንታዊ መጽሐፍ ቅዱስ ሰራርዛችሁና ደላልዛችሁ፣ ጥቅሶችን እንደ ልባችሁ ቀያይራችሁ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ስታሳትሙ ያየነው:: ለመሆኑ እርሱ መጽሐፍ ነገረ ክርስቶስ ላይ ምን ያህል እንደ ተበላሸ ታውቅ ይሆን?

"የቅዱስ አትናቴዎስ ተከታዮች መሆናችሁን ትናገራላችሁ፤ ቅዱስ አትናቴዎስ ስድሳ ስድስቱን መጻሕፍት ብቻ ሲቀበል፣ እናንተ ግን ከስድሳ ስድስቱ ውጭ እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ መጻሕፍት ሰብስባችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጨምራችሁ አትማችኋል:: 'እናቴ እስክንድርያ፣ አባቴ ማርቆስ' ትላላችሁ፤ ነገር ግን የእስክንድሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸውን ወንጌልን የሚቃረን ሐሳብ ያላቸው፣ በሰዋሰብ አገባብ፣ በታሪክ ፍሰት፣ በምሳሌያዊና በመልከዐ ምድራዊ አገላለጽ ሳይቀር የተፋለሱና የተዘበራረቁ መጻሕፍትን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዶላችኋል:: ለስሙ 'ሰብአ ሊቃናት'ን ተረጕምን በማለት፣ አይሁዳውያን እንኳ የማይቀበሏቸውንና ሰብአ ሊቃናት ውስጥ የሌሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ከእናት ቋንቋቸው ውጭ እየደረሳችሁ፣ 'ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው' ትላላችሁ፤ ያውም መጻሕፍቱ ሰማንያ አንድ አይደሉም እኮ! ሊቃውንታችሁ ሕዝቡ ትክክለኛውን ቃለ እግዚአብሔር እንዳያገኝ ደብቀው፣ ወደ እውነት እንዳይደርስ ዐይኑን ሸፍነው ለጥፋትና ለሞት እያዘጋጁት ነው::[6] አንድዬ ለሕዝቡ ካልራራ ድርጊታቸው አሥጊና አስፈሪ ነው::" ፊቱ ላይ ኀዘን ገጥላት ጀምሯል፤ ድምፁ ዝቅ ቢልም ንግግሩን አላቋረጠም::



"እንዲህም ሆኖ ግን የእናንተ ቀሳውስት ከውይይት፣ ከመረዳትና ከማስረዳት ይልቅ ሲጠየቁ ውግዘት ይቀናቸዋል:: ከመድኀኔ ዓለም ይልቅ ገብርኤልን ይፈራሉ፤ ሚካኤልን ያከብራሉ፣ በጊዮርጊስ ይመካሉ፤ ... አንድዬን፣ የነፍሳቸውን ዋስትና በመላእክት፣ በሰማዕታትና በቅዱሳን ከልለውታል:: ክርስቶስ ወደ አብ ሊያቀርበን ሰው ሆኖ መጥቶ፣ 'ወደ እኔ ቅረቡ' ብሎ እየተጣራ ወደ እርሱ በመቅረብ ፈንታ ሌላ መካከለኛ ፍለጋ መባዘን ምን ይረባናል? በእውነቱ፣ ጽድቅ ከክርስቶስ በቀር በሌሎች የሚገኝ ከሆነ፣ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ (ገላ. 2፥21)!

"የመስቀሉን ሥራ ተረት አድርጋችሁ፣ የገድል ተረታችሁን እውነት አድርጋችሁ ታወራላችሁ:: መስቀል የተገኘበትን ቀን በድምቀት እያከበራችሁ፣ የጌታን የመስቀል ሥራ ችላ ብላችኋል:: ለመሆኑ ገድሉ ከቅዱሱ መጽሐፍ ጋር ሲጋጭ የትኛውን ነው የምታምኑት? ገድሎች ሕዝበ ክርስቲያኑን ገደል ከተቱት እኮ! በእውነት ጌታ እጁን እንዲዘረጋላችሁ እንጸልይላችኋለን::

"ሆኖም ዛሬ ባላችሁበት ቦታ ብቻ መታየት የለባችሁም:: ቤተ ክርስቲያኒቱም ዕድሜያም ናትና የዛሬ መድከማችሁና ከእውነቱ ፈቀቅ ማለታችሁ ብቻ አይደለም ሙሉው ገጽታ:: ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ጌታቸውን በከዱ ደቀ መዛሙርት መሆኑን አንዘነጋም::[7] እስቲ ጳውሎስንና ጴጥሮስን ተመልከቱ:: ጴጥሮስ ጌታውን ሦስቴ ከዷል፤ ጳውሎስም በክርስቲያኖች ላይ የተካሄደውን የመጀመሪያ ስደት መርቷል:: የእግዚአብሔር ጸጋ እነዚህን ሁለቱን ሰዎች ዐቅፎ ነው ቤተ ክርስቲያን የታነጸችውና የተስፋፋችው::[8] እናንተንም እግዚአብሔር ሊያስባችሁና ፊቱን ሊመልስላችሁ ይችላል:: አይዞህ፤ ከሁሉ መጻሕፍት ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን ትኵረት ሰጥቶ ማንበብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቂያው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን አለመዘንጋት፣ ወደ እውነቱም ለመድረስ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ነው ወሳኙ ነገር! ያለ እግዚአብሔር ጸጋ ማንም ምንም አይደለም!"

ያቆላለፋቸውን እግሮቹን ሲያቀያይር ጠረጴዛውን ስለ ገጨው ዳር ላይ የነበረው ባዶ የለስላሳ ጠርሙስ መሬት ተንከባለለ:: በእጆቹ ለማስቀረት ከመሞከር ይልቅ በዐይኑ ይዞ ለማስቀረት የሚሞክር ይመስላል፤ ደግነቱ አልተሰበረም:: ግራና ቀኝ በድንጋጤ ሙልከት አደረገና በዝግታ አንሥቶ ጠረጴዛው መኻል ገፋ አድርጎ አስቀመጠው::

"ልክ ነህ" አለ ኦርቶዶክሳዊው፤ ጠርሙሱን አስተካክሎ እስኪጨርስ ጠበቀውና:: ዐይኖቹ ቅዝዝ ብለዋል፤ "ንግግርህ ትክክል ነው፤ ያለ ጸጋው ዋጋ የለንም:: ሥራችንማ እኛንስ መች ያረካና! እግዚአብሔር ቢያቆመን በጸጋው

እንቆማለን፡፡ ጸጋውንም በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ገልጦልናል፡፡ ድሮም ሆነ ዛሬ በአብ ፊት የሚቆምልን ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ይህንንም አባ ጊዮርጊስ በመጽሐፈ ሰዓታት ድርሰቱ 'እግዚአብሔር በተከላት በምስክር ድንኳን ለቅዱሳን የሚቆምላቸው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው' በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለሙ ሁሉ ፍጹም መሥዋዕትን ያቀረበ ዘላለማዊ ሊቀ ካህን መሆኑን ተናግሯል፡፡[9] ቅዱስ ቄርሎስም የክርስቶስን ከአብ ጋር አስታራቂነት በሃይማኖተ አበው ላይ ይናገራል፤ 'እርሱ ለራሱ ልመናን የሚሻ መስሎ ከጥንት ጀምሮ ያገኘንን ፍዳ ከእኛ ያርቅ ዘንድ አብን ማለደው፤ እንደገና ደግሞ እንዲያስበን፣ ከእርሱም እንዳይለየን ስለ እኛ አብን ይማልደው ዘንድ ባሕርያችንን ነሥቷልና' (ሃይ. አበው ዘቄርሎስ ፸፱ ከ፶፥፴፫)፡፡ አባቶቻችንም ይህንን ያውቁና ያምኑ ነበር ማለት ነው፡፡ ሥላሴያውያን መሆናችንንም አትዘንጉ፡፡ አንዱ ጌታ የሁላችንም ጌታ ነው፤ ስለዚህ ወንድማማቾች ነን፡፡ የጠፋው ልጅ ወደ ቤቱ ሲመለስ እንደ ታላቅ ወንድሙ እንዳትሆኑ እናንተም አስቡበት …"

* * *

“'ወንድማማቾች ነን' ነው ያለው? እኮ የአንድ አባት ልጆች? ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ትውስ አለኝ፡፡

> ነጋድራስ ገብረ ሕይወት በብርቱ ታሞ ሳለ … *ሥጋ* አምላክ ለመቀበል ፈልጎ ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህናት አስታውቆ ቈርቦ ኖሮ፣ በኋላም ወደ ድሬዳዋ ከመጣ ወዲህ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልኮ ሁለተኛ ስለ ቈረበ፣ ያስታምመው የነበረው ወዳጁ … “ወንድሜ ሆይ ምነው ይሄን ማድረግህ?” ብሎ ቢጠይቀው “እኔ ሃይማኖቴ ኦርቶዶክስ ነው፤ ጅቡቲ የወረድኩ ጊዜ በሽታዬ ስለ በረታ ምናልባት የሞትኩ እንደ ሆነ ቈርቤ ልሙት በማለት የኦርቶዶክስም ቤተ ክርስቲያን ጅቡቲ ስላልነበረ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቍርባን የተቀበልኩት ስለዚህ ነው፡፡ ጥቂት ተሽሎኝ ድሬዳዋ ከመጣሁም ከዚያው ከእኛው ቤተ ክርስቲያን አስመጥቼ [*ሥጋ* ወደሙ] ተቀበልኩ፡፡ ከማናቸውስ ብቀበል ምን የሚያስደንቅህ ነገር አለ? እኔ የምሻው ያድነኛል ብዬ [የማምንበትን] የኢየሱስ ክርስቶስን *ሥጋ* ብቻ ነው፡፡ *ሥጋ* ቤቶቹ ቢለያዩ *ሥጋው* ያው የክርስቶስ ነውና የምሻውን አግኝቻለሁ፤ ሌላውን ከትልቅ ነገር አልቈጥረውም” አለው ይባላል፡፡[10]

በእርግጥ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ይህን ሲሉ ካቶሊካውያንና ኦርቶዶክሳውያን በቅዱስ ቍርባን አስተምህሯቸው ተቀራራቢ በመሆናቸውም ጭምር እንደ ሆነ እስባለሁ፡፡ ሆኖም እኔም አንድ እሑድ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ግሪክና አርመን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሄጄ አምልኮ ተካፍዬ ስወጣ አቤት የተሰማኝ ደስታና እርካታ! በዚህም ላይ ለቅዱስ ቍርባን ያላቸው አክብሮት በብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ያላየሁት ነው፡፡



*ታዲያ* ልዩነታችንን የምናውቀውን ያህል አንድ ለሚያደርጉን ጉዳዮች ትኩረት የማንሰጠው ለምንድን ነው? አንድ ኮሜድያን፣ “የስሜን አየርላንድ ሰዎችን በእግዚአብሔር መኖር እንደማላምን ነገርኳቸው፡፡ ያኔ አንዲት ሴት ከጉባኤው ተነሣችና፣ 'እሺ፤ ግን በካቶሊኮች እግዚአብሔር ነው ወይስ በፕሮቴስታንቶች እግዚአብሔር መኖር ነው የማታምነው?' በማለት ጠየቀችኝ” እያለ ይቀልዳል፡፡[11] የተለያየ እግዚአብሔር ነው እንዴ ያለን? ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ እና ወንጌላውያን ክርስቲያኖች *ሥላሴያውያን* አይደለን? *ሥላሴያውያን* በሙሉ አንድ አምላክ ነው ያላቸው፡፡ ሰው ለመዳን በነገር ሁሉ ወንጌላውያን ክርስቲያኖችንም ሆነ ኦርቶዶክሳውያንን መምሰል አይጠበቅበትም፤ ጌታ ኢየሱስ ለኀጢአቱ እንደ ሞተለት ቢያምን ይድናል፡፡ መሪኮታችን ለክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ እንዴት እንደ ተመቸው እንዳይታየን ማን አዚም አደረገብን?

አንድ ወንጌላዊና አንድ ኦርቶዶክሳዊ አማኝ በመደማመጥ ይህን ሁሉ መነጋገራቸውን ብናገር ማን ያምነኛል? በሰላምና በመከባበር መወያየት ብርቅ እንደ ሆነብንስ እስከ መቼ ይቀጥላል? መናበብና ማንበብስ ለምን አቃተን? ይህንን እያሰላሰልኩ ገጾቹ ያለቁትን አነስተኛ ማስታወሻዬን አጥፌ ኪሴ ከተትኩ፡፡ ከዚያም ማኪያቶ የጠጣሁበት አፌን ተጉመጥመጥኩና ከካፌው ወጣሁ (አንድ ያለኝ መልክ ጥርሴ ስለሆነ በጥንቃቄ ነው የምጠብቀው)፡፡ ታክሲ መያዣው ጋ ስደርስ ነጠላ የለበሱ ምዕመናንና አንድ ቄስ ታዩኝ፡፡ ጠጕራቸውን ጄል የተቀቡ ባለሙሉ ልብስ ፓስተሮችም እጅብ ብለዋል፡፡ ቄሱ ፓስተሮቹን ሳያውቋቸው አልቀሩም፤ እንዳይረክሱ የሚጠነቀቁ ይመስል ፊንጠር ብለው ይገላምጧቸዋል፡፡ ጥቂት እንደ ቆየን አንድ ታክሲ መጣና ካህኑ አጠገብ ቆመ፡፡ ካህኑ ሊገቡ ሲሉ ከኋላ የነበሩት ወጣት ፓስተሮች ተሽቀዳድመው ገቡ፡፡ (ለአገልግሎት ቸኩለው ይሆን?)

ሌላ ታክሲ ሲመጣ ቄሱን አስቀድሜ ለመከተል በማሰብ አጠገባቸው ቆምኩ (ባናግራቸው መስቀል አውጥተው እንዲያሳልሙኝ በር መክፈት ይሆን?)፡፡ “አባ፣ አይጋፉም እንዴ? አሊያኮ እዚሁ ሊውሉ ነው”፤ እንደ ምንም ደፈር ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡ ትክ ብለው በፈገግታ አዩኝና በእርጋታ መለሱልኝ፤ “ቀሚሴ አይፈቅድልኝም!”

የተከታተልኩት ውይይትና ድርጊት ተጭኖኛል፤ ሁለቱም ወገኖች የጌታን *ሥጋ* የራሳቸው ብቻ ለማድረግ የሚፈልጉ፣ ሌላውን ግን የሚያከላ

ክሉ ሥጋ ቤቶችን ይመስላሉ። ሆኖም የክርስቶስ ኢየሱስን ወደ አብ መድረሻ ብቸኛ መንገድነት መጽሐፉ በግልጽ ይናገራል። ለጥቂት ደቂቃዎች ጉዳዩን ሳወጣ ሳወርድ ቈየሁና ተመልሼ ወደ ቤቴ ማዝገም ጀመርኩ። በዚህም ላይ ሐሳቦቼ ሳይበታተኑብኝ መልክ አስይዤ እንዴት እንደምጽፍ አሳሰቦኛል ...

## ማስታወሻ


1. በቀለ ወ/ኪዳን፤ *ሪቫይቫል፣ ኢትዮጵያ እና የመጨረሻው መጨረሻ* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም) ገጽ 63።
2. Philip Yancey, *What Good Is God? In Search of a Faith that Matters* (New York: Faith Words, 2010), 134.
3. *ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች* (አዲስ አበባ፤ አአዩ ፕሬስ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 27።
4. Arthur Wallis, *God's Chosen Fast* (Fort Washington, PA: CLC Publication, 2007), 25.
5. Alister McGrath, *The Christian Theology Reader, 3rd ed.* (Oxford: Blackwell Publishers, 2007), 277.
6. በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሁለት ጠቃሚ መጻሕፍት አሉ። ቀሲስ ደረጀ ገ.፤ *ገመና ዘ8፡6* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም) እና ቴዎድሮስ ደመላሽ፤ *ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን* (አዲስ አበባ፣ 2004 ዓ.ም)። የመጀመሪያው፣ በተለምዶ "ሰማንያ አሐዱ" ስለሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ በመረጃ የተደገፉ አስደንጋጭ እውነታዎችን የያዘ አንቂ መጽሐፍ ነው። ይህን "መጽሐፍ ቅዱስ" ማሳተምና ማሠራጨት የእግዚአብሔርን ቃል ንጽሕና የሚበርዝ የጥፋት ተግባር ሆኖ ሳለ ይህ የቤተ ክርስቲያኒቷና የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ድርጊት ግራ እንደሚያጋባ መጽሐፉ ያስረዳል። ሁለተኛው ደግሞ፣ ይህንኑ እውነታ በሰከነ መልኩ ያስረዳል።
7. Philip Yancey, *Soul Survivor: How My Faith Survived the Church* (London: Hodder, 2003), 273.
8. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 275።
9. ቀሲስ ተስፋ እንዳለ፤ *ነገረ ሥጋዌ* (አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2001 ዓ.ም) ገጽ 65።
10. ራስ እምሩ ኀ/ሥላሴ፤ *ካየሁት ከማስታውሰው* (አዲስ አበባ፣ አአዩ ፕሬስ፣ 2001 ዓ.ም) ገጽ 89-90።
11. Lee Strobel, *The Case For Faith* (Michigan: Zondervan, 2000), 155.




# የሸለቆ ጩኸት

ትናንት ብዙ ተስፋ፣ ብዙ ጉጉት፣ ብዙ ናፍቆት ነበረኝ። ወይን ጠጅ እንደ ተሞላ አቁማዳ ተወጥሬ መፈንዳት ሲፈታተነኝ ነበር። ተስፋና ደስታ ምርኩዞቼ ነበሩ። ካልተሳሳትኩ ተስፋው እረፍት ነሥቶኝ እንደ ነበር ትዝ ትዝ ይለኛል። ትናንቴ ውስጥ ነገ እየታየኝ ብርቱ እንደ ነበርኩ አስታውሳለሁ። የምሄድበትን መንገድ ዐውቃለሁ፤ የዕለት ተዕለት እርምጃዬን በኩራት የምራመደው መጨረሻው ስለሚታየኝ ነበር። ለምን ሰው ሁሉ እንደ'ኔ እንደማይታደልና እንደማይጠነክርም ጥያቄ ነበረኝ።

ዛሬ ግን፤ ዛሬዬ ውስጥ ትናንትን አጣሁት። ዕውን ይህ "ዛሬ" የትናንቱ ነው? ትናንቴ ውስጥ ያየሁት ዛሬ ከዛሬው ዛሬ ጋር ምኑ ይመሳሰላል? የሆነበት መንገድ ስቼ እንጂ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የምሄድበት ይቅርና የምረግጠው መሬት ግራ የሚገባኝ ለምንድን ነው ታዲያ? እንደ ተኰነነ ሰው እያንዳንዱን እርምጃዬን እየተጠራጠርኩ እንዴት እኖራለሁ?

ምንኛ ጎስቋላና ምስኪን ሰው ነኝ! ከገባሁበት ዋሻ ማን ያወጣኛል? አገባቤ ላይ በደስታና በተስፋ ተሞልቼ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ታዲያ አሁን እንዴት ልውጣ? ዐውቃለሁ፤ ዋሻው መውጫ ይኖረዋል። ግን እንዴት ልወቀው? በድፍረት አንዱን መንገድ እንዳልመርጥ ፈሪ ሆኛለሁ፤ የለየልኝ በቅቧቃ። የድሮ ልበ ሙሉነቴን በሚስተካከል መልኩ ልበ ሥሥ ሆኜ ራሴን አግኝቼዋለሁ። ለነገሩ ከዋሻው ብወጣስ ምንድን ነው የማገኘው? ሐሳቡ ራሱ ሲያስፈራ! ተስፋን እንዳልናፈቅሁት፣ ተስፋ ማድረግን ፈራሁት! ለካ ተስፋ ማድረግ አድካሚም ይሆናል። ተስፋ መቍረጥን ተስፋ የማደርግበት ቦታ ደርሼ ይሆን?

እሺ ለማን ልንገር?! ለነገሩማ የምነግረው ሰው አያስፈልገኝም! እዚያው ዋሻው ውስጥ ተቀምጬ ለግድግዳውና ለወለሉ አወራለሁ። ዋሻውን እየለመድኩትና እየወደድኩት መጣሁ ልበል? በዚህ ላይ ብዙ ርቄ ሄጃለሁ፤ ገና ለገና ዛሬ ፈተና ገጠመኝና እንዴት ወደ ኋላ እመለከታለሁ? ዋሻውስ ቢሆን ዋሻነትን መርጦ አልተሠራ፤ ዕጣ ክፍሉ ሆኖ እንጂ! ታዲያ ለእርሱስ ማን አለው? ቢያንስ ትንፋሼ እንኳ ያሙቀው እንጂ! ደ'ሞ እኮ ያለኝን ሕይወት ሁሉ ታቅፌ ነው ውስጡ የገባሁት። ያንን ትቼ መውጣት አይሆንልኝም፤ አላደርገውም፤ በጭራሽ!

ሕይወትን ግን ፈራኋት፤ መኖርን ጠረጠርኩት፤ ከፉኛ ሠጋሁ! እኔ እኔን አልሆንኩም፡፡ ምናልባት ሁሉ ሰው የሚሰበርበት ቦታ እያጣውምና እዚያ እየደረስኩ ይሆን? ወደ ራሴ ቀራንዮ!? አዎን የራሴ ኢየሩሳሌም ከነበረኝ፣ የራሴ ጎልጎታም ግድ ነው!

እያንዳንዱ ሰው የየራሱን መስቀል መሸከም አለበትና አይቀርልኝም፡፡ ለጊዜው ጌቴሴማኒ ደርሻለሁ፡፡ መስቀሌን እንዳልተወው በፍቅር ተለውሷል፤ ታዲያ እንዴት እተወዋለሁ!? "ጌታ ሆይ ይህች ጽዋ ከእኔ አትለፍ፤ ዐቅም ስጠኝ እንጂ፣ ጸጋህ ይርዳኝ እንጂ፣ ጽዋዋን ከእኔ አትውሰዳት! ትናንት ላይ ሆኜ ለዛሬ ያየሁትን፣ ለዛሬ ያለምኩትን ብርሃን ጭላንጭሉን ብቻ አሳየኝ፡፡ መኖሩን ልወቅ፤ እባክህ! እርሱን ለአፍታም ቢሆን ማየት ከታደልኩ ዓመት እጓዛለሁ፡፡ ከዚያ ሲያቅተኝ እንደገና ማየት ይሻለኛል፡፡ ይህንን የምለው ፈቃድህ መሆኑን የተረዳሁ መስሎኝ ነው፡፡" ግን ሣቄ ይመለስ ይሆን?

ማዕበሉን፣ "ጸጥ በል" የሚለው ትእዛዛዊ ድምፅ ናፈቀኝ፡፡ ለትንሣኤ አልጓጓሁም፤ እርሱ አይቀሬ ነው (እኔን ለመሞት ያብቃኝ እንጂ!) አሁን መሻቴ የማዕበሉ ጸጥ መሰኘት ብቻ ነው! በዋሻ ውስጥ ማዕበል? እንዴት እችለዋለሁ? ከልክ ያለፈ ነገር እየጠየቅሁ ይሆን!?"

"እግዚአብሔር ሆይ፤ መድኀኒትህን እጠብቃለሁ" (ዘፍ. 49፥18)፡፡



# ስላልተመለሱ ጸሎቶቼ አመሰግንሃለሁ!

ለእርሱ የመጀመሪያው ናት፤ እርሷ ግን ከእርሱ በፊት ሌሎችን ታውቃለች፡፡ በዕድሜ 8 ዓመት ስለምትበልጠው ከዕድሜው በላይ ትልቅ ለመምሰል (እርሷ ላይ ለመድረስ) ታግሏል፤ ቤተ ሰቦቹና ጓደኞቹ ውሳኔውን እንዲቀበሉለትም ጥሯል፡፡ ከዚያም ግንኙነታቸው ወደ ጋብቻ እንዲመጣ አቅደው መነጋገር፣ መጾምና መጸለይ ቀጠሉ፡፡

እርሱ፣ "ተጋብተን፣ ሳንወልድ እንማር" የሚል ሐሳብ ያቀርባል፤ የእርሷ አቋም ደግሞ፣ "ቅድሚያ ለልጅ" ነው (ሁለቱም 12ኛ ክፍል ጨርሰው ነው የተቀመጡት)፡፡ አንድ ጊዜ ከአሜሪካ ኤምባሲ ይዛ የመጣችውን የጕዞ ወረቀት ይዞ፣ "ከእኔና ከዚህ ወረቀት ማን ይበልጥብሻል? 'አትሂጂ' ብልሽ ትቀሪያለሽ?" የሚል "የልጅ ጥያቄ" ጠይቋት እንደ ነበር ያስታውሳል፡፡ "እንዴ! አሜሪካ እኮ ነው!" ነበር መልሷ፡፡ የዚያን ቀን፣ "እንዴት ለአፏ እንኳን ሌላ መልስ አልሰጠችኝም?" በማለት በልቡ ነገር ያዘ፡፡

አብረው ስለሚጸልዩ ስለ ነገ ብዙ የተስፋ ቃል እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ሆኖም የ6 ዓመት ተራርቆ መኖር የራሱን ጫና ይዞ መጣ፡፡ ሁለቱም በያሉበት ልባቸው ተከፈለ፡፡ እርሱ ከዚህ በፊት ያላነሣቸው ጥያቄዎች አሁን ልቡን እየጎተቱት ይንሸራተት ጀመር፡፡ እርሱ ሳያውቅ እርሷ ጋ ይደርሱ የነበሩ አሉባልታዎችም ልቧን ይሸረሽሩት ገቡ፡፡ ስለዚህ ድንገት ደውላ ከዚህ በኋላ አብረው እንደማይቀጥሉ አሳወቀችው፡፡ ከዚያም፣ "ሚዜአችን ይሆናል" በማለት ያስተዋወቀችውን ሰው እዚያው ማግባቷን ሰማ፡፡ ያ ሁሉ ጸሎት፣ ያ ሁሉ ተስፋ፣ ያ ሁሉ እንባና እግዚአብሔርን በመጠበቅ ያለፈ 6 ዓመት ውሃ በላው (ተመልሶ አይገኝ ነገር!)፡፡ ይህ ወጣት ከዚያን ጊዜ በኋላ እንዴት ይጸልይ? ሕይወቱ ከመሠረቱ ተናጠ፡፡ ጾም የሚባል ነገርማ መስማት ጠልቶ መሸሽ ጀመረ ("በሉም በረቱም" የሚለውን ጥቅስ መመሪያው አደረገ)፡፡ የጸሎት ሕይወቱ ከሥሩ ተናግቶበታልና ከስንት አንዴ ቢጸልይም፣ "በቀኝ አውለኝ፤ ሽረኛንና ምቀኛን ያዝልኝ!" ከማለት አይዘልም፡፡ "ለምን?" ብሎ የሚጠይቀው፣ "ምን ዋጋ አለው?" የሚል መልስ ያገኛል፡፡

የማይመለሱ ጸሎቶች አሉ ማለት ነው፡፡ ጸሎት ምላሽ ስለማያገኙባቸው ምክንያቶች መጽሐፍ ቅዱስም ይነግረናል፡፡ አንዳንዶቹ ተለይተው የሚታወቁ ችግሮች ናቸውና አንድ በአንድ ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ

ከእኛ አእምሮ በላይ የሆኑ ምክንያቶችም አይጠፉም፤ በጸሎት ጉዳይ ሁላ ችንም ለማጆች ነንና!

## የተሳሳቱ ጸሎቶች እና ኀጢአት

አዲስ ኪዳን በቀጥታ ለጌታ ኢየሱስ የቀረቡ የሞኝ ጥያቄዎችን ይነግረናል:: ሙሴና ኤልያስ ድንገት በደብረ ታቦር ተራራ ላይ በመገለጣቸው የተደነቀው ጴጥሮስ ለሁለቱ ነቢያትና ለኢየሱስ ዳስ ለመሥራት ጠይቆ ነበር፤ አልተሳካም:: ደቀ መዛሙርቱ ያዕቆብና ዮሐንስ በምኞት ከተዋጠች እናታቸው ጋር በመሆን ጌታ ኢየሱስ በመንግሥቱ ዋነኛ ስፍራ እንዲይዝላቸው ጥያቄ አቅርበው ነበር:: "የምትለምኑትን አታውቁም" በማለት ገሠጻቸው (ማቴ. 20፥20-22):: ይህን የተናገረው መልእክቱን በመሳታቸው በማዘን ሳይሆን አይቀርም:: እነዚሁ በቀለኛ ወንድማማቾች ሰማርያ ላይ እሳት ለማውረድም ጠይቀዋል፤ ይህንንም ተከለከሉ እንጂ (ሉቃ. 9፥54-55)::

እነኚህን መሳይ ጸሎቶች ለራስ ጥቅም ብቻ የታሰቡና ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር የሚጋጩ ናቸው:: በእግዚአብሔር ነገሮች ላይ ሳይሆን፣ በእኛ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ:: ቅዱስ ያዕቆብ ኋላ ላይ፣ "ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁና" የሚለው ለዚህ ነው (ያዕ. 4፥3 - አ.መ.ት)::

ከኀጢአታችን የተነሣ ጸሎታችን የሚከለከልበት ወቅትም ይኖራል (መዝ. 66፥17-18):: የጋብቻ ቃል ኪዳንን (በዝሙትና በፍቺ) ማፍረስ ጸሎታችን በእግዚአብሔር ጆሮ እንዳይደርስ ያደርጋል (ሚል. 2፥12-16):: ሐዋርያው ጴጥሮስም ጸሎታችሁ እንዳይከለከል ሚስቶቻችሁን አክብሩ በማለት ይመክራል (1ጴጥ. 3፥7):: ይቅር ያለ ማለትም ሌላኛው ጸሎታችንን የሚከለክል ሳንካ ነው (ማር. 11፥25):: ስደተኛን መጨቆን፣ ምግብን ለተራብ መስሰትና መጠለያ መከልከል (ኢሳ. 1፥15)፣ ለሠራተኞች ተገቢውን ደሞዝ አለመክፈልና ለችግረኞች አለማዘን (ኢሳ. 58፥3-9)፣ የጸሎት ጠሮች ናቸው:: ስለዚህም ምሳሌ 21፥13 "የድኻውን ጸሎት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው፣ እርሱ ራሱ ይጮኻል አይሰማለትምም" ይለናል:: ገጣሚው እንዳለው፣

> "በሰፈሩት ቁና ..." እንዳይሆን ነገሩ፣
> ይሰማህ ወንድሜ ያሳቤ ምስጢሩ፣
> አቤት ባይ ሲመጣ -
>         ይቅር ላለማለት ጆሮህን እንዳትሰጥ፣
> በርህን ስትዘጋ ጥሪው ውጪ ሲቀልጥ፣
> አቤት ባይ ስትሆን ድምጥህ እንይቋረጥ::[1]



ጸሎቶች ሁሉ የማይመለሱት የተሳሳቱ ስለ ሆኑ ወይም በኀጢአት ምክንያት ነው ብሎ ማጠቃለል ግን አይቻልም::

## ጸሎት ወዲህ፣ ተግባር ወዲያ

አንዳንዴ ጸሎታችን ምላሽ የማያገኘው ተግባራችን የጸሎታችን ተቃራኒ ስለሚሆን ነው:: ለምሳሌ፣ ትምህርቱን የማያጠና ተማሪ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ለማምጣት የጸለየው ጸሎት ምላሽ ባያገኝ ምን ይገርማል? ለጤንነቱ የሚጸልይ ነገር ግን ስኳር፣ ጨውና ጮማ ለመቀነስ (ለመተው)፣ አትክልት ለማዘውተር፣ የሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴ ለማድረግና ክብደት ለመቀነስ ዝግጁ ያልሆነ ሰው ጸሎትም ተመሳሳይ ዕጣ ሊገጥመው ይችላል (ወደ ሠላሳዎቹ ከገባሁ ጀምሮ ይህ ያሳሰበኝ ጀምሯል):: ጥሩ የትዳር ሕይወት የሚሻ፣ ነገር ግን ሚስቱን ለመከባከብ፣ ለማስደነቅና ለማስደሰት ምንም ጥረት የማያደርግ፣ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ለሚኖረው ግንኙነት ገደብ የማያበጅ ሰው፣ እንዲሁም ልጆቹ ጥሩ እንዲሆኑለት እየናፈቀ ልጆቹን የማያቀርብና አብሯቸው ጊዜ የማያሳልፍ፣ በኑሮው ምሳሌ የማይሆናቸው፣ ሲያጠፉ ለመቅጣት የሚሳሳ ወይም በጭከና የሚቀጣ ሰው አንድ ናቸው፤ ድርጊታቸው የጸሎታቸው ባላንጣ ነው:: ጸሎት ከድርጊት ጋር መጣጣም አለበት:: በዕውቀት ለማደግ የሚጸልይ ሰውም የተለያዩ መጻሕፍትን ማንበብ፣ ዜና መከታተል (ኢቴቪን አላልኩም) እና በሐሳብ ከሚለዩት ሰዎች ጋር ውይይት ማካሄድ የማይመቸው ከሆነ በመጸለይ ባይደክም ይመረጣል::

ሰውየው እግዚአብሔር "ከጠጅ እስራት" እንዲገላግለው ይጸልያል:: ጠዋት ተነሥቶ ወደ ጠጅ ቤት እያመራ፣ "እባክህን ወደዚያ ብሄድም ጠጅ ቤት እንዳልገባ ዕርዳኝ" ብሎ ጸለየ:: ጠጅ ቤቱ ደርሶ እየገባ፣ "ጠጅ እንዳላዝ አግዘኝ" ሆነ ጸሎቱ:: ጠጅ ቤት ገብቶ ካዘዘ በኋላ ደግሞ፣ "እንዳልጠጣ ጠብቀኝ" አደረገው ጸሎቱ፤ (መጨረሻውን እናንተው ገምቱ!):: በተለያዩ ጉዳዮች ተመሳሳይ ሁኔታ የሚያሳልፉ ሰዎችም አሉ:: የጸሎትና የድርጊት ልዩነት፣

> ውሃው እንዳይፈስ ጸልያለሁ
> ቧንቧውን ግን ከፍቼያለሁ::
> ውሃው እንዲፈስ ጸልያለሁ
> ቧንቧውን ግን ዘግቼያለሁ::[2]

እንዳለው ነው ገጣሚው::

## ከወተት ወደ ዐጥንት

"እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን፣ ኀይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፤ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፤ አይደክሙም" (ኢሳ. 40 31 - አ.መ.ት)

የክርስትና ሕይወት ከልጅነት ቢጀምርም ወደ ዐዋቂነት፣ ከወተት ወደ ዐጥንት የሚደረግ የዕድገት ጉዞ ነው:: ከላይ ያነበብነው ምንባብ ላይ ያለው ቅደም ተከተል ግን የተዛነፈ ይመስላል:: ከእርምጃ ወደ ሩጫ፣ ከዚያም ወደ መብረር መምጣት ሲገባው፣ ከበረራ ወደ እርምጃ የኋሊት ነው የሚመጣው::

ሆኖም ትክክለኛው የመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞ ይኸው ነው:: የልጅነት ወራት ጸሎታችን ሁሉ (ትንሹም ትልቁም) በቀላሉ መልስ የሚያገኝበት፣ በደስታ የምንንሳፈፍበትና እንደ ንስር የምንበርበት ነው፤ መሬት አይነካንም:: ሥጋት የለብንም:: ለጥቆም ልጅነታችንን እየሻርን ወደ መሮጥ እንመጣለን፤ አሁን ግን የመታከት ሥጋት ይኖራል:: ከዚያም በእግዚአብሔር ቤት እየኖርን፣ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ስንመጣ ሕይወታችን እየተለወጠ መምጣቱ አይቀርም:: ዕድገታችን እየጨመረ፣ ፍላጎታችን እየተቀየረ፣ ዕይታችን እየጠለቀ ይመጣል:: ያኔ የምንፈልገውን ሁሉ ላንፈልግ - ብንፈልግም ላናገኝ እንችላለን፤ ከመሮጥ ወደ መራመድ አድገናል ማለት ነው (መራመድ እስከንለምድ ይዘነው የነበረውን እጁን የሰማዩ አባታችን ይሰበስበው ይሆን?):: አሁን አንድ ምዕራፍ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ደርሰናል:: ስለዚህ ስንራመድ ላለመድከም የእግዚአብሔርን ጸጋ እንጠይቃለን::

መንፈሳዊ ብስለት ይኸው ነው:: የምንፈልገውን ብዙ ጊዜ አናገኝም፤ ሆኖም እግዚአብሔርን መከተልም አናቆምም:: ዶ/ር አር ኢ አ ኋይት እንደሚናገሩት፣ "ከሚጠይቅና ከሚያገኝ እምነት የሚበልጥ በሳል እምነት አለ፤ ይኸውም የሚጠይቅና ሳያገኝ ሲቀር በትዕግሥት የሚጓዝ ነው:: ... በሳል እምነት በጸሎት መልሶች አይኖርም፤ በጸሎት እንጂ::"[3]

በዚህ ወቅት ምናልባት የሚያቆመን ብቸኛ ነገር እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ "ጌታ ሆይ፤ ወደ ማን እንሄዳለን?" የሚለው መሄጃ የማጣት ስሜት ሊሆን ይችላል (በዚህ ብቻ የቆምኩባቸው ቀኖቼን አስታውሳለሁ):: በእውነት ከኢየሱስ ወዴት ይኬዳል? ጸሎቴ አልተመለሰልኝም ብለው የሚተዉት አምላክስ ነውን?

## ክልከላ ወይስ መዘግየት?

አንዳንዴ ደግሞ ጸሎታችን የተከለከለ የሚመስለን ካሰብነው ጊዜ ስለ ዘገየብን ብቻ ነው:: ስለዚህ ለምን እንደምንጸልይ ሳይገባን መጸለያችንን እንቀጥል ይሆናል:: ምናልባት አንድ የአገራችን ኀምቱ ፖለቲከኛ እንዳሉት፣ ኀይለኛነታችንን መግሪያም ሊሆን ይችላል::[4] የምንጸልይበት ጉዳይ ባይለወጥም ጸሎታችን ቢያንስ እኛን ይለውጠናል:: ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር የጸሎት መልስን ጨምሮ የተለያዩ የእግዚአብሔር በረከቶች በራሳቸው ፍጻሜ አለመሆናቸውን ነው::

> የእግዚአብሔር በረከቶች በራሳቸው ፍጻሜዎች አይደሉም:: እግዚአብሔር እኛን ወደ እርሱ ለመሳብ የሚጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው:: ... እግዚአብሔርን፣ ሊያደርግልን በሚችለው ነገር ሳይሆን በራሱ ማንነት እስከንወደው ድረስ፣ ወይም አንድ ሰው እንዳለው፣ እጆቹን ሳይሆን ፊቱን እስከንፈልግ ድረስ፣ በረከቱን ያዝ ያደርገው ይሆናል:: እግዚአብሔር፣ ከእርሱ ስጦታዎች ይልቅ የእርሱን ኅብረት የሚመኘውን እምነት ያከብራል::[5]

ዐቅማችን ሳይጎለብት የምናገኛቸው ነገሮች ይጎዱን ይሆናል:: እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ የሚሰጠን ነገር ከእኛ የመቀበልና በአግባቡ የመያዝ ዐቅም ሊበልጥ ይችላል:: በቅድሚያ ዐቅማችን ሊጎለብት ይገባል:: ስለዚህ ጆርጅ ማትሰን እንዳለው፣ "የጠፋውን ልጅ ይመስል፣ የሚደርሰኝን ድርሻ ሁሉ *በአንድ ጊዜ* ማግኘት የምፈልግ ነኝ፤ ካልተሰጠኝ ደግሞ የተከለከልኩ ይመስለኛል:: እናም ጌታዬ ሆይ፤ የዘገዩ መልሶችህን ውበት አስተምረኝ"ብለን መጸለይ ያስፈልገናል::[6] ጸሎት ነገሮችን ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ማየት ነውና::

የጸሎት መዘግየት ሁሌም በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ ሆነን እንድንኖር የሚያግዝበት ሁኔታም አይጠፋም:: አንድ በመጠጥ ሱስ የተቸገረ ሰው፣ የመጠጥ ጥማቱ እንዲወገድለት በየቀኑ ሲጸልይ እንደ ነበር ይናገራል:: ሆኖም ሁል ጊዜም ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነቃ መጀመሪያ የሚያስበው የለመደውን ውስኪ ነው:: "አንድ ቀን ግን የመጠጥ ፍላጎቴ በየቀኑ እንድጸልይ ምክንያት እንደ ሆነኝ አስተዋልኩ:: ድካሜ ወደ እግዚአብሔር እንድቀርብ አደረገኝ" ብሏል::[7]

## ጸሎት ሁሉ ይመለሳል?

ደጋግሜ ካየኋቸው ኮሜዲ ፊልሞች አንዱ "Bruce Almighty" ነው:: ብሩስ (ጂም ኬሪ) በኑሮው እጅግ ይማረራል:: በሥራ ቦታው ደስተኛ አይደለም:: መንገድ ላይ ዱርዬዎች ይተነኩሱታል:: ውሻው የሳሎኑ ሶፋ ሥር ካልሆነ ሽንቱ አይመጣትለትም:: ስለዚህ ሁሌም እግዚአብሔርን እንዳማረረ ነው፤ "እርሱ ቢፈልግ ኖሮ ሕይወቴን በ5 ደቂቃ ማስተካከል ይችላል" እያለ ያጉተመትማል::

በዚህ መካከል አንድ ቀን እግዚአብሔር፣ "በል ለትንሽ ጊዜ ዓለምን አንተ አስተዳድራት" በማለት ሥልጣኑን ሰጥቶት ይሄዳል፤ ከአንዳንድ ገደቦች ጋር። ያኔ ብሩስ "ዓለምን እንዲያስተዳድር" የተሰጠውን ሥልጣን ተጠቅሞ የግል ፍላጎቱን ይፈጽማል፤ የወደደውን ሁሉ ያደርጋል። በየጊዜው የሚፈታተኑትን የመንገድ ላይ ወንበዴዎችና የሚያስቸግሩትን የቢሮ ሠራተኞች ልክ ያገባቸዋል። ውሻው ሽንት ቤት መቀመጫ ላይ ተቀምጦ ይጸዳዳል። ኧረ ከዚያም ዐልፎ ጋዜጣ እያነበበ መጸዳዳት ሁሉ ይጀምራል። ብሩስ ከፍቅር ጓደኛው ጋር ለፍቅር የሚመች "ሙድ" ለመፍጠር ሲል ጨረቃንና ከዋክብትን ወደ ቤቱ በረንዳ ቀረብ ያደርጋቸዋል፤ በዚህም ዳፋ ጃፓንን ማዕበልና በወጀብ ይመታታል።

ብሩስ የሰዎችን ጸሎት አንድ በአንድ እያዳመጠ ለመመለስ ሞከረ፤ አንዱን ጥያቄ ሳይመልስ እልፍ ጸሎቶች በላይ በላይ ይጨመራሉ። በመልከ በመልኩ እየተሰደሩ በማኅደር እንዲቀርቡለት አደረገ፤ ብዛቱን የሚቋቋመው አልሆነም። ስለዚህ የሁሉም ጸሎት እንዲመለስ በጥቅሉ በእሺታ ፈቀደ (ከ"select all" በኋላ "ok"ን ጠቅ አደረገ)። ያኔ ወንዶች ቁመታቸው ረዘመ፤ ሴቶች ጡታቸውና ሌላ ነገራቸው መጠኑ በተመኙት መልኩ ተስተካከለ። ሎተሪ እንዲያሸንፉ ይጸልዩ የነበሩ 400,000 ሰዎች ሁሉ አንዱን ዕጣ ስላሸነፉ የሎተሪ ድርጅቱ ካዝና ባዶ ሆነ።

ለመሆኑ በዚህች ምድር ሳለን ጸሎታችን ሁሉ ይመለሳልን? ጸሎት ሁሉ መልስ የሚያገኝበት ዓለምስ ምን ይመስላል? አላውቅም (መነፅር ለማድረግ የማልገደድበት እንደሚሆን ግን ተስፋ አደርጋለሁ!)። ጸሎታችን ሁሉ ተመልሶና የምንፈልገውን ሁሉ አግኝተን ብንኖር፣ ሕይወት ምን ትመስል ይሆን? ጣዕም ይኖራታልን? ዛሬ ለነገ ስንጸልይ፣ ነገ ደግሞ የትናንቱን ጸሎት ጠልተን ሌላ ስንጸልይ መገኘታችን እውነት አይደለምን? ሌላው ቢቀር ለትዳር የጸለይ ነው ጸሎት ሁሉ መልስ ቢያገኝ የስንት ሰው የትዳር ጓደኛ እንሆን ነበር!?

ጸሎታችንስ ምን ይመስላል? አንድ ጊዜ በአንድ ጉባዔ የተነገረ የትንቢት መልእክት ልጥቀስ። በዚያ ጉባዔ ለነበረ ራሰ በራ ሰው ነው መልእክቱ የመጣው፤ "መቼ ነው ጠጉሬ የሚበቅለው?" እያለ መጸለዩንና መጨነቁን ትቶ ለሕይወቱ የሚጠቅመው ጸሎት እንዲጀምር የሚመክር ተግሣጽ ነው የተነገረው። ጸሎት ሁሉ አዎንታዊ ምላሽ የሚያገኝ ቢሆን ጸሎታችን ምን ይመስል ነበር? ቁመታችንን፣ የቆዳችንን ቀለም፣ የአፍንጫችንንና የዐይናችንን መጠን፣ የአነጋገር ዘይቤአችንን የማንወድ ሰዎች ምን ብለን እንጸልያለን? (የወገባቸው "ሞባይል" የሚያሳስባቸው እኅቶች ግን የሚበጃቸው አጭር "ፓትሌት" ያለውን ሱሪ መተው እንጂ ጸሎት አይደለም!) ጸሎታችን ሁሌም አንደኛ ዕጣ ሎተሪ እንዲወጣልን፣ ትምህርት ቤት ሰቃይ እንድንሆን፣ በየመሥሪያ ቤቱ እልቅና እንድናገኝ፣ ገበያ እንዲደራልን፣ ከሰው በላይ እንዲያውለን፣ የምንገባበትን ውድድር በአንደኝነት እንድናሸንፍ፣ ተከለ ቁመናችንና ቅርጻችን እንዲያምር፣ ጠጉራችን ዞማ እንዲሆንና ብዛት እንዲኖረው ... ይሆን ነበር አይደል!? ታዲያ ከጸሎት መካከል የሚመለስና የማይመለስ መኖሩ ምክንያታዊ አይመስላችሁም!?



ሁሉም ጸሎታችን የሚመለስ ከሆነ፣ ዓለምን እኛ እንደ ወደድን እንድናስተዳድር እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጥቶናል ማለት ነው። በተፈቀደልን ትንሽ ኀይል እንኳ እንዴት እንደ ተጠቀምንበት ታሪክ ይመሰክራል - ጦርነቶችን ቆስቁሰናል፤ የዘር ማጥፋት አካሂደናል፤ በአየርና በውሃ ላይ ብክለት ፈጽመናል፤ ኢፍትሓዊ የፖለቲካ ሥርዐቶችን መሥርተናል፤ ያልተመጣጠነ የሀብት ክፍፍል አበጅተናል (ያለ ልክ የናጠጡ ሀብታሞችና ከድኽነት ወለል በታች ሌላ ወለል የሚፈለግላቸው ድኾችን) ፈጥረናል።[8] ታዲያ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሁሉ በመመለስ፣ ያንን ኀይል እንድናገኝ ቢፈቅድልን ምን ይከሰታል?

ማሃተማ ጋንዲን "ዓለምን እንደገና የምታበጅበት ኀይል ብታገኝ መጀመሪያ ምን ታደርጋለህ?" በማለት የሆነ ሰው ጥያቄ አቀረበላቸው። እሳቸውም፣ "ያ ኀይል ከእኔ እንዲወሰድ እጸልያለሁ" በማለት መለሱ።[9]

ጌታ ኢየሱስም በምድር ላይ እያለ ኀይልን አምብዛም አይጠቀምም ነበር። ፈታኙ ያቀረበለትን ኀይልን የመጠቀም ጥያቄ፣ (ሕዝቡን በታምራት እንዲያስደንቅ፣ ዓለምን እንዲመራና ራሱን ከጉዳት እንዲከለክል) በእምቢታ መልሷል። በእርግጥ ልዕለ ተፈጥሯዊ ኀይልን ተጠቅሞ ያውቃል። ሆኖም ይህንን ኀይል የተጠቀመው ራሱን ለማስተዋወቅ፣ ሕይወቱን ከጉዳት ለመከላከልና ለታይታ ሳይሆን፣ በኀዘኔታና በርኅራኄ ሆኖ በተወሰነ አካባቢ እንጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ አልነበረም።[10]

በእግዚአብሔር ቤት ስንኖር አነጋጋሪና ግራ አጋቢ ከሆኑ ነገሮች አንዱ (ምናልባትም ዋነኛው) ጸሎት ነው። የጸለይነውን ሁሉ እናገኛለን? የሚለው ጥያቄም ብዙ ጊዜ የሚሰነዘር ጥያቄ ነው። ጸሎት ሁሉ የእሺታ ምላሽ እንደሚያገኝ መናገር ይከብዳል፤ መጽሐፍ ቅዱስ የተመለሱ ጸሎቶችን ብቻ ሳይሆን፣ ያልተመለሱ ጸሎቶችንም ዐቅፎ ይዟልና!

## ያልተመለሱ ጸሎቶች

ነቢያቱ ሙሴ፣ ኤልያስና ዮናስ፣ እንዲሁም ጻድቁ ኢዮብ እግዚአብሔር እንዲወስዳቸው (እንዲሞቱ) ጸልየዋል። ኤልያስ፣ "ይበቃኛል፤ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ" ብሎ ለምኗል። ኤልያስን ሳስበው ድብታ (depression)

ያለበት ይመስለኛል፤ እጅግ ልበ ሙሉ ሆኖ በተገለጠ በማግስቱ ሐሞቱ ፈስሶ ነው የተገኘው። ንጉሡን ፊት ለፊት ሲጋፈጥ የኖረው ሰው፣ የእቴጌዪቱ ቊጣ በፍርሀት መግቢያ አሳጣው (ለነገሩማ፣ ከተቈጣች ሴት በላይ ምን የሚያስፈራ አለ?)። ስለዚህም መብላትም ሆነ መጠጣት አልፈለገም። "ውሰደኝ" በማለት ከጸለየ በኋላ በዚያው ሞቶ እንዲቀር የፈለገ ይመስል (ስንቶች ይህንን ተመኝተን ይሆን?)፣ ከክትክታ ዛፍ በታች ተጋደመና አንቀላፋ (1ነገ. 19፥4)።

እግዚአብሔር ግን መልአኩን ልኮ ቀሰቀሰውና ምግብ አቀረበለት። ኤልያስ ድብታው አልለቀቀውም፤ በልቶ ሲጨርስ ተመልሶ ተኛ። እግዚአብሔርም አልለቀቀውም፤ መልአኩ በድጋሚ ቀሰቀሰውና ሩቅ መንገድ ለመሄድ እንዲዘጋጅ እያሳሰበ አሁንም እንዲበላ ጋበዘው (ድብታ ውስጥ በገባንና ልባችን በወደቀብን ቊጥር ለመሞት የምንለምን ከሆነ፣ እግዚአብሔር ሊያደምጠን ይገባልን?)።

ሙሴ ደግሞ፣ "በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ በእኔ ላይ የሚሆነውን መከራ እንዳላይ እባክህ ፈጽሞ ግደለኝ" በማለት አስተዛዝኖ ጸለየ (ዘኍ. 11፥15)። ዮናስም፣ "ከሕይወት ሞት ይሻለኛል" አለ (ዮና. 4፥8)። አንዳቸውም የጸለዩትን አላገኙም።

ንጉሥ ዳዊት ልጁ እንዳይሞት ዐልጋውንና ዙፋኑን ትቶ መሬት በመተኛት ለሰባት ቀን ጾሞ ጸልዮአል። ጸሎቱ ግን ልጁን ከመቀሠፍ አላዳነውም (2ሳሙ. 12፥15-18)። ያ "ልበ አምላክ" ሰው ጸሎቱ ተቀባይነት አላገኘም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ያሠቃየው የነበረው የሥጋ መውጊያ እንዲወገድለት ጸልዮአል፤ ያውም ደጋግሞ (ሦስት ጊዜ)። ይህ የሥጋ መውጊያ ምን እንደ ሆነ አላውቅም፤ መልካም ነገር እንዳልሆነ ግን ግልጽ ነው፤ መልካም ነገር ቢሆን እንዲወገድለት አይጸልይምና። እግዚአብሔር ግን የዚያን ታማኝ ሐዋርያ ጸሎት ሰምቶ መውጊያውን መንቀል አልፈለገም፤ እንዳይታበይ ይጠቅመው ስለ ነበር፣ "ጸጋዬ ይበቃሃል" አለው እንጂ (2ቆሮ. 17፥7-9)።

የእነዚህ ቅዱሳንና ጻድቃን ጸሎት የተጠበቀውን ምላሽ አለማግኘቱ ስለ ጸሎት ምን ያስተምረናል?

## በመሸነፍ ማሸነፍ

ምላሽ ያጣ ጸሎት ሰዎችን ይሰብራል፤ አንዳንዴም መጽናናት እስኪያቅት ድረስ ይጎዳል። ሆኖም ሁሌም ኀዘንንና ስብራትን ማስከተል አይኖርበትም፤ ምስጋናንም ሊያስከትል ይችላል። በእርግጥ ስላልተመለሱ ጸሎቶቻችን ምስጋና ማቅረብ የምንችለው ጊዜ ሲያልፍና ተረጋግተን ስናስብ ነው። መለስ ብለን በማየት



የተካሄደውንና እየተካሄደ ያለውን ነገር ካለንበት ሁኔታ ጋር በእርጋታ ማጤን ስንችል ብቻ ነው።

አንዳንድ ጸሎቶች ምላሽ ቢያገኙ ከባድ ጥፋት ይሆን እንደ ነበር አስባለሁ። ለምሳሌ፣ ከላይ የጠቀስናቸው ጸሎቶች ሁሉ ቢመለሱስ ኖሮ? ዳዊት ከሰው ሚስት ጋር አመንዝሮ የወለደው ልጅ በሕይወት ቢኖርና አድጎ በሰሎሞን ምትክ ቢነግሥስ ኖሮ? ነቢያቱ ሙሴ፣ ኤልያስና ዮናስ እንዲሁም ኢዮብ "ውሰደኝ" በማለት ጸልየው እንደ ጨረሱ ቢሞቱስ ኖሮ? ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳይታበይ የተሰጠው የሥጋ መውጊያ ተነቅሎለት ቢሆንስ ኖሮ? ግዙፍ ጥፋቶች ይሆኑ ነበር።" የጸሎት ምላሽ አለማግኘት በረከትም ሊሆን ይችላል ማለት ነው! ያልተመለሰ ጸሎትም ለካ መልስ ይሆናል?

የተጠየቁትን ሁሉ መፍቀድ መልካምነትን ያሳያል? የትኛውስ ወላጅ ይህንን በልጁ ላይ ይፈጽማል? "እንዲት ቀላል ጸሎት መስማት፣ መቀበልና መመለስ የሚያቅተውን አምላክ ላመልክ አልችልም፤ ነገር ግን እያንዳንዱን የግልም ሆነ የኅብረት ጸሎትና ጥያቄ ሁሉ የሚፈቅድ አምላክም ክፉ አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር ሳይሆን ጋኔን ነው" ይላል ጆርጅ ማክዶናልድ።[12]

ጸሎታችን ምላሽ አላገኘም ማለት ግን በፍጹም ከስረናል ማለት አይደለም። ሁኔታዎቹ ባይለወጡ እንኳ እኛ መለወጣችን አይቀርም። የማታ ማታ እግዚአብሔርን ማወቃችንና በሌላ መንገድ በማይገኝ ቅርበት ከእርሱ ጋር መቀራረባችን አይቀርም። ይህ ትርፋችን አይሆንምን? ሮናልድ ደን በቤተ ሰቧ ያለው የተበላሸ ኅብረት እንዲፈወስ ለአምስት ዓመት ያህል በየቀኑ ትጸልይ ከነበረች ሴት መነጋገራቸውን ጽፈዋል። ይህች እኅት ለአምስት ዓመት ጸልያለች፤ "መጨረሻው ግን" አለች ስትናገር፣ "አልተሳካም፤ እግዚአብሔር ጸሎቶቼን አልመለሰም።"

እናም ሮናልድ ደን ነገሩን አጤኑት። ለአምስት ዓመታት በየቀኑ ጸልያለች፤ ጸሎቷ ግን አልተመለሰም። ጥያቄ አቀረቡላት፤

> "ለመሆኑ እነዚያን የጸለይሽባቸውን አምስት ዓመታት እንደ ባከኑ ትቈጥሪያቸዋለሽ?"
>
> "በፍጹም" አለች። "እንደዚያ ዐይነት ግምት አሳድሬብህ ከሆነ አዝናለሁ። በአንድ በኩል እነዚያ የሕይወቴ ምርጥ አምስት ዓመታት ነበሩ፤ የዚያን ጊዜውን የሚያህል የእግዚአብሔር አብሮነትና ፍቅር በፍጹም በሌላ ጊዜ ተሰምቶኝ አያውቅም።"

> ከዚያም ለእፍታ አመነታችና እንዲህ አለች፤ "... ያልተመለሱ ጸሎቶችና የቤተ ሰብ ችግር የነበሩባቸው እነዚያ አምስት ዓመታት፣ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ላደረገልኝ ነገር በደንብ ይመጥናሉ፡፡ ያልተመለሱ ጸሎቶቼን እግዚአብሔር በዚያን ወቅት ካደረገልኝ ነገር ጋር መለዋወጥ የምችል ቢሆን አላደርገውም፡፡"[13]

አንዳንዴ እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሚመልሰው ጸሎታችንን ባለመመለስም ነው፡፡ ስለዚህ የጸሎታችን መልስ ያለ ማግኘት ለተሻለ ነገር በር ሲከፍት ይገኛል፡፡ የቅዱስ አውግስጢኖስ (Augustine) እናት ሞኒካ ልጇ ሥጋዊ ስሜቱን ለማርካት ሲፋንንና የተለያዩ ፍልስፍናዎችን ተከትሎ ሲነጉድ ወደ ጌታ እንዲመጣ አብዝታ ታነባ ነበር፡፡ (አውግስጢኖስ ጌታን ለመከተል መጨረሻ ሲወስን፣ ለጽሑፎቹ ጥልቀትና ስፋት በመስጠት ለምዕተ ዓመታት የሚያገለግሉ ክርስቲያናዊ እሳቤዎችን እንዲያበጅ የረዱት እነዚሁ ልምምዶቹ ናቸው፡፡) እናትዬው ስለ ልጇ መዳን ሁሌ ብታነባም ልጁ እየባሰበት ሄደ፡፡ ልጇን አግኝተው እንዲያነጋግሩትና እንዲሞግቱት የጠየቀቻቸው ካህን የምታወርደውን የእንባ ጎርፍ ሲያዩ ተረብሸው፣ "እባክሽን ከዚህ ሂጂልኝ፤ ይህ ሁሉ እንባ የሚፈስስለት ልጅ ሊጠፋ አይችልም" ብለው መልሰዋታል፡፡[14] ልጇም ኋላ ሲናገር፣ "በሥጋ ስትወልደኝ ከደረሰባት የሚበልጥ ምጥና ሕመም በመንፈሳዊ እርግዝናዋ ወቅት ዐልፎባታል" ይላል፡፡[15]

አንድ ጊዜ እናቱ ሞኒካ ልጇ ወደ ርኩሷ ከተማ ሮም እንዳይሄድ እግዚአብሔር እንዲያስቀርላት ሌሊቱን ሙሉ ስትጸልይ አደረች፤ ልጇ ግን ዋሽቷትና አታልሏት በመርከብ ወደዚያው ተጓዘ፡፡ በእርግጥ አውግስጢኖስ ክርስትናን የተቀበለው በዚያ ጉዞ ላይ ነበር፡፡ በኋላ ግን፣ እግዚአብሔር የእናቱን የሁልጊዜ ጸሎት ለመመለስ ይህኛውን ጸሎቷን እንደ ከለከላት ተናግሯል፡፡[16]

ታዲያ ይህች እናት ይህ ጸሎቷ አዎንታዊ ምላሽ ባለማግኘቱ እግዚአብሔርን አላመሰገነች ይሆን? ትልቁን ሥዕል ካየች በኋላ ማለቴ ነው፡፡ እኛስ ተመሳሳይ ነገር አላጋጠመንም? ለአንዱ ጸሎታችን መልስ ለመስጠት ብዙዎቹን አለመመለስ ግድ ቢሆንስ?

ድንግል ማርያምና ኤልሳቤጥ ስለ እርግዝናቸው የሰሙት በአስደናቂ መንገድ ነበር፡፡ ማርያም በደስታና በተስፋ በዘመረችው መዝሙር ውስጥ፣ "ገዢዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል" ብትልም (ሉቃ. 1፥47-55)፣ ልጇ ከዙፋን እንደሚያዋርዳቸው ተስፋ ባደረገቻቸው ገዢዎች ተሰቅሎ ሲሞት ምን ይሆን የተሰማት? የኤልሳቤጥ ባል ካህኑ ዘካርያስ፣ "ማዳኑ ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው" በማለት ተንብዮ ነበር (ሉቃ. 1፥71)፡፡ ልጁ አንበጣ በላተኛ ሆኖ ሲያድግና ከእነዚህ ጠላቶች በአንዱ ራሱ ተቈርጦ ሲሞት ሲያየው ምን ተሰምቶት ይሆን (በሕይወት ከነበረ)? እነዚህ ሁለት ቤተ ሰቦች በትጋት የጸለዩበትንና የጠበቁትን ነገር አላገኙም፡፡[17]



እግዚአብሔር ሰው ሆኖ መምጣቱ ከዚህ በፊት ስለ መሲሑ የነበሩትንና ተቀባይነት ያገኙትን ሐሳቦች ሁሉ አፈራርሷቸዋል፡፡ ባልተጠበቁ መንገዶች ነው የመጣው፡፡ በእኛም ጸሎት እንዲሁ ነው፡፡ ባልተገመተ መንገድ ቢሆንም እነዚህ ጸሎቶች መልስ ያገኙ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በኋላ ዘወር ብሎ ለተመለከተው የጸሎቶቹ ምላሽ አለማግኘት የምስጋና ፕሮግራም ለማዘጋጀት አሳማኝ ምክንያት የሚሆን ይመስላል፡፡

## በድንግዝግዝ ከማየት ... ወደ ብርሃን

"ጸሎታችን ምላሽ የማያገኝ ከሆነ ለምን እንጸልያለን?" የሚል ጥያቄ ቢነሣስ? አንድ መጋቢ የቤተ ክርስቲያናቸው አባል የሆኑ ሁለት ሰዎች በታመሙ ጊዜ ወደ ቤታቸው እየሄዱ እጃቸውን በመጫን ይጸልዩ ነበር፡፡ ሆኖም ሁለቱም ከበሽታቸው ፈውስ ሳያገኙ ወደ ጌታ ሄዱ፡፡ እነዚህ ክስተቶች መጋቢውን ተስፋ አስቈርጠዋቸው እንደሆን ጥያቄ አቀረብኩላቸው፡፡ "በፍጹም!" ነበረ መልሳቸው፡፡ "ሕሙማኑ ነገ እንደሚሞቱ እያወቅሁ እንኳ ዛሬ እጄን ጭኜ እጸልያለሁ፡፡ ወደ ፊትም መቀጠሌ አይቀርም፡፡ ከበሽታቸው ባይፈወሱም፣ በጌታ ላይ ያላቸው እምነት ሳይናወጥ ጸንተው የሚሞቱበትን ጸጋ የሚቀበሉት በዚህ ጸሎት ውስጥ ቢሆንስ?" በማለት ጥያቄዬን በጥያቄ መለሱት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ በምን ዐይነት ሁኔታ በጸሎቱ ይታገል እንደ ነበር ከሚናገርባቸው ተደጋጋሚ ክፍሎች አንዱ እንዲህ ይላል፤ "እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንንና ምልጃን አቀረበ" (ዕብ. 5፥7)፡፡ በእርግጥም ግን ጸሎቱ ተሰምቶለት ከሞት አላመለጠም፡፡ ታዲያ መጸለዩ ምን ዋጋ አለው? ሀዶን ሮቢንሰን እንዲህ ይላሉ፤

> ጌታ ኢየሱስ የደም ላብ ያላበው የት ነው? በጲላጦስ ችሎት ወይም ወደ ጐልጐታ ሲጓዝ አልነበረም፡፡ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ነው፡፡ [...] እዚያ ቦታ ተገኝቼ ይህንን ትግል ብመለከት ኖሮ የወደፊቱ ሁኔታ ያስጨንቀኝ ነበር፡፡ "ገና ጸሎት ላይ ሳለ፣ መከራው ሳይከሰት እንዲህ ከተሰበረና ከተጨነቀ፣ እውነተኛውን መከራ ሲጋፈጥ ምን ሊሆን ነው? ይህንን ክስተት እያንቀላፉ እንዳሉት ደቀ መዛሙርት በመረጋጋትና በልበ ሙሉነት ሊጋፈጠው

አይችልም?" ብዬም እጠይቅ ነበር:: ሆኖም የፈተናው ሰዓት ሲደርስ፣ ኢየሱስ ወደ መስቀሉ በወኔ ተራመደ፣ ሦስቱ ወዳጆቹ ግን ሸሽተው ተበታተኑ::[18]

ጌታ ኢየሱስ መስቀሉ ላይ ካሰማቸው ጩኸቶች ሦስት ያህሉ ጸሎቶች ናቸው:: ቀደም ብለን እንዳየነው፣ "ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን" ሲያቀርብ፣ እግዚአብሔርን ስለ መፍራቱ እንደ ተሰማለት ተነግሮናል:: በቀጥታ ግን ከሞት አልዳነም፤ ከሞተ በኋላ ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ እንጂ!

አባትና እናት ለልጃቸው አጥብቀው ይጸልያሉ:: ጥሩ መረዳት የነበራቸው መንፈሳውያን ናቸውና የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ እንዲያድግ የሚያስፈልገው ሁሉ ተደርጎለታል፤ በእግዚአብሔር መንገድ አሳድገውታል:: ሲያድግ ግን ተቃራኒውን ሆነ:: ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ቤት ይወስዳል ተብሎ ሲጠበቅ፣ በተለያየ አጋጣሚ የሚያገኛቸውን ሴቶች እያግባባ ወደ ዐልጋ ይወስዳል:: በቤተ ሰቦቹ አገልግሎት ወደ ጌታ የመጡ ሰዎች በጌታ ስላገኙት ዕረፍትና ሰላም ሲናገሩ እርሱ አይገባውም:: ሰላምና ዕረፍት አጥቶ የማያውቅ ሰው እንዴት ይህ ሊገባው ይችላል?

ከዓመታት በኋላ በደማስቆ መንገድ ላይ እግዚአብሔር ተገናኘው፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ደማስቆ አለውና:: ከዚያ ማን ይቻለው? ምናልባትም ወላጆቹ ካሰቡትና ከጸለዩት በላይ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚጠቅም ሆነ:: ጠጋ ብሎ ለጠየቀው እነዚያ የከፉ ዓመታት የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲያውቅ፣ የራሱን ደካማነት እንዲገነዘብ፣ ሰላምና ዕረፍት ማጣት ምን ማለት እንደ ሆነ እንዲያስተውል እንዳደረጉት ይናገራል:: እርሱ በድካም በማለፉ፣ አሁን በድካም የሚያልፉትን ለመረዳት እንዳስቻለው ይመሰክራል:: የራሱን ምኞት ለመፈጸም ሲሄድ፣ እግዚአብሔር የታሰረበትን ገመድ ከመበጠስ ይልቅ ገመዱን ረዘም እንዳደረገለትም ሲያወራ እየሣቀ ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን ..." እንደሚል (1ቆሮ. 13፥12)፣ ስላልተመለሱ ጸሎቶቻችን ጠቅላላውን ሁኔታ በትክክል መገንዘብ የምንችለው ያኔ ነው:: አሁን ግን ...

## በግራ አሳይቶ በቀኝ

እስከ ዛሬ ስላልተመለሱት ጸሎቶቼ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ! ከአንዳንዶቹ ትዕግሥትንና መጠበቅን ተምሬባቸዋለሁ (አሁንም ግን ብዙ ይቀረኛል):: የአንዳንዶቹ ምላሽ አለማግኘት ድምር ሌላኛው ጸሎቴ እንዲመለስ ረድቶኛል (የቅዱስ አውግስጢኖስን እናት ያስታውሷል):: ትናንት ትክክል ከመሰሉኝና ዛሬ ግን ስሕተት መሆናቸውን ከተረዳኋቸው የተሳሳቱ ፍላጎቶቼም ተጠብቄባቸዋለሁ:: ይህን ሁሉ ሳጤን፣ ዛሬ ላይ ሆኜ ስመለከት ደግሞ ከአንዳንድ ጸሎቶቼ ስለ ጠበቀኝ ጌታን አመሰግናለሁ!



በጽሑፉ ጅማሬ ላይ ያነሣነው ወንድም ዛሬ የ8 ዓመት ታናሹ የሆነች እጮኛውን ለማግባት ዝግጅት ላይ ነው:: ለልጅቱ እርሱ የመጀመሪያዋ ሲሆን፣ እርሱ ግን ብዙ አይቷል:: አሁን እርሱ 3ኛ ዲግሪውን ጨርሶ "ዶክተር" ሊባል ጥቂት ቀርቶታል፤ እርሷ ደግሞ የመጀመሪያ ማስተርሷን ጨርሳ ሁለተኛ እየሠራች ነው:: ለትምህርቷ ወደ ውጭ አገር መሄጃዋ ሲደርስም ከመሄድ ይልቅ እርሱ ጋር ለመቅረት እያለቀሰች ስላስቸገረችው ተቈጥቶ፣ አባብሎና መክሮ እንድትሄድ ማድረግ ነበረበት:: አሁን ያለበት ሁኔታ የዚያ የመጀመሪያው ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው!

አሁን ዘወር ብሎ ሲያይና ሁለቱን እኅቶች ሲያወዳድር የዚያን ጊዜ ጸሎቱ ስላልተመለሰለት ደስተኛ ሆኗል:: የዚያን ጊዜ ጸሎቱ ምላሽ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ይሄኔ የት እንደ ነበር ሲያስብ በድንጋጤ ይንቀጠቀጣል፤ የእግዚአብሔር መልካምነት ከራሳችን ጸሎትም እንዲታደገን እንደሚያደርገው አስተውሷል:: ከአንዳንድ ጸሎቶቹ እግዚአብሔር ስለ ጠበቀው እየደጋገመ ነው የሚያመሰግነው:: ይህ ብቻም አይደለም፤ ዛሬ "በቀኝ አውለኝ" ከማለት ያለፈ ጸሎት አለው:: "ምስኪንነት ያልተሰማው ጸሎተኛ ገና ጸሎት አልጀመረምና"[19] ምስኪን ሆኖ ነው ወደ ጸሎት የሚቀርበው:: ስለዚህም ጸልዮ ከጨረሰ በኋላ፣ "ፈቃድህ ከሆነ" በማለት ማሳረጉን አይዘነጋም፤ በልቡ ያለውን ሁሉ እግዚአብሔር ፊት ያፈስስና "ፈቃድህ ከሆነ" በማለት ይደመድማል::

ምክንያቱም "ፈቃድህ ከሆነ" የሚለው ጸሎት ጌታ ኢየሱስም፣ "ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ" የሚለውን ተደጋጋሚ ጸሎት ካቀረበ በኋላ እንዳደረገው መጨረሻ ላይ ነው የሚጸለየው፤ መጀመሪያ አይደለም (ማቴ. 26፥36-42):: ይህንን በቅድሚያ ከጸለይንማ ጸሎታችን ላይ አርትዖት ለመሥራት፣ ፍላጎታችንን ለመጨቈን እንፈተናለን::[20] ከዚህ ይልቅ በልባችን ያለውን ሁሉ ዘርግፈን በነጻነት ከነገርነው በኋላ፣ "ፈቃድህ ከሆነ" በማለት ጸሎታችንን ሸብ ማድረጉ ሸጋ ነው:: ባለታሪካችንም የሚያደርገው ይህንኑ ነው!

"እግዚአብሔር ሆይ፤ ባልገቡኝ ነገሮች ላይ እንኳ አንተ ጻድቅ ነህ!"

## ማስታወሻ

1. ደበበ ሰይፉ፤ *ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ* (አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም) ገጽ 74።
2. ዳዊት ጸጋዬ፤ *እርካታ የወጡ ሐሳቦች* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም) ገጽ 13።
3. R. E. O. White, *The Exploration of Faith: Triumphs in Hebrews Eleven* (Moody Press, 1969), 112-115.
4. መስፍን ወ/ማርያም፤ *አገቱኒ ተምረን ወጣን* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም)፣ ገጽ 3።
5. ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *የእምነት ኀይል* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም)፣ ገጽ 134።
6. Edwin and Lillian Harvey, *Kneeling We Triumph* (Harvey Christian Publishers, 2012 ), p. 31.
7. Philip Yancey, *What Good is God? In Search of a Faith that Matters* (New York: FaithWords, 2010), 240.
8. Philip Yancey, *Prayer Does It Make Any Difference?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2006), 228.
9. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 229።
10. ዝኒ ከማሁ።
11. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 234።
12. George MacDonald, *Creation in Christ* (Wheaton, Illinois: Harold Shaw, 1976), 315.
13. ሮናልድ ደን፤ *የእምነት ኀይል*፣ ገጽ 86።
14. Henry Chadwik, *Saint Augustine Confessions* (Oxford: Oxford University Press, 1992), 51.
15. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 83።
16. Yancey, *Prayer*, 241.
17. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 241።
18. ዝኒ ከማሁ፤ 86-87።
19. ንጉሤ ቡልቻ፤ *መስተአየት፣ ራስ ታዛብና ተሐድሶአውያን መጣጥፎች* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 212።
20. Yancey, *Prayer*, 108.



# የቱ ይቅርታ?

ጃይሜ ካርዲናል ሲን በፊሊፒንሷ ዋና ከተማ ማኒላ የምትገኘው ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ናቸው፤ በዚያ በተካሄደው የሕዝብ የነጻነት እንቅስቃሴም ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። እኚህ ጳጳስ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበለችውን መልእክት ለመንገር ስትል በሳምንታዊ መርሐ ግብሮቻቸው ላይ ያለ ማቋረጥ ትካፈል ስለ ነበረች ሴት የሚናገሩት ታሪክ አላ ቸው። ጳጳሱ ብዙ ጊዜ ፊት ቢነሷትም ተመልሳ ትመጣለች።

> በመጨረሻም፣ "ይኸውልሽ እኛ ካቶሊኮች ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጡ ራእዮችንና መልእክቶችን በሚመለከት ጥብቅ መመሪያዎች አሉን፤ እናም ትክክለኛነትሽን ማጣራት ይኖርብኛል። ስለ ዚህ አሁን ተመልሰሽ እንድትሄጂና በቅርቡ በግሌ ንስሓ ስለ ገባሁበት አንድ ኀጢአት እግዚአብሔርን እንድትጠይቂው እፈልጋለሁ። እግዚአብሔርን ይህንን ጠይቀሺው ከነገረሽ ራእይሽ ትክክል እንደ ሆነ ዐውቃለሁ" አሏት።
>
> በሚቀጥለው ሳምንት ሴቲቱ ተመልሳ መጣች። ትንሽ እየተረበሹ፣ "እሺ፤ ስለ ኀጢአቴ እግዚአብሔርን ጠየቅሺው?" በማለት ጠየቋት።
>
> "አዎን፤ ጠይቄዋለሁ።"
>
> "እናስ እግዚአብሔር መለሰልሽ?"
>
> "አዎን።"
>
> "ምን አለሽ?"
>
> "እንዳላስታወሰው ነው የነገረኝ።"[1]

በእርግጥ እግዚአብሔር ኀጢአታችንን በፈቃዱ ዳግመኛ አያስብብንም (ኢሳ. 43፥25፤ ዕብ. 8፥12)፤ ከእኛም ያርቅልናል (2ሳሙ. 12፥13) እንጂ ማስታወስ የሚያቅተው ወይም የሚረሳ አይደለም። ሆኖም ብዙዎች ስለ ይቅርታ ሲያነሡ፣ "ይቅርታ ማድረግና መርሳት አለባችሁ" በማለት የሚመክሩት ከዚህ ዐይነቱ የእግዚአብሔር ባሕርይ በመነሣት ሊሆን ይችላል። ምክር እና ቦክስ ለሰጪው ቀላል ሆኖ እንጂ፣ ይቅርታ ማድረግ በራሱ ፈታኝ ነው፤ እንኳንስ

መርሳት ተጨምሮበት:: ምክንያቱም በደልን በፈቃዱ የመተው ችሎታ ያለው
እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ እኛ አይደለንም:: እኛ ንስሓ ስንገባ፣ እርሱ
አንዴ ይቅር ይለንና ኀጢአታችንን ዳግመኛ አያስብብንም፤ ለዘላለም::

## አሐዱ - ይቅርታ መጠየቅ

እግርና እግርም ይጋጫልና በሕይወት መንገድ ላይ ግጭትም ሆነ ጥፋት መፈጸ
ማችን አይቀርም:: ሆኖም ያንን ለማስተካከል ይቅርታ እየጠየቅን እንጓዛለን፤
ይህ የክርስቲያናዊ ኀላፊነታችን አካል ነው::

ሆኖም ሁሉም ዐይነት ጥፋት አንድ ዐይነት አይደለምና ይቅርታችንም
አንድ ዐይነት ላይሆን ይችላል:: አንዳንዱ ጥፋታችን እግዚአብሔርን ብቻ የሚ
መለከት ነው:: አንዳንዱ ደግሞ በዋናነት የበደልነው እግዚአብሔርን ቢሆንም፣
በደላችንን የሰሙና ያዩ ሰዎችን (ወይም ቤተ ክርስቲያንን) ከጎዳ ሁሉንም ወገን
ይቅርታ መጠየቅ ይጠበቅብናል:: ያሳዘንነው ሥጋ ለባሽን ከሆነ ደግሞ፣ በእግ
ዚአብሔር ፊት ወድቀን በንስሓ እርቅ ከማውረዳችን በፊት ከበደልነው ባልንጀ
ራችን ምሕረትን እንድንለምን እንገደዳለን::

በተለይ የመጨረሻውን ዐይነት ጥፋት ከሚመለከተው ንስሓ ጋር በተያ
ያዘ ብዙ ችግሮች እንዳሉብን ይስተዋላል፤ በርካታ በደሎቻችን ሌሎችንም
ሰዎች የሚነኩ ናቸው:: በትዳር ጓደኛቸው ላይ የሚያመነዝሩ፣ እምነት የሚያ
ጐድሉ፣ ስም የሚያጠፉና ፍርድ የሚያጣምሙ እግዚአብሔርንና ሰዎችን በአን
ድነት የበደሉ በመሆኑ የሁሉም ወገን ይቅርታ ነው የሚያስፈልጋቸው::

በተለያዩ ከባድ ጥፋቶች የተገኙ ሰዎች ጥፋታቸውን በመግለጽ ይቅርታ
ለመጠየቅ የሞከሩባቸውን ጥቂት መጻሕፍት አንብቤአለሁ:: ሆኖም ከሞላ
ጐደል የተጻፉት የራስን ጥፋት ለማድበስበስ፣ ራስን ለመከላከልና ለ"ገጽታ ግን
ባታ" ሆነው አግኝቻቸዋለሁ::

በ"ዋተርጌቱ ቅሌት" ሥልጣናቸውን እንዲለቅቁ የተገደዱት የአሜሪካ
ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን ወንጀላቸውን ላለማመን ብዙ ጥረዋል፤ ባይሳካላቸ
ውም:: በመጨረሻም "ስሕተት" መሥራቱን ሸፋፍነው ለመግለጽ ነው የሞከ
ሩት:: የፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተንንም ጉዳይ አብዛኞቻችን የምናውቀው ሳይ
ሆን አይቀርም፤ ከሞኒካ ሉዊኒስኪ ጋር የፈጸሙትን ማለቴ ነው:: ክሊንተን
እውነቱን ለመናገር መሐላ ፈጽመው እንኳ ዋሽተዋል:: ቃላት እየሰነጠቁ ለማ
ምለጥ ሞክረዋል:: ሚስታቸውን፣ የአሜሪካን ሕዝብና እግዚአብሔርን መበደላ
ቸውን በይፋ ገልጸው ይቅርታ የጠየቁት ወንጀላቸው በማስረጃ በመረጋገጡ፣
ማምለጫ ሲጠፋቸውና ሥልጣናቸውን ሊያሳጣቸው ሲቃረብ ነበር:: የሥል



ጣን ዘመናቸው ካበቃ በኋላ ባሳተሙት የሕይወት ታሪካቸውም ጥፋታቸውን
ለማለባበስ ብዙ ሙከራ አድርገዋል::

በእኛም አገር ይኸው ነው:: ኮሎኔል መንግሥቱ ኀ/ማርያም ከዐፄ ኀ/
ሥላሴ ስድሳ ባለሥልጣናት በተጨማሪ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ወጣቶችን ያለ
ፍርድ አስገድለዋል፤ ብዙ ደምና እንባ አፍስሰዋል:: ግና አሁን ከሥልጣናቸው
ተባርረው ዚምባብዌ እየኖሩ እንኳ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ ሞት
ሆኖባቸዋል:: እንዲያውም በሁለት ቅጾች የታተሙት "የኮሎኔል መንግሥቱ
ትዝታዎች" የተሰኙት መጻሕፍት እንደሚነግሩን ራሳቸውን አሳዛኝ አድርገው
ለማቅረብና በሌላ ለማላከክ ርቀው ይሄዳሉ::

ምንም ሁነኛ ሰው እንዳልነበረን በጭፍን ላለመናገር አንድ ሁለት ሰው
እጠቅሳለሁ:: በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የብሪታንያ ዲፕሎማት ፕላውደን ዐፄ
ቴዎድሮስን እየተከታተለና እያጠና ወደ አገሩ ያስተላለፋቸው መልእክቶች
ነበሩ:: በእነዚያ መልእክቶች ውስጥ ንጉሡ ባነስተኛ ጭፍሮቻቸው ላይ
በንዴት በደል ቢፈጽሙም እንኳ በደላቸውን በጸጋ ተቀብለው ከልብ ይቅርታ
እንደሚጠይቁ ምስክርነት ሰጥቷል::[2]

ስለ ዐፄ ምኒልክ የሚነገርም ታሪክ አለ:: ምኒልክ ያልተጣራ ወሬ ሰም
ተው የአንዱን ራስ ጭፍሮች ለሌላኛው ራስ ይሰጡበትና እርሱን ከሥራ አግ
ደው ቤቱ እንዲቀመጥ ያደርጉታል:: ከአንድ ዓመት በኋላ ግን እውነቱን ተገነ
ዘቡ:: ያኔ ሰውየውን አስጠሩና ሰዎች ባሉበት ጎንበስ ብለው፣ "ይቅር በለኝ
በድዬሃለሁ፤ ጎድቼሃለሁ" ይሉታል:: ሰውዬው ግን ምንም እንዳልተጎዳ፣ እንዲ
ያውም ሌሎቹ ባለሥልጣኖቻቸው እንዳይቸገር እህሉንና ሰንጋውን በየዐይነቱ
እየላኩለት ተንቀባርሮ እንደ ኖረ ይገልጽላቸዋል:: ጃንሆይም፣ እነዚያን ባለ
ሥልጣናት አስጠርተው፣ "እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይክፈላችሁ፤ እኔ ተሳስቼ
ብበድለው እናንተ በእግዚአብሔር እንዳልወቀስና እንዳልኰነንባችሁ ላደረጋች
ሁት አመሰግናችኋለሁ" በማለት አሰናበቷቸው:: ንጉሡ "ከእፈርኩ አይመል
ሰኝ" ማለት ሲችሉ እግዚአብሔርን ፈርተውና እውነቱን ተቀብለው ይቅርታ
ጠይቀዋል:: እንዲህም ዐይነት ሰው ነበረን![3] (እነርሱ የተጣሉትን ሰው ተደር
በን ካልተጣላንላቸው እኛን የሚጣሉን ሰዎች ትዝ አላሏችሁም?!)

ሰዎች፣ የበደሉትን ሰውና አምላካቸውን ገና ከመጀመሪያው ይቅርታ
ከመጠየቅ ይልቅ አለባብሰው በማኖር ጒዳያቸው (ጒዳቸው) በአደባባይ እስኪ
ዝረከረክ የሚጠብቁት ለምንድን ነው? ከተጋለጡስ በኋላ ለምን ይፈራገጣሉ?
በአንድ በኩል ከአባታችን ከአዳም የተወረሰ ይመስለኛል፤ የመጀመሪያው ኀጢ
አተኛ ሰው እርሱ በመሆኑ:: እንዳይበላ የታዘዘውን ፍሬ ስለ መብላቱ እግዚአ

ብሔር ሲጠይቀው፣ "የሰጠኸኝ ሴት አሳተችኝና በላሁ" በማለት ጥፋቱን በእርሷና እርሷን በሰጠው አምላክ ላይ ለማላከክ ሞከረ እንጂ ለራሱ ድርጊት ኀላፊነቱን አልወሰደም። እርሷም ስትጠየቅ ይቅርታ በመጠየቅ ፈንታ በእባብ በማሳበብ የባሏን ፈለግ ተከተለች (ዘፍ. 3፥11-13)፤ "ባልና ሚስት ከአንድ ባሕር ይቀዳሉ" እንዲሉ።

ሰውን መፍራትም ሌላ ሰበብ ነው። በደልን የሠራ ሰው እግዚአብሔር ይቅር ቢለውም ሰዎች በቀላሉ ይቅር እንደማይሉት ይፈራል። በተለይ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ዋና ሥጋት ይህ ይመስለኛል። ሀዶን ሮቢንሰን የተባለ አንድ መጋቢ ከሞላ ጐደል እያንዳንዱን ስብከቱን የሚጀምረው፣ "ጌታ ሆይ፤ እነዚህ ሰዎች አንተ ስለ እኔ የምታውቀውን ነገር ዐውቀው ቢሆን ኖሮ የምናገረውን አንድም ቃል አይሰሙኝም ነበር" በማለት ነው።[4]

ማሃተማ ጋንዲ በሚያስፈልግ ጊዜ ራሳቸውን የሚተቹ ሰው ነበሩ፤ ስሕተት በሠሩ ጊዜ ሁሉ በአደባባይ ይናዘዙ ነበር።[5] ለግልጽ ስሕተታቸው "ይቅርታ" ማለት ሽንፈት የሚመስላቸው ሰዎችም አሉ፤ በየመንገዱ ገጭተውንና ረግጠውን እንኳ "ይቅርታ" ማለት የሚተናነቃቸው ሰዎችን የምናየው ለዚህ ነው። አንዳንዶች ደግሞ ቢያስፈልግ ስጦታ በመስጠትና በሌላ መንገድ ይቅርታቸውን ይገልጻሉ እንጂ "ይቅርታ" የምትለዋ ቃል ከጒሮሮአቸው አልወጣ በማለት ታስቸግራቸዋለች።

በቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ይህ ታይቷል። በተለይ በአባቶቻችን ትውልድ (አባቴን ጨምሮ) የነበሩ አገልጋዮች በቀላል ነገሮች በመካከላቸው ግጭት ሲፈጠር እንኳ በይቅርታ ማስተካከል ተራራ ሆኖባቸው ዐይቻለሁ። ከግትርነታቸው የተነሣም አብያተ ክርስቲያናት ተከፍለዋል፤ ስንቱን መከራ ተደጋግፈው ያለፉ ወንድማማቾች ተነጣጥለው ቀርተዋል፤ ቤተ ሰቦቻቸው ውድ ዋጋ ከፍለዋል። "እርሱን ይቅርታ ከመጠየቅ፣ ከእርሱ ጋር አብሮ ከመሥራት ለምን ሁሉ ነገር ጥንቅር አይልም!" የሚሉ ይመስላሉ። በችግሮቻቸው ላይ ዘመናት ቢቈጠሩም ይቅርታ መጠያየቅም ሆኖ መቀባበል ተስኗቸዋል፤ የተጣሉት ሰው ሲሞት ግን ድንጋይ ላይ እየተፈጠፈጡ ያለቅሳሉ!

በንስሓ ጒዳይ ቅዱስ ዳዊትን ማንሣት የግድ ሳይሆን አይቀርም። ዳዊት ከሰው ሚስት ጋር ከተኛ በኋላ አንዱ ኀጢአት ወደ ሌላው ይመራልና የኀጢአቱን ደብዛ ለማጥፋት የሴትየዋን ባል በግፍ አስገደለ። ይህን ሁሉ አድርጎም እግዚአብሔር የማያየው ይመስል በሌላው ላይ እየፈረደ "ሰላማዊ" ኑሮውን ቀጠለ፤ እዚህ ጋ ዳዊት ሁላችንንም መስሎ ነው የተገኘው። ግና እርሱም ሆነ ሌሎች እርሱን መሳይ ሰዎች ማስታወስ የማይወድዱት ነገር አለ፤ የትኛውም የተደበቀ ነገር አንድ ቀን መገለጡ አይቀርም።



እግዚአብሔር የኀጢአተኛውን ሞት አይወድምና ንጉሥ ዳዊትን ኀጢአቱ እየሰለሰለ ከሚጨርሰው አጋልጦ ሊያድነው ወደደ! ስለዚህም የተሸፋፈነውን ኀጢአቱን ነቢዩ ናታን ፊት ለፊት በጥበብ ገለጠበት። ዳዊት ሁላችንንም ለማስተማር የሚበቃው ከዚህ በኋላ በሠራው ድርጊት ነው። "ናታን ለዳዊት ኀጢአቱን ካሳየው ጀምሮ እውነተኛ ስብራት ነው ዳዊት ላይ የታየው። ራሱን መከላከልም ሆነ ሰበብ መደርደር፣ ወይም ሌሎች ላይ ማላከክ አልታየበትም።"[6] ከናታን ግሣጼ በኋላ ዳዊት አንዳች ሳያቅማማ፣ "እግዚአብሔርን በጣም በድያለሁ" በማለት ከዙፋኑ ወርዶ መሬት ተደፋ (2ሳሙ. 12፥7-17)።

ንጉሥ ዳዊት ነቢዩ ናታን ሲያፋጥጠው የኀጢአቱን ጥልቀት ወዲያውኑ ነው የተረዳው። የበደለው ኬጢያዊውን ኦርዮ ብቻ ሳይሆን ጌታንም መሆኑን ተገንዝቧል። "አንተን፣ በእርግጥ አንተን ብቻ በደልሁ" በማለት ያለቀሰው ለዚህ ነው (መዝ. 51፥40)። ዳዊት ንስሓ ከገባ በኋላ ገመናውን ሸፋፍኖ ማለፍ የሚችልባቸው በርካታ መንገዶች ነበሩት፤ እርሱ ግን እንዲህ አላደረገም። ኀጢአቱን በዝርዝር ጽፎ መዝሙር አዘጋጀ፤ መዝሙር ምዕራፍ 51ን። "ለአንድ ንጉሥ የሥነ ምግባር ውድቀቱን ለአንድ ነቢይ በግል መናዘዙ አንድ ነገር ነው። ያ ኑዛዜው በመላ አገሪቱ እንዲዘመር ዝርዝር መዝሙር ማዘጋጀቱ ግን ሌላ ነገር ነው።"[7]

እርግጥ ነው፣ "የእስራኤሉ ንጉሥ ከሁሉ ይልቅ የከፋ አወዳደቅ ወድቋል፤ ነገር ግን እርሱም ሆነ ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ፍቅርና ይቅርታ ውጭ ሊወድቅ አይችልም።"[8]

ዳዊትን ኀጢአቱ ከባድ ዋጋ አስከፍሎታል። ከዚያ በኋላ ቤተ ሰቡን መምራት እንኳ አቅቶት ታይቷል። በልጆቹ ላይ ሊኖረው የሚገባውን የሞራል የበላይነት አሳጣው። ስለዚህ ከዚህ ኀጢአቱ በኋላ አንደኛው ልጁ እኅቱን ደፈረ፤ ሌላኛው ልጁ ደግሞ ወንድሙን ገደለና በራሱ በዳዊት ላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አደረገ (እግዚአብሔር በምሕረቱ ጣልቃ ባይገባ ኖሮ ዳዊት አብቅቶለት ነበር!)።

ይቅርታ ሲታሰብ ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ጎንም መመልከት አለብን። ምሕረትና ይቅርታ የሚያስፈልገን ከሁለቱም አቅጣጫ ነው። እግዚአብሔርን ብቻ ምሕረት መጠየቅ በቂ አይደለም።

ጌታ ኢየሱስ እንደሚነግረን ከሆነ፣ የገባበትን ጣጣ በንስሓና በይቅርታ ያላስተካከለ ሰው የያዘውን መባ እንኳ መስጠት አይችልም። የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ትኵረቷ ለገንዘብ ሆኖ እንጂ፣ በየአምልኮው ቀን መባ ከመሰብሰቧ በፊት፣ "ሰውን አሳዝናችሁ ወይም ጎድታችሁ የመጣችሁ መባችሁን ቁጭ አድርጉና ሄዳችሁ ሰላም አውርዱ" እያለች መምከር ነበረባት። የእነዚህ ሰዎች መባ

ከተቀረው መባ ጋር መቀላቀል ያለበት ሰላም አውርደው ከመጡ በኋላ ብቻ
ነው (ማቴ. 5፥23-24)! ይቅርታ ከየትኛውም አገልግሎት ይቀድማል።

አብረውን ጌታን ከሚያመልኩ ወገኖች ጋር ነገራችን ተበላሽቶ፣ ከእግዚ
አብሔር ጋር ትክክል ሊሆን አይችልም። መጽሐፉ የሚነግረን፣ "እርሱ በብር
ሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየ
ሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል" በማለት ነው (1ዮሐ. 1፥17)።
ሰዎችን በድለውና ከወገኖች ጋር ያላቸውን ኅብረት አበላሽተው ሳለ በግላቸው
ንስሓ ስለ ገቡ ብቻ ነገሩ የሚስተካከል የሚመስላቸውም አይጠፉም። ሆኖም
ንስሓ ገብተው የነበራቸውን ኅብረት ካላስተካከሉ ንስሓቸው ዋጋ የለውም።
ሐዋርያው ዮሐንስ በዚህ ክፍል እንደሚነግረን "እግዚአብሔር ኀጢአትን በጨ
ለማ ውስጥ ይቅር አይልም! ጨለማችን ውስጥ ቈይተን እግዚአብሔር እንዲያነ
ጻን መጠበቅ አንችልም። ጨለማውን ለቅቀን ወደ ብርሃን መምጣት አለብን።
ንስሓ ይህ ነው።"[9] ይህ ካልሆነ ግን፣ "የፈለጋችሁትን ያህል ንስሓ ልትገቡ፣
እስከ ውድቅት ድረስ ይቅርታ ስትለምኑ ልትቈዩ ትችላላችሁ፤ ከወንድሞቻችሁ
ጋር በኅብረት መሆንን እምቢ እስካላችሁ ድረስ ግን ጊዜያችሁን በከንቱ እያባከ
ናችሁ ነው።"[10] ኅብረት የሚጠበቀው ደግሞ በንስሓ እና በይቅርታ ነው።

በቅርቡ፣ "በዳዩን መጠየቅ ይቅርታ፣ ይሄ ነው ወንጌሉ የጌታ" የሚል
መዝሙር ሰምቼ ነበር። ግን የጌታ ወንጌል ይህንን የሚያስተምረው የት ነው?
አንዳንድ አስታራቂዎችም ከ"መንፈሳዊነታቸው" የተነሣ ተበዳዩ ስለ ጌታ ብሎ
በዳዩን ይቅርታ እንዲጠይቅ ("ይቅር እንዲል" አላልኩም፣ "ይቅርታ እንዲጠ
ይቅ" እንጂ) እስከ መጠየቅ ይደርሳሉ። ይህን "ጥበብ" ከየት እንዳመጡት አላ
ውቅም፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደማያስተምር ግን ዐውቃለሁ። በእርግጥ
ተበዳዩ ሰው ይቅርታ ሳይጠየቅ ቅሬታውን ከልቡ ሊያጸዳ ይችላል። ነገር ግን
የተበደለ ወገን በዳዩን በፍጹም ይቅርታ መጠየቅ አይኖርበትም። እንዲያውም፣
ሰዎች ከልባቸው ይቅርታን እስካልጠየቁ ድረስ ይቅር እንዳላችኋቸው መንገር
እንኳ አይኖርባችሁም። ይቅርታ እንዲህ ርካሽ አይደለም።

ተበዳዩ ሰው በዳዩን ይቅርታ የሚጠይቅ ከሆነ በጥፋቱ እንዲቀጥል ያደ
ርገዋል። ያ ሰው በክፋት ይታነጻልና ሲያጠፋም ትክክል እያደረገ እንደ ሆነ ያስ
ባል። ሰዎች ይቅርታ በመጠየቅ ውስጥ ትሕትናን፣ አስተዋይነትን፣ ፍቅርንና
ኀላፊነትን ይማራሉ። በመሆኑም ያጠፋን ከመገሠጽ ይልቅ ይቅርታ እንዲጠየቅ
ስናደርግ እነዚህን በጎ መንፈሳዊ ጠባያት የሚያገኝበትን ዕድል እናሳጣዋለን።
ይሄን ማጣራት የምትፈልጉ ሰዎች የትዳር ጓደኞችሁን ወይም ልጆቻችሁን
በጥፋታቸው እናንተ ይቅርታ እየጠየቃችሁ አሳዩአቸውና ከጥቂት ጊዜ በኋላ
ምን እንደሚከሰት ታያላችሁ።



ከዚህ ይልቅ፣ ያዘነብን ሰው (በእርሱም ጥፋት ቢሆን) ነገሩን የሚያስተ
ካክልበት መልካም አጋጣሚ የሚያገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ግን ጠቢብነት
ነው። የበደለ ሰው ይቅርታ የመጠየቅ ኀላፊነት ቢኖርበትም፣ ተበዳይ ነገሮች
በሰላም እንዲስተካከሉ መንገድ ቢያመቻች፣ ለስምምነት ራሱን ቢያዘጋጅ ይመ
ሰገናል። ችግሩ እንዲወገድ በዳዩን ለማነጋገር ተነሣሽነቱን መውሰድ የሚጠበቅ
የእግዚአብሔር መንግሥት አሠራር ነው (ማቴ. 5፥23-24)። የሰው ልጅ እግ
ዚአብሔርን ቢበድለውም፣ ሰው ንስሓ ገብቶ እርቅ ያወርድ ዘንድ ሁሉን ያመ
ቻቸው እግዚአብሔር መሆኑን መዘንጋት የለብንም። የበደለንን ሰው እግዚአብ
ሔር ይቅር እንዲለው መጸለይም ይቻላል፤ ልብን ከቂም ማጽዳት መንፈሳዊነት
ነውና። ጌታ ኢየሱስ መስቀል ላይ ያዋሉትን ሰዎች፣ ይቅርታ ሳይጠይቁትና
ንስሓ ሳይገቡ፣ "አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"
ማለቱ ለዚህ ትክክለኛ ማሳያ ነው (ሉቃ. 23፥34)። ተበዳይ እነዚህን ሁሉ ሊያ
ደርግ ይችላል፤ በዳዩን ይቅርታ እንዲጠይቅ ግን መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም!

ይልቁኑ ጥፋት የፈጸመ፣ በደል ያደረሰ ሰው ማንንም ሳይጠብቅ ቶሎ
ይቅርታ መጠየቅ አለበት። ብልኀ ሰው እንደ ዳዊት የምሩን ይናዘዛል እንጂ ዛሬ
ነገ በማለት ሲያመነታ አይከርምም፤ ከአካን ውድቀት ይማራል (ኢያሱ 7)።
ዊሊያም ኔቪንስ እንደሚናገረው፣ "ንስሓ ለመግባት ጊዜ የሚጠብቅ ሰው፣ ሲጠ
ብቁት የማይመጣን ነገር ነው የሚጠብቀው። በዚህም ላይ ሰው ራሱ ሊፈጽም
የሚገባውን ነገር መጠባበቁ ግራ ገብ ነው።"[11]

## ከልሔቁ - ይቅርታ ማድረግ

መንፈሰ ብርቱዎች ሲያጠፉ ይቅርታ ይጠይቃሉ፤ ይቅርታ ሲጠየቁም ይቅርታ
ያደርጋሉ። መንፈሰ ደካሞች ግን ይቅርታ መጠየቅ ሽንፈት ይመስላቸዋል፤ ይቅ
ርታ ማድረግም ሞታቸው ነው። ማሃተማ ጋንዲ፣ "ደካማ በፍጹም ይቅርታን
አያውቅም፤ ይቅርታ የብርቱዎች መገለጫ ነው" ያሉት ለዚህ ይሆናል።

ሉዊስ ስሜደስ፣ "ይቅርታ ማድረግ ማለት እስረኛን መፍታት ነው፤
ያም እስረኛ አንተ ነህ" ይሉናል። ይቅርታ በማድረግ ራሳችንን ነጻ እናወጣ
ለን። ቂመኝነት መርዝ ነው፤ ስለዚህ ይቅርታ አለማድረግ ራሳችኑ ነው የሚጎ
ዳን። የበደለውን ሰው የጎዳ እየመሰለው ይቅርታ የማያደርግ ሰው፣ ጠላቱን
ለመጕዳት ሲል ራሱ መርዝ እንደሚጠጣ ቂል ነው። ይቅርታ ሳያደርጉ መቅ
ረት ራስን ከመጕዳት በቀር ጥቅም የለውም።

ራሳቸውን ይቅር ባለማለት የሚቸገሩም ሞልተዋል፤ በእኔ ዕይታ እነ
ዚህ ኅሊና ያላቸው ሰዎች ናቸው። ነገር ግን ጸጸታቸውን በንስሓ አወራርደው

ነጻ ካልወጡ ሰይጣን ኅሊናቸውን በክስ እየቀወረ ሊጫወትባቸው ይችላል:: የአስቆሮቱ ይሁዳ ከእነዚህ ዐይነት ሰዎች አንዱ ይመስለኛል:: መሳሳቱን ዐውቆ ተጸጸተ፤ ይህንንም የካህናት አለቆች እንዲያውቁለት ጣረ፤ በጥፋቱ ያገኘውን ጥቅም አሽቀንጥሮ ጣለ (ሰዎች ይህን ማድረግ ሲከብዳቸው ዐይቻለሁ):: ሆኖም ንስሓ በመግባት የእግዚአብሔርን ምሕረት መቀበልም ሆነ ራሱን ይቅር ማለት አቃተው:: ስለዚህ የሰይጣንን ክስ መቋቋም አልቻለምና በቀጭን ገመድ ራሱን አንጠለጠለ (ማቴ. 27፥3-5):: ሌሎችን ይቅር አለማለት እግዚአብሔርን መበደል ነው (ኤፌ. 4፥31-32)፤ በዚያው ልክ፣ "በራሳችን ላይ መመረር፣ በራሳችን ላይ ቂም መያዝና ራሳችንን ይቅር ያለ ማለትም ኀጢአት ነው::"[12] ስለዚህ ራሳቸውን ይቅር የማይሉ ሰዎች ኀጢአት እየሠሩ መሆኑን ይወቁት::

ይቅርታ ማድረግ ይከብድ ይሆናል፤ ይቅርታ አንድ ሰው ሊከፍለን የሚገባውን ብድር መሰረዝ ማለት ነው:: ሆኖም ይቅርታ ከትናንት መላቀቅም ነው:: ይቅርታ ስናደርግ የተበዳሪውን የዕዳ ጽሕፈት እንቀድዳለን፤ ስለዚህ ብድሩን መቼም አናገኝም::[13] ይቅርታ መጠየቅ ለብዙዎቻችን ጣር ቢሆንብንም፣ ከባዱ ነገር ይቅርታ ማድረግ ይመስለኛል:: ይቅርታ ጠያቂው የሠራውን ሠርቶ ከዐንገቱም ይሁን ከአንጀቱ ይቅርታ ሊጠይቅ ይችላል:: ተበዳዩ ግን ቍስሉ እያመመው እንኳ ይቅርታ መስጠት ይኖርበታል::

ሊጋቡ ቀን እየቈጠሩ ያሉ ፍቅረኞችን ዐውቃለሁ:: ያው ፍቅረኞች በየትንንሹ ነገር ሲኮራረፉና ይቅርታ ሲባባሉ ይውሉ የለ? እነዚህም ይኸውናቸው:: እርሷ ይቅርታ ለመጠየቅ ገና ተናግራ ከመጨረሷ በፊት እርሱ ይቅር ሊላት አይቸገርም:: ለከርክር የሚጠቅመው ሆኖ ባገኘው ቍጥር ግን "የበደሏን ዝርዝር" ቅደም ተከተሉን ሳያዛንፍ ማቅረብም የዚያኑ ያህል ይቀለዋል:: ይቅርታ ማድረግ ማለት ግን ይቅርታ ያደረጉበትን ጕዳይ በደለኛውን ሰው ለመጕዳትም ሆነ ለመቃወም በማስረጃነት ዳግመኛ አለማቅረብ ነው:: እርሱ ይቅርታ ሲጠይቃት ደግሞ "ተሳስቻለሁ ይቅርታ" በማለት ሙሉ ዐረፍተ ነገር ካልተናገረ አትለቀውም፤ "'ይቅርታ' የሚለው ነጠላ ቃል የእኔን ቍጣ ለማብረድ የምትናገረው እንጂ ጥፋትህን ማመንህን አያሳይም" ትላለች::

አንዳንዴ "ይቅርታ" የምንለው ከልባችን ሳይሆን ነገር ለማብረድ ስንል ብቻ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ልባዊ ይቅርታ ጥቅሙ ብዙ ነው:: እነዚህም ፍቅረኞች በተደጋጋሚ እየተጋጩ ይቅርታ ቢጠያየቁም ይበልጥ እየተጣበቁ ሲሄዱ እንጂ ሲራራቁ አይታይም:: ትዳርንም ከሁለት ፍቅረኞች ቤት ይልቅ፣ የሁለት ይቅር የሚባባሉ ሰዎች ቤት አድርጎ መውሰድ ለእውነታው የተጠጋ ትርጓሜ የሚኖረው ለዚህ ነው:: ቤት በይቅርታ ይጸናል:: ከይቅርታ ውጭ ፍቅር የለም፤ ከፍቅር ውጭም ይቅርታ የለም:: የተበላሹ ነገሮች መስተካከል የሚችሉ



ትም በጸጋና በይቅርታ ብቻ ነው፤ "ፍቅር ብዙ ኀጢአትን ይሸፍናልና" (1ጴጥ. 4፥8):: ይቅርታ ፍቅር ላይ፣ እውነት ላይ፣ ትሕትና ላይ መመሥረት አለበት::

ከልቡ ለሚጸጸት ሰው ልባዊ ይቅርታ መስጠት ፈርጀ ብዙ ጥቅሞች አሉት:: አንደኛ፣ በደለኝነት የሚያመጣውን የጸጋ አልባነት አዙሪት መስበር የሚችለው ይቅርታ ብቻ ነው:: ሁለተኛው የይቅርታ ኀይል ደግሞ በጥፋተኛው ሰው ውስጥ የተገነባውን የበደለኝነት ምሽግ መስበር መቻሉ ነው:: ይቅርታ እነዚህን ሁለት ነገሮች የሚያደርገው ተበዳዩንም ከበዳዩ ጋ ተመሳሳይ ስፍራ ላይ በማስቀመጥ ነው::[14]

በወንድሜ ዐይን ውስጥ ያለውን ስንጥር ይቅር ማለቴ የዐይኔ ግንድ በእግዚአብሔር ይቅር መባሉን እንዳስታውስ ያደርገኛል:: እኔም ሆንኩ በዳዬ በዚህ ተመሳሳዮች ነን ማለት ነው:: ዋልተር ዊንክ ይህንን በአስደናቂ ሁኔታ ይገልጸዋል፤ "በሌላኛው ሰው ውስጥ ያለው 'ስንጥር' በዚህኛው ዐይን ውስጥ ያለው የዚያው ግንድ ስንጣሪ ነው::"[15]

ተበዳዮችን ከበዳዮች ጋር አንድ የሚያደርጋቸው ነገር አለ፤ ሁለቱም የእግዚአብሔር ምሕረትና ይቅርታ የሚያስፈልጋቸው መሆኑ:: ለሰዎች ይቅርታ ስናደርግ እኛም የእግዚአብሔር ይቅርታ የሚያሻን ምስኪኖች መሆናችንንና እርሱ ለሸከም የከበደ ኀጢአታችንን ለቍጥር ለሚታክት ጊዜ ይቅር እንዳለን እናስታውሳለን:: ሌላውን ይቅር ካላልን ደግሞ በደላችን ይቅር አይባልም:: አሊያ፣ "እኛም ደግሞ የበደልነውን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን" በማለት መጸለይ አንችልም:: ምክንያቱም፣ "እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር ይላችኋል:: ነገር ግን የሰዎችን ኀጢአት ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁም ኀጢአታችሁን ይቅር አይልላችሁም" ተብሏልና (ማቴ. 6፥12-15 - አ.መ.ት)::

ይቅር ማለት ቀላል አይደለም፤ ሕመም አለው:: በተለይ በደል ያደረሰብን ሰው የቅርባችን ወይም የምናምነው ሰው፣ ማለትም መጋቢያችን ወይም የትዳር ጓደኛችን፣ ወላጃችን ወይም ልጃችን ከሆነ ቍስሉ ነፍሳችን ውስጥ ተቀብሮ ለመቅረት ይታገለን ይሆናል:: ሮናልድ ደን እንደሚናገሩት ይህ የኖረ ታሪካችን ነው፤

> ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከወዳጅ በተሰነዘረ ፍላጻ በተጐዱ ሰዎች ታሪክ የተሞላ ነው፤ አቤል በወንድሙ ቃየን ተገድሏል፤ ዔሳው ብኵርናውን በወንድሙ ያዕቆብ ተሠርቋል፤ ዮሴፍ በወንድሞቹ ተከድቷል፤ ጌታ ኢየሱስ በሐዋርያው ጴጥሮስ ተክዷል፤ ሐዋርያው ጳውሎስም እስር ቤት ሳለ በወንድሞቹ ተትቷል::[16]

ሆኖም "ይቅር ለማለት ልቤ እምቢ አለኝ" የሚሉ ሰዎች ቍጥር ቀላል አይደለም። እዚህ ጋ ግን አንድ ነገር ማወቅ አለብን፤ "ይቅር ማለት የልብ ሳይሆን የፈቃድ ጕዳይ ነው። ይቅር ማለት ባይሰማን እንኳ ይቅር ለማለት ወስነን ስሜቱን በጊዜው እንዲያመጣው እግዚአብሔርን መታመን እንችላለን።"[17] ምክንያቱም፣ "ይቅርታ በክርስትና ሕይወት ጐዳና ላይ በምርጫ የሚካተት አይደለም። ወደድንም ጠላን ይቅር ከማለት በቀር ምርጫ የለንም። ይቅርታ ስሜት አይደለም፤ ውሳኔ ነው። ይቅር የተባሉ ይቅር ማለት አለባቸው።"[18] ስሜት በምንም መልኩ የየትኛውም ውሳኔአችን አለቃ መሆን የለበትም።

ይቅር ለማለት ያለ መፈለግ ጌታን መበደል ቢሆንም፣ ይቅርታ ማድረግ እየፈለጉ ዐቅም የሚያጡ ወይም ዐቅም ማጣታቸውን የሚናገሩ ደጋግ ሰዎችም ይኖራሉ። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ (ርዳታ) ቢጠይቁ መልካም ነው፤ መፍትሔም ይሆናቸዋል። ፊሊፕ ያንሲ ስለ ጸሎት በጻፉት መጽሐፋቸው እንዲህ ይላሉ፤

> በልቤ ቂም ካለና ይቅር ለማለት ዐቅም ካጣሁ፣ ቍስሌንና ያቈሰለኝን ሰው ይዤ ወደ እግዚአብሔር እቀርብና በራሴ ማግኘት ያቃተኝን ብርታት እግዚአብሔር እንዲሰጠኝ እጸልያለሁ። ... በውጤቱም ከባዱን ሸክሜን በተሻለ ሁኔታ ሊሸከም ለሚችለው ለእርሱ አስተላልፋለሁ። ከጊዜ ጋር ቍስሉም እየሻረ ይሄዳል። እኔ በራሴ ውስጥ ማድረግ ያልቻልኩትን ነገር እግዚአብሔር በውስጤ ይሠራልኛል።[19]

ይቅር የምንልበት መነሻ ለእኛ የተደረገልን ምሕረት መሆኑን ሁሌም መረዳት ይኖርብናል። ይቅርታ የምናደርገው ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ወይም ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖረን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እኛን ስለ ማረን ነው። ይቅርታ የምናደርገው የበደለን ሰው ድጋሚ እንደማይበድለን ስላ ረጋገጠልን አይደለም፤ እግዚአብሔር ይቅር ስላለን ነው። ይቅርታ ለማድረግ፣ የበደለን ሰው ዳግመኛ እንደማይበድለንና የአካሄድ (የጠባይ) ለውጥ ማምጣቱን ማረጋገጥ አይኖርብንም፤ ይቅርታችንን ሰጥተን፣ ልባችንን ከቁርሾና ከምሬት ነጻ ማውጣት ይበጀናል። ያ ሰው ዘላቂ ለውጥ ማምጣቱን ማረጋገጥ የሚያስፈልገን በተፈጠረው በደል ምክንያት የወሰድነውን እርምጃ (ውሳኔ) ለመቀየር ስናስብ ብቻ ነው፤ ይቅርታ ለማድረግ አይደለም።

ይቅርታ የምናወርደው ለበደለን ሰው የእጁን ከሰጠነው በኋላም አይደለም፤ እግዚአብሔር እንዲሁ ይቅርታ ስላደረገልን ነው። የበደለን ሰው መጥቶ ይቅርታ ስለ ጠየቀንም አይደለም። በእርግጥ ይቅርታ ማድረጋችንን መንገር ያለብን ይቅርታ ስንጠየቅ ብቻ ቢሆንም፣ ይቅርታውን ለማድረግ እስከንጠየቅ



መጠበቅ አያስፈልገንም። ይህን ባለማወቅ፣ አሁን በሕይወት በሌሉ ሰዎች ላይ ሳይቀር ቁርሾ ኖሮአቸው በቂም ነቀርሳ የሚሠቃዩ ሰዎች አሉ። ይቅርታ ባንጠየቅም ልባችንን ከቂምና ከቁርሾ ነጻ ማድረግ ይጠበቅብናል።

በዚሁ መሠረት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ ተቀብሎ ለሰው ይቅርታ ማድረግ ያቃተው ሰው ምን እንደሚመስል ጌታ ስለ ሁለት ባለ ዕዳ ሰዎች ታሪክ ነግሮናል። ታሪኩ ለሐዋርያው ጴጥሮስ፣ "ወንድሜን ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው?" የሚል ጥያቄ ምላሽ ነው። "አንተንስ እግዚአብሔር ስንት ጊዜ ይቅር ይበልህ?" ነው መልሱ። ምክንያቱም ሊከፍለው የማይችለው ትልቅ ዕዳ የተተወለት ባሪያ፣ ሊከፈል የሚችልን ዕዳ በተራው ይቅር ማለት ካቃተው መጀመሪያ የተሰጠው ይቅርታ ይሰረዝበታል፤ ምሳሌው እንደሚነግረን። ታሪኩ የሚጠናቀቀው፣ "ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባቴም እንደዚሁ ያደርግባችኋል" በሚል ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው (ማቴ. 18፥23-35)። ጆርጅ ሄርበርት እንደሚሉት፣ "ለሌላው ይቅርታ ማድረግ የማይችል ሰው፣ ራሱ የሚሻገርበትን ድልድይ የሚሰብር ሰው ነው"።

ፊሊፕ ያንሲ እንዲህ ይናገራሉ፤

> እነዚህ ቃላት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይኖሩ አጥብቄ ብመኝም፣ ያውም በራሱ በክርስቶስ አንደበት ነው የተነገሩት። እግዚአብሔር ግዙፍ የውክልና ሥልጣን ሰጥቶናል፤ ሌሎችን ይቅርታ ስንከለክል፣ ለእግዚአብሔር ይቅርታ ብቁ አለመሆናቸውን እየወሰንን ነው፤ በእኛም ላይ ይኸው ነው። በሆነ ምስጢራዊ መንገድ፣ መለኮታዊ ይቅርታ በእኛ ይወሰናል።[20]

ይቅርታ የጸሎት ቅድመ ሁኔታ መሆኑንም ጌታችን ተናግሯል፤ "የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፤ ይሆንላችሁማል። ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ፣ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኀጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፣ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት" (ማር. 11፥22-25)። ስለዚህ ይቅርታ የማያደርግ ሰው ጸሎቱ ተቀባይነት አያገኝም። ይህ ብቻ ግን አይደለም፤

> በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሁሉ ይልቅ የሚሠቃየው ሰው ከቍጣ፣ ከቅሬታና ይቅር ካለማለት ጋር ተጣብቆ የሚኖር ሰው ነው፤ ታሥሯል፤ መንፈስን አጥፍቷል፤ ጸሎቱም አይረባም፤ አምልኮው ፈራርሷል። ምንም ነገር ቢሠራ እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችልም። የዚህ ሰው የምስጋና መዝሙር በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው፤ ለጸሎቶቹም ጆሮዎቹ ዝግ ናቸው፤ ይቅርታን ፍሊጋ የሚያደርገው ጩኸትም ችላ ይባላል።[21]

መቼም መዘንጋት የሌለብን ነገር አለ፤ እግዚአብሔር ይቅር የሚለን እኛ ሰዎችን ይቅር ስንል ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም፣ "ምሕረት ያላደረገ ሁሉ ያለ ምሕረት ይፈረድበታል" (ያዕ. 2፥13 - አ.መ.ት)

**ሠልስቱ - ከዚያስ?**

"ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?" የሚለው የጴጥሮስ ጥያቄ፣ (ማቴ. 18፥21) ከመርሳት ይልቅ መቁጠር እንደሚቀለን ያስረዳል፡፡ ሮናልድ ደንም ሲናገሩ፣ "ለመርሳት መሞከር አንድን ነገር ለማስታወስ ምርጡ ዘዴ ነው" ይሉና "ይልቁኑ የደረሰባችሁን በደል በምታስታውሱበት ጊዜ ሁሉ፣ ይቅር ማለታችሁንም አስታውሱ" በማለት መፍትሔውንም አብረው ይመክራሉ፡፡[22]

በተጨማሪ ግን እዚህ ጋ ጥቂት ነገሮችን ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡ ይቅርታ ቅድመ ሁኔታ ስለሌለው በዳዩ ሰው ከጥፋት መንገዱ ባይመለስም ይቅር ማለት እንዳለብን ተነጋግረናል፡፡ ነገር ግን ነገ ሌላ ጥፋት እንዳይፈጸም እርምጃ መውሰድ ያስፈልገንም ይሆናል፡፡ አጥፊው ከተደጋጋሚ የጥፋት መንገዱ በይቅርታ ተመልሶ እስኪታረም ማዕቀብ መጣል ግድ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ወሳኝ እርምጃ የምንቀይረው ይቅርታ ስለ ተጠየቅን ብቻ ሳይሆን፣ ያ ሰው አስፈላጊውን የለውጥ እርምጃ ሲወስድ ነው፡፡ አንዳንድ ገራገር ሰዎች ይቅርታ ስለ ተጠየቁ ብቻ ነገሩ ሁሉ የተለወጠና የተሻሻለ ስለሚመስላቸው ተመሳሳይ ወጥመድ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይቅርታ ማድረግ ለነገ ጥንቃቄ እንዳናደርግ አይከለክልም፤ ምክንያቱም ይቅርታ ከትናንት ጋር ነው የሚያያዘው፤ የለውጥ ውሳኔ የነገ ጉዳይ ነው፡፡

ለምሳሌ የተሰጠውን ገንዘብ አላግባብ የሚያባክን ልጅ ይቅርታ ሲጠይቅ ይቅርታ መስጠት ተገቢ ቢሆንም፣ ከዚህ በኋላ የገንዘብ አወጣጡን መቈጣጠርና እንዳስፈላጊነቱ ገንዘብ መስጠትን ማቆም ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ችግር በተፈጠረ ቍጥር መቈጣትና መጮኽ የሚያዘወትር ባል ይቅርታ ሲጠይቅ ይቅርታ መስጠት የሚጠበቅ ቢሆንም፣ መጮኹን ትቶ በእርጋታ መናገር እንዲጀምር መምከር ጥሩ ነው፡፡ ይህን መልመድ ካቃተው ጮኾ እስኪጨርስ ወጣ ማለት ወይም ጎረቤት መቈየት ይቻላል፡፡ በምስጢር መያዝ ያለባትን ነገር ላገኘችው ሁሉ እያዳረሰች ያስቸገረችን ሚስት ይቅር ብሎ ከዚህ በኋላ ለእርሷ ምስጢር ማካፈልን ማቆም መፍትሔ ለማበጀት ያግዛል፡፡ ነገም ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይፈጸም ምንጩን ለማድረቅ የራሱ አስተዋጽኦ አለው፡፡



ይቅርታ የለውጥ ሂደት ጅማሬ ነው፤ ፍጻሜ አይደለም፡፡ በተለይ አገልጋዮችን በሚመለከት የተለየ ጥንቃቄን ይሻል፡፡ ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ አገልጋይ ሊኖረው ስለሚገባው ሥነ ምግባር መስፈርቱን ለጢሞቴዎስ ሲነግረው፣ "ስሙ እንዳይነቀፍ ... በውጭ ባሉት ዘንድ መልካም ምስክርነት ሊኖረው ይገባል" ይለዋል (1ጢሞ. 3፥7 - አ.መ.ት)፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው በይፋ የታወቀ ውድቀት ካለበት ይቅርታ ቢጠይቅም ሮጦ ወደ አገልግሎት መመለስ አይኖርበትም፡፡ ይቅርታ መጠየቅ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የተግሣጽ እርምጃም ያስፈልጋል፡፡

በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አንዱ ተማሪ የሌላኛውን ንብረት መስረቁ ተደረሰበት፡፡ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር መጀመሪያ ካነጋገረው በኋላ ለትንሽ ጊዜ ገለል ብሎ ራሱን እንዲያይ መክሮ አሰናበተው፡፡ ከዚያም በቀጣዩ ሳምንት አስጠርቶ፣ "ሕይወት እንዴት ነው?" ሲል ጠየቀው፡፡ ተማሪውም ሕይወት ጥሩ እንደ ሆነና እሑድ ዕለት በአንዲት ቤተ ክርስቲያን በዝማሬ ከማገልገሉ ባሻገር በቀጣይ ሳምንታትም ሌሎች አገልግሎቶች እንዳሉት ዘረዘረ፡፡ ቁጭ ብሎ ሕይወቱን ከመመርመር ይልቅ አገልግሎቱን መቀጠል ለምን እንደ ፈለገ ሲጠየቅ፣ "አስቀድሜ የያዝኳቸው አገልግሎቶች ስለሆኑ ነው" የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ለመሆኑ ቅድሚያ የምንሰጠው ለየትኛው ነው? ለሕይወት? ወይስ ለአገልግሎት? ከሕይወት ያልተረፈ አገልግሎት ምናችን ነው?

አሁን አሁን ግን ሰዎች ነውራቸው በኢአማንያን ዘንድ እንኳ እየታወቀ ምንም ያልተፈጠረ ያህል መድረክ ላይ ሲወራጩ ታዝበናል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ምስል የሚያጠፋ በደል ቢፈጽሙም ራሳቸውን ከማዋረድ ይልቅ በተቃራኒው ራሳቸውን ከፍ ከፍ ሲያደርጉ እናያለን፡፡ ከአገልግሎት ገለል ማለት ሲኖርባቸው፣ የእግዚአብሔርን መድረክ መዋያ ማደሪያ አድርገውት ይታያሉ፡፡

በጓዳቸው አድገው ያልጨረሱ ሰዎች በአደባባይ ሲወድቁ ብናይም፣ ይቅርታ መጠየቅና ነገሮች እስኪስተካከሉ ከመድረክ ገለል ሲሉ አንመለከትም፡፡ በንስሓ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስለ መቀበል ብናወራም፣

> የወደቁ ሁሉ እንደገና ቆመው ያገለግሉ ይሆናል ወይም ማገልገል ይችላሉ ማለት አይደለም፡፡ በአንዳንዶች ኀጢአትና ውድቀት የተፈጸመው ጥፋት ከፍተኛ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሙሉ አገልግሎት እንደሚመለሱ ማሰብ ተቀባይነት የሌለው ነገር ነው፡፡[23]

በመሆኑም እንዲህ ዐይነቱ ሰው አገልግሎቱን ጋብ በማድረግ ራሱን መፈተሽ ይኖርበታል፡፡ ይቅርታ የለውጥ ሂደት መጀመሪያ በመሆኑ እንዲህ ዐይ

ነት ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ጋር በመመካከር ለተወሰነ ጊዜ ከአገልግሎት መታቀብ አለባቸው፤ በዚህም ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ያላቸውን ክብር ይገልጣሉ። በዚህ መንገድ ከስብከታቸው ባሻገር ሕይወታቸውም ሌሎችን ለማስተማር ይውላል።

በዚህ ጉዳይ አንዳንድ መጋቢያንና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ትልቅ ደዌ እንዳለባቸው ይታያል። ኀጢአቱ ይፋ የወጣ አገልጋይ አገልግሎቱን አቁሞ ራሱን እንዲመረምር ከመምከር ይልቅ ቲፎዞነታቸውን ለማሳወቅ ኮንፈረንስ እያዘጋጁ ይጋብዙታል። በዚህም ሰውየው መሳሳቱንና ይቅርታም መጠየቅ እንዳለበት እንዳያስተውል በማሳወር የጎላ ሚና ይጫወታሉ። አገልጋዩም እንደ ባለውለታ የሚቀበለው፣ ከአገልግሎት ገለል ብሎ ሕይወቱን እየመረመረና ክፍተቱን እየፈተሸ እንዲቆይ የሚመክረውን ሳይሆን፣ መድረክ የሰጠውንና ፖስተር ላይ ያስለጠፈውን ሰው ይመስለኛል። ይቅርታና ንስሓ እንዲህ መቀለጃ የሆነው እንዴት ነው?

በመጨረሻም፣ ይቅርታ ስንጠየቅ ይቅርታ ጠያቂው ጥፋቱ ተሰምቶት ራሱን ዝቅ አድርጎ ይመጣል እንጂ እኛ እንዲዋረድና ዝቅ እንዲል መጠየቅም ሆነ መጠበቅ የለብንም። የይቅርታ ጠያቂውን ሰብዕና ለማዋረድ ማሰብ ነውርን አለማወቅ ነው። በትሕትና ይቅርታ ለሚጠይቅ ሰው ተገቢውን አክብሮት መስጠትም በሳልነት ነው። ይቅርታ ቁጭትን መወጫ አይደለም፤ ለዕርቅ ድልድይ መሥሪያ ነው። ይቅርታውን ለሌላ ጊዜ በማጥቂያነት መጠቀምም ተገቢ አይደለም። እንዲያውም ያ ሰው እንዲበድለን እኛ ያደረግነው አስተዋጽኦ መኖር አለመኖሩን ማጤንና እኛም የራሳችንን ኀላፊነት መውሰድ እንዳለብን መዘንጋት አይኖርብንም፤ ሁልጊዜም። ምክንያቱም፣

ተጠየቅ ልጠየቅ
 በላ ልበልሃ - ማለት በቻለበት፤
ቅንጣት ታህል ቅንጣት፣
ደቃቅ ታህል ዕብሪት፣
ጥፋት ያዋጣበት፤
'ገዳይ' ብቻ ሳይሆን 'ሟችም' ዕዳ አለበት።
ዐልፎ ሰው ባይገድልም፣
በጁ ነፍስ ባይጠፋም፣
በዚያው በራሱ ሞት
 ሟችም እጁ አለበት።
በፍቅሩ ከልሎት ሞቱን ካላስጣለ፤
ሕያው ብቻ አይደለም - 'የሞተም' ገደለ![24]



ማስታወሻ

1. Philip Yancey, *Prayer: Does It Make Any Difference?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2006), 271.
2. ተፈራ ኀይለ ሥላሴ (አምባሳደር)፤ *ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ ከ፲፰፻፺፯-፲፱፻፳፯* (አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 1999 ዓ.ም) ገጽ 26-27።
3. መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቱኒ ተምረን ወጣን* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 88።
4. Yancey, *Prayer*, 31.
5. Clayborne Carson, *The Autobiography of Martin Luther King Jr.* (London: Abacus, 2008), 128.
6. R. T. Kendall, *Second Chance* (London: Hodder & Stoughton, 2009), 164.
7. Philip Yancey, Brenda Quinn, *Meet the Bible* (Grand Rapids: Zondervan, 2000), 216.
8. ዝኒ ከማሁ።
9. ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *የወዳጅ ፍላጻ* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 116።
10. ዝኒ ከማሁ።
11. Kendall, *Second*, 70.
12. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 220።
13. Henery Cloud & John Townsednd, *Boundaries* (Grand Rapids: Zondervan, 1992), 267-268.
14. Yancey, Quinn, *Meet the Bible*, 91.
15. Walter Wink, *Engaging the Powers: Discernment and Resistance in a World of Domination* (Philadelphia: Fortress Press, 1992), 271.
16. ሮናልድ ደን፤ *የወዳጅ ፍላጻ*፣ ገጽ 11።
17. Yancey, Quinn, *Meet the Bible*, 274.
18. ሮናልድ ደን፤ *የወዳጅ ፍላጻ*፣ ገጽ 123።
19. Yancey, *Prayer*, 313.
20. Philip Yancey, *What's So Amazing About Grace?* (Grand Rapids: Zondervan, 1997), 88.
21. ሮናልድ ደን፤ *የወዳጅ ፍላጻ*፣ ገጽ 130።
22. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 143።
23. Kendall, *Second Chance*, 201.
24. አብርሃም ረታ ዓለሙ፤ *እቸኩችክ፡ የቃሊቲ እንጉርጉሮዎች* (አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም)፣ መግቢያ ገጽ።

# ዕፍረትን ያያችሁ!?

ልጅት በደስታ ተሞልታለች:: የነበረችበትን ትርጒም የለሽ የጭንቅ ኑሮ ስታስብ አሁን ያገኘችው ሰላምና ዕረፍት አስደንቋታል:: አዲስ ክርስቲያን ብትሆንም ክርስቶስ የሰጣትን ዕፎይታ ለሁሉ ትመሰክራለች:: የቆመው ታከሲ ጋቢና ውስጥ ለሹፌሩም የምትነግረው ይህንኑ ነው:: ሹፌሩም ባልተለመደ አርምሞ አቀርቅሮ ያዳምጣል:: ተናግራ ስትጨርስ የእርሱን ምላሽ በመጠበቅ ጸጥ አለች::

"የምትዪውን አንድም አልተከታተልኩም:: ጭንሽን ነበር የማየው" አላት ሹፌሩ ጭኖቿን እየጠቆመ:: ገና ዛሬ ያወቀቻቸው ይመስል ደንግጣ አየቻቸው:: አጭሩና ጠባቃው ቀሚስ ጭኖቿን መሸፈን አቅቶታል:: በዝምታ በሩን ከፈተችና ከመኪናው በዝግታ ወረደች:: ያገኘችው ሕይወት የሚያድግ በመሆኑ ልብሷ ልቧን ተከትሎ መገበሩ አይቀርም፤ አሁን ግን ከልቧ በተቃራኒነት ነው የቆመው::

አለባበስ እያስቸገረ ነው:: ከላይ ጡትን ለማሳየት ሲባል ሲረግብ፣ ከወገብ ደግሞ እምብርትን ለማስመረቅ ሲባል ቲ ሸርቱ ወደ ላይ፣ ሱሪው ደግሞ ወደ ታች ሲሳብ፣ ጭንን ለማስጎብኘት ተብሎ ቀሚሱ ወይም ሱሪው ከጒልበት በላይ ሲሸበሸብ - ብቻ ምን አለፋን ከተሸፈነው ያልተሸፈነው ክፍል እያደር እየበዛ ነው:: አንዳንድ አይነኬ የአካል ክፍሎችን ደጉ ጌታ ከመጀመሪያውም አስተማማኝ ቦታ ከተታቸው እንጂ ጉድ ፈልቶ ነበር (ዝግመተ ለውጥ በሂደት እዚያ ቀረቀራቸው ልበል ታዲያ?)

- ሀ -

ሰዎች ልብስን ያያሉ፤ እግዚአብሔር ልብን ያያል:: ታዲያ ምን ይሻላል? ሀ) ልብን ማሳመር ለ) ልብስን ማሳመር ሐ) ልብንም ልብስንም ማሳመር መ) መልሱ አልተሰጠም

አንዳንዶች እግዚአብሔር ልብን ስለሚያይ፣ ለልብስ የሚደረግ ጥንቃቄ ፋይዳው አይታያቸውም፤ የልባቸውን ንጽሕና ሁሉ እንዲያይላቸው ደረታቸው ላይ ትንሽ መስኮት ቢኖር ይመኛሉ:: ያ መስኮት እስኪከፈት ልብሳቸውን አደብ የማስገዛቱ ፋይዳ ግን አልተገለጠላቸውም:: እነዚህ፣ "ስለ ሰው ቀድጄ ልልበሰው" በማለት የሚያዜሙ ናቸው::



ሌሎች ደግሞ ልባቸው በክፋት ተሞልቶ ውጪአቸውን በረጅም መጋረጃ ይጠቀልላሉ፤ ተንቀሳቃሽ ድንኳን ነው የሚመስሉት:: እነርሱ ግን በድንኳናቸው ሽንቁር ዐላፊ አግዳሚውን እየተመለከቱ በምኞት ይቃጠላሉ:: ምናልባት ከአለባበሳቸው የሚገኝ ነገር ቢኖር ሌላውን ከጥፋት ለመጠበቅ በጎ መዋጮ ሊሆን መቻሉ ነው:: የእነርሱን የልብ ንጽሕና ግን አያመለክትም::

ይህም ልባችንን ለእግዚአብሔር፣ ልብሳችንን ደግሞ ለሰው ስንል ማሳመሩን ተገቢ ያደርገዋል፤ እግዚአብሔር የሚያኖረን በሰዎች መካከል ነውና:: የእግዚአብሔር ሕግጋት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖርበትን ብቻ ሳይሆን፣ ሰው ከሰው ጋር የሚኖርበትንም መርሕ ያስቀምጣሉ:: ለምሳሌ ዐሥርቱን ትእዛዛት ለሁለት ከፍለን ብንመለከት፣ የመጀመሪያው ክፍል ሰውና እግዚአብሔርን ይመለከታል:: ሁለተኛው ደግሞ ሰውን ከሰው ጋር ያኖራል (ዘፀ. 20፥3-17):: በአዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ትእዛዛቱን ሁሉ በፍቅር አጠቃልሎአቸዋል:: ይህም ግን ሁለትዮሽ ነው፤ "ጌታ አምላክህን ውደድ" ፊተኛው፣ "ባልንጀራህን ውደድ" ደግሞ ኋለኛው (ማቴ. 22፥35-40):: እናም ለሰው መጠንቀቅ ይገባል::

ሰዎች ልብስን ያያሉ፤ በዚህም የለባሹን ማንነት ይገምታሉ:: ጥሩ ልብስ ለለበሰው የከበሬታ ቦታ ሰጥተው፣ ኰስቆል ያለውን ፊት ይነሡታል:: ጥቂት ያይደሉ ሰዎች ጥሩና ንጹሕ የለበሰን እንደ ተማረና እንደ ምግባረ ሸጋ ስለሚወስዱ፣ እንሰረቃለን ብለው ሳይገምቱ በዘነጠ ሰው ተሰርቀዋል (ሙሰኛው ሁሉ ዘናጭ አይደል እንዴ?):: ስለዚህ ሰዎች ከበሬታን ፍለጋ ውድ ልብስ ለብሰው ለመታየት የተቻለውንና ያልተቻለውን ሁሉ ያደርጋሉ:: የሥነ ምግባር ሕግንም እስከ መጣስ ይደርሳሉ::

ሰዎችን በአለባበሳቸው ብቻ እየመዘኑ ፊት መንሳትም ሆነ ማከበር ክርስቲያናዊ አይደለም:: "የወርቅ ቀለበት ያደረገና ያማረ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ጉባኤያችሁ ቢገባ እንዲሁም ያደፈ ልብስ የለበሰ ድኻ ሰው ደግሞ ቢገባ፣ ያማረ ልብስ ለለበሰው የተለየ አክብሮት በማሳየት፣ 'ለአንተ የሚሆን መልካም መቀመጫ ይኸውልህ' ብትሉትና ድኻውን ግን፣ 'አንተ በዚያ ቁም' ወይም 'ከእግሬ በታች በወለሉ ላይ ተቀመጥ' ብትሉት፣ ... በክፉ ሐሳብ የተያዛችሁ ፈራጆች መሆናችሁ አይደለምን?" (ያዕ. 2፥2-3 - አ.መ.ት)::

ልብስ የሁሉ ጒዳይ ቢሆንም በተለይ እኅቶችን ይመለከታል:: እኅቶች ለውበት የተለየ ዐይን አላቸው፤ ትኩረት ፈላጊም ናቸው:: ይህ ለውበትና ለትኩረት የሚሰጡት ቅድሚያም ሳይታወቅ ችግር ሲፈጥር ይገኛል:: አንዳንዶች ልበ ሙሉ አለመሆናቸውን በአልባሳት መሸፈን ነው የሚፈልጉት:: ልባቸው

በጌታ አላረፈም። ስለዚህ የተጋነነ የአድናቆት ጥማት አለባቸው። ልባቸው በክርስቶስ ባለመርካቱ፣ የሌሎች ሙገሳና ትኩረት ይርባቸዋል። ይህንን በቀላሉ ማግኚያው መንገድ ደግሞ ልብስ ነው። ስለዚህ አንድ ዐይናቸው ልብሳቸው ላይ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ አላፊ አግዳሚው ላይ ነው። እነዚህን ትኩረት ማጣት ይገድላቸዋል።

ልብሳቸው እያደር እያነሰና እየተሸራረፈ የመጣው ለዚህ ነው። (አንዳንዶቹ ለብሰው ሳይጨርሱ በችኮላ የወጡ ነው የሚመስሉት!)። ይህ ግን የራሱ ጠንቆች አሉት። ከአለባበሳቸው የተነሣ በማንነታቸው፣ በሞያቸው፣ በዕውቀታቸው ማግኘት ያለባቸውን ከበሬታ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። አንዳንድ ወንዶች ከፊታቸው ያለችውን ሴት መምህርነት፣ ተማሪነት፣ አገልጋይነት፣ አለቅነት (ሥራ አስኪያጅነት) ሳይሆን ሴትነቷን ብቻ እንዲያዩ ይገደዳሉ። ለዚህ ኀላፊው ማነው? በዚህ ላይ ደግሞ ባለ አጭር "ፓትሌት" ሱሪና ቀሚስ በማዘውተራቸው ወገቧ ላይ "ሞባይል" የሌላት ሴት እንዳትገኝ ወደ ማድረጉ እያዘነበለ ነው። እነርሱ ግን ቤተ እግዚአብሔር ሲሄዱ እንኳ ቦታውን የሚቃረን ልብስ ሲለብሱ ይታያል። በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን የሄደ ሁሉ ክርስቲያን አይደለም፤ ገና ክርስቲያን ለመሆን የሚሄዱም አሉና።

ቢሆንስ፣ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ሲኬድ ወንዱ የሱሪው ፓትሌት እስከ ጕልበቱ ወርዶ "ግልገል ሱሪው" መታየት አለበት? ሴቷንስ ውስጥ ሱሪዋ ወደ ላይ ተንጠልጥሎ ማየት አለብን? ("ፓንት" ማድረግ ብርቅ ነው እንዴ?) የመቀመጫስ ቦይ ለሁሉ የሚቀርብ ትርኢት ነው? (ቡዳ ቢቀር ምች የለም እንዴ?) ጉንጭና ጡትም ልዩነት አላቸው። ጡትየው መሸፈን አለበት፤ የባል ነውና (ምሳሌ 5፥19)። ታዲያ ሁሉም ሜዳ ላይ ከተሰጣ ባል ምን ተረፈው? (አንዳንዴማ ጡታቸውን እንዴት እንደሚያደርጉት ሲታይ፣ "አንደኛውኑ በትሪ ቢያቀርቡልን አይሻልም?" ያሰብላል)። ለመሆኑ ዕርቃኗን ለነፋስ ሰጥታ ከተቀመጠች ሴት ኋላ ተቀምጠን ስብከተ ወንጌልን እንዴት እንከታተል? (በቀሚስና ነጠላ የሚኬድበት የአያቶቻችን ቤተ ክርስቲያን ናፈቀኝ!)

ሰዎች ለአለባበሳቸው ትኩረት እንዳይሰጡ እየመከርኩ አይደለም፤ ይዘንጡ! ቀለሙ እርስ በርስ በማይጣጣም ልብስ ተዝጎርጉሮ ከአላፊ አግዳሚው ጋር "ማች" የሚያደርግ ሰው ምኑ ያምራል? በጠራራ ፀሓይ የእራት ልብስ ለብሰው የሚሄዱ ሴቶችንም ማየትስ ምኑ ያስደስታል? አንዳንዶቹ የተገላለጠ ልብስ ለመልበስ ካላቸው ጕጕት የተነሣ፣ ወገባቸው ላይ ተጠምጥሞ የሚያሽበሽበውን ሥጋ አጭር ቲሸርት ለብሰው ሲያስመርቁ ይውላሉ (የሚያምራቸውን እንጂ የሚያምርባቸውን አያውቁምና)።



ታላቁ መምህር፣ "ወደ ሴት ያየ [ወንድ] ሁሉ የተመኛትም ... በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል" በማለት አስተምሯል (ማቴ. 5፥27)። ይህም ወንድ ዐይኑ ሲያይ፣ ልቡ ሊመኝ እንደሚችል ነው የሚነግረን። አብዛኛውን ወንድ የተገላለጠ አካልና ገላ ላይ የተጣበቀ ልብስ የለበሰች ሴት ወዳለችበት የሚያዞረው የሆነ ኀይል አለ። ማየት ባይፈልግ እንኳ ዐንገቱ በራሱ ጊዜ የሚዞር ይመስላል። (ወንድ ሴትን ዞር ብሎ ማየት ትቶ ሴቲቱ ወደምትሄድበት አቅጣጫ ፊቱን አዞሮ የሚጠብቀው ሚስቱ አጠገቡ ስትኖር ነው።) እኅቶች ስለዚህ ጕዳይ እያወቁ አያውቁም። ስለሚያውቁማ ነው እንዲህ የሚለብሱት፤ ትኩረትን በመሻት። ሆኖም የዚህ ተፈጥሮ (ባሕርይ) ጥልቀት አይታወቃቸውም፤ ቢያውቁማ ለወንድሞቻቸው ሲሉ አለባበሳቸውን በገሩ ነበር።

ክርስቲያን እኅቶች፣ "ወንድሜን ከማሰናከለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም" ያለውን ሐዋርያ የሚረሱት አይመስለኝም (1ቆሮ. 8፥13)። ስለዚህ ሌላውን ፈተና ውስጥ የሚከት ልብስ ከሚለብሱ ልብሱን ጨርሰው ቢተዉትስ? ያ ሰው እነርሱን ባያይ እንኳ ወደ ኀጢአት መግባቱ ባይቀርም፣ እነርሱ ለምን ሰበብ ይሆናሉ? "መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም፤ ነገር ግን መሰናክሉን ለሚያመጣ ወዮለት" በማለት ጌታችን መናገሩን ያስተውሏል (ሉቃስ 17፥1)። በመሆኑም ክርስቲያን ሴቶች ገላቸውን በግላጭ የሚያሳይ ወይም የሚወጣጥር ልብስ አያስፈልጋቸውም።

ሱሪያቸው ረዝሞ መሬት እየጠረገ፣ ከላይ "ግልገል ሱሪአቸውን" እያስጎበኙ የሚሄዱ ወጣት ወንዶችም እየበዙ ነው፤ በየሲኒማው ከሚያዩአቸው ጥቍር አሜሪካውያን የወሰዱት ይመስለኛል። እነዚያ እንዲህ የሚያደርጉት በባርነት ዘመናቸው እግራቸው ላይ ይታሰር የነበረውን ሰንሰለት ለማስታወስ እንደ ሆነ ነው የሚነገረው። የእኛዎቹ ጎረምሶች ግን እንዲሁ ኮርጀውታል። እንዲህ ዐይነት ወጣት መንገድ ላይ ገጥሞኝ፣ "ኧረ ሱሪህ ወደቀብህ! ከፍ አድርገው እንጂ" የሚል ምክር ሰጥቼ ዐውቃለሁ። አንዳንዴ ወደማስተምርበት ክፍል ስገባ ሱሪያቸው ታች ወርዶ "ፓንታቸውን" እያስመረቁ ተከትለውኝ የሚገቡ ተማሪዎች ያጋጥሙኛል። ያኔ የሱሪያቸውን ወገብ ግራና ቀኝ ይዤ ብድግ በማድረግ እንደሚጠቀጠቅ የሲጋቱራ ጆንያ እየነቀነቅሁ ልብሳቸው ውስጥ ልከትታቸው እመኛለሁ።

ልብስ እርቃንን መሸፈኛ ነው። አዳምና ሔዋን ዕራቍታቸውን መሆናቸውን ሲያውቁ መጀመሪያ ያደረጉት ዕርቃናቸውን መሸፈን ነበር። ለዚህም አገር በቀል ምርት ነው የተጠቀሙት (ቅጠል ቀጣጥለው ለበሱ)። ዕርቃንን የመሸፈንን ተገቢነትም ለእኛ ለልጆቻቸው አስተማሩ (ዘፍ. 3፥7)። ስለዚህ በልብስ ዕርቃንን መሸፈን የዘራችን ነው!

እግዚአብሔርም በዚህ ተስማምቷል፤ የልብሱ ሥሪት የቅጠል በመሆኑ ግን አልተደሰተም:: ስለዚህ ቅጠሉ በነፋስና በፀሓይ ጠውልጎ ገመናቸው እንዳ ይገለጥ የተሻለ ልብስ አዘጋጀላቸው፤ "ሌዘር" አለበሳቸው (ዘፍ. 3፥21):: የጥንት፣ ጥንት፣ ጥንት ምንጅላቶቻችንና የሁልጊዜውም እግዚአብሔር ተመሳ ሳይ ነገር ይነግሩናል፤ ልብስ ዕርቃንን ሊሸፍን ይገባል::

- ለ -

ሰዎች ልብስን ያያሉ፤ እግዚአብሔርም ልብስን ያያል:: ስለዚህ ምን ይበጃል?
ሀ) ልብስን ማሳመር ለ) ልብስ የራሱ ጉዳይ ሐ) መልሱ አልተሰጠም

አይሁዳውያን ስለሚለብሱት የልብስ ዐይነት መመሪያ ተሰጥቷቸዋል:: ወጥ ልብስ እንጂ ጉራማይሌ እንዳይለብሱም ተመክረዋል:: ወንድ የሴትን፣ ሴትም የወንድን ልብስ እንዳይለብሱ ተነግሯቸዋል (ዘዳ. 22፥5፤ 11)፤ እግዚአብ ሔር ከልብስ ጋር ጉዳይ አለውና::

ከዚህ የተነሣ ሴቶች ሱሪ እንዳይለብሱ የሚከለክሉ ወገኖች አሉ፤ ይህን ንም እንደ ትልቅ አጀንዳ ያራግቡታል:: ለመሆኑ ሊቀ ነቢያቱ ሙሴ ይህንን ሲናገር ወንዶች ሱሪ ነበር የሚለብሱት? (ከየት መጥቶ?!) ያኔ የወንዶች ልብስ ወጥ ቀሚስ ሲሆን፣ የሴቶቹ ደግሞ መከናነቢያ ያለው ቀሚስ ነበር:: ታዲያ አሁንስ ሴቶች የወንዶችን ሱሪ ነው የሚለብሱት? የሴትና የወንድ ሱሪ ልዩነት እንዳለው የምታውቁ እናንተው መልሱት:: በመሆኑም ሴቶች ሱሪ እንዳይለ ብሱ ለመከልከል መጽሐፍ ቅዱስ በምክንያትነት ሊቀርብ አይገባም፤ እንዲያ ውም ሱሪ መልበስ ለሴቶች አስፈላጊ የሚሆንበትም ወቅት ይኖራል፤ ከአንዳ ንድ አጓጉል ቀሚሶች በብዙ የተሻሉ ሱሪዎች መኖራቸውንም አንዘንጋ:: ስለ ዚህ የሱሪው "ጨዋነት" ነው ጥያቄው::

ይልቁኑ ምንባቡ ወንዱ የሴት ልብስ ለብሶና ራሱን እንደ ሴት አድርጎ ለሌላ ወንድ ማቅረቡና ሴቷም ራሷን እንደ ወንድ አድርጋና ለብሳ ከሌላ ሴት ጋር መገናኘቷ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ መሆኑን ነው የሚናገረው:: ሰዶማዊነትን የሚቃወም ምንባብ ነው::

ክርስቲያን ለአለባበሱ ሥነ ሥርዐት ሊኖረው ይገባል፤ ሰዎች መንፈሳዊ መሆን ሲጀምሩ ሥርዐት አልበኛ አይሆኑምና! የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሲነ በቡ ብዙ ሥርዐቶች ይገኛሉ:: የመቅደሱ ሥርዐት፣ የክህነቱ ሥርዐት፣ የአለባ በስ ሥርዐት ...:: መንፈሳዊነት ሥርዐት አለው::

አዲስ ኪዳንም ወንዶች ጠጉራቸውን እንዳያሳድጉ፣ ሴቶችም ጠጉራቸ ውን እንዲሸፍኑ ያስተምራል (1ቆሮ. 11፥4-6)፤ የጠጉር አያያዝ የእግዚአብሔ



ርም ጉዳይ ነውና:: ሆኖም ይህን ወስደን ሁሉም ሴቶች ጠጉራቸውን እንዲሸ ፍኑ እናስገድድም፤ ትእዛዙ ባል ያላቸውን ሴቶች ብቻ ይመለከታል:: እነርሱ ንም ቢሆን ሁሌ ሳይሆን፣ ሲጸልዩና ትንቢት ሲናገሩ ብቻ እንዲፈጽሙት ነው የሚጠይቀው:: ይህ ምንባብ ግን ሌላም ገጽታ አለው፤ "ራሱን ተከናንቦ የሚጸ ልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ማንኛውም ወንድ ... ራሷን ሳትሸፍን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ..." ነው የሚለው:: ይህም በአገልግሎት ጊዜ ሊደረግ የሚገባው የአለባበስ ጥንቃቄ መኖሩን ያሳየናል:: ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ከምን ተነሥቶ ይህን እንዳዘዘ መጠየቅና በእኛ ዐውድ በምን እንደሚተረጐም ማጠየቅ መልካም ነው::

ስለዚህ እዚህ ምንባብ ላይ ተመሥርተን ስለ ሕግ ባናወራም ስለ መርሕ ማውራት እንችላለን:: ለአገልግሎት የተለየ የአለባበስ ጥንቃቄ ያስፈል ጋል ማለት ነው:: በዚህም ለእግዚአብሔር መድረክና ለእግዚአብሔር ሕዝብ አክብሮትን መግለጥ ይቻላል:: ሰዎች ለአገልግሎት በእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት ሲቆሙ ሰርከ ከሚያደርጉት የአለባበስ ጥንቃቄ የተለየ ያስፈልጋቸዋል::

የእግዚአብሔር መድረክ ይቅርና ባንኮች እንኳ ለሠራተኞቻቸው የሚያ ስቀምጡት የአለባበስ ሥርዐት አለ፤ አንዳንድ የምሽት ክበቦች ዘንድ ለመግባ ትም አለባበስ ይታያል:: ፓርላማ ሲገባና ወደ አንዳንድ የስብሰባ ቢታዎች ሲኬ ድም ወንዶች ሙሉ ልብስ፣ ሴቶች ደግሞ ቀሚስ እንዲያደርጉ ሲያስገድዱ እናያ ለን:: በየኮሌጁም ሰዎች መመረቂያ ሥራዎቻቸውን ሲያቀርቡ ጂንስ ለብሰን እንቀርባለን ቢሉ ዋጋቸውን ያገኛሉ:: እነዚህን ሁሉ ስናይ በቤተ እግዚአብሔር መድረክ ላይ የአለባበስ ሥርዐት ቢጠበቅ አያስገርምም፤ ተገቢም ነው::

በእርግጥ ታዳሚው ወጣት በሆነበት ጉባኤ 'ወጣታዊ' ልብስ መልበስ ይቻላል፤ ያጠረ፣ የሳሳና የተጣበቀ ግን በእግዚአብሔር ቤት ቦታ የለውም! ይህ ግን በአንዳንድ ወጣት አገልጋዮች ዘንድ የተስተዋለ አይመስልም:: ጠጉራቸ ውን በፍሪዝ ገምደው፣ የቱፓክ ምስል ያለበትን ሸሚዝ፣ ላያቸው ላይ የተጣበቀ ቲ ሸርት፣ ተንዘላዝሎ ወይም ተንጀላጅሎ ሊወድቅ የደረሰ ሱሪ ... አድርገው ዐውደ ምሕረት ላይ ይቆማሉ (ኧረ ነውር ነው!):: ለአገልግሎት ሲባል የሚደረግ የአለባበስ ጥንቃቄ መኖር አለበት:: አሁን አሁን እየተለመደ የመጣ ውን በእንቅስቃሴ የታጀበ የመዝሙር ትዕይንት (choreography) የሚያሳዩ ወጣቶች በተለይ ይህን ልብ ሊሉ ይገባል:: ትዕይንቱ ኋላቸውን ለተመልካቹ ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱም ስለሚያደርጋቸው ለአለባበሳቸው ጥንቃቄ ያድርጉ::

ይህም ሁሉ ሆኖ ክርስትና ዐውዳዊ መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: እኛ ኢትዮጵያውያን እንጂ እስራኤላውያን አይደለንም:: ክርስትና የክርስቶስ ሕይ ወት ነው (ማንነቱ፣ ልደቱ፣ መስቀሉ፣ ትንሣኤው ...):: መሠረቱም መጽሐፍ

ቅዱስ ነው፡፡ በየትኛውም ቦታ በእነኚህ ወሳኝና መሠረታዊ ጉዳዮች እንስማማ ለን፤ ውጫዊው ሥርዐት ግን እንደ ባህላችን፣ እንደ ወጋችን ይለያያል፡፡

ስለዚህ፣ "ኢየሱስ ምን ይለብስ ነበር?" በማለት አስሰን የእርሱን ዐይነት ልብስ መልበስ አያስፈልገንም፡፡ የሐዋርያቱ ልብስ ምን ነበረ? ብለን ለመኮረ ጅም አንሟሟትም፡፡ ያኔም ሆነ አሁን በመካከለኛው ምሥራቅ (እስራኤል ያለ ችበት) አካባቢ የሚለበሱ አልባሳትን ለመልበስ አንገደድም፡፡ ውስጣዊ ሕይወ ታቸውን፣ ትሕትናቸውን፣ ቅድስናቸውን፣ ፍቅራቸውን እንኮርጃለን እንጂ የል ብሳቸው ቀለምና ቅርጽ ጉዳያችን አይደለም (ታዲያ ወንጌላውያን ክርስቲያ ኖች ዘንድ የምዕራቡ ዓለም ተጽዕኖ ለምን ጎላ?)፡፡

ልብስ ሥራንም ይገልጣል፤ እንደ ደንብ ልብስ፡፡ አይሁዳውያን ጋለሞ ታን የሚያውቁት በልብሷ ነው (ምሳሌ 7፥10፤ ዘፍ. 38፥15)፡፡ ይህም ዐውዳዊ ነው፡፡ በአንዳንዱ ባህል ጋለሞታ ትከናነባለች፤ ስለዚህ በዚያ ያለች ክርስቲያን እንድትከናነብ አይመከርም፡፡ ጋለሞቶች ተገላልጠው የሚኖሩበት ቦታ ያሉ እኅ ቶችም ከእነርሱ ለየት ማለት አለባቸው፡፡ በኢትዮጵያ የቆዳ ስፋትና የባህል ልዩ ነት የየቦታውን ዝሙት አዳሪዎች አለባበስ እዚህ ማቅረብ አይቻልም፡፡ የአዲስ አበባንና የከተሞችን ግን መናገር እችላለሁ፡፡ የተጣበቀ፣ አጭር፣ ስስ ልብስ ያዘ ወትራሉ፡፡ መቀመጫቸውን፣ ጡታቸውንና ጭናቸውን ማጋለጥ ይወዳሉ፡፡ የጠጕርና የከንፈር ቀለማቸው ከነሽቶአቸው ከሩቅ ይጣራል፡፡ በእዚህ አካባቢ የሚኖሩ እኅቶች እንዲህ መምሰል አይኖርባቸውም፡፡

ታዲያ እንዴት ይለበስ? ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይነግረናል፡፡ "ሴቶች በሚገባ ልብስ ከዕፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸ ልሙ" (1ጢሞ. 1፥9-10)፡፡ መንገዱ ይኸው ነው፤ ዕፍረትና ራስን መግዛት፣ እግ ዚአብሔር ለልብስ እንደሚገደው ማወቅ፡፡ ዕፍረት ጸጋ ነው! አንዳንዶች የተን ጠለጠለና የተሸበሸበ ልብሳቸውን ሠላሳ ጊዜ ሲጎትቱና ሲሳቀቁ ስናይ፣ መጀመ ሪያውኑ ልብሱን ሲለብሱ ዕፍረታቸው የት እንደ ነበር እንጠይቃለን (የታናሽ እኅታቸውን ሱሪ ለምን ይለብሳሉ?)፡፡ ብርዱን ባይፈሩ፣ ሰዉን አያፍሩም? የጠፋውም ይኸው ነው፤ ዕፍረት! ዕፍረት! ዕፍረት!

* * *

*"O, shame where is thy blush?"*
*(ዕፍረት ሆይ ቅላትሽ ወዴት አለ?)*

*ሼክስፒር*



# "የተገኘውን" እንሰብካለን!

አንዲት ቤተ ክርስቲያን አጥር (ግድግዳ) ላይ የተሰቀለ ከቆርቆሮ የተሠራ ታፔላ አለ፤ "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" ይላል፡፡ ታፔ ላው የተሰቀለበት አቅጣጫ የተንጋደደ በመሆኑ የፀሓይ ብርሃን እኩል አያገኘ ውም፡፡ ስለዚህ፣ "እኛ ግን" የሚለውን ቃል ብዙ የፀሓይ ጨረር ስለ በዛበት ከጊዜ ብዛት እየደበዘዘ ሄደ፡፡ ጥቅሱ፣ "የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" ማለት ጀመረ ማለት ነው፡፡ ከዚያ ደግሞ "የተሰቀለውን" የሚለው ቃል ቀለሙ እየጠፋ፣ "ክርስቶስን እንሰብካለን" ቀረ፡፡ ከረጅም ጊዜ በኋላ ደግሞ "ክርስ ቶስን" የሚለው ቃል ቀለም ደበዘዘና ጭራሹኑ ጠፍቶ ዐረፈው፡፡ ከዚያች ቤተ ክርስቲያን አጥር ላይ "እንሰብካለን" የሚለው ነጠላ ቃል ብቻ ቀረ፡፡

የዘመናችንን ቤተ ክርስቲያን ይህ የሚገልጣት ይመስለኛል፡፡ እንሰብካ ለን፤ እስኪደክመን እንሰብካለን፤ "ታላቅ ኮንፈረንስ"፣ "ትንቢታዊ ኮንፈረንስ" ... እያልን በዘማሪ፣ በፓስተርና በ"ነቢይ" ፎቶ ያሸበረቀ ፖስተር ለጣጥፈን ሕዝብ እንጠራና እንሰብካለን፡፡ "ምንድን ነው የምንሰብከው?" ብሎ የሚመረምር ልባም ቢገኝ፣ "የተገኘውን" ነገር ስንሰብክ ያገኛል፡፡ ቀስ በቀስ መጽሐፍ ቅዱ ሳዊ ትምህርት በፊታችን ሞገስ እያጣ ነው፡፡

ብዙ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ፈልሰው የመጡባት ቀዳሚዋ ቤተ ክር ስቲያን በዚህ ችግር ትታወቃለች፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ገድል፣ ታምር እየ ተባለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ በርካታ ትምህርቶችና ስብከቶች ነግሠውባ ታል፡፡ አንዳንዶቹ ልቦለድ ለመሆን እንኳ ተአማኒነት ይጐድላቸዋል፡፡

ብዙ ወገኖች "በተረት" የተሸፈነው ወንጌል እስኪገለጥላቸው እዚያ ተጨናብሰው ቈይተዋል፡፡ ወንጌሉ ሲገለጥላቸው ደግሞ ሁሉን ጣጥለው እዚህ መጡ፡፡ የሚያሳዝነው ግን አሁን እዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እየተሸረ ሸረ መሆኑ ነው፡፡ የነጠረው እውነት፣ የእግዚአብሔር ቃል እየቀረ "የተገኘው ሁሉ" እየተሰበከ ተቸግረናል፡፡ ሰው ሁሌ ጊዜያዊ ፋይዳ ያላቸውን ስብከቶች እየተመገበ እስከ መቼ ይኖራል? የነካን ምን ይሆን?

ኀጢአተኞች ወደ ጌታ ይመጡ የነበረው እርሱ የተለየ መሆኑን ስላወቁ ነው፡፡ ትምህርቶቹና የሚያስተምርባቸው መንገዶች በወቅቱ ከነበሩ የሃይማኖት መሪዎች የተለዩ ናቸው፡፡ ታዲያ አሁንስ ማዝናናትንና ሰዎችን ደስ ማሰኘትን

ብቻ ግቡ ያደረገው መልእክታችን ከሌላው በምን የተለየ ሆኖ ነው ሰዎች ወደ እኛ የሚመጡት? ሚዛኑን የጠበቀ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ለምን ተጠላ?

ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ያለን ፍላጎት በመጽሐፍ ቅዱስ አያያዛችንም ይገለጻል:: ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሜዳሊያ ወደ ሕዝቡ የሚወረውር ሰባኪ ብታዩ ምን ትላላችሁ? ለመነሻ አንድ ጥቅስ ብቻ አንብቦ ሌላ ሌላውን ሲዘባርቅ የሚውለውንስ? የራሱን ገድል መተርተር የተጠናወተውንስ ምን ትሉታላችሁ? ዕድሜ ልኩን የብሉይ ኪዳን ትምህርት ሲሰብክ የሚኖረውንስ ምን እንበለው? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ዋና ነገር ይህ ነው፤ ሚዛኑን የጠበቀ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት! ትምህርት! ትምህርት!

የምናመልከው የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔርን ያወቅነውና የተከተልነውም መጽሐፍ ቅዱስ ነግሮን ነው:: ታዲያ መጽሐፍ ቅዱሱን ከተውነው የትኛውን እግዚአብሔር ልንከተል ነው? መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከጣልንና ፊት ከነሣነው መንገዳችን ወዴት መሆኑ ነው?

ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሚዛኑን ጠብቀው ካልተማሩ የሚጨብጡት ነገር አይኖርም:: ለሁሉ ያጨበጭባሉ:: ያመኑትን አያውቁምና በተለያዩ የስሕተት ትምህርቶች ይወሰዳሉ:: ቀላል የሕይወት ፈተና ሲገጥማቸው እንኳ ሳያጠና ለፈተና እንደ ቀረበ ተማሪ ድንጉጥ ናቸው፤ እምነትም፣ ዕውቀትም የላቸውም::

አስገራሚው ነገር ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር አንዴ እንኳ ያላነበቡ በጌታ ቤት ግን ብዙ ዓመታትን ያስቈጠሩ ሰዎች መኖራቸው ነው:: ከእነዚህ ወገኖች መኻል አገልጋዮችም አሉበት::

ለዚህ የየአብያተ ክርስቲያናቱ አስተዋጽኦ አለበት:: የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ማተኮር በራሱ ልክ አይደለም:: ከሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ውስን ምንባቦችን ብቻ መርጦ ማዘውተር ጤናማውን ወንጌል እንዳለማመን ነው የሚቈጠረው፤ ሚዛንን ያሳጣል:: ሆኖም አንዳንዶቹ ዘንድ ሁሌም የሚሰበከው ብሉይ ኪዳን ብቻ ሲሆን፣ ሌሎቹ ዘንድ ደግሞ አዲስ ኪዳን ብቻ ነው:: ሲሻቸውም ያንኑ አዲስ ኪዳን ይሸራርፉታል:: መጀመሪያ፣ "ለቤተ ክርስቲያን የተጻፉት መልእክቶች ብቻ ናቸው" በሚል ከፊት ወንጌላቱን "ፎሪ" ያወጧቸዋል:: ከዚያ ደግሞ፣ "ግልጽ አይደለም፤ አይገባም" በሚል ከኋላ ከራእየ ዮሐንስ ፊታቸውን ይመልሳሉ:: ከዚህም የተነሣ ራእየ ዮሐንስን ማንበብ የሚፈሩ ምዕመናን ብዙ ናቸው ("'ሆረር' ፊልም ማየት የማይፈሩ፣ የዮሐንስን ራእይ የሚፈሩ" እንበላቸው?)::



አንዳንዴማ ከአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ስንነጋገር የክርስትና መሠረታዊ አስተምህሮ የሆኑትን ነገረ ክርስቶስንና ነገረ ሥላሴን በሚመለከት "ጨዋ" ሆነው ይገኛሉ:: ስለ ጉባኤ ኒቅያ ሲነሣ፣ "ኒቅያ ምንድን ነው?" የሚላችሁን የቤተ ክርስቲያን መሪ ምን ትሉታላችሁ? "ከመጠምጠም መማር ይቅደም" አይደል የሚባለው? (ለእኛ ሰዎች እንዲመች፣ "ከመ'ቀባት መማር ይቅደም" እናድርገው ይሆን ?)

አማኙ የክርስትናን መሠረታዊ አስተምህሮ ካላወቀ፣ በክርስቶስ "ፍጹም ሰው - ፍጹም አምላክ"ነት ላይ የጋራ መረዳት ከሌለው፣ እንዴት ነው አንድ የሚኮነው?

የአንዳንዶች ሥነ አፈታት ደግሞ እጅግ ያስደነግጣል:: ሁሉን ነገር ከስኬትና ከብልጽግና ጋር ካላገናኙ አይሆንላቸውም:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስኬትና ስለ ብልጽግና የሚያወራባቸው ቦታዎች ቢኖሩም፣ የመጽሐፉ ግብ ግን ይህ አይደለም:: "መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ውጪአዊ ስኬት በጭራሽ ዋነኛ ግብ ሆኖ አያውቅም:: ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዴት 'ስኬታማ' እንደሚሆን አይደለም ሲመክረው የነበረው፤ መለኮታዊውን ልኬት እንዴት እንደሚከተል እንጂ::" ከዚህ ውጭ ላለማውራት የማሉ የሚመስሉ ሰዎች ግን መድረኮቻችን ላይ አሉ:: ስለ "ይሆንላችኋል" እና ስለ ብልጽግና ማውራት ብቻ ነው የሚፈልጉት፤ "ትሻገራላችሁ"ን ብቻ ነው የሚያውቁት:: መጽሐፉን እንደ ስልክ ማውጫ የሚፈልጉትን ቅንጣት ለማግኘት ብቻ ነው የሚያገላብጡት:: ከዚህ ይልቅ የእግዚአሔርን ሁለ-ገብ ምክር ለማግኘት እርሱ በርሱ እያያዙ ማስተንተኑ ነው የሚጠቅመው::[2] ሙሉው ምክረ መለኮት ነው የሚያሻን:: ለዚህም ቢሆን ስለ ሥነ አፈታት የሚያስተምሩ መጻሕፍትን ቢያነቡ ምናለበት? ዳራውን ተረድተው፣ ዐውዱን ጠብቀው ቢሰብኩ ማን ይሞታል?

"ያውቃሉ" ከተባሉቱ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው በላይ ማብራሪያዎችን (commentaries)፣ ያነበቡአቸውን የተለያዩ መጻሕፍት፣ እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስተማሪያቸውን የሚያምኑ አሉ:: እነዚህ መጻሕፍት የመጽሐፉ ኢጋዦች እንጂ የመጽሐፉ ምትኮች አይደሉም:: የመጨረሻው ሥልጣን የቅዱሱ መጽሐፍ መሆኑ መታወቅ አለበት:: የነገረ መለኮት ትምህርታችን መጽሐፍ ቅዱስን እንድናከብርና መጽሐፍ ቅዱስን እንድናስተምር ካላደረገን ምን ይፈይድልናል?

በእርግጥ መደበኛ የትምህርት መርሐ ግብር ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ዐልፎ ዐልፎ ይኖራሉ:: በተለያዩ ርዕሰ ጒዳዮች ላይ ትምህርት መስጠት እየጀመሩ ያሉ አጥቢያዎችንም ዐውቃለሁ:: ይህ ተስፋ የሚያሳድር ነገር ነው:: እንዲያውም ትምህርቱ በሲዲና በካሴት እየተዘጋጀም ይሸጣል:: ስለዚህ በረ

ከቱ በቦታው ላልተገኙ ሰዎች እንኳ ይተርፋል:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ኅላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ነውና ይመሰገናሉ::

የአዲስ ኪዳን መልእክት ጸሓፊዎች (ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ...) የተሳሳቱ ትምህርቶችን በመቃወም ጽፈዋል:: የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን ምንም ዐይነት የተሳሳቱ አስተምህሮዎች ቢነሡ ለመቃወምና በጤናማ ትምህርት ለማረቆት ግድ ያላቸው አይመስሉም፤ ትኩረታቸው በተለያየ ነገር ተወስዷል::

በተለይ አሁን አሁን በቴሌቭዥን የሚሠራጩ ስብከቶችን ሳይ መንታ ሓሳብ ውስጥ እገባለሁ:: በአንድ በኩል፣ ይህ ዕድል መገኘቱና የክርስቶስ ወንጌል በተለያየ መንገድ ወደየ ቤቱ መግባቱ ያስደስተኛል:: በሌላ በኩል ግን፣ የስብከቶቹና የልምምዶቹ መዘበራረቅ ያስደነግጠኛል:: ጨፍጋጋ ስሜት ውስጥ እገባለሁ:: ከቅዱስ ቃሉ የተኳረፉና ዝንፈት የበዛባቸው፣ የተቀየጡና ያልጠለሉ፣ የተበረዙና የተምታቱ መልእክቶች እየተረጩ ያሉት በዚሁ የቴሌቭዥን መስኮት ነውና::

ከዚህም ባሻገር የኮንፈረንሶቹ እና የሰንበቱ ስብከት አካሄድ አሳሳቢ ይመስለኛል:: ሰባኪያኑ በአሜን ለሚደግፋቸው ሕዝብ ብቻ የመስበክ ጉልበት ነው ያላቸው፤ በሓሳብ ከእነርሱ የተለየ አቋም ባለው ወይም አሜን አሜን እያለ በማያሟሙቃቸው ጉባዔ ለመናገር ዐቅመ ቢስና ድንጉጥ ናቸው:: ይህም የስብታቸው ዋና ግብ ሰዉን ማስደሰት እንዲሆን አድርጎታል:: ስለዚህም ብዙውን ጊዜ የሚሰበከው ጌታ ኢየሱስና የእግዚአብሔር መንግሥት አይደለም:: ሚዛኑን የጠበቀ ስብከትንም የሚፈልግ የለም፤ የሚያቆላምጥ እንጂ:: በእኔ ግምት አንዳንዶች ይህንን የሚያደርጉት ራሳቸውም ያልተማሩ በመሆኑ ነው:: ስለዚህ ስብከታቸው ሚዛኑን ያልጠበቀ ሀብትና ብልጽግና ብቻ ነው:: ሌላም ምክንያት ይኖር ይሆናል:: የሕዝቡ ፍላጎት እንዲህ እየሆነ በመምጣቱ ብዙዎችን በማስደሰት አድናቂና ወዳጅ ማብዛት አንዱ ሰበብ ሊሆን ይችላል::

አዎን፤ ብዙዎች ቤተ ክርስቲያን መጥተው መዝናናትን መፈለግ ጀምረዋል:: ጥሩ ስሜት ተፈጥሮባቸው መሄድ ነው የሚሹት:: የሚፈልጉትንም ለማግኘት ጥያቄ ያቀርባሉ:: ገበያ መሩ አገልግሎትም የሚፈልጉትን ለመስጠት ዝግጁ ነው፤ የገበያው ፍላጎት አቅርቦትን ይፈጥራልና:: ነገር ግን እያንዳንዱ ቅቡል አገልግሎት በአዎንታዊውና በአሉታዊው መካከል ሚዛን ሊኖረው ይገባል:: መገሠጽ የማይችል አገልጋይ ተልእኮውን እየተወጣ አይደለም::[3]

የአድማጮችን ጎሽታ ለማትረፍና ለማስደነቅ ሲሉ ብቻ ጆሮ የሚኮረኩሩ ሰባኪያን ገበያው ላይ ሞልተዋል:: ግና ጆን ማካርተር እንደሚናገሩት



ከሆነ፣ የእግዚአብሔር እውነት ጆሮን የሚኮረኩር ሳይሆን በቡጢ የሚጠልዝ ነው፤ ጆሮን የሚያነድ ነው:: መጀመሪያ ይገሥጻል፣ ይወቅሳል ከዚያ ያበረታታል:: ሚዛኑ መጠበቅ አለበት::[4] ማጽናናት፣ ማበረታታትና ማባበል ብቻ ሳይሆን፣ ንጉሤ ቡልቻ እንደሚናገሩት፣ "የቁጣ ቴዎሎጂ ሳያስፈልገን አይቀርም::"[5]

በቅርቡ አንድ የአደባባይ ሰባኪ ምስባኩ ላይ ቆሞ ስለ ራሱ አብዝቶ ያወራል:: አንዱ ድንገት ተነሥቶ፣ "እባክህ ክርስቶስን ስበክ" ብሎት ጉባዔውን ትቶ ወጣ:: ተናጋሪው ደንገጥ ብሎ ቈየና ራሱን ማዜሙን ቀጠለ:: ተጠናውቶታል ማለት ነው! ሌላኛው ወንድም ደግሞ አንዲት ቤተ ክርስቲያን በተከታታይ መካፈል ጀመረና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጥሎ ወጣ:: "ምነው?" ስለው "ኢየሱስ ናፈቀኝ" በማለት መለሰልኛል::

አካሄዳችን ሚዛን የጠበቀ ባለመሆኑ ጌታን ተቀብለዋል የተባለላቸው መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቁ ምዕመናንን እያመረትን ነው:: ክርስትናቸው ልማዳዊ እንጂ የሕይወት ለውጥ የሚታይበት አይደለም:: ጌታን ለመከተል የወሰንኩበት ጊዜ ትዝ ይለኛል:: በተለመደው አባባል "ጌታን ከመቀበሌ" (እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሠራውን ሥራ ከመቀበሌ) በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ነው የተቀበልኩት:: መዳን፣ የሕይወት ለውጥም ሆነ የእምነት ጽናት መጽሐፍ ቅዱስ ዘንድ ነው የሚገኙት፤ እርሱን ችላ ካልን በነበርንበት እንቀራለን እንጂ ዕድገት አይኖረንም:: የምንገልጠው መጽሐፍ ሁሌም ስለ ጌታ መናገር አለበት (ዮሐ. 5፥39):: ይህ ካልሆነ መንገዳችን ትክክል አይደለምና ቆም ብለን ማሰብ መጀመር ያስፈልገናል::

አንዳንድ ፓስተሮች ለራሳቸው ብለው መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት ከመማር ይጀምሩ፤ በጎ ለውጥ ለማምጣት ከፈለጉ:: እርስ በርስ "ፓስተር"፣ "ነቢይ"፣ "ሐዋርያ" ከመባባሉ ጋር እነዚህን ኀላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት የሚረዳ ትምህርት ይኑር:: ሕዝቡን የመመገብ ዐቅም የሌላቸው ፓስተሮችን እያበዛን መጓዝ ከቀጠልን የቤተ ክርስቲያን መጨረሻ አያምርም:: እንዲህ ዐይነት ፓስተሮች ሲያጋጥሙት፣ "እነዚህን መግረፍ ነበር!" የሚል ወዳጅ አለኝ (የልቤን ማን ነገረው?)::

እንዲህ ዐይነቶቹ ሰዎች መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት እንኳ በቅጡ ሳያውቁ ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናትን ለመገንባት ከፍተኛ ጥማት ያላቸው መሆኑ ነው የሚገርመው:: ለዚህ ደግሞ ሕዝቡን ወደ እነርሱ የሚስብ ዘዴ ያስፈልጋቸዋል:: ስለዚህም አሁን አሁን እንደምናየው፣ "የዘመነኛ አገልጋዮች ሞዴላቸው ነቢይ ወይም እረኛ ሳይሆን፣ ፖለቲከኛ፣ የማስታወቂያ ወይም የመዝናኛ ዝግጅት ባለሞያ ነው::"[6]

መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዓለምን ስለ መገለባበጣቸው ያወራል (የሐዋ. 17፥6)። በእኛ ትውልድ ግን ዓለም ቤተ ክርስቲያንን እየገለባበጠች ነው።[7] ሰዎች ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ይገንባላቸው እንጂ፣ ብዙ ሕዝብ ይሰብስብላቸው እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ስብከት፣ ሚዛናዊውን እውነት መሠዊያ ላይ አቅርበውም ቢሆን ያደርጉታል። ሌት ተቀን የሚታትሩት መንግሥተ እኔን ለመመሥረት ነውና!

ጆን ማክአርተር፣ በትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ሐቲታዊ (feature) ጽሑፍ የሚያዘጋጅ ጋዜጠኛ ሊያናግራቸው ወደ ግሬስ ቻፕል እንደ መጣ ይናገራሉ። "ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናትን የመሥራት ፍላጎት ሁሌም ነበረህ?" ነበር መጀመሪያ ያቀረበላቸው ጥያቄ። ያልተጠበቀ ጥያቄ ቢሆንም፣ ወዲያውኑ መልስ ሰጡት፤ "አንድም ቤተ ክርስቲያን የመሥራት ፍላጎት የለኝም፤ አንድም!"። ጋዜጠኛው ግራ በመጋባት እየተመለከታቸው፣ "አልገባኝም" ብሎ ተናገረ። "ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚሠራ ተናግሯልና ከእርሱ ጋር መፎካከር አልፈልግም" ነበር መልሳቸው።[8]

ሁሌም ግን ተስፋ የማደርገው ነገር አለ። አበቃ በተባለ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ተሐድሶን ያስነሣል፤ ራሱን ያለ ምስክር አይተውምና። ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱስን ከማስተማር ይጀምራል። ያኔ ትምህርቶቻችንና ልምምዶቻችን ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እየተፈተሹ ነው ተቀባይነት የሚያገኙት። ማርቲን ሉተር ሲነሣ ካሰማቸው ጩኸቶች አንዱ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ!" (Sola Scriptura) የሚል ነበር። የእኛስ ቀን መች ይሆን?

ማስታወሻ

1. John F. MacArthur, Jr. *Ashamed of the Gospel: When the Church Becomes Like the World* (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 1993), 29.
2. ንጉሤ ቡልቻ፤ *መስተአየት፣ ራስ ታዘብና ተሐድሶአውያን መጣጥፎች* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 82።
3. MacArthur, *Ashamed,* 34-35.
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 37።
5. ንጉሤ ቡልቻ፤ *መስተአየት፣* ገጽ 106።
6. MacArthur, *Ashamed,* 80.
7. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 51።
8. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 173።



# ሰው መሆኔን ማን ይንገረኝ!?

ሮም፣ ልዕለ ኃያል በነበረችበት ጊዜ፣ ሮማውያን አንድን ጦርነት ሲያሸንፉ የሚያደርጉት ሥርዐት ነበራቸው። ድል አድራጊው ሠራዊት ወደ ከተማዪቱ የሚገባበት ቀን ይወሰናል። በዚያን ቀን አሸናፊው ጄኔራል ጠላቶቹን ሙሉ በሙሉ ድል ማድረጉን በከተማ ላለው ሕዝብ ማስረጃ ይሆን ዘንድ የምርኮኛ ወታደሮችን ትጥቅ አስፈትቶ በአደባባይ እየነዳ ያሳያል (ሐዋርያው ጳውሎስ ቈላስይስ 2፥15ን የጻፈው በዚህ ላይ ተመሥርቶ እንደ ሆነ ይታመናል[1])።

ሕዝቡ ድል አድራጊውን ሠራዊት ለመቀበል ወደ አደባባዩ ይጐርፋል፤ ልክ እኛ አትሌቶቻችን የኦሎምፒክ ወርቅ ይዘው ሲመጡ እንደምናደርገው። የጦሩ አዛዥ በእልልታና በጭብጨባ ሊቀበለው በወጣው ሕዝብ ፊት ሠራዊቱንና የማረካቸውን ምርኮኞች እየመራ ሲገባ አየሩ በየመንገዱ ዳር በሚጤሰው መልካም ሽታ (መዐዛ) ይታወዳል (ይሄም ለሐዋርያው ጳውሎስ 2ቆሮ. 2፥14 መልእክት መንደርደሪያ መሆኑ ይታወቃል[2])።

በዚህን ጊዜ ድል አድራጊው ጄኔራል በሠራዊቱ ታጅቦ፣ በወርቅ ሰረገላ ተቀምጦ ነው የሚጓዘው። በሰረገላው ላይ የወርቅ አክሊል ከፍ አድርጎ ይዞ ከኋላ የሚቆም አንድ ባሪያ ግን ሁሌም ይኖራል። ይህ ባሪያ የራሱ አስደናቂ ተግባር አለው። ዛሬ ድል አድራጊው የጦር መሪ በከፍታ ላይ ቢሆንም፣ ነገ ግን ሌላ ቀን እንደ ሆነ እንዳይረሳ በተደጋጋሚ ያስገነዝበዋል። በድል ነሺነት ልቡ ተሞልቶ በየመንገዱ በሚደረግለት ሆታና እልልታ በስሜት ተውጦ፣ በሰሙ በሚደረገው ጭፈራ መንፈሱ ተነቃቅቶ ሲጓዝ ይህ ባሪያ በየተወሰነ ጊዜ ወደ ጆሮው እየተጠጋ፣ "አንተም ሟች (ሰው) መሆንህን አትርሳ!" (Memento mori) በማለት ያስታውሰዋል።[3]

ሮማውያኑ ይህንንም እያደረጉ እንኳን መሪዎቻቸው ሁሌም መመለከን የሚፈልጉ ነበሩ። የሚማር ልብ ያለው ሰው ከዚህ ብዙ መማር ይችላል። የሰው ልጅ በሥልጣንና በስኬት መሰላል ከፍ ከፍ ማለት ሲጀምር ትናንትን የመርሳት፣ በዛሬ የመኩራራትና ሌሎችን የመናቅ ዝንባሌ አለው።

እግዚአብሔር ታላቅነቱን የሚገልጸው ሌሎችን ባለመናቅ ሲሆን (ኢዮብ 36፥5)፣ ሰው ግን እንዲህ አይደለም። በየአገሩ (በተለይ በአፍሪካችን) የተንሰራፉትን መሪዎች ስናይ፣ ሟች መሆናቸውን የሚያስታውሳቸው ሰው

እንዲኖራቸው ያስመኛል:: በምድር ላይ የነበሩ አምባገነኖች ሁሉ አወዳደቃቸው አያምርም፣ መስሎቻቸው ግን ዘሬም መፈጠር አላቆሙም:: ሰው መች ይሆን ከታሪክ የሚማረው?

በእግዚአብሔር ቤት በስኬትና በዝነኛነት እየተራመዱ ያሉ ሰዎችም እንደ ሌላው ሰው ሁሉ በትዕቢት ሊዋጡ ይችላሉ:: የዚህ ጽሑፍ የትኩረት አቅጣጫም የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል::

ፊሊፕ ያንሲ እንዲህ ይላሉ፤

> የትኛውንም የእግዚአብሔር ተከታይ የሚያጋጥመው ትልቁ አደጋ ስኬት ነው ...:: ሙሴ ይህን ጠንቅቆ ያውቃል:: በሕይወቱ የተከሰቱ ትልልቅ ውድቀቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ከመደገፍ ይልቅ ለራሱ ክብርና ዝና በመንቀሳቀስ ትኩረቱን ወደ ራሱ ለማድረግ በመሞከር ሂደት ውስጥ የተፈጠሩ ናቸው:: ግብፃዊውን ሲገድል፣ በምድረ በዳ ዐለቱን በበትር ሲመታ የተከሰተው ይኸው ነው::[4]

እኛ ካልተጠነቀቅን፣ እግዚአብሔርም ካልረዳን ይህ አደጋ ሁላችንም ላይ ሊከሰት ይችላል:: ከአገልግሎት በኋላ፣ "የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፤ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል" እንድንል ጌታችን የመከረን ከዚህ የተነሣ ነው (ሉቃስ 17፥10)::

ሐዋርያው ጳውሎስም፣ "በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፣ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፣ ይኸውም እንዳልታበይ ነው" ማለቱ የነገሩን አሳሳቢነት ይገልጸል (2ቆሮ. 12፥7):: ቅዱስ ጳውሎስ ታላቅ ነገር ቢገለጥለትም፣ ሰው መሆኑን ይህ መውጊያ ያስታውሰው ነበርና አልታበየም::

በአገልግሎት ስኬትንና ዝናን ማግኘት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመሠረተ ነው፤ ግና በሌሎች መንፈሳዊ ባልሆኑ ዘርፎች እንደሚታየው ሁሉ፣ "ሰው ጤፉ" የሆኑ ጸገኞች ቊጥር እያደር እየጨመረ ይመስላል:: ሆኖም ራሳቸውን ብቻ እንጂ የሰውን ምክር የማይሰሙ አገልጋዮቻችን፣ "ሰው መሆንህን አትርሳ" ከሚላቸው "ባሪያ" ይልቅ የሚያንበድድላቸውን ነው የሚመርጡት::

የዚህ ዐይነቱ ተዐብዮ የሚፈጠርባቸውን አንዳንዶቹን ምክንያቶች ለማየት መሞከር እንደምንችል እስባለሁ፤



## ሀ. ራስን አለማወቅ

ይህ ሁሉ ውጥንቅጥ የበዛው አንድም ሰዎቻችን ራሳቸውን (ልባቸውን) ባለማወቃቸው ነው:: ድካማቸውንና የልባቸውን ክፋት አያውቁትም:: ይህ የመጀመሪያ ትምህርት ቢሆንም፣ ሲያውቁት አይሹም:: ምናልባት አድናቂዎቻቸው ጥሩነታቸውን ሲነግሩአቸውና እነርሱም ይህንኑ ብቻ ደጋግመው ሲሰሙ ስለኖሩ እውነት መስሏቸዋል:: አንድ ጊዜ አንዱ፣ "ጌታ ሆይ ልቤን አሳየኝ" በማለት መጸለይ ጀመረ:: ልቡ እጅግ ንጹሕ ከመሆኑ የተነሣ፣ እግዚአብሔር ደረቱ ላይ ትንሽ መስኮት አበጅቶለት ልቡን ለሰው ሁሉ በዐውደ ርእይ ማቅረብ ነበር ፍላጎቱ:: ጌታም አንድ ቀን አይጥ የቦጓደሰው ዳቦ በራእይ አሳየው:: አሁንም ስላልገባው፣ "ጌታ ሆይ ይህ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀ:: "ልብህ!" ነበር መልሱ::

ራስን ላለማወቅ አንደኛው ምክንያት ትናንትን መርሳት ነው:: አንድ የቻይና ፈላስፋ ከፊቱ ባለውና በሚጓዝበት መንገድ ሐሳቡ እንዳይወሰድ፣ ይልቁንም የመጣበትን መንገድና የነበረበትን ቦታ ማሰላሰል እንዲችል በበቅሎ ሲጓዝ ፊቱን ወደ ኋላ አዞሮ ለመጓዝ ሐሳብ አቅርቧል::[5]

አዛውንቱ ፕሮፌሰር በአንዱ መጽሐፋቸው ስለ ጉዳዩ ይናገራሉ፤

> ትናንትን አልረሳም፤ ከአደግሁበት ደሀነት ብወጣም ደሀነትን አልረሳም፤ ለምሳሌ ቤት ስከራይ እኔ ያደግሁበት ዐይነት ትንሽ ቤት አጠገቡ መኖር አለበት፤ ወደ አሁኑ "የጌትነት" ቤቴ ስገባ ያደግሁበትን ማስታወስና ትዕቢትን ማስተንፈስ አስፈላጊ ሆኖ ይታየኛል፤ ችላ ካሉት እንደ ደሀነት ቶሎ የሚረሳ ነገር የለም፤ [6]

ዛሬ ዛሬ የተነሡበትን የረሱ አገልጋዮች በየመድረኩ ቈዳቸውን ሲያዋድዱ እናያለን:: እነዚህ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ቤትና ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ግድ የላቸውም፤ ትኩረታቸው ለራሳቸው ነው:: ግድ ሊኖራቸው ከቻለም እነርሱን የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው:: ስለ ራሳቸው ሲያወሩ ይውላሉ:: ትናንት የምናውቃቸው ሰዎች ዛሬ መድረክ ላይ ከወጡ በኋላ ስለ ትናንታቸው ሲያወሩ ግን ስለ ማን እንደሚያወሩ ግራ እየገባን ነው፤ የሚነግሩን ልቦለድ ነውና!

ስለ ፍቅር፣ ስለ መስጠት፣ ስለ ጸሎት ካነሡ በተደጋጋሚ ስለ ራሳቸው ታላቅነት ይነግሩናል:: ምናለ ደካማነታቸውንም አብረው ቢነግሩን?

ሐዋርያው ጳውሎስ ልኩን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር:: ለመንፈሳዊ ልጁ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ፣ "ከኀጢአተኞች ዋና እኔ ነኝ" ይለዋል (1ጢሞ.

1፥15)፡፡ እንደ ጭንጋፍ የሚቈጠር መሆኑን ይናገራል (1ቆሮ. 15፥8)፡፡ ስለ ታማኝነቱ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ታማኝ አድርጐ እንደ ቈጠረው ይመሰክራል (1ጢሞ. 1፥12)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የትልልቅ የእግዚአብሔር ሰዎችን ውድቀት ሳይደብቅ ይነግረናል፡፡ የዛሬዎቹ አገልጋዮቻችን ግን "ፍጹምነታቸውን" እና እንከን የለሽነታቸውን ይሰብኩናል፡፡

ከእንግሊዝ ኀያላን መሪዎች መካከል ኦሊቨር ክሮምዌል አንዱ ነበር፡፡ ይህ ብርቱ ሰው በሥልጣን ላይ ሳለ የተሠራለትን ምስል ሲመለከት እጅግ ተቈጣ፡፡ የፊቱ ምስል በዘመናዊ ፎቶግራፍ እንደሚታየው ፍጹም ንጹሕና የተወለወለ ሆኗል፡፡ "ብጕሮቼ፣ ጠባሳዎቼና የግንባሬ መስመሮች የታሉ?" (Where are the warts?) ብሎ ጠየቀ፡፡ ሠዓሊው እንዳስወገዳቸው ነገሩት፡፡ ክሮምዌልም ሥዕሉ እንደገና እንዲሣልና ከነጕድለቶቹ (warts and all) ለታሪክ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጠ፡፡[7]

መጽሐፍ ቅዱስ ጀግኖቹን እንዲህ ነው የሚያቀርባቸው፡፡ ውድቀታቸውን አይደብቅም፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስናጠና ሕይወታቸው ስለ ተለወጠ፣ ነገር ግን በከፉ ነገር ውስጥ ወድቀው ስለ ነበሩ ሰዎች ይናገራል፤ በዘመናዊ ግለ-ታሪኮች (biographies) እንደምናየው አይደለም፡፡

በየመጽሔቱ ቃለ መጠይቅ የሚደረግላቸው ዘማሪዎች፣ መጋቢዎችና ሌሎች አገልጋዮች ራሳቸውን ውድቀትና ድካም አልባ አድርገው መሣላቸው እንደ እኛ አይደሉም በማለት እንድናስብ እየገፋፉን ነው፡፡ ጠያቂዎቻቸውም ሚዛናዊ ለመሆን ሲሉ እንኳ ድካማቸውን በጥቂቱም ሊዳስሱት አይፈልጉም፡፡

ስለ ጸሎት ሲያነሡ፣ ምን ያህል እንደሚጸልዩ፣ ስለ ፈውስ ሲነሣ፣ ምን ዐይነት ታላቅ ፈዋሽ እንደ ሆኑ ወሬያቸውና ዝማሬያቸው ሁሉ "እኔ፣ እኔ፣ እኔ ..." ነው፡፡ መጽሔቱ የተሞላው በእኔነት ገድል ነው፡፡ የዘማሪዎች የመዝሙር አልበም ሁሉ ጌታን አመስግነው ስላለመጥገባቸው፣ የእነርሱ አምልኮ መሬት እንደማይወድቅ፣ ሕይወታቸው ቅድስናና ታዛዥነት የሞላበት እንደ ሆነ ... በሚገልጹ ስንኞች ተገጥግጧል፡፡ በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ድንኳን፣ "እኔ የተሻልኩ ነኝ" የሚል ባህል እንደ ሰርዶ ሥሩን ሰዷል፡፡ ምን ይሻለናል? እውነትን ፍለጋ የት እንሂድ?

መርካቶ ሰዎች ዕቃ ተሻሽጠው ብር ሲቀባበሉ ያዩ ሰዎች "ባየ፣ በተመለከተ" እየተባለ ትንሽ ብር እንደሚደርሳቸው ወይም ምሳ እንደሚጋበዙ እንስማለን፡፡ አንድን ሰው እግዚአብሔር ሲፈውሰው በዕለቱ የነበሩ አገልጋዮች ሁሉ "ባየ፣ በተመለከተ" ዐይነት ክብርን ፍለጋ መድረክ ላይ ቪዲዮ ለመቀረጽ ሲገፋፉና ሲተረማመሱ እናያለን፡፡ እውን ይህ  ጌታን ለማሳየት ነውን?



"እኔ ላንስ አንተ ልትልቅ ይገባል" የሚል ሰው ለመጥፋት የተቃረበ ዝርያ እየሆነ ይመስላል፡፡ የብዙዎች ግፊያ ወደ አምልኮተ እኔ አዘንብሏል፡፡ የኢየሱስ ስም ራሳቸውን ለማግነን የሚጠቀሙበት መንደርደሪያ ብቻ ሆኗል፡፡ አንዱ ከሌላው የተሻለ መሆኑን ለማሳየት፣ እርሱ የሚያካሂደው (የሚሰብክበት) ኮንፈረንስ "ታላቅ" መሆኑን ለማሳየት ይጣጣራል፤ ይተራመሳል፡፡ ለዚህ ይሆን ኮንፈረንሶች ሁሉ "ታላቅ ... ኮንፈረንስ" እየተባሉ ያሉት? እንዲህ የማይል የኮንፈረንስ ማስታወቂያ ያየ አለ? ታናሽነቱን የሚያምን ማነው? ለመሆኑ ታናሽ በሌለበት ታላቅ መሆን ይቻላልን? ሁሉስ ታላቅ ይሆናል?

### ለ. የሹመት ጥማት

የአገልግሎት ግብ ከስም በፊት የሚደነቀር መጠሪያ ሹመት ለማግኘት ይመስል በአገልግሎት ስም ለዝናና ለጥቅም ሲደረግ የምናየው መሟሟት ከፍተኛ ነው፡፡ በእርግጥ ምክንያት አላቸው፤ በአገልግሎት ሰበብ ስም ካላገኙ በሌላ በኩል ስም ለማግኘት ብቃት የላቸውም፡፡ ሰዎች ቦታ የሚያገኙት በስም እየሆነ ነው! በዚህም ላይ በአገልግሎት ምክንያት መጠሪያ ማግኘት "እገሌ" ለመባል ርካሹ መንገድ ነው፡፡ በቅርቡ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ለሚካሄድ የሽማግሌዎች ምርጫ አንዳንድ የቀድሞ ሽማግሌዎች ስልክ እየደወሉ፣ በየቤቱ እየሄዱና እያባበሉ፣ አንዳንዶቹንም እያስፈራሩ "የምረጡኝ" ቅስቀሳና ዘመቻ ሲያካሂዱ ነበር፡፡ እውነት ይህ ሁሉ ጥረት እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው? "ሟች (ሰው) መሆናችሁን አትርሱ" የሚላቸው ሰው የላቸውም?

ስለዚህ ዛሬ ዛሬ መጋቢያንን የምናውቀው ሕዝቡን ሲመግቡ አይደለም፤ ፖስተር ላይ ፎቶአቸው ሲለጠፍ ነው፡፡ ፎቶአቸውን ፖስተር ላይ ስናይ "እገሌም 'ፓስተር' ሆነ?" እንላለን፡፡ እንዲያውም ፖስተሩ ሳይሆን ፓስተሮቹ እንደ ተለጠፉ ማሰብም ያስኬዳል፡፡ 'ፓስተርነት' ፖስተር ላይ መለጠፍና የኮንፈረንስ ተናጋሪ ብቻ መሆን መሰለሳ! ሰው በየቦታው ምስሉን ካልለጣጠፈ 'ፓስተር' የሆነ አይመስለውም ልበል?

የመጋቢው ፎቶ
    በደማቅ ቀለም አሸብርቆ፣
    በክራቫት ታንቆ፣
ምስሉ
    ግምቡ ላይ ተለጥፏል፤
ከታች
    "ፓስተር እገሌ" ይላል፡፡

ደግሞ ጥቂት ዐለፍ እንዳሉ
ብዙ ምሰሶ ላይ ብዙ ፓስተር ያያሉ፤
በቃ፤
ፓስተር ሁሉ ተለጥፎ፣
በታላቅ ድል ራሱን ጽፎ፣
በየግርግዳው ስሙ ገነነ፤
ይኸውላችሁ፤
ፓስተርነት ፖስተር ሆነ።[8]

አንድ ጊዜ ሦስት ሆነን ስንነጋገር፣ አንዲት እኅት ከመካከላችን አንዱን አየችና፣ "ፓስተር" ብላ ስትጠራው ተወርውሮ ሄደ። አነጋገሯት ሲመለስ፣ "ፓስተር ሆነሃል እንዴ?" ብዬ ጠየቅሁት። እንዳልሆነ ሲነግረኝ፣ "ታዲያ ለምን መሳሳቷን አልነገርካትም?" የሚል ተያያዥ ጥያቄ አስከተልኩ። ከሰሞኑ ፓስተር ለመሆን እያሰበ መሆኑን ነገረኝ (በሚታሰብ መሆኑ ነው)። ከጥቂት ጊዜ በኋላም "ፓስተር" ሆነ። በዚህ ዘመን ፓስተር መሆን ፈጣን ሎተሪን ከመፋቅ ይልቅ ቀላል ሆኗል። ለቤተ ክርስቲያን ከፈታም አንድ ወዳጄ እንዳለው፣ "በቂ ኩርፊያና ድፍረት" ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ይህ ሰው ከሰሞኑ ሳገኘው ደግሞ ሐዋርያ መሆኑን ማውራት ጀምሯል። እንዲህ ቀላል ነው ማለት ነው? ነን የሚሉትን ነገር የምር ራሳቸውም ያምኑበት ይሆን?

ከኢትዮጵያ ዕውቅ ሰዎች መካከል ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ (አባ መላ) አንዱ ናቸው። እኚህ ስመ ጥር ጀግናና ነገር ዐዋቂ ከታናሽነት ተነሥተው ነው የምኒልክ ዋነኛ ሰው ወደ መሆን የደረሱት። የሚመጥናቸው ማዕረግ እንዲሰጣቸው (ራስ እንዲሆኑ) ተወስኖ ነበር። አባ መላ ግን፣ "የስም መለዋወጥ እኔን አይጠቅመኝም። ሰው የሚከበረው እንዲሁም የሚታወቀው በሠራው ሥራ እንጂ በስሙ ብቻ አይደለም" ብለው እምቢ አሉ። ሆኖም እሳቸው ፊታውራሪ ሆነው ሌሎችን ሰዎች ደጃዝማችነት (ከፊታውራሪነት ይበልጣል) ድረስ ይሾሙ ነበር።[9] አባ መላ እስከ ዛሬም በፊታውራሪነት ነው የሚታወቁት።

አንድ መጋቢ ደግሞ ያሉትን ልንገራችሁ። አንድ ቦታ ተጋብዘው ስብከታቸውን ሊጀምሩ ሲሉ ያስተዋወቃቸው ሰው "መጋቢ" ብሎ መጥራት ረስቶ "ወንድም" በማለት አስተዋወቃቸው። እሳቸውም፣ "በስንት መከራ ያገኘሁትን ፓስተርነት ትተህ እንዴት 'ወንድም' ትለኛለህ?" በማለት ተቈጥተውት ስብከታቸውን ጀመሩ። ለካ ፓስተርነት ከወንድምነት ይበልጣል!?

ጌታ ኢየሱስ፣ "እናንተ ግን መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለ ሆነ እናንተም ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ። አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ። ሊቃ



ችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ ነውና ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ" (ማቴ. 23፥8-10) በማለት ለምን አስተማረ?

ትምህርት ቤት ሳለን ብዙዎቹን አስተማሪዎቻችንን "ቲቸር" ብለን ነው የምንጠራቸው (አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ቦታ እንዲህ መሰለኝ)። ይህ አጠራር የማይስማማቸው አንዳንድ መምህራን ግን አሉ። አንደኛው አስተማሪ "ቲቸር" ሲባሉ፣ "ተስፋዬ ነው ስሜ!" ይላሉ ተቈጥተው። ከዚያም፣ "ገበሬ ስታገኙ 'ገበሬ፣ ገበሬ' ብላችሁ ልትጠሩት ነው?" በማለት መልሰው ይጠይቁናል። እኔን የሚናፍቀኝ ነገር "ፓስተር" ወይም "ነቢይ" ተብሎ ሲጠራ "ተስፋዬ ነው ስሜ!" የሚል ሰው ማግኘት ነው (ይኖር ይሆን?)። ለመሆኑ ይሄ ነገር ሹመት ነው ወይስ አገልግሎት?

እውነተኛ መጋቢ ስለ መሆናቸው ባናውቅም፣ ፓስተር የሚል መጠሪያ ያላቸው ሰዎች በዝተው "ሞከሼ፣ ሞከሼ" ተባብለው የሚጠራሩበት ደረጃ ደርሰዋል። መጋቢ መባላቸው ባልከፋ፣ አንዳንዶቹ ሥልጣናቸውን እንጂ ሕዝቡን የሚወዱ አለመሆናቸው በተለያየ መልኩ የሚገለጥ ሆነ እንጂ! ሰዎችን የማይወድ ሰው እንዴት መጋቢ ይሆናል? (እነዚህ ሊመግቡን ነው ሊመገቡን?)

በተለያዩ ቦታዎች ሰባኪዎችን ሁሉ "ፓስተር" ብሎ መጥራትም ተጀምሮአል። በእነርሱ ቤት እነርሱን የሰበከ ሁሉ ፓስተር ነው። ስለዚህ አንዳንዶቻችን ስብከታችንን የምንጀምረው "ፓስተር" አለመሆናችንን ("ወንድም" መሆናችንን) በማስረዳት ሆኗል። አገልግሎቱን በአግባቡ እያካሄዱ "ወንድም" እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች ምን ጐደለባቸው? በአገልግሎታቸው በብዙ አቅጣጫዎች ለበርካቶች ዕረፍት፣ መነቃቃትና መታደስ ምክንያት የሆኑ ወንድም ብቻ ተብለው እየተጠሩ ያሉ ሰዎች የሉምን? (በዚህ ጒዳይ ወንድም ንጉሤ ቡልቻን እና ወንድም ማሙሻ ፈንታን እንጠይቃቸው ይሆን?)

የሹመትና ከሌላው ተለይቶ የመታየት ጥማት ቅጥ አጥቷል። "ፓስተርነት" ረከስ እያለ ሲመጣ ደግሞ ሐዋርያ የሚባሉት ሰዎች ቍጥር እየጨመረ ነው። ሐዋርያነት የመጨረሻ እንደማይሆን ከዚህ በፊትም ግምቴን ገልጫለሁ። "ሐዋርያ ነኝ" ከሚሉት ወገኖች ሁለቱ (ለጊዜው ያወቅኋቸው እነርሱን ብቻ ነው) "መልአክ ነኝ" ማለት ጀምረዋል። አንደኛው ሰው በሚያሳትመው ጋዜጣ እስከ ዛሬ "ሐዋርያ" እያለ ራሱን ሲጠራ ከረመና አሁን ደግሞ፣ በግልጽ ራሱን መልአክ አድርጎ እያስተዋወቀ ነው።[10] ሌላኛውም መልአክ መሆኑን መስበክና ማስተማር ቀጥሏል። "መላእክት ነን" የሚሉ ሌሎች ሲመጡባቸውስ "የመላእክት አለቃ ነን" ይሉን ይሆን? ይህም ግን የመጨረሻ እንደማይሆን እፈራለሁ (ለነገሩ "ሐዋርያ"ም ሆነ "መልአክ" መልእክተኛ ማለት አይደል?)

የሚገርመው መጠራት የሚፈልጉት በዚህ ራሳቸውን በሾሙበት ማዕረግ እንጂ በመዝገብ ስማቸው አለመሆኑ ነው፤ የትም ቢሆን! ለመሆኑ ዕድር ቦታ ሐዋርያ አገሌ ተብሎ መጠራት ፋይዳው ምንድን ነው? ኳስ መመልከቻ ቦታ ፓስተር ተብሎ መጠራት ለምን አስፈለገ? ከዚህ በፊት የምሠራበት ቦታ የመጣ አንድ ሰው ያመጣልኝን ዕቃ መረከቤን የሚገልጥ ደረሰኝ ልቈርጥለት ስሙን ስጠይቀው፣ "ሐዋርያ አገሌ" በማለት ነገረኝ። ደረሰኙን "ለአቶ ሐዋርያ" ብዬ ቈረጥኩለት። ሙሉ ስሙን የነገረኝ ነበር የመሰለኝ፤ እርሱ ለካ "ሐዋርያ ነኝ" ማለቱ ነበር (አልተገናኝቶ!)።

በመጽሔትና በፖስተር ሐዋርያት፣ በመጽሔትና በፖስተር ነቢያት፣ በመጽሔትና በፖስተር ፓስተሮች ትርምስ ተሰላችተናል። "ሐዋርያት ነን፣ ነቢያት ነን፣ ፓስተሮች ነን፤ ዕወቁን" የሚል ጩኸት ሊያደነቁረን ተቃርቧል።

ፖስተር ማስታወቂያ ነው፤ ሌላ ሥራ የለውም። ግን የፖስተሮቹ ብዛትና በላያቸው የሚጻፉት ነገሮች አስተዛዛቢ እየሆኑ ነው። ችግሩ፣ ሐዋርያና ነቢይ ነኝ ባይ ሁሉ የዝና ጥማቱን የሚያረካባቸው በመምሰሉ እንጂ፣ ዘመኑ የሚጠይቀውን ማስታወቂያ መጠቀምማ ምን ክፋት አለው? እኔን የሚታየኝ ግን ፖስተሩ ግብ እየሆነ መምጣቱ ነው፤ ዓላማ እየሆነ ነው።

አንድ ሁለት ምሳሌ ልጥቀስ። አንድ ፖስተር ትዝ ይለኛል። ፖስተሩን የሞላው የሰውዬው ትልቅ ምስል ሲሆን፣ ምስሉ ላይም፣ "ባለ ራእዩ እኔ ነኝ" (2ሳሙ. 9፥19) የሚል ጥቅስ ተጽፎበታል።

ሌላኛው ደግሞ በፖስተሩ የላይኛው ክፍል የአንደኛው ፎቶ ገጭ ብሏል፤ ባሕረ ጥምቀት እንዳደረ ታቦት የእርሱ ፎቶ በሌሎች ዝነኞች ፎቶ ተከቧል፤ እነርሱ ደግሞ ከታች ተሰልፈዋል (አብዛኞቹ የተለያዩ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ፓስተሮች፣ ነቢያትና ሐዋርያት ነን ባዮች ናቸው)። የላይኛው ሰውዬ ምስል ላይ፣ "የመሪዎች ኅብረት መሪ" ተብሎ ተጽፏል። እርሱ መሪ ሲሆን፣ ከታች ያሉት ተመሪዎች መሆናቸው ነው። እሺ ይህ አንድን ኮንፈረንስ ለማስተዋወቅ ብቻ ተብሎ የተዘጋጀ ነው ወይስ ራስን ማግነኛ?

በአንዳቸው የሐዋርያነት "በዐለ ሲመት" ላይም ተገኝቼ ነበር፤ በመጥሪያ ካርድ ነበር የተጠራሁት። እዚያ ቦታ ይህ ሰው፣ "እንደ መልከ ጼዴቅ ለዘላለም ካህን ነህ" ሲባል ነበር፤ በአደባባይ! ሰዎች የአገልግሎት ኀላፊነቱን እንጂ ክብርና ዝናን ባይፈልጉ ኖሮ፣ "እንደ መልከ ጼዴቅ ለዘላለም ካህን ነህ" ሲባሉ መደንገጥ ነበረባቸው። ይህ የተነገረው ለጌታ ሲሆን፣ ከእርሱ ሌላ ሊባልለት የተገባው አንድም ሰው የለም፤ አልነበረምም። አባባሉ ተመችቷቸው በዝምታ መቀጠላቸው ሲታይ ብንደነግጥ ይፈረድብናል? በዚህም ላይ፣ "ተሳስቻለሁ"



የሚል ቃል ከአፋቸው አይወጣም። ገድላቸውን ከሚናገሩበት ከዚያ ሁሉ ዕልፍ ነገር መካከል "ተሳስቻለሁ" ማለት ማንን ገደለ? ግን እስከ መቼ እንዲህ ይቀጥላሉ? ወደ ጆሮአቸው ጠጋ ብሎ፣ "አንተም ሟች መሆንህን አትርሳ!" በማለት ተገቢውን መልእክት የሚነግራቸው "ባርያ" እንዴት ይጥፋ!?

### *ሐ. የአድናቂዎች መብዛት*

ሌላኛው ችግር ደግሞ የአጃቢዎች መብዛት ነው። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማሳት በዚህ ዘመን እየተጠቀመባቸው ካሉት ዘዴዎች አንዱ ይህ ይመስለኛል። ዐዋቂ ሰው፣ እግዚአብሔር ከአጃቢዎች እንዲጠብቀው ይጸልያል። ከአድናቂና አጃቢ ይልቅ "ሰው መሆንህን አትርሳ" የሚል ሰው እንዳያሳጣው ይጸልያል። ወዳጁንም፣ "ከአጃቢዎች ይጠብቅህ" እያለ ይመርቃል።

ሰዎችን ማድነቅ መልካም ነገር ነው። አንዳንዴ ደግሞ ግድ ይሆናል። ለምሳሌ ሻለቃ ኀይሌ ገ/ሥላሴን፣ ኔልሰን ማንዴላንና ማርቲን ሉተር ኪንግን አለማድነቅ ይቻላል? ወደ መንፈሳዊው ዓለም ስንመጣ ግን "አድናቂ" የሚለው ቃል ላይ ጥርጣሬ አለኝ።

መጽሐፍ፣ "ብር በማቅለጫ፣ ወርቅ በከውር እንደሚፈተን፣ ሰውም በሚቀበለው ምስጋና ይፈተናል" ይላልና (ምሳ. 27፥21 - አ.መ.ት)፣ በሌሎች መመስገን ራሱን የቻለ ፈተና ነው። ምስጋና ሲቀርብልን ምስጋናውን ወደ እግዚአብሔር የማዞር፣ ወይም ምስጋናው የተገባን እንደ ሆነ የመቍጠር ምርጫ አለን። ሐዋርያው ጳውሎስ የፊተኛውን መርጧል። "ከሁላቸው ይልቅ ግን እኔ ደከምሁ፤ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም" (1ቆሮ. 15፥10)። ታዲያ ማድነቅ ያለብን ማንን ነው? ጳውሎስን ወይስ የእግዚአብሔርን ጸጋ?

ተቃዋሚ ያጣና በደጋፊዎቹ ብቻ የታጠረ ሰው ብዙ ርቀት አይጓዝም፤ በትዕቢት ይወድቃል። ተቃዋሚዎች ሞልተውት ደጋፊ የሌለው ሰው ደግሞ ጦርነቱ ልቡን ያዝለውና ተስፋ ይቈርጣል። ስለዚህ፣ "አድናቂህ ነን" የሚሉ ሰዎች አገልጋዩን እግር በእግር እየተከታተሉ ከሚያጨበጭቡለት ይልቅ የሚመክሩት፣ የሚጸልዩለት፣ የሚያበረታቱት፣ እንዲሁም ጠንካራና ደካማ ጎኑን የሚጠቁሙት ቢሆኑ ይበልጥ ይጠቅሙታል። ያም ልቡ እንዳይዝልና ተስፋ እንዳይቈርጥ ያግዘዋል።

ተቃዋሚዎች ሲኖሩ መልካም ነው። አገልጋዩ አገልግሎቱንና ሕይወቱን በአግባቡ እንዲመራ ያስችለዋል። ተቃዋሚ ያለባቸው ሰዎች ስብከታቸው፣ ጽሑፋቸው፣ ዝማሬያቸው ላይ እንከን እንዳይገኝ ተገቢውን ጥንቃቄ

ያደርጋሉ:: የደጋፊዎች መኖር መታከትን፣ የተቃዋሚዎች መኖር ደግሞ ስሕተትን ለመቀነስ ያግዛልና ሚዛናችንን ጠብቀን እንድንጓዝ ሁለቱም ያስፈልጉናል:: መልካሙ እግዚአብሔር መልእክቴን ለመቀበል ዝግጁ ልብ ባላቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ በተቃዋሚዎችም ስለ ባረከኝ ላመሰግን ይገባኛል::

ስሕተቶቼን ያወቅሁት ተቃዋሚዎቼ የቻሉትን ያህል ነቅሰው ስለሚያወጧቸው ሲሆን፣ አሁንም ስሕተት እንዳይገኝብኝ የምታትረውም ከእነርሱ የተነሣ ነው:: "ስሕተቱን ማን ሊያስተውል ይችላል?" መጽሐፍ እንደሚል (መዝ. 19፥12 - አ.መ.ት)፣ ስሕተት መሥራቴን እንድገነዘብ ስሕተቶቼን የሚነግሩኝ ሰዎች ያስፈልጉኛል:: ለእስካሁኑ፣ ምክንያታዊ ተቃዋሚዎቼንና ምክንያታዊ ደጋፊዎቼን ከልብ አመሰግናለሁ (ከጭፍን ደጋፊዎችና ከጭፍን ተቃዋሚዎች ፈጣሪ እንዲጠብቀኝ ግን እጸልያለሁ):: የሚያበረታታኝን ሰው ሳገኝ የምጠነክረውን ያህል፣ ምክንያታዊ ተቃዋሚ ሲኖረኝ እግዚአብሔር በቤቱ ሥራ በተሻለ ሊያስነብተኝ እንደ ፈለገ ነው የሚታየኝ::

ቅድስት ማርያምና ቅዱስ ዮሴፍ ከቤተ መቅደስ ሲመለሱ የብዙ ሰዎች ግርግር ስለ ነበር ጌታ ኢየሱስ አብሮአቸው አለመሆኑን ለማወቅ አንድ ቀን ፈጅቶባቸዋል (ሉቃ. 2፥41-44):: ብዙ አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ጋር ሲተላለፉ እንኳ የማይነቁት ግርግር እየበዛባቸው ይሆን? አጃቢ ሲያጡ ብርድ ብርድ የሚላቸው አገልጋዮች ሁሌም ተከብበው ነው የሚታዩት:: አለመታጀብ መታደል እንደ ሆነ አያውቁምና ለፍቅርም ሆነ ለጠብ የሚፈልጋቸው ለብቻ አያገኛቸውም:: ለመሆኑ ብቻነት አያምራቸውም? ሌላው ቀርቶ ራሳቸውን ቢያጡና ቢናፍቁ አይገርመኝም::

እነ ሐዋርያው ጳውሎስን ብዙ ቀን እየተከተለች፣ "የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው" እያለች የምትጮኽ አንዲት ሴት ነበረች:: ቅዱስ ጳውሎስ ግን በዚህ ስለ ተቸገረ ያለባትን ርኩስ መንፈስ ገሥጾ እርሱን እየተከተለች ከመሄድ ገላግሏታል (የሐዋ. 16፥16-18):: አድናቂዎቻችንን መመርመር (መጠርጠር) ብልህነት ነው:: በተለይ አንዳንድ የመድረክ ሰዎች በጥፋታቸው ሲገሠጹ ነገሩ ተገቢ (ትክክል) ቢሆን እንኳ፣ "ለምን ተነኩ?" በማለት አካኪ ዘራፍ የሚቃጣቸው አድናቂዎች ይህን የሚያደርጉት በስሜታዊነትና በወገናዊነት ብቻ ባይሆንስ? ይህን ዐይነቱን ጭፍን ድጋፍ ሰይጣን ሊጠቀምበት አይችልምን?

በተለይ በጭፍን የሚያደንቁን ሲበዙ መቃብራችን እየተቈፈረ መሆኑን አትጠራጠሩ፤ እንደማንሳሳት የሚያስቡ አድናቂዎች ውድቀታችንን ያፋጥናሉ:: አንዳንዶቹ የሚያቀርቡትን መወድስ በአጋጣሚ ብትሰሙማ፣ "ሰው እነዚህን



እየሰማ እንዴት ትእቢተኛ አይሆንም?" የሚል ጥያቄ ማሳደራችሁ አይቀርም:: መፍትሔው ከእንዲህ ዐይነቶቹ አድናቂዎች መራቅ ነው:: ማንንም ቢሆን በጭፍን ለማድነቅ ፈቃደኛ መሆን የለብንም:: እኔ በበኩሌ ጌታ ኢየሱስንም እንኳ በጭፍን አልተከተልኩትም፤ ነፍሴ ከነጥያቄዎቿ ተሸንፋ፣ አሳምኖኝ እንጂ!

መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የሚሰጠው መናፍስትን የመለየት ጸጋ የሚረዳን ጠቋርንና ቡዳን ለመለየትና ለማስወጣት ብቻ አይደለም:: ከአንዳንድ አድናቂዎች፣ አገልግሎቶችና ዕቅዶች ጀርባ ያለውን ሐሳብና መንፈስ ለመረዳትም ይጠቅማል:: ስለዚህ እግዚአብሔር ይህን ጸጋ እንዲሰጠን ብንጸልይ ይበጀናል:: ይህ ጸጋ በትክክል ቢኖረን፣ የራስን ስም ለማስጠሪያ የተዘጋጁ በርካታ ኮንፈረንሶች ይሰረዙ እንደ ነበር አስባለሁ!

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ብዙ ተከታዮች፣ እንዲያውም እርሱ ባይፈልግ እንኳን የግድ ሊያነግሡት የሚፈልጉ አጃቢዎች ቢኖሩትም አይደሰትባቸውም ነበር:: ስለዚህ በአስጨናቂ ንግግሩና ጠንካራ ትምህርቱ ከአጠገቡ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል (ዮሐ. 6፥15-66)::

ከአድናቂዎች የሚቀርብልንን ሙገሳ ሁሉ መቀበል ያለብንም አይመስለኝም:: አንድ ጊዜ ከአለቆች አንዱ ጥያቄ ይዞ ወደ ጌታ ኢየሱስ መጣና፣ "ቸር መምህር ሆይ" ብሎ መናገር ጀመረ:: እርሱ ግን፣ "ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም" በማለት መለሰለት (ሉቃ. 18፥18-19):: ጌታ ቸር ነው፤ ሆኖም፣ "ለምን ቸር ትለኛለህ?" ብሎ ጠይቆ፣ ጠያቂውን ወደ እግዚአብሔር መርቶታል:: እኛስ?

እኛማ እናጨበጭባለን! አገልጋዩ ወደ መድረክ ሲወጣ እናጨበጭባለን:: ማገልገል ሲጀምርና በየመካከሉም እናጨበጭባለን፤ ሲጨርስም አጨብጭበን እንሸኘዋለን:: የጭብጨባ ዘመን! ለሁሉ የማጨብጨብ ክፉ ልማድ! ኤፍሬም እንዳለ የተባሉ የአዲስ አድማስ ጋዜጣ ዐምደኛ፣ "አንድዬ፣ 'ምድርንም በጭብጨባ ሙሏት' ምናምን ብሎ ያጻፈው ሕግ አለ እንዴ! እህ ብዙዎቻችን የመንግሥተ ሰማያት አቋራጭ በጭብጨባ በኩል ነው የተባልን ይመስላል!" በማለት የሰጡትን የትዝብት አስተያየት እኔም እዚህ እጋራዋለሁ::"

በአድናቂዎች ብዛትና በጭብጨባ ሩምታ ብዙዎች ሞተዋል:: እስቲ "ያለ ቀን የሞቱ" የሚለውን ቀጣዩን ግጥም አብረን እንመልከት፤

ጦርነቱ በዛ፣ ብዙ ሰው ተፈጀ፣
አንዱም ዕድሜ አልበቃው፣
... አንዱም አላረጀ

ገና በማለዳ በየለጋው ዕድሜ፣
    አገር ተላለቀ፣
ፍሬ የቋጠረውም፣ ጀማሪው ደረቀ፤
በሽታው ሳይታይ የሐኪም ደጅ ሳያየው
    ሟቾች በረከቱ፣
በሕዝብ ጭብጨባ
    አያሌዎች ሞቱ፡፡[12]

የትንኝ ልጅ ለበረራ ሙከራ ውጭ ወጥታ ስትመለስ ደስ ብሏት እናቷን፣ "ዛሬ ሰው ሁሉ ሲያጨበጭብልኝ ዋለ" አለቻት አሉ፡፡ "አዬ" አለች እናት፣ "ጨፍልቀው ሊገድሉሽ እየሞከሩ እንጂ እያጨበጨቡልሽ አልነበረም እኮ!"

እንደ ጭብጨባ ሳይታወቅበት ታላላቁን ሰው እየነጠለ የሚገነድስ መሣሪያ ይኖር ይሆን? ፕሮፌሰር መስፍን ይቀጥላሉ፤ "... የሕዝቡ ጭብጨባና ውዳሴ ላልለመደው ሰው እንደ ከፉ መጠጥ የሚያሰክርና ጭንቅላትን የሚያሳብጥ ነበር" በማለት የጭብጨባን ሞቅታና አደጋ ያስረዳሉ፡፡[13] በዕድሜ፣ በዕውቀትና በተሞክሮ የደረጀ ምክር ነው፡፡

ይህ እንዲህ ሲሆን አገልጋዮቹ እየገዘፉ፣ የአገልግሎታቸው ግብ (አገልግሎቱ ለእግዚአብሔር የሚያመጣው ክብርና ለሕዝቡ የሚሰጠው ጥቅም) እየኮሰሰ ይመጣል፡፡ ከዚህ ውድቀት እንዳይወጡ ደግሞ በአድናቂዎች ተከበዋል፡፡ በዚህ መልኩ ሕዝቡ ከፍ ከፍ የሚያደርጋቸው ዘማሪዎች፣ "ፓስተሮች"፣ "ነቢያት" እና "ሐዋርያት" ራሳቸውን ከፍ ከፍ እያደረጉ ሲታዩ ፈራሁላቸው፡፡ የተሰቀለውን ጌታን እንዲሰብኩና እንዲተርኩ በተሰጣቸው እስትንፋስ ራሳቸውን ሲሰብኩ ቆይተው መውረዳቸው ሌላም ከባድ ችግር አለው፡፡ ምዕመናኑ ካልተሰበከለት ኢየሱስ ይልቅ የተሰበኩለት አገልጋዮች ተከታይ እየሆነ ነው፡፡ የአገልጋዮች ቲፎዞ ሲሆንም፣ "እኔ የእገሌ ነኝ፤ እኔ ደግሞ የእገሌ ..." ማለት ይጀምራል፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንኳ የግለ ሰቦች ሆና "የእገሌ ቸርች" መባል ተጀምሯል፤ ሰዉም ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ ማለቱን ትቶ፣ "እገሌ ጋ እሄዳለሁ" ሲል እየሰማን አይደል?

ውዳሴና ምስጋና ሲበዛ፣ አፋሽ አከንፋሽ የበረከተበት ሰው ፈተና ውስጥ ይገባል፡፡ የሆነውን ሁሉ እግዚአብሔር ሳይሆን፣ ራሱ ያደረገው ይመስለዋል፡፡ የእርሱ ዐይነት ሰው እንደ ጠፋና ተተኪ እንደሌለው መገመት ይጀምራል፡፡ ያኔ የውድቀት ቀን መድረሱን መጠርጠር ደግ ነው፡፡ ለዚህም ነው በመንፈስ የጀመሩ ሰዎች በሥጋ የሚጨርሱት፤ በትሕትና የጀመሩ በትዕቢትና በውድቀት የሚያጠናቅቁት፡፡ ከታበዩ መዋረድ ግዴታ ነው፡፡



ኩራትና ትዕቢት የሞሉት እናት
ሰይፍና ጎራዴ የመቱት ዐንገት
አይገላገሉም እንዲህ በቀላሉ
እመሬት ላይ ወድቀው ሳይንከባለሉ፡፡[14]

እግዚአብሔር ደግሞ በምንም ታሪክ ትዕቢትን አያልፍም፤ ሳጥናኤልን በጣለበት "በነካ እጁ" ነው የሚያሰናብተን፡፡ ቅዱስ ዳዊት ከሰው ሚስት ጋር ሲያመነዝርና ኀጢአቱን ለመሸፈን ንጹሕ ደም ሲያፈስ፣ በአንድ እጅ ጣቶች የሚቈጠሩ ሰዎች ናቸው የሞቱት፡፡ ዳዊት በትዕቢት ሲጠመድ ግን ሰባ ሺህ ሰዎች ሞተዋል (1ዜና 21፥14)፡፡ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል (1ጴጥ. 5፥5፤ ያዕ. 4፥6)፡፡ የሚታበይ ሰው ቅጣቱን እጅ በእጅ ይቀበላል፤ ይህም ቅጣት ውድቀት (ውርደት) እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ ይናገራል (ምሳ. 11፥2፤ 16፥5፤ 18፥12)፡፡ ትዕቢተኛ መጨረሻው አያምርም፡፡

እግዚአብሔር አስደናቂ ጸጋ የሰጣቸው ሰዎች በትሕትና በማገልገል ፈንታ ገድላቸውን መተረክ ለምን እንደሚወዱ ግራ ይገባኛል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ከአብዛኞቹ አስደናቂ ፈውሶች በኋላ ሰዎቹ ለማንም እንዳይናገሩ ያስጠነቅቃቸው የነበረው ለምን ነበር? ከመታወቃቸው በፊት ጥሩ አገልግሎት የነበራቸው ሰዎች፣ በየመጽሔቱ ሽፋን ላይ ፎቶአቸውን መለጠፍና "የሠሩትን" ተአምራት መተረክ ሲጀምሩ ትኩረት ቢስቡም፣ አገልግሎታቸው እንደ በፊቱ አሳማኝ ሲሆን አይታይም፡፡ የአገልጋዩ ዝና እየጨመረ፣ ጸጋው ግን እየቀነሰ ይመጣል፡፡ ሰዎቹ ብዙ የአገልግሎት በር ቢከፈትላቸውም፣ የተከታያቸው ቍጥር ቢጨምርም፣ "ያኔ ድሮ ሳገለግል እንዲህ ሆነ ..." በማለት እያወሩ ነው የሚኖሩት፤ መሞት ጀምረዋል ማለት ነው፡፡

እማሆይ ቴሬዛ አገልግሎታቸው የሰዎችን ትኩረት መሳብ ሲጀምር ደስታ ሳይሆን ፍርሀት እንደ ገባቸው ነው ለመንፈሳዊ አማካሪያቸው ደብዳቤ የጻፉት፡፡ "ከመጠን ያለፈ ትኩረት እያገኘን ስለሆነ በጣም ፈርቻለሁ፡፡ ... እኔ ለዓለም ትርጕም እንዳይኖረኝና ዓለምም ለእኔ ምንም ትርጕም እንዳይኖረው እባክህን ጸልይልኝ" ብለዋል፡፡[15] እማሆይ የጌታን ድምፅ ሰምተው ያንን የተባረከ አገልግሎት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ ለማድረግ ነበር ምኞታቸው፤ ተሳክቶላቸዋልም፡፡

የጌታን ድምፅ ሰምተው በምሪት የጀመሩት Missionaries of Charity የተባለው ምግባረ ሰናይ ድርጅትን ራእይና አጀማመር የተገለጹባቸው የመመሥረቻ ሰነዶች እንዲወድሙላቸውም ደጋግመው ይወተውቱም ነበር፡፡ ይኸውም ለእግዚአብሔር ብቻ ሊሰጥ እንደሚገባ የሚያምኑበት ትኩረትና ከበሬታ ወደ እርሳቸው እንዳይዞር ፍርሀት እንደ ነበራቸው ያሳያል፡፡[16]

እንዲያውም በአንድ ወቅት ስለ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ታሪክ የሚጽፍ ሰው ሲመጣ፣ "መጽሐፉን ስትጽፍ ስለ እኔ ግላዊ ሁኔታ እባክህ አትጻፍ። ስለ ሚያገለግሉት እኅቶችና ስለ አገልግሎቱ ሁሉንም ነገር መጻፍ ትችላለህ። እኔንና ቤተ ሰቤን ግን እባክህ ከጽሑፉ ውጭ አድርገን" ብለው ለምነውታል።[7]

እግዚአብሔር፣ አገልግሎትን በተመለከተ ራሳችንን ማሳየታችንን አይወድም። በእርሱ ላይ እንጂ በራሳችን እንድንተማመንም አይፈልግም። ሙሴ እችላለሁ ብሎ ሲያስብ እግዚአብሔር አብሮት ሊሠራ አልወደደም። ይልቁንም በዚህ "እችላለሁ" ባይነቱ ከአገሩ ተሰድዶ ለ40 ዓመት ተንከራተተ። "አልችልም፣ ሌላ ሰው ይፈለግ" በሚልበት ጊዜ ግን እግዚአብሔር ሥራውን እንዲጀምር አደረገው። ሙሴ በራሱ በጀመረ ጊዜ ሁሉ ጥፋት ነበር ያመጣው። እማሆይ ቴሬዛም፣ "አልችልም ጌታ ሆይ፣ አንተ የምትፈልገውን ነገር ግማሹን እንኳ መረዳት አልቻልኩም። የማልበቃ ነኝ። ኀጢአተኛና ደካማ ነኝ። ሌላ ብቁና ሊጋስ የሆነን ሰው ፈልግ እባክህ" በማለት ይማጸኑ ነበር።[18] እግዚአብሔር ሥራውን የሠራው ግን በእርሳቸው በኩል ነው።

አንድ ጥሩ መዝሙር ሠርተው "ጎሽ" ሲባሉ፣ "ምድር የማትሸከመውን ጸጋ እግዚአብሔር በእኛ ላይ አስቀምጦ ..." በማለት ጉራ የሚነዙ ዘማሪዎችን ዐውቃለሁ። "ሙዚቀኛው ካልተቀደሰ ለእኔ መዝሙር ሙዚቃ መጫወት አይችልም" የሚል ትዕቢት ሲጀምራቸው አይቻለሁ። ሰባኪዎችም "ትንሽ ጉባኤ" ላይ መስበክ እንደማይመጥናቸው ሲናገሩ አድምጫለሁ፤ ዘልቀው የሚጓዙ ግን አይደሉም። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል። ራሳችንን ዝቅ ዝቅ በማድረግ ለእግዚአብሔር ክብር ካልሰጠን እግዚአብሔር አይደሰትብንም (አገልግሎታችን ግን ምናልባት ይቀጥል ይሆናል)። እግዚአብሔር ካልተደሰተብን መጨረሻችን ውድቀት መሆኑ አይጠረጠርም። ታዲያ እንዳንወድቅ የሚያግዘን ከሆነ፣ "ሰው መሆናችሁን አስታውሱ" የሚለን ብቻ ሳይሆን፣ ዱላ ይዞብን የሚመጣ ሰውስ ቢኖረን ምናለበት?!

## ምን ተሻለን ታዲያ?

እግዚአብሔር እንድንሰብክ፣ እንድንዘምር፣ ምክር እንድንሰጥና እንድንጽፍ አይደለም በቀዳሚነት የጠራን፤ እንድንኖርለት እንጂ! በመጀመሪያ ክርስቶስ ትቶልን ያለፈውን የሕይወት ፈልግ እንድንከተል (እንድንኖርለት)፣ ከዚያም እንድናገለግለው ይሻል። ለዚህም መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናልና በትሕትና እንኑር! የመንፈስ ቅዱስ ዋና ዓላማ ኢየሱስን ማክበር ነው፤ ራሱን ማክበር እንኳ አይደለም። ዛሬ ራሱን (ስሙን) ማግነንና ማክበር የሚሻ ሰውም ሆነ ድርጅት ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሲያድርብን፣ "ግዛኝ፣ ምራኝ፣ እኔ



አልችልበትም" ነው የምንለው። ራስን ዝቅ ዝቅ አድርጎ ጌታን ከፍ ከፍ ማድረግ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት አንዱ ማስረጃም ነው። መንፈስ ቅዱስን ዕድል ከሰጠነው ሰው መሆናችንን ያስታውሰናልና "ሰው መሆናችሁን አትርሱ" የሚለንን ድምፅ ማድመጥ ይኖርብናል።

እኛ ግን የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ረስተናል፤ ለመልእክታችን ትክክለኛነት ማረጋገጫ እንዲሆነን መጠቀሚያ ብቻ አድርገን ወስደነዋል። ስለዚህ ሰዎችን አሳምነን ይሁን አግባብተን "ሃሌሉያ" ካሉልንና አዳራሹ በሆታ ከደመቀ መንፈስ ቅዱስ "የወረደ" ነው የሚመስለን። እኛ ራሳችን ዐቅም እንደሌለን፣ እርሱ ግን ሁሉን እንደሚችልና እንደሚያስችለን ዘንግተን፣ በችሎታችን ላይ ብቻ ተማምነናል። ምክሩን፣ ወቀሳውንና ተግሣጹን ችላ ብለናል።

እግዚአብሔር ታላቅ ነውና ማንንም አይንቅም። "የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፤ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም" ይላልና (መዝ. 51፥17)። በተለይ ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ሰው አይናቅም። ሆኖም የማይናቁት ሁሉም ሰዎች አይመስሉኝም፤ እግዚአብሔር የናቃቸው ሰዎችም አሉ፤ ሳዖል አንዱ ነው። እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤ "በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት ለሳዖል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው?" (1 ሳሙ. 16፥1)።

"ማንንም አይንቅም" የተባለለት እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ሲንቅ እናያለን። በሰው ፊት እየተከበሩ በእግዚአብሔር ከሚናቁት ወይም በሰው ፊት ቢናቁም ባይናቁም በእግዚአብሔር ከሚከበሩት ሰዎች አንዱ ለመሆን ምርጫው የእኛ ነው። ከትልቅነቱ የተነሣ አይተኬ፣ ከትንሽነቱ የተነሣ አይጠቅሜ ሰው በእግዚአብሔር ቤት የለም፤ ሁሉ ቦታ አለው። ነገር ግን ሁሌም "ሰው *ብቻ መሆናችንን*" ማስታወስ፣ ልካችንን ማወቅ፣ ይህንን ለሚያስገነዝቡን ሰዎች ቦታ መስጠት (ማክበር)፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ቅዱሱን መንፈስ ማድመጥ ይበጀናል። የእግዚአብሔርን ሥራ ለስማችን ማስጠሪያ እንዳናደርገው መጠንቀቅም ይጠቅመናል። ራሳችንን ከፍ ከፍ እንድናደርግና ሁሉ በእኛ የተደረገ እንዲመስለን ማድረግ ከሚቃጣቸው ሰዎች መሸሽም ደግ ነው፤ "ሳይቃጠል በቅጠል" እንዲሉ!

ጆሮ ያለው ይስማ!

## ማስታወሻ

1. *The NIV Study Bible* (Michigan: Zondervan Publishing House, 1985), 1815.
2. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 1765፡፡
3. http://en.wikipedia.org/wiki/Memento_mori መጋቢት 2004 ዓ.ም.
4. Philip Yancey, *The Bible Jesus Read* (Grand Rapid, Michigan: Zondervan, 1999), 89.
5. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 24፡፡
6. መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቱኒ ተምረን ወጣን* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 15፡፡
7. R. T. Kendall, *Second Chance* (London: Hodder & Stoughton, 2009), xvii.
8. ዳዊት ጸጋዬ፤ ያልታተመ፡፡
9. ታደሰ ዘወልዴ (ቀኛዝማች)፣ *ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ (አባ መላ)፣ አጭር የሕይወት ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ 1997 ዓ.ም) ገጽ 62፡፡
10. ይህ ጌታቸው ታሪኩ የተባለ ግለ ሰብ ከሚያዘጋጀው "የእግዚአብሔር ክብር" ከተሰኘ ጋዜጣ በተጨማሪ የተለያዩ መጻሕፍቱ ገበያ ላይ መታየት ጀምረዋል፡፡ የመጽሐፎቹ የፊት ለፊት ሽፋን ላይ ስሙን ከጠቀሰ በኋላ፣ "የክብር መገለጥ ሐዋርያና የትንሣኤው መልአክ" በማለት ራሱን ሲያሞካሽ፣ ጋዜጣው ላይ ደግሞ (ቊ. 007 - ነሐሴ 2001 ዓ.ም እትም) "የክብር መገለጥ ሐዋርያና የ7ኛው ሚሌኒየም የትንሣኤና ሕይወት መልእክተኛ፣ የዘላለም ወንጌል መልአክ" በማለት ራሱን ገልጿል፡፡
11. አዲስ አድማስ ጋዜጣ፣ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም፡፡
12. ደረጀ በላይነህ፤ *ብልግ ጀንበር ... እና የፍቅር ደብዳቤዎች* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም) ገጽ 54፡፡
13. መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቱኒ*፣ ገጽ 51-52፡፡
14. ከበደ ሚካኤል፤ *የቅኔ አዝመራ* (አዲስ አበባ፣ 1956 ዓ.ም) ገጽ 153፡፡
15. Mother Teresa, *Come Be My Light – The revealing Private Writings of the Nobel Peace Prize Winner* (London: Rider, 2007), 152.
16. ዝኑ ከማሁ፣ 4፡፡
17. ዝኑ ከማሁ፣ 205፡፡
18. ዝኑ ከማሁ፣ 96፡፡



# ያልተመለሰው የኢየሱስ ጸሎት?

በትውፊት "ጸሎተ ሐሙስ" ተብሎ ይታወቃል፤ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ላይ የምናገኘው ጸሎት፡፡ ይህ ሊቀ ካህናታዊ ጸሎት ብዙ የሚባልለት ቢሆንም፣ ለጊዜው አንዲት ሰበዝ ብቻ መዝዘን እንመልከት፤ አንድነታችንን፡፡ ጌታ ኢየሱስ፣ "ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው" (ቊ. 11)፤ "አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ፡፡ እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ... በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ ..." በማለት ጸለዮአል (ቊ. 21-23)፡፡

ጌታችን በመጨረሻው ሰዓት ለአንድነታችን እንዲህ ደጋግሞ ጸሎት ማቅረቡ አንድነታችን ምን ያህል ክብደት እንዳለው ጥቊምታ ይሰጠናል፡፡

"እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ..." መባሉም አንድነታችን በአብና በወልድ መካከል ያለውን ዐይነት መሆን እንዳለበት ያስገነዝበናል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስም፣ "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" በማለት አዟል (ኤፌ. 4፥3)፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን፣ "የመንፈስን አንድነት ፍጠሩ" እንዳልተባለ ነው፡፡ የመንፈስ አንድነት አለ፤ እርሱን ተከባከቡ፤ "ለመጠበቅ ትጉ" ነው የተባልነው፡፡ አንድ ዐይነት አይደለንም፤ ሆኖም አንድ ነን፡፡ ይህንን ነው መጠበቅ የሚኖርብን፡፡ አንድነት አንድ ዐይነትነት አይደለምና ማንነታችን አይደመሰስም፡፡ ሆኖም ሊጠፉና ሊበላሽ የማይችልን ነገር መጠበቅ ሞኝነት መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ የሚጠፋው አይመስለኝም፡፡ አንድነታችን ካልተጠበቀ ይጠፋል ማለት ነው፡፡

የአንድነታችንን ስስነት ከሚያሳዩን ነገሮች ዋነኛው የብሔር፣ የነገድና የቋንቋ ጒዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔሮች፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች (ትርጒማቸውን የሚያውቅ ይኖር ይሆን?) እንዳሉባት ይነገራል፡፡ ይህም ውበታችን እንደ ሆነ እምናለሁ፡፡ ስብጥራችን ጥንካሬአችንም ነው፡፡ የተለያየ ቋንቋ በሚናገሩ ክርስቲያኖች መካከል ያለው ጥምረትና ትብብር ለረጅም ወቅት በመልካምነት ቈይቷል፡፡ አሁን አሁን ግን ይህንን በቅጡ ባለመረዳት በግልጽና በስውር ለጎሳ የማድላት ችግሮች እየታዩ ነው፡፡ ቋንቋም ለልዩነት ሰበብ እየተደረገ ነው (ምን አዲስ ነገር ተገኘ?)፡፡

## ማስታወሻ

1. *The NIV Study Bible* (Michigan: Zondervan Publishing House, 1985), 1815.
2. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 1765፡፡
3. http://en.wikipedia.org/wiki/Memento_mori መጋቢት 2004 ዓ.ም.
4. Philip Yancey, *The Bible Jesus Read* (Grand Rapid, Michigan: Zondervan, 1999), 89.
5. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 24፡፡
6. መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቶኒ ተምረን ወጣን* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 15፡፡
7. R. T. Kendall, *Second Chance* (London: Hodder & Stoughton, 2009), xvii.
8. ዳዊት ጸጋዬ፤ ያልታተመ፡፡
9. ታደሰ ዘወልዴ (ቀኛዝማች)፣ *ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ (አባ መላ)፣ አጭር የሕይወት ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ 1997 ዓ.ም) ገጽ 62፡፡
10. ይህ ጌታቸው ታሪኩ የተባለ ግለ ሰብ ከሚያዘጋጀው "የእግዚአብሔር ክብር" ከተሰኘ ጋዜጣ በተጨማሪ የተለያዩ መጻሕፍቱ ገበያ ላይ መታየት ጀምረዋል፡፡ የመጽሐፎቹ የፊት ለፊት ሽፋን ላይ ስሙን ከጠቀሰ በኋላ፣ "የክብር መገለጥ ሐዋርያና የትንሣኤው መልአክ" በማለት ራሱን ሲያሞካሽ፣ ጋዜጣው ላይ ደግሞ (ቍ. 007 - ነሐሴ 2001 ዓ.ም እትም) "የክብር መገለጥ ሐዋርያና የ7ኛው ሚሌኒየም የትንሣኤና ሕይወት መልእክተኛ፣ የዘላለም ወንጌል መልእክ" በማለት ራሱን ገልጿል፡፡
11. አዲስ አድማስ ጋዜጣ፣ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም፡፡
12. ደረጀ በላይነህ፤ *ብልጥ ጀንበር ... እና የፍቅር ደብዳቤዎች* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም) ገጽ 54፡፡
13. መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቶኒ፣* ገጽ 51-52፡፡
14. ከበደ ሚካኤል፤ *የቅኔ አዝመራ* (አዲስ አበባ፣ 1956 ዓ.ም) ገጽ 153፡፡
15. Mother Teresa, *Come Be My Light – The revealing Private Writings of the Nobel Peace Prize Winner* (London: Rider, 2007), 152.
16. ዝኑ ከማሁ፣ 4፡፡
17. ዝኑ ከማሁ፣ 205፡፡
18. ዝኑ ከማሁ፣ 96፡፡



# ያልተመለሰው የኢየሱስ ጸሎት?

በትውፊት "ጸሎተ ሐሙስ" ተብሎ ይታወቃል፤ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ላይ የምናገኘው ጸሎት፡፡ ይህ ሊቀ ካህናታዊ ጸሎት ብዙ የሚባልለት ቢሆንም፣ ለጊዜው አንዲት ሰበዝ ብቻ መዘዘን እንመልከት፤ አንድነታችንን፡፡ ጌታ ኢየሱስ፣ "ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው" (ቍ. 11)፤ "አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ፡፡ እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ... በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ ..." በማለት ጸልዮአል (ቍ. 21-23)፡፡

ጌታችን በመጨረሻው ሰዓት ለአንድነታችን እንዲህ ደጋግሞ ጸሎት ማቅረቡ አንድነታችን ምን ያህል ክብደት እንዳለው ጥቍምታ ይሰጠናል፡፡

"እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ..." መባሉም አንድነታችን በአብና በወልድ መካከል ያለውን ዐይነት መሆን እንዳለበት ያስገነዝበናል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስም፣ "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" በማለት አዟል (ኤፌ. 4፥3)፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን፣ "የመንፈስን አንድነት ፍጠሩ" እንዳልተባለ ነው፡፡ የመንፈስ አንድነት አለ፤ እርሱን ተከባከቡ፤ "ለመጠበቅ ትጉ" ነው የተባልነው፡፡ አንድ ዐይነት አይደለንም፤ ሆኖም አንድ ነን፡፡ ይህንን ነው መጠበቅ የሚኖርብን፡፡ አንድነት አንድ ዐይነትነት አይደለምና ማንነታችን አይደመስስም፡፡ ሆኖም ሊጠፋና ሊበላሽ የማይችልን ነገር መጠበቅ ሞኝነት መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ የሚጠፋው አይመስለኝም፡፡ አንድነታችን ካልተጠበቀ ይጠፋል ማለት ነው፡፡

የአንድነታችንን ስስነት ከሚያሳዩን ነገሮች ዋነኛው የብሔር፣ የነገድና የቋንቋ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔሮች፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች (ትርጕማቸውን የሚያውቅ ይኖር ይሆን?) እንዳሉባት ይነገራል፡፡ ይህም ውብታችን እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡ ስብጥራችን ጥንካሬአችንም ነው፡፡ የተለያየ ቋንቋ በመናገሩ ክርስቲያኖች መካከል ያለው ጥምረትና ትብብር ለረጅም ወቅት በመልካምነት ቈይቷል፡፡ አሁን አሁን ግን ይህንን በቅጡ ባለመረዳት በግልጽና በስውር ለጎሳ የማድላት ችግሮች እየታዩ ነው፡፡ ቋንቋም ለልዩነት ሰበብ እየተደረገ ነው (ምን አዲስ ነገር ተገኘ?)፡፡

ዋነኛው ሰበብ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ለብሔርና ለቋንቋ ልዩነት የተለ ጠጠ ትኩረት ከሰጠበትና ሁሉን ነገር በዚሁ መነፅር ማየት ከተጀመረበት ወቅት ይመዘዛል:: ያኔ ቤተ ክርስቲያን ያልተዘጋጀችበት ከባድ የቤት ሥራ ነበር የተቀለለባት:: ችግሩ ሲፈጠር ቤተ ክርስቲያን ምንም ዐይነት ነገረ መለኮታዊ ዝግጅት አልነበራትም::[1] የዴሞክራሲ አያያዝና አጠቃቀምም ልምድ አልባ ነታችንም የውጭው ውጥንቅጥ ወደ ውስጥ ሰተት ብሎ እንዲገባ ከፍት በር ሰጥቶታል:: የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ቤተ ክርስቲያን የሚ ገጥሟትን የተለያዩ ችግሮች ለመፍታት ምን ማድረግ እንዳለባቸው የመነጋገር ልምድ ባላማዳበራቸውም በጎሳና በቋንቋ ልዩነቶች የተፈጠሩ ውጥረቶች ድን ገት ንጠውናል::

ስለ ብሔር እና ስለ ቋንቋ ሲነሣ በእግዚአብሔር ድንኳን ሁለት የተወ ጠሩ ጎራዎች ይታያሉ:: የመጀመሪያው በልዩነት ውበት የማያምንና ሁሉን ጨፍልቆ አንድ ወጥ ማድረግ የሚያምረው ነው:: በአንድነት ልብስ አንድ ዐይ ነትነትን ይሰብካል:: የሌሎችን ቋንቋ፣ ባህልና አመለካከት ማክበር ይተናነቀ ዋል:: ሆኖም ክርስትና ቋንቋና ብሔር ዘለል ነው:: የእምነት አንድነትም የብ ሔር አንድነት አይደለም::

"ክርስትና የራሱ ብሔርም ሆነ ቋንቋ የለውም፤ ሁሉም ቋንቋ ለስብከተ ወንጌል ይውላልና::"[2] ከመጀመሪያውም እንዲህ ነበር:: ያኔ ብንገደድማ ኖሮ ዛሬ ዕብራይስጥ፣ ግሪክ ወይም ላቲን ተናጋሪዎች በሆንን ነበር::

ሁለተኛው ጎራ ደግሞ የዘር (የብሔር) ማንነቱን በክርስቶስ ካገኘው ማንነቱ በላይ ለማድረግ የሚቃጣ ገዳዳ አመለካከት አለው:: ስለዚህም በአገ ሪቱ እንደሚታየው ብሔርና ቋንቋ በቤተ ክርስቲያንም ትኩረት እያገኘና ግዘፍ እየነሣ መምጣቱ እውነት ሆነ:: በማስረጃ ላስደግፍ፤

> አንድ የነገረ መለኮት መምህር በአንድ ወቅት በኢ.ወ.ቤ.መ.ኢ ሰሚናርየም ያስተምሩአቸው የነበሩትን ተማሪዎች፣ "በዘራችሁ ወይም በክርስትናችሁ ካላችሁ ማንነት የትኛው ነው በጣም ጠቃሚ?" ብለው ሲጠይቁ፣ ሁለት ሦስተኛው "ዘራችን" ብለው መለሱ::[3]

ተጠያቂዎቹ የነገረ መለኮት ተማሪዎች በመሆናቸው የተሻለ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሚዛናዊ አስተያየት ቢጠበቅባቸውም አቋማቸው የባለ አእምሮ ክርስ ቲያን ሆኖ አልተገኘም ("ቢያጠምቋት ባሰበት!" እንዲሉ):: ምላሻቸው እንደሚ ያሳየን ክርስቶስን ከሁሉ በላይ ቅርሳቸው፣ ንብረታቸው፣ ሕይወታቸው አድር ገው አልያዙትም:: ጎሳቸው ቅርሳቸው ነው፤ ቋንቋቸው ታቦታቸው ነው፤



ሙጭጭ ያሉት ደማቸው ላይ ነው፤ ለክርስቶስ ደም ቦታ የላቸውም:: ምንኛ ኪሳራ ነው!

የከፋው ጥፋት ደግሞ ከሁለቱ አመለካከቶች አንደኛው የሌላኛው መር ዘኛነት ማርከሻ ተደርጎ መታሰቡ ነው፤ በክርስቶስ ደም ያልተዘማመድን ይመ ስል አንዱ ያልተመቻቸውና ያልጣማቸው በሌላኛው ጽንፍ ይጠለላሉ:: ሁለት ስሕተቶች ግን አንድ ትክክል (እውነት) አይሆኑም፤ "Two wrongs don't make right." እንዲሉ::

በተለይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተስፋፋ ያለው ዘረኝነት ባሕር ማዶ በሚኖሩ ወገኖች መካከል እንኳ ጎልቶ ሲወጣ ይታያል:: በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን መድብለ ብሔር ብትሆንም፣ አሁን አሁን አብያተ ክርስቲያናት የብሔር መደብ እየተቀረጸባቸው ነው:: ደጎና መልእክት የያዙ ይመስልም ይህንን ልምሹ አስተሳሰብ በተለያዩ ድረ ገጾች ሲያራግቡት ይስተዋላል::

ይህንን የምናገረው ከምንም ዐይነት የተንሻፈፈ ቅድመ ግንዛቤ በመነ ሣት አይደለም:: ትምህርት እንደ ልብ በሚገኝበት፣ ዴሞክራሲያዊ አገር እየ ኖሩ እንዲህ የሚያስቡ ሰዎች መገኘታቸው አስገራሚና አሳፋሪም ስለ ሆነ ነው (ኢትዮጵያዊ "መልኩ" እንደማይቀየር ማረጋገጫ ይሆን? ወይስ የሰው ልብ ከፋት በትምህርትና በሥልጣኔ እንደማይለወጥ ማሳያ ነው?):: እንደ እኔ እንደ እኔ፣ በአሜሪካም ሆነ በአውሮፓ በአላዋቂነት ለመኖር መወሰን ይመስለኛል::

"Hotel Rwanda" የተሰኘውን ፊልም ስንቶች አይታችኋል? "ሁቱ" እና "ቱትሲ" በተሰኙ ሁለት የሩዋንዳ ብሔሮች መካከል በተፈጠረው ግጭት በ100 ቀናት ውስጥ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በሞቱበት ዘግናኝ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ የተሠራ ፊልም ነው:: እዚያ ፊልም ላይ አንዱ ፈረንጅ ሁለት ጥቊር ሴቶችን ያይና ስለ ተመሳሰሉበት፣ "እኅትማማቾች ናችሁ?" ብሎ ይጠይቃቸዋል:: ግን አንዷ ቱትሲ፣ ሌላኛዋ ደግሞ ሁቱ ነበሩ:: በቃ:: ፈረን ጆቹ እንደ ሆነ እንኳን በብሔራችን በኢትዮጵያዊነታችንም ለይተው ላያውቁን ይችላሉ:: ስለዚህ በአንድ ትልቅ ከረጢት ውስጥ ነው የሚጨምሩን፤ ሁላች ንም አፍሪካውያን ነን:: ፈረንጅ አገር የሚኖሩ ወገኖች ይህንን ሳያውቁ ቀር ተው ነውን?

በቅርቡ በአሜሪካ የተካሄደው ምርጫ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቊሩ ሰው ቁንጮውን ሹመት አግኝተው ወደ ነጩ ቤተ መንግሥት መግባት እንዲልተከለ ከሉ ያሳያል:: የባራክ አባማ ማሸነፍ አሜሪካውያን ከቀለምና ከዘር አሻግረው ማየት መቻላቸውን ያረጋግጣል::

ተመራጩ ፕሬዚዳንትም፣ "ጥቁር፣ ነጭ፣ ስፓኒሽ፣ እስያዊ፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ወጣት፣ አረጋዊ፣ ዴሞክራት፣ ሪፐብሊካን የለም፡፡ የተባበረች አሜሪካ ናት ያለችው" በማለት ከልዩነት ይልቅ አንድነትን መሰበክ ነው የመረጡት፡፡ ኦባማ ይህንን ያሉት ስለ አገራቸው ነው፡፡ እኛ ግን ስለ ወንጌል ይህንን ማለት ሳይሆን ኖሮ ማሳየት እያቃተን ይመስላል፤ ከገቢር የተቃረነ፣ በንባብ ብቻ የሚውተፈተፍ ሕይወት ያታይብናል፡፡ በወንጌል አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ ከምባታ፣ ሃዲያ፣ ሱማሌ ... የሚል ልዩነት የለም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፥32 ላይ ሦስት ዋና ዋና የብሔር ቡድኖችን ለይቶ ያስቀምጣል፤ እነዚህም አይሁድ፣ ግሪክና የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ናቸው፡፡[4] እግዚአብሔር ከልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች አንድን አዲስ ብሔር ፈጠረ፤ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን![5] ኬቪን ኮነር እንደሚሉት፣ "ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ እግዚአብሔር በአዲስ ብሔርነት ያበጃት ፍጥረት ናት፤ ብሔራዊ መነጣጠሎችም ሕልውናቸው በኢየሱስ ክርስቶስ አክትሟል፡፡"[6]

ስለዚህም ራሷን ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ብሔር ልንወስዳት እንችላለን፡፡ የዘር፣ የጾታ፣ የሀብት መጠን ልዩነቶች ቢኖሩም፣ ከልዩነቶቹ ጋር ተያይዘው የሚመጡት ማግለልና መድልዎ መጥፋት አለባቸው፡፡ የጥሉ ግድግዳ በክርስቶስ ፈርሷል፡፡ ትናንት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የተፈጸሙትን ችግሮች በማቆር ዛሬ ወደ እግዚአብሔር ቤት አምጥተን፣ ለነገ ጠብ ማሳደር የለብንም፡፡ አንድ ነን፤ ቤተ ክርስቲያን አንድ "ብሔር" ናት!

ይህንን ኖረን ማሳየት ግን ፈታኝ እየሆነብን ነው፤ አግላይነት እዚህም እዚያም ይታያል፡፡ ጎሰኝነት የእኛ ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪካ ችግር ነው፡፡ የዩጋንዳው ፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቬኒ፣ "What is Africa's Problem?" (የአፍሪካ ችግር ምንድን ነው?) በሚለው መጽሐፋቸው፣ "ጎሰኝነትና ሌሎች የመለያየት ቅርጾች አፍሪካን የሚያዳክሙ አስከፊና ግዙፍ ችግሮች ናቸው" (One of the biggest weakening factors in Africa is tribalism and other forms of sectarianism.) ይላሉ፡፡[7] አብያተ ክርስቲያናትም ከዚህ ነጻ አይደሉም፡፡ ጳውሎስ አላና የተባሉ ኢትዮጵያዊ፣ በርካታ የአፍሪካ ክርስቲያናት፣ አማኝ ያልሆነውን የጎሳቸውን ተወላጅ ከሌላ ጎሳ ተወላጅ ክርስቲያን ይልቅ እንደሚያምኑ ያስረዳሉ፡፡ ይህም፣ በሩዋንዳ ሁቱና ቱትሲ ጭፍጨፋ ላይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ተሳታፊ እንዲሆኑ እንዳደረጋቸው ያብራራሉ፡፡[8]

የኢትዮጵያ ክርስትና በብሔር ጉዳይ እጅጉን እንደ ተሠቃየ ለውጭ ተመልካችም ይታያል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን እንደሚሉት፣ "ክርስትናም በጎሰኝ



ነት እየታመሰ የኢትዮጵያዊነት የክብር ልብሱ እየተቀደደበት ነው፤ እስካሁን ድረስ ጎሰኝነትን ተጋፍጦ በቈራጥነት የተቋቋመው እስልምና ብቻ ነው፡፡"[9] ፕሮፌሰሩ የጠቀሱት ስለ ወንጌላውያን አማኞች ቢሆንም ባይሆንም፣ የወንጌላውያን አማኞች ሁኔታም ከሌላው ብዙም የሚለይ አይመስለኝም፡፡ ከኅብረታችን ይልቅ ብሔራችን ጎልቶ እየወጣ ነው፡፡ ወንጌላዊው ክርስትና የኢትጵያዊነት የክብር ልብሱን እንዲያውም ያወቀ አይመስልም፤ ገና ከመነሻውም፡፡ ታዲያ ጨረቃውያኑ ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን ትተው ሲጓዙ እያየን የእኛ በዘር ጉዳይ ለቅራኔ መትጋት ተገቢ ይሆናል?

የትልቁን እግዚአብሔር ትልቅ መልእክት እንዲሸከሙ የተጠሩ ሰዎች የብሔር መልእክት ለመሸከም ለምን ራሳቸውን እንደሚያወርዱ አላውቅም፡፡ ጥላቻን ለማራገብና ዘረኝነትን ለማስፋፋት ምንም ዐይነት ስፍራ የሌለውን ወንጌል የያዘ ሰው እንዴት የሌላን ብሔር ተወላጆችና ቋንቋ እንደሚወግድም አልገባኝም፡፡ "ስሙን ተሸክመን እንደ ታማኝ አሽከር፣ የጓዳችን ወሬ የቋንቋና የዘር" እንዳለው ነው ዘማሪ ደረጀ ከበደ፡፡ ወንጌል ኢየሱስ ነው፡፡ እናም በመስቀል ከዋለልን ጌታ በቀር ሌላ ትምክሕት ካለን ስለ ክርስትናችን በቅጡ ራሳችንን ልንጠይቅ ግድ ይላል፡፡

የዘር ትምክሕታቸውን የሚገሥጽ ጽሑፍ ሲጻፍም ቍጣቸውን ለመግለጥ በእንግሊዘኛ ደብዳቤ የሚጽፉ ሰዎች አጋጥመውኛል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈን ጽሑፍ አንብቦ ተቃውሞን በእንግሊዘኛ የሚጽፍ አበሻ መገኘቱ "ዘይገርም" ነው፡፡ ይህ ስለ ጸሓፊዎቹ ማንነት - ሓሳቡ ላይ ብቻ ሳይሆን ቋንቋውም ላይ ጥላቻ እንዳላቸው ያሳብቃል፡፡ እንዲህ ዐይነቶቹ ሰዎች ላይ ስለሞን ዴሬሳ የተባለ "ወለጌ" ገጣሚ፣ "ከጎንደር ዋሸንግተን የሚቀርበው ኦሮሚፋ ተናጋሪ ኬክ ይብላ" በማለት በመጽሐፉ ይቀልዳል፡፡[10]

በሰማይ እኛን አስመልክቶ ስለ በጉ ስለ ኢየሱስ የሚዘመር መዝሙር አለ፡፡ "በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋም ሁሉ፣ ከወገንም ሁሉ፣ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥት ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው ..." እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ (ራእይ 5፥9-10)፡፡ ከምን ከምን እንደ ተዋጀን ልብ በሉ፤ "ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋም ሁሉ፣ ከወገንም ሁሉ፣ ከሕዝብም ሁሉ" መሆኑን መዝሙሩ ፍንትው አድርጎታል፡፡ በጌታ ዳግም መምጣት የሚጀመረው መጻኢው ዘመንም ለዘር ልዩነት ቦታ አይመድብም፡፡

በላይ በሰማይ ያሉት የእኛን መዋጀት አይተው ይደሰታሉ፤ ይዘምራሉ፡፡ የተዋጀነው እኛ ደግሞ፣ ከመዋጀታችን በፊት ወደነበርንበትና ወደ ተውነው ቤት ለመግባት ቁልቁል እናያለን፡፡ የተዋጀነው፣ የመንፈስ አንድነታችንን

ለመጠበቅ መትጋት አቅቶን የዕውር ድንብራችንን በዘር እንራኮታለን:: የእኛን መዋጀት ያዩት ግን በእኛ መዋጀት በሰማይ "አዲስ ቅኔ ይዘምራሉ"::

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘርንና ቋንቋን በሚመለከት ምንም ጥፋት አልተሠራም ብሎ መካድ የሚቻል አይመስለኝም:: ትናንት የተዘሩ እንክርዳዶች ናቸው ዛሬ እየበቀሉ ያሉት:: ሰዎች ቅስናን ለመቀበል ስም ለመቀየር ይገደዱ የነበረበት አሳፋሪ ዘመን ነበር:: ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ግን የዚህ የውድቀት ታሪክ ተሳታፊ አልነበሩም:: ስለዚህ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያለውን ታሪክ ጎትቶ እዚህ ማምጣት ኢርትዐዊ ይሆናል:: ጠብ ጫሪነትም ነው::

እንዲያውም በአገራችን የወንጌላውያን ክርስትና ታሪክ መነሻ ደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ እንደ ሆነ አስባለሁ:: ወደ አንዳንድ የደቡብ ክልል ዞኖች ሲኬድ አብዛኛው ሰው አማኝ ሆኖ የሚገኝባቸው ሁኔታዎች ጥቂቶች አይደሉም፤ አንዳንድ የኦሮምያ አካባቢዎችም ተመሳሳይ ነው:: ሰሜን ኢትዮጵያ ግን ከዚህ እጅግ ይለያል:: እዚያ አካባቢ በፊትም የኦርቶዶክስ ክርስትና የተስፋፋበት ስለ ነበረ የወንጌላውያን ክርስትና ዘግይቶ ነው የገባው:: "ክርስቲያን ወዳልሆነው ሕዝብ ሄዳችሁ ስበኩ" በማለት ሚሲዮናዊያኑን ነገሥታቱ ከዚያ ያርቋቸው እንደ ነበር ይታወቃል፤ የመስበኪያ ፈቃድም አይሰጧቸውም ነበር:: ታዲያ ደቡብና ምዕራብ አካባቢ ያሉት አማኞች በወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገለል እንደ ደረሰባቸው ሊቆጥሩ የሚችሉበት ታሪክ የሚፈጠረው እንዴት ነው? እነርሱ ጀማሪ፣ እነርሱ መሪ በሆኑበትና፣ እነርሱ በስፋት በያዟቸው ቦታዎች ይህ እንዴት ሊከሰት ይችላል?

ይህን አመለካከት የሙጥኝ ያሉ ወገኖች ትናንት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያጋጠማቸውን መገለል ያወግዛሉ፤ የእነርሱ የዛሬ ሥራ ግን ከዚያ የተሻለ አይደለም:: የቂም እሹሩሩአቸውን አሳድገውታል:: ስለዚህም ከጥበቃ ሠራተኛ እስከ ቤተ ክርስቲያኒቱ ፕሬዚዳንት ድረስ በአብዛኛው የአንድ ብሔር ተወላጅ ቦታ የሚይዝባትን ቤተ ክርስቲያን እያየን ነው:: እነዚህ ሰዎች ኀላፊነት ላይ ባሉባቸው ቦታዎች ሁሉ ከዚህ "ዘር" ያልተወለደ ሰው ርትዐዊ በሆነ መንገድ ሥራ ለማግኘት ይቸገራል:: በወንጌላዊነት የምትገኘው ገንዘብ እንኳ ገንዘብ ሆና፣ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ለመሆን ከጥሪ ይልቅ ዘር ሚዛን የሚደፋባቸው አብያተ ክርስቲያናትም አሉ:: መዳን ምን ማለት ነው? መንፈሳዊነትስ? በውስጥ ያለው ሁኔታ እንዲህ ከጨለመ፣ ውጭው ምን ሊሆን ነው? ለመድኀኒትነት የታሰበው ኪኒን መርዝ ሆኖ ሲገኝ ምንድን ነው የሚባለው?

በአንጻሩ ደግሞ፣ የመኻል አገር ሰው ካልሆነ እግዚአብሔር ቢጠቀምበት እንኳ፣ "እንዴት በዚህ ተብታባ እግዚአብሔር ይናገራል?" የሚሉ ዕብሪተ



ኞችንም በቤተ ክርስቲያን እናያለን:: ወንዛዊነት ሥር ሰዶ፣ ከልልተኝነት ተንሰራፍቶ፣ ዘረኝነታቸውን በክርስትና ጭምብል የሸፈኑ ሰዎች ስለ በዙ፣ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉም የራሱን ሰውና የራሱን ጎጥ ብቻ ለይቶ ለመጥቀም፣ ቋንቋውን ለማግነን ይውተረተራል:: ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ ምን ይለን ይሆን?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌል ሊሰብክ በሄደበት ሁሉ "በዕብራይስጥ ካልሰበክሁ" አላለም:: ጥረቱ የራሱን ቋንቋ ማግነን ሳይሆን፣ ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል ሰምተው እንዲያምኑና ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ነበር:: በበዐለ አምሳ ቀንም መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ ቋንቋዎችን ነው የተጠቀመው፤ ያውም በእስራኤል መዲና፣ በኢየሩሳሌም (የሐዋ. 2፥8)::[11] እነዚህ ሰዎች በጋራ የሚሰሙት የአካባቢው ገናና ቋንቋ አልነበረምን? መንፈስ ቅዱስ ግን ከግሪክ፣ ከዕብራይስጥና ከአረማይስጥ ይልቅ በየቋንቋቸው ሊያነጋግራቸው መረጠ::[12] አፍ መፍቻ ቋንቋ ለወንጌል ተሐድሶ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ታሪክም ምስክራችን ነው:: ለምሳሌ ልበ ብርሃን የሆነው ኦናሲሞስ ነሲብ ከ100 ዓመት በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ በመተርጐሙ በምድራችን ለወንጌል መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል::[13] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ የአገራችን ቋንቋዎች የሚተረጕመውም ለዚህ ነው:: ሰዎች ሁሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወንጌል ሲሰሙ ውጤቱ ያምራል::[14] ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናት "የቋንቋ ፖሊሲ" ቢኖራቸው ተገቢ ነው::

በሁለቱም ወገን ያሉ ጽንፈኞች እንደሚሉት ሳይሆን፣ የተናጋሪዎች ብዛት እየታየ በተለያዩ ቋንቋዎች መንፈሳዊ ጉባኤዎች መዘጋጀታቸው ይጠቅማል:: በአዲስ አበባ እንግሊዝኛ ቋንቋን የሚጠቀሙ የአበሻ አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸው ይታወቃል:: ሆኖም፣ ሰዎች በሚያውቁትና በሚረዱት ቋንቋ ወንጌል ከሚሰሙና ከሚጸኑ ይልቅ "እኛ በማይገባን ቋንቋ አይሰበክም" በማለት የሚሟገቱ እልከኞችም በመካከላችን አሉ:: ይህም የዕርቀ ሰላሟን መንበር የአምባጓሮ ዐውድማ አድርጓታል:: መጽሐፉ እንደሚለን፣ "እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ጽንፈኝነትን ያስወግዳል" (መክ. 7፥18 - ኢ.መ.ት):: ይህ ጉዳይ ተዛንፎ ወደ ልዩነት ቢያመራ ጠላት እንጂ ቤተ ክርስቲያን እንደማትጠቀም እንዳናይ ሆነናል:: ምኒልክ አስፋው እንደሚናገሩት፣

> ከሁሉ የሚያስደንቀው ወንጌልን ለመስበክ ድንበር አቋርጠውና ወንዝ ተሻግረው ወደ ሌላ ሕዝቦች የሚሄዱ ቤተ እምነቶች በሚሄዱበት አካባቢ እንዲመሩ የሚፈልጉትና እንዲነገርም የሚሹት የገዛ ሰዎቻቸው ቋንቋ መሆኑ ነው:: በዚህ ሓሳብ የተተበተቡ አብያተ ክርስቲያናት የኋላ ኋላ ለአንድነታቸውና ለምስክርነታቸው ጠንቅ መሆናቸው አይቀርም::[15]

በአገሪቱ መዲና ቢኖሩም አማርኛ ቋንቋን የማይሰሙና የማይናገሩ
ሰዎች እንደማይጠፉ ግልጽ ነው፤ የእነዚህ ሰዎች አስፈልጎት መሟላት እንዳለ
በት አይካድም:: በሌላኛው አቅጣጫ ደግሞ የአገሪቱን የሥራ ቋንቋ ከማንም
በተሻለ ማቀላጠፍ እየቻሉ ለቋንቋቸው ክብር ሲሉ ብቻ ቤተ ክርስቲያንን የሚ
ያምሱና የሚከፍሉ ልበ ሸውራሮችም አሉ:: እነዚህ ሰዎች ሊገነዘቡ የሚገባ
ቸው ቤተ ክርስቲያን የብሔር ማንነት ማስፋፊያና መጠበቂያ ማዕከል አለመሆ
ኗን ነው:: የክርስቶስ ንግሥና መግለጫ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን የእነርሱ
ቋንቋ ካልነገሠ፣ ፍርድ ቤት የሚካሰሱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማየት እጅግ
ያምማል፤ ያሳፍራልም (ማፈር ቀርቶ ይሆን?):: ከወንጌሉ መልእክት ይልቅ
ለቋንቋቸው ብቻ ትኩረት የሚሰጡ ሰዎችን እግዚአብሔር፣ "ጎሽ፤ አበጃችሁ"
አይላቸውምና ከመንገዳቸው ቢመለሱ እንዴት ባማረባቸው! (የፍርድ ቤት
ውሳኔ መች ማግኘት የእግዚአብሔርን ቡራኬ ማግኘት ሆነና!?)

በክርስቶስ ድንኳን ጎሰኝነትን የሚያራምዱ ሰዎች የሚናገሩት ልክ
ጠባብ ዕይታ እንዳለው ፖለቲከኛ ነው:: የእነርሱ "ወገን" የሆነ ምዕመን
የእነርሱ "ወገን" ካልሆነው አማኝ ጋር ቆሞ ሲያወራ ሲያዩ ደማቸው ይንተከ
ተካል:: በክርስቶስ ደም የተገኘውን አንድነትም ሆነ ምሕረትን የማያውቁ፣
ቂምንና ቁርሾን አዝለው ይኖራሉ:: የክርስቶስ መሆናቸው አይታወቅም:: መዳ
ናቸው በምን ይሆን ነው የሚታወቀው?

አሁን አሁንማ የትኛዋ ቤተ ክርስቲያን የየትኛው ብሔር እንደ ሆነች
ምደባ ወደ መስጠት ተደርሷል:: ጌታን የመሰከርኩለት ሰው ጉራጌ ከሆነ የምወ
ስድበትና ትግሬ ከሆነ የምወስድበት አጥቢያ ይለያያል ማለት ነው:: በወንጌል
ስብከት የዳኑት ከምባታና ሃዲያም ቢሆኑ ያው ነው፤ ሌላኛው ቦታ ነው የምወ
ስዳቸው:: "ጎጃሜዎቹ ጋ" እና "የሶዶ ቤተ ክርስቲያን" ሲባልም ይደመጣል::

አብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙት የአካባቢው ተወላጆች በሚበዙበት
ሰፈር ቢሆን ኖሮ ምንም ማለት አልነበረም:: ነገዳውያኑ ከሩቅ እየተጠሩ የሚ
ሰባሰቡበት ከሆነ ግን ሌላ ጉዳይ ነው:: ችግሩ የቋንቋ እንዳልሆነ የሚያስታው
ቀው ቋንቋውን ቢችሉም፣ የዚያ ብሔር ተወላጅ ባለመሆናቸው ብቻ ሞገስ
ያጡና ገሸሽ የተደረጉ ሰዎች መኖራቸው ነው:: ለመሆኑ ክርስቶስ በዳኑ ሰዎች
መካከል ዘውጌ ብሔረተኝነትን (Ethnic Nationality) ያራምድ ነበርን? አንድ
ወቅት ከሳውዲ አረቢያ የመጣ መጋቢ አግኝቼ ነበር:: እዚያ ኢትዮጵያውያንና
ኤርትራውያን ያለ ምንም የቋንቋ ችግር በአንድነት የጉባዔ አምልኮ እንደሚያደ
ርጉ ሲነግረኝ ተገርሜአለሁ፤ ምናልባት በመንግሥት በኩል በይፋ የሚካሄ
ደው ስደት ሊሆን ይችላል አንድ ያደረጋቸው:: እኛም አንድነታችን እንዲጠ
በቅ ስደት እዚህም ተመልሶ እንዲመጣ (እንዲጠናከር) እንናፍቅን?



የ"ብሔር፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች" ባህል ቋንቋና ማንነት መከበር እን
ዳለበት የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ይደነግጋል:: አንዱ ብሔር ከሌላው
እንደማይበልጥም ይታወቃል:: በነጻነት የመደራጀት መብትም ዕውቅና ተሰጥቶ
ታል:: ሐሳቤ ግን ከእነዚህ መብቶች ጋር የተገናኘ አይደለም:: ይልቅዬስ የአ
ሁኑ ጩኸት፣ "ዘረኝነትን በወንጌል ለውሳችሁና ሸፍናችሁ አትስጡ፤ ከክርስትና
ጋር አትቀይጡ፤ ወንጌላችንን አትበርዙብን" የሚል ነው::

ዛሬ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ይህ ነቀዝ ውስጥ ውስጡን የበላት
መሆኑ ያሳስባል:: ትናንትና ለብሔራቸው ነጻነት ሲታገሉ የነበሩ ሰዎች፣ ዛሬ
እንደ ወንጌል አርበኛ እየተቈጠሩ ታሪክ እንደ ገና ሊጻፍ የሚሞከርባት አገር
ናት - ኢትዮጵያ:: የብሔርና የቋንቋ ትግልን ከወንጌል ጋር ካስታከክነውና
ይህም ወንጌልን ከበረዘ ስሕተት ነው፤ ሰውን በጎሳ እንጂ በክርስቶስ ማወቅ
አለመቻል ኑፋቄም ነው:: ለጎሳ መሞት ሌላ፣ ለወንጌል መሞት ሌላ! ምን አገና
ኛቸው? የጎሳና የጎጥ ትግል ራሱን ችሎ የማይቆም ይመስል ከወንጌል ጋር
ጥግግቱ ለምን አስፈለገ?

ትልቁ ችግር የቤተ ክርስቲያን አንዳንድ መሪዎች መሆኑን ዛሬም አምና
ለሁ:: በቀጥታ ተሳታፊ በማይሆኑበት ጊዜ እንኳ ነገሮች ሲበላሹ እያዩ እንዳ
ላዩ አርምሞን (ዝምታን) መርጠዋል:: ነገሩ ሥር ስለ ሰደደም ብዙ ምዕመናን
ተሰናክለውበታል:: የአማራን ወንድ ካልሆነ እንደማታገባ የምትምልና የምትገ
ዘት አማራ፣ ኦሮሞ ሴትን ካልሆነ ማግባት የማይሻ ኦሮሞ፣ ጉራጌዋን ካላገኘ
ሌላ ሴት ሴት የማትመስለው ጉራጌ፣ በቤተ ክርስቲያን መገኘታቸው ብርቱ
ኪሳራ ነው፤ ለእግዚአብሔር ቤት:: የዚህ ምክንያቱ የብሔር ጥላቻ መሆኑ ላይ
እንጂ የባህል ግጭትን በመሸሽ ይህን የሚፈጽሙም እንደሚኖሩ ግልጽ ነው::
ብርቱ የቤተ ሰብ ተጽእኖ ያለባቸው ወገኖች መኖራቸውንም መዘንጋት የምን
ችል አይመስለኝም::

አንዳንድ ክርስቲያኖች በአካባቢ ልማትና ዕድር፣ ሌሎቹ ደግሞ ወንጌል
በማድረስ ስም በዘውግ ላይ የተመሠረቱ ቡድኖች አባላት ሆነዋል:: ይሄም
ይሁን ይባል፤ ነገር ግን አጠገባቸው ያለውን አማኝ ወገናቸውን የሚያገልሉ
ከሆነ አደጋ ላይ ነን:: ጓደኝነትን ለመመሥረት ብሔርን የምንጠይቅ ከሆነ ተሳ
ስተናል:: የክርስቶስ ተከታይ ከሆነው የሌላ ነገድ ተወላጅ ይልቅ የክርስቶስ
ተከታይ ያልሆነው የራሳችን ነገድ ተወላጅ የሚቀርበን ከመሰለን ወንጌሉ ገና
አልገባንም::

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከይሁዳ ነገድ መወለ
ዱን እናውቃለን:: ሆኖም ስለ እስራኤል እንጂ ስለ ይሁዳ ሲያስተምርና ሲቀሰ

ቅስ አልተሰማም:: ለነገዱ አንድም የተለየ ትኩረት አላደረገም:: ሳምራዊቷን ሴትም ሲያናግር የባህልን፣ የጾታንና የልማድን ድንበር ተሻግሮ ነው፤ እናም ወንጌል እነዚህን ድንበሮች መሻገር ካልቻለ ወንጌል አይደለም፤ ወንጀል እንጂ!!

ሐዋርያው ጳውሎስም ብንያማዊ ነበር:: እርሱም ግን ስለ እስራኤል መዳን እንጂ ለብንያማውያን የተለየ ሸክም አልነበረውም:: እንዲያውም ይህንና ሌሎቹን በሥጋ የሚታመንባቸውን ነገሮች ይዘረዝርና መደምደሚያው ተቃራኒ ነው፤ "ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ" ይላል (ፊልጵ. 3፥4-7):: ከራሱ ዐልፎም፣ "ከንቱ ከሆነ ክርክርና ከትውልድ ሐረግ ቈጠራ ... ራቅ" በማለት ወዳጁን ይመክራል (ቲቶ 3፥9 - አ.መ.ት):: ታዲያ ምነው እኛስ የዘር ትምክሕታችንን እንደ ጉዳት መቍጠር አቃተንሳ?

ሐዋርያት ሁሉ አይሁዳውያን (እስራኤላውያን) ናቸው:: በኢየሩሳሌሙ ጉባዔ ግን፣ አሕዛብ ወደ ክርስትና ሲመጡ የአይሁድን ወግና ባህል የመከተል ግዴታ እንደሌለባቸው ወስነዋል፤ ይህንንም፣ "እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል" በማለት ነው የገለጹት (የሐዋ. 15):: ለአይሁዳዊ ማንነታቸው መከበር ተሟጋቾች አልነበሩም፤ ሌሎችንም ወደ እነርሱ ለማምጣት አላስገደዱም::

ሰዎች ሁሉ በአርአያ ሥላሴ ስለ ተፈጠሩ በዘራቸው ሳይሆን፣ በማንነታቸው ልንቀበላቸው ግድ ነው:: አማኞች ሲሆኑ ደግሞ በተጨማሪ በክርስቶስ ደም አንድ ቤተ ሰብ መሆናችንን ማስታወስ አለብን:: ታዲያ ወንጌልን ያህል ከሁሉ የላቀ የምሥራች በብሔር ደረጃ እንዴት ይነስ? በዚህ ሁኔታስ አንድነታችን እንዴት ይጠበቃል?

ወንጌል ግድ በአገር ደረጃ መታሰብ አለበት ለማለትም አልፈልግም:: በሶማልያም ይሁን በኢንዶኔዥያ ወንጌል እንዲደርስ መጸለይ ይኖርብናል:: አጠገቤ ካለው በጌታ ያላመነ ወንድሜ ይልቅ፣ በጌታ ካመነ ጀርመናዊ ጋር የሚኖረኝ ኅብረት ዘላለማዊ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ:: ምክንያቱም፣ "በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነው" (ሮሜ 10፥12):: "አይሁድ ብንሆን፣ የግሪክ ሰዎችም ብንሆን፣ ባሪያዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል:: ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል" (1ቆሮ. 12፥13)::

ይህ ማለት ግን ክርስቲያን በመሆኑ ብቻ ግሪካዊ ግሪካዊነቱን፣ አይሁዳዊም አይሁዳዊነቱን ይተዋል ማለት አይደለም:: ግሪካዊው አይሁዳዊ፣ አይሁዳዊውም ግሪካዊ አይሆኑም:: እንዲህ የሚያስቡ ሰዎች ካሉ ተሳስተዋል:: ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው



የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" ብሏል (ገላ 3፥28):: ይህን ሲል ግን፣ የጾታና የዘር ልዩ ልዩነት እንዲጠፋ እየተመኘ አይደለም:: በጾታና በዘር ልዩነት ምክንያት የሚደረግን (ጭፍን) ጥላቻ፣ ማግለል፣ መድልዎ ተቃወመ እንጂ ልዩነቱ ተጨፍልቆ አንድ ይውጣው አላለም::[16]

አንዳንዶች ለዚህ ኋላ የቀረ ድርጊት፣ ለዘር ልዩነት መጽሐፍ ቅዱስን ሰበብ ያቀርባሉ:: በተለያየ ወቅት ቅኝ ገዢዎችና ጨካኞች በዚህ መንገድ ራሳቸውንና ብዙዎችን ሲያታልሉ ነበር:: እዚህም ይሄን ድውይ ድርጊታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማስታከክ የሚፈልጉ አሉ:: በፍጹም ግን እውነት አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናየው በሰዎች መካከል ያለው ልዩነት፣ "የተመሠረተው በሃይማኖት ልዩነት ላይ እንጂ በዘር ወይም በመደብ ልዩነት ላይ አልነበረም::"[17] እስራኤል ከሌሎች የምድር አገራት ተለይታ የምትታየው በእግዚአብሔር ላይ ባላት እምነት፣ በሃይማኖቷ እንጂ በደሟ ጥራት አልነበረም:: መጽሐፍ ቅዱስ የዘር ልዩነትን ማራመጃ መሠረት የለውም::

እግዚአብሔር ለ"ብሔርና ብሔረ ሰቦች" መምጣቱን አላውቅም፤ ለሰዎች ነው የመጣው! ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን እንጂ ብሔርን አልፈጠረም:: ለመሆኑ "ብሔር ብሔ ረሰብ" የሚባል ፍጥረት አለ? በስንተኛው ቀን ነው የተፈጠረው? የት ነው የሚኖረው? የቤት ቍጥሩን ታውቁታላችሁ? የየት ቤተ ክርስቲያን አባል ነው? መቼ ነው የተጠመቀው? የቤተ ክርስቲያን ሽምግልናስ ተመርጦ ይሆን? እግዚአብሔር የፈጠረው ሰውን ነው:: ልጁንም የላከው ሰውን ለማዳን ነው:: አሁንም በልጁ ከሚያምኑ ሰዎች አንድን አዲስ ሰው ለመሥራት ይፈልጋል::

ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፍሏልን? ወንጌል አማራ ነው፣ ትግሬ? ወይስ ኦሮሞውም ወላይታውም የየራሱ ክርስቶስ አለው? ወደድንም ጠላን አንድ ነን:: እግዚአብሔር ሁለት ዐይነት ሰዎችን ብቻ ነው የሚያውቀው፤ በክርስቶስ የሆኑና ያለ ክርስቶስ የሆኑ:: በጾታ፣ በዘር፣ በኤኮኖሚና በኑሮ ደረጃ የተለያየን ብንሆን እንኳ መከፋፈል አልተፈቀደልንም:: አካሉ ተነጣጥሎ የተበታተነ ሰው በሕይወት መቈየት ይችላልን?

እኛ የምናምነውና የምንከተለው ክርስቶስ፣ "በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ" እና "አንድ አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ፣ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፣ ጥልንም በመስቀል ገድሎ" ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀን ጌታ ነው (ኤፌ. 2፥15-16):: ለልዩነት የሚሆን አንዳችም ድጋፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ አናገኝም:: ለመሆኑ በመንግሥተ ሰማያትስ በየብሔራችን ቀበሌ ተዘጋጅ

ቶሎን ነው እንዴ የምንኖረው? አብረን የምንኖር ከሆነ ይሄ ሁሉ መናናቅ፣ መቈ ሳሰልና መጠላላት ለምን አስፈለገ?

በዚህ በሠለጠነ ዘመን እየኖርን በብሔር ደረጃ ብቻ ማሰቡ ሳይንሳዊም አይደለም:: ብሔር የሚባለው ነገር መሞቱ አይቀርም፤ እየሞተም ነው:: በዴ ሞክራሲ፣ በንግድ፣ በኪነ ጥበብ፣ በስፖርት፣ በቴክኖሎጂ ወ.ዘ.ተ ... የተፈጠ ረው ሉላዊነት (globalization) እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አዳጊ አገሮች ሳይቀር የመጨረሻውን የብሔር ሞት እያፋጠነው ነው:: ትልልቅ የብሔር ድርጅቶች እየተሰነጣጠቁና እየተዳከሙ፣ የኅብረ ብሔራዊ ድርጅቶች ደጋፊም እየበዛ መሄዱ አይቀሬ ነው::

እንዲያውም በአንድ ጎኑ ችግሩ ያለው የከተሜነት መስፋፋት ላይ ነው:: ከተማ አካባቢ ያሉ ሰዎች (አማኞችን ጨምሮ) ከብሔረ ሰባዊ ቡድን ይልቅ ግላዊነትን ያስቀድማሉና ጎሳውያኑ ይህንን ነው እንደ ሥጋት የሚቈጥ ሩት:: ሰዎች፣ ግለ ሰብ ከብሔረ ሰብ እንደሚቀድም ማወቅ ሲጀምሩ፣ በስፋት ተቀባይነት ያለውን ባህል ማስተናገድ፣ በቡድን ከማሰብ ይልቅ በግላቸው ማሰ ብን ይመርጣሉ:: በስፋት የሚነገር ቋንቋን መጠቀም ይመቻቸዋል:: በክልል ከተሞች አማርኛ፣ አዲስ አበባ ደግሞ ፈረንጅኛ ተወዳጅነት እያገኘ የመጣው ለዚህ ይሆን?

ታዲያ መሠረቱ እየተናጋ ባለና ለመሞት አንድ ሐሙስ በቀረው የብ ሔር ማንነት ላይ ክርስትናን ለመገንባት መሯሯጡ ምን ይሉት ኋላ ቀርነት ነው? ወንጌልን እዚህ ላይ ከገነባነው ድቡሽት (የአሸዋ ክምር) ላይ እንደ መሠረ ትነው ነው የሚቈጠረው:: ይልቁኑ ግለ ሰባዊ ማንነትን ከወንጌል ጋር እንዴት እንደምናጣጥመው ማሰብና መዘጋጀቱ ይጠቅመናል:: ምክንያቱም ከተሞች አካባቢ እንደሚስተዋለው ግለ ሰባዊነት ሊነግሥ አሰፍስፎ ተራውን እየጠበቀ ነው:: ይሄን ማስቀረት ስለማንችል በብሔር፣ በጎሳና በነገድ ተቧድነን ከምን ፋጠጥ ቀጣዩ ሥጋታችን ላይ ብናተኵር ይበጃል::

ክርስትና ባህላዊም ዘመናዊም ባይሆንም የአሜሪካ ሥልጣኔና የአው ሮፓ ሕዳሴ (Renaissance) መሠረት መሆኑን መካድ አይቻልም:: የእኛም ክርስትና የአገራችን ሕዳሴ መሠረት እንዲሆን ከፈለግን ከዘውጌ ብሔረተኝነት መላቀቅ አለብን:: ብሔረተኝነትን በኢትዮጵያዊነት መነፅር በማየት አይደለም ይህንን የምናገረው፤ ብሔረተኝነትን ከክርስትና አኳያ በማየት እንጂ:: ብሔረተ ኝነት ላይ የተመሠረተ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ በእሳት ተፈትኖ ዋጋ ሊያሰጠን ይቅርና ራሱ ፈራሽ ነው:: ኋላ ቀርነትም ነው:: ያለነው በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑንም እንዘንጋ! የዘመን ጅራት ለመሆን ካልፈለግን በቀር የብሔር



ሙግት ውስጥ ምን ከተተን? በሚሞት ነገር ላይ መሯሯጡን ለዘውጌ ፖለቲከ ኞች እንተውላቸውና ንጹሑንና እንከን የለሹን ወንጌል ብቻ ዓላማችን እናድ ርግ:: ወንጌል ሞትን ይሻገራል፤ ሞትንም ያሻግራል!

በመሠረቱ ፖለቲከኞቹም ለግል ጥቅማቸው በማሰብ ካልሆነ በቀር የጎሰኝነት እንቅስቃሴ ለአገራችንም የሚሰጠው ዘላቂ ፋይዳ የለውም:: የዘር ፍጥጫ፣ የብሔር ሽኩቻ አይረባንም፤ አደገኛ አቅጣጫ ነው:: ሟቹ የሞዛም ቢክ መሪ ሳሞራ ማሼል የጎሰኝነት እንቅስቃሴን "የጸረ-አፍሪካውያን ኀይላት ጠቅላይ አዝማች" (the commander in-chief of anti-African forces) ይሉታል::[18] ታዲያ ጎሰኝነት ጥቅሙ ምን ላይ ነው? የትኛዋንስ አገር አሳድጓል? ለቤተ ክርስቲያንስ ምን ጥቅም ያስገኝላታል?

ይህ ወጥመድ ትልልቅ የሚመስሉ አገልጋዮችን ሳይቀር ሲጠልፍና ሲያ ንኮታኩት አይተናል:: ስለዚህ መንቃቱ ይሻለናል:: ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን ከሚመለከተው ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር የተያያዘውን ችግር ለመፍታት ነገረ መለኮታዊ ጥረቶች መደረግ አለባቸው:: ኮንፈረንስና ድግስ አድማቂዎች ያል ሆኑ፣ ከዘር ባሻገር የሚያዩ፣ መድልዎ የማያደርጉ፣ ደቀ መዝሙር ሆነው ደቀ መዝሙር የሚያፈሩ መሪዎች ያስፈልጉናል:: አሊያ፣ "ሩቅ አሳቢ፣ ቅርብ አዳሪ" እንሆናለን:: ምክንያቱም፣

> አዲስ ኪዳን በዘርና በብሔር ስም የሚደረገውን መድልዎ እንደ ንዋጋ እንጂ እንድናስተጋባ ዕድል አይሰጠንም:: ማንኛውም መድልዎ ለክርስቲያኖች ውጉዝ ከመ አርዮስ ነው:: ዘረኝነትና ብሔርተኝነት ኑፋቄ ነው:: ... በዘመኑ መጨረሻ ላለነው ለእኛ ግን በዚህ እኩይ ሐሳብ ተተብትቦ መገኘት ከቶ የማይታሰብ ነው:: ... ይህን የማናደርግ ከሆነ ግን የወንጌሉን ክቡር መልእ ክት እየረገጥን ነው::[19]

አስቀድመን እንዳልነው፣ "እኔና አብ አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ" በማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸልዮልናል:: አንድነታችን ማነጻጸሪያ አለው፤ በአብና በወልድ መካከል ያለው አንድነት! የመንፈስ አንድነታችን እን ዲህ እንዲሆን፣ ትስስራችንና ኅብረታችን ይህን እንዲመስል ይጠበቃል፤ ጸሎ ቱም ያስፈለገው ለዚህ ነው:: የምናየው ግን ተቃራኒውን ይመስላል:: ለነገሩ፣ ጸሎቱ እንዴ ተመልሶ የሚያበቃለት ጸሎት ነው እንዴ? ወይስ የየዕለቱ ርምጃች ንና ድርጊታችን ላይ የተመሠረተ፣ በየጊዜው የሚመለስ ጸሎት ነው? ታዲያ በእኛ ዘመን የዚህ ጸሎት ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን?

## ማስታወሻ


1. Paulos Olana Djini, "The Church in a Divided World: Ethnic & Liniguistic Diversities and the Challenge of the Chruch in Ethiopia". *Contemporary Theological Perspectives* (Addis Ababa: Mekane Yesus Seminary, June 2011), 66.
2. ዝኔ ከማሁ፣ ገጽ 83።
3. Bo Eriksson, et al, *The Gospel of Restoration: Experiences From a Field Study in Ethiopia 1998* (Uppsala: Swedish Institute of Missionary Research, 1999), 71.
4. Paulos, "The Church", 69.
5. ዝኔ ከማሁ፣ ገጽ 85።
6. J. Kevin Conner, *The Church in the New Testament* (Portland: Bible Temple Publishers, 1989), 11.
7. Tokunboh Adeyemo, *Is Africa Cursed? A Vision for the Radical Transformation of an Ailing Continent* (Nairobi: WordAlive Publishers, 2009), 31.
8. Paulos, "The Church", 95.
9. መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቱኒ ተምሪን ወጣን* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 129።
10. ሰለሞን ዴሬሳ፤ *ዘበት እልፊቱ* (አዲስ አበባ፣ 1991 ዓ.ም) ገጽ 11።
11. Paulos, "The Church", 85.
12. ዝኔ ከማሁ።
13. ሰለሞን ጥላሁን፣ *ሥምረት ገ/ማርያም፤ ደማቆቹ /ፀሐያተ ሌሊት/* (አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም) ገጽ 21-37።
14. *ቃሉ ይናገር፡* ለ2004 ዓመታዊ ጉባዔና የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን አከባበር ልዩ እትም (አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር) ገጽ 5፣ 16።
15. ምኒልክ አስፋው፤ *ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፡ ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች* (አዲስ አበባ፣ 1999 ዓ.ም) ገጽ 70።
16. Paulos, "The Church", 70.
17. ሮበርትሰን ማኩልከን (ተርጓሚ ገበየሁ አየለ)፤ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ ምግባር፡ የመግቢያ ሐሳቦች* (አዲስ አበባ፣ ኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 388።
18. Adeyemo, *Africa, 31.*
19. ምኒልክ፤ *ክርስቲያናዊ፣ ገጽ 93።*




# አቋም የለሽ አቋም

ማንዴላን ሲያስብ በአፍሪካዊነቱ የማይኮራ ማነው? እኚህ ሁሉ የሚያከብራቸው ትልቅ ሰው፣ ትልቅ ከስተት ናቸው። ከማንዴላ ብዙ መማር ይቻላል። ዓለም ማንዴላን ሲያጣ የተቃረበበት አንድ ወቅት ግን ነበር፤ የመጀመሪያ ሚስታቸው ኤቭሊን ከምትከተለው ሃይማኖት የተነሣ።

ኤቭሊን *የይሆዋ ምስክር* ሃይማኖት ተከታይ ነች፤ ይህ ሃይማኖት ደግሞ ለፖለቲካ ትግል ቦታ አልነበረውምና አገርን ማገልገል እግዚአብሔርን የማገልገል ተቃራኒነቱ ነበር የሚታያት። ማንዴላ የትግሉን አስፈላጊነት ሊያስረዱት ሲሞከሩ፣ የሃይማኖተኝነትን ጠቀሜታ ልታስረዳቸው ትሞክራለች። ማንዴላ አገሪቱን እያገለገሉ መሆኑን ሊያሳምኗት ሲሞክሩ፣ አምላክን ማገልገል እንጂ አገርን ማገልገል ዋጋ እንደሌለውና እንደማያስፈልግ ትነግራቸዋለች። ማንዴላ ልጆቻቸውን ስለ ፖለቲካ ትግል ሲያስተምሩ፣ *የይሆዋ ምስክሮችን* በራሪ ጽሑፎች እንዲያሰራጩ ነበር እርሷ የምትፈልገው። በነበረችበት ሃይማኖት አመለካከት መሠረት ለእኩልነት፣ ለነጻነትና ለፍትሕ መታገል እግዚአብሔርን ማገልገል አይደለም። እግዚአብሔርን ማገልገል በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተገደበ ሱታፌ ብቻ ሆኖ ነበር የሚታያት፤ ለእርሷ።

ልዩነታቸው እየሰፋ እየሄደ ሳለ ማንዴላ እንደ ተለመደው በጨቋኙ የአፓርታይድ መንግሥት ተይዘው ወህኒ ወረዱ። ከ15 ቀን በኋላ በዋስ ተለቅቀው ሲወጡ ሚስትየው ልጆቻቸውን ይዛ ቤቱን ለቅቃ ሄዳ ነበር። የመስኮቱን መጋረጃ እንኳ አውርዳ ወሰዳለች።[1]

ዛሬ ሲታይ ግን ማንዴላ ለሚስታቸው ፖለቲካን አግላይ ሃይማኖታዊ ፍላጎት እጅ ሳይሰጡ፣ ለጥቁሮች ነጻነትና ለሰዎች እኩልነት ባደረጉት ትግል እግዚአብሔርን ልናመሰግን እንችላለን።

ማንዴላ ለፍትሕና ለእኩልነት ያደረጉት ትግል 27 ዓመት በወህኒ እንዲሠቃዩ አድርጓቸዋል። በሮቢን ደሴት በነበሩበት ጊዜ ከአሜሪካ የመጡ ጋዜጠኞች አነጋግረዋቸው ነበር። ማንዴላ የትጥቅ ትግልም ደጋፊ ስለ ነበሩ የ*ዋሽንግተን ፖስት* ጋዜጠኞች የኮምዩኒስት ሽብርተኛ እንጂ ክርስቲያን እንዳልሆኑ ቈጥረዋቸዋል። ማንዴላ ግን፣ "ክርስቲያን እንደ ነበርኩና ሁሌም ክርስቲያን ሆኜ እንደ ኖርኩ ነገርኳቸው" ይላሉ። የትጥቅ ትግል ያደረጉትም አማራጭ ስላጡ መሆኑን አስረዱ። "ክርስቶስ እንኳ ምርጫ ስላልነበረው ገንዘብ ለዋጮችን

ከቤተ መቅደስ ለማስወጣት ኀይልን ተጠቅሟል:: እርሱ የነውጥ ሰው አልነበረም፤ ከፉን ለመቃወም ግን ኀይልን ከመጠቀም በቀር አማራጭ አልነበረውም" ይላሉ::[2] (ከማንዴላ በተጨማሪ ፊደል ካስትሮም ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል (ዮሐ. 2፥13-22) ኀይልን ከመጠቀም ጋር አገናኝተው ያዩታል::[3] ሆኖም ኀይልን ከመጠቀምም ሆነ የትጥቅ ትግልን ከማካሄድ ጋር ክርስቶስን ማያያዝ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም አይደለም::)

ሌላኛው ክርስቲያን ታጋይ ማርቲን ሉተር ኪንግ ነው:: እርሱም በጥቊሮቹ ሃይማኖተኝነት ተቸግሮ ነበር:: ጥቊሮች መዘመርና ከመዘሙሩ ጋር አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግን እንደሚወዱ የታወቀ ነው፤ ከዚያ ያለፈ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ግን አልነበራቸውም:: ለፍትሕና ለእኩልነት መታገልን ያን ያህል አያውቁም:: ስለዚህ ማርቲን ሉተር ኪንግ በወቅቱ ስለ ነበረው የእኩልነት እንቅስቃሴ ሲናገር፣ "በጥቊሮች ሃይማኖት [ክርስትና] ስሜታዊነት ላይም ነው ያመፅኩት:: አልገባኝም፤ ያሳፍረኛልም:: በእውነት ሃይማኖት በእግሮቻችንና ቅልጥሞቻችን ውስጥ ያለውን ያህል በልባችንና በነፍሳችን ውስጥ ቢኖር ዓለም ይቀይር ነበር" ብሏል::[4]

ምሉእ ወንጌል ለሰዎች ሁለንተና ግድ ይለዋል:: ስለዚህ ሰው ነፍሱ ከዳነ፣ ሌላው ጒድለቱ ጒዳዮችን እንዳልሆነ ማሰብ የክርስቶስን የግዛት ክልል በቅጡ ካለመረዳት ይመነጫል:: ክርስቶስ የሰዎች "መንፈሳዊ" ኑሮ ብቻ ሳይሆን ፍትሕና ማኅበራዊ እኩልነትም ይመለከተዋል:: "ክርስቶስ ጌትነቱ በመላው ዓለም ላይ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ላይ ብቻ ስላልሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ ዐልፋ፣ ለድምፅ አልባዎች ተናጋሪ (ድምፅ)፣ ለደካሞችና ለተቆርቋሪ አልባዎች ተሟጋችና ተከላካይ መሆን አለባት::"[5] የፖለቲካና የሥነ መለኮት ሰው የነበሩት አብርሃም ኩፐር (Abraham Kuper) እንደተናገሩት፣ "በምድር ላይ ክርስቶስ የእኔ ነው የማይለው አንድም ስንዝር ስፍራ የለም::" ("There is not a single inch of which Christ the Lord does not claim as His own."[6]) ስለዚህም ክርስትና ለፍትሕና ለእኩልነት ከመቆም ጋር ሊፋታ አይችልም:: ወንጌል እነዚህን ሁሉ የሚያካትት ሰፊ ማዕቀፍ ያለው የሰዎች ሁሉ መድኀን ነው::

ይህንን በልብ ማመኑ ብቻ ግን በቂ አይደለም፤ በአፍ ከመናገር ባሻገር ተግባርንም ይጠይቃል:: በመሆኑም ክርስትና ከግለ ሰብ መዳን እንዲያልፍና ቤተ ክርስቲያንም ላለችበት ሰፊ ማኅበረ ሰብ ሸክም እንዲኖራት ይጠበቃል:: አሁን እንደምናየው ማኅበረ ሰቡ ውስጥ ፍትሕና እኩልነት መታጣቱ የማያሳስበውና ትኩረቱን በግላዊ የኑሮ ስኬት ላይ ብቻ የሚያውል ክርስትና ግን ጤናማ አይደለም:: "ግለ ሰቡ ጋር የቆመ ሃይማኖት አብቅቶለታል::"[7]



ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ ተሰፋ ቈርጠው በነበሩበት ጊዜ የጌታን ድምፅ መስማታቸውን ይናገራሉ፤ "ማርቲን ሉተር፣ ለጽድቅ ቁም፣ ለፍትሕ ቁም፣ ለእውነት ቁም:: እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" የሚል ድምፅ::[8] ስለዚህም እኒሁ መጋቢ ለዚሁ ዓላማ ጸንተው በመታገል ለውጥ አምጥተዋል:: በትግሉም ውስጥ የአብያተ ክርስቲያናት ድርሻ ብዙ ነበር::

እዚህ ግን የአማኞችን ሕይወት በመግራት ጥሩ ዜጎች እንዲሆኑ ከምታደርገው ጥረት ውጭ ቤተ ክርስቲያን በአገሪቱ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁለንተና ውስጥ ፈክቶ የወጣ ተጽዕኖ የላትም:: ግለ ሰባዊ ድኅነትን ከማኅበራዊ ርኅራኄ ነጥለው የሚያመነኙጉም ሞልተዋል:: ይህ እኔነት የሚበዛው "ክርስትና" እንደ ሆነ አስባለሁ፤ ምናልባት የ"እምነት እንቅስቃሴ" ወይም "የብልጽግና ወንጌል" ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል:: "እኛ" ብንልም አባል ከሆንንባት አጥቢያ ወይም ቤተ እምነት ቅጥር አናልፍም:: ጠንካራ ኅብረት መመሥረት ያቃተን ለዚህ ይሆን?!

ከራሳችን ውጭ ያለው የፍትሕና የነጻነት መታጣት የሚቆረቁረን አይመስልም፤ ኢፍትሐዊነት በነገሠበት ቦታ ሳንቸገር "እናመልካለን":: ጒዳዩ ሲነሣ "እንጸልያለን" የሚል መልስ ብቻ ይኖረናል:: ጸሎት ከተግባር የመሸሸ ሰበብ ተደርጎ ይወሰዳል:: በእርግጥ አንዳንዴ ስለ ፍትሕና እኩልነት በሚያምሩና በተከሹ ቃላት ብንጸልይም ተግባረኞች አይደለንም:: ዋጋ መክፈል አንፈልግም::

ለመሆኑ የነጻነት፣ የፍትሕና የእኩልነት ምንጭ፣ እንዲሁም በሁሉ ላይ ጌታ የሆነው እግዚአብሔር ጌትነቱ በቤተ ክርስቲያን በኩል ለሁሉ እንዳይገለጥ አጥር ያበጀነው በምን ምክንያት ነው? በአገራችን ያለው ክርስትና ከሃይማኖትነት እንዳይዘል ምን አነቀው? በአገር ጒዳይ የዳር ተመልካችነት አባዜ የተጠናወተው ለምንድን ነው? ፍትሕ ሲጓደል የማያመን ምን ነክቶን ነው? ክርስትናችን የብዛታችንን ያህል በአገሪቱ ነፍስ ውስጥ ዘልቆ አልገባም:: "እፍርት" እና "ጭቦ" የበዛበት ምርጫ ሲካሄድ ቤተ ክርስቲያን የትኛውንም ወገን መናገር ይሳናታል:: ፍትሕ ስትጣል ለማንሣት ትንሹን ጣቱን እንኳ የሚዘረጋ የቤተ ክርስቲያን መሪም አሁን አላየንም:: የገዢዎችና የሕዝቡ ልብ መራራቅ በብርሃን ዓመት እየተሰፈረ ቢመጣም ጒዳዬ ያለው የለም:: ስለዚህም በአገሪቱ የፖለቲካ ድርና ማግም ሆነ የየዕለት ውሎ ይቅርና በሕዝቡ የሥራ ባህል (work ethics) ላይ እንኳ ተገቢውን ተጽዕኖ ማምጣት አልቻልንም::

ለፍትሕና ለሰብአዊ መብት መቆም እንዲያውም የነቢይነት አገልግሎት አንድ መገለጫ መሆኑ ይታወቃል:: የምድራችን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በ"ነቢይ ነኝ" ባዮች እየተጣበበች ነው:: እነዚህም "ነቢያት" የብሉይ ኪዳን ነቢያት የነበራቸው ሥልጣንና ተሰሚነት እንዲኖራቸው የሚመኙና ለዚህም የሚ

ሟሟቱ ናቸው:: ለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ስለ ፍትሕና ስለ ማኅበራዊ እኩልነት ጥብቅና አይቆሙም ነበርን? ለመንግሥት የግሣጼ መልእክትስ አልነበራቸውም? የትኛውስ ነቢይ መንግሥታዊ ስሕተትን እያየ በማለፍ፣ በአድርባይነትና በፈሪነት ይከሰሳል? "ነቢያት" የበዙብን፣ ነቢያዊ አገልግሎትን ለማየት ግን ያልታደልን መሆናችን ያለንበትን ሁኔታ አሳዛኝነት ያከፋዋል::

መሪዎቻችን የሚጨነቁት አዳራሾቻቸው ሳይሞላ ሲቀርና የሚሰበሰበው መባ (ዐሥራት) መጠን ሲያንስ ብቻ ሳይሆን አይቀርም:: ምዕመናኑም ማኅበረ ሰቡ ምንም ዐይነት ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ቢኖር በየሰንበቱ ተሰብስበን "በመንፈስና በእውነት" እያመለክን አዳራሹን በዝላይና በእሜን ከማናወጥ የዘለለ ክርስትና ከነመኖሩም አናውቅም::

በምድሩ ላይ የሚካሄደው ነገር እንደማይመለከተው ቄጥሮ ወደ ሰማይ የሚያንጋጥጥ ሰው ወንጌሉ አልገባውም:: የክርስትና አእማድ የሆነው ሚዛናዊነት የጐደለው ይህ ዐይነቱ ሰው መሬት ላይ በአንድ እግሩ እንደ ቆመ ሰው ነው የሚቈጠረው:: ሂትለርን ተቃውሞ ሕይወቱን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለው ተጽዕኖ እየጨመረ የመጣው ጀርመናዊ የነገረ መለኮት ሰው ቦንሆፈር እንደሚለው፣ "በምድር ላይ በአንድ እግሩ ብቻ ለመቆም የሚሞክር ክርስቲያን በሰማይም በአንድ እግሩ እንዳይቆም እፈራለታለሁ::"[9]

ምናልባት፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በአሕዛብ እንዳስቀናቸው፣ ካልተጠበቀ ስፍራ ሌሎችን አስነሥቶ ስለ ድምፅ አልባዎች እንዲናገሩና ለፍትሕ እንዲሟገቱ በማድረግ እንዲያስቀናን እየጠበቅን ይሆን?

## ክርስቲያን እና ፖለቲካ

ክርስቲያን ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ነጻ መሆን እንዳለበት የሚሰብኩ ሰዎች በአደባባያችን አሉ:: አማኙ ከጸሎት ያለፈ ቀጥተኛ ሚና እንዳይኖረው የሚያቀነቅኑ ሰዎች ሞልተዋል:: አንድ ክርስቲያን ፖለቲካ ውስጥ ሲገባ በእምነቱ እንደ ደከመ የሚቈጥሩ ሰዎች ነበሩ፤ አሁንም አይጠፉም:: ሌላ ክርስቲያን ስፖርት ውስጥ ሲገባስ ለምን ዝም ይላሉ? ንግድ ውስጥስ መግባት አለበት? ደራሲና ተዋናይስ መሆን አለበት? ዳኛስ? ፖለቲካን ከእነዚህ ምን ይለየዋል? ፖለቲካ ሕዝብን የማስተዳደር ጥበብ ከሆነ፣ ከክርስቲያን በላይ ሕዝብን በእኩልነትና በነጻነት የማስተዳደር ሸክም ያለው መኖር ነበረበት?

ፖለቲካ የሕዝብ አስተዳደር መዘውር ነውና እርሱም ብርሃንና ጨው ያስፈልገዋል:: እንግዲያውስ አገራችን ለገባችበት የመከራ አዘቅት መድኀኒት ለመሆን የእውነተኛ ክርስቲያኖች ተሳትፎ መተኪያ አይገኝለትም::



ለመሆኑ ከፖለቲካ ነጻ መሆንስ ይቻላልን? የማምለኪያ ቦታና የአምልኮ ነጻነት እንፈልጋለን፤ እነዚህ የፖለቲካ ውሳኔዎች አይደሉምን? ስለ ትምህርትና የኢኮኖሚ ዕድገት እንናገራለን፤ እነዚህስ የፖለቲካ ውሳኔዎች መሆናቸውን ሳናውቅ ቀርተን ነው? የጾታና የሃይማኖት እኩልነትን፣ የጋብቻን ክቡርነት እየደገፍን፣ የቤት ውስጥ ጥቃትን፣ ፍቺንና ውርጃን እንቃወማለን፤ እነዚህስ ከፖለቲካ ውሳኔዎች ነጻ ናቸው? በየአካባቢያችን መሠረተ ልማቶች እንዲኖሩ እንሻለን፤ ይሄስ ከፖለቲካ ውጭ የሚሆነው እንዴት ነው? ታዲያ እንዴትና በምን ሁኔታ ከፖለቲካ ነጻ መሆን ይቻለናል?

እንዲህ ሲባል ቤተ ክርስቲያን ከፖለቲካ ኀይል ጋር ተጣብቃ መኖር አለባት ማለት አይደለም፤ የሕዝቦች የኀሊና፣ የነጻነትና የፍትሕ ጠበቃ መሆን አለባት ለማለት እንጂ:: ቤተ ክርስቲያን ከግፈኞች ጋር የተባበረችባቸው ብዙ ጊዜአት ግን አሉ:: ፋሽስቱ ጣልያን ኢትዮጵያን ሲወርር የሮማው ጳጳስ "የተቀደሰ ጦርነት ነው" በማለት ባርከው ነው ወራሪውን የላኩብን::[10] (ለዚህ ድርጊቷ ቫቲካን ኢትዮጵያን ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባት አምናለሁ::) የጀርመኗ ቤተ ክርስቲያንም ለሂትለር ልቧን ሰጥታ ነበር፤ ሂትለርን ተቃውሞ የሚቆም የቦንሆፈር ዐይነት ልባምና አርቆ ተመልካች ሰው ተገኘ እንጂ! የደቡብ አፍሪካዋ ደች ሪፎርምድ ቤተ ክርስቲያንም በዚያ የነበረውን፣ በቀለም ላይ የተመሠረተውንና የነጮችን የበላይነት የሚያራምደውን ርዕዮተ ዓለም ስትደግፍ ነበር::[11] ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ከጨካኞችና ከግፈኞች ጋር ስትተባበር ራሷም መወገዝ አለባት:: የግፈኞችን ድርጊት ዐይታ እንዳላየ መሆኗም ከግፈኞች ጋር ከመተባበር ተለይቶ መታየት ያለበት አይመስለኝም::

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የፓለቲካው ኀይል መልካም ነገር ሲያደርግ መደገፍ፣ ስሕተት ሲሠራ ደግሞ በቅደም ተከተል መምከር፣ መንቀፍና መቃወም ይኖርባታል፤ ሚዛናዊነት ይጠበቅባታል:: በአገራችን የምናየው ግን ይህን አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት ዘፈን ከበሮ ታነሣለች:: መንግሥት ሲያጠፋ፣ ኀላፊነቱን ሳይወጣ ሲቀርና ፍትሕ ሲዛባ ግን እንደ ቀረበ ሰው አፏ ተሸብቦ ይታያል:: ታዲያ የፍትሕ፣ የነጻነትና የእውነት ምንጭና ባለቤት እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ፣ ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ ጠበቃና ተከራካሪ ካልሆነች የመኖሯ ፋይዳ ምንድን ነው?

ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም ፖለቲካ ውስጥ መግባት የለባትም፤ ሕግም አይፈቅድላትም:: ቤተ ክርስቲያን የየትኛውም የፖለቲካ ኀይል ንብረት አይደለችም:: የገዢው መንግሥት ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች ስብከተ ወንጌልን ሰምተው (አካሂደው)፣ ዘምረውና ዐሥራታቸውን ሰጥተው የሚሄዱባት ቦታ ናት:: በእርግጥ የፖለቲካ ልዩነትን ይቅርና ቀላል የሐሳብ

ልዩነትን አቻችለን መኖር መቻላችን እንኳ አጠራጣሪ ቢሆንም ቤተ እግዚአብሔር ማንም በፖለቲካ ጎራ ለይቶ የሚቆምባት አይደለችም፤ ሆና ከተገኘች ለክርስቶስ ወንጌል ከፍተኛ ከስረት ነው። እዚህ ጋ መንገዱ ቀጭን በመሆኑ፣ ሚዛንን ጠብቆ ከመራመድ ውጭ ምርጫ የለንም።

ቤተ ክርስቲያን በምድር መኖሯም ወንጌልን ለመስበክ ሲሆን፣ ይህም ለፍትሕ፣ ለሰላምና ለእኩልነት መቆምን ያካትታል። ቅዱስ ቃሉም፣ “መልካም ማድረግን ተማሩ፤ ፍትሕን እሹ፣ የተገፉትን አጽናኑ (ጨቋኙን ገሥጹ)” በማለት ይናገራል (ኢሳ. 1፥17 - አ.መ.ት)። ሰዎች መቼም ቢሆን ያለ ማመቻመች ሊቆሙላቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። ልክ ለክርስቶስ በጽናት መቆም ተገቢ የሆነውን ያህል ሰላምና ማኅበራዊ ፍትሕም ከዚህ የሚመደቡ ይመስሉኛል። ክርስቲያኖች ለእነዚህም መቆም ይጠበቅባቸዋል።[12] ሰዎችን ከነሕይወታቸው በምድራዊ ሲኦል የሚከትተውን የማኅበረ ሰቡን ሁኔታ ችላ ብለው ስለ ሰማያዊ ክብር ብቻ የሚያወሩ አገልጋዮች ደረቅ ሃይማኖት የሚሰብኩ ናቸው።[13] ክርስትና ደግሞ ደረቅ ሃይማኖት አይደለም፤ በቸልተኝነታችን ልናደርቀው ካልፈለግን በቀር!

በሌኛው አቅጣጫ ግን ማኅበራዊ ወንጌልን ለመስበክ ሲባል ሰማያዊ ክብርን በመሥዋዕትነት ማቅረብም አግባብ እንዳልሆነ ማወቅ አለብን። ለፍትሕ፣ ለሰላምና ለእኩልነት መቆም ወንጌልን የመስበክ አካል እንጂ ምትክ ሊሆን አይችልም።

ለዚህ አገልግሎት ብቁ ለመሆን ደግሞ የራስን ቤት ማስተካከል ግድ ነው። ይህ ትልቁ የቤት ሥራችን ነው። እንዲያውም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ያለው ውስጣዊ ችግር በፖለቲካ ሥርዐቱ ውስጥ ካለው ችግር ይብሳል። ሁኔታውን ቀረብ ብሎ ላስተዋለው፣

> ከመንግሥት ፖለቲካ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የፖለቲካ (church politics) እርሾ እጅግ እየከመጠጠ የመጣበት፣ ጎሰኝነት፣ ሙስና፣ መገፋፋትና አለመቻቻል የቤተ ክርስቲያን ገጽታ እየሆኑ የመጡበት ጊዜ አሁን ሳይሆን አይቀርም። ይህ የውስጥ ገጽታ ካልተለወጠ ደግሞ የተቃና አገልግሎት ማገልገል ለቤተ ክርስቲያን አስቸጋሪ ይሆናል።[14]

አሁን እንደምናየው ገንዘብ ባላቸውና በሌላቸው መካከል አድልዎ የምታደርግ፣ መልካም ስም የሌላቸው መሪዎች ያሏት ቤተ ክርስቲያን ከበሬታና ተደማጭነት እንደማይኖራት መታወቅ አለበት።[15]



ይህን ተረድተን እርምጃችንን ካላስተካከልን ስለ አገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት ያለንን ምኞት ከሕልም ሩጫነት ማስቀረት አንችልም፤ ያልተፈለገ ውጤት ማስከተሉም አይቀሬ ነው።

## ዐይን አፋርነት?

ባለፉት ሥርዐቶች በፖለቲካ ምክንያት የተከሰቱትን ጥፋቶች መለስ ብሎ ማየቱ ሰዎች በዙሪያቸው የሚካሄደውን ጥፋት “አላየሁም፣ አልሰማሁም” በማለት እንደ ዔሊ ጭንቅላታቸውን ቀብረው እንዲኖሩ ሊፈታተን ይችላል። በእርግጥ ወደ ኋላ ማየት ያስፈልጋል፤ ዋነኛው ጉዞ ግን ወደ ፊት ነው። መኪና የሚያሽከረክር ሰው የፊቱን መስታዎት በአብዛኛው ቢመለከትም የኋላውንና የጎኑን መስታዎቶችም መመልከት እንዳለበት የትራፊክ ትምህርቱ እንደሚያዝ ይታወቃል። እስቲ ወደ ፊት ለመጓዝ እንዲረዳን የራሳችንን ሙብት በመጠቀም ጉዳይ እንኳ ዐይን አፋርነት ምን ያህል እንደሚገዳደረን የሚያሳዩ ሁነቶችን ከኋላ መልከት አድርገን ወደ ፊት እናቅና።

በጅማ ከተማና አካባቢው በክርስቲያኖች ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት ደርሷል። አብያተ ክርስቲያናት ፈራርሰዋል፤ ሰዎች አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። ግን እንደ ተለመደው ከመጸለይ በቀር አንድም የሚታይ እንቅስቃሴ በአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የተደረገ አይመስለኝም፤ ወይም የተደረገ ካለ እንድናውቀው አልተደረገም። ተነሣሽነቱን ወስዶ መገናኛ ብዙኃንን በመጥራት ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ዘንድ ይታወቅ ይሆን? ሰላማዊ ሰልፍስ? ይህማ አይታሰብም! ግን ለምንድን ነው ዴሞክራሲያዊ መብታችንን የማንጠቀመው? ብዙዎቻችን የምንጠቅሰው ሐዋርያው ጳውሎስ የዜግነት መብቱን ይጠቀም አልነበረምን? (የሐዋ. 16፥35-39፤ 22፥24-29)። በዚህ ሁኔታ እስከ መቼ እንቀጥላለን?

አማኞች በሽውራራ የፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ሳይሆን፣ የቤተ እምነት (ወይም የኅብረት መሪዎች) ሚናቸውን ባለመወጣት ቤተ ክርስቲያንን ዐቅም በማሳጣት ተጠያቂ እንደ ሆኑ እስባለሁ። ምክንያቱም መሪዎች ቢያንስ ከየትኛውም ምዕመንና አገልጋይ ይልቅ የመንግሥት ባለሥልጣናትን የማግኘት አንጻራዊ ዕድል ይኖራቸዋል፤ ከተጠቀሙበት። ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠታቸው ብቻ መንግሥት ለዚያ ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጥ ሊያደርገው ይችላል። ግን ይህንን መብታቸውን የማይጠቀሙ መሪዎች ናቸው ያሉን፤ የመንግሥትን ፊት እያዩ የሚኖሩ ናቸውና።

ለዚህ ማስረጃ አቀርባለሁ። በኅዳር 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተካሄደውን 16ኛው የአይካሳ ስብሰባ (International Conference on AIDS and

Sexually Transmitted Infections in Africa) በማስታከክ ግብረ ሰዶማዊ
ነት ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚፈልግ አንድ ማኅበር አባላትና ደጋፊዎች ከተለ
ያዩ አገራት ተጠራርተው አዲስ አበባ ውስጥ ስብሰባ ለማካሄድ መዘጋጀታቸው
ተነገረ። የዚህን ጸያፍ፣ ከሥነ ምግባር ውጭ የሆነና ባህልን የሚያንቋሽሽ አጀ
ንዳ ለማስፈጸም ተነሣሥቷል የተባለውን ቡድን እንቅስቃሴ በመቃወም የተለ
ያዩ ተቆርቋሪ ግለ ሰቦች በፌሰቡክ እና በተለያዩ ማኅበራዊ ድረ ገጾች ቅስቀሳ
ማድረግ ጀመሩ።

ጉዳዩ የተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ከሚስማሙባቸውና የጋራ
አቋም ከሚይዙባቸው ጉዳዮች አንዱ ነበር። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየ
ሱስ፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች
ጠቅላይ ምክር ቤት መሪዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት ስብሰባ ጠሩ፤
"ይበል" የሚያሰኝ ትብብር ነበር። የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ ግን ድንገት መጥ
ተው መሪዎቹን በዝግ አነጋገሯቸውና ጋዜጣዊ መግለጫው "ላልተወሰነ ጊዜ"
ተራዘመ። ጋዜጣዊ መግለጫው ከመጀመሩ በፊት የተነሡ ፎቶዎች እንኳ በደኅ
ንነት ሠራተኛ እንደ ተሰረዙ ሪፖርተር ጋዜጣ ዘግቧል።[16]

አቋም አልበኛዋ ቤተ ክርስቲያን ከዚያም በኋላ በዝምታዋ እንደ ጸናች
አለች። የግብረ ሰዶማውያኑ ስብሰባ የታሰበውን ያህል ባይሳካም መካሄዱ አል
ቀረም። እ.ኤ.አ በ2007 በ44 አገሮች በተካሄደ ጥናት (2007 Pew Global
Attitudes Project) ከኢትዮጵያ ሕዝብ 97 በመቶው ግብረ ሰዶማዊነትን
ይቃወማል፤ ይህም ጥናቱ ከተካሄደባቸው አገራት በተቃውሞ ከፍተኛነት ሁለ
ተኛው ነው።[17] የተሻሻለው የቤተ ሰብ ሕግ ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት
ሴት መካከል የሚፈጸም መሆኑንም ይደነግጋል (ክፍል ፩፣ አንቀጽ ፪፣ ፫፣ ፬)።
የተሻሻለው የወንጀል ሕግ (1996) ደግሞ ግብረ ሰዶማዊነትን በወንጀልነት አስ
ቀምጦታል (ክፍል ፪፣ አንቀጽ ፮፻፳፱)። ከላይ እንደ ተጠቀሰው የሌሎች ሃይ
ማኖቶች ስምምነትም አለበት። ታዲያ በዚህ ብርቱ ጉዳይ ላይ መንግሥት ሲፈ
ቅድልን ብቻ እየተናገርን፣ ሲቈጣን ደግሞ ዝም ማለት አለብን? ቤተ ክርስቲያን
ሓሳብን በነጻነት የመግለጥ ሕገ መንግሥታዊ መብቷን የማትጠቀመው ለምን
ድን ነው? ዝምታው ከየት መነጨ? መንግሥትስ ግብረ ሰዶማዊነት በኢትዮጵያ
ሕግ ወንጀል ሆኖ ሳለ፣ ጉዳዩን የሚያቀነቅን ቡድን በአገሪቱ ሲሰበሰብ በዝምታ
በማየቱ ኀላፊነቱን ባለመወጣት ሕግን እየጣሰ አይደለምን?

በዚህ ሁሉ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሽቁጥቁጥነቷና የመንግሥትን ፊት
ዐይቶ አዳሪነቷ በተግባር እየታየ ነው። ለእውነት ደፍረው በሚቆሙ መሪዎች
አልታደለችምና! የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ፈሪና አቋም አልባ በመሆና



ቸው በባለሥልጣናት ዘንድ ተወዳጅነትን የሚያገኙ ቢመስላቸውም ንቀትን
ነው የሚያተርፉት። ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ሰዎች ዘንድ ክብርና ሞገስ ያጣ
ችውም ለዚህ ይመስለኛል! አቋም የለሽን ማን ያከብራል!?

በዚህ አካሄድ ነገ መንግሥት ዐይኑን በጨው ታጥቦ "የምፈልገውን
'ልማታዊ' ስብከት ብቻ ስበኩ" ቢለን ከእሺታ የተለየ መልስ ይታወሰን ይሆን?
በየመድረካችሁ ላይ ማን መስበክና መዘመር እንዳለበት ፈቃድ የምሰጠውና
የምነሣው እኔ ነኝ ቢልስ፣ "አይሆንም" የማለት ዐቅማችንን ብጠራጠር የሚፈር
ድብኝ ይኖራል? ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ከሌሎች የክርስትና ዘርፎች በተ
ለየ የአማኞችን ሁሉ ክህነት እንደምናምን ይታወቃል። በመሆኑም መንግሥት
ይህን ካሰበ ለምዕመናን ሁሉ ፈቃድ መስጠት ይኖርበታል ማለት ነው። ታዲያ
ለዚህ እውነት የሚቆሙ መሪዎች እንደሚኖሩን ተስፋ ማድረግ እንችላለን? ለነ
ገሩ አሁንም ቢሆን "መመሪያ የምናገኘው ከመሬታዊው መንግሥት ነው ወይስ
ከሰማዩ?" ብሎ መጠየቁ አግባብ ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም ከኢቴቪና
ከቤተ ክርስቲያን ፑልፒት የምንሰማው እየተወራረሰብን የምንቸገርበት ጊዜ
አለና። በዚህ ከቀጠልን ከምድርም ከሰማይም ተጣልተን እንዳንቀር ያሠጋል።

ቤተ ክርስቲያን እጇን አጣጥፋ በመቀመጥ፣ መንግሥት "ሁኚ" የሚላ
ትን ብቻ የምትሆነው መንግሥትን እንደ አሳቢ አባት የመመልከት ልማድ
በመኖሩም ነው። ግን መንግሥት አባት ነው እንዴ? በፍጹም!! መንግሥት
የሕዝብ አገልጋይ ነው። ስለዚህ ሥራውን በአግባቡ እንዲሠራ ማበረታታትና
ሲያጠፋም መምከርና መገሠጽ እንጂ በጭራሽ እንደ አባት ልንመለከተው
አይገባም። በአገልጋይነቱ ሥራውን (ኀላፊነቱን) ካልተወጣ ሌላ አገልጋይ ሊቀ
ጠር ይገባል። "የሰጣችሁኝን ሥራ፣ ይሄንና ያንን ሠርቼላችኋለሁና ወደዳች
ሁም ጠላችሁ የትም አልሄድም፤ ካልተስማማችሁ የፈለጋችሁበት ልትደርሱ
ትችላላችሁ" በማለት ቀጣሪዎቹን የሚያስፈራራ አገልጋይ ጤነኛ ሊሆን አይች
ልም። "ማሳደግ የጀመርኩት ልጅ አድጎ ራሱን እስኪችል ድረስ ላለመውጣት
ወስኛለሁና 'ሂጂ' ብትሉኝም ከዚህ ቤት አልሄድም" የምትል ሞግዚትን እስቲ
አስቡ፤ ስሜት ይሰጣል?

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፍርሀትና በምንም መልኩ ቢሆን በምድር
ተደላድሎ መኖርን ግብ አድርገው መያዛቸው ደግሞ ሌላኛው ሰበብ ነው።
ለዚህ ግብ ሲሉ የማይደረግ ያደርጋሉ። በዚህም ራሳቸው ሞገስ እንዳይኖራቸ
ውና የሚመሯት ተቋምም ከበሬታ እንድታጣ ምክንያት ሆነዋል። እውን ወን
ጌሉ እንዲህ አድርባይ በመሆን ነፍሳቸውን እንዲያቈዩ አስተምሯቸዋልን? ለእ
ውነት ዋጋ ከመክፈል ይልቅ እያመቻመቹ መኖርን ግብ ማድረግስ ክርስትና
ነው?

ነፍስን ማቈየት ለሌሎች ግብ ሊሆን ቢችልም፣ የክርስትና ዋጋ አሰጣጥ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው:: ክርስትና፣ ዓለም ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን ነገሮች ፊት ይነሣቸዋል፤ ዓለም ዋጋ የሚነሣቸውን ነገሮች ደግሞ ያከብራል:: በዚህ መንገድ ነፍሳቸውን ያኖሩትን ነፍሳቸውን እንዳጡ ሲቈጥር፣ ነፍሳቸውን አሳልፈው የሰጡትን ደግሞ እንዳገኙት ይቈጥራል!

## የሰላም ጠበቃነት

በዚህ ዘመን ከየመገናኛ ብዙኀኑ የምንሰማው አንድ ጉልጥምት (ጉቶ) ቃል አለ፤ "ጸረ" የሚል:: ጸረ ሰላም፣ ጸረ ልማት፣ ጸረ ሕዝብ ...:: የፖለቲካ ቡድኖች ከእነርሱ የተለየ ሐሳብ የሚያራምድን ሌላ አካል "ጸረ-ሰላም" የሚል ታፔላ ይለጥፉበታል:: ሁሉም በተገኘው መድረክ ራሱን የሰላም ጠበቃና ዋስትና አድርጎ ያቀርባል፤ ሌሎችን ደግሞ "ጸረ ሰላም ኀይላት" በማለት ይፈርጃል::

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የሰላሙን ጌታ የምታመልክና የሰላሙን ወንጌል የምትሰብክ የሰላም ጠበቃ መሆኗ ይታወቃል:: በመሆኑም የሰላም ጠር የሆኑ ኀይላትን ትመከራለች፣ ትገሥጻለች፣ ትጸልይላቸዋለች፣ ትቃወማቸዋለች ብሎ ማሰብ ትክክል ነው:: ግና ስለ ሰላም መዘፈን ብቻ ሰላም ወዳድ ያደርጋል?

ይህን ለመረዳት ሰላም እንዴት እንደሚመጣ ማወቅ አለብን፤ ጥቂት የማይባሉ ወገኖች ሰላም ማለት ዝምታ ብቻ ይመስላቸዋል:: ሕዝብ በፍርሀት ተሸብቦም ቢሆን ዝም ማለቱ የሰላም መኖር ተደርጎ ሲወሰድ ይታያል:: የመንግሥትና የሌሎች የሰላም ትርጓሜ የሚለያየው እዚህ ጋ ሳይሆን አይቀርም::

ሰላም ፍትሕን፣ እኩልነትን፣ ምሕረትንና ነጻነትን ትሻለች:: ፍትሕ እየተዛባ ሰላም ልትኖር አትችልም:: ምሕረት ሳይኖር ሰላም አትታሰብም:: ነጻነት በሌለበት ሰላምን መፈለግ፣ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ነው:: የታፈነ ሕዝብ፣ የተነፈገ ነጻነት፣ የተዛባ ፍርድ፣ የተረገጠ መብት ባለበትና ፍርሀትና ሥጋት በተንሰራፋበት ቦታ ሁሉም ነገሮች ቢኖሩ እንኳ ሰላም ከቶውንም አትገኝም:: ማንዴላ እንደተናገሩት፣ ማኅበራዊ እኩልነትና ሚዛናዊ የልማት ሥርጭት ሳይኖር ሰላም አትኖርም::[18] በአጭሩ፣ "ዴሞክራሲ ከሌለ ሰላም የለችም::"[19] ብዙውን ጊዜ እነዚህን ነገሮች የማድረግ ዐቅም ያላቸው ደግሞ መንግሥታት ናቸው::

ስለዚህ በሌሎች ላይ "ጸረ ሰላም" የሚል ጽሑፍ የሚለጥፍ የትኛውም መንግሥት የሕግ የበላይነትን፣ ፍትሕንና እኩልነትን አክብሮ ካላስከበረ ራሱ ቀንደኛ ጸረ ሰላም ነው:: ስለዚህ እንዲህ ዐይነቱን ድርጊት መቃወም የሰላም



ጠበቃነት ነው:: አሊያማ ነገ የሚፈነዳ ቦምብ እየቀበሩ "ሰላም ሰላም" በማለት የሚዘፍኑትን አካላት የሰላም ኀይላት አድርጎ መውሰድ ራስን ማታለል ነው:: ምክንያቱም ሰላም ያለ አንዳች ኮሽታ በፍርሀትና በዝምታ መኖር አይደለችም፤ እንዲያውም፣ "ሰላም የዝምታ ተቃራኒ ናት"::[20]

ጌታ ኢየሱስ በቃልም ሆነ በሥራ ብርቱ ስለ ነበረ፣ ቤተ ክርስቲያን ለሰላም አስተዋጽኦ ማድረግ ከፈለገች አገር ላይ የሚፈጠሩ ውጥረቶችን ለመቀነስ ከስብከት ባሻገር ሥራም መሥራት አለባት:: ለአብነት በገዢዎችና በሕዝቡ መካከል፣ በገዢውና በተቃዋሚዎች መካከል፣ በብሔረ ሰቦች መካከል፣ ትናንት በተሠሩ ጥፋቶችና ስሕተቶች ላይ ብሔራዊ መግባባትና ዕርቅ እንዲኖር መሥራት ትችላለች:: አሳዛኙ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያናችን የራሷን ውጥረት እንኳ ለማስተካከል ዐቅም የላትም:: ስለዚህ ቦብ ማርሌይ ተቀናቃኝ ፖለቲከኞችን በዘፈኑ ያስታረቀውን ያህል በመዝሙራችን መሥራት አልቻልንም፤ በእግሮቻችንና በእጆቻችን ውስጥ ያለውን ያህል ክርስትና በልባችን ይኖር ይሆን!?

ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰላም ማውራት፣ መናገር፣ ማስተማር ካለባት ስለ ፍትሕ፣ ስለ እኩልነት፣ ስለ ነጻነት፣ ስለ ሕግ የበላይነት ማውራት አለባት:: ወንጌሉ የእነዚህ ጉዳዮች ጠበቃ እንድንሆንና ያገባናል እንድንል ግድ ይለናል:: የቤተ ክርስቲያን ሙሉ ተልእኮ እነዚህንም ያካትታል:: "ስለ ራሳቸው መናገር ለማይችሉት፣ ለችግረኞችም ሁሉ መብት ተሟገት:: ተናገር፣ በቅንነትም ፍረድ፤ የምስኪኖችንና የድኾችን መብት አስከብር" ይላልና (ምሳሌ 31፥8-9 - አ.መ.ት) ለራሳቸው መናገር ለማይችሉ መናገር ጥሪዋ ነው:: አሊያ ጐዶሎ መልእክት የያዘች ጐዶሎ መልእክተኛ ትሆናለች! ስለ እነዚህ ክቡር ጉዳዮች መናገር ከተሳናት ስለ ሰላም ለማውራት የሞራል ብቃት አይኖራትም::

## የነጻነት ጉዳይ

የነጻነት ምንጭ እግዚአብሔር ነው:: ሐሳብን የመግለጽ፣ የአምልኮ፣ የነጻነት፣ በሕይወት የመኖር መብቶች ለሰዎች ልጆች ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጡ (ሰብአዊ) መብቶች ናቸው:: የሕገ መንግሥቱ ሥልጣን ለእነዚህ የተፈጥሮ መብቶች ዕውቅናና ዋስትና መስጠት እንጂ፣ የመብቶቹ ሰጭና ነሺ መሆን አይደለም:: የመብቶች ምንጭ እግዚአብሔር ነው::

እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው ከነጻነት ጋር ነው:: ማንዴላ እንደሚሉት ማንኛችንም ከነጻነት ረኃብ ጋር አልተወለድንም፤ ማሰብ በምንችለው በየትኛውም መንገድ ነጻ ሆነን ነው የተወለድነው::[21] እግዚአብሔር ነጻነትን የሰጠን በነጻነት ወደ እውነቱ እንድንደርስም በማሰብ ነው::

መንግሥት ሕዝቡን ሲያስተዳድር፣ ሕዝቡም ለመንግሥት ሲገዛ በነጻነት መሆን እንዳለበት ከጥንትም ተቀባይነት ያገኘ ሐሳብ ነው:: ይህ የጥሩ መንግሥትነትና የጥሩ ዜጋነት ማሳያ ነው:: አሪስጣጣሊስ (Aristotle) እንደሚለው፣ "ጥሩ ዜጋ እንደ ነጻ ሰው መገዛትንና መግዛትን መቻል አለበት::" (A good citizen must be able both to rule and to be ruled as a freeman.) በዚህ መነፅር ሲታይ የእኛ ነገር እንዴት ይሆን?

ነጻነት ማለት ግን ማድረግ ያለብንን ነገር የማድረግ መብት እንጂ ደስ ያለንን ነገር ሁሉ የመፈጸም ፈቃድ አይደለም:: በፖለቲካው ክልልም ነጻነት እግዚአብሔር ያዘዘው ፍጹም መብት አይደለም:: ነጻነት ፍጹም ሊሆን አይችልም፤ የአንዱ ነጻነት የሌላኛውን ነጻነት ሊጋፋ ይችላልና::[22] ነጻነት ከኀላፊነት ጋር የተሰጠ ነገር ነው:: የግብረ ሰዶማውያኑን ስብሰባ በመቃወም ለመስጠት ታስቦ የነበረው መግለጫ በመንግሥት ጫና መቅረቱ ማድረግ ያለብንን ነገር የማድረግ ችሎታችን (ነጻነታችን) ምን ያህል እንደ ተገደበ ማስረጃ ይሆናል::

ይህንን ችሎታቸውን የተከለከሉ ሌሎች የኅብረተ ሰብ ክፍሎች ሊኖሩስ አይችሉም? ነጻነት ማጣቱ በቀጥታ እኛ ጋ ካልደረሰ እንዳላየ ስንሆን የምንገኝበት ጊዜ ግን ጥቂት አይደለም:: ነጻነት አይሸነሸንም፤ የአንዱ ሰው ሰንሰለት የሁሉም ሰንሰለት ነው፤ የሁሉም ሰንሰለት የእኛም ሰንሰለት ነው::[23] ሁላችንም ነጻ ካልሆንን ማናችንም ነጻ አይደለንም:: እኛ ካልተነካን ሁሉ ሰላም እንደሆነ ማሰብ ራሱ የራሳችን ጠላት ያደርገናል፤ ክርስቲያናዊ ምግባርም አይደለም:: ሌላው ቀርቶ፣ ተጨቋኙ ነጻ መውጣት ያለበትን ያህል ጨቋኙም ነጻ መውጣት አለበት:: የሌላውን ነጻነት የሚገፍፍ ሰው የጥላቻ እስረኛ ነውና::[24]

በዘመነ ናዚ የነበሩት ኒሞለር የተባሉ የጀርመን ቤተ ክርስቲያን መሪ በማሠቃያ ካምፕ ውስጥ በሂትለር የግል እስረኛነት ለ8 ዓመት ሲታሰሩ የተናገሩትን እዚህ ጋ እናስታውስ:: "ናዚዎቹ መጀመሪያ ሶሻሊስቶቹን ለማጥቃት መጡ፤ እኔ ግን ሶሻሊስት ስላልነበርኩ ምንም አልተናገርኩም:: ቀጥለው ወደ ንግድ ማኅበራት መሪዎች መጡ፤ ያኔም ምንም አላልኩም - የንግድ ማኅበራት መሪ አልነበርኩምና:: ከዚያ ደግሞ ወደ አይሁዳውያን መጡ፤ በዚያን ጊዜም አንዳች አልተናገርኩም - አይሁድ አልነበርኩምና:: በመጨረሻም ወደ እኔ መጡ፣ ያኔ ግን የሚናገርልኝ ሰው አልነበረም" ነበር ያሉት::[25]

የየትኛውም ሰው ወይም ቡድን ነጻነት ሲጣስ ቤተ ክርስቲያን ይመለከታታል፤ በምድር የእግዚአብሔር ወኪል ናትና:: እዚህም ጋ ግን መንገዱ ቀጭን ነው! የእነዚህ ሰዎች (ቡድኖች) ድርጊት ሕግን ሲተላለፍ፣ የሕዝቡን ሥነ ምግባር የሚበርዝ ሆኖ ሲገኝ፣ ድርጊቱን በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን ፈትሾ ማውገዝ ያስፈልግ ይሆናል (ግብረ ሰዶማዊነትን ያስታውሷል!)::



ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ስለ ነጻነት ስትናገር የራሷን ነጻነት ብቻ በማሰብ መሆን የለበትም:: እንዲህ ዐ[illegible]ቲ "ቤተ ክርስቲያን" እንደ ክርስቶስ አካልነቷ የኀላፊነት ድርሻዋን ተወጥ[illegible]ቶ ለማለት ያዳግተኛል:: ነጻነት ሲባል ሁሉም ነጻ ሆኖ፣ መብቱ ተከብሮና ተቻችሎ በሰላም የሚኖርበትን አግባብ ማሰብ ተገቢ ነው:: "በሰላም አብሮ የመኖር ችሎታ የሌለበት ነጻነት እርሱ እውነተኛ ነጻነት አይደለም::"[26]

ዊንስተን ቸርችል እንደሚሉት "አንድን ማኅበረ ሰብ መገምገም የሚቻለው በወህኒ ቤቶቹ ነው::"[27] ለምሳሌ የኢትዮጵያ እስር ቤቶች ምን ይመስላሉ? ያለ ፍርድ የታሰሩ የሉም? ማረፊያ ቤት ግፍና በደል አይፈጸምም? በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ወህኒ የታጎሩና እዚያው የተረሱ ሰዎች የሉም? ቤተ ሰብ፣ የሃይማኖት አባትና ጠበቃ እንዳያገኟቸው የተደረጉስ አይታወቁም? ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ግን በአገራችን እነዚህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በስፋት እንደሚታዩ በየጊዜው መግለጫ ማውጣታቸውን እንደ ቀጠሉ ናቸው::

በ1974 ዓ.ም ከ150 አገራት የተወከሉ አብያተ ክርስቲያናት ያጸደቁት "የሉዛን ቃል ኪዳን" ስለ ማኅበራዊ ኀላፊነት እንደሚከተለው ይናገራል፤[28]

> እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ ፈጣሪና ዳኛ መሆኑን እናምናለን:: ስለዚህም በሰዎች መካከል ለፍትሕና ለዕርቅ፣ እንዲሁም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከየትኛውም ጭቆና ነጻ እንዲወጡ ያለውን ሸክም እንጋራለን:: ... ወንጌል ሥርጭትና ማኅበራዊ ኀላፊነት እርስ በርስ የተለያዩ አድርገን በማሰባችንና በቸልተኛነታችን ንስሓ እንገባለን:: ... ወንጌል ሥርጭትና ማኅበራዊ የፖለቲካ ተሳትፎ በአንድነት የክርስቲያናዊ ኀላፊነታችን አካል ናቸው:: ምክንያቱም ሁለቱም የትምህርተ እግዚአብሔርና የትምህርተ ሰብ፣ ባልንጀራችንን የመውደዳችንና ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለን ታዛዥነት አስፈላጊ መግለጫዎች ናቸውና:: የድነት መልእክት በየትኛውም ዐይነት አግላይነት፣ ጭቆና እና ዘረኝነት ላይ ፍርድ የያዘ መልእክትም በመሆኑ ክፋትንና ኢፍትሐዊነት በሚገኙበት ስፍራ ሁሉ ማውገዝ አለብን:: ...[29]

ታዲያ ቤተ ክርስቲያን ምን እየሠራች ነው? የምትኖርበትን ማኅበረ ሰብ ነባራዊ ሁኔታ የማታውቅ ቤተ ክርስቲያን ምን ዐይነት የክርስቶስ አካል ናት? በተለያየ ኢኮኖሚያና ማኅበራዊ ቀውስ የሚያልፉ ሰዎች በእግዚአብሔር ዝምታ የሚሠቃዩበት አንዱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያንና የእግዚአብሔር ሰዎች

ዝም በማለታቸው ነው።[30] ቤተ ክርስቲያን በምድር የእግዚአብሔር ወኪልነቷን በተግባር ካላሳየች ሌላ ምድራዊ ተቋም ሊተካት ይችላልን? የምድራችን ቤተ ክርስቲያን ግን ዐይኖቿን በእጆቿ ሸፍና ስኬትንና መከናወንን ብቻ ትሰብካለች። ወደ ሰው ሕይወት ዘልቆ ያልገባ፣ በአገሪቱ ሰብአዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ጉልሕ አስተዋጽኦ የማይታይበት ስብከት!

## የመንግሥት "ቲፎዞ"?

ይህ ሁሉ አንድ ቀን መለወጡ የተፈጥሮ ሕግ ነውና አይቀርም። ዛሬ እጃችንን አጣጥፈን ተቀምጠን፣ በመንግሥት የሚቀርብልንን ዜማ ማዜሙንና በመንግሥት ዘፈን መጨፈሩን ቀጥለን የመንግሥትን ጥፋት ማየት ካልቻልን ኀላፊነታችንን አልተወጣንምና ዋጋ ስንከፍል እንኖራለን። የነገው ባለተራ በዛሬው አርምሞአችን በወገንተኝነት አይፈርጀን ይሆን? ለዚህ አስረጅ አቀርባለሁ።

በታሪካዊው የ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ክርስቲያኖች በምርጫ እንዲሳተፉ ቅስቀሳ ሲያካሂድ ነበር። ከምርጫው በኋላ ግን ዐመፅና ምስቅልቅል ተፈጥሮ ሰዎች ሕፃን፣ ዐዋቂ፣ ወንድ፣ ሴት ሳይባሉ ሲገደሉና ብዙዎች ታፍሰው ሲታሰሩ ኅብረቱ ትንፍሽ አላለም። ለእውነትና ለፍትሕ ዋጋ ለመክፈል የጨከነ መሪ አልነበረንም። መንግሥትን ለመገሠጽ፣ ለመምከርና ከሕዝቡ ጋር ለማቀራረብ ከቤተ ክርስቲያን በኩል የተደረገ ጥረት መኖሩም አይታወቅም። መሪዎቻችን ዛጎላቸው ውስጥ ገብተው ነበር። መሪነት ለጭንቅ ጊዜ ሕዝቡን ካልረዳ ፋይዳው ምንድን ነው? መሪ የሚሆኑ ሰዎች የጥሪውን ክብር ብቻ ከማሰብ ስካር የሚላቀቁት መቼ ነው?

በዚያን ጊዜ ካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረች ድርጊቱን በማውገዝ ይፋዊ መግለጫ ያወጣችው። ይህም ማን ገለልተኛና ለእውነት እንደሚቆም በማሳየት የራሱ ሚና ነበረው። ቀጣዩ ምርጫ በ2002 ዓ.ም ሲደረግም ውጥረት ስለ ነበር ችግር እንደሚከሰት ብዙዎች ሥጋት ነበራቸው። ስለዚህ የእኛን ሰዎች ጨምሮ ሌሎችም የሃይማኖት ተቋማት የፖለቲካ ቡድኖችን ለማቀራረብና ውጥረቱን ለማርገብ የመካከለኛነት ሚና ለመጫወት ጥሪ አቀረቡ። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቀር የትኛውንም የሃይማኖት መሪ እንደማያምኑ ለመናገር አልተቸገሩም፤ ለዚህም የ97ቱን ክስተት ነበር የጠቀሱት።

ያ ሁሉ ጥፋት በደጇ ሲፈጸም የአፍሪካ ኅብረትን ይመስል የምታንቀላፋ ቤተ ክርስቲያን የገዢው ቡድን ደጋፊ ተደርጋ ብትቈጠርና የሞራል ተጽዕኖ የማሳደር ዐቅሟ ቢናቅ ምን ይገርማል? ነገስ ችግር ቢፈጠር እንደ በፊቱ እንዳ



ላየ ነው የምታልፈው? ወይስ አቋም ትወስዳለች? ትክክለኛውንና ቀጥተኛውን አቋም አለመውሰድ በሌላ አቅጣጫ ያልተፈለገ አቋም መውሰድ አይደለምን? ስለዚህ ገዢው ቡድን ጥፋት ሲፈጽም አቋም ሳትወስድ ስትቀር የገዢውን አካል ለመደገፍ አቋም ወስዳለች ማለት ነው። ታዲያ ነገ ሌሎች ወደ ሥልጣን ቢመጡ (ዘላለም ሲገዛ የሚኖር የለምና!) ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ሊመለከቷት እንደሚችሉ አሻግሮ የሚያይ መሪ የሚኖረን መቼ ነው? ወይስ እንደ ተለመደው ነገን ችላ ብለን፣ ዛሬን ብቻ እያመለከን እንኖራለን?

አድርባይነታችን፣ ፍርሀታችንና ዳተኝነታችን ለወንጌል እንቅፋት ያደርገናል። እድፋችንን በንጹሑ ወንጌል ላይ እንጠርጋለን። ለእውነት ብንቆም ግን፣ ቤተ ክርስቲያን በኢአማንያን ዘንድ እንኳ ክብርና ተቀባይነት ይኖራታል፤ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታም ይከብራል። ብዙዎችም ተከታዮቹ ይሆናሉ።

ሆኖም ሕዝብን ከሚያስለቅሱ፣ በሙስና አፍንጫቸው ድረስ ከተዘፈቁ ባለ ሥልጣናት ጋር መታየት እንደ ሕፃን የሚያፍነከንካቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማየት ልብ ይሰብራል። እንዲህ ዐይነት ግፈኞችን በስመ ክርስቲያንነት ብቻ በየመጽሔታቸው በቃለ መጠይቅ ለማሞገስ የሚጣደፉ ባለ መጽሔቶችና ለጸሎት ቤት ምርቃት የሚጋብዙ መጋቢዎች ተስፋ ያስቈርጣሉ። እውን እኛ በምድር የእግዚአብሔር ወኪሎች ነን?

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማርቲን ሉተር ያለውን ነገር ሁሌ ቢያስታውሱት መልካም ነው፤ "ቤተ ክርስቲያን ... የመንግሥት ጌታም ሆነ አገልጋይ አይደለችም፤ የመንግሥት ኅሊና እንጂ። ስለዚህም የመንግሥት አቅጣጫ አመልካችና ተቺ (ኀያሲ) እንጂ መሣሪያ መሆን የለባትም።"

## ሃይማኖት እና መንግሥት

አንዳንዶች የመንግሥትን ጥፋት ዐይቶ እንዳላየ ለማለፋቸው የሚያቀርቡት መከራከሪያ የሃይማኖትና የመንግሥት ልዩነት በሕገ መንግሥቱ መቀመጡን ነው (የሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ፪ አንቀጽ ፲፩)። አዎን፤ ዛሬ በዓለም ላይ ከጥቂት አገራት በስተቀር ሃይማኖትና መንግሥት በሕግ ተፋትተዋል፤ አገራችንን ጨምሮ። ስለዚህም መንግሥታዊ ሃይማኖትም ሆነ ሃይማኖታዊ መንግሥት አይኖርምና ክርስቲያናዊ መንግሥት እንዲኖረን ማሰብ አንችልም። ከሞላ ጐደል ሕዝቡ አንድ ሃይማኖት በሚከተልባቸው ጀርመንን በመሳሰሉ የአውሮፓ አገራት ክርስቲያናዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ፤ እንደ ኢትዮጵያ ዐይነት የተለያዩ ሃይማኖቶች ባለ ብዙ ተከታዮች በሆኑባት አገር ግን ሃይማኖታዊ ፓርቲዎችን መፍቀድ አደጋው ብዙ ነው። ስለዚህ በምንም መልኩ ሃይማኖታዊ መንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ሃይማኖት አለመኖሩ በሁሉም መልኩ ይደገ

ፉል፡፡ በሌላ መልኩ ሲታይም፣ "ሃይማኖታዊ አምባገነንነት ከዓለማዊ አምባገነ
ንነት አይሻልም፡፡"[31] ስለዚህ ሃይማኖታዊ መንግሥት እንዳይኖር በተቻለው
መንገድ ሁሉ መሥራት አለብን፡፡

የመንግሥትና የሃይማኖት ፍቺ ለቤተ ክርስቲያንም መልካም ነው፡፡
መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በአንድ ያደሩበት ዘመን በክርስትና ላይ ዝቅጠት
ንና ጥፋትን ከማስከተል በቀር የሚበጅ አልነበረም፡፡ በእርግጥ ወንጌላውያን
ክርስቲያኖች ኢትዮጵያ ውስጥ በቄሳር ጡጫ የተመረሩበት እንጂ ቤተ ክርስቲ
ያናችን የቄሳር የጡት ልጅ የነበረችበት ጊዜ አልነበረም፡፡ እንዲያውም የተወረሱ
የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች የተመለሱት፣ ተጨማሪ የማምለኪያና የመቃብር
ቦታዎች የማግኘትና የአምልኮ ነጻነት መብታችን የተከበረው ከመንግሥት
ለውጡ ወዲህ ነው፡፡ ሆኖም መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን አንድ ሲሆኑ
ለወንጌል አደጋ እንደሚሆን ለመረዳት ታሪክን መፈተሽ በቂ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ የሩቅ ብቻ ሳይሆን የቅርብ ታሪክም አለ፡፡ ለምሳሌ
እ.ኤ.አ በ1991 ኮምዩኒዝም ከፖላንድ ሲወገድ 70 በመቶ የሚሆኑ ዜጎች የካቶ
ሊክ ቤተ ክርስቲያንን የሞራልና የመንፈሳዊነት ኀይል አድርገው ተቀብለዋት
ነበር፤ አሁን ግን ወደ 40 በመቶ ወርደዋል፡፡ ተቀባይነቷ እንዲቀንስ ምክንያቱ
ደግሞ የመንግሥት ኅሊና ከመሆን ይልቅ ፖለቲካ ውስጥ የምታደርገው
ተሳትፎ ነው፤ ዘመናዊቷ ፖላንድ የመንግሥትንና የሃይማኖትን ልዩነት አትቀ
በልምና፡፡[32]

በአንዳንድ አገራት ደግሞ መንግሥታዊ ሃይማኖት ወደ "ሃይማኖት
የለሽ" መንግሥትነት አምርቷል፡፡ ይህ ግን ከባድ አደጋ ነው፡፡ ምክንያቱም በዓ
ለማችን ላይ በማደግ ላይ ያለው "ሃይማኖት የለሽ" መንግሥት ከሃይማኖት የለ
ሽነት ዐልፎ ጸረ ሃይማኖትም እየሆነ በመምጣት ላይ ነውና፡፡[33] ስለዚህ ጥቅማ
ችንን በበለጠ የሚያስጠብቅልን ሕግ እንዲወጣና በሥራ ላይ እንዲውል ግፊት
ማድረግ ሊኖርብን ይችላል፡፡ ከግል ጥቅም ጋር ባልተያያዘ መልኩ ዕውቀትን፣
ገንዘብን፣ ጉልበትንና ጊዜን መሥዋዕት በማድረግ ለአገርና ለወገን የሚጠቅሙ
ለውጦች እንዲመጡ በመንግሥት ላይ አዎንታዊ ጫና ማሳደርም ተገቢ ነው፡፡
በዚህ ጊዜ ግን ቤተ ክርስቲያን የሌሎችን መብት የሚነካ የተለየ ጥቅም ለማግ
ኘት ጥያቄ ማቅረብ የለባትም፡፡ ከመንግሥት ጥቅሞችን ለማግኘት ስትል አላስ
ፈላጊ ድርድር ከማድረግም መራቅ ያስፈልጋታል፡፡[34]

የአገራችን ሕገ መንግሥት እንደሚናገረው መንግሥት በሃይማኖት
ጉዳይ፣ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገቡም፡፡ ሆኖም ሕገ መን
ግሥቱ በሃይማኖት ቡድኖች ሲጣስ መንግሥት ሕገ መንግሥቱን ለማስከበር
መንቀሳቀሱ እንደማይቀር ግልጽ ነው፡፡ ታዲያ ሕገ መንግሥቱ ላይ የሠፈሩት



ሰብአዊ መብቶች በመንግሥት ሲጣሱስ ቤተ ክርስቲያን ለሕገ መንግሥቱ መከ
በር ጥብቅና ብትቆም አመክንዮአዊ አይሆንምን?

የቤተ ክርስቲያን አንዳንድ የኋላ ታሪክ እንደሚያስተምረን መንበረ ሃይ
ማኖት ከመንበረ መንግሥት ጋር/በተቃራኒ ጠቃሚ ሚና መጫወት እንደምት
ችል መረዳት አይከብድም፡፡ ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ጉዳይ
ጣልቃ አትግባ ማለት፣ ስለ ፍትሕና ስለ ሰብአዊ መብት አትናገር ማለት ነውን?
እነዚህ ጉዳዮች የመንግሥት ብቻ ናቸው ለማለት የሚቻል አይመስለኝም፤
ሁሉንም የሚመለከቱ ናቸውና፡፡ ፍትሕና ማኅበራዊ እኩልነት መንፈሳዊ ጉዳ
ዮች አይደሉም ማለት ይቻላልን? የሃይማኖትና የመንግሥት ልዩነት ኖሮም ቤተ
ክርስቲያን ተጽዕኖ የማሳደር ኀይሏን በመጠቀም ለመልካም ጉዳዮች ጣልቃ
መግባት እንደምትችል ከሠለጠኑት አገራት እንኳ ማየት ይቻላል፡፡ ስለዚህ መን
ግሥትና ቤተ ክርስቲያን አንዳቸው በሚሠሩት ሥራ ላይ ሌላኛቸው ዐይናቸ
ውን ጨፍነው ዝም ይላሉ ማለት አይደለም - በጭራሽ!

እንዲያውም ሁለቱ ተቋማት (ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት) የሚሠሩት
ሥራ እንደሚደጋገፍና የአንዳቸው ሚና ለሌላኛቸው ጠቃሚታ እንደሚኖረው
ግልጽ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ሁለቱም የእግዚአብሔር አገልጋይ ተብለው
ተጠቅሰዋልና "የእግዚአብሔር ዓላማ በምድር እንዲሰምር የየራሳቸው ሚናና
ኀላፊነት አላቸው፤ ስለዚህም እንደ አጋር ሊታዩ ይችላሉ፡፡"[35]

በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን የምታገኘውን ማንኛውንም ፖለቲካዊ
ዕድል ትክክለኛ ሕግን ለመርጃና ለማስፋፊያነት፣ ማኅበራዊ ጭቆናን ለመቃወ
ሚያነትና ክርስቲያኖችን ለመርዳት ልትጠቀምበት ይገባል፡፡[36] በመሆኑም መን
ግሥት የሕግ የበላይነትን ሲጥስ፣ ፍትሕን ሲያዛባ፣ ዜጎችን በፖለቲካ አመለካከ
ታቸው ብቻ ሲያስርና ሲያሳድድ፣ ሐሳብን የመግለጽ ተፈጥሮአዊ መብትን
በየሰበቡ ሲሸረሽር፣ ፍትሓዊ የሀብት ክፍፍል ሲጠፋ፣ የኑሮ ውድነቱ ሰማይ
ሲነካ ቤተ ክርስቲያን "አያገባኝም" የምትለው፣ ወይም "አያገባሽም" የም
ትባለው በምን መሠረት ነው? እውነቱን እንናገር ከተባለ፣ በዚህ ሰበብ ዳር
ቆሞ መመልከት ከአላዋቂነት በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም!

መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ሁሌም አጋሮች ሆነው አይኖሩምና የሚላ
ተሙበትና በተቃራኒ የሚቆሙበት ጊዜም ይኖራል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የመንግሥ
ትን ጥፋትና ቸልታ እየገለጠች የፍትሕ አቀንቃኝ ስትሆን መንግሥት በጭብ
ጨባ እንደማይቀበላት የሚጠበቅ ነው፤ ለውጥ ሲጀምር ነውጥ ይኖራልና፡፡
እንደ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ሊቈጠርባትም ይችላል፡፡ ጌታ ኢየሱስ መንግ
ሥቱ ከዚህ ዓለም እንዳልሆነች በመናገር ከምድራዊ ሥልጣን ራሱን ቢያር
ቅም፣ በወቅቱ የነበሩት የፖለቲካ ኀይሎች ማለትም የሮም ገዢዎችና የአይሁድ

ሸንነ ግን እርሱ በሚለው መንገድ ሊረዱትና ሊቀበሉት ፈጽሞ አልቻሉም:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት፣ እርሱ እያቋቋመ የነበረው አዲስ ሥርዐት ለዘመናት ተንሰራፍተው የቈዩትን ማኅበራዊ ግንኙነቶች በሙሉ የሚያፋልስ መሆኑ ስላሳ ሰባቸው ነበር::[37]

ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን የገሃነም ደጆች እንኳ እንደማያሸንፏት አለ መርሳት ነው፤ በመሆኑም ለእውነትና ለፍትሕ ትቁም እንጂ በየትኛውም ምድ ራዊ ኀይል አትሸነፍም:: ይልቁኑ ቤተ ክርስቲያን የምትሸነፈው ለእውነት መቆም ሲያቅታት፣ ኢፍትሐዊነትን ዐይታ እንዳላየ ስታልፍ፣ ለመሪዎቿ ምድ ራዊ ጥቅም በእውነት ላይ ስታመቻምች፣ ከመንግሥት ጋር ስትሞዳሞድ ነው፤ ታሪክም ያስተማረን ይህንኑ ነው:: ለእውነት የምትቆም፣ ለፍትሕ የምትሟገት፣ የአገር ኅሊናና ሞራል ጠባቂ፣ የድምፅ አልባዎች ድምፅ የምትሆን፣ ለእኩልነት፣ ለሰላምና ለነጻነት የምትታገል ቤተ ክርስቲያን አትሸነፍም:: መቼም!

## የሕግ ነገር

አንዳንድ መንግሥታት ለጥፋታቸው ሕጋዊ ከለላ ለመስጠትና ጥፋታቸውን የሚቃወም እንዳይኖር ገዳቢ ሕግ ያወጣሉ:: በዚህ ሁኔታ የሚወጣ ሕግ ኢፍ ትሐዊ የሚሆንበት ጊዜ ሞልቷል፤ ወይም ኢፍትሐዊነቱ አተረጓጐሙ (አፈጻ ጸሙ) ላይ ይሆናል:: ያኔ ሰዎች ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት ከመረጋገጡ በፊት እንደ ንጹሕ የመቈጠር መብታቸው ይጣሳል:: ፍርድ ቤት ያልወሰነባ ቸው ተከሳሾችም (ተጠርጣሪዎችም) በመንግሥት ከፍተኛ ባለ ሥልጣናትና መገናኛ ብዙኀን "ወንጀለኞች" እየተባሉ ሲጠቀሱ ይደመጣል::

ሕዝብን ለማስተዳደር የሚወጡ ሕግጋት ፍትሐዊ መሆን አለባቸውና ቤተ ክርስቲያን ኢፍትሐዊ ሕግጋት ሲወጡ ዝምታ አይጠበቅባትም:: ለምሳሌ፣ የናዚ ጀርመን አይሁዳውያንን የማሳደድ፣ የማሠቃየት፣ በመጨረሻም የማጥፋት ድርጊቱን ሕጋዊ ድጋፍ ሰጥቶት ነበር የሚፈጽመው:: በዚያን ጊዜ የነበሩ ክርስ ቲያኖች ግን አይሁዳውያንን ከሞትና ከሥቃይ ያስመልጡ ነበር፤ ሕጉን እየ ጣሱ:: ቦንሆፈርን እና ኮሪ ቴን ቡምን መጥቀስ ይቻላል:: ለዚህ ድርጊታቸው ግን ዋጋ ከፍለውበታል::

ምዕራባውያን መንግሥታት የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግሬስ (ANC) የሚ መራውን የእኩልነት እንቅስቃሴ በሽብርተኝነት ፈርጀውት ነበር፤ የኮምዩኒዝም መስፋፋት ሥጋት ለዚህ መነሻ ምክንያታቸው እንደ ነበር ይነገራል:: የእንግ ሊዝ ቤተ ክርስቲያን (አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን) ግን የአገሪቱን ሕግ ጥሳ ኤ ኤን ሲን ትደግፍና ትረዳ ነበር::[38] ያውም ቤተ ክርስቲያኒቷ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ሆና ሳለ::



ማርቲን ሉተር ኪንግ የዘር ልዩነትን መሠረት ያደረጉ ሕግጋትን ራሱ መጣስ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎችንም በማስጣስ ነበር ኢፍትሐዊነትን ማጋለጥ የቻ ለው:: እንደ እርሱ አባባል አንድ ሕግ ሕግ ሆኖ ስለ ወጣ ብቻ መከበር የለበ ትም:: ቅጣቱን ለመቀበል ወስኖ በደስታ ሕጉን መጣስ አስፈላጊ ሊሆን ይች ላል፤ ሕጉ ፍትሐዊና ትክክለኛ ካልሆነ::[39] ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግና ማን ዴላ ነጻነት የሚያሳጣውን፣ ጨቋኙንና በዘር ልዩነት ላይ የተመሠረተውን ሕግ ሕገ ወጥ ሕግ አድርገው ስለ ቈጠሩት ጥሰውታል:: ቅጣታቸውንም በደስታ ተቀብለዋል:: ቅዱስ አውግስጢኖስ ከዛሬ 1600 ዓመት በፊት እንደ ተናገረው "ትክክለኛ ያልሆነ ሕግ ጭራሹኑ ሕግ አይደለም::" የሕግ የበላይነትንና ሰዎች በሕግ ፊት ያላቸውን እኩልነት የሚጥስ ሕግ ከኢፍትሐዊነት ይመደባል::

ኢያሪኮዊቷ ረዓብ (ኢያሱ 2)፣ ግብፃውያኑ አዋላጆችም (ዘፀ. 1፥15-21) የራሳቸውን መንግሥት ተቃውመዋል እንጂ የተባሉትን ሁሉ በዝምታ የሚታ ዘዙ አልነበሩም:: ለዚህ አለመታዘዛቸውም በእግዚአብሔር ሲሸለሙ (ኢያሱ 6፥25)፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳውያኑ የእምነት ጀግኖች ጋርም የክብር ስፍራ ተሰጥ ቷቸዋል (ማቴ. 1፥5፤ ዕብ. 11፥31)::[40]

ሕጉን ለማስቀየር መታገልም ይቻላል:: ዊልያም ዊልበርፎርስ እና ተባ ባሪዎቹ የጸረ ባርነት ሕግ እንዲወጣ ("Amazing Grace" የተሰኘውን ፊልም መመልከት ይቻላል::)፣ ፋብሪካዎችና እስር ቤቶች ለሰዎች ምቹና ተስማሚ እንዲሆኑ ሲታገሉና በአናሳ ሕዝቦች ላይ የሚደረገውን የዘር ልዩነት ሲቃወሙ ነበር:: የእሑድ ሰንበትነትም ጸንቶ እንዲቀር ማድረግ ችለዋል::[41]

"ፍትሕ የጐደለውን ሕግ ለሚያወጡ፣ ጭቁና የሞላበት ሥርዐት ለሚ ደነግጉ ወዮላቸው! የተጨቈነውን ሕዝቤን ፍትሕ ለሚያዛቡ ... ወዮላ ቸው!" (ኢሳ. 10፥1-2 - አ.መ.ት)::

## መገዛት ምንድን ነው?

ከሁሉ በፊት ግን ክርስቲያኖች ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንት የመጸለይ ትእዛ ዝም ልዩ መብትም እንደ ተሰጠን ማወቅ አለብን (1ጢሞ. 2፥1-2):: ቤተ ክርስ ቲያን ለእነርሱ ስትጸልይ ባለሥልጣናት ኀይላቸውን በጥበብ በትክክል እንዲጠ ቀሙ ታግዛቸዋለች:: ከዚህ የተነሣ መሪዎች በአግባቡ ሲያስተዳድሩ ዜጎቻቸው ሰላማዊ ኑሮ መኖር ይችላሉ:: ይህ ደግሞ ወንጌል ለመስበክ ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታም ይፈጥራል:: ስለ ጸሎት ካነሣን ዘንዳ፣

> መሪዎቻችንን የመምረጥ ዕድሉ ባለበት አገር የምርጫ ድምፃች
> ንን እንነፍጋቸው እንደ ሆን እንጂ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ

> ስለ እነርሱ መጸለይንና ማሳየት የሚገባንን ከበሬታ መንፈግ ግን አንችልም:: እዚህ ላይ ሊታሰብበት የሚገባው ትልቁ ጉዳይ በጸሎት ሰበብ የቤተ ክርስቲያንን መድረክ ለፖለቲካ ወገናዊነት ማንጸባረቂያና ለፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ መሣሪያ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ነው::[42]

በተጨማሪም ፖለቲከኞቹን እግዚአብሔር እንዲመራ ከመጸለይ ባሻገር እግዚአብሔር የሚመራቸው አማኞች ፖለቲካው ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ ለምርጫም እንዲወዳደሩ ማበረታታት ወቅቱ የሚጠይቀው ነው::

አንዳንድ ሰባኪያን ግን ክርስቲያኖች ከመጸለይ በቀር መንግሥትን መቃወም እንደሌለባቸው ይሰብካሉ:: በዚህም ሳያበቁ፣ አማኞች ከመጸለይ ባሻገር መገዛት እንጂ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባል መሆን እንኳ እንደሌለባቸው እስከ መናገር ይደርሳሉ:: ይህ አመለካከት የመንግሥትን ሥልጣን ፍጹማዊ የሆነ ያስመስላል:: ሥልጣን ከእግዚአብሔር ቢመነጭም ካያያዝ ሊበላሽ እንደሚችል እነዚህ ሰዎች ሳይዘነጉት አልቀሩም:: ለዚህ አቋማቸው መነሻ የሚያደርጉት ሮሜ ምዕራፍ 13ን ሆኖ ይገኛል::

በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚ ፓርቲ አይደለችም:: በኢትዮጵያ ዐውድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የፖለቲካ ድርጅት አባላት ባይሆኑ ይመረጣል (ምዕመናንን አይመለከትም):: አለበለዚያ ሚዛናዊነታቸው አደጋ ላይ ይወድቃል፤ የተለያዩ ውስብስብ ችግሮችንና የጥቅም ግጭቶችንም ይፈጥራል:: ከዚህ የተነሣ መሪዎች የሚወስዱት የተሳሳተ ወይም ወገንተኛ ውሳኔ የቤተ ክርስቲያን ተአማኒነትን አደጋ ላይ ይጥላል::

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን እዚህ ውስጥ ይገኛሉ:: ለምሳሌ ትናንት ቄስ ጉዲና ቱምሳ የኦነግ አባል እንደ ነበሩና ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ወደ ውጭ አገር ሲሄዱ የኦነግንም መልእክት ይዘው እንደ ሄዱ በዚያው ጎራ የነበሩት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ይናገራሉ::[43] ዛሬም ቢሆን በገዢውም ሆነ በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባልነት የሚታሙ የቤተ እምነት መሪዎች መኖራቸው ይነገራል:: እነዚህ ሰዎች የፓርቲ አባልነቱ ከበለጠባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪነታቸውን እንዲያስረክቡ ይመከራሉ፤ የሚሻላቸውን መምረጥ አለባቸው:: ምናልባት ቤተ ክርስቲያን ሚዛናዊነት የማጣቷ እና የመሪዎች የፖለቲካ አድርባይነት ምክንያቱ ይህ ይሆን?

ለማንኛውም ሮሜ 13ን እንመልከት፤

> ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት ሹማምት መገዛት ይገባዋል፤ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ



> ሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው:: ስለዚህ በባለ ሥልጣን ላይ የሚያምፅ በእግዚአብሔር ሥርዐት ላይ ማመፁ ነው፤ ይህን የሚያደርጉትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ያመጣሉ:: ገዦች ክፉ ለሚሠሩ እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና:: ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትፈልጋለህን? እንግዲያስ መልካምን አድርግ፤ እርሱም ያመሰግንሃል፤ እርሱ ለአንተ መልካሙን ለማድረግ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና:: ነገር ግን ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ምክንያቱም ሰይፉን በከንቱ አልታጠቀም፤ ክፉ የሚያደርገውን ለመቅጣት የቍጣ መሣሪያ የሆነ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው:: ስለዚህም ቅጣትን በመፍራት ብቻ ሳይሆን፣ ለኅሊና ሲባል ለባለ ሥልጣን መገዛት ተገቢ ነው:: ግብር የምትከፍሉትም ደግሞ ለዚህ ነው፤ ባለ ሥልጣናቱ፣ በዚህ ተግባር ላይ የተሠማሩ የእግዚአብሔር አገልጋይ ናቸውና፤ ለእያንዳንዱ የሚገባውን ስጡ፤ ግብር ከሆነ ግብርን፣ ቀረጥ ከሆነም ቀረጥን፣ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ (ሮሜ 13፥1-7 - አ.መ.ት)

ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ለመንግሥት እንድንገዛ ሲነግረን፣ አለመቃወም እየነገረን ነውን? ክፍሉን በቀጥታ ከመተርጐም ይልቅ አንዳንድ ጥያቄዎችን በማንሣት ለመተርጐም መሞከሩን እመርጣለሁ፤

1. ለመንግሥት መገዛት መንግሥት የሚባለውን ተቋም መቀበል ማለት ቢሆንስ? ክርስቲያን በየጊዜው ሥልጣኑን የሚይዙትን ጌቶች ሳይሆን፣ መንግሥት የሚባለውን ሥርዐት መቃወም የለበትም:: መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚነግረን መንግሥትን የፈጠረው እግዚአብሔር ነውና መንግሥት የሚባል ተቋም እንዳይኖር ማሰብና መሞከር ጤና ማጣት ነው:: መንግሥት ከሌለ እንደ ሶማሊያ ነው የሚኮነው:: መንግሥት ከሌለ ወንጌልን በአግባቡ ማሠራጨት፣ በሰላም ወጥቶ መግባት፣ ሥራ ሠርቶ ቤተ ሰብን ማስተዳደር፣ ልጆችን ወልዶ ማሳደግ አስቸጋሪ ይሆናል፤ እውነት ነው! ስለዚህ ለመንግሥት ተገዙ ማለት የተቋሙን ሕልውና አትቃወሙ ማለት ብቻ ቢሆንስ?

2. በእርግጥም፣ "ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለም" (ቍ. 1):: ግና ለባለ ሥልጣን ተገዙ ማለት ዐልጋውን የያዘውን ወገን ሲደግፉ መኖር ማለት ነው? ሥልጣን ላይ ያሉት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠላቸው የሥልጣን ዘመን ሲያበቃስ? ቀጥለው ወደ ሥልጣን ከሚመጡት ጋር የእግዚአብሔር ይሁንታ አይኖርም?

ሥልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከሆነ፣ ዐፄ ኀይለ ሥላሴን የሾማቸው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ደርግንስ ያመጣው ማነው? ታዲያ 1966-67 ዓ.ም ብንኖር አቋማችን እንዴት ነበር የሚሆነው? ደርግ ተሸንፎ ኢሕአዴግ ሥልጣን የያዘበት 1983 ዓ.ም ላይ ማንን ደግፈን፣ ማንን ነበር የተቃወምነው? በዳዊትና በሳዖል መካከል ብንሆንስ? ሁለቱም የተሾሙት በእግዚአብሔር ቢሆንም ዳዊት የተተካው የመጀመሪያው ንጉሥ (ሳዖል) ኀላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ሥልጣኑን መልቀቅ ስለ ነበረበት መሆኑ አይዘነጋም።

3. መገዛት እንጂ መቃወም ካልቻልን እግዚአብሔርን ሁሌም የአሸናፊዎች ወገን እናደርገዋለን። ታዲያ የግፉአንስ ወገን ማን ነው? ደርግ ንጉሡን ሲቃወም የእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃዋሚ ነበር ማለት ነው። ሥልጣን ሲይዝስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚ ሆነ? ኢሕአዴግ ጫካ ሳለ፣ በእግዚአብሔር የተሾመውን ደርግን ሲቃወም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይቃወም ነበር ማለት ነው። አሸንፎ ሥልጣን ሲይዝ ግን፣ እርሱን መቃወም በተራው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደ መቃወም ከተቈጠረ፣ እግዚአብሔር የአሸናፊዎች ወገን፣ የአስገባሪዎች አምላክ፣ የጕልበተኞች ደጋፊ ነው ማለት ነው? ዋናው ነገር ማሸነፍ መሆኑ ነው? የእግዚአብሔር ፈቃድም የአሸናፊዎች ፈቃድ ነው ማለት ነው?

4. መንግሥት ራሱ የፈለጉትን ፓርቲ የማቋቋም፣ የመደራጀት፣ መንግሥትን የመቃወምና አሸንፎ ሥልጣን የመያዝ መብትን ለዜጎች ሰጥቶ ሳለ፣ ሰዎች መንግሥትን መቃወም እንደሌለባቸው መስበክ ከሕግ ውጭ አያደርግም? አንድ ሰው ክርስቲያን ስለ ሆነ ብቻ ይህን መብቱን ያጣል?

5. ለመንግሥት መገዛት (ባለ ሥልጣናትን መታዘዝ) ያለብን *በነገር ሁሉ* ነውን? ከእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ጋር የሚጋጭ ነገር ብንታዘዝስ? እንደ ሐዋርያት፣ "ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል" (የሐዋ. 5፥29) ልንል የምንችልበት ሁኔታ የለም? እነ ዳንኤል፣ ሐናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል ገዢዎችንና ሕግን መታዘዝን እምቢ አላሉምን? ታዲያ መገዛት የሚያስፈልገውን ያህል የማንገዛባቸው ነገሮችስ አይኖሩም? ይህ ምንባብ መንግሥት ፍትሕን፣ ነጻነትን፣ እኩልነትን፣ የሕግ የበላይነትን ሲጥስ "እምቢ" ከማለት ይከለክላል? እግዚአብሔርስ ከፈቃዱ ሲወጡ መንግሥታትን ይቃወም የለምን!?

6. "ተገዙለት" የተባለው ባለ ሥልጣን ክፉ አድራጊዎችን እንጂ መልካም አድራጊዎችን የሚያስፈራ እንዳልሆነ ተገልጿል (ቍ. 3)። እንዲህ ካልሆነስ? መልካም አድራጊዎችን እየበደለ፣ ክፉ አድራጊዎችን ቢሸልምስ? በቅንነትና በእውነት የሚሠሩ ተበድለውና ተገፍተው፣ ሙሰኞችና አድርባዮች ሲከብሩና ከፍ ከፍ ሲሉ ስናይስ መገዛታችን መቀጠል አለበት? የሂትለር፣ የስታሊን፣ የፖል ፖት፣ የኢዲ አሚንና የጋዳፊ ዐይነት መሪዎችስ እንዴት ሊታዩ ነው? ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ባለሥልጣናት መገሠጽና መቃወም የለባትም? እነዚህን መሪዎች መቃወም ነው ስሕተት የሚሆነው ወይስ አለመቃወም?



7. ግብር፣ ቀረጥ፣ ክብርና አክብሮት እንደሚጠበቅብን ተነግሯል (ቍ. 6-7)። መገዛት ማለት ግብር መክፈልና አክብሮት መስጠት ቢሆንስ? ታዲያ ይህ መቃወምን ይከለክላል?

8. "ከኀሊና የተነሣ ተገዙ" ማለት ምን ማለት ነው? ክርስቲያኖች የመንግሥት ነገረ ሥራ ከኅሊናቸው ጋር ሲጋጭ ምን ያድርጉ? ከገዛ ኅሊናቸው ጋር እየተጣሉ ለመንግሥት መገዛት አለባቸው?

9. "ኀጥኣን ከፍ ከፍ ሲሉ ሕዝብ ይጨነቃል" የሚለው የጠቢቡ ሰሎሞን አነጋገር ፖለቲካን ታሳቢ ያደረገ ነው። የክፉ መሪዎች ሥልጣን መራዘም አንዱና ዋነኛው ምክንያትም የመልካም ሰዎች ዝምታና ትኅትነት መሆኑ ግልጽ ነው። ታዲያ ጨካኝና ክፉ መሪዎችን አለመቃወም (በጸጥታ መገዛት)፣ በክፋታቸው እንዲቀጥሉ በተዘዋዋሪ ማበረታታት (መፍቀድ) አይሆንም? ዝምታችን ከመፍትሔው ይልቅ የችግሩ አካል አያደርገንም?

10. መንግሥትን በጸሎት እየተቃወሙ በተግባር መቃወምን መከልከል ግብዝነት አይሆንም? መቃወም መቃወም ነው። መንግሥት ጸሎታችንን ስለማይሰማብን በጸሎታችን ስሞታ እያቀረብንና በብርቱ እየተቃወምን (ልክ በቀደመው ሥርዐት ላይ ሲደረግ እንደነበረው)፣ ተግባራችንን ግን ስለሚያይብን "ጨዋ" መምሰል ክርስቲያናዊ ነው? ("አፉ ቅቤ፣ ልቡ ጩቤ" እንዲሉ!)

ምንባቡ፣ "ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትፈልጋለህን?" ማለቱ (ቍ. 3)፣ መንግሥትን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ እንድንኖር እንዳልተጠራን ያሳያል። ታዲያ በየተገኘው አጋጣሚ "ተገዙ፣ አትቃወሙ" በማለት በስብከት ከማስፈራራት እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ መጣሩ አይበጅም?

## ምን ይደረግ ታዲያ?

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር የሚኖራትን መስተጋብር በሚመለከት ማኒፌስቶ እንኳ እንደሌለን ይታወቃል፤ አካሄዳችን ውል አልባ ነው (ግን እስከ መቼ?)። ደርግ አማኞችን ሲቀጠቅጥ በመኖሩ አንዳንዱ፣ "አገሬ በሰማይ ነው" በማለት ስለ መንግሥት መስማት የማይፈልግ ሆኗል፤ ኮት የለበሱና ክራቫት ያሰሩ መነኮሳትን እያፈራን ለመሆኑ ማስረጃ ነው። ሌላኛው ወገን ደግሞ፣ "ነጻነት የሰጠን ይሄ መንግሥት ነው" በማለት መንግሥት ላይ ጥምጥም ያለ ይመስላል። እርግጥ ነው መንግሥት

ለሠራቸውና እየሠራቸው ላሉ መልካም ነገሮች ሁሉ መመስገን አለበት! እዚህ ላይ አንዳች ማመንታት ሊኖር አይገባም:: ጥያቄው ግን መንግሥት ሲያጠፋ ምን ይደረግ? የሚል ነው!

የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን የምትኖርበትን አገር መንግሥት በሚመለከት በጸሎት ሳትገደብ ተጨማሪ አቋሞች ሊኖሩአት ይገባል:: በተለይ መንግሥት ፍትሕን፣ ነጻነትንና መብትን ሲጥስ ቀጣዮቹ ሦስት አቋሞች እንደየ ደረጃቸው አስፈላጊ ይሆናሉ::

1. ለመንግሥት ጥያቄ ማቅረብ፣ ለምን እንዲህ ዐይነት ድርጊቶችን እንደሚፈጽም መጠየቅ፣ መናገር፣ መገሠጽ እንጂ የመንግሥትን ስሕተቶችና ውድቀቶች በቸልታ አለማለፍ፤

2. በመንግሥት ድርጊት ሰለባዎችን፣ ግፉአንን መከባከብ፣ የፖለቲካ እስረኞችን መጠየቅ፣ ቤተ ሰቦቻቸውን መጐብኘትና የሚያስፈልጋቸውን ርዳታና ድጋፍ (የገንዘብ፣ የጸሎት፣ የሥነ ልቡና) መስጠት፤

3. ይህም ሁሉ ሆኖ ለውጥ ካልተገኘ እንዳስፈላጊነቱ ከመንግሥት በተቃራኒ መቆምና መንግሥትን መቃወም::[44]

ስለዚህ መንግሥትን ሰላማዊውን መንገድ ብቻ በመምረጥ መቃወም ይቻላል! በአደባባይ ማውገዝን እዚህ ጋ በምሳሌነት መውሰድ እንችላለን:: ነገር ግን መንግሥትን መቃወም የግድ ተቃዋሚዎችን መደገፍ ማለት አለመሆኑን ማስተዋል ይጠቅማል:: በተጨማሪም በዚህ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ መንግሥትን ማሸነፍ ሳይሆን ነጻነት፣ ፍትሕ፣ እኩልነትና የሕግ የበላይነት እንዲያሸንፉ ማገዝ ነው::

ታሪክ እንደሚነግረን ባርነትን ለማስቀረት ክርስቲያኖች አድማ ማድረግንም ይጠቀሙ ነበር:: ሃና ሙር የተባለች አገልጋይ የጸረ ባርነት እንቅስቃሴን ለማገዝ "ጨዋ ሴቶች" በሻያቸው ውስጥ የዌስት ኢንዲስን ጨው እንዳይጠቀሙ ታሳድም ነበር:: በዚያን ወቅት የወንጌላውያን ክርስቲያኖች ትልቁ ዐቅማቸው በሕዝብ አስተያየት ላይ መልካም ተጽዕኖ ለማሳደር የተቻላቸውን ማድረግ ነበር:: በዚህም ጥረታቸው ከአንድ ትውልድ ባነሰ ዕድሜ ውስጥ ባርነትንና በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚደረግን ተጽዕኖ ለማስቀረት ችለዋል::[45]

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን መንግሥት ጉዳትን የሚያመጣና ከሕዝቡም ሆነ ከእግዚአብሔር ሓሳብ ጋር የሚጋጭ አካሄድን ሲከተል መክሮና አስጠንቅቆ የመመለስ ኀላፊነት አለባት:: ይህንን ኀላፊነቷን ግን በፍቅር፣ በትሕትናና መሥዋዕትነትንም በመክፈል እንጂ በኀይል ወይም በሰይፍ የማከናወን መብት አልተሰጣትም::[46] ድንጋይ ውርወራም የቤተ ክርስቲያን መንገድ አይደለም::



አፍሪካ ውስጥ መፈንቅለ መንግሥትና ጦርነት የሚበዛው ችግርን መፍታት የሚቻለው በኀይል መሆኑ ስለሚታመን ነው:: ችግርን በኀይል ከመፍታት የተሻለ አማራጭ መኖሩን የሚያምን ትውልድ ያስፈልገናል፤ ለዚህም አማኞች ኀላፊነት አለብን:: ግዴለሽ ለመሆን እግዚአብሔር ምርጫ አልሰጠንም!

ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ለፍትሕና ለምሕረት ለመቆም እንድትችል የተሰጡ፣ ደፋር፣ በመንፈስ የተሞሉ፣ ዕውቀትና መረዳት ያላቸው መሪዎች ሊኖሯት ይገባል:: በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትና የሚኖሩበትን ማኅበረ ሰብ በሚያስጨንቁት ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው መሪዎች ያስፈልጓታል::[47]

## ተግባራዊ የታሪክ ምስክር

ሰባኪዎቻችን እንደሚሉት ሳይሆን ነጻነትና እውነተኛ ዴሞክራሲ በሌሉበት ኮምዩኒስታዊ ስፍራ ያሉ ክርስቲያኖች ጸሎትንና ሰላማዊ እንቅስቃሴ በመጠቀም ለውጥ ያመጡበትን የቅርብ ጊዜ ታሪክ መጥቀስ ይቻላል::

> አረመኔውና ኮምዩኒስቱ ኤሪክ ሆኔከር የምሥራቅ ጀርመን ፕሬዚዳንት የነበሩበት ዘመን ነው፤ እ.ኤ.አ. 1989:: በላይፐዚግ ከተማ የነበሩ አራት አብያተ ክርስቲያናት በየሳምንቱ ሰኞ ሰኞ ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ የሚካሄድ የጸሎት መርሐ ግብር ጀመሩ:: ጸሎቱ በአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ሰባት ዓመት ቀደም ብሎ የጀመረ ነው፤ ስለ ሰላም ለመጸለይ:: መጋቢዎቹ በአንድ እጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ በሌላኛው ደግሞ ጋዜጣ በመያዝ የሉተራውያንን ነባር ዝማሬዎች በመዘመር ለተከበቡት ምሥራቅ ጀርመናውያን ተስፋንና የሕይወትን ትርጒም ለማሳየት ሞከሩ:: መጀመሪያ አካባቢ በጸሎቱ የሚካፈሉት እፍኝ የማይሞሉ ክርስቲያኖች፣ ሲበዛ ደግሞ ጥቂት ደርዘኖች ነበሩ::
>
> ቀስ በቀስ ግን የጸሎቱ ተሳታፊዎች ቍጥር እየጨመረ፣ የክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ተቃዋሚዎችንና የተራዜጎችን ትኩረት መሳብ ጀመረ:: ከእያንዳንዱ የጸሎት ስብሰባ በኋላ ተሰብሳቢዎቹ ሻማና ጥቅሶችን በመያዝ በጨለማው ጐዳና ላይ ተያይዘው ይጓዛሉ፤ ምቹ ፖለቲካዊ ተቃውሞ:: በመላ አገሪቱ ይካሄዱ የነበሩ የተቃውሞ ሰልፍ መሳይ ነገሮች ሁሉ የሚጀመሩት በዚህ መንገድ ነበር፤ በአምልኮ::
>
> ቀስ በቀስ፣ የምዕራቡ ዓለም የዜና ማሠራጫዎች ታሪኩን መዘገብ ጀመሩ:: በዚህ የተደናገጡት የኮምዩኒስቱ አስተዳደር ባለ ሥልጣናትም ሰላማዊውን ተቃውሞ እንዴት ማቆም

እንዳለባቸው መሟገት ጀመሩ:: ምስጢራዊ የጸጥታ ሠራተኞች አብያተ ክርስቲያናቱን መከበብና አንዳንዴም ተሳታፊዎቹን ማወክ ተያያዙት:: ነገር ግን በላይፐዚግ ከተማ ስብሰቡ እየጨመረ ሄደ፤ መቶዎች፣ ሺዎች፣ ከዚያም አምሳ ሺህ::

የቅዱስ ኒኮላይ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ዎንበርገር ሳይታሰብ ራሱን የዚህ እንቅስቀሴ መሪ ሆኖ አገኘው:: የጸጥታ ሠራተኞች በስልክ የግድያ ዛቻ እያቀረቡበትና በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙሪያ የቁጥጥር ጣቢያዎችን እያቋቋሙ እንኳ ሰላም መስበኩንና ስለ ሰላማዊ የተቃውሞ ዘዴዎች ተግባራዊ ምክሮችን መስጠቱን ቀጠለ::

በጥቅምት 9 ከሞላ ጐደል እያንዳንዱ ሰው ፖለቲካዊ ጫናው ጡዘት ላይ እንደሚደርስ ጠብቋል:: ቀኑ ምሥራቅ በርሊን የኮምዩኒስታዊቱን አገር አርባኛ ዓመት የምታከብርበት ስለ ነበር በላይፐዚግ የሚደረገው ሰልፍ እንደ ጠብ ጫሪነት ነበር የታየው:: የፖሊስና የጦር ኀይል ሠራዊት አባላት ወደ ላይፐዚግ በብዛት ገቡ፤ የምሥራቅ ጀርመኑ መሪ ኤሪክ ሆኔከርም ሰልፈኞቹ ላይ ተኩስ እንዲከፈት ትእዛዝ ሰጡ:: የላይፐዚግ ሉተራን ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ እልቂት እንደሚኖር አስጠነቀቁ፤ ሆስፒታሎች የአስቸኳይ ጊዜ ሕክምና መስጫ ክፍሎቻቸውን ነጻ አደረጉ፤ አብያተ ክርስቲያናትና ቲአትር ቤቶች ፈጣን ከለላ ለሚፈልጉ ሰልፈኞች በሮቻቸውን ክፍት አደረጉ::

በቅዱስ ኒኮላይ ቤተ ክርስቲያን የሚካሄደው ጸሎት ሰዓቱ ሲደርስ ሁለት ሺ የፓርቲ አባላት እየተንጋጉ በመግባት ቦታ ያዙ:: በኋላ *ክርስቲያን ሴንቸሪ* የተባለው ጋዜጣ እንደ ዘገበው ፕሮግራሙ ለፓርቲ አባላቱም ከእንቅልፍ መባነኛ ነበር የሆነላቸው:: ጉባዔውን ለመረበሽ ታስቦ በጉባዔው እንዲካፈሉ የተደረጉ የፓርቲ አባላት ቤተ ክርስቲያን እውነትም ለሰላማዊ ለውጥ እየሠራች እንደ ነበር አስተዋሉ::

ወታደሮቹ ለምን ተኩስ እንዳልከፈቱ ማንም አያውቅም:: ሚካኤል ጎርባቾቭ ራሳቸው ስልክ ደውለው ሆኔከርን ማስጠንቀቃቸው ይነገራል:: ሠራዊቱ በሕዝቡ ብዛት በመዋጡ ምክንያት መሆኑንም የሚናገሩ አሉ:: በመጨረሻ 70,000 ሰዎች በላይፐዚግ መኻል ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ:: በሚቀጥለው ሰኞ 120,000 ሆኑ:: ከሳምንት በኋላ 500,000 ለሰልፍ ወጡ፤ ከመላው የከተማዪቱ ነዋሪ ጋር የሚመጣጠን ቁጥር::



> ኅዳር ውስጥ እጅግ ከፍተኛው ሰልፍ ተደረገ:: ምሥራቅ ጀርመን ውስጥ 1 ሚሊዮን ሰዎች ሰላማዊ ተቃውሞ አደረጉ:: ኤሪክ ሆኔከር ሥልጣን ለቀቁ:: በኅዳር 9 ማንም ያልገመተው ነገር ተከሰተ፤ በተጠላው የበርሊን ግንብ ላይ ወደ ምዕራብ በርሊን መሻገሪያ ተከፈተ:: ግንቡን ለመሻገር የሚሞክርን የትኛውንም ሰው ተኩሰው እንዲገድሉ ትእዛዝ የተሰጣቸው ጠባቂዎች ዐይናቸው እያየ ምሥራቅ ጀርመናውያን ሻማ ይዘው እየጎረፉ መንግሥትን ሲጥሉ የአንድም ሰው ሕይወት አልጠፋም::
>
> ... ምሥራቅ ጀርመናውያን እነዚያን ቀናት እንደ ተአምራት ይቈጥሯቸዋል:: "ጸሎት ተራሮችን ቢያንቀሳቅስም ባያንቀሳቅስም፣ የላይፐዚግን ሕዝብ አንቀሳቅሷል" በማለት *ኒው ሪፐብሊክ* የተሰኘው ጋዜጣ ዘግቧል:: ቀጥሎም፣ "'እምላካችን ብርቱ መጠጊያችን' በማለት ሲዘምሩ መስማት ብቻ እንድታምኑት ያደርጋችኋል" ሲል ጽፏል:: ከጥቅምት 9 መነሣሣት ከጥቂት ሳምንት በኋላ፣ በላይፐዚግ ጐዳና ላይ ትልቅ የጽሑፍ ሰሌዳ ታየ፤ "ቤተ ክርስቲያን፣ እናመሰግንሻለን!" የሚል::[48]

ወደ አገራችን ስንመለስ አሁን ያለው ነጻነት በቀደሙት ሥርዐቶች ከነበረው ነጻነት የተሻለ መሆኑን መካድ አይቻልም:: ይህንንም መጻፍና ማሳተም የተቻለው ለዚህ ነው:: መንግሥት ይህን ነጻነት በማክበሩ መመስገን አለበት፤ ከልከኛው ስፍራ ግን በብዙ ኋላ ቀርተናል:: ስለዚህ ከዚህ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ እንዳንሄድ ነፍጥ ከሚያነሡ ኀይላት መራቅ ለሰላም አስተዋጽኦ ማድረግ ነው:: ሕገ መንግሥቱ በሚያዘው መሠረት በነጻና ገለልተኛ ምርጫ ብቻ መንግሥታዊ ሥልጣን የሚተላለፍበትን አካሄድ መደገፍም የእያንዳንዱ አማኝ ዜጋ ኀላፊነት ነው::

በዚህ ሁሉ መኻል ግን የሰላም፣ የፍትሕና የእኩልነት ጠበቃ መሆንና ለዚህ መንቀሳቀስ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ መሆኑ መዘንጋት የለበትም:: ስለዚህ መንግሥት ልማትን ሲሠራ ማመስገን ብቻ ሳይሆን፣ ጥፋትን ሲፈጽም ተግሣጽን ማስተላለፍም ጥሪዋ ነው:: በደልና ግፍ የተንሰራፋበትን አመራርም ሆነ አሠራር ማወደስ ሳይሆን መገሠጽ አለባት:: ይህም፣ ሕይወትን መሥዋዕት እስከ ማድረግ የሚዘልቅ ተጋድሎንና የማይገለባበጥ ክርስቲያናዊ አቋምን ይጠይቃል:: ታዲያ የምድራችን ቤተ ክርስቲያን ለፍትሕ፣ ለነጻነት፣ ለሰብአዊ መብትና ለሕግ የበላይነት መከበር በለሆሳስ እንኳ ትናገር ይሆን? ለዚህስ የምትመሰገንበት ዘመን ይመጣ ይሆን?

ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች ... በኢትዮጵያም ትሁን!

## ማስታወሻ

1. Nelson Mandela, *A Long Walk to Freedom* (London: Abacus, 2007), 239-243.
2. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 620።
3. Fidel Castro, *My Life* (London: Penguin Books, 2008), 156.
4. Clayborne Carson, *The Autobiography of Martin Luther King, Jr.* (London: Abacus, 2008), 15.
5. Eric Metaxas, *Bonhoeffer - Pastor, Martyr, Prophet, Spy: A Righteous Gentile Vs. The Third Reich* (Tennessee: Thomas Nelson, 2010), 315.
6. ኤልያስ በቀለ፤ *ክርስቲያን እና ፖለቲካ፡ በፖለቲካ ሂደት ውስጥ የሚኖረው የቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያኖች ተሳትፎ* (አዲስ አበባ፣ ኤስ አይ ኤም፣ 1996 ዓ.ም) ገጽ 26።
7. Carson, *Autobiography*, 18.
8. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 77-78።
9. Metaxas, *Bonhoeffer*, 81.
10. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ* (አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1964 ዓ.ም) ገጽ 202-206።
11. Diarmaid MacCulloch, *A History of Christianity: The First Three Thousand Years* (London: Penguin, 2009), 982-4.
12. Metaxas, *Bonhoeffer*, 260.
13. Carson, *Autobiography*, 179.
14. ኤልያስ በቀለ፣ *ክርስቲያን፣* ገጽ 55።
15. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 30።
16. ሪፖርተር ጋዜጣ፣ የኅዳር 20፣ 2004 ዓ.ም እትም።
17. http://globalvoicesonline.org/2011/12/01/ethiopia-homosexuality-debate-arises-as-ethiopia-hosts-aids-conference/ መጋቢት 2004 ዓ.ም.
18. Nelson Mandela, *Nelson Mandela by Himself: The Authorised Book of Quotations* (Johannesburg: Macmillan, 2011), 183.
19. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 78።
20. Metaxas, *Bonhoeffer*, 241.
21. Mandela, *Long Walk*, 750.
22. ሮበርትሰን ማኩሌከን (ተርጓሚ ገበየሁ አየለ)፤ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ ምግባር፡ የመግቢያ ሐሳቦች* (አዲስ አበባ፣ ኤስ አይ ኤም፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 605።
23. Mandela, *Long Walk*, 751.



24. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 751።
25. Metaxas, *Bonhoeffer*, 192.
26. ዝኒ ከማሁ፣ 681።
27. Philip Yancey, *Finding God in Unexpected Places* (Colorado Springs: WaterBrook Press, 2008), 160.
28. እ.ኤ.አ በ1974 በስዊዘርላንዷ ከተማ ሉዛን የተካሄደ 150 አገራትን የወከሉ አብያተ ክርስቲያናት የተገኙበት የ10 ቀናት ስብሰባ ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የወንጌልን ሥርጭት ኮንግሬስ (International Congress on World Evangelism) ተብሎ ይታወቃል። በታዋቂው ወንጌላዊ ቢሊ ግራሃም ጥሪት የተገኙት 2400 ተሰብሳቢዎች በሌላኛው ዕውቅ ወንጌላዊ ጆን ስቶት የተረቀቀ፣ ወንጌልን በዓለም ስለ ማሠራጨት ለማቀድ፣ ለመጸለይና ለመሥራት ቃል የተገባበትን የቃል ኪዳን ሰነድ አጽድቀዋል። ይህም "የሉዛን ቃል ኪዳን" ተብሎ የሚታወቀው ሰነድ ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና ኀይል፣ ስለ ክርስቶስ ልዩታ (uniqueness)፣ ስለ ወንጌል ሥርጭት፣ ስለ ክርስቲያን ማኅበራዊ ኀላፊነት የሚያትቱ አንቀጾች አሉት።
29. Thom S. Rainer, *The Book of Church Growth: History, Theology and Principles* (Nashville, Tennessee: Broadman Press, 1993), 78-79.
30. Yancey, *Finding*, 82-3.
31. ማኩሌከን፤ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣* ገጽ 578።
32. Yancey, *Finding*, 153.
33. ማኩሌከን፤ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣* ገጽ 581።
34. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 588።
35. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 569።
36. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 591።
37. ኤልያስ በቀለ፤ *ክርስቲያን፣* ገጽ 10።
38. MacCulloch, *History*, 982-983.
39. Carson, *Autobiography*, 194.
40. ማኩሌከን፤ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣* ገጽ 615-616።
41. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 570።
42. ኤልያስ በቀለ፤ *ክርስቲያን፣* ገጽ 27።
43. ዳንኤል ተፈራ ጂ.፤ *ዳንዲ የኔጋሶ መንገድ* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም) ገጽ 109-10።
44. Metaxas, *Bonhoeffer*, 153-155።
45. ማኩሌከን፣ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣* ገጽ 571።
46. ኤልያስ በቀለ፣ *ክርስቲያን፣* ገጽ 26።
47. ማኩሌከን፣ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣* ገጽ 593-594።
48. Yancey, *Finding*, 178-181.

# “ተዘልሎ መኖር”?

ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ጥቅሶች መካከል በርካታ ሰዎች የተለያዩ ዐይነት ጥቅሶችንና አገላለጾችን ይወድዳሉ:: የእኔ ምርጫ፣ “ተስፋ ስላለህ ተዘልለህ ትቀመጣለህ” የሚለው ነው (ኢዮብ 11፥18):: ይህንን ክፍል ሌሎች ትርጉሞች “በመተማመን ትኖራለህ” እና “ተደላድለህ ትቀመጣለህ” በማለት ይፈቱታል:: “ተዘልሎ መኖር” የሚለው ሐረግ በመሳፍንት 18፥7 ላይም ይገኛል:: ይህንን ደግሞ አዲሱ መደበኛ ትርጉም “ያለ ሥጋት በጸጥታ” መኖር በማለት ይገልጸዋል:: በ1997 ዓ.ም. የታተመው አዲስ ትርጉም ደግሞ ተዘልለው ስለሚኖሩ ሰዎች ሲያብራራ “በሰላም የሚኖሩ”፣ “ከማንም ጋር ሳይጋጩ ጸጥ ባለ መንፈስ የሚኖሩ ሰላም ወዳዶች”፣ “ከማንኛውም ሕዝብ ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው ... በመራቅ ተገልለው” የሚኖሩ በማለት ያብራራል::

ይህንን ተዘልሎ የመኖር ተስፋ ከኢዮብ ወዳጆች አንደኛው ነው ለኢዮብ በመንገር የሚያስጎመጀው፤ በእርሱ አመለካከት ኢዮብ ያልተገለጠ ኀጢአት ነበረበትና እርሱን መተው ከቻለ ተዘልሎ የመኖር መብት እንዳለው ያስገነዝበዋል:: ኢዮብ ደግሞ ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ ሰው እንደ ነበር ራሱ እግዚአብሔር መስክሮለታል:: ታዲያ ሁሌም ተዘልሎ የመኖር መብት አለው ማለት ነው?

ኢዮብ በተለያዩ አቅጣጫዎች - በወዳጆቹ፣ በደረሰበት ኀዘንና በሕመሙ የስንግ የተያዘ “ምስኪን” ሰው ነበር:: ሕመሙና ቤተ ሰቦቹን ማጣቱ ብቻ ሳይሆን፣ አእምሮውም በፈታኝ መንትያ ሓሳቦች ተወጥሯል:: ፊሊፕ ያንሲ እንደሚሉት፣

> እግዚአብሔርን ቢክድ፣ በእግዚአብሔር መልካምነት ላይ ያለው በዐለት ላይ የተመሠረተ እምነቱ ሊናድበት ሆነ፤ ይህ ደግሞ የሕይወቱ ዋነኛ ዕሴት ነው:: ሥቃይና መከራውን መቀበል የተገባው እንደ ሆነ ቢያምን ደግሞ እስከ ዛሬ ቅንና መንፈሳዊ ሕይወት መምራቱን ሊክድ ሆነ፤ ለዚህ ዐይነቱ ዘግናኝ ቅጣት የሚዳርገው ምንም ዐይነት ጥፋት ያልሠራ ንጹሕ ሰው መሆኑንም ያምናል:: ወዳጆቹ በጥሩና በክፉ መካከል ያለውን አስከፊ ጦርነት ያስረዳሉ:: ኢዮብ ግን በመልካምና በመልካም መካከል በሚካሄድ እጅግ አስከፊ የሞራል ፍልሚያ ተወጥሯል::[1]



ለዚህ ሰው ነው እንግዲህ፣ “ተስፋ ስላለህ ተዘልለህ ትቀመጣለህ” የተባለለት! ለመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ የኢዮብ “ጠላት” ማነው? ኢዮብን እዚህ ውስጥ ምን ከተተው? ፊሊፕ ያንሲ ይህን ያስረዳሉ፤

> ሰይጣን ከምዕራፍ 2 በኋላ በፍጹም አልተጠቀሰም:: ምክንያቱም የእርሱን አመለካከት የሚያራምዱለት የኢዮብ ወዳጆች ባሉበት ሁኔታ ሰይጣን መገኘት አያስፈልገውም:: እንዲያውም የመጽሐፉ አስደናቂ (ሆኖም የተሳሳተ) ነገረ መለኮት የተገኘው ከእነዚሁ ስለ እግዚአብሔር ከሚከራከሩ ሰዎች ነው:: በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ተቈጥቶ ዝም አሰኝቷቸዋል::[2]

ታዲያ ኢዮብ የት ነው “ተዘልሎ” የተቀመጠው? ማንም ሳይደርስበት፣ ምንም ክፉ ሳይነካው መኖር ተችሎታልን? ችግሩስ የጀመረው እርሱ በማያውቀው ሁኔታ ስለ እርሱ ሕይወት ሰይጣንና እግዚአብሔር ሲነጋገሩ አይደለምን?

እስቲ በሰይጣንና በእግዚአብሔር መካከል የተካሄደውን ውይይት እንመልከት፤ “ከዕለታት አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፤ የአምላክ ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም መጡ፤ ሰይጣንም ደግሞ በመካከላቸው መጣ:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን፣ ‘ከወዴት መጣህ?’ አለው:: ሰይጣንም፣ ‘ምድርን ሁሉ ዞርሁአት፤ በእርስዋ ተመላለስሁ’ ብሎ ለእግዚአብሔር መለሰ:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን፣ ‘በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም’ አለው” (1፥6-8):: ሮናልድ ደን እንዲህ ይላሉ፤

> እስቲ አንዴ ቈዩ! የኢዮብን ስም ያነሣው ለካ ሰይጣን አልነበረም፤ እግዚአብሔር ነው:: ኢዮብ ላይ ሊመጡ ያሉት መከራዎች ሁሉ የመጡት እግዚአብሔር ስለ እርሱ ይኵራራ ስለ ነበር ነው:: ይሄ ነገር ምናልባት እግዚአብሔር ከሰይጣን ጋር ወደፊት በሚያደርገው ውይይት ውስጥ ስሜን እንዳይጠቅስ እንድጠይቀው ያደርገኛል::[3]

እግዚአብሔር ሰይጣንን በማስጐምጀት ብቻ አልተወሰነም፤ ኢዮብ በጣም በፈለገው ጊዜም ሊገኝለት አልቻለም:: “እርሱን ወዴት እንዳገኘው ምነው ባወቅሁ! ... እነሆ፣ ወደ ፊት እሄዳለሁ፣ እርሱም የለም፤ ወደ ኋላም እሄዳለሁ፣ እኔም አላስተውለውም፤ ወደሚሠራበት ወደ ግራ ብሄድ አልመለከተውም:: በቀኝም ይሰወራል፣ አላየውምም” (23፥3፣ 8-9):: በፈተናና በጭንቅ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔርን ማጣትን ያህል የከፋ ነገር ይኖር ይሆን? እግዚአብሔር ግን ራሱን ከአማኙ የሚሰውርበት ወቅት አለ:: “የእስራኤል አምላክ መድ

ጎኒት ሆይ፤ በእውነት አንተ ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ" በማለት መጽሐፍም ይነግረናል (ኢሳ. 45፥15)። በሮናልድ ደን አገላለጽ፣

> ሰይጣን በዚህ ታሪክ ውስጥ አናሳ ሚና ነው የተጫወተው። በሽታውን ያመጣው ሰይጣን ቢሆንም፣ በኢዮብ አስደናቂ ሕይወት ላይ ትኩረት ሰቦ ነገሩን ሁሉ የጀመረው እግዚአብሔር ነው። ኢዮብም ቢሆን ለተፈጠረው ነገር ሰይጣን ኀላፊነቱን እንደሚወስድ መናገር ይቅርና ስሙን እንኳ አልጠቀሰም። እንደ ቅዱስ አውግስጢኖስ ግንዛቤ ኢዮብ፣ "እግዚአብሔር ሰጠ፤ ዲያብሎስ ነሣ" አላለም። የኢዮብ መጽሐፍ በልዝብነት እጅ የመስጠት ታሪክ አይደለም፤ የጠንካራ ተጋድሎ ... ታሪክ ነው። የኢዮብም ፍልሚያ ከዲያብሎስ ጋር አልነበረም፤ ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ።[4]

እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች ሁሌም በጠሪያቸው እግዚአብሔርና ሊያገለግሉት በተጠሩት ሕዝብ መካከል ሲጨመቁ እንደሚኖሩ ከዚሁ መረዳት አይከብደንም።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ኢዮብን ሊያጽናኑት የመጡት ወዳጆቹ ለአፍታ እንኳ ዕረፍት ሊሰጡት አልቻሉም። ስብከታቸው ሰላም የነሣው ደግሞ እርሱን ብቻ ሳይሆን በቦታው የነበረውን ሌላኛውን ሰው፣ ኤሊሁንም ነበር። ይህን ሁሉ እያዩና እየሰሙ እንዴት ዝም ማለት ይቻላል? የኢዮብ ወዳጆች በአጠቃላይ እውነትነቱ የሚያውቁትን አሠራር ሁሉ ያላግባብ እየመዘዙ ኢዮብ ላይ በመሰንዘር ሲጠዘጥዙት ኤሊሁ በዝምታ ለማለፍ ታግሷል። አሁን ግን ሊፈነዳ ደረሰ። ስለዚህ ሽማግሌዎቹን በጨኸት አቋርጦ ጕልማሳው መናገር ጀመረ፡ "... በውስጤ ያለውም መንፈስ ገፋፍቶኛል። ውስጤ እንደ ተከደነና መተንፈሻ እንዳጣ የወይን ጠጅ፣ ሊፈነዳ እንደ ተቃረበም አዲስ የወይን ጠጅ አቁማዳ ሆኖአል። ተናግሬ መተንፈስ አለብኝ" አለ (32፥18-20 - አ.መ.ት)።

ከዚህ ፉከራ በኋላ ግን እርሱም መልካም ቃል ሊወጣው አልቻለም። ኢዮብ ገላውን በገል እስኪፍቅ እንደ ተሠቃየ እያየ፣ ምራቁን እስኪውጥ ድረስ ፋታ እንዳጣ እያወቀ የማጽናኛ ቃል መናገር አልሆነለትም። ያውም፣ "ኢዮብ እስከ ፍጻሜ ድረስ ምነው በተፈተነ ኖሮ!" በማለት አፉን ሞልቶ ለመናገር ደፈሯል (34፥36)። ከዚህ በላይ ኢዮብ እንዴት መፈተን ነበረበት? የትኛውስ ሰብአዊ ፍጥረት በኢዮብ ላይ ይህንን የመመኘት መብት አለው? ከነፍሱ በቀር ምን የቀረለት ነገር አለ? ሰይጣንስ ቢሆን፣ "ሕይወቱን ብቻ አትንካ" አይደል የተባለው? ለመሆኑ ኤሊሁ ከሌሎቹ የኢዮብ ወዳጆች የተለየ (የተሻለ) ምን ተናገ



ሯል? ኋላም ቢሆን እግዚአብሔር እንደ ሌሎቹ የኢዮብ ወዳጆች አልገሠጸውም፤ አላመሰገነውምም። ኢዮብም ምንም ምላሽ አልሰጠውም (ከነመኖሩም ቁብ ያለው አልነበረም ማለት ነው?)።

እግዚአብሔር ሲገለጥ ደግሞ የሚናገረው ስለ ሌላ ነገር ነበር፤

> ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ የት ነበርህ?
> በእርግጥ የምታስተውል ከሆንህ፣ ንገረኝ።
> ካወቅህ፣ መጠኗን ለይቶ ማን ወሰነ?
> በላይዋስ መለኪያ ገመድ የዘረጋ ማን ነው?
> (38፥4-5 - አ.መ.ት)

ሙሉውን ምዕራፍ ስናነብ እግዚአብሔር ስለ ባሕር፣ ደመና፣ ማዕበል፣ ንጋት፣ ብርሃን፣ በረዶ፣ መብረቅ፣ ዝናብ፣ የከዋክብት ከምችት፣ የተለያዩ እንስሳትና ታላቅነቱን ስለሚገልጡ ነገሮች ሲናገር ነው የምናገኘው። እግዚአብሔር ጥያቄዎችን እየመለሰ ሳይሆን፣ ራሱ እየጠየቀ ነበር። ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለው ነገር የሚናገር ይመስላል፤ ነገር ግን በዚያን የውጥረትና የፈተና ወቅት ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ከማሰብ፣ ከማስታወስና ከማሰላሰል የተሻለ ምን መፍትሔ ሊያገኝ ይችላል!?

ነገር ግን በሁለት ወገን ተወጥሮ መኖር የእግዚአብሔር ሰው መለያ ይሆን እንዴ? ሙሴም ተመሳሳይ ትግል ነው የገጠመው።

ሙሴ ለእስራኤላውያን አስቦ ግብፃዊውን ሲገድል፣ "ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር። እነርሱ ግን አላስተዋሉም" (የሐዋ. 7፥25)።

ሙሴ ወንድሞቹ እርስ በርሳቸው ሲጣሉ እንኳ ሊያስታርቃቸው በመሞከሩ "ያጨበጨበለት" አልነበረም (ሙሴ "የራሳቸው ጉዳይ!" ማለት ለምን አልቻለም?)። ለዚህ ተቆርቋሪነቱ ያገኘው ምላሽ ልብ የሚሰብር ነበር። አንደኛው ዕብራዊ፣ "'አንተን በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማን ነው? ወይስ ትናንትና የግብፁን ሰው እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትወዳለህን?' ብሎ ገፋው" (ቍ. 26-28)፤ አዲሱ መደበኛ ትርጕም፣ "ገፈተረው" ይላል (ተሳስቶ አንገበቱው ይሆን እንዴ?)።

የተከበረውን "የፈርኦን የልጅ ልጅ"፣ የባሪያ ልጅ ገፋው! ያውም መልካም ካደረገላቸውና ከሚያስብላቸው ባሮች መካከል አንዱ!

ሙሴ ይህንን ሰው ምንም ማድረግ ይችል ነበር! ዐቅምን፣ ኀይልንና ሥልጣንን በሚመለከት ይህ ዕብራዊ ከሙሴ ጋር ሲተያይ እንደ ሞተ ውሻ

ነበር! ሙሴ የሚታገለው ግን ለዚሁ ሰው ነበር፡፡ ሊያድነው የሚፈልገው ሰው አዳኙን ገፋው (ጌታ ኢየሱስ ትዝ አለኝ)፡፡ ሙሴ "ተዘልሎ እንዳይኖር" እግዚአ ብሔር በልቡ እሳት አስቀምጦ ዕረፍት ነስቶታል፡፡ ጥሪውን ካልኖረ እግዚአብ ሔር ፋታ እንደማይሰጠው ያውቃል፤ ተዘልሎ መኖር አይችልም፡፡ ጥሪውን እንዳይኖር ደግሞ የተጠራላቸው ሰዎች ይገፉታል! ምን ይሻላል?

ለትልቅ ዓላማ እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች አንዳንዴ እግዚአብ ሔር ከሰጣቸው የሌለ የሚመስልበት ሁኔታ ይፈጠራል! ሙሴ ከዚህ ክስተት ጀምሮ በምድረ በዳ ለ40 ዓመት በእረኝነት አሳልፏል፡፡ በቤተ መንግሥት የኖ ረው፣ ከክቡራትና ክቡራን ጋር ትከሻ ለትከሻ እየተገፋፋ የሚውለው ሰው የሚ ስቱ አባት ተቀጣሪ እረኛ ሆነ፡፡ እዚያም "ተዘልሎ" እንዳይኖር ግን እግዚአብ ሔር መጣ፤ ጠራው፡፡

ከላይ ከቤተ መንግሥት ክብርን አስጥሎ ያስወጣው ጥሪ እዚህ ታችም ተከተለው!

ጥሪውን ተቀብሎ ሲወጣም ልጁ አልተገረዘምና እግዚአብሔር ሊገድ ለው ፈለገ (ዘፀ. 4፥24-26)፡፡ ይህ ነገር እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ ላይ ይበ ልጥ እንደሚጠነክር አያሳየን ይሆን? "እግዚአብሔር ወዳጆቹን እንዴት እንደ ሚይዛቸው ሲታይ፣ ብዙ ወዳጆች የሌሉት መሆኑ አያስገርምም" በማለት አንድ ሰው ተናግሯል፡፡

ከእንደዚህ ዐይነት (በእግዚአብሔርና በሰዎች ተወጥረው ከተያዙ) ሰዎች ነቢዩ ኤርምያስ ሌላኛው ነው፡፡ ኤርምያስ የራሱን መንገድ ለመሄድ ነጻ ነት አልነበረውም፡፡ በትዳር እንኳ እንዳይጸናና እንዳያገባ እግዚአብሔር ከልክ ሎታል፤ ሕዝቡ ደግሞ ሥራዬ ብሎ እያንዳንዱን እርምጃውን ሲሰልለው ይው ላል፡፡ መውደቁን የሚጠብቁ ወዳጆችም ነበሩት፡፡ እርሱ ግን መውደቁን እየጠ በቁ እንኳ፣ "የሰላሜ ሰዎች" ይላቸዋል (ኤር. 20፥10)፡፡ ሆኖም እያንዳንዱን ድርጊቱን በክፉ ስለሚተረጒሙበት ርስቱን ለመቀበል ሲሄድ እንኳ ወደ ባቢሎ ናውያን ልትኮበልል ነው ተብሎ ለእሥር ተዳርጓል (37፥12-15)፡፡

"ቃልህ ተገኘቷል፤ እኔም በልቼዋለሁ፤ ... ቃልህ ሐሤትና የልብ ደስታ ሆነኝ" (15፥16) ሲል የነበረው ነቢይ ካለፈበት ምሬት የተነሣ መመረር ጀመረ፡፡ "እናቴ ሆይ፤ ወዮልኝ! ለምድር ሁሉ የክርክርና የጥል ሰው የሆንሁትን ወለድ ሽኝ፡፡ ለማንም አላበደርሁም፤ ማንም ለእኔ አላበደረም፤ ነገር ግን ሁሉ ይረግመ ኛል" በማለት ምሬቱን ገልጧል (15፥11)፡፡ ከአስደሳች የአገልግሎት ዝግጅት በኋላ አገልግሎቱ ሲጀመር ምሬት ተከተለ፡፡ "አልቃሻው ነቢይ" እስኪባል ደረሰ፡፡ ካላበደረ፣ ካልተበደረ ከሰዉ ጋር ምን አጣላው? የእግዚአብሔር ጥሪ!



ኤርምያስ በተለያየ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኧል፤ ካገኛቸው ምላ ሾች አንዱን ማወቅ ትፈልጋላችሁ? "ከእግረኞች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደ ክሙህ፣ ከፈረሶች ጋር መታገል እንዴት ትችላለህ? በሰላምም ምድር ታምነህ ብትቀመጥ፣ በዮርዳኖስ ትዕቢት እንዴት ታደርጋለህ?" (12፥5)፡፡ ምን ማለት ይሆን?

> "እንዲህ ዐይነት አልቃሻ ሕፃን አትሁን ኤርምያስ፡፡ ይህ መጥፎ ነው ብለህ ታስባለህ? ገና ይብሳል፡፡ ማቆም ትፈልጋለህ? ገና መቼ ጀመርከውና!?"
>
> የኤርምያስ ከሁሉ የከፋ ትግሉ መልእክቱን ከማይቀበሉ ትና ሊገድሉት ከሚፈልጉት ዐንገተ ደንዳና ሕዝቦች ጋር አልነበ ረም፤ ከጠራው ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ፡፡[5]

ለምን ታዲያ ሁሉን ችላ ብሎ በዝምታ ተዘልሎ አይኖርም? እርሱም ሳያስበው የቀረ አይመስለኝም፡፡ ግን እንዴት አድርጎ!? "የእግዚአብሔርን ስም አላነሣም፤ ከእንግዲህ ወዲህም በስሙ አልናገርም ብል በዐጥንቶቼ ውስጥ እንደ ገባ እንደሚነድድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ፤ ደከምሁ፤ መሸከምም አልቻ ልሁም" በማለት ተናግሯል (20፥9)፡፡ ስለ እግዚአብሔር ባይናገር ውስጡ የሚ ፈጠረውን ዕረፍት የሚነሣ ስሜት ኤርምያስ በትክክል ገልጦታል፡፡ ተዘልሎ እንዳይኖር ዐጥንቶቹን ሁሉ የሚያነድ እሳት ውስጡ አለ!

ሕዝቡስ ይቀበሉት ይሆን? ከባቢሎን ምርኮ የተረፉት እስራኤላውያን በሽሽት ወደ ግብፅ መሄድ ፈለጉና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲነግራቸው ነቢዩ ኤርምያስን ጠየቁት፤ "አምላክህ እግዚአብሔር በአንተ እጅ ወደ እኛ የላከ ውን ነገር ሁሉ ባናደርግ እግዚአብሔር በመካከላችን እውነተኛና ታማኝ ምስ ክር ይሁን፡፡ የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል በመስማታችን መልካም እን ዲሆንልን መልካም ወይም ክፉ ቢሆን አንተን ወደ እርሱ የምንልክህ የአምላካ ችንን የእግዚአብሔርን ቃል እንሰማለን" አሉት (42፥5-6 - ሙሉውን ምዕራፍ ማንበብም ይቻላል)፡፡

ወደ ግብፅ እንዳይገቡ እግዚአብሔር መናገሩን አሳወቃቸው፡፡ "የምት ፈሩት ሰይፍ በዚያ በግብፅ ያገኛችኋል ... የምትደነግጡበት ራብ በዚያ በግብፅ ይደርስባችኋል" አላቸው (ቍ. 16)፡፡

እነርሱ ግን ሊቀበሉት አልወደዱም፡፡ ባቢሎናውያንን በሚመለከት ሲናገርና ሲጮኽ የነበረው መዓት ሁሉ ሲፈጸም "በዐይናቸው በብረቱ" ያዩ ሰዎች አሁንም የሚናገራቸውን መቀበል አልፈለጉም፡፡ የእግዚአብሔር ነቢይ

እንደ ሆነ ያውቃሉ፤ ትንቢቱ ሁሉ ቃል በቃል ሲፈጸም አይተዋል:: “መልካም ወይም ክፉ ቢሆን ... የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል እንሰማለን” በማለት አስቀድመው ቃል ገብተውለት ነበር:: አሁን ግን፣ “ሐሰት ተናግረሃል፤ አምላካ ችን እግዚአብሔር 'በዚያ ትቀመጡ ዘንድ ወደ ግብፅ አትግቡ' ብሎ አልላከህም ...” አሉት (43፥2-3):: ኤርምያስ መዋሸቱን ለመናገር መነሻቸው ምንድን ነው? እነርሱ ለመስማት የሚፈልጉትና የሚመኙት ስኬትን፣ ድልን፣ በረከትንና ብል ጽግናን እንዲተነብይላቸው ነበር (ዛሬም ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የወጣ ሁሉ ስኬትን የሚያወራው ለዚህ ይሆን?!):: ከዚያ ግን “አትሂዱ” ወደተባሉ በት ግብፅ ጓዛቸውን ጠቅልለው አመሩ፤ ኤርምያስንም አስገድደው ወሰዱት (43፥6)!

ትልቁ ንጉሥ ናቡከደነፆር ነቢዩ ኤርምያስን በሚመለከት ለባለ ሥል ጣኑ ያስተላለፈው ትእዛዝ ነበር፤ “ውሰደውና በመልካም ተመልከተው፤ የሚሻ ውንም ነገር አድርግለት እንጂ ክፉን አታድርግበት” ብሎለታል (39፥11-12):: የክብር ዘቡ አለቃም ኤርምያስን፣ “አምላክህ እግዚአብሔር ይህን ክፉ ነገር በዚህ ስፍራ ላይ ተናገረ፤ እግዚአብሔርም አመጣው፤ እንደተናገረውም አደ ረገ:: ... አሁንም እነሆ በእጅህ ካለችው ሰንሰለት ዛሬ ፈታሁህ:: ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎን መምጣት መልካም መስሎህ ቢታይህ፣ ና እኔም በመልካም አይሃ ለሁ:: ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎን መምጣት መልካም መስሎ ባይታይህ ግን፣ ተቀ መጥ እነሆ አገሪቱ ሁሉ በፊትህ ናት፤ ትሄድ ዘንድ መልካም መስሎ ወደሚታ ይህ ደስ ወደሚያሰኝህም ስፍራ ሂድ” ብሎት ነበር (40፥4)::

ጠላቶቹ መብቱን ያከብራሉ፤ ይጠብቃሉ:: የራሱ ሰዎች ግን እነርሱን፣ “አትሂዱ” ወዳላቸው ክፉ ስፍራ እርሱንም አስገድደው ወሰደውታል:: እግዚአ ብሔር እንደ ጠራውና ዓላማ እንዳለው ሰው የመከራን ቀንበር የሚሸከም አለን? የእግዚአብሔር ዓላማ ያለበት ሰው ዓላማም መሆን ግዴታው ነውን? እንዲህ ዐይነቶቹ መልእክተኞች ተዘልሎ መኖርን ይደርሱበት ይሆን?

“ለዓለም፣ ለመላእክትም፣ ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናል፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳ ደረገን ይመስለኛልና” ይላል ቅዱስ ጳውሎስ (1ቆሮ. 4፥9):: እንዲህ ዐይነት ሰዎችስ ተዘልለው መኖር ይችላሉ? ለራሳቸው መኖር ተፈቅዶላቸዋል? ይልቁኑ በሁለት ወገን ተወጥረው የሚኖሩ አይደሉምን? የነቢዩ ኤርምያስም ሆነ የሐዋ ርያው ጳውሎስ ተሞክሮ የሚነግረን ለራሳቸው መኖር አለመቻላቸውን ነው::

የሐዋርያው ጳውሎስ የአገልግሎት ጥሪ መከራ መቀበልን ያካትት ነበር:: እግዚአብሔር ስለ እርሱ ለሐናንያ ሲናገር፣ “ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀ



በል እንዲያስፈልገው እኔ አመለከተዋለሁና” ብሎታል (ሐዋ. 9፥16):: እናም የቀረው መከራ አልነበረም:: ለጥሪው ታማኝ ለመሆን ብዙ መከራ ማለፍ ነበረ በት:: ይህም፣ ሌሎች ብልጥ ሲሆኑ እርሱ እና አብረውት የሚያገለግሉት ሞኞች መሆናቸውን፣ ሌሎች ሲበረቱ እነርሱ መድከማቸውንና ሌሎቹ ሲከብሩ እነርሱ መዋረዳቸውን ይመለከታል:: ተጨማሪ ሸክሞቹም ራብ፣ ጥማት፣ እር ዛት፣ ጉሰማ፣ እንክርት፣ የሥራ ድካም ሲሆኑ፣ ክፉ ለሚያደርግበት ሰው መል ካም ምላሽ መስጠትንም ያካትታል (1ቆሮ. 4፥10-13)::

ሐዋርያው ጥሪው የመከራ ጥሪም ነበርና በብዙ መከራ ዐልፏል፤ በእስያ የደረሰበትን፣ “በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ ድረስ ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን ነበር:: በእርግጥም የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደብን ይሰማን ነበር” በማለት ገልጾታል (2ቆሮ. 1፥8-9)::

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ “ሰውነቱ ... ሲታይ ደካማ” እንደ ሆነ ይነገራል (2ቆሮ. 10፥10):: ያለ ዕረፍት ብዙ እንግልትና ውርጅብኝ ያለፈበት ሰው ስለ ነበር ይህ ቢሆን አይገርምም (2ቆሮ. 7፥5፤ 11፥23-27):: በአገልግሎቱ ፍጻሜም ከትግሉ እፎይታም ሆነ ተዘልሎ መኖርን አላገኘም::

2ኛው የጢሞቴዎስ መልእክት የመጨረሻ መልእክቱ እንደ ሆነ ይታሰ ባል:: የአገልግሎቱ ፍጻሜ መቃረቡንም ዐውቋል፤ “ሩጫውን ጨርሻለሁ” ማለቱ ይህን ያመለክተናል (2ጢሞ. 4፥7):: በዚያን ወቅት በዕድሜም ሸምግ ሏል፤ ግን የጠበቀው እስር ነው፤ ከምድር በታች ያለ ቀዝቃዛ እስር ቤት! ያኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታሰር በተከራየው ቤት ሆኖ በዐይነ ቁራኛ ብቻ እየተጠ በቀ ይኖር ነበር (ሥራ 28፥30):: አሁን በመጨረሻ ግን ነገሮች እየከፉ መጡ:: እስር ቤቱ ለሸማግሌው ጳውሎስ እጅግ ከፍቶበታል:: በሰንሰለት መታሰሩ ሳያንስ (2ጢሞ. 1፥16፤ 2፥9)፣ በርኖስ የሚያስፈልገው ፈታኝ ቅዝቃዜ ገጥሞታል (4፥13)::

በዚህ ሁኔታ ውስጥም ግን ከሰዎች ጋር የነበረው መስተጋብር እንደ በፊቱ ነው:: ዛሬም ሰዎች ይከዱታል፤ ይጐዱታል:: “የናስ አንጥረኛው እስክን ድሮስ እጅግ ከፋብኝ፤ ጌታ እንደ ሥራው ይመልስለታል:: አንተም ደግሞ ከእ ርሱ ተጠበቅ፤ የምንናገረውን እጅግ ተቃውሟልና:: በፊተኛው ሙግቴ አንድ ስንኳ አልደረሰልኝም፤ ሁሉም ተዉኝ እንጂ፤ ይህንንም አይቈጠርባቸው” (ቊ. 14-16):: በዚህኛው መልእክቱ ጳውሎስ ፍርሀቱንና ብቸኝነቱን አሳይቷል::

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየኖሩ መከራ የሚቀበሉ ሰዎች መከራ ቸው የላቀ ዓላማ ሊኖረው እንደሚችል ማሰብ አለባቸው:: ሌሎችን ማጽናናት መቻል አንደኛው ጥቅሙ ነው:: ለምሳሌ፣ “እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናል፤

ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን” ይላል (1ቆሮ. 1፥4-5):: አጽናኞቹም መጽናና ታቸው ግን አይቀርም:: ምክንያቱም ሐዋርያው ቀጠል አድርጎ፣ “የክርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ እንደ በዛ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልና” በማለት ይናገራል:: እግዚአብሔር ያልተፈተኑ ባርያዎች የሉትም!

የእግዚአብሔር ሰዎች ይህንን ሁሉ መከራ የሚቀበሉት ግን ያለ ዋጋ አይደለም፤ ብድራት አላቸው:: የተባረከው መጽሐፍ፣ “በዚህች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፣ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነንና” እንደ ሚል (1ቆሮ. 15፥19)፣ ብድራታቸው በዚህ ምድር ላይሆን ይችላል:: በዚያኛው ዓለም ግን ሌላ ክብር ይጠብቃቸዋል:: ይህኛው መከራ ከዚያኛው ክብር ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ የሚባል አይደለምና እዚህ ያላረፉ ያኛውን ዕረፍት ሁሌ ይናፍቃሉ::

አንድ ጊዜ አንድ ሚሲዮናዊ ከረጅም ጊዜ የውጭ አገር አገልግሎት በኋላ ወደ አገሩ ለመመለስ በመርከብ ጉዞ ይጀምራል:: አገልግሎቱ በብዙ ድካም፣ ኀዘን፣ እንግልትና ሥቃይ የተካሄደ ስለ ነበር ዕረፍትን እጅግ ናፍ ቋል:: በዚህም ላይ አገሩ ሲገባ ምን ሊገጥመው እንደሚችል አለማወቁም አስ ጨንቆታል:: ልክ መርከቢቱ ከወደቧ ስትደርስ እየተደረገ የነበረውን ዝግጅት አየ:: ብዙ ባለሥልጣናትና ጋዜጠኞች ተሰብስበዋል፤ የሙዚቃ ባንዱ ሙዚቃ ይጫወታል፤ ዕቅፍ አበባ የያዙ ሕፃናት ይታያሉ፤ አዳዲስና ሽንጠ ረጃጅም መኪኖች ተሰልፈዋል፤ ሕዝቡም ግልብጥ ብሎ አካባቢውን ወርሮታል:: አንድ የአሜሪካ ባለሥልጣን ከውጭ አገር ጉዞው እየተመለሰ ነው::

ሚሲዮናዊው ይህንን ፍዝዝ ብሎ ሲመለከት ቈየና እርሱን የሚቀበል አንድም ሰው ባለመኖሩ ተከፋ:: “ምነው ጌታ ሆይ፤ ይህንን ያህል ዘመን፣ በዚያ ሁሉ ውጣ ውረድ ሳገለግልህ ከርሜ እንዴት አንድም የሚቀበለኝ ሰው ልጣ? ይህ ባለሥልጣን እንኳ ወደ ቤቱ ሲመለስ እንዴት ዐይነት የክብር አቀባ በል እየተደረገለት እንደ ሆነ እያየሁ ነው:: ምነው ጌታ ሆይ?” አለ እንባ ያቀ ረሩ ዐይኖቹን ወደ ላይ አቅንቶ:: ምላሹም ጊዜ አልፈጀም፤ “አንተ ወደ ቤትህ ገና መች ተመለስክ?!” የሚል ነበር::

አዎን! ወደ ላይኛው ቤታችን ስንሄድ ብዙ ክብር ይጠብቀናል:: ለዚያ ክብር ለመብቃት ግን ሩጫውን መጨረስ ተገቢ ነው:: “በመሥዋዕት እንደሚ ደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፤ የምሄድበትም ጊዜ ደርሷል:: መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል” (2ጢሞ. 4፥6-8)::



ወንጌልና መከራ የማይነጣጠሉ ዘመዳሞች ናቸው:: ነገር ግን በማወ ቅም ይሁን ባለማወቅ የሚደረጉ የሁለቱን ዝምድና ነጣጥለው የሚያሳዩ ትምህ ርቶች በብዛት ስለምንሰማ ባዳዎች ይመስሉናል:: ሆኖም ወደድንም ጠላን የሰ ማነው የወንጌል ቃል በሕይወታችን መከራን ማስከተሉ አይቀሬ ነው (ማቴ. 13፥21)::

በሥነ አመክንዮ የትምህርት ዘርፍ የተለያዩ ዐይነት የተፋለሱ ክርክሮች (የተሳሳቱ የሙግት መንገዶች) ይታወቃሉ:: ከእነዚህም አንደኛው፣ ማስረጃ መደበቅ (suppressed evidence) ይባላል:: መራራውን እውነትና የሚያስበረ ግገውን ማስረጃ በመደበቅ፣ ደስ ደስ የሚለው ከፊል መረጃ ብቻ ሲቀርብላ ቸው ብዙዎች ይታለላሉ:: ሰይጣን በዚህ የተካነ ነው፤ ይህንን ዘዴ መንግሥ ታት ይጠቀሙበታል፤ ፖለቲከኞችማ ትጥቃቸው ነው::

ወንጌል ላይም እንዲህ ዐይነት ስሕተት የተሠራ (እየተሠራም ያለ) ይመስለኛል፤ በውጭ ሰዎች ሳይሆን በቤተኞች:: በምዕመናን ሳይሆን በሰባኪያ ንና በአስተማሪያን! በዚህ መንገድ ሰዎችን ማብዛት ተችሏል:: እነዚህ መከራ እንደሌለ የተነገራቸው አማንያን ቀድመው ያልተዘጋጁበትና ያልጠበቁት መከራ ሲመጣ ወደ ኋላ ሲመለሱ መንገድ እናገኛቸው ይሆናል:: ዋጋቸውን ለመተ መን የሚያስፈልጋቸውን ማስረጃ የሰጣቸው አልነበረም፤ ተዘልሎ መኖር ተነግ ሯቸው ተወጥሮ መኖር ሲደርስባቸው ምን ይላሉ?

ወንጌል መከራም ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ መከራ የሚቀበሉትን ሰዎች የሚያጽናናበት አንድ ትምህርት ነበረው፤ “ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል” የሚል (ሥራ 14፥22):: (“ያስፈልገ ናል” የሚለው ቃል ይሠመርበት::) ይህንን ሲናገር እርሱ ራሱም መከራን እየተ ቀበለ ነበር:: እንዲህ ሲሰበክ ከሰማን ስንት ጊዜ ሆነን?!

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 1፥29 ላይ አስደንጋጭ አባባል ይሰነ ዝራል፤ “በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበ ሉም ይህ ጸጋ ተሰጥቷችኋልና” (አ.መ.ት):: ለክርስቶስ መሠቃየት ማለት ማመን የመዳን አካል እንደ ሆነው ዐይነት ነው:: ሁለቱም የጸጋ ስጦታዎች ናቸው::[6] ብዙ ሰዎች ግን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑት ምን እንደሚል ስለማ ያውቁ ነው:: *ለሥቃይ ተጠርተናል!* ለተሰሎንቄ ሰዎች የሚነግራቸውም ይህ ንኑ ነው፤ “በዚህ መከራ ማንም እንዳይናወጥ፣ ለዚህ እንደ ተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና:: በእውነት ከእናንተ ጋር ሳለን፣ መከራ እንቀበል ዘንድ እንዳ ለን እንነግራችሁ ነበር” (1ተሰ. 3፥3):: ለበረከት መጠራታችን እውነት የሆነ ውን ያህል ለመከራም ተጠርተናል::

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ “እኛ ራሳችን የሞትን ፍርድ በውስጣችን ሰምተን ነበር” ብሎ ስለ ራሱም ተናግሯል (1ቆሮ. 1፥9)። ክርስቲያን የክርስቶስ ወታደር መሆኑ ይታወቃልና ጢሞቴዎስን፣ “እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል” በማለት ይመክረዋል (2ጢሞ. 2፥3)። መከራ መቀበል የጥሪአችን አካል ነው ማለት ነው።

ከባድና ተደጋጋሚ ሥልጠና የውትድርና መሠረታዊ ክፍል ነው። ቀላል ሥልጠና በወሰደውና በብዙ ውጣ ውረድና ትግል ባለፈው ወታደር መካከል ግልጽ ልዩነት አለ። የትኛው ጸንቶ እጅ ሳይሰጥ ለፍጻሜ እንደሚበቃና ውጤታማ እንደሚሆን ማንም አያጣውም። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ኢዮብና ነቢዩ ኤርምያስ እስከ መጨረሻው የጸኑበት ምክንያትም ከዚህ የራቀ አይደለም።

እውን አገልግሎቱ በምድር ላይ የሚያስከትለውን ክብር፣ ዝናና ምቾት ባያይ ኖሮ የላይኛውን ክብር በማሰብ ብቻ ዛሬ ራሱን ለእውነተኛ አገልግሎት የሚለይ አገልጋይ ይኖር ነበርን?

ለነገሩ ማንም መከራ የሚያስከትልን አገልግሎት አይወድም! “ወንጌልን ብሰብክ እንኳ የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኛ ነውና፤ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ” ብሏል ሐዋርያው ጳውሎስ (1ቆሮ. 9፥16)። ለዝናና ለምቾትማ ስንት መንገድ ሞልቶ የለ?! እርሱን ግን እግዚአብሔር ለዚህ ሥራ ጠርቶታልና ምን ማድረግ ይችላል?! ሕልሙ ምድራዊ ክብር፣ ንዋይ፣ ሹመትና ዝና አልነበረም። የእግዚአብሔርን የፍቅርና የእውነት መልእክት ተሸክሞ መኖር ነበር ዓላማው! ተዘልሎ ለመኖር ሳይሆን፣ ተንገላትቶም ይሁን ተወጥሮ እየኖረ እግዚአብሔርን መምሰልና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ነበር ግቡ!

አይደለም ለክብረት ለንዋይ ተዳምሮ
አይደለም ለሹመት ለተጫፍሮ ኑሮ
አይደለም ለዝና ለጠፊ ውሎ አድሮ፤ ...
ለትሑት ሕይወት ነው፣ እኔ መሯሯጤ
በዘልማድ መንገድ ጉዞ አለመምረጤ፤
ደቂቀ ብርሃንን -
ውበት - ፍቅር - እውነትን
        ለመገላገል ነው የዘወትር ምጤ።
ይኸው ነው መስቀሌ፣
ይህም ነው አክሊሌ፣
ይኸው ነው ድካሜ፣
ይህም ነው ብርታቴ።[7]



ይህን ሁሉ ታግሦ እስከ መጨረሻ የጸና የክብር አክሊል ይቀበላል።

## ማስታወሻ

1. Philip Yancey, *The Bible Jesus Read* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1999), 56.
2. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 54።
3. ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *ሰማዩ ዝም ሲል* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም) ገጽ 80።
4. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 24-25።
5. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 25።
6. ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *የወዳጅ ፍላጻ* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም) ገጽ 51።
7. ደበበ ሰይፉ፤ *ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ (የብርሃን ፍቅር ቅጽ ፪)*፤ (ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም) ገጽ 95።

# ምን አገባኝ?!

ልጆች ሳለን ከብጤዎቻችን ጋር ስንጋጭ በየአጋጣሚው ከምንሰማቸው አባባሎች አንዱ "ምን አገባህ?" የሚል ነበር፡፡ "ምን አገባህ?" የተባለው ሰው "ሚስት" በማለት መልስ ይሰጣል፡፡ ወይም፣ "አንተን አማክሬ ነው የማገባው?!" ይላል፡፡ ይህን የመሳሰሉ አባባሎች በልጅነት ያከተሙ መስሎኝ ነበር፤ ተሳስቻለሁ፡፡

ችግሮች ሲፈጠሩ፣ የተፈጠሩትን ወይም የተገለጡትን ችግሮች በግልጽ የሚናገር ሰው፣ "አንተ ምን አገባህ?" ይባላል፤ አሁንም፡፡ "አብዛኛው ሰው የሚሞተው በማያገባው እየገባ ነው" ተብሎም ይመከራል፡፡ ድንበሩን እያለፈ የሰዎች የግል ጉዳይ ውስጥ የሚገባ ሰው፣ "ምን አገባህ?" ቢባል ብዙም አያስደነግጥም፤ በአገር ወይም በእግዚአብሔር ቤት ጉዳይ ሲሆን ግን ያስደነግጣል፡፡ አባባሉ ሰዎች እነርሱን በግል የሚጎዳ ነገር ካልደረሰባቸው በቀር ግዴለሾች እንዲሆኑ የሚገፋፋ ነው፡፡

አንድ ዜጋ ለአገሩ ሊያደርግ የሚችለው ዋነኛው ነገር ተሳትፎ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ "ያገባኛል" የሚሉ ዜጎች ያጣች አገር ወዮላት! የሚካሄደው ልማትም ሆነ ጥፋት የሚገዳቸውና የሚቆረቁራቸው ዜጎች የሌላት አገር ዋጋም የላት! አገሩን የሚወድ የትኛውም ሰው ልማት፣ ምርጫ፣ ዘመቻ ሲኖር፣ "የአገሬ ጉዳይ ይመለከተኛል" በማለት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ውጤቱ ተስፋ አስቈራጭ ቢሆንበት እንኳ ለለውጥ ይታገላል እንጂ "ምናገባኝ!" አይልም፡፡ እንዲህ ዐይነት ዜጎች ያሏት አገር ደግሞ የተባረከች ናት፤ ለውጥ፣ ነጻነትና እድገት የሚመጣው በእንዲህ ዐይነት ዜጎች ነውና፡፡

በእግዚአብሔር ቤትም ተመሳሳይ ነው፡፡ በ"ያገባኛል" ስሜት የሚመላለሱ፣ የሚካሄደው ነገር ሁሉ "እኔንም ይመለከተኛል" የሚሉ ምዕመናን ሲኖሩ መልካም ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ትጠቀማለች፤ ትባረካለች፡፡ የትኛውም ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤትን ለተወሰኑ አገልጋዮች ከሚተው ይልቅ ይህንን ቢያደርግ የተሻለ አደረገ፡፡

ይሁን እንጂ ይህን ሰው ሌሎች አጨብጭበው ይቀበሉታል ማለት አይቻልም፤ "ምን አገባህ?" የሚል ማስፈራሪያ ይሰነዝሩበት ይሆናሉ፡፡ "የአንተ ትምህርትና ሞያ ሌላ ነው፤ ምናገባህ?" የሚሉ ገጥመውኛል፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ለመቆርቆር የትምህርት ዐይነትና ደረጃ ይጠይቃል እንዴ? ክርስቲያንነት



አይበቃም!? ሞያን የጥሪ አጋዥ ከማድረግ ይልቅ ምትክ ማድረግ ጀምረናል ማለት ነው? ቅዱስ ሉቃስ በሞያው ሐኪም እንደ ነበር ይታወቃል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም "የተወደደው ሐኪሙ ሉቃስ" በማለት ይመሰክርለታል (ቈላ. 4፥14 - አ.መ.ት)፤ ታዲያ ወንጌሉንና የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ምን አግብቶት ነው?

አሞፅ የእስራኤልን ኀጢአት በሚመለከት ፊት ለፊት መናገርና መገሠጽ ሲጀምር፣ የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች ተቃውሞ አቅርበውበት ነበር፡፡ የአሞፅ መልስ ይህን ይመስላል፤ "እኔ ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ ነኝ እንጂ ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም፤ እግዚአብሔርም በጐቼን ከመከተል ወሰደኝ፤ እግዚአብሔርም 'ሂድ ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት ተናገር' አለኝ" (7፥14-15)፡፡ አሞፅ ያለ ሞያው ጌታ ሲጠራው ምን ማድረግ ይችላል? ወይም እንደ ራሱ አባባል፣ "አንበሳው አገሣ የማይፈራ ማነው? ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ ትንቢት የማይናገር ማን ነው?" (3፥8)፡፡

እግዚአብሔር የላካቸውን ሰዎች፣ "ምን አገባችሁ?" ማለት ራሱን እግዚአብሔርን፣ "አልቀበልም" ከማለት በምን ይለያል?

አይሁዳውያን እነርሱን የማይመቻቸው (ደስ የማያሰኛቸው) ነገር ሲፈጸም ሮጠው የማንነትና የሥልጣን ጥያቄ በማቅረብ የተካኑ ናቸው፡፡ የድርጊቱ ተገቢነት ላይ ግድ የላቸውም፤ ትኩረታቸው፣ "አንተ ማን ነህ?" ላይ ብቻ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የሚያሳስባቸው የሥልጣን ጉዳይ ነበር፡፡ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ አገልግሎቱ እየታወቀ ሲመጣ ማንነቱን ለመጠየቅ ሰዎችን ላኩበት (ዮሐ. 1፥19)፤ ማንነቱን አስታወቃቸው፡፡ ያኔ፣ "ለምን ታጠምቃለህ ታዲያ?" የሚል ጥያቄ አስከተሉ (ቊ. 24)፡፡

ዮሐንስ "የማያገባው" ውስጥ የሚገባ ሰው ነበር፡፡ ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሲያገባ ዮሐንስን ማንም ምክር አልጠየቀውም፡፡ እርሱ ግን ንጉሡን ፊት ለፊት፣ "እርስዋ ለአንተ ትሆን ዘንድ አልተፈቀደም" በማለት ገሥጾታል፡፡ አጠቃላይ መርሕ መስጠትን ብቻ ሳይሆን፣ በቀጥታ የሰውዬውን ድርጊት መቃወም ነው የመረጠው፡፡ ለዚህ ተግባሩም በመጀመሪያ እስራት፣ በመጨረሻም ሞት ነው የተከፈለው (ማቴ. 14፥1-12)፡፡ ("በማያገባው ገብቶ ሕይወቱን አጣ!" በማለት ሌሎችን ለመምከሪያ እንጠቀምበት ይሆን?)

ጌታ ኢየሱስንም እንዲሁ ብለውታል፡፡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የተጧጧፈ ንግድ ነበር፤ የማይሸጥ ነገር አልነበረም፡፡ ንግዱ የተጀመረው መሥዋዕት ለማቅረብ የሚመጡ አማንያን ለመሥዋዕቱ የሚሆኑ ግብዐቶችን በማጣት እንዳይቸገሩ ተብሎ ነው፡፡ ለመሥዋዕት የሚያስፈልጉ እንስሳትንና ሌሎች ቁሳቁሶችን እዚያው በአቅራቢያው ለመሸጥ መሞከራቸው ችግር ፊቺ ይመስላል፡፡

ሆኖም ቀስ በቀስ የድርጊቱ ዓላማ ተለወጠ፤ ኢጋዥ ድርጊቱ ራሱ ዓላማ ሆነ፡፡ ሰዎች ወደዚያ የሚመጡት ለንግድ ብቻ መሰለ፡፡ ይህንን የተመለከተው ጌታ፣ “የቤትህ ቅናት በላኝ” ተብሎ እንደ ተጻፈ ጅራፉን አንሥቶ የአባቱን ቤት ለማጽዳት እርምጃ ወሰደ (ማር. 11፥15-17)፡፡

ለዚህ ተግባሩ ግን ምስጋና አልቀረበለትም፡፡ የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች የእግዚአብሔር ቤት “የወንበዴዎች ዋሻ” ሲሆን አልቆረቆራቸውም፡፡ ጥፋቱ አልጐረበጣቸውም፤ ሥልጣናቸው አልተነካምና፡፡ የማጽዳት እርምጃው ግን አልጣማቸውም፡፡ ስለዚህም ያቀረቡለት የመጀመሪያ ጥያቄ፣ “እነዚህን ለማድረግ ይህን ሥልጣን ማን ሰጠህ?” የሚል ነበር፡፡ እርሱ ግን በቀጥታ ከመመለስ ይልቅ፣ ስለ ዮሐንስ መጥምቁ ጥያቄ አቀረበላቸው፡፡ እነርሱ ደግሞ ያቀረበላቸውን ጥያቄ ለመመለስ ትሕትናም ሆነ ድፍረት አልነበራቸውም (ማር. 11፥27-33)፡፡ ዮሐንስንም ያስነሣው እግዚአብሔር መሆኑን ማመን አልፈለጉም (የሁሉንም አገልጋይ ጥሪ ከደው እንዴት ይዘልቁታል?)፡፡

በኢየሱስ የምድር ዘመን የነበረው ቤተ መቅደስ በብዙ መልኩ ከዛሬዋ የእግዚአብሔር ቤት ጋር ተመሳስሎው ጉልሕ ነው፡፡ ዛሬም ቤተ ክርስቲያንን የሚያጤን ተመሳሳይ ነገሮች ሲካሄዱ መመልከት ይችላል፡፡ ይህ ተሰምቶት ጥያቄ ቢያቀርብ ግን ራሱ ጥያቄ ይቀርብበታል፡፡ ጥያቄው፣ “ማን ነህ? ማን ላከህ? ማን ሥልጣን ሰጠህ? ምን አገባህ?” የሚል ይሆናል፤ ለድርጊቱ ተገቢነት ብዙም ግድ ያለው ያለ አይመስልም፡፡

ለዚህ ማስረጃው “ያገባኛል” በማለት ስሕተትን የሚጠቍም ሰው ከማበረታቻ ይልቅ ተቃውሞ ሲግተለተልበት መታየቱ ነው፡፡ “ጨለምተኛ ነው” ይባላል፡፡ “ብርጭቆው ግማሽ ውሃ ቢይዝና ይህ ሰው ቢጠየቅ፣ ‘ብርጭቆው ግማሹ ባዶ ነው’ ማለትን ይመርጣል” ይባላል (ለነገሩ ብርጭቆው ግማሹ ሙሉ ሆነ ማለት፣ ግማሹ ባዶ ነው ማለት አይደል?)፡፡ ደግ ነገር እንደማይታየውና ቦምቦሊኖ ቢሰጡት፣ “ቦምቦሊኖው ለምን ቀዳዳ ኖረው?” ማለትን እንደሚመርጥ በማውራት ሊሳለቅበት የሚሞክርም አይጠፋም፡፡

የዛሬ 2000 ዓመት አካባቢ እስራኤል በካህናቱ ስትታይ ብርጭቆው ግማሽ ሙሉ ነበር፡፡ የሚያምር ቤተ መቅደስ እየተገነባ ነው፤ ሰዱቃውያን በቤተ መቅደሱ፣ የሕግ መምሕራን ደግሞ በየምኵራቡ ሞልተዋል፡፡ እስራኤል ውስጣዊ አስተዳደር ነበራት፡፡ የቤተ መቅደሱ ሥርዐት ቀጥሏል፡፡ መሥዋዕት አቅራቢዎች እንዳይቸገሩ ደግሞ ገቢያው እዚያው አለላቸው፡፡ ከተለያዩ አገራት ለሚመጡ ምዕመናን ሲባልም የገንዘብ ምንዛሪ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት ግቢው ውስጥ አሉ፡፡ ምን ጠፍቶ?



እነርሱ በሚታየው ነገር ቀልባቸው ተወሰዷል፤ እግዚአብሔር ግን የብርጭቆው ጐድለት ነበር የታየው፡፡ ስለዚህም የፍቅር ጌታ የሆነው ኢየሱስ ጅራፉን ይዞ ወደ መቅደሱ ግቢ ገባ፡፡ በዚህም ሳይወሰን ድንጋይ በድንጋይ ላይ እስከማይቀር መቅደሱ እንደሚፈርስ ትንቢት ተናገረ፡፡ ይህም ተፈጸመ እንጂ በከንቱ አልቀረም፡፡ ያኔ፣ “ለራሳችሁ አልቅሱ” ብሎ መከሯቸው ነበር (ሉቃ. 23፥28-31)፤ የዋይታና የመከራ ዘመን ነበር የሚታየው ማለት ነው፡፡

ለነገሩ ሰው ሁሉ፣ “ብርጭቆው ግማሽ ሙሉ ነው” በሚልበት ጊዜ “ኧረ ግማሹ ባዶ ነው” ማለት ለሚዛናዊነት አያግዝም? ሁሉስ በአንድ አቅጣጫ ያያል? በዚህም ላይ “ግማሽ ሙሉ” የተባለለት ብርጭቆ የተሞላው በመርዛም ፈሳሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ፈሳሹ ተደፍቶና ብርጭቆው ተለቅልቆ እንደገና በሌላ ጤናማ ፈሳሽ እንዲሞላ መናገር ስሕተቱ ምኑ ላይ ነው?

ግና ብዙዎች ከሚታያቸው ነገር የተለየ ማየት ያስኰንናል፡፡ አንድ ጊዜ አንድ የእስራኤል ንጉሥ ወደ ጦርነት ለመሄድ ነቢያትን ሲጠይቅ፣ ሁሉም ነቢያት እንደሚሳካለት ይነግሩት ጀመር፡፡ ንጉሡ የማይወደው አንድ ሚክያስ የሚባል ነቢይ ግን በቦታው አልነበረም፡፡ ንጉሡም፣ “ክፉ እንጂ መልካም ትንቢት አይናገርልኝምና እጠላዋለሁ” በማለትም የጥላቻውን ምክንያት ግልጽ አድርጎታል (1ነገ. 22፥8)፤ “ጨለምተኛ ነው” ማለቱ ነው፡፡

ይህ “መልካም ነገር የማይታየው” ነቢይ እንዲመጣ መልእክተኛ መላኩ ግን አልቀረም፡፡ ሊጠራው የሄደ መልእክተኛም፣ “እንደ ሌሎቹ መልካም መልካሙን ብቻ ተናገር” በማለት ሊያግባባውና ሊያባብለው ሞክሯል (ቍ. 13)፡፡ ቆፍጣናው ነቢይ ግን፣ “ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር የሚናገረኝን እርሱን እናገራለሁ” በማለት መለሰለት፡፡ “ብርጭቆው ግማሽ ጐዶሎ ነው” በማለት እግዚአብሔር በሚናገርበት ጊዜ እንዴት፣ “ግማሽ ሙሉ ነው” ማለት ይችላል?

ነቢዩ እግዚአብሔር የገለጠለትን ጕድለት በመናገሩ ጥፊ ቀምሷል (2ዜና 18፥23)፤ “እኔ ያልታየኝ ነገር አንተን እንዴት ይታይሃል?” መሆኑ ነው፡፡ አልታይ ያለው ሰው ለምን ሁሉ እንደ እርሱ “እንዲያይ” ይጠብቃል? ለምን እንዳልታየው ራሱን መጠየቅ ነው ያለበት፡፡ አጥርቶ ማየት የፈለገ መነፅሩን መወልወል ወይም መቀየር፣ ሲሻውም የቈመበትን ቦታ መለወጥ የራሱ ድርሻ ነው፡፡

በእግዚአብሔር ቤት የሚፈጸመውን ጥፋት የሚጠቁም ሰው፣ “ለማፍረስ ነው እንዴ የተጠራው?” ሊባል ይችላል፡፡ ሁሉም አገልግሎት ለማነጽ መሆን እንዳለበት በየአጋጣሚው አጠር ያለች ስብከት ቢጤም ይደረግለታል፡፡

ለአንዳንዶቹ ማነጽ ማለት፣ "ማሞጋገስና ጥሩ ጥሩ ነገርን ብቻ መናገር" ይመስላቸዋል:: እግዚአብሔር ኀጢአተኛውን፣ "ኀጢአተኛ ነህ" ሲለው ማነጽ አይደለምን? ኀጢአተኛው ኀጢአተኛነቱ ተሰምቶት በንስሓ ከተመለሰና መንገዱን ካስተካከለ ታነጸ ማለት አይደል? እግዚአብሔር፣ ሌባውን "ሌባ"፣ አመንዝራውን "አመንዝራ"፣ ክፉውን "ክፉ" ብሎ ነው የሚናገረው:: ታዲያ ይህ የማነጽ አገልግሎት አይደለምን?

ነቢዩ ኤርምያስ እግዚአብሔር ከማሕፀን የጠራው አገልጋይ ነው:: አገልግሎቱ ደግሞ "የማፍረስ፣ የማጥፋት፣ የመገልበጥ፣ የመሥራትና የመትከል" ነበር (ኤር. 1፥10):: የቱ ነው የሚቀድመው? ማፍረስ፣ ማጥፋትና መገልበጥ ይቀድማል:: የተሳሳተው ግንባታ፣ የተበላሸው ግድግዳ በቅድሚያ መፍረስ ነበረበት፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ተስተካክሎ እንደገና ይታነጻል:: ስለዚህ የማነጽ አገልግሎት ከማፍረስ፣ ከማጥፋትና ከመገልበጥ ሊጀምር ይችላል:: "ለማነጽ አገልግል" ባዮች ይህን ይወቁ! ማፍረስ ቀላል ነው፤ እንደገና ለመሥራት በሚመች መልኩ ማፍረስ ግን ጥንቃቄንና ጥበብን ይጠይቃል:: ይህ ደግሞ ለሁሉ የተሰጠ አይደለም፤ የጥቂቶች ጥሪ ነው!

በዚህም ላይ የሰዎች አገልግሎት እንደ አገልጋዩ ማንነት እንደሚለያይ መታወቅ አለበት:: ሐዋርያው ዮሐንስ፣ "ልጆች ሆይ ኀጢአትን እንዳታደርጉ ..." ማለትን ሲመርጥ (1ዮሐ. 2፥1)፣ ቅዱስ ያዕቆብ ግን ለአማኞች ሲጽፍ፣ "አመንዝሮች ሆይ፤ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን?" ብሎ ነው የጻፈው (ያዕ. 4፥4):: መጥምቁ ዮሐንስ ደግሞ፣ "እናንተ የእፉኝት ልጆች" በማለት ይናገር ነበር፤ ያውም ንስሓ ሊገቡ የመጡትን ሰዎች (ሉቃ. 3፥7):: ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ሕዝቡን በፍቅር ሲያስተምር ይቈይና የቤተ መቅደስና የምኩራብ አለቆችን ግን በብርቱ ቃል ይዘልፋቸዋል:: ስጦታቸው ይለያያል::

አንዳንዴ ደግሞ የሚገሥጹት ሰዎች ስማቸው የገዘፈና "አይነኬ" ከሆኑ እነርሱን መናገር የሚያስቀሥፍ ይመስላል:: ስም ላላቸው ሰዎች፣ ሁሉ እንዲያ ደገድግ ይፈሊጋል:: የትልልቆችን ስሕተት የሚናገር ሰው እንደ ባለጌ ይቈጠራል (ጥፋት እያዩ ምንም እንዳልተፈጠረ ማለፍ ብልግና አይደለምን?):: ትንንሾችን መገሠጽ ደግሞ ከጨካኝ ያስመድባል (ጨካኝነት የሰዎችን ጥፋትና ውድቀት እያዩ ቸል ማለት አይደለምን?):: ከሰው ጋር ላለመጣላት ቸልተኝነትን እንደ አማራጭ መውሰድ ደግሞ ለማንም አይበጅም:: ቸልተኝነት በምድራዊውም ሕግ እንኳ ያስቀጣል:: ታዲያ ትልልቁንም ትንንሹንም በአግባቡ መንቀፍ የሚያስነቅፍ ከሆነ ምን ተሻለ?



ሰዎች ስሕተታቸው ከሚነገራቸው፣ "ጎሽ፣ ቀጥሉ" መባልን ይወዳሉ:: ስለዚህም ተናጋሪውን ይጠሉታል፣ ያሳድዱታል! እንዲህ ዐይነቱ ሰው እግዚአብሔር ጉበኛ አድርጎታልና ብዙውን ጊዜ ከፍተት፣ ጉድለትና እጥረት የሚታየው ነው፤ "ተመለሱ" ማለት ያበዛል:: ሁኔታዎች ካልተስተካከሉ ነገ የሚፈጠረው አደጋ ሥጋት ዕንቅልፍ ያሳጣዋል:: የሚያገኘው ምላሽ ግን ጤናማ ላይሆን ይችላል:: ከመገለል ባሻገር በሐሰት ስም ማጥፋት ይደርስበትም ይሆናል:: ጌታችን ላይም የካህናት አለቆች ብዙ የሐሰት ምስክሮችን አዘጋጅተውበት ነበር (ማቴ. 26፥59-60፤ ማር. 14፥55-56):: በክፉ ቃል በመናገር ሰዎችን መጕዳት ከመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በአንዳንድ መሪዎች ዘንድ ይታይ የነበረ ክፋት ነው:: ዲዮጥራጢስ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ ነው፤ ነገር ግን "በክፉ ቃል እየለፈለፈ" አገልጋዮችን የሚያስቸግር ሰው ነበር (3ዮሐ. 10)::

በፈጠራ ወሬ (በአሉባልታ) ብዙዎች ተጎድተዋል፤ ተሠቃይተዋል:: ሆኖም በግል ጕዳይ አይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ጕዳይ ጠላት ማፍራት አያሳፍርም:: ብድራትም አለው፤ ጌታ ኢየሱስ፣ " ... በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዐን ናችሁ" ብሏልና (ማቴ. 5፥11)!

ነቢዩ ኤርምያስ መቼም ቢሆን በሰላም መኖርን ጠልቶ አያውቅም:: ለራሱም ለሕዝቡም የነበረው ቅናት ችግሮቹ ተስተካክለውና ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው በሰላም እንዲኖሩ ነበር:: ሆኖም እግር በእግር እየተከታተሉ ኑሮውን የምሬት ያደረጉበት እነዚያው ችግራቸውን የሚነግራቸው የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንጂ ጠላቶቹ ባቢሎናውያን አልነበሩም:: የራሱ ወገኖች ሞትን እስኪመኝ እርሱን አስመረሩት እንጂ ደጋግሞ የሚነግራቸውን ስሕተት አርመው ከጥፋት አልዳኑም:: እርሱ ለራሱ ሳይኖር ዘመኑን ሁሉ አገልግሏቸዋል፤ ከጥፋት ሊያድናቸው ግን አልቻለም - አልሰሙትምና!

የማይሰማ ወጭት ጥጄ
　　እፍ ስል የከሰመ ፍም፣
ውርዴም ይፈወሳል ብዬ
　　የሰው እከክ ስዘመዝም፣
በሰው ቍስል ከመቍሰል በቀር
　　እኔ ለእኔ ኖሬ አላውቅም::
የማይነጋ ሕልም ሳልም
የዘመን ደዌ ሳስታምም
የማይድን በሽታ ሳክም
የሰው ሕይወት ስከረክም
እኔ ለእኔ ኖሬ አላውቅም::[1]

ይህ የጸጋዬ ገ/መድህን ግጥም ለኤርምያስ ተገቢ ይመስለኛል:: ለራስ መኖር አለመቻል ምን ይባላል? እርግማን፣ በረከት? ወይስ በረከተ መርገም? እንደዚያ "ተመለሱ" በማለት ሲጨቀጭቃቸው ቢከርምም ከጥፋት አላመለጡም:: ታዲያ ከጥፋት ሊያስመልጣቸው ካልቻለ ምን አግብቶት ሲናገር ቆየ?

እንኳር ክርስቲያናዊ አስተምህሮች በአደባባይ ሲናዱ እንኳ አብያተ ክርስቲያናት በቸልታ ሲመለከቱ፣ አንዳንድ ግለ ሰቦች ለእውነት ሲቆሙና ሲጋፈጡ ተመልክተናል:: "ያገባኛል" የሚሉ ሰዎችን ስላላጣን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

ወደድንም ጠላን ችግራችንን የሚነግሩን ሰዎች፣ እንደ ኅሊና ቢከታተሉን እንኳ ብርሃኖቻችን ናቸው፤ ዛሬን ብቻ ሳይሆን ነገንም ያሳዩናል:: ብርሃን ሲኖር ግን ሙቀት ወይም ግለት አብሮ ሊኖር ይችላል፤ ግለቱን ከጠላን ብርሃኑንም አብረን መጥላታችን ነው::

አንዳንዶች ደግሞ ሙቀት ቢኖርም ባይኖርም ብርሃንን ይጠላሉ:: ጌታችን እንዲህ አለ፤ "ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ... ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፣ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም" (ዮሐ. 3፥19-20):: በመሆኑም ክፉ አድራጊዎች ያቺን ብርሃን ለማጥፋት አብሪውን ትል ከመግደል አይመለሱም::

ስለዚህ ዛሬም ሁለት ምርጫዎች አሉን:: የመጀመሪያው ፈርቶ ዳር መቆም ነው:: ሁለተኛው ግን "ያገባኛል" በማለት ፍልሚያው መካከል መግባት ነው::

"ያገባኛል" ካልን መናገር ያለብን ብዙ ነገር አለ፤ አንዳንዱን መጥቀስ ይቻላል:: ለመሆኑ አንድ ባል ሚስቱን ሳያማክር እስከ ስንት ብር ለሰው ይሰጣል? ሚስትስ ከባሏ ሳትማከር ስንት ብር ድረስ ለሰው የመስጠት መብት አላት? የአንድ መሥሪያ ቤት ሥራ አስኪያጅ የአገሪቱንም ሆነ የድርጅቱን የገንዘብ አወጣጥ ሥርዐት ሳይከተልና በጀቱን ሳያማክር ስንት ብር መስጠት ይችላል? ታዲያ አንድ መጋቢ በተገኘበት ቦታ ድንገት ተነሥቶ፣ "ይህን ያህል ሺህ ብር ሰጥቻለሁ" የሚለው ከምን ተነሥቶ ነው? እስከ ስንት ብር ድረስ ነው ከራሱ ጋር ብቻ እየመከረ የሚመነዝረው? ወይስ ገደብ የለሽ መብት ተሰጥቶታል? ከራሱ ኪስ ቢሆን እንኳ ይህንን በግልጽ ማሳወቅ የለበትም? የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በስንት ሰው ስም ነው የሚቀመጠው? አስቀማጮቹስ ባልና ሚስት፣ የመጋቢው ወንድምና እኅት መሆን ይችላሉ? አንድ መጋቢ ውድ መኪኖችን ለራሱም ሆነ ለሚስቱ ሲሸልም ገንዘቡ ከየት እንደ መጣ ለማኅበረ ምዕመናኑ በይፋ ማሳወቅ የለበትም?



በዚህስ ላይ በየወቅቱ የሚሰበሰበውን መባና ዐሥራት ምዕመኑ በየሳምንቱ እንዲያውቀው የማይደረገው ለምንድን ነው? እኔ እንኳ በአዲስ አበባ ይህን የሚያደርጉ ሁለት አብያተ ክርስቲያናትን ዐውቃለሁ (ቤዛ ባፕቲስት እና ኢንተርናሽናል ኢቫንጄሊካል ቸርች):: ሌሎቹስ የተሰበሰበውን ገንዘብ በውስጥ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ቢለጥፉ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን አያበረታታም? በሌላ ጎኑ ደግሞ፣ ፕሮግራሙ ላይ የተሰበሰበውን ገንዘብ ሳይቈጥሩም ሆነ ሳያስቈጥሩ ይዘው የሚሄዱ "መጋቢዎችንም" ዐውቃለሁ::

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን "ለቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ማሠሪያ ገንዘብ አምጡ" በማለት ከዓመት ዓመት ገንዘብ ይሰበስባሉ፤ መሬቱ ሲገዛ ግን በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም አይደለም:: ዝም ማለት ይቻላል?

ስም ያለው ሰው ከሆነ ሁለቴ አይደለም ሦስቴ ራሱን ሲድር በአደባባይ ያጋቡታል፤ እንዳላዩ ማለፍ ይቻላል? ለጌታችንና መድኀኒታችን ብቻ የተሰጠን ስም እስከ መጠቀም በሚደርስ ሙገሳ እርስ በርሳቸው መካካብ ጀምረዋል (በብሉይ ኪዳን ቢሆን ያስገድል ነበር!)፤ ችላ ማለት ይቻላል? ተተኪ አፍርተው ቦታ ከመልቀቅ ይልቅ በሥልጣናቸው ላይ ሌላ ለመጨመር ይጥራሉ፤ "አያገባኝም" ይባላል? የፍቅር ሰውና አስታራቂ መሆን ሲኖርባቸው መሠሪ፣ ትሑት መሆን ሲገባቸው በትዕቢት ፈረስ ሽምጥ የሚጋልቡ፣ ሚዛናዊነት ሲጠበቅባቸው ለሰው ፊት የሚያደሉ ሆነዋል:: ምንም እንዳልተፈጠረ መቀጠር ይቻላል? "ተሳስቻለሁ" ማለት የሞት ያህል ይከብዳቸዋል፤ ይህስ በዝምታ ይታለፋል?

"የእግዚአብሔር ቤት ለምን ተተወ?" ማለት ጤናማ ጥያቄ ነው:: በእግዚአብሔር ድንኳን ሥነ ምግባር ሲጠፋ ያገባናል! በእግዚአብሔር ስም ሲነገድ ያገባናል! ሰዎች በእግዚአብሔር ቤት ሲበደሉ ያገባናል! ሠራተኞች ተርበው፣ ያልሠሩት ሲጠግቡ ያገባናል! ገንዘብ በባንክ ተከማችቶ፣ የተቸገሩ ምዕመናን የሚረዳቸው ሲያጡ ማየት ያስቈጣል:: የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ ለስማቸው ማስጠሪያ ሲያደርጉት ይቆጠቁጣል:: እኛን፣ "አታድርጉ" የሚሉትን ነገር እነርሱ ሲያደርጉት ያመናል:: የእግዚአብሔር ቤት የአባታችን ቤት ነውና የሚደረገው ሁሉ ይመለከተናል::

አንዳንዶች የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የግል ድርጅታቸው አድርገዋታል:: እንዲያውም አኗኗራቸው ሲታይ፣ በቤተ ክርስቲያንም የሀብት ምዝገባ ቢደረግ ያስመኛል:: ድኻ ምዕመናንን የያዘች የድኻ አገር ድኻ ቤተ ክርስቲያን ሀብታም ፓስተሮችን ስታፈራ እንዴትስ "እኔን አያገባኝም" ማለት ይቻላል?! ቤቱ የሁላችንም አይደለምን!?

ነገር ግን "ያገባኛል" በማለት ለሚነሣ ሰው አበባ የሚያስታቅፈው የለም፤ ደረቱ ላይ ጦር የሚሰድበት እንጂ! ስለሆነም ይህንን የሕይወት ጐዳና የሚመርጥ ሰው አስቀድሞ ዋጋውን መተመን አለበት:: ቦታው ለጭብጨባ ወዳዶች፣ የራሳቸውን ኑሮ ብቻ ለመኖር ለሚፈልጉ፣ እልልታ ለሚናፍቃቸው ሰዎች የሚሆን አይደለም:: ሽልማቱ ያለው ጠሪው ዘንድ ብቻ ነው::

"እኔ ምን አገባኝ" የምትሉት ሐረግ
እርሱ ነው አገሬን ያረዳት እንደ በግ
የሚል ግጥም ልጽፍ
        ብድግ አልኩኝና
"ምን አገባኝ" ብዬ
        ቁጭ አልኩ እንደ ገና::[2]

እንደማያገባን እንድንኖር የሚፈልጉ ሰዎች አሉ:: እሺ፣ ይሁና፤ እኔስ ምን ያገባኛል!?

ማስታወሻ

1. አሳምነው ባረጋ፤ *የትሮይ ፈረሶች እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም) ገጽ 82::
2. ኑረዲን ዒሣ፤ *መደድ* (አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም) ገጽ 29::



# ሞትን ማን ያመልጣል?!

"መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ::"

ይህ ግጥም የአበሻን ነገር ዐዋቂነት፣ የአማርኛ ቋንቋን ጉልበትና የቴዎድሮስን ጀግንነት በድምቀት ይናገራል:: ቴዎድሮስ በተለያዩ መሳፍንት ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ በማድረግ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲኖራት አድርገዋል፤ በየአውራጃው ሥር የሰደዱትን ባላባቶች በኀይል እያስገበሩ የአንድነቱን መሠረት ባይገነቡ ኖሮ፣ "ከርሳቸው ቀጥለው የነገሡት ዐፄ ዮሐንስና ዐፄ ምኒልክ ምቹ የአንድነት ጊዜ ወርሰው በመጠንከር በየዘመናቸው የተነሡባቸውን የግብፅንና የኢጣሊያን ወራሪነት በቀላሉ መመለስ ያዳግታቸው ነበር" ይላሉ ታዋቂው ታሪክ ጸሓፊ ተክለጻድቅ መኩሪያ::[1]

ዐፄ ቴዎድሮስ አገራቸውን ለማሠልጠንም ብዙ ለፍተዋል:: ከርሳቸው በኋላ እንደ ነበሩት ዐፄ ምኒልክ የውጭ ምርት ወደ አገራችን ከማስገባት ይልቅ አምራቾቹ ወደ አገራችን እንዲገቡና ምርቱ እዚሁ እንዲመረት ታግለዋል:: ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር እንዲጣሉ ያደረጋቸውና ለሞታቸው ሰበብ የሆነው ጉዳይም፣ የአገራቸውን ሰው የሚያሠለጥኑ ባለሞያዎች እንዲሰዱላቸው ያስተላለፉት መልእክት ተግባራዊ ምላሽ ባለማግኘቱ ነበር::

ከሁሉ በላይ ግን የሚታወቁት በጀግንነታቸው ነው:: የእንግሊዝ የጦር መኮንን ናፒየር እጃቸውን እንዲሰጡ ሲጠይቃቸው፣ "... ከተወለድኩኝ እስካሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበር:: ... ወንድ ያቀፈው ወንድ ተመልሶ አይታቀፍም" በማለት መልሰው ጽፈውለታል::[2] ይህንንም ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን በውብ ሁኔታ ገልጸውታል፤

"ይልቅስ ተረት ልንገርሽ የተላከ ከእንግሊዝ ዘንድ
'እጅህን ስጥ' አለኝ ፈረንጅ፤ እጅ ተይዞ ሊወሰድ፤
ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ?
አያውቅም ክንዴ እንደሚያነድ:: ... "[3]

የመጨረሻው ጦርነት እየተካሄደ እንኳን ጦርነቱ የሰለቸው ወይም የከበደው አንድ ወታደር፣ "ከምናልቅ እጃቸውን ይዘን ለእንግሊዝ እንስጣቸውና እንገላገል" ቢል ጓደኞቹ፣ "አንተ ዋሾ! ማነው እሳትን በእጁ የሚጨብጥ?"

ብለው የተግሣጽ ጥያቄ ካቀረቡለት በኋላ፣ "ደኅና ነው፤ በል አንተ ለመያዝ ሞክርና እኛ በኋላ እናግዝሃለን" ብለው አፌዙበት::[4]

ዐፄ ቴዎድሮስ ሲፎክሩ፣ "መይሳው ካሣ" ማለት ይወዳሉ:: ካሣ፣ ከመንግሣቸው በፊት የነበረ ስማቸው ሲሆን፣ "መይሳ" ማለት ደግሞ፣ "የሚመልስ ወደ ኋላ የሚያስኬድ እንዲያፈገፍግ የሚያደርግ" ማለት ነው::[5] ስንቱን ጀግና የማረኩትና ያርበደበዱት ቴዎድሮስ እስከ መጨረሻው ከተዋጉ በኋላ እጃቸውን ከመስጠት ሽጉጣቸውን ጠጥተው ከሕይወት መሰናበትን መረጡ:: ሞት ከንዳቸውን አንጠልጥሎ ወሰዳቸው::

ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉባትን ጥይት የሰሙ ሁለት የአይሪሽ ወታደሮች ሲደርሱ ቴዎድሮስ "ሕይወታቸው ገና አላለፈም ነበር:: እነኚያም የአይሪሽ ወታደሮች ... እግራቸውን እየጐተቱ ካንገላቷቸው ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ ሕይወታቸው ጨርሳ ዐለፈች::"[6]

እንግሊዞቹም ከገቡ በኋላ በዚያ የነበረ ሕዝብ ሁሉ እያወካና እየጮኸ የቴዎድሮስን ሬሳ ደበደበ:: ፍጹም እራቁት እስኪሆኑ ድረስም ልብሳቸውን ቀዳደደው:: ቴዎድሮስም በተወለዱ በ50 ዓመታቸው፣ በነገሡም በ15ኛው የግዛት ዘመናቸው ሞቱ:: ስንቱን ጀግና ሲያስፈሩና ሲያርበደብዱ ቢኖሩም አስፈሪነታቸው ከሞት አላስቀራቸውም:: በፊት ሲፈሯቸው የነበሩ ሁሉ ሞታቸውን ሲያውቁ አቀለሏቸው:: ማርከሃም ሲተች፣ "... አስፈሪው ጊዜ ዐልፏልና ያ አስፈሪው ሰው እንደ ሞተ ቀበሮ ሆነ ..." ይላል::[7]

የቴዎድሮስ ወንድነት አስደናቂ ነበር፤ ራሳቸውን ከገደሉ በኋላ እንኳ፣

"የትግሬውን ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ፣
የሸዋውን ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ፣
ወንድ አለራስዎ ገድለውም አያውቁ!" ተብሎላቸዋል::

ወንድነት ከሞት አያስቀርምና እኚህን ያህል ጀግና ሞት አሸነፋቸው:: ማን ሞትን ያመልጣል? ከሞት በላይ ጀግና የት ይገኛል? ከሞትስ ማን ይበረታል?

* * *

በዓለም ላይ ከነገሡት ነገሥታት ሁሉ እንደ ናፖሌዮን ታሪኩ የብዙ ደራስያንን መንፈስ የማረከ፣ ብዙ ሐተታ የፈጠረ፣ ብዙ ወረቀትና ቀለም የጨረሰ፣ ተነበና ተጽፎ ያልተጠገበ ንጉሥ አይገኝም:: ኪርኪሴን የሚባል ታሪክ መርማሪ ስለ ናፖሌዮን የተጻፉት ጽሑፎች እስከ 2 መቶ ሺህ እንደሚጠጉ



ተናግሯል:: እንደዚሁም ሙሉ ያልሆነ፣ ስለ ናፖሌዎን ታሪክ የሚናገር አንድ ቤተ መጻሕፍት ለማቋቋም ቢታሰብ በትንሹ ዐሥር ሺህ መጻሕፍት እንደሚገኝ ተገምቷል::[8]

"በአንድ ሰው እጅ ተቀጥቅጦ የተቋቋመ መንግሥት ይህን ያህል ገናናነትና ግርማ ሲያገኝ በጁልየስ ቄሳርም ሆነ በአውግስጦስ ቄሳር ወይም በትልቁ እስክንድር ጊዜ ታይቶ አልታወቀም" ሲሉ ታሪክ መርማሪዎች ይናገራሉ::

ከናፖሌዎን ጋራ ታሪካቸው የሚመሳሰል ትልቁ እስክንድር፣ አኒባል፣ ጁልየስ ቄሳርና ሻርለማኝ ናቸው:: ነገር ግን ናፖሌዎን የተገኘው ከእነዚህ ሁሉ በኋላ ስለ ሆነና ታሪክ መርማሪ ስለ ነበር ከእርሱ በፊት የነበሩትን የታላላቅ ነገሥታት የሕይወት ታሪክ እያነበበ ስሕተታቸውን ትምህርት በማድረግ በጦረኛነት ሊበልጣቸው ችሏል:: እንደዚሁም በፖለቲካና ሕዝብ በማስተዳደር ከፍ ያለ ስጦታ ነበረው::[9]

በናፖሌዮን ዘንድ ነገሥታት እንደ ተራ ሰው ነበር የሚቈጠሩት:: ለምሳሌ አንድ ቀን ናፖሌዮን ግብዣ አድርጐ በግብዣው ላይ ሌሎች ነገሥታት ታዳሚ ነበሩ:: የዓሣ ወጥ እንዲቀርብላቸው ተጋባዦቹ ሲጠብቁ አሳላፊው ስለ ዘገዬ ናፖሌዮን ተቈጥቶ፣ "የናፕል ንጉሥ ሆይ አሳላፊው በምን ምክንያት እንደ ዘገየ ሄደህ እይ" ብሎ ስላዘዘው ... ተነሥቶ ሄደ:: እሱም ሳይመለስ ስለቈየ ናፖሌዮን ተቈጥቶ ደገመና፣ "የናፕል ንጉሥ ምን ሆኖ እንደ ቀረ ሄደህ እይ" ብሎ ሌላኛውን ንጉሥ አዘዘው:: ሁለቱም በመዘግየታቸው ናፖሌዎን ተቈጥቶ የሆላንድን ንጉሥ ሉዊን ሊልከው ሲያዘው የተላኩት ነገሥታት የዓሣውን ወጥ አስይዘው ተመለሱ::[10]

እንደ እርሱ ያሉትን ሰዎች ፈረንጆች "ዤኒ" ይሏቸዋል:: ይኸውም "ጄኒውስ" ከሚለው ከላቲን የመጣ ቃል ነው:: ... ባጭሩ ልዩ ፍጡሮች ማለት ነው::[11]

ኮንት ደ ናርቦን የሚባለውን ሰው አንድ ቀን ናፖሌዮን ሲያነጋግረው፣ "ሰዎች እኔን ምን ይሉኛል?" ብሎ ጠየቀው:: እሱም፣ "ግማሾቹ አምላክ ነው ይሉሃል፤ ግማሾቹ ሰይጣን ነው ይሉሃል:: የሆነው ሆኖ ፍጥረቱ የሰው ነው የሚልህ ሰው የለም" ብሎ መለሰለት::[12]

ናፖሊዎንም ለራሱ ያለው ግምት ከፍተኛ እንደ ነበር ይታወቃል፤ "እኔ ተራ ሰው ስላልሆንኩ የሥነ ምግባርና ግብረ ገብ ሕግጋት ለእኔ አይሆኑም" (I am not an ordinary man, and the laws of morals and of custom were never made for me.) በማለት ይናገር ነበር::[13]

አንድ ታሪክ ጸሐፊ ስለ ናፖሌዎን ሲናገር እንዲህ ይላል፤ “በጻፍኩት ታሪክ ውስጥ፣ ‘ናፖሌዎን ዓለም በጥባጭ፣ ጨካኝ፣ ደም አፍሳሽ ነው’ ብዬ ወቀስኩት፡፡ ነገር ግን አሁን ተመልሶ መጥቶ የጦር ሠራዊቱን በነጋሪት ድምፅ እየመራ በነጭ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ በቤቴ አጠገብ በዐውራ መንገድ ሲያልፍ ባየው ብዕሬን ወርውሬ መጻሕፍት ከተደረደሩበት ገበታዬ ላይ ተነሥቼ ጠመንጃ ተሸክሜ ወደ ጦርነት ቦታ ተከትዬው ሄጄ ደሜን እንደማፈስለት አይጠረጠርም፡፡ ይህንኑም አያቴ ያደረጉት ነገር ነው፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩት አያቶቻችን የድካማቸውን ዋጋ ሳያገኙና ሳይጠይቁት በእጃቸውና በጕልበታቸው አገልግለውታል፡፡”[14]

ላፋዬት የሚባለው የፈረንሳይ ጄኔራል ስለ ናፖሌዮን ጉዳይ፣ “በኀይሉ የሚነሣ ሰው ሁሉ አንድ ቀን የወደቀ እንደ ሆነ የሚደግፈው ሰው የለም፡፡ ስለዚህ ናፖሌዮን በመንግሥቱ ላይ ተቀምጦ ለመኖር ቢፈልግ ሁልጊዜ ድል ማድረግ አለበት፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን የተሸነፈ እንደ ሆነ ወዮለት” ሲል ተናግሮ ነበር፡፡[15] ያም ቃል ደረሰ፡፡ ሁልጊዜ ድል ማድረግ ለማንም አይቻለውምና ናፖሌዮን በመሰሪዋ እንግሊዝ አስተባባሪነት፣ በጄኔራሎቹ ከፍተኛ ክህደት የተነሣ ተሸነፈ፡፡

በቅድስት እሌኒ ደሴት ታስሮ ከቈየ በኋላ በሕመም የመሞቱ ዜና ተሰምቶ በፓሪስ ሲወራ የናፖሌዎን ወታደር ለነበረ ሰው፣ “ናፖሌዎን ሞተ” ብሎ ሌላ ሰው ነገረው፡፡ ወታደሩ ግን እየሣቀ ራሱን ነቀነቀና፣ “ውሸት ነው አትመን፤ እንዲያው ለነገሩ ናፖሌዮን ምን እንደ ሆነ እንደማታውቀው አሳበቀብህ፡፡ እኔስ ... አብሬው ተዋግቻለሁና ደኅና አድርጌ አውቀዋለሁ፡፡ ናፖሌዮን አይሞትም!” ብሎ መለሰለት፡፡[16] ናፖሌዮን ግን ሞቷል፡፡ ጀግና ነው ብሎ ሞት አልማረውም፡፡ ዛሬ ታሪክ ብቻ ነው፡፡ ከሁሉ የሚበልጥ ጀግና በሆነው ሞት ተሸንፏል፡፡

* * *

“ምኒልክ መጓዙን የምትጠይቁኝ፤
ፊትም አላለፈ ኋላም አይገኝ፡፡”

ይህ ደግሞ ለምኒልክ የተገጠመ ነው፤ ከእርሳቸው በፊት የእርሳቸውን ዐይነት ንጉሥ እንዳልነበርና ከዚህ በኋላም እንደማይኖር ያስረዳል፡፡

ስለ ምኒልክ ስናነሣ ጠቢብነታቸው፣ ትዕግሥታቸውና ጀግንነታቸው ይነገራል፡፡ ኢንሳይክሎፒድያ ብሪታኒካ፣ “Ethiopia's strong and wise king” (የኢትዮጵያ ብርቱና ጠቢብ ንጉሥ) በማለት ይገልጣቸዋል፡፡[17] የኢትዮጵያ ሕዝብም ምኒልክን እጅግ ከመውደዱ የተነሣ እንደ እናት ነበር የሚያያቸው፤ ስለዚህም፣ “እምዬ ምኒልክ” የሚል ለወንድ የማይሰጥ መጠሪያ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ ግን እንከን የለባቸውም ለማለት አይደለም፤ ፍጹም አልነበሩምና፡፡

ምኒልክ ምንጊዜም ከማይረሱት ልማዳቸው አንዱ፣ ሠራዊታቸው ምግብ ሳይበላ እሳቸው አይበሉም ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ከዳጃች ውቤ ቤት ተጋብዘው ሄዱ፡፡ ደጃች ውቤም አማታቸውን ምኒልክን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ቤት እንዲገቡ ቢጠይቋቸው፣ “በፊት አሽከሮቼን አስገባና አብላልኝ” ብለው እምቢ አሉ፡፡ አሽከሮቹ ለግብር ሲገቡ የምኒልክንና የየመኳንንቱን በቅሎዎች የያዙ አሽከሮች ቀሩ፡፡ ይህን ያዩት ምኒልክ በቅሎአቸውን “ወዲህ አምጣት” ሲሉ፣ አሽከሮች እየሮጡ በቅሎአቸውን አቀረቡላቸው፡፡ አብረዋቸው ያሉት መኳንንት፣ “ወዴት ሊሄዱ ነው?” እያሉ ሲጠይቁ ምኒልክ የበቅሎዋን መሳቢያ ለኮ ከአሽከራቸው ተቀብለው፣ “ሂድ ግባና ምሳህን ብላ” አሉት፡፡ ሁሉም ደነገጡ፡፡ ምኒልክም አሽከሮቻቸውን ተቈጥተው ወደ ግብር እንዲገቡ ሲያደርጉ፣ አፈታቸው የነበሩት ጸሓፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ከምኒልክ እጅ በቅሎዋን ለመቀበል፣ “ይስጡኝ እኔ ልያዛት” አሏቸው፡፡ ምኒልክም፣ “የኔን ተውልኝና ያንተን ካንተ አሽከር ተቀበል” አሏቸው፡፡ ከዚህ በኋላ መኳንንቱ ሁሉ ከአሽከሩ በቅሎውን እየተቀበለ ሲይዝ አሽከር ምሳውን ሊበላ ወደ ግብር ገባ፡፡ ምኒልክ ከአንዲት የኮክ ዛፍ ሥር በቅሎአቸውን ይዘው ቆመው አሽከሮቻቸው በልተው እስቲወጡ ድረስ ጠጅ እየጠጡ ይጠብቁ ጀመር፡፡[18] “እምዬ ምኒልክ” የሚለውን ስም እንደ ኖሩት ይህ አንድ ማረጋገጫ መሆን ይችላል፡፡

ምኒልክ ለሕዝቡ አባትም ናቸው፡፡ ሲናደዱ የተለየ ጠባይ ነበራቸው፡፡ ወዲያውኑ እርምጃ አይወስዱም፡፡ ጥቂት ቈየት ብለው አንድ ክፍል ውስጥ ይገቡና ያን ያናደዳቸውን ሰውዬ ያስጠራሉ፡፡ ሰውዬው ተጠርቶ እስኪመጣ ምኒልክ ደኅና ቆመጥ ዱላቸውን ይዘው ይጠብቃሉ፡፡ ጥፋተኛው ወይም ያናደዳቸው ሰው ካሉበት ክፍል ሲገባ በያዙት ዱላ ደኅና አድርገው ደብድበው ይለቁታል፡፡ ምኒልክ ሰውዬውን ሲመቱ የሚመቱት እስኀንበሰው ጀርባውን ነው፡፡ ይህም አጉል ቦታ ተመትቶ እንዳይደማ ወይም እንዳይበላሽ ነው፡፡ ደብድበው ሲበቃቸው ሁለቱም ከነበሩበት ቦታ ያለ ቂም ወዳጅ መስለው ይመለሳሉ፡፡ ተደብዳቢው ያልተነካ መስሎ በፈገግታ ቢመለስም ሁሉም የቀመሰውና የሚቀምሰውም ስለሆነ ጒዳዩን ያውቀዋል ...፡፡ ተደብዳቢውን ጓደኞቹ፣ “ስንት ፍትፍት ጎረስክ?” ወይም “ስንት ብርሌ ጠጅ ጠጣህ?” እያሉ ይቀልዱበታል፡፡ ይህም ድብደባ ለተራ ሰዎች ብቻ ሳይሆን እስከ ራስ ማዕረግ ድረስ ያሉት ሁሉ የቀመሱት ነው፡፡ በዚህ ነው ሕዝቡ አባታችን ይላቸው የነበረው፡፡[19]

ምኒልክ አገራቸውን ለማሳደግ ብዙ ለፍተዋል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት፣ ባቡር፣ ስልክ፣ ፖስታ፣ ኤሌክትሪክ፣ አውቶሞቢል፤ ባሕር ዛፍ፣ የቧንቧ ውሃ፣

ዘመናዊ ሕክምና፣ ሆስፒታል፣ የመድኃኒት መሸጫ ሱቅ፣ ባንክ፣ ገንዘብ፣ ማተሚያ፣ ጋዜጣ፣ ሆቴል፣ ፖሊስ፣ ፎቶግራፍ፣ የጽሕፈት መኪና፣ ሲኒማ፣ ወፍጮ፣ ጫማ፣ የሙዚቃ ትምህርት፣ የሙዚቃ ሸክላ፣ ብስክሌት፣ ላስቲክ ... ወዘተ ወደ አገሪቱ ያስገቡት ወይም ያስጀመሩት እሳቸው ናቸው።

እኚህ ሰው የአድዋ ጀግና ናቸው። በአፍሪካ የጦርነት ታሪክ ሁለት የተከበሩና የተደነቁ ጦርነቶች አሉ። አንደኛው ከ2000 ዓመታት በፊት ሀኒባል አውሮፓውያንን ድል ያደረገበት ጦርነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከ2000 ዓመት በኋላ ኢትዮጵያውያን በአድዋ ጦርነት አውሮጳን ድል ያደረጉበት ጦርነት ነው። የአድዋው ጦርነት ኢትዮጵያን በዘመናዊው የዓለም ካርታ ውስጥ ስሟን አስገባት።[20] ከአድዋው ጦርነት በኋላ በጣልያን አገር ከፍተኛ ሽብር መነሣቱ ይታወቃል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣኑን ለቋል። ብዙ ጣል ያናውያን ወጣቶችም፣ "ምኒልክ ሕያው ይሁን" እያሉ ይጮኹና ሌሎችም እን ዲሉ ያስገድዱ ነበር።[21]

ምኒልክ ሲታመሙ ግን ድካማቸው ታወቀ። ፈረንጅ ሐኪሞቻቸውን፣ "ሳልሞት አድኑኝ ... ገና የምሠራው ብዙ ሥራ አለኝ ... " ወደሚል ልመና ገቡ።[22] ግና ሥራቸውንም ባይጨርሱ ሞት ምን ቸገረው? ልመናስ የት ያውቅና! የአድዋው አንበሳ መዳን እየለመኑ ተሸነፉ። ሞት ጀግናን ይምራል?

በእርግጥ እምዬ ምኒልክ ከዚያ በፊትና በኋላ ለኢትዮጵያውያን መሪዎች ያልተፈቀደ የሚመስለውን ታምሞ የመሞት ዕድል አግኝተዋል። ሆኖም ተወ ዳጅ ከመሆናቸው የተነሣ ሞታቸው ከተሰማ አገር ይረበሻል ተብሎ ስለ ተሠ ጋም "በሕይወት አሉ" እየተባለና እየተወራ ሞታቸው ለሁለት ዓመት ከዐሥር ወር ድረስ ከሕዝብ ተደብቆ ቈይቷል።[23] ሞት ግን የሕዝብን ፍቅር መች ይፈራና?!

ጀግና ምን ቢጀግን ገዳዩን አይገድልም (ሞትን ለማለት ነው)። ሞት የጀግኖች ሁሉ ጠላት ነው፤ የጀግኖች ጀግና ነው፤ ታላላቅ ጀግኖችን ሁሉ አስገ ብሯል። ጠቢቡ ሰሎሞን፣ ነቢዩ ሙሴ፣ ንጉሥ ዳዊት፣ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ፣ በላይ ዘለቀ፣ ራስ አሉላ አባነጋ፣ አበበ ቢቂላ፣ ዊንስተን ቸርችል፣ ክዋሚ ንኩሩ ማህ፣ ጆሞ ኬንያታ፣ ኦሊቨር ታምቦ፣ እማሆይ ቴሬዛ፣ ጁልየስ ቄሳር፣ ትልቁ እስክንድር፣ አብርሃም ሊንከን፣ ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ ካርል ማርክስ፣ አልበርት አነስ ታይን፣ ዊልያም ሼክስፒር፣ ይሳቅ ራቢን፣ ማርቲን ሉተር፣ ሀዲስ አለማየሁ፣ አክሊሉ ሀ/ወልድ፣ ማሃተማ ጋንዲ ... ሁሉም በሞት ቍጥጥር ሥር ናቸው።

ሞት ከሁሉ በኋላ የሚሸነፍ ጠላት ነው (1ቆሮ. 15፥26)። ስለዚህም ሞት የሚሸነፍበትን ቀን ሰው ሁሉ ይናፍቃል።



ጊዜ በረርክ በረርክ፣
ጊዜ በረርክ በረርክ፣
ግና ምን አተረፍክ፣
ግና ምን አጐደልክ?
ሞትን አላሸነፍክ፣
ሕይወትን አልገደልክ።

እንደተባለው ነው።[24] ሕይወትም ይኖራል፤ ሞትም ይኖራል ማለት ነው። ሞት ይሸነፍ ይሆን? መቼ? የሰው ሁሉ ጥያቄ ነው።

"ለሁሉ ጊዜ አለው" ይላል ሰሎሞን፤
እጠይቀው ነበር በተገናኘን
ሞት የሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን?[25]

በማለት አንዱ ሲገጥም፣ ሌላኛው ደግሞ፣ "የት አባቱ! ሞትም ይሙት!" በማለት ቍጭቱን ለመወጣት ይሞክራል።[26] ሆኖም ሰዎች ተሰብስበው ግጥም ቢገጥሙበት፣ ቢፎክሩና ቢያቅራሩ ለሞት ምኑም አይደለም፤ እየፎከሩም ወስዷቸዋል (ይወስዳቸዋልም)።

ሰዎች አንድ ጊዜ መሞት፣ ከዚያ በኋላም ፍርድ ተመድቦባቸዋልና (ዕብ. 9፥27) ሁሉም ይሞታሉ። እስከ ዛሬ ዓለማችን ያፈራቻቸው ጀግኖች፣ ጠቢባን፣ ነገሥታት፣ ኀያላንና ተወዳጆችን ሁሉ ያሸነፈው ሞት፣ አሁን ያሉትን ማንዴላን፣ ኤርየል ሻሮንንና መሐመድ አሊን ብቻ ሳይሆን፣ ነገ የሚመጡ ትንም መርታቱ አይቀሬ ነው። ሁሉን ያሸንፋል። የሁሉ የበላይ ነው።

* * *

ግና ሞት በታሪኩ አንድ ጊዜ ተሸንፏል፤ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት! በብዙ ጥረትና ሤራ ሽንፈቱን አፍኖ ሊያስቀር ቢሞክርም የዚያን ቀን ብቻ ተረትቷል! አምን ደም ግባት የሌለው፣ የተናቀ፣ የተገረፈ፣ የደከመ፣ የተጠማ፣ ሥቁይና የሕማም ሰው ሞትን አሸንፏል። ይህም ቀላል ወይም የአንድ ሰው ጉዳይ ብቻ አልነበረም። ከዚያ በኋላ ትንሣኤ የሚባል ነገር ወደ ዓለም ገብቷል። "ሞት በአንድ ሰው በኩል እንደ መጣ የሙታንም ትንሣኤ በአንድ ሰው በኩል ሆኖአል። ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ፣ እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ" (1ቆሮ. 15፥21-22)።

ሞት ለጊዜው ከእጁ ያፈተለኩትንም ቢሆን አድብቶ አሸንፏቸዋል። በጣም ጠንቃቃ ነው። ጠላቶቹን አይንቅም፤ ማንንም አያምንም። ስለዚህ ይህ ንንም ሰው ስለ ተጠራጠረ አለቅነትንና ሥልጣናትን ሁሉ በላይ በላይ ደራርቦ

መቃብሩን አስጠብቆ ነበር፡፡ ታዲያ ምን ዋጋ አለው?! የተቀበረውን እዚያው ለማስቀረት የቻለውን ሁሉ ጥሯል፡፡ የአሁኑ ግን እስካሁን እንደ ነበሩት አይደለም፤ የተለየ ነው፡፡ ክርስቶስ ከሙታን መነሣት ብቻ ሳይሆን፣ "ወደ ፊት እንዳ ይሞት፣ ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና" (ሮሜ 6፥10)፡፡

ኢየሱስ ሲሞት ሁሉ ነገር ማብቃት ነበረበት፡፡ ግን እንዲያውም ሁሉ ነገር የጀመረው ያኔ ነው፡፡ የእግዚአብሔርም የኀይሉ ታላቅነት የተገለጠው ዓለ ምን ሲፈጥር አልነበረም፡፡ እስራኤልን ከግብፅ ሲያወጣም አልነበረም፡፡ የዮርዳ ኖስን ወንዝ ከፍሎ ሕዝቡ በደረቅ መሬት ሲሻገርም አልነበረም፡፡ ከፍጥረት በፊትም ይሁን በኋላ ከተገለጡት ሥራዎቹ መካከል የእግዚአብሔር ታላቅነት የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሣ ነው (ኤፌ. 1፥19-20)፡፡

የኢየሱስ ትንሣኤ የእግዚአብሔር ትልቅ ኀይል የተገለጠበት ቢሆንም፣ እንደ ቀላል የተደረገ ይመስላል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ፣ ድል አድርጎ ሲነሣ ብዙዎቻችን እንደምናስበው መቃብሩ አልተፈነቃቀለም፡፡ መቃብሩ ሳይ ፈነቃቀል እርሱ ሞትን ፈንቅሎ ወጥቷል፤ መቃብር ሊይዘው አይችልምና! ድንጋዩም አልተንከባለለም ነበር፤ ድንጋዩ የተንከባለለው ከእርሱ መነሣት በኋላ ነው (ማቴ. 28፥2)፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶ እንኳ፣ ድንጋዩ ባለመንከባለሉ ጠባቂዎቹ ጥበቃቸውን ቀጥለዋል፤ ባዶ መቃብር ጥበቃ (ማቴ. 28፥1-5) (ይህንንና የሐዋርያት ሥራ 5፥21-25ን ሳነብ ሣቄ ይመጣል፡፡ "እግዚ አብሔር 'sense of humour' የለውም" የሚል ይኖር ይሆን?)፡፡

እንደ አልዓዛር በተገነዘበት ከፈን እንደ ተጠቀለለም አልተነሣም፡፡ ልክ ደቀ መዛሙርቱ በተዘጋ በር ተቀምጠው ሳሉ ግድግዳውን ዐልፎ እንደገባው ሁሉ፣ የተገነዘበትን ልብስም ዐልፎ ተነሣ፡፡ ስለዚህ ከተልባ እግር የተሠራው ከፈን፣ በራሱ ላይ ተጠምጥሞ የነበረው ጨርቅ በነበሩበት በትክክለኛ ቦታቸው እንዳሉ እርሱ በውስጣቸው የለም (ዮሐ. 20፥5-7)፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሞትን አሸነፈ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተወደደም ተጠላ ታሪክ ለሁለት እንደ ተከፈለ ቀርቷል፡፡

ሞት ያኔ ተሸነፈ! ዛሬም ጕልበት ያለው ቢያስመስልም፣ አማኞች ሞት መሸነፉን እናውቃለን፤ አሸናፊውንም እናምናለን፡፡ ጌታ ኢየሱስን በእውነት ለምንከተል ለእኛ፣ ሞት እንደ እንቅልፍ ነው፡፡ ብዙዎች በሞት ተሸንፈዋል፤ ጌታ ክርስቶስ ግን በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን በሞቱ አሸንፏል፤ በዚህም ከሞት ፍርሀት ነጻ አውጥቶናል (ዕብ. 2፥14-15)፡፡ ስለዚህ ሞት ወደ ምንናፍቀው አምላካችን መሄጃ ድልድያችንም ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "ሞትም ጥቅም ነውና" በማለት የሚናገረው ለዚህ ነው (ፊልጵ. 1፥21)፡፡



በትንሣኤም እናምናለን፤ የሞትና የሲኦል መከፈቻ በማን እጅ እንዳለ እናውቃለን (ራእይ 1፥18)፡፡ ዶ/ር ቫንስ ሃቭነር የተባሉ አገልጋይ ከሚስታቸው ሞት በኋላ፣ "ባለቤትህን ማጣትህን ሰማን" እያሉ ለሚጠይቋቸው ወገኖች፣ "በፍጹም" በማለት ይጀምሩና፣ "የት እንዳለች በትክክል ዐውቃለሁና አላ ጣኋትም፡፡ ሰዎች ያሉበትን ቦታ በትክክል ካወቃችሁ አላጣችኋቸውም!" በማ ለት ይመልሱ ነበር፡፡ ከዚያም፣ ሚስታቸው ከክርስቶስ ጋር በመሆኗና ክርስቶስ ደግሞ ከእሳቸውም ጋር በመሆኑ አሁንም በክርስቶስ ውስጥ አብረው እንዳሉ ያስረዳሉ፡፡[27] ሞት ድል በመነሣቱ ያገኘናቸውን ትሩፋቶች ዘርዝሮ መጨረስ ያዳግታል፡፡

እናቴ ባረፈችበት ሌሊት ሐኪም ቤት ሆኜ ራሴን ብዙ ጥያቄዎች ጠይ ቄአለሁ፡፡ ትንሣኤ ምንድን ነው? እውነትስ ነው? በምን እናውቃለን? ትንሣኤ ሰዎች ራሳቸውን ለማጽናናት የፈጠሩት አስደሳች ተረት ቢሆንስ? ... በርካት ጥያቄዎች ነበሩኝ፡፡ በዚያ ረዥም ሌሊት ይህን የመሳሰሉ ነገሮችን ሳነሣና ስጥል ነበር ያደርኩት (ማደር ከተባለ!)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱን ሳስብ ግን ጥያቄዎቼ ሁሉ ይበተናሉ፡፡ ታሪክ የተቀየረው በእርሱ ትን ሣኤ ነው፡፡ ለካ የእርሱ ትንሣኤ የእርሱ ብቻ አይደለም፤ ከሙታን በኩር መሆኑ የእኛንም ትንሣኤ ይጠቁማል (1ቆሮ. 15፥20)፤ እርሱን አምነው የሞቱ ይነሣሉ፡፡ ይህ እውነት በጌታ ትንሣኤ ተረጋግጧል፡፡ ከእናቴ ሞት ተጽናንቼ፣ ወደ ዕረፍትና ማንቀላፋት መሄዷን አምኜ የወጣሁት በጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ ላይ ሆኜ ነው፡፡ እናቴ ያለችበትን ዐውቃለሁና አላጣኋትም፡፡

ጌታ ኢየሱስ ዛሬም ሰዎችን ሲያሸንፍ አስገራሚ ነው፡፡ ራሱን ከሁሉ በላይ የቆለለውን መሬት አውርዶ ይማርከዋል፡፡ ባለ ሥልጣኑንና ፈላጭ ቈራ ጩን ወህኒ ያስገባውና ብቻውን ይገናኘዋል፡፡ ጠቢቡና ዐዋቂውም ዕውቀትን ሲፈልጉ፣ ጥበብን ሲከተሉ ይገናኝና ከሁሉ የሚበልጥ ጥበብና ዕውቀት እርሱን ማወቅ መሆኑን ያሳያቸዋል፡፡ ማን ከልካይ አለበት?! አጀብ የበዛበትን ሰው በዚያ ሁሉ አጀብ መኻል ብቸኝነት እንዲሰማው ያደርግና ይገለጥለታል፤ ሲፈ ልግም ነጥሎ ይወስደዋል፡፡ ብቻውን በምድረ በዳ ያለውም አያመልጥም፡፡ ጀግናውን ያለ አንዳች መሣሪያ ያንበረከካል፡፡ አንድም ቀን ጦር መሣሪያ ታጥቆ አያውቅም፤ ጦረኞች ሁሉ ግን በፊቱ ይርዳሉ፡፡ ሞትን ያሸነፈ ሌላው እንዴት ያቅተዋል? የዘመናት ጠላቶቹን የዘላለም ወዳጆቹ ያደርጋቸዋል፡፡ ሞትን ማም ለጥ የፈለገ የግድ እርሱን መከተል አለበት፤ ሞት እንኳ ይፈራዋልና!

ጌታ ኢየሱስ ብቻ ሞትን አሸንፏል፡፡ እኛም ግርማውን ዐይተን በፈቃ ዳችን ተንበርክከንለታል፤ ፍጥረት ሁሉ የግዱን የሚንበረከክበት ቀን ግን ይመ ጣል፡፡ አቤት! ማምለክስ እርሱን ነው!

## ማስታወሻ


1. ተክለጻድቅ መኩሪያ፤ *ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት* (አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1981 ዓ.ም) ገጽ 438::
2. ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ቴዎድሮስ* (አዲስ አበባ፣ 1985 ዓ.ም) ገጽ 293::
3. ጸጋዬ ገ/መድህን፤ *እሳት ወይ አበባ* (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም) ገጽ 123::
4. ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ቴዎድሮስ*፣ ገጽ 433::
5. *አማርኛ መዝገበ ቃላት* (አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር፣ 1993 ዓ.ም)::
6. ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ቴዎድሮስ*፣ ገጽ 304::
7. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 306::
8. ከበደ ሚካኤል፤ *ታላላቅ ሰዎች* (አዲስ አበባ፣ 1960 ዓ.ም) ገጽ 110::
9. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 134::
10. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 137::
11. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 111::
12. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 138::
13. Philip Yancey, *Rumours of Another World* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2003), 103.
14. ከበደ ሚካኤል፤ ታላላቅ ሰዎች፣ ገጽ 139::
15. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 125-126::
16. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 140::
17. *Britannica's Concise Pictured Encyclopaedia Volume 4* (Chicago, Overseas Edition, 1967), 491.
18. ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ምኒልክ* (አዲስ አበባ፣ 1984 ዓ.ም) ገጽ 434::
19. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 433::
20. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 217::
21. ተክለጻድቅ መኩሪያ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ: ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ* (አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1964 ዓ.ም) ገጽ 98::
22. ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ምኒልክ*፣ ገጽ 468::
23. *ዝኒ ከማሁ*፣ ገጽ 493::
24. ደበበ ሰይፉ፤ *ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ* (አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም) ገጽ 96::
25. ከበደ ሚካኤል፤ *የቅኔ ውበት* (አዲስ አበባ፣ 1961 ዓ.ም) ገጽ 70::
26. ጸጋዬ ገ/መድህን፤ *እሳት ወይ አበባ* (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም) ገጽ 123::
27. ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *ሰማዩ ዝም ሲል* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም) ገጽ 104::




# ቦንሆፈር - ጨለማውን የሰነጠቀ ኮከብ

ዲትሪች ቦንሆፈር መካከለኛ መደብ ካለው የተማረ ቤተ ሰብ ተወለደ:: አባት በነርቭ ሕክምና ስመ ጥር ፕሮፌሰር ናቸው፤ ታላቅ ወንድሙ ከአልበርት አነስታይን ጋር ምርምር ይሠራል:: የአባቱን ዱካ እንደሚከተል ሲጠበቅ የነበረው ባለ ብሩህ አእምሮው ቦንሆፈር፣ ነገረ መለኮት ለመማር የወሰነው በዐሥራዎቹ ዕድሜው ነበር፤ ይህም ለቤተ ሰቦቹ አሳዛኝና አስደንጋጭ ውሳኔ ሆኖባቸዋል:: ታላቅ ወንድሙ፣ "ቤተ ክርስቲያንን ለመሰለች ድኻ፣ ድኩም፣ የማትረባና ቡርዣ ተቋም" ሕይወቱን እንዳያባክን ሲመክረው፣ የዐሥራ አራት ዓመቱ ቦንሆፈር፣ "የምትናገረው እውነት ከሆነ፣ ልለውጣት ይገባል!" በማለት መልሶለታል::

ትጉህና ታታሪ ነፍሱ በ21 ዓመቱ ዶክትሬቱን እንዲቀበል አስቻለችው:: በቤተ ክርስቲያን ሁሉን አቀፋዊነት ላይ የሚያተኩረው መመረቂያ ሥራው ስለ ቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ትልቅ ፋይዳ ያለው ምልከታ የቀረበበት ሲሆን፣ ዕውቁ የነገረ መለኮት ሰው ካርል ባርዝ፣ "ነገረ መለኮዊ ተአምር" ሲል ገልጾታል:: በዚያው የነገረ መለኮት መምህር የሆነው ቦንሆፈር ከባርዝ ጋር ጉድኝት ፈጠረ::

ሰይጣናዊው ሂትለር የጀርመንን መንበር ለመያዝ ሲያደባ ቀድሞ የነቃው ቦንሆፈር ማስጠንቀቅ ጀምሮ ነበር፤ ሰሚ አጣ እንጂ! የጀርመን ሉተራን ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ድጋፍ የሚሰጣት ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ነበረች:: ሂትለር አይሁዶችን ከሥራና ከደሞዝ፣ ... ሲያግድ ቤተ ክርስቲያን መልስ አልነበራትም:: አይሁዶች ጀርመናውያንን ቀጥረው ከማሠራትና ጀርመናውያንን ከማግባት በሕግ ሲከለከሉም ቤተ ክርስቲያን ዝምታን መርጣለች:: ከጀርመን እያጋዘ ለሞት ሲማግዳቸውም ለውጥ አልነበረም:: ቦንሆፈር ግን ወዳጆቹን በማስተባበርና ገንዘብ በማሰባሰብ ጥቂት ቢሆኑም አይሁዳውያንን ወደ ሌላ አገር አስመልጧል:: መከራ ከሚቀበሉ ጋር መከራ መቀበልን መርጧል!

ከዚያም አደጋውን ካስተዋሉ ጥቂት የቤተ ክርስቲያን መሪ አገልጋዮች ጋር ተባብሮ፣ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ የሆነች "Confessing Church" የተሰኘች ቤተ ክርስቲያንን አደራጀ:: ቦንሆፈር በኅቡዕ ለተመሠረተው የዚህች ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት ተቋም መሪ በመሆን ቀን ከሌሊት በማስተማር ይባትል ነበር::

ዘመኑ እየከፋ፣ ጨለማው እየከበደ መጣ፤ በሂትለር ወጣቶች አስተባባሪነት ጀርመንን ከአይሁዳውያን ለማጽዳት ዘመን ዘለቅ ብርቅዬ መጻሕፍት በአደባባይ ነደዱ:: መጽሐፍ ቅዱስን ከአይሁዳውያን "ለማላቀቅ" መንግሥት ባሳደረው ጫና ብዙ ታሪኮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ተወገዱ፤ አንዳንዶቹም ተቀየሩ:: ጌታ ኢየሱስ እንኳ በሥጋ አይሁዳዊ እንዳልሆነ ከህደት ማስተማር ተጀመረ:: ቦንሆፈር ግን ታሪካዊ ዱራውን የጠበቀ መንፈሳዊ መጽሐፍ በድብቅ አዘጋጅቶ አሳተመና አሠራጨ፤ ከዚያ ግን መጽሐፍ ከማሳተምም ሆነ ይፋዊ ንግግር ከማድረግ ታገደ::

ቤተ ክርስቲያን ከሂትለር ጋር በነበራት የአቋም መጣጣም ተስፋ የቈረጠው ቦንሆፈር በመጋቢነት ለማገልገል ወደ ለንደን ሄደ:: እዚያም ሆኖ ግን *ለኮንፌሲንግ ቸርች* ዕድገት እገዛና ድጋፍ ያደርግ ነበር፤ ሁለት ዓመቱን ሲጨርስ ወደ ጀርመን ተመለሰ::

ነገሮች በአገሪቱ ላይም ሆነ በቦንሆፈር ላይ እየከረሩ ሲመጡ ወዳጆቹ ወደ አሜሪካ እንዲሸሽ አደረጉት:: እርሱ ግን፣ "ሕዝቤን በመከራው ወቅት አብሬው ካልሆንኩ፣ ከጦርነቱ በኋላ በሚኖረው ክርስትናን እንደገና የመገንባት ሥራ የመሳተፍ መብት አይኖረኝም" በማለት ወደ እሳቱ ተመልሶ ገባ:: አንዳንድ የሂትለር የወታደራዊ መረጃ መኮንኖች ከሚመሩት የሂትለርን ወንጀል ማስረጃ ከሚያሰባስብ ኅቡዕ ቡድን ጋር መሥራት ጀመረ:: በውስጣዊ ርምጃ ሂትለርን ለማስወገድ ዝግጁነታቸውን ለብሪታንያ መንግሥት ቢገልጡም ቸርችል ሊረዳቸው አልወደደም:: በመጨረሻም ቡድኑ ሂትለር ላይ ግድያ እንዲፈጸም ወሰነ::

ቦንሆፈር አይሁዳውያንን ከአገር ለማሸሽ ያሰባሰበውን የውጭ ምንዛሪ ዱካ የተከተለው የናዚ ፖሊስ አይሁዳውያንን ማስመለጡን ደረሰበት፤ ቦንሆፈር ለአንድ ዓመት ተኩል ያለ ፍርድ ታሰረ:: መንፈሳዊ እንቅስቃሴውን ግን እስር ቤትም አልተወም:: በድብቅ የወጡ ደብዳቤዎቹ በመጽሐፍ መልክ ታትመው ተሰራጭተዋል:: የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ማምለጫ መንገድ አዘጋጅተውለት ነበር፤ እርሱ ግን ቤተ ሰቦቹ ላይ የሚያመጣው ጣጣ ፈርቶ እምቢ አለ::

ሂትለር ጦርነቱ እንዳበቃለትና መጨረሻው እንደተቃረበ ቢያውቅም፣ ቦንሆፈር ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ስለ ነበረው፣ ጀርመን ትርምስ ውስጥ ገብታ እስረኞች ከቦታ ቦታ በሚዘዋወሩበት ወቅት አፈላልጎ የሚገድለው ቡድን ላከበት:: ቦንሆፈር ያለ ምስክር፣ ያለ ማስረጃ ሞት ተፈረደበት:: "ይህ መጨረሻው ነው - ለእኔ ደግሞ የሕይወት መጀመሪያ" የሚለውን ስብከቱን እንደ ጨረሰ አንድ ማሠቃያ ካምፕ ውስጥ ልብሱን አስወልቀው በስቅላት ገደሉት:: በቦታው የነበረው ሐኪም ስለ ቦንሆፈር የጸሎት ትጋት፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን ስለ ማስገዛቱና ከአጭር ጸሎት በኋላ ወደ መሰቀያው ስላደረገው ልበ ሙሉ ርምጃ ልብ የሚነካ ምስክርነት ሰጥቷል:: ከሁለት ሳምንት በኋላ ያ ከተማ በአሜሪካ ጦር እጅ ወደቀ:: የሶቭየት ጦር ደግሞ ከሦስት ሳምንት በኋላ በርሊንን ያዘ፤ ሂትለርም ራሱን ገደለ::

አንዱ ቦንሆፈር ብዙ ሰው ነው፤ በሠላሳ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜው ቢያልፍም ሕይወቱና ኑሮው በጀርመን ቤተ ክርስቲያን ላይ ጉልሕ ተጽዕኖ አለው:: ክርስትና አገራዊ ኀላፊነትን በሚመለከት ተግባራዊ እምነት መሆኑን በተግባር ገልጧል:: ለዓለም ሰላም ሮጧል:: ከሌሎች የክርስትና ቡድኖች ጋር በትብብር መሥራትን አሳይቷል:: ጥልቅ ፋይዳ ያላቸው ነገረ መለኮታዊ መጻሕፍትን ትቶ ዐልፏል:: ክርስትናን ለዘመናዊው ዓለም እንደገና በመተርጐምም ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: ራሱን መሥዋዕት በማድረግ ድቅድቁን ጨለማ የሰነጠቀው በራሪ ኮከብ ዛሬም በብዙዎች ልብ እንዳበራ ነው!



# ዋቢ ጽሑፎች

## መጻሕፍት

ሃይማኖተ አበው፡ የጥንት አባቶቻችን ሃይማኖት (አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ፣ 1982 ዓ.ም)::
መርስዔ ኀዘን አበበ፤ *ሙሻዙር* (አዲስ አበባ፣ 1981 ዓ.ም)::
መስፍን ወልደ ማርያም፤ *አገቱኒ ተምረን ወጣን* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም)::
ሜሮን ጌትነት፤ *ዙረት* (አዲስ አበባ፤ 2002 ዓ.ም)::
ምኒልክ አስፋው፤ *ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፡ ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች* (አዲስ አበባ፣ 1999 ዓ.ም)::
ሮበርትሰን ማኩልከን (ተርጓሚ ገበየሁ አየለ)፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ ምግባር፡ የመግቢያ ሐሳቦች (አዲስ አበባ፡ ኤስ አይ ኤም ፣ 2002 ዓ.ም)::
ሮናልድ ደን (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ የወዳጅ ፍላጻ (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም)::
__________ (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ የእምነት ኀይል (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም)::
__________ (ትርጒም ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ ሰማዩ ዝም ሲል (አዲስ አበባ፡ 2003 ዓ.ም)::
ሰለሞን ዴሬሳ፤ *ዘበት እልፊቱ* (አዲስ አበባ፣ 1991 ዓ.ም)::
ሰለሞን ጥላሁን፣ *ሥምረት ገ/ማርያም፤ ደማቆቹ /ፀሐያተ ሌሊት/* (አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም)::
በቀለ ወ/ኪዳን፤ *ሪቫይቫል፣ ኢትዮጵያ እና የመጨረሻው መጨረሻ* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም)::
ተስፋ እንዳለ (ቀሲስ)፣ *ነገረ ሥጋዌ* (አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2001 ዓ.ም)::
ተክለጻድቅ መኩሪያ፤ *ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት* (አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ 1981 ዓ.ም)::
______________ ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ* (አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1964 ዓ.ም)::
ተፈሪ ሙዘይን (ቄስ) እና ኬርቱ ኒዩገሬን (ሲ/ር)፤ *ዲቁና (ተግባራዊ ክርስትና)* (አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክ መካነ ኢየሱስ፣ 1998 ዓ.ም)::
ተፈራ ኀይለ ሥላሴ (አምባሳደር)፤ *ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ ከ፲፰፻፺፯-፲፱፻፴፯* (አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 1999 ዓ.ም)::
ታደሰ ዘወልዴ (ቀኛዝማች)፤ *ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ (አባ መላ)፣ አጭር የሕይወት ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ 1997 ዓ.ም)::
ቴዎድሮስ ደመላሽ፤ *ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን* (አዲስ አበባ፣ 2004 ዓ.ም)
*ኒቆድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች* (አዲስ አበባ፣ አአዩ ፕሬስ፣ 2002 ዓ.ም)::
ኑረዲን ዒሣ፤ *መደድ* (አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም)::
ንጉሤ ቡልቻ፤ *መሰተአየት፣ ራስ ታዘብና ተሐድሶአውያን መጣጥፎች* (አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም)
አለማየሁ ገላጋይ፤ *ስብሐት ገብረእግዚአብሔር፡ ሕይወትና ክህሎት* (አዲስ አበባ፣ ማኅሌት አሳታሚ፣ 2000 ዓ.ም)::
*አማርኛ መዝገበ ቃላት* (አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር፣ 1993 ዓ.ም)::
አሳምነው ባረጋ፣ *የትሮይ ፈረሶች እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም)::
አብርሃም ረታ ዓለሙ፤ *እቸክቸክ፡ የቃሊቲ እንጉርጉሮዎች* (አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም)::

ኤልያስ በቀለ፤ *ክርስቲያን እና ፖለቲካ፡ በፖለቲካ ሂደት ውስጥ የሚኖረው የቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያኖች ተሳትፎ* (አዲስ አበባ፣ የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 1996 ዓ.ም)፡፡
ራስ እምሩ ኃ/ሥላሴ፤ *ካየሁት ከማስታውሰው* (አዲስ አበባ፣ አአዩ ፕሬስ፣ 2001 ዓ.ም)፡፡
ከበደ ሚካኤል፤ *ታላላቅ ሰዎች* (አዲስ አበባ፣ 1960 ዓ.ም)፡፡
__________፤ *የቅኔ ውበት* (አዲስ አበባ፤ 1961 ዓ.ም)፡፡
ደረጀ በላይነህ፤ *ብሌፕ ጀንበር ... እና የፍቅር ደብዳቤዎች* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም)፡፡
ደረጀ ገ. (ቀሲስ)፤ *ገመና ዘ8ዱ* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም)፡፡
ደበበ ሰይፉ፤ *ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ (የብርሃን ፍቅር ቅጽ ፪)* (ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም)፡፡
ዳንኤል ተፈራ ጀ.፤ *ዳንዲ የነጋሶ መንገድ* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም)፡፡
ዳዊት ጸጋዬ፤ *አርነት የወጡ ሐሳቦች* (አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም)፡፡
ዴሪክ ፕሪንስ (ተርጓሚ ጳውሎስ ፈቃዱ)፤ *የጋብቻ ኪዳን* (አዲስ አበባ፣ 1994 ዓ.ም)፡፡
ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ምኒልክ* (አዲስ አበባ፣ 1984 ዓ.ም)፡፡
__________፤ *አጤ ቴዎድሮስ* (አዲስ አበባ፣ 1985 ዓ.ም)፡፡
ጸጋዬ ገ/መድህን፤ *እሳት ወይ አበባ* (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም)፡፡
ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፤ *ኦቶባዮግራፊ* (የሕይወቴ ታሪክ) (አዲስ አበባ፣ አአዩ ፕሬስ፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

የተሻሻለው የቤተ ሰብ ሕግ (1992 ዓ.ም)፡፡
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት (1987 ዓ.ም)፡፡
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ (1997 ዓ.ም)

Adeyemo, Tokunboh, *Is Africa Cursed? A Vision for the Radical Transformation of an Ailing Continent* (Nairobi: WordAlive Publishers, 2009).
Bonhoeffer, Dietrich, *Letters and Papers from Prison* (York: Macmillan, 1953).
*Britannica's Concise Pictured Encyclopaedia Volume 4* (Chicago: Overseas Edition, 1967).
Buckingham, Jamie, *Daughter of Destiny* (Plainfield, N.J.: Logos International, 1976).
Carson, Clayborne, *The Autobiography of Martin Luther King, Jr.* (London: Abacus, 2008).
Chadwik, Henry, *Saint Augestine Confessions* (Oxford: Oxford University Press, 1992).
Chapman, Colin, *Cross and Crescent: Responding to the Challenge of Islam* (Downers Grove, Illinois: IVP Books, 2007).
Cho, Paul Yonggi, *The Fourth Dimension: The Key to Putting Your Faith to Work for Successful Life* (Plainfield, New Jersey: Logos International, 1979).
Cloud, Henery & Townsednd, John, *Boundaries* (Grand Rapids: Zondervan, 1992).



Conner, J. Kevin, *The Church in the New Testament* (Portland: Bible Temple Publishers, 1989).
Donne, John, *Devotions Upon Emergent Occasions* (Michigan: The University of Michigan Press, 1986).
Eriksson, Bo, et al, *The Gospel of Restoration: Experiences From a Field Study in Ethiopia 1998* (Uppsala: Swedish Institute of Missionary Research, 1999).
Feinberg, John S., *Where Is God? A Personal Story of Finding God in Grief and Suffering* (Nashville, Tennessee: Broadman & Holman Publishers, 2004).
Fidel, Castro, *My Life* (London: Penguin Books, 2008).
Fisher, G. Richard and Goedelman, et al, *The Confusing World of Benny Hinn* (Saint Louis, Missouri: Personal Freedom Outreach Plainfield, 2001).
George, MacDonald, *Creation in Christ* (Wheaton, Illinois: Harold Shaw, 1976).
*Harper's Bible Dictionary* (New York: Harper & Brothers, 1952).
Harvey, Edwin and Lillian, *Kneeling We Triumph* (Harvey Christian Publishers, 2012).
Kendall, R. T., *Second Chance* (London: Hodder & Stoughton, 2009).
Lewis, C. S., *A Grief Observed* (London: Faber and Faber, 1961).
MacArthur, John F., *Ashamed of the Gospel: When the Church Becomes Like the World* (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 1993).
MacCulloch, Diarmaid, *A History of Christianity: The First Three Thousand Years* (London: Penguin, 2009).
Mandela, Nelson, *A Long Walk to Freedom* (London: Abacus, 2007).
__________, *Nelson Mandela by Himself: The Authorised Book of Quotations* (Johannesburg: Macmillan, 2011).
McGrath, Alister, *The Christian Theology Reader, 3rd ed.* (Oxford: Blackwell Publishers, 2007).
Metaxas, Eric, *Bonhoeffer - Pastor, Martyr, Prophet, Spy: A Righteous Gentile Vs. The Third Reich* (Tennessee: Thomas Nelson, 2010).
Munroe, Myles, *Single, Married, Separated and Life After Divorce* (Shippensburg, PA: Destiny Image Publishers, 1992).
Obama, Barack, *The Audacity of Hope* (New York: Three Rivers Press, 2006).
Piper, John, *Desiring God: Meditations of a Christian Hedonist* (Nottingham, England: IVP, 2003).
Prince, Derek, *God is a Matchmaker: Let Him Choose!* (UK: Derek Prince Ministries, 1986).
Rainer, Thom S., *The Book of Church Growth: History, Theology and Principles* (Nashville, Tennessee: Broadman Press, 1993).
Sheikh, Bilquis with Schneider, *Richard, I Dared to Call Him Father: The Miraculous Story of a Muslim Woman's Encounter with God* (Life Journey, 2004).

Strobel, Lee, *The Case For Faith* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2000).
Tada, Joni Eareckson, *A Place of Healing: Wrestling with the Mysteries of Suffering, Pain, and God's Sovereignty* (Colorado Springs: David C. Cook, 2010).
Teresa, Mother, *Come Be My Light – The Revealing Private Writings of the Nobel Peace Prize Winner* (London: Rider, 2007).
*The NIV Study Bible* (Michigan: Zondervan Publishing House, 1985).
Wallis, Arthur, *God's Chosen Fast* (Fort Washington, PA: CLC Publication, 2007).
Wink, Walter, *Engaging the Powers: Discernment and Resistance in a World of Domination* (Philadelphia: Fortress Press, 1992).
White, R. E. O., *The Exploration of Faith: Triumphs in Hebrews Eleven* (Moody Press, 1969).
Wolterstorff, Nicholas, *Lament for a Son* (Grand Rapids, Michigan: William B. Eerdmans Publishing Company, 1987).
Yancey, Philip, *Church: Why Bother?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1998).
__________, *Finding God in Unexpected Places* (Colorado Springs: WaterBrook Press, 2008).
__________, *Prayer: Does It Make Any Difference?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2006).
__________, *Reaching for the Invisible God: What Can We Expect to Find?* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2000).
__________, *Rumours of Another World* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 2003).
__________, *The Bible Jesus Read* (Grand Rapids, Michigan: Zondervan, 1999).
__________, *Soul Survivor: How My Faith Survived the Church* (London: Hodder, 2003).
__________, *What's So Amazing About Grace?* (Grand Rapids: Zondervan, 1997).
__________, *What Good is God? In Search of a Faith that Matters* (New York: FaithWords, 2010)
Yancey, Philip and Brand, Paul (Dr), *The Gift of Pain* (Michigan: Zondervan, 1997).
Yancey, Philip and Quinn, Brenda, *Meet the Bible* (Grand Rapids: Zondervan, 2000).

## መጽሔቶች

*ቃሉ ይናገር፡* ለ2004 ዓመታዊ ጉባዔና የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን አከባበር ልዩ እትም (አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር)።
*ጠይም መጽሔት፣* 1ኛ ዓመት ቍጥር 7 (ነሐሴ 2000 ዓ.ም)።



## ጋዜጦች

*ሪፖርተር፣* ኅዳር 20 ቀን፣ 2004 ዓ.ም እትም።
*አዲስ አድማስ፣* ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም።
__________፣ ግንቦት 15 ቀን 2001 ዓ.ም።
*አዲስ ነገር፣* ኅዳር 13 ቀን፣ 2001 ዓ.ም።
*የእግዚአብሔር ክብር (ቍ. 007)፣* ነሐሴ 2001 ዓ.ም እትም።

## ጆርናሎች

Ali, Shah, with Woodberry, Dudley, "South Asia: Vegetables, Fish, and Messianic Mosques", *Theology, News and Notes* (Pasadena, California: Fuller Theological Seminary, March 1992).
Paulos Olana Djini, "The Church in a Divided World: Ethnic & Linguistic Diversities and the Challenge of the Church in Ethiopia" *Contemporary Theological Perspectives* (Addis Ababa: Mekane Yesus Seminary, June 2011).
Woodberry, J. Dudley, "The Middle East: Crescent, Cross, and Plowshare". *Theology, News and Notes* (Pasadena, California: Fuller Theological Seminary, March 1992).

## ድረ ገጾች፣ ...

http://en.wikipedia.org/wiki/Memento_mori መጋቢት 2004 ዓ.ም
http://globalvoicesonline.org/2011/12/01/ethiopia-homosexuality-debate-arises-as-ethiopia-hosts-aids-conference/ መጋቢት 2004 ዓ.ም

Microsoft ® Encarta ® 2009. © 1993-2008 Microsoft Corporation.

# ቀደምት ሥራዎች

ያልተንኳኩ በሮች 168 ገጽ

*ዋችማን ኒ*

የዘላለም ኪዳን (The Better Covenant) 144 ገጽ
የተሸነፈ ዓለም (Love Not the World) 88 ገጽ
የጸጋው ብርታት (Changed Into His Likeness) 124 ገጽ
የዕረፍት ሕይወት (Sit, Walk, Stand) 56 ገጽ

*ሮናልድ ደን*

የእምነት ኀይል (Don't Just Sit There, Have Faith) 160 ገጽ
የወዳጅ ፍላጻ (Surviving Friendly Fire) 160 ገጽ
ሰማዩ ዝም ሲል (When Heaven is Silent) 176 ገጽ

*ዴሪክ ፕሪንስ*

የጋብቻ ኪዳን (The Marriage Covenant) 64 ገጽ